

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች ቅጽ-15

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ችሎት ውሣኔዎች



## ቅጽ-15

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ - 15

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ሐምሌ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

www.chilot.me



## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

ለተመሳሳይ ጉዳዮች በጣም የተራራቁ ውሳኔዎችን በመስጠት ይታይ የነበረውን ችግር በመቅረፍና የውሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ የሰበር ውሳኔዎች አስገዳጅ መሆን ከፍተኛ ውጤት አስገኝቷል ማለት ይቻላል፡፡ አልፎ አልፎ በውሳኔዎች ጥራትና ስርጭት ሊታዩ የሚችሉ ችግሮች ሥርዓቱ እየተጠናከረ ሲሄድ የሚፈቱ ሲሆን እነዚህን ችግሮች ለማቃለል እኛም ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡ ጥረታችን ሊሳካ የሚችለው በውሳኔዎች ላይ በህግ ምሁራንና ባለሙያዎች ገንቢ የሆኑ ትችቶችና አስተያየቶች ሲቀርቡ ነው፡፡

ለሰበር ውሳኔዎች ጥራትም ሆነ ለፍርድ ቤቶች መጠናከር እና በአጠቃላይ ለስራችን መሻሻል ሊረዱ የሚችሉ አስተያየቶች ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

የሰበር ውሳምኔችን ቶሎቶሎ ለማሳተም ባደረግነው ጥረት ቅፅ 15ን በአጭር ጊዜ ማሳተም የቻልን ሲሆን ይህን የ2005 እና 2006 ዓ.ም ውሳኔዎች የያዘውን ቅጽ 15ን ጨምሮ ከዚህ በፊት የታተሙትን ቅጾች በሙሉ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረ ገጽ www.fsc.gov. et ላይ ማግኘት እንደሚቻል ማስታወስ እወዳለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

በ2005 እና 2006 ዓ.ም  የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች

ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | |
| 1. | • አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የደረሰበትን የአካል ጉዳት በተመለከተ የጉዳት ካሣ ክፍያ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችለው በአማራጭ አንድም በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ መሠረት አሰሪውን ያስጥፋት በሥራ ክርክር ችሎት ክሶ በመጠየቅ ወይም የአሰሪውን ጥፋት መነሻ በማድረግ የጉዳት ካሣ ክፍያ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በፍ/ሔር ችሎት በአሠሪው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>• በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የጉዳት ካሣን ለመጠየቅ በህጉ የተመለከቱትን መብቶች በአግባቡና በትክክል ተገንዝቦ እንደ ጉዳቱ ሁኔታ፣ አይነትና አግባብነት በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅመውን የመብት አድማስ አውቆ በመለየት ተገቢው መብቱ ከመነጨበት የህግ አግባብ አንፃር ክሱን ሊያቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 ድንጋጌ ይዘት አድማሱ በግልጽ በተወሰኑ ጭብጦች ላይ ብቻ ሣይሆን በተከራካሪ ወገኖች ቢነሱ ኖሮ ሊወሰኑ ይችሉ የነበሩ ጭብጦችን ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ፣ | 80343 | ዋሊያ የቆዳ ማለስለሻ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ደረጀ ውለታው | ግንቦት 06/2005 | 2 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1)¸97 109¸ 138(1)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80(2) | | | | |
| 2. | አሠሪ ሠራተኛውን እንደ ሠራተኛ በመቀበል የሚሰራውን ሥራ ባልሰጠበት ሁኔታ ሠራተኛውን ከሥራ ገበታው ቀርቷል በሚል ያለ ማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1) ለ | 82091 | ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ<br>እና<br>አቶ ለገሠ ደሣለኝ | መጋቢት 25/2005 | 9 |
| 3. | የሥራ መሪ የሆነ ሠራተኛ ያለ አግባብ ከሥራ መሰናበቱ ተረጋግጦ ሲወሰንና የአሰሪው የመተዳደሪያ ደንብ የሚፈቅድለት ከሆነ በአዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት ኪሣራ ታስቦ ሊከፈለው የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2574(2)<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 43(4) (ሀ) | 84661 | አቶ ዳዊት ሽዋቀና<br>እና<br>ስኳር ኮርፖሬሽን | መጋቢት 27/2005 | 12 |
| 4. | ከሥራ ጋር በተገናኘ እንዲከፈል በሚል የሚቀርቡ የደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓት እና ሌሎች ክፍያዎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ሠራተኛው ክፍያዎቹን መጠየቅ ይችላል (ይገባዋል) ከሚባልበት ግዜ ጀምሮ እንጂ የሠራተኛው የሥራ ውል ከተቋረጠበት ግዜ ጀምሮ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(1-4) | 79476 | ኢትዩ ቴሌኮም እና<br>እነ<br>አቶ ዘሪሁን ታዬ (ዘጠና ስድስት ሰዎች) | የካቲት 12/2005 | 17 |
| 5. | የስራ ውል የሚመሠረተው ማንኛወም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሠነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመስራት የተስማማ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2(3),4 | 81814 | እነ ወ/ት ፌቨን የሺጌታ (12 ሰዎች)<br>እና<br>የኢትዮጵያ አየር መንገድ | ሐምሌ 18/2005 | 24 |
| 6. | በአሠሪው ንብረት ላይ ጉዳት በማድረሱ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የተሰናበተ ሠራተኛ ጉዳቱን ያደረስኩት በሥራ መደራረብ እና ከልምድ ማነስ ነው የሚል ምክንያት አቅርቦ የተከራከረ መሆኑ ስንብቱን ህገ ወጥ ነው ለማለት የሚያበቃ (የሚያስችል) ስላለመሆኑ፣ | 86284 | ሆራይዘን አዲስ ጎማ (አ.ማ)<br>እና | መጋቢት 13/2005 | 27 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሽ), 13(3) | | አቶ መኮንን ዓለሙ | | |
| 7. | አንድ ሠራተኛ የቅጥሩ ውል አይነት ቋሚም ይሁን ግዜያዊ ለሠራተኛ በህጉ በተፈቀዱ ጥቅሞች የመጠቀምና ህጉ የሰጣቸውን ከለላዎች የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 42(2) | 87338 | ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ ገብሬ በላይነህ (አምስት ሰዎች) | ግንቦት 21/2005 | 30 |
| 8. | አንድ ሠራተኛ ከሥራ መቅረቱ በህመም ምክንያት መሆኑ እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የሚችለው በህጉ አግባብ፣ በህመሙ ምክንያት ስለመቅረቱ ለአሰሪው ያሳወቀና ፈቃድ ያገኘ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 85(4) | 87285 | ወ/ሮ የውብዳር ንጋቱ<br>እና<br>ገነት ሆቴል | መስከረም 23/2006 | 34 |
| 9. | የሥራ ኃላፊነቱን ባለመወጣት ተገቢነት የሌላቸው ሰዎችን ወደ አሰሪው ድርጅት ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ በማድረግ ጥፋት የፈፀመ የጥበቃ ሰራተኛ ወደ ድርጅቱ በገቡት ሰዎች ምክንያት የተፈጠረ የፀጥታና የደህንነት ችግር አልተከሰተም በሚል ምክንያት ብቻ አሰሪው በሰራተኛው ላይ የፈፀመውን የስራ ውል ማቋረጥ ተግባር ህገ ወጥ ነው ሊያስብል የሚችል ስላለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሽ), 17(1)(ሽ)(ቀ), 14(2)(ሀ) | 90389 | የኢትዮጵያ ኤርፖርት ድርጅት<br>እና<br>አቶ በሪሁን በላይ | ጥቅምት 18/2006 | 38 |
| 10. | አንድን ሠራተኛ የሥራ መሪ ነው ለማለት የሚቻለው በህግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሰሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈፀም እንዲሁም በተጨማሪነት ወይም ይህንን ሳይጨምር ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣ የመመደብ ወይም ሌሎች የሥነ-ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውን እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3(2)(ሐ)<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(1)(ሐ) | 92466 | ሳይግን ቴክስታይል ቢዩልዲንግ ኮንስትራክሽን ትሬድ ኢንዳሪኢንክ ኢትዮያ ብራንች<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ጥላሁን | ጥር 02/2006 | 41 |

| ውል | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 11. | የንግድ ቤትን ከመንግስት የተከራየ ተከራይ ከአከራዩ እውቅና ውጭ ለ3ኛ ወገን የንግድ ቤቱን ማስተላለፉ አከራዩ የመጀመሪያውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ፣ በዚሁ መሠረትም አከራዩ ቤቱን ለማስለቀቅ የሚያያደርግው እንቅስቃሴ ሁከት ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1140, 1149 | 82670 | እነ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር ፅ/ቤት (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ዋጋዬ አሰፋ | መጋቢት 09/2005 | 46 |
| 12. | •አንድን በጽሁፍ የተደረገ ውል ዋና ሰነድ ጠፍቷል በማለት ክርክር በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤት በማስረጃነት በቀረበው የውሉ ሰነድ ኮፒን ተቀብሎ በውሉ የተመለከቱትን ምስክሮች ሊሰማ የሚገባው ጠፍቷል የሚለው ወገን ዋናው ሰነድ ስለመጥፋቱ በተመለከተ በአግባቡ ያስረዳ እንደሆነና የውሉንም ኮፒ አግባብነት ያለው አካል ዋናው የውል ሰነድ ጋር ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>• የምስክሮቹ ቃል ሊሰማ የሚገባውም የውሉ ቃል ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2011(1),2003 ,1730(1) | 84330 | አቶ መንግስቱ ኦሾ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ እመቤት ጥላሁን (አምስት ሰዎች) | ሚያዝያ 10/2005 | 50 |
| 13. | አስቀድሞ በተደረገ የኪራይ ውል መነሻነት አንድን የአከራይ ንብረት ይዞ ሲጠቀም የቆየ ተከራይ የኪራይ ውል ግዜው ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ አከራዩ የኪራዩን ዋጋ በመጨመር አዲስ የኪራይ ዋጋ እንዲከፈል ገልፆ እያለ ተከራዩ በቀረበው አዲስ የኪራይ ዋጋ ሳይስማማ ወይም እየተቃወመ በንብረቱ መገልገሉን በቀጠለ ጊዜ ተከራይ ለአከራዩ ሊከፍለው የሚገባውን የኪራይ ዋጋ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2950(1) (2), 1687 | 81163 | አቶ ሲሳይ ረታ<br>እና<br>የኢትዩጵያ እህል ንግድ ድርጅት | የካቲት 11/2005 | 55 |
| 14. | • ከውል አፈፃፀም ሂደት ጋር በተገናኘ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኪሣራ ሊሰላ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>• የኪሣራው ልክ ከውል ውጪ የሚደርስ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በርትዕ ሊወሰን | 79794 | የማይክሮሊንክ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ | ሚያዝያ 22/2005 | 59 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 1800, 2102(1)(2) | | ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር | | |
| 15. | አንድ ውል (ስምምነት) ህግ በጽሑፍ እንዲሆን ሲያስገድድ ውሉ በጽሁፍ መደረግ ያለበት እና በተዋዋይ ወገኖችና በሁለት ምስክሮች ፊርማ ሊረጋገጥ የሚገባ ስለመሆኑና መሀይማንና ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ውል በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት የተደረገ ካልሆነ በቀር በውሉ የማይገደዱ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1727, 1728(3), 2005 | 83674 | ወ/ሮ እቴነሽ ካሳ<br>እና<br>ሀጂ ጀማል ይማም | ግንቦት 19/2005 | 65 |
| 16. | በመያዣ ውል መነሻነት አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከነይዞታው የያዘ ሰው በይዞታው ላይ የንብረቱ ባለቤት ሳይቃወመው ግንባታ የፈፀመ ከሆነ ተጠቃሹ የመያዣ ውል አይፀናም በሚል ተዋዋዮቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ሲደረግ የንብረቱ ባለቤት በመያዣው ይዞታ ላይ የወጣውን የግንባታ ወጪ ግንባታውን ሳካሄደው ወገን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1818, 2162 | 90862 | ወ/ሮ ተዋበች ኃይሌ<br>እና<br>ወ/ሮ አያንቱ በዪቻ | ታህሳስ 14/2006 | 69 |
| 17. | የማይንቀሣቀስ ንብረት ተከራይ የሆነ ሰው ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለ3ኛ ወገን በኪራይ ሊሰጥ የሚችለው ተከራዩ አስቀድሞ ለአከራዩ አሳውቆ አከራዩ የማይቃወም መሆኑ ሲታወቅ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2957(1)(2), 1731<br>በአ.አ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ቢሮ ደንብ ቁጥር 3/2004, 4/2004 | 86847 | አቶ ፀጋዬ አማን<br>እና<br>እነ አቶ መሐመድ ነጋሽ (ሶስት ሰዎች) | ጥቅምት 18/2006 | 73 |
| 18. | ከሠራተኛ ቅጥር ውል ጋር በተገናኘ የዋስትና ግዴታ የገባ ሰው የሠራተኛው የቅጥር ውል እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ከተደረገ በኋላ ሠራተኛው ከተሻሻለው ወይም ከተለወጠው የቅጥር ውል ጋር በተያያዘ ያለበትን ተጠያቂነት አስመልክቶ አስቀድሞ | 86813 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት<br>እና | መስከረም 22/2006 | 77 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በገባበት የዋስትና ግዴታ መሰረት ተጠያቂ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1827(1) | | እነ ሰሚር መላኩ<br>(ሶስት ሰዎች) | | |
| 19. | • ተከራካሪ ወገኖች በአንድ የሰነድ ማስረጃ ላይ የተመለከተን ፊርማ የማን ስለመሆኑ በሚመለከተው የመንግስት አካል ተጣርቶ ውጤቱ ከቀረበና ከታወቀ በኂላ ሰነዱ በውጭ አገር ተመርምሮ ውጤቱ እንዲታወቅ በማለት የሚያቀርቡት ጥያቄ በህግ አግባብ አጥጋቢና አሣማኝ ምክንያትን በመጥቀስና በማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ እንደሆነ ጥያቄው ተቀባይነት ሊኖረው የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• የፍ/ቤት የተሰጠ ትእዛዝ /ውሣኔ/ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻለው በተከራካሪ ወገኖች ፍትህ የማግኘት መብት ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2008, 2007, 2001, 2005 | 86187 | አቶ ዳንኤል ዘሚካኤል<br>እና<br>አቶ ቢሃሪ ባቡላል ሞዲ | ሰኔ 21/2005 | 80 |
| **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | | |
| 20. | • በፍ/ብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲነጠር የሚደረገውም በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣<br>•ማስረጃ እንዲሠማ የሚፈልግ ወገን ማስረጃው የሚሰማበትን ነጥብ ለይቶ የማስረጃውን አይነትና የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በመጥቀስና በእጁ ላይ ያለውንም አያይዞ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.223¸234¸137(3)¸145¸256,136-138,246,248 | 77983 | እነ አቶ እንድሪስ አደም (አምስት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አስናቀች ጥላሁን | መጋቢት 24/2005 | 87 |
| 21. | አንድን ጉዳይ በተመለከተ ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው በተለያዩ ፍ/ቤቶች (ችሎቶች) አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ክሶች ባቀረቡ ግዜ (የክርክሮቹ ደረጃ ምንም ይሁን ምን) ክሶቹ ተጣምረው ታይተው ሊወሠኑ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 8(1),11,244, 245 | 81275 | ወ/ሮ ዘምዘም ወንድሙ<br>እና<br>አቶ አብዲሰቡር አብዱሰመድ | ሰኔ 05/2005 | 92 |
| 22. | • ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ጋር በተገናኘ መብቱን ለማስፈፀም ጠይቆ በአፈፃፀም | 83007 | እነ ወ/ሮ አልማዝ | ሰኔ 03/2005 | 98 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶ እያለ ባለመብት ነኝ የሚለው ወገን የሚያነሣው የመብት ጥያቄና ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• በአንድ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በህግ አግባብ እስካልተሻረ ድረስ የውሣኔው አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት በባለጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን በማናቸውም አስፈፃሚ አካላትና በማናቸውም ፍርድ ቤት ላይ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 79(2) | | ገመቹ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ፋዩ ገመቹ | | |
| 23. | በአንድ ጉዳይ ተከሣሽ የሆነ ወገን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ካቀረበ ፍ/ቤቱ ከቀረቡት ክሶች መካከል በሥረ-ነገር ስልጣኑ ሥር ያሉትን መርጦ ለማየትና ከሥረ-ነገር ስልጣኑ በላይ የሆነውን ጉዳይ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቅረብ በማለት የከሣሽን ክስና የተከሣሽን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ተነጣጥለው እንዲታዩ በማድረግ የሚሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 30(1)¸324(1) (ሀ),215(2)¸17(3) | 83169 | ፕሮፌሰር አደም ዓሊ አህመድ<br>እና<br>አዳማ ጠቅላላ ሆስፒታልና ሜዲካል ኮሌጅ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 28/2005 | 103 |
| 24. | • አንድ ስምምነት በፍ/ቤት ሊፀድቅ የሚችለው ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት በመታየት ሂደት ላይ እያለ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ መሆኑን ገልፀው ይኼው ስምምነት ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣<br>• ከፍርድ ቤት ውጪ በሚደረግ እርቅ ወይም ግልግል መሰረት ያለመግባባትን ያስቀሩ ወይም ለጉዳያቸው እልባት ያገኙ ሰዎች የእርቁን ወይም የግልግሉን ስምምነት በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ወይም ማስፀደቅ የማያስፈልጋቸው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312 እና 3324 | 85873 | እነ ወ/ሮ ኒኢማ አባድጋ አባዋጂ<br>እና<br>አቶ ጣሐ ጀማል አደም | መጋቢት 13/2005 | 108 |
| 25. | አንድን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የሚመለከት ፍ/ቤት በህጉ አግባብ ክስ ተሻሽሎ ከፍ ያለ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ሁኔታ በግምት ላይ ተቃውሞ ቀርቦ ግምቱ እንዲጣራ ሲደረግ የንብረቱ ግምት ከፍ ማለቱ በመረጋገጡ ብቻ ቀድሞ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ | 86551 | ወ/ሮ ብዙነሽ ወ/ሚካኤል<br>እና | መጋቢት 25/2005 | 112 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1) ,92, 225, 226, 250,136 | | እነ አቶ ሽመልስ ቦጋለ | | |
| 26. | ወራሽነትን በማረጋገጥ በተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ ላይ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ሥለመሆኑ እና ተረጋግጦ የተሰጠውን ማስረጃ በሌላ ክርክር መቃወም የሚችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | 79871 | እነ ወ/ሮ የውብዳር ባንቱ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሎሚ ተሲላ (አምስት ሰዎች) | የካቲት 11/2005 | 116 |
| 27. | አንድን ጉዳይ አስመልክቶ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው እስከሆነና ጉዳዩን ለማየት በህግ በግልጽ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ሌላ አካል እስከሌለ ድረስ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊስተናገድና ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችልና የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1), 79(1)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4 | 80202 | እነ አቶ ሐጎስ ሽጎፅ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የመሸነ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የካቲት12/20<br>05 | 120 |
| 28. | የክስ አቀራረብ ሥርዓቱን አሟልቶ ያልቀረበ ክስን ፍ/ቤቶች ሌላኛውን ወገን ሳይጠሩ ለመዝጋት ስለመቻላቸው፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 33, 80, 222, 225, 226 እና 231 | 83915 | አቶ ዩሐንስ በቀለ<br>እና<br>የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የካቲት 29/2005 | 123 |
| 29. | የማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም ክስ ጋር በተያያዘ ክርክር ቀርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በክርክሩ ተሣታፊ የነበረ ወገን ንብረቱን አስመልክቶ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መክኗል በሚል የሚያቀርበው አዲስ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በፍርዱ መሠረት የተጀመረው አፈፃፀም ሂደትን ለማስቆም የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195,1196<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6,358,378<br>የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(1), 79(1)(4) , 37 | 42501 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>የአስር አለቃ ደምሴ ዳምጤ ወራሾች (ሶስት ሰዎች) | የካቲት 28 /2005 | 126 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 30. | የማይንቀሣቀስ ንብረት (ቤት) ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ስመ-ንብረት የሚመለከተው አካል ወደ ገገርው ለማዞር እንዲችል በሚመለከተው ክፍል ቀርቦ ተገቢውን እንዲፈፀም በማለት ገዥ የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1)(ሀ), 33(2-3), 222, 224 | 82234 | አቶ አየለ መኮንን<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ጦቢያው ወንድም ገዛው<br>(ስድስት ሰዎች) | የካቲት 26/2005 | 130 |
| 31. | ፍርድ ቤቶች ለቀረበላቸው ጉዳይ አወሣሠን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን የተገነዘቡ ከሆነ ይሄው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያሉትን ማጣራት ሁሉ ለማድረግ ስለመቻላቸው፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136, 137, 272, 327(3), 345 | 72980 | ወ/ሮ ይርገዱ አዲሱ<br>እና<br>እነ ህጻን ምስጋናው ዘሪሁን (ሶስት ሰዎች) | ሐምሌ 06/2004 | 134 |
| 32. | ሚስትነትን በተመለከተ የአመልካችን ማስረጃ ብቻ በመቀበል ሚስትነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ማስረጃ (Declaratory Judgment) በማናቸውም ጊዜ ተዓማኒነትና ክብደት የሌለው ማስረጃ መሆኑን ለማሳየት ክርክር ሊቀርብበትና ተቃራኒ ማስረጃ ተሰምቶ ውድቅ ሊደረግ የሚችል እንጂ ማስረጃውን በተሰጠው ፍ/ቤት ተቃውም በማቅረብ ያልተሻረ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ | 82679 | ወ/ሮ ከበቡሽ ሽዋረገድ<br>እና<br>ወ/ሮ እንዳገር ጌቱ | መጋቢት 27/2005 | 138 |
| 33. | በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ከነበረ ክርክር ጋር በተገናኘ በተከራካሪዎቹ ወገኖች አመልካችነት ጉዳይ በእርቅ በማለቁ የተከራካሪዎቹን የእርቅ ስምምነት ተቀብሎ በማጽደቅ እንዲመዘገብ በማለት በፍ/ቤት የተሰጠ ትእዛዝ ላይ መብቱ ወይም ጥቅሜ ተነክቷል የሚል ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚያቀርበው የመቃወሚያ አቤቱታ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ትእዛዙን የሠጠው ፍ/ቤት አቤቱታውን ተቀብሎ ሊያስተናግደው የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,360,277(1)(2) | 83582 | ወ/ሮ ወርቅነሽ ውብነህ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አልማዝ ዓለሙ (ሶስት ሰዎች) | መጋቢት 27/2005 | 144 |
| 34. | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 ተፈፃሚነት በተከራካሪ ወገኖች መካከል በዋናው ጉዳይ ላይ ከላይ ወደ ታች በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ከተደረገ ክርክርና ከተሰጠ ውሣኔ ጋር በተገናኘ እንጂ በአፈፃፀም ከተሰጠ ትእዛዝ (ውሣኔ) ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ ነው ሊባል የማይችል | 84446 | ጠበቃ አንበርብር ዓባይነህ<br>እና | ሚያዝያ 24/2005 | 149 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 32 | | ፍትህ ሚኒስቴር | | |
| 35. | አንድን ጉዳይ ለማየት በህግ ስልጣን በሌለው ፍ/ቤት ታይቶ የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልደተረገ በቀር በጉዳዩ ላይ አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 212 | 85718 | አቶ ቴዎድሮስ አማረ<br>እና<br>አቶ አዲሱ ፍሰሃ | ሰኔ 03/2005 | 153 |
| 36. | በአንድ የቀረበ ክስ በተከሣሽነት የተሰየመ ወገን በከሳሽ ከቀረበበት ክስ ጋር በተገናኘ ክስ በቀረበበት ንብረት (ጉዳይ) ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ በህጉ አግባብ የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱን ተገቢውን ዳኝነት በመክፈል ያቀረበ ካልሆነ በስተቀር ዳኝነት ሊሰጥ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1) (ረ)(ሠ), 215(2), 235(2) | 86454 | እሪ ወ/ት ፍሬወይኒ አለም (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አለም መሐሪ | ግንቦት 23/2005 | 156 |
| 37. | •ከሣሽ የሆነ ወገን የሚያቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ አይነትና መጠኑን በክሱ ማመልከቻ በግልጽ በማስፈር ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>•ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በህግ የተፈቀደን መፍትሔ ለማግኘት በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ የሚገባቸው ስለመሆኑ፣<br>•የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241 ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማ ተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ያቀረቡት ክርክር ለማብራራት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 246-248 መሠረት ጭብጥ ለመመስረት እንዲያግዝ እንጂ በጽሁፍ ማመልከቻ ላይ ያልሰፈረን የዳኝነት ጥያቄ ተከራካሪዎች እንዲጠይቁ የሚያስችል ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 222, 234, 235, 236, 83, 224, 182, 241, 246-248, 251, 255 | 86510 | ሙሉ ኤሌክሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል /አ.አ/ | ሰኔ 18/2005 | 160 |
| 38. | በፍ/ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተመለከተው 60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ግዜ ታሳቢ የሚያደርገው እና ተፈፃሚ የሚሆነው ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ውሣኔ መሰጠቱን ወይም ለውሣኔ የሚያበቃ ክርክር የተደረገ መሆኑን ተረድተው ቀርበው ለመከታተልና የዳኝነቱን ውጤት ለመስማትና ለማወቅ ያልፈለጉትን ወይም ደግሞ የተከራካሪዎችን የመደመጥ መብት ማክበር ይቻል ዘንድ በህጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ጥሪ | 87190 | ቄስ ዳንኤል አርኬ<br>እና<br>የኮልፌ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ | መስከረም 21/2006 | 164 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተደርጉላቸው በጥሪው መሠረት ክርክራቸውን በአግባቡ ለመምራት ባልቻሉ ወገኖች ላይ ስለመሆኑ፣ | | | | |
| 39. | • የኑዛዜ ህጋዊነት ጋር በተያያዘ በተካሄደ ክርክር ተሣታፊ ሆኖ ተቀባይነት ያጣና ኑዛዜው በፍርድ ቤት የፀደቀበት ሰው በሌላ ጊዜ የኑዛዜውን ህጋዊነት አስመልክቶ በመቃወሚያነት የሚያቀርበው ክርክር ወይም አዲስ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባው በስርዓቱ መሠረት የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ መሠረት በማድረግ እንጂ ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ተገቢ አልነበረም በሚል ምክንያት ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5,212<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 | 85102 | አቶ ሰንደቁ አበበ<br>እና<br>አቶ ሐብታሙ ቃበቶ | መስከረም 21/2006 | 168 |
| 40. | •በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ መደበኛውን የሙግት ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ መከናወን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>•በፍርድ አፈፃፀም ደረጃ ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር በሚል የመቃወሚያ አቤቱታ በቀረበ ግዜ ጉዳዩን የያዘው የአፈፃፀም ችሎት በንብረቱ ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ በሚል የቀረበውን የመቃወም አቤቱታ በመደበኛው የሙግት ሥነ-ሥርዓት ሂደት ክርክሩን በማስተናገድ ንብረቱ እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የሚያደርግ ህጋዊና በቂ ምክንያት መኖር ያለመኖሩን በማስረጃ በማጣራት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 419, 421 | 86133 | እነ አቶ ፍቅሩ ከበደ<br>(አስራ አንድ ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር አርአያ<br>(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 20/2006 | 172 |
| 41. | የፍርድ ቤትን እገዛ በመጠየቅ ማስረጃ ማስቀረብ የሚቻለው ጠያቂው ተከራካሪ ወገን እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ ትክክለኛ ግልባጭ በቅርብ ግዜ ለማምጣት የማይችልበትን ወይም ለማስገልበጫ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመክፈል የማይቻል መሆኑን እንዲሁም ማስረጃው ለክርክሩ ምን ያህል ጠቃሚነት እንዳለውና ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያስችል ስለመሆኑ በጽሁፉ ገልፆ ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ | 89494 | የኢትዩጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>የሟች ዘካሪያ ኢብራሂም ባለቤት ሳዲያ ኢብሮሽ | ጥቅምት 19/2006 | 177 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145(1)(2), | | | | |
| 42. | • ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጋር በተገናኘ አንድ ሰው ሟች በተውት ኑዛዜ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ክፍያ እንዲከፈለው ክስ አቅርቦ ገንዘቡ እንዲከፈል ዳኝነት ከተሰጠ በኂላ በሌላ ግዜ የሟቹ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በማለት የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• ኑዛዜን መሠረት አድርጐ የሚቀርብ የኑዛዜ ተጠቃሚት መብት ይረጋገጥልን ጥያቄና የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆነ የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዬች ስለመሆናቸው፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(2) | 90543 | እነ አቶ ተሾመ አሰፋ (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሪት መስታወት አሰፋ | ጥቅምት 21/2006 | 183 |
| 43. | በችሎት በመገኘት ስልክን ማስጮህ ብሎም ፍርድ በሚነብበት ጊዜ በችሎት ዳኛው ሥነ-ሥርዓት እንዲይዝ ሲነገረው ችሎቱ በሥነ-ሥርዓት ያናግረኝ በማለት ያልተገባ ባህሪ ማሣየት በችሎት መድፈር ወንጀል ሊያስቀጣ የሚችል ተግባር ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 481<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 449(1)(ሀ) | 92459 | አቶ ፍጽም ብርሃን ገ/ክርስቶስ<br>እና<br>ተጠሪ፡ የለም | ጥቅምት 19/2006 | 186 |
| 44. | • ከወጪና ኪሣራ አወሣሠን ጋር በተገናኘ ከቅን ልቦና ውጪ ለክርክር የተዳረገ ወገን የክርከሩ ረቺ መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ቅን ልቦና ከሌላው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት በሚል ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• የወጪና ኪሣራ ጥያቄን አስመልክቶ ፍ/ቤቶች በመጠኑ ላይ ለመወሰን በህግ ስልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑና ረቺ የሆነ ወገን ሁል ግዜ ወጪና ኪሣራ እንዲተካለት ሊወሰን ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 462-464 | 91103 | ዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር<br>እና<br>እነ የአቶ ፉአድ መሃመድ እናት ወራሽ ወ/ሮ ማሪያም አብዱላሂ (ሁለት ) | ታህሳስ 16/2006 | 188 |
| 45. | በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ እንዲነሣ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ፍ/ቤቱ አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ያነሳውና አቤቱታ አቅራቢው ክርክሩን እንዲያቀርብ በድጋሚ እድል ከተሰሠጠው | 90452 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ጥር 14/2006 | 191 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በኋላ የጽሁፍ ክርክሩን ያላቀረበና ክሱ በሚሰማበት ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ ክርክሩን እንደገና ለመስማት በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት የከሣሽ ክስና ማስረጃ እንደገና ተመርምሮ ተገቢው ውሣኔ ከሚሰጥበት በቀር እንዲነሣ ትእዛዝ የተሰጠበት የቀድሞው ውሣኔ በቀጥታ ተመልሶ እንደገና እንዲፀና ሊደረግ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፡<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78(2), 70(ሀ) | | እና<br>አቶ ገ/ሥላሴ በርሄ | | |
| 46. | ሀሰተኛ ማስረጃ ለፍ/ቤት በመቅረቡ የተነሣ የተወሰነበት ተከራካሪ ወገን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)ን መሠረት በማድረግ ፍርዱ በድጋሚ እንዲታይለት አቤቱታ ባቀረበ ጊዜ ሀሰተኛ ማስረጃውን የሰጠው አካል በምን ምክንያት በህገ ወጥ ተግባር ሀሰተኛውን ማስረጃ ሊሰጥ እንደቻለ የማስረዳት ግዴታ ጭምር አለበት ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 403፣405 | 91968 | አቶ ግርማ ሰንበት<br>እና<br>ወ/ሮ አልማዝ ገብረየስ | ታህሳስ 15/2006 | 194 |
| 47. | • ተከራካሪ ወገኖች በቅድሚያ ሊያቀርቧቸው ሲችሉ ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት ያላቀረቧቸውን ማስረጃዎች በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠቡ ሊያቀረቡ ወይም የማስረጃ ማሰባሰብ ሥራውን ፍርድ ቤት እንዲያከናውን ሊጠይቁ የሚችሉበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>• በፍ/ቤት እገዛ ማስረጃ የሚቀርበው ተከራካሪ ወገን አጠቃቅሎ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ፍ/ቤቱ የተጠየቀው ማስረጃ ለተያዘው ጉዳይ ያለውን አግባብነት በተመለከተ የተቀበለው እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1) | 85468 | ሣባ ኢንጂንሪግ<br>ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>የፕራይቬታይዜሽንና<br>የመንግስት ልማት<br>ድርጅቶች ተቆጣጣሪ<br>ኤጀንሲ | መስከረም 24/2006 | 197 |
| 48. | • ተከራካሪ ወገኖች ለክርክራቸው ምክንያት ሊሆን የሚችለውን ጉዳይ ወይም ያከራከራቸውን ጉዳይ በእርቅ ስምምነት የጨረሱ እንደሆነ የእርቅ ስምምነቱ ግብ ተከራካሪዎቹ (ታራቂዎቹ) በግላቸው ያላቸውን መብትና ግዴታ እንደሁኔታው በማስተካከል ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን ጉዳይ በስምምነት ማስቀረት ስለመሆኑና የእርቅ ስምምነቱ ውጤትና ተፈፃሚነቱ እርቁን ባደረጉት ተከራካሪ ወገኖች መካከል ብቻ ተገድቦ | 87834 | በኮልፌ ቀራኒዮ<br>ክ/ከተማ የመሬት<br>ልማት አስተዳደር<br>ጽ/ቤት<br>እና | መስከረም 21/2006 | 204 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚቀር እንጂ የሌሎች 3ኛ ወገኖች መብትና ግዴታ ሁሉ በማካተት የ3ኛ ወገኖች መብትና ግዴታን አብሮ በእርቅ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ፣<br>• የተከራካሪ ወገኖች የእርቅ ስምምነት በፍ/ቤት ትእዛዝ (ውሣኔ) መጽደቅና መመዝገብ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል 3ኛ ወገኖች የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3311<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | | ፀዳለ ካሣቀ (ሶስት ሰዎች) | | |
| 49. | አንድ ፍርድ ቤት ክርክርን በሚሰማበት ወቅት የሚሰጠው ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ (Interlocutory order) ላይ በመነጠል ክርክር የሚካሄድበት ዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችለው የተሰጠው ትእዛዝ በባህሪው የሰውን መታሰር ወይም የንብረት ማስተላለፍን ወይም ስም ማዞርን ጉዳይ በተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(3)(4) | 89893 | ኮንቴክ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ወልዱ ህሉፍ | መስከረም 24/2005 | 207 |
| 50. | • የዳግም ዳኝነት (Review of Judgement) ዓይነተኛ ዓላማ ተገቢ ሁኔታዎችና ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸው ሲረጋገጥ በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በመደለያና በመሰል ወንጀል ጠቀስ ድርጊቶች ምክንያት የተዛነፈን ፍትህ ወደ ነበረበት መመለስ ስለመሆኑ፣<br>• የዳግም ዳኝነት ጥያቄ (አቤቱታ) ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ጥያቄው ለሰበር ችሎት በቀረበ ጊዜ ችሎት አቤቱታውን ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ላላቸው የስር ፍ/ቤቶች ሊመራውና ሊያስተላልፈው በሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ)(ለ)<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) | 93137 | ወ/ሮ ብጥር ታገለ<br>እና<br>ወ/ሮ አገር ተሰማ | የካቲት 11/2006 | 210 |
| 51. | በተከራካሪ ወገኖች ክርክር በሚካሄድበት ወቅት በፍ/ቤት ትእዛዝ በተከራካሪ ወገን ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ታግዶ እንዲቆይ ተደርጐ ትእዛዙ ፀንቶ በነበረበት ግዜ በገንዘቡ ላይ | 83771 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | መጋቢት 10/2005 | 214 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወለድ ሊታሰብ ይገባል ወይስ አይገባም በሚል ክርክር የተነሣ እንደሆነ ከጉዳዩ ልዩ ባህሪ ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የልዩ አዋቂ ምስክርነትና የባለሙያ ማብራሪያን አስቀርበው በማጣራት ሊወስኑ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136 | | እና<br>እነ ወ/ሮ ዘነበች አለማየሁ (ሁለት ሰዎች) | | |
| 52. | ባለ አምስት ዳኞች የሚሰየሙባቸው የክልል ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች በአጣሪው ችሎት ጉዳዩ ያስቀርባል በሚል በተመለከተው ነጥብ (ጭብጥ) ሳይገደብ ሌላ (ሌሎች) ጭብጦችን በመመስረት ክርክሩ እንዲሰማ በማድረግ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣ | 90298 | አቶ ኃይሉ ዴሬሳ<br>እና<br>ወ/ሮ ሱፌ አለሙ | የካቲት 10/2006 | 217 |
| **የንግድ ህግ** | | | | | |
| 53. | • የንግድ መደብር ኪራይ ከንግድ ቤት ኪራይ የተለየ ስለመሆኑ፣<br>• የንግድ መደብር የተከራየ ሰው ያለአከራዩ እውቅና እና ፈቃድ መደብሩን ለ3ኛ ወገን በኪራይ አሳልፎ ለመስጠት ስለመቻሉ፣<br>የንግድ ህግ ቁ. 127 (ሐ),145(ለ), | 79561 | አቶ ፀጋዬ አማን ለጃ<br>እና<br>በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት | የካቲት 11/2005 | 221 |
| 54. | የንግድ ማህበር ሒሣብ ከተጣራና ትርፍና ኪሣራው ተለይቶ ከቀረበ በኂላ የማህበር አባል (ባለአክሲዮን) የሆነ ሰው ከትርፍ ሊደርሰው የሚገባውን የድርሻ ክፍያ በመለየት ክፍያ እንዲፈፀምልኝ በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ ቁጥር 211, 517, 518, 532(1) | 82503 | እነ ወ/ሪት ቤዛ ዱጉማ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ዘሚሊ ቀለም ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 21/2005 | 224 |
| 55. | • የህብረት ሥራ ማህበራት ንብረት እንደ የአባለቱ የጋራ ሀብት (ንብረት) ተቆጥሮ ንብረቱን ለመሸጥ የሁሉም አባላት ስምምነት ያስፈልጋል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• የህብረት ሥራ ማህበራት አሰራር ጋር በተያያዘ ውሣኔ ለማሳለፍ የሚችለው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስለመሆኑ፣ | 85009 | ሃጅ ፈዩ ገመቹ ሄዳአ<br>እና<br>እነ አቶ ዓለሙ በቀለ (አስራ አምስት ሰዎች) | መስከረም 21/2006 | 229 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 147/91 አንቀጽ 21, 18, 32, 19<br>ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 20(2) 123 | | | | |
| 56. | አበዳሪ የሆነ ባንክ ለተበዳሪው ላበደረው ገንዘብ በመያዣነት ለያዘው ንብረት የመድን ሽፋን የገባለት እና የአርቦን ክፍያን ለመክፈል የተስማማ እንደሆነ ለመድን አስገቢው ተቋም የአረቦን ክፍያውን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>• የንግድ ህግ ቁጥር 657, 675 | 83489 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ግንቦት 19/2005 | 233 |
| **ቤተሠብ** | | | | | |
| 57. | ከሟች በስጦታ ወይም በኑዛዜ የተሰጠን ንብረት ወደ ውርስ መልሶ ማግባት (Collation) ስለሚከናወንበት ሥርዓት፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1065-1078 | 80920 | ወ/ሮ ውድነሽ እሸቱ<br>እና<br>አቶ ፍቅረማሪያም ወርቁ | የካቲት 25/2005 | 237 |
| 58. | ኑዛዜ ፈራሽ ነው በሚል ስለሚቀርብ ክስ እና ክሱ ሊቀርብ ስለሚገባበት የጊዜ ገደብ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973, 974 | 82585 | እነ ወ/ሮ ሱዛን ሞንታልባን (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ ሙራድ አሊ (ስድስት ሰዎች) | የካቲት 13/2005 | 240 |
| 59. | ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጋር በተገናኘ የውርስ ሀብት ተጣርቶና ሪፖርት ቀርቦ በመጽደቁ መነሻነት ሀብቱ ተከፋፍሎ ከተፈፀመ በኂላ ወራሾቹ ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሣይኖራቸው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ አድርጓል በሚል እውነተኛ ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት በሚል ለመጠየቅ የሚችለው ተገቢውን የዳኝነት ክፍያ በመክፈል አዲስ ክስ በመመስረት እንጂ ክፍፍሉ ተፈጽሞና ውሣኔ አግኝቶ የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1), 998(1), 999 | 89641 | እነ ወ/ሮ ሐረገወይን ብርሃኑ(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አዜብ ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 21/2006 | 243 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91, 6 | | | | |
| 60. | ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ፍቺ አስመልክቶ ጉዳዩ በመደበኛው ፍ/ቤት ቀርቦና ክርክር ተካሄዶ ውሣኔ ከተሰጠበት በኂላ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጉዳይ ሀይማኖታዊ ስርዓትን በመጠቀም በሸሪአ ፍ/ቤት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1)(2), 244(2)(ሰ), 245(2)<br>አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 5(4), 6(2)<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 34(5) | 93779 | ወ/ሮ ጂእቶ ያሲን ሺበሺ<br>እና<br>አቶ ሐሰን መሐመድ | ታህሳስ 30/2005 | 247 |
| 61. | • የአባት ስም እንዲስተካከልልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• አንድ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞችና የአባት ስም ሊኖረው ስለመቻሉና የአንድ ልጅ የአባት ስም የሚሆነው የአባቱ የግል ስም ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231 (1)(ሀ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 32(1)፣ 36(1) | 95995 | ወ/ት ሞሚና ሡልጣን ኮርዋሳ<br>እና<br>ተጠሪ፡- የለም | የካቲት 10/2006 | 251 |
| 62. | የቤተ ዘመድ ስም እንዲለወጥ በፍ/ቤት ጥያቄ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 42 , 33(1) , (2) | 87420 | ወ/ሪት ማህሌት ልዑለቃል<br>እና<br>ተጠሪ የለም | ሚያዝያ 24/2005 | 254 |

## ጉምሩክ/ግብር/ታክስ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 63. | ግብር የተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ የማጽደቅ ስልጣን ያለው (የተሰጠው) የመንግስት አካል ግብሩ መከፈሉን ሣያረጋግጥ ዝውውሩን እንዲቀበል፣ እንዲመዘግብ ወይም እንዲያፀድቅ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 37(7) | 79189 | የኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ባለስልጣን<br>እና<br>ጂ.ኤም.ቲ ኢንዱስትሪያል | መጋቢት 9/2005 | 258 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ኃ/የተ/የግል ማህበር | | |
| 64. | • አንድ ሰው ለመንግስት ሊከፍል የሚገባውን ግብር ባለመክፈሉ በወንጀል ተግባር ሊጠየቅና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችለው ግብሩን ላለመክፈል በማሰብና ግብር አስገቢው መ/ቤትም ንብረቶቹን በመያዝና በመሸጥ የግብር ገንዘቡን ገቢ እንዳያደርግ ለማድረግና ግብር የመክፈል ኃላፊነቱን ለማምለጥ ንብረቶቹን ለማሸሽ፣ የመሰወር ወይም ሌሎች ተገቢነት የሌላቸው ህገ ወጥ ተግባራትን በመፈፀም ግብርን ያልከፈለ መሆኑ ሲረጋገጥ እንጂ በሌሎች በህግ ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች ግብሩን ለመክፈል ሳይችል የቀረ እንደሆነ ስላለመሆኑ፣<br>• ማንኛውም ሰው በፍ/ብሔር ጉዳይ ያለበትን እዳ ለመክፈል ባለመቻሉ ምክንያት ብቻ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የማይገባ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 49<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 96, 162<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 13(2)<br>ደንብ ቁጥር 78/94<br>ICCPR- አንቀጽ 11 | 84623 | እነ ጅ. አግሪ ፖክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | ሰኔ 04/2005 | 261 |
| 65. | የንግድ ሥራ ፈቃድ ኖሮት ነገረ ግን በህግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱ ሳይታደስ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ ሰው የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ በወንጀል ኃላፊነት ጥፋተኛ ተደርጐ ሊያስቀጣው የሚችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 2(10), 36, 60(1) | 86388 | አቶ ባዘዘው ይሁን<br>እና<br>የአ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ | ሰኔ 17/2005 | 268 |
| 66. | ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተገናኘ ከሚመለከተው የገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ፈቃድ ሳያገኝ ተገቢ ያልሆኑ ፓዶችን (የVAT ደረሰኞችን) ማሳተምና መገልገል በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑና የድርጅቱ ባለሀብት (ሥራ አስኪያጅ) ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው ያልነበረ መሆኑን በመግለጽ የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው ማንኛውም በጐ አሳቢ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ጥንቃቄ ያደረገና ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ድርጅቱን በመምራት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን ማስረዳት | 86597 | ግሎሪ ኢትዩጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ በርሀ ረዳ ኪዳኑ | መስከረም 21/2006 | 271 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56(3),(ለ), 3(1)(ለ), 2(11), 3(1)(ሀ)<br>አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 2, 19(50) (ሐ) | | | | |
| 67. | አንድ በንግድ ሥራ የተሰማራ ሰው (ድርጅት) በተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ አለበት ለማለት የሚቻልበት እንዲሁም መመዝገብ ሲኖርበት ሳይመዘገብ ቀርቶ ግብር ሊጣልበት ስለሚችልበት አግባብ፣<br>አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 3(1)(3), 16(1)(ለ) | 82061 | አቶ አብዴልቀድር ሁሴን<br>እና<br>የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | መስከረም 20/2006 | 274 |
| 68. | የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ ነጋዴ (ሠው) ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሽያጭን አከናውኗል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት አግባብ፣<br>አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 11(1)(2)፣ 22(1)(3)<br>አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 11(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2)፣ 58(3)<br>ደንብ ቁጥር 139/1999 | 86672 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ<br>እና<br>አቶ በቀለ ተሰማ<br>(ሁለት ሰዎች) | መስከረም 22/2006 | 277 |
| 69. | • ከጉምሩክ ህግና አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በኮንትሮየባንድ ወንጀል ተጠርጥሮ በጉምሩክ ተቋም በቁጥጥር ሥር እንዲውል የተደረገ የንግድ ተሽከርካሪን አስመልክቶ ለንብረቱ ባለቤት የተቋረጠ ጥቅም (ገቢ) እንዲከፈል ሲወሰን የካሣውን መጠን ለመወሰን የተሽከርካሪውን ዓመታዊ የተጣራ ገቢ በተመለከተ ባለንብረቱ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በህጉ አግባብ ያሳወቀውን የገቢ መጠን ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብና መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• በአንድ የመንግስት ባለስልጣን ተረጋግጦ የተሰጠ የሰነድ ማስረጃ በህጉ መሠረት ተቃውሞ ቀርቦበት ዋጋ የሌለው ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ማስረጃው በማስረጃነት ዋጋ ሣይሰጠው ሊታለፍ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ | 89640 | የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>ሰይፈዲን አብዱልቃድር | መስከረም 23/2006 | 281 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010, 2011, 2090, 2091, 2141, 2152, 2153<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136, 138, 180 (1) | | | | |
| | **ንብረት** | | | | |
| 70. | የአንድ እምነት ወይም ሐይማኖት ተከታይ ወይም አማኝ በመሆን በሐይማኖታዊ ተቋሙ ውስጥ የመቃብር ቤት ገንብቻለሁና የቤቱን ግምት ይከፈለኝ በሚል ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር በተገናኘ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179 ድንጋጌ ተፈፃሚ ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1179<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 11,27 (1-3)<br>UDHR-Art. 18<br>ICCPR.Art. 18(1) | 85979 | የሐረር (ደ/ሳ) ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን<br>እና<br>ወ/ሮ ማንያህልሻል አበራ | መጋቢት 13/2005 | 286 |
| 71. | ከመንግስት የተከራየውን ቤት ከአከራዩ ፈቃድ ውጪ ለ3ኛ ወገኖች አከራይቶ ሲገለገል የነበረ ሰው በመንግስት መመሪያ መሠረት ቤቱ ተከራይቶ ሲሰራበት ለነበረው ሰው በመተላለፉ ምክንያት የመጀመሪያው ተከራይ በመመሪያው መሠረት ቤቱ የተላለፈለት ሰው ላይ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 88798 | አቶ ሙሉ አብርሃ ገ/ሕይወት<br>እና<br>እነ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት (ሶስት ሰዎች) | ሐምሌ 18/2005 | 291 |
| 72. | •የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጥበቃ ሥር የሆነ ይዞታ ሲኖረው ስለመሆኑ፣<br>•የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም አይነት መብት በሌለው ሰው ላይ ስለመሆኑ፣<br>•የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርብ ሰው ንብረቱ በይዞታው ሥር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚዉ የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጥር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ፣ | 80241 | ጽናት የሆቴል ቱሪዝም ስራዎች ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ ዳመነ ነጋ (አምስት ሰዎች) | የካቲት 12/2005 | 295 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | •የሁከት ተግባር ተፈጥሯል ለማለት ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ሥር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ወይም ረብሻ የፈጠረበት ስለመሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>•በህግ አግባብ በተደረገ የኪራይ ውል መነሻነት ይዞታን በእጁ ያደረገ ሰው (ተከራይ) ላይ አከራይ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | | | | |
| 73. | የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተገናኘ ንብረትነቱ ከአገር የወጡ ኤርትራዊያን የሆነ ቤትን ለማስተዳደር ውክልና የተሰጠው ሰው የመሸጥ ውክልና በባለቤቱ ያልተሰጠ ቢሆንም እንኳን በሚመለከተው የመንግስት አካል በተሰጠ (በተላለፈ) መመሪያ መሠረት ከተወካዩ ቤቱን የገዛ ገዥ ተወካዩ ቤቱን የሸጠለት በሌለው የውክልና ስልጣን ነው በሚል ገዝቶ ስመ ንብረቱ ከተላለፈለት በኂላ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ቤቱ ለባለቤቱ ሊመልስ ይገባል ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀጽ 2(1), 4(1), 5(1)(ሀ) | 83060 | ገ/ማሪም ገ/መድህን<br>እና<br>ጣዕመ ወ/ስላሴ | ሰኔ 21/2005 | 300 |
| 74. | የውርስ ሀብትን እንዲያጣራ የተመደበ የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረትነቱ የሟች የግል ሀብት መሆን በተመለከተ በሪፖርቱ ገልጿል በሚል ምክንያት ከንብረቱ ጋር በተገናኘ የባለሀብትነት ክርክር ያቀረበውን ወገን ጥያቄ በአግባቡ ባለማስተናገድ ውሣኔ ላይ መድረስ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መግስት አንቀጽ 40(1), 37<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1206 | 83665 | ወ/ሮ እታፈራሁ ፀጋዩ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሰረት<br>ግርማ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 22/2005 | 305 |
| 75. | • አንድ ሰው ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የሚችለው በህግ ጥበቃ የሚደረግለትንና ያለውን መብት እንጂ የሌላውን መብት ስላለመሆኑ፣<br>• በህግ ጥበቃ የሚደረግለት መብት ሣይኖር በስሙ የተመዘገበ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቅተ ከያዘ ሰው ንብረቱን በመንደር ውል የገዛ ገዢ ተገቢውን ማጣራት በማድረግና፣ በጥንቃቄ፣ የገዛና የቅን ልቦና ያለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት | 88084 | ወ/ሮ ወጋየሁ ታምሩ<br>እና<br>እነ የወ/ሮ አስካለ<br>ወሰኔ ወራሽ<br>ፍሬዘውድ ጌታቸው<br>(ሁለት ሰዎች) | ህዳር 19/2006 | 309 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ደንብና አሰራርን መሠረት ያላደረገ እንዲሁም ከስልጣን ውጪ የተሰጠና በህግ ፊት የማይፀና ስለመሆኑ በማናቸውም ማስረጃ ለማረጋገጥ የተቻለ እንደሆነ በተሰጠው የምስክር ወረቀት የተፈጠረውን የህጉን የህሊና ግምት ማፍረስ የሚቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196, 2884, 2882-2884<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(1)(2) | | | | |
| 76. | ፍርድ ቤቶች ከሣሽ በክሱ ገልፆ በትክክል ዳኝነት የጠየቀበት ጉዳይ በቤት ላይ ያለውን የባለሀብትነት መብት ለማስከበርና የመፋለም ክስ ሆኖ እያለ ክሱ የቀረበው በአዋጅ የተወረሰ ቤት ወይም ከአዋጅ ውጪ በባለስልጣን ቃል ትእዛዝ ወይም በቀላጤ የተወሰደን ቤት ለማስመለስ ነው በሚል ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሚሰጡት ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 47/67<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2257 | 86049 | አቶ ሻፊ አብዱራህማን አብዱ<br>እና<br>ወ/ሮ አንሻ እንድሪስ (ሶስት ሰዎች) | መስከረም 20/2006 | 313 |
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | |
| 77. | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት አንድ ሰው በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ንብረት ባለቤት ለንብረቱ የመድን ዋስትና የገባ ሆኖ የመድን ተቋሙ በመድን ውሉ መሠረት ጉዳት ለደረሰበት ወገን የጉዳት ካሣ በመክፈል በጉዳት አድራሹ ንብረት ባለቤት ላይ ብቻ ክስ በመመስረትና ጉዳቱን በቀጥታ ያደረሰውን ሰው በመተው ጉዳቱ ለደረሰበት ሰው የከፈለውን የጉዳት ካሣ ክፍያውን እንዲከፍለው ለመጠየቅ ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677, 1896, 2081, 18, 2156<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 36(2) | 89504 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ<br>እና<br>እነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን (ሁለትት ሰዎች) | መስከረም 22/2006 | 317 |
| 78. | • ባለፎቶግራፍ ወይም ባለስዕሉ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ ወይም ስዕል በህዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑና ፎቶው ወይም ስዕሉ ጥቅም ላይ ለዋለበት የማስታወቂያ ሥራ ባለፎቶው ወይም ባለስዕሉ ካሣ ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ፣ | 91710 | ሕጻን ሪያን ሚፍታህ<br>እና<br>ኤልሲውዲ ኬብልስ | ህዳር 16/2006 | 319 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • ለባለ ፎቶው ወይም ለባለስዕሉ የሚከፈለውን የካሣ መጠን ድርጊቱን የፈፀመው ሰው በዚሁ ድርጊት ያገኘው ሀብት (ጥቅም) ተመዛዛኝ በሚሆንበት መጠን በዳኛች ሊወሰን ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 28 29(2), 2142 | | ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር | | |
| 79. | • ጥቅምን መሠረት ባላደረገ ሁኔታ ህፃናትን (እድሜው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰውን) አሳፍሮ በመንዝ ወቅት በደረሰ አደጋ ምክንያት በህፃናቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለቤትና በወቅቱ በተሽከርካሪው ሲገለገል የነበረ ወይም ሹፌሩ የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርባቸው ስለመሆኑ፣<br>• የተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው ጥቅም በሌላው ግንኙነት መነሻ በተሽከርካሪው ተሳፍሮ ሲንዝ በነበረ ሰው ላይ ለሚደርስ የአደጋ ጉዳት ካሣ ለመክፈል የማይገደድ ቢሆንም ጉዳቱ የደረሰው ከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ ሊደረግላቸው በሚገባ ህፃናት ላይ በሆነ ጊዜና ህፃናቱም ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ በተሽከርካሪው ላይ የተጫኑ (የተሣፈሩ) እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 36(2), 15, 25<br>የህፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3, 6(1)<br>የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4(1), 5(1)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2126(2), 2127, 2130 2131, 2089(2), 2081(1) | 92020 | እነ የኢ.ፌ.ዲ.ፌ ፌዴሬሽን ምክር ቤት (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ቄስ ማሞ ይታፈሩ | ታህሳስ 15/2005 | 323 |
| 80. | አንድ ሠው በሰራው ሥራ ወይም በፈፀመው ድርጊትና ድርጊቱ በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ምክንያት በ3ኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በፍ/ብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ የሚሆን ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2069 | 88432 | ወጣት ደሣለኝ ወንታ<br>እና<br>አቶ ኡስማን መሐመድ | መስከረም 22/2006 | 327 |
| 81. | •አንድ የመንግስት መ/ቤት በሠራተኛው ተግባር በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው በሠራተኛው የተፈፀመው ጥፋት የሥራ ጥፋት ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣<br>•አንድ ጥፋት የሥራ ጥፋት ነው ተብሎ የሚወሰደው ጥፋት አድራጊው በጥፋቱ ላይ | 82154 | አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ<br>እና | መጋቢት 24/2005 | 330 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወደቀው በቅን ልቦና በስልጣኑ ለሥራው ክፍል መልካም ያደረገ መስሎት የፈፀመው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ከዚህ ውጪ በሆነ ጉዳይ ግን ጥፋቱ እንደ ግል ጥፋት የሚቆጠር ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2126, 2127 (1)(2)(3) | | ተጠሪ፡ አቶ ፍቅሩ ኃይሌ | | |
| **የዳኝነት ስልጣን** | | | | | |
| 82. | ከንግድ ምዝገባ ፈቃድ ጋር በተገናኘ የሚነሱ የፍሬ ነገር ክርክሮችን የመደበኛ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 686/2002 አንቀጽ 61 | 81934 | የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት<br>እና<br>50 አለቃ ታምራት ከበደ | የካቲት 28/2005 | 336 |
| 83. | ከአስጐብኚና የጉዞ ወኪል የንግድ ሥራ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ መኪኖችን በተመለከተ የሚቀርብ ክርክርን መደበኛ ፍ/ቤቶች በቀጥታ ክስ ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 87(1), (5), (9), (10),<br>ደንብ ቁጥር 146/2000 | 86817 | የኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>ግሎሪ ኢትዩጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር | መስከረም 22/2006 | 338 |
| 84. | የክርክሩ ገንዘብ መጠን ከአምስት ሺህ ብር በታች በመሆኑ ምክንያት ብቻ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የሚቀርብን ክርክር የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን አላቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 138, 142<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(1), 231(1)(ለ),<br>አዋጅ ቁ. 416/96 አንቀጽ 41(1), | 89530 | ቲኤንቲ ኮንስትራክሽንና የንግድ ስራዎች ድርጅት<br>እና<br>አቶ እያዩ ደጀኔ | ጥቅምት 21/2006 | 341 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 85. | ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በተገናኘ የማህበር የሥራ ኃላፊዎችን በተመለከተ ገንዘብ አጉድለዋል በማለት ገንዘቡ እንዲከፈል ማህበሩ በኃላፊዎቹ ላይ የሚያቀርበው ክስ አስቀድሞ በእርቅ ካልተቻለ ደግሞ በሽምግልና ሊታይ የሚገባው እንጂ በቀጥታ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት አይችልም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49(1-4), 47(1), 26(2), 39(1)(ለ)(ሐ), 152<br>አዋጅ ቁጥር 402/96 አንቀጽ 46<br>ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 14(ሀ)(ሐ)(መ) | 90737 | የንጋት ኮከብ ሸማቾች ኃ/የተ የግል ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ የሴፍ እንድሪስ (አስር ሰዎች) | ህዳር 16/2006 | 344 |
| 86. | አንድን ክርክር በማስተናገድ ላይ ያለ የክልል ፍ/ቤት በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ተቋም (ድርጅት) አግባብነት ያለው የጣልቃ ገብ አቤቱታ በቀረበለት ጊዜ ጉዳዩን ጣልቃ ገቡን ወደ ክርክሩ በማስገባት አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሌለው በመሆኑ ክርክሩ ጣልቃ ገብን ባካተተ መልኩ ለማየት ወደሚችለውና ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ጉዳዩ ቀርቦ ሊታይ የሚገባ መሆኑን ገልፆ መዝገቡን መዝጋትና ተከራካሪዎችን ማሰናበት የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),14<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(4)<br>የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 64(4)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 231(1)(ለ) | 90920 | ዓባይ ኢንሹራንስ አ.ማ<br>እና<br>አቶ አለማየሁ አሰፋ | ህዳር 06/2006 | 347 |
| | **ወንጀል** | | | | |
| 87. | አንድ ሠው በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኂላ በተመሳሳይ ማስረጃ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ተጠያቂ ነው (ኃላፊነት አለበት) ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 141 | 78470 | አቶ ታሪኩ ጫኔ<br>እና<br>የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | ሚያዝያ 07/2005 | 351 |
| 88. | አንድ ሠው በአንድ ወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ የሆነ ውሣኔ ተሰጥቷል | 85237 | ዘካሪያስ ገ/ጻዲቅ | መጋቢት 27/2005 | 355 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በማለት በድጋሚ ልከሰስ አይገባም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ከዚህ ቀደም ተጣርቶ ክስ የቀረበበትና የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት የወንጀል ድርጊትን በድጋሚ (ለሁለተኛ ጊዜ) ክስ ቀርቦበታል ከተባለው የወንጀል ድርጊት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 2(5), 678, 696(ሐ) እና 378<br>ህገ መንግስት አንቀጽ 23 | | እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | | |
| 89. | በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሣሽ ላይ የሚወሰነው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም እንዲገደብ ለማድረግ ስለማይችልባቸው ሁኔታዎች፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 194(1) እና (2)¸190¸192 | 85596 | እነ ሰይፉ ደስታ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ | መጋቢት 25/2005 | 359 |
| 90. | ህጋዊ መከላከል (Legitimate self-defense) በወንጀል የማያስቀጣው የራስን ወይም የሌላን ሰው መብት ህገ ወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገ ወጥ ጥቃት ለማዳንና ጥቃቱ እንዳይደርስ ከማድረግ ሌላ አማራጭ (መንገድ) ሣይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 78 ,79 | 86570 | ጌታቸው ገላዬ ፈረደ<br>እና<br>የደቡብ ክልል ዐቃቤ ሕግ | ሚያዝያ 07/2005 | 363 |
| 91. | • አንድ ሠው የአራጣ ወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት አግባብ፣<br>• በወር 10% ወለድ ታስቦ እንዲከፈል በመስማማት ገንዘብ ማበደር በአራጣ የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ 667(1) | 80119 | አቶ ተድላ ተገኘ<br>እና<br>የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ | የካቲት 11/2005 | 367 |
| 92. | • በሌላ ሰው ጥቅም የሥራ አመራር ላይ ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>•በተከታታይ ለተፈፀመ ወንጀል ይርጋ ስለሚቆጠርበት አገባብ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/፣702/3/፣219/2/ | 79389 | እነ ዶ/ር ታጁዲን ያህያ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የአማራ ክልል ዐ/ሕግ | መጋቢት 12/2005 | 371 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 93. | አንድ ሰው በስራው ስልጣን መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የህዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጐዳ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 411 መሠረት በወንጀል ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 411(ሐ), 407 | 86845 | የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ<br>እና<br>አቶ ሰለሞን ዩሐንስ | መስከረም 22/2006 | 374 |
| 94. | •የአንድ ደርጊት ወይም ግድፈት ወንጀልነት በህግ በግልጽ ተደንግጐ በማይገኝበት ሁኔታ የድርጊቱን ወይም የግድፈቱን ፈፃሚ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>•በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለ ድርጊቱና አፈፃፀሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ህግ አነጋገር በጣም የተቀራረበ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>•በንግድ ሥራ ለተሰማሩ ወይም ሌሎች ሰዎች በግለሰብ ደረጃ መጠኑ በርካታ የሆነ ገንዘብን በተደጋጋሚ በብድር የመስጠት ተግባር በህግ የተከለከለ ወይም በወንጀል የሚያስቀጣ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 2, 23(2), 3, 61<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 112<br>አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1), (ሽ), 2(ሀ), | 81178 | የኢዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ<br>እና<br>እነ አቶ ከበደ ተሰራ (ሁለት ሰዎች) | መስከረም 21/2006 | 380 |
| 95. | ነፍሰጡር (እርጉዝ) የሆነች ሴትን ሆዷ ላይ በመምታት ጽንሱ እንዲሞት ማድረግ ድርጊቱን በፈፀመው ሰው ላይ በግድያ ሙከራ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 27(1), 581(ለ), 540 | 90089 | ዘኒት አባቡ<br>እና<br>የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ዐ/ህግ | ጥቅምት 20/2006 | 384 |
| 96. | • አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈጽሟል ሊባል የሚችለው የድርጊቱን ውጤት እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ድርጊቱ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ማወቅ ይችል ነበረ ለማለት የሚቻል እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>• አንድ ሰው የፈፀመው ድርጊት በቸልተኛነት ነው ለማለት በመስፈርትነት ሊወሰድ የሚገባው የድርጊቱ ፈፃሚ በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ | 93741 | አቶ አብነት ዋቆ ብሩ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ | ታህሳስ 14/2005 | 387 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ስለመሆኑና ይህም የድርጊቱ ፈፃሚ የነበረው እውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባውን እውቀትና ግንዛቤ መመዘን ያለበት ከግለሰቡ እድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ የትምህርት ደረጃ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 59(1), 543(2), 57 | | | | |
| 97. | ፈቃድ የሌላቸው የጦር መሳሪያዎችና ጥይቶችን በቤቱ ውስጥ አከማችቶ የተገኘ ሰው መሣሪያዎቹን ለመነገድ በሚል ሀሳብ የያዘ መሆኑ የተረጋገጠ ካልሆነ በስተቀር ግለሰቡ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ሣይሆን በአንቀጽ 809(ሀ) ሥር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ), 809(ሀ) | 93173 | እነ አቶ ተዋበ እስጢፋኖስ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ | ታህሳስ 17/2006 | 391 |
| 98. | አንድ ሠው የአንድን ጉዳይ መከሰት በምክንያትነት በመግለጽ ከሌላ ሰው ገንዘብን ተበድሮ መውሰድ ተከስቷል የተባለው ጉዳይ ካለመከሰት ጋር በተገናኘ ተበዳሪው በእምነት ማጉደል ወንጀል ሊያስጠይቀው የሚችል ስላለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 675 | 89276 | ተፈሪ ሚናሞ<br>እና<br>የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ዐቃቤ ሕግ | መስከረም 23/2006 | 395 |
| 99. | • አንድ ሠው ወንጀል አደረገ የሚባለው ህገ ወጥነቱ እና አስቀጪነቱ በህግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ስለመሆኑ፣<br>• ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በሙላ አሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆኑ ድርጊቱን የራሱ ያደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 2፣23(1)፣ 32(1) | 91535 | አቶ አህመድ አደም በሽር<br>እና<br>የአማራ ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ | የካቲት 12/2006 | 400 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 111፣112፣141፣142 | | | | |
| **ባንክ እና ኢንሹራንስ** | | | | | |
| 100. | የመድን ዋስትና ሽፋን ውል ተደርጓል እንዲሁም ውሉ ተሻሽሏል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>የንግድ ህግ፡ 657 | 78180 | አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር ንጉሴ | መጋቢት 09/2005 | 405 |
| 101. | • አንድ ውል በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ ለማከናወን ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• የመድን ዋስትና ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ከትራንስፖርት ጋር በተገናኘ በወጡ ህጐች ከተፈቀደው የመጫን አቅም በላይ ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ መድን ሰጪው የዋስትናውን ሽፋን ገንዘብ ለመድን ገቢው የመክፈል ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ) | 90793 | ግሎባል ኢንሹራንስ<br>እና<br>እነ አቶ ፍጹም ሳቀው (ሁለት ሰዎች) | ታህሳስ 04/2006 | 410 |
| **አፈፃፀም** | | | | | |
| 102. | • በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለማስፈፀም ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>• በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድን በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም ሂደቱ ክርክር በተነሣ ግዜ የፍርድ አፈፃፀሙን በያዘው ፍ/ቤት ክርክሩ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 458-460 | 78206 | እነ ወ/ሮ ዩስራ አብዱልመኢን (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አብዱልቀኒ አብዱልሙኢን | ሰኔ 20/2005 | 415 |
| 103. | • በአንድ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ ፍርድ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁ የፍርድ ባለገንዘቦች ያሉ እንደሆነ አፈፃፀሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 መሠረት ሊስተናገድ የሚገባ እንጂ በሌላ የፍ/ባለመብት ምክንያት በሌላ የአፈፃፀም መዝገብ ላይ የተሰጠው | 88867 | ሪዩስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማህበር<br>እና | ታህሳስ 28/2006 | 423 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የእግድ ትእዛዝ ተነስቶ የአፈፃፀም ጥያቄው ካልቀረበ በስተቀር ሊቀጥል አይችልም ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• አፈፃፀሙ በሚካሄድበት ወቅት በንብረቱ ላይ የመያዣ ውልን መነሻ በማድረግ የቀዳሚነት መብት አለን የሚሉ ወገኖች ያሉ እንደሆነም ጥያቄው በቀረበ ጊዜ እንደየአግባብነቱ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>• አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በንብረቱ ባለቤት ላይ የገንዘብ ክፍያ ፍርድ አስጥተው እና ገንዘቡም እንዲከፈላቸው ጥያቄ ያቀረቡ የፍርድ ባለገንዘቦችን አስቀርቦ ጥያቄያቸውን በመመርመር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አኳያ አገናዝቦ በመመልከት አፈፃፀሙ ሊመራ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403, 378 | | የአክሱም ኮንስትራክሽን ባለቤት አቶ ጌታሁን ሁሴን | | |
| 104. | ለፍርድ አፈፃፀም ከተያዘ የሀራጅ ጨረታ ሽያጭ ጋር በተገናኘ ለሁለተኛ ጊዜ በወጣው ጨረታ የተያዘው ንብረት ሊሸጥ የሚገባው ባለሙያ ካቀረበው የንብረቱ ግምት ዋጋ በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ብቻ ሣይሆን የባለሙያው ግምት ሳይጠበቅ በሁለተኛው ጨረታ ከተወዳዳሪዎች መካከል ከፍተኛ የሆነውን ዋጋ ላቀረበው ተጫራች ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 428(1) | 89088 | የኢትዩጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ሞላ እርቄ | ታህሳስ 17/2006 | 426 |
| 105. | አንድን የተሰጠ ፍርድ ከማስፈፀም ጋር በተገናኘ የአፈፃፀም ስልጣን መሰረቱ ፍርዱን መስጠት ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም የሚያስችል ውክልና ማግኘት እንጂ የፍርድ ባለዕዳውን ወይም ባለመብቱ የሚኖርበት ክልል (ከተማ) ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | 85764 | እነ አቶ ኃ/ሚካኤል ታደሰ (አራት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ተስፋ ታደሰ | መስከረም 21/2006 | 429 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | |
| 106. | የመሬት አስተዳዳር ጽ/ቤት ቀድሞ የተሰጠን የቤትና ቦታ ካርታና ፕላን ጠፍቷል በሚል ሲጠየቅ በምትኩ ሌላ ሊሠጥ የሚገባው በ3ኛ ወገኖች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት | 81023 | አቶ ገላና ኦልጅራ<br>እና | ግንቦት 5/2005 | 433 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለማስወገድ በቅድሚያ ጠያቂው በቂ ዋስትና እንዲሰጥ በማድረግ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1197(2) | | እነ አቶ ገዛኸኝ ፋይስ<br>(ሶስት ሰዎች) | | |
| 107. | •አንድ የመንግስት ሠራተኛ መ/ቤቱን በመወከል ተቋሙ ከ3ኛ ወገን ጋር ካለው አለመግባባት ጋር በተገናኘ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት በዳኝነት ተሰይሞ ለጉባኤው የሚከፈለውን አበል ክፍያ መወሰኑ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሟል ሊያስብለው የሚችል ስላለመሆኑ፣<br>•በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ዳኝነት የተሰየመ ዳኛ በህግ ስላለበት ኃላፊነት፣<br>•የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ሰው በግልግል ዳኝነቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ በወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 351(2)(መ), 317, 318(መ)<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 399<br>የአ.አ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አዋጅ ቁ. 6/2000 አንቀጽ 31 | 80301 | አቶ አንተነህ ሲሳይ<br>እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ | ሚያዝያ 24/2005 | 440 |
| 108. | የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታነት፣ ወይም ወደ አክስዮን ማህበር፣ በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለሀብቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ ሒሣቦችን ለመሰብሰብ ዕዳዎችን ለመረከብና የፍርድ ቤት ጉዳዮችን ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 208/92 አንቀጽ 5፣6 | 88060 | የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ምስጋናው ጥሩነህ | መስከረም 23/2006 | 444 |
| 109. | • የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የማስተዳደር ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ፣<br>• የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በህግ የተሰጠውን የማስተዳደር ስልጣን መሠረት በማድረግ በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬት በተመለከተ የከተማዋን መሪ ፕላን እንዲሁም የከተማውን ማህበረሰብ ፀጥታና ደህንነት ታሣቢ በማድረግ በከተማው የሚገኝ ቦታ (መሬት) ለምን ለምን አገልግሎት መዋል እንዳለበት የመወሰን ስልጣንና ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑና ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደ የሁከት | 88959 | የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>ደብረ አማን ተክለኃማኖት ቤተክርስቲያን | ህዳር 17/2006 | 447 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተግባር ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 11(2)(ለ)(ሰ), 38 | | | | |
| 110. | በአቃብያነ ህግ ሙያ የተሰማሩ ሠዎች ላይ ከዲሲፒሊን ጉዳዩች ጋር በተያያዘ ክስ በቀረበ ጊዜ ጉዳዩ በተዋረድ በተቋቋሙትና ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ታይቶ ሊወሰን ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የአቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁ. 44/1991 አንቀጽ 78, 79, 82(1)(2), 83(1)(3), 84(ሀ), 85, 86(ሀ)<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 25, 37 | 92546 | አቶ አብዱራዛቅ ኢብራሒም<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ህግ | ታህሳስ 18/2006 | 450 |
| 111. | አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በህጉ ከተመለከው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበሰብ ሊፈቅድ የማይችል ስለመሆኑ፡-<br>አዋጅ ቁ. 621/2001 አንቀጽ2/2/፣3/4/፣14/5/፣14/2/፣6፣90፣111/2/፣112፣108፣110<br>ደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 18/3/፣10/2/፣36 | 75877 | የኢትዮጲያ የህግ ባለሙያ ሴቶችማህበር<br>እና<br>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ | መስከረም 23/2005 | 454 |

# አሠሪና ሠራተኛ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 80343

ግንቦት 6 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ዋሊያ የቆዳ ማለስለሻ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አቶ አይሸሹም መድፉ በመዝገብ ቤት እሰማለሁ በማለታቸው ዛሬ አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** አቶ ደረጀ ውለታው - ተጠሪም በተመሳሳይ ምክንያት አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ ሠራተኛ በስራ ላይ እያለ ለደረሰ የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያ እንዲከፈለው በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1) አግባብ አሰሪውን ያለጥፋት በስራ ክርክር ችሎት ከሶና አስፈርዶ ክፍያውን ከተቀበለ በኋላ በዚያው ጉዳት የአሰሪውን ጥፋት መነሻ በማድረግ የጉዳት ካሳ ክፍያ ከውል ውጪ ባለው ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በተጨማሪ እንዲከፈለው በፍ/ብሔር ችሎት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የህግ አግባብ መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ነበር፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ በመስራት ላይ እያለ አራት የቀኝ እጅ ጣቶች እና ሦስት የግራ እጅ ጣቶች በማሽን የመቆረጥ የአካል ጉዳት እንደደረሰበትና ጉዳቱም የደረሰው በአሰሪው ጥፋት መሆኑን በመግለፅ እና በዚህ ምክንያት ሊከፈለው የሚገባው የጉዳትና ሞራል ካሣ ክፍያ በድምሩ ብር 335,680 አመልካች እንዲከፍለው እንዲወሰንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ አሁን ክስ ባቀረቡበት የአካል ጉዳት ካሣ ክፍያ ከዚህ ቀደም በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1)፣ 97 እና 109 ድንጋጌዎች መሰረት በስራ ክርክር ችሎት ክስ አቅርቦና በዚሁ መሰረት ብር 24,000 አስፈርዶ ገንዘቡን በአፈፃፀም ከተቀበለ በኋላ በዚያው ጉዳት ተጨማሪ የጉዳት ካሣ ክፍያ ጥያቄ ለማቅረብ የማይችል መሆኑን በመጀመሪያ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ-ነገር ደረጃም ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ጥፋት ባለመሆኑ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንና በድጋሚ የቀረበው የክስ አቤቱታም የህግ መሰረት እንደሌለው በመግለፅ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ሊወሰን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አሁን የቀረበው ክስ ከከዚህ ቀደሙ ክስ ጋር ጭብጣቸው የሚለያይ ነው በሚል ምክንያት የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉን ከገለፀ በኋላ ፍሬ-ነገር ክርክሩን አስመልክቶ አሠሪው ተጠሪ በሚሰራበት ማሽን ላይ ተገቢ የጉዳት መከላከያ መሣሪያ ባለመግጠሙ እና በአሰሪው

ጥፋት ጉዳቱ የደረሰ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው ሲል ከወሰነ በኋላ የጉዳት ካሣ መጠኑን በተመለከተም ተገቢ ነው ባለው አኳኋን አስልቶ ባጠቃላይ ብር 139,219.9 አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ቀርበው እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ የበታች ፍ/ቤት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡ አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ለሁለቱም ክሶች ብቸኛ ምክንያት የሆነውና በተጠሪ ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት ካሣ ክፍያ በስራ ክርክር ችሎት ተወስኖለት በአፈፃፀም ካሳውን የተቀበለ ሲሆን ሆኖም ግን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 96(3) ድንጋጌ አግባብ የጉዳት ካሣ ጥያቄ የማቅረብ መብት የተሰጠው ሰራተኛው ከፍ/ብሔር ህጉና ከአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህጉ አንዱን በመምረጥ በአሰሪው ላይ ያለጥፋት ኃላፊነት ወይም በጥፋት ላይ በተመሰረተ በአንዱ ክስ የማቅረብና እንዲካስ እንጂ ያለጥፋት ክስ አቅርቦ ካሣውን ከተቀበለ በኋላ በዚያው የአካል ጉዳት በጥፋት ላይ በተመሰረተ ኃላፊነት ድጋሚ የጉዳት ካሣ ለመጠየቅ አይደለም፡፡ የአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 በአዋጁ ውስጥ እንዲካተት የተደረገው በሰራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት በአሰሪው ጥፋት ከሆነ ለሰራተኛው ሊከፈለው የሚገባ የካሣ መጠን በአዋጁ አንቀጽ 109 ስር በተወሰነው እንዳይገደብ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባው ከፍ ሲል በተገለፀው መልኩ ሆኖ ሳለ የበታች ፍ/ቤቶች ለድንጋጌው የሰጡት ትርጉም ከድንጋጌው አነጋገር ጋር የማይሄድ ከመሆኑም በላይ አንድ ተጎጂ ለአንድ ጉዳት ሁለት ጊዜ ካሣ የመጠየቅና ሁለት ጊዜ ካሣ የማግኘት መብት አለው በማለት የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ከበቂ ኪሣራና ወጪ ክፍያ ጋር ተሽሮ እንዲወሰንለት በመጠየቅ አመልክቷል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ተጠሪ አንድ ጊዜ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ያለጥፋት ኃላፊነት በአመልካች ላይ በስራ ክርክር ችሎት ክስ አቅርቦ እና አስፈርዶ የጉዳት ካሳ ክፍያውን ከተቀበለ በኋላ በዚያው ጉዳት እንደገና አሰሪውን በጥፋት ላይ በተመሰረተ ኃላፊነት በፍ/ብሔር ክርክር ችሎት ሌላ ክስ አቅርቦ የጉዳት ካሳ እንዲከፈል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ ጉዳት ከደረሰበት አሰሪው ጥፋት ባይኖርበትም ለደረሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ ስር የተመለከተ ሲሆን የካሣ መጠኑም በህጉ በተቀመጠው ስሌት መሰረት የሚከፈል ስለመሆኑ ከተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 109 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን የጉዳት ካሣ ዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ እና አይቶ ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው አካልም የሥራ ክርክር ችሎት እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 138(1)(ሠ) ድንጋጌ ስር ተለይቶ የተቀመጠ ጉዳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ጉዳቱ በሰራተኛው ላይ ሊደርስ የቻለው በአሰሪው ጥፋት ምክንያት የተነሳ እንደሆነ ሰራተኛው የጉዳት ካሣ ክፍያ ጥያቄውን አግባብ ባለው ህግ መሰረት መጠየቅ እንደሚችል ከተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 96(3) ድንጋጌ



www.chilot.me

ይዘት መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በዚህ ንዑስ አንቀጽ አግባብ መሰረት የሚቀርብ የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄም በፍትሐብሔር ክርክር ችሎት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተጠቃሹ አዋጅ እና አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው ሰራተኛው በህጉ የተመለከቱትን መብቶች በአግባቡ እና በቅጡ በትክክል ተገንዝቦ እንደየጉዳዩ ሁኔታ ዓይነት እና አግባብነት በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅመውን የመብት አድማስ አውቆ በመለየት ተገቢው መብቱ ከመነጨበት ህግ አግባብ አንፃር ለማቅረብ ሲችል ነው፡፡ ሰራተኛው ከደረሰበት ጉዳትና ከጉዳቱ አፈፃፀም በመነሳት ከሁለቱ የአሰሪ ኃላፊነት መንገዶች ውስጥ አንዱን ብቻ በመምረጥ አሰሪውን ያለጥፋት ወይም የአሰሪውን ጥፋት መሰረት ባደረገ ኃላፊነት ክሱን ከወዲሁ ለይቶ የተሻለ መብቱ ከመነጨበት ህግ አኳያ ከሚያቀርብ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 96(1) እና 96(3) ስር የተመለከቱትን መብቶች ሁለቱንም በማፈራረቅ እንደፈለገ እንዲጠቀም ለማስቻል ታስቦ እና ተፈልጎ አይደለም፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው ክሱን መስርቶ ዳኝነት በሚጠይቅበት ጊዜ በክስ አቤቱታው ላይ የሚጠይቀውን መብት የሚያቋቁሙለትን ትክክል የሆኑትንና የሚታዩትን ተጨባጭ ፍሬ-ነገሮችን ብቻ ገልፆ በማስፈር ክስ ማቅረብ እንዳለበት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 80(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ይህ በክስ አቤቱታው ላይ ተገልፀው የሚቀርቡት ፍሬ-ነገሮችም እውነት ስለመሆናቸው በአቤት ባዩ መረጋገጥ እንዳለበት እንዲሁ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 92 ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡

የክስ አመሰራረት እና አቀራረብን አስመልክቶ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህጉ ከተደነገጉት አግባብነት ካላቸው ከፍ ሲል ከተገለፁት መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ከዚህ አኳያ ደግሞ አንድ ሰራተኛ አንድ ጊዜ በስራ ላይ የደረሰበት ጉዳትን መነሻ በማድረግ አንዴ የአሰሪውን ያለጥፋት ኃላፊነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ፍሬ-ነገሮችን በመግለፅ በሌላ ጊዜ ደግሞ ያንኑ ጉዳት በሚመለከት የአሰሪውን በጥፋት ላይ በተመሰረተ ኃላፊነት የሚያስከትሉ ፍሬ-ነገሮችን እንደፈለገ እና በዘፈቀደ በመግለጽ የተለያየ ዓይነት ክሶችን ለማቅረብ፣ በክርክር አመራር ስርዓት የሚደገፍ እና ተቀባይነት ያለው ድርጊት አይደለም፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ለዚህ ክርክር መነሻ በሆነው ጉዳት መነሻነት አመልካችን ያለጥፋት ለጉዳቱ ኃላፊ በሚያደርገው አኳኋን በስራ ክርክር ችሎት ክስ አቅርቦ እና የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያውን ብር 24,000 አስፈርዶ በአፈፃፀም መቀበሉ ይታወቃል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከፍ ሲል በተገለፀው መልኩ በሌላ ጊዜ በድጋሚ ያንኑ ጉዳት በሚመለከት በጥፋት ላይ በተመሰረተ ኃላፊነት የጉዳት ካሳ ክፍያ ከውል ውጪ ባለው ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በፍትሐብሔር ችሎት ታይቶ እንዲወሰንለት ያቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም ምክንያቱም ጉዳዩ በሌላ አኳኋንና መልክ ይዞ ቢሆንም አስቀድሞ ቀርቦ ውሳኔ እንዳገኘ የሚቆጠር ነው፡፡ የመጨረሻ ውሳኔ ስላገኙ ጉዳዮች የሚያወሳው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 ድንጋጌ ይዘት አድማሱ በግልጽ በተወሰኑ ጭብጦች ላይ ብቻ ሳይሆን በተከራካሪ ወገኖች ቢነሱ ኖሮ ሊወሰኑ ይችሉ በነበሩ ጭብጦች ሁሉ ላይም ጭምር በመሆኑና ከዚህ አኳያ ተጠሪ በኋላ ላይ ያቀረበው የክስ ጭብጥም አስቀድሞ እንደቀረበ እና ውሳኔ እንዳገኘ ጉዳይ የሚቆጠር በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5(2) አንፃር በድጋሚ ሊቀርብ አይችልም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች በድጋሚ የቀረበውን የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ ተቀብለው እና አይተው አመልካች ለተጠሪ ብር 139,219.9 እንዲከፍል በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ መስጠቱም ሆነ ይሄው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም መታረም ሲገባ መፅናቱ ከፍ ሲል በተገለፁት ምክንያቶች ሁሉ በአግባቡ እና ስነ-ስርዓታዊ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ፤ መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 23356 መስከረም 20 ቀን 2004 ዓ/ም ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ 117346 ሚያዝያ 18 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በህጉ ከተቀመጡት አማራጮች የላቀውን ጥቅም ወይም መብት የሚያስገኝለትን በመለየት የጉዳት ካሳ ጥያቄውን ማቅረብ ሲገባው በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ መሰረት ጥያቄውን በስራ ክርክር ችሎት አቅርቦና አስፈርዶ የካሳ ክፍያውን ከተቀበለ በኋላ እንደገና ያንኑ ጉዳይ በሚመለከት ከውል ውጪ ኃላፊነት በሚያስከትሉ ድንጋጌዎች አግባብ ያቀረበው ሁለተኛ ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በአዋጁ አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ አኳኋን የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ በስራ ክርከር ችሎት አቅርቦና አስፈርዶ የተቀበለ በመሆኑ ሌላ ተጨማሪ የሚከፈለው የጉዳት ካሳ ክፍያ የለም ብለናል፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የሃሳብ ልዩነት

እኔ በሶስተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የማልስማማ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ በሀሳብ የተለየሁባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ከላይ በአብላጫው ድምፅ ውሳኔ እንደተገለፀው ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ የነበረ መሆኑና በስራ ላይ እያለ አራት የቀኝ እጁን ጣቶች እና ሶስት የግራ እጁን ጣቶች በማሽን በመቆረጣቸው የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ጣቶቹ ከተቆረጡ በኋላ አመልካች ያለጥፋት አሰሪ በመሆኑ በስራ ላይ ለደረሰብኝ የአካል ጉዳት መክፈል የሚገባውን ካሳ ይክፈለኝ በማለት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96(1) መሰረት በማድረግ ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርከር ችሎት እስከ እዚህ ሰበር ችሎት ተከራክሮ አመልካች ለተጠሪ ብር 24,900 (ሃያ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር) እንዲከፍል ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እያለ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ችሎት ማሽኑ በሰባት ጣቶቼ ላይ ጉዳት ያደረሰብኝ የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ሳይገጠምለት በመቅረቱ ነው ፤ ጉዳቱ በአሰሪው ጥፋት የደረሰ በመሆኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በፍትሐብሔር ሕጉ ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት በሚወስኑት ድንጋጌዎች መሰረት ካሳ እንዲከፍለኝ ይወሰነልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በስራ ክርከር ችሎት ክስ አቅርቦ ጉዳዩ ውሳኔ አግኝቷል ፤ ሁለተኛ የካሳ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም በማለት መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያው ክስና በሁለተኛው ክስ የሚነሳው ጭብጥ አንድ አይደለም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ አመልካች



www.chilot.me

ለተጠሪ ብር 139,219.90 (አንድ መቶ ሰለሳ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ አስራዘጠኝ ብር ከዘጠና ሳንቲም) እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

2. አብላጫው ድምጽ በሥራ ላይ እያለ ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ አሰሪውን ጥፋት ሳይኖረው በአሰሪነቱ የጉዳት ካሳ በአዋጁ አንቀጽ 96(1) መሰረት እንዲከፍለው ከጠየቀ በኂላ ጉዳቱ የደረሰው በአሰሪው ጥፋት በመሆኑ ካሳ ይክፈለኝ በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96(3) መሰረት ለመጠየቅ አይችልም፤ ተጠሪውን በሁለቱም ድንጋጌዎች መክሰስ አይችልም፤ መጀመሪያውኑ ከሁለቱ አንደኛውን የመምረጥ ኃላፊነት አለበት በማለት ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በእኔ በኩል የአዋጅ ቁጥር 377/96 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች በአማራጭ የሚጠቀሱና የሚፈፀሙ ሳይሆኑ ጎን ለጎን በአንድ አሰሪ ላይ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ድንጋጌዎች ናቸው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ለዚህም ምክንያቴ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ድንጋጌዎች አቀራረጽና መሰረታዊ ዓላማዎች የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ስለካሳ አከፋፈል የሚያራምዳቸው መርሆዎች ናቸው፡፡

3. አዋጅ ቁጥር 377/96 በስራ ምክንያት ስለሚመጡ ጉዳቶች በምዕራፍ ሁለት ከአንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 ይደነግጋል፡፡ አዋጁ እነዚህን ድንጋጌዎች በሁለት ዘርፍ የከፈላቸው ሲሆን በዘርፍ አንድ ኃላፊነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ከአንቀጽ 96 እስከ አንቀጽ 99 ደንግጓል፡፡ በዘርፍ ሁለት የካሳ አከፋፈል ሥርዓቱን በአንቀጽ 101 እና አንቀጽ 102 ደንግጓል፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 95 ገዥነት ያለውን መርህ የሚደነግግ ሲሆን መርሁ አንድ ሰራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ጉዳት ከደረሰበት በምዕራፍ ሁለት የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑና በአዋጁ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡

4. ትርጉሙና ተፈፃሚነቱ አከራካሪ የሆነው የአዋጁ አንቀጽ 96 "በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ ኃላፊነት" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን ንኡስ አንቀጽ 1 "አሰሪው ጥፋት ባይኖረውም ሰራተኛው በስራ ላይ ሳለ በሚደርስበት ጉዳት ኃላፊ ነው፡፡ ይህም ኃላፊነት የሚወሰነው በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል" የአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 2 ከጠቅላላው መርህ ከተደነገገው በልዩ ሁኔታ ሰራተኛው ሆነ ብሎ በራሱ ላይ ላደረሰው ማንኛውም ጉዳት፣ አሰሪው ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንና ሰራተኛው በአሰሪው አስቀድሞ በግል የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች በመጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን በመተላለፍ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሰክሮ በመገኘቱ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ሰራተኛው ሆነ ብሎ በራሱ ላይ እንዳደረሰው ጉዳት እንደሚቆጠር የሚደነግግ ነው፡፡ የአንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 3 አሰሪው ሰራተኛው በሥራ ላይ ለደረሰበት ጉዳት በአዋጅ ቁጥር 377/96 ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሕጎች መሰረት ኃላፊ የሚሆንበት ልዩ ሁኔታ የሚያስቀምጥ ድንጋጌ ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ "የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ማንኛውም ሰራተኛ በአሰሪው ጥፋት የተነሳ በስራ ላይ ጉዳት ሲደርስበት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ካሳ የመጠየቅ መብቱን አይነኩበትም" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 3 የእንግሊዘኛው ቅጅ "The provision of sub Art 1 of this article shall not affecte the right of the workers to claim damage in accordance with the relevant law where an ocupational injury is a resulet of

fault on the part of the employer" የሚል ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 3 የቃላት አሰካክ አቀራረፅና ሙሉ ንባብና መልዕክት፣ በአሰሪው ጥፋት በሰራተኛው ላይ ጉዳት መድረሱ ከተረጋገጠ ሰራተኛው አሰሪው ከአንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 ባሉት ድንገጌዎች ካሳ እንዲከፍልው የሚያቀርበው ጥያቄና የሚወሰነው ውሳኔ ሰራተኛው አሰሪውን በሌላ ሕግ መሰረት ለጉዳቱ ኃላፊ እንዲባልና ካሳ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብቱን የማይነካበት መሆኑን የሚገልፅ ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

5. በእኔ እምነት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አሰሪው ለሰራተኛው በአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ኃላፊ ከሚሆንበትና ከአንቀጽ 101 እና አንቀጽ 102 መሰረት ከሚከፍለው ካሳ በተጨማሪ አሰሪው ጥፋት በፈፀመ ጊዜ ኃላፊ የሚሆንበት ድንጋጌ ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ከስራው ጋር በተያያዘ የሰራተኛው ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የሚያስፈልጉት እርምጃዎችን ሁሉ የመወሰድና እነዚህንም እርምጃዎች በሚመለከት ረገድ አግባብ ባላቸው ባለስልጣኖች የሚሰጡትን ደረጃዎችና መመሪያዎች ባለመከተል፣ ወይም በመጣስ ሰራተኛው በስራ ላይ ለአደጋ ካጋለጠና አደጋ እንዲደረሰበት ካደረገ፣ ማናቸውም አሰሪ ከሚከፍለው የካሳ ክፍያ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ምክንያት ሰራተኛው ለደረሰበት ጉዳት ከአሰሪና ሰራተኛ ከተደነገገው ውጭ በሌሎች ሕጎች ኃላፊ የሚሆንበትን የሚደነግግ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 አሰሪው በአዋጅ አንቀጽ 12(4) እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት በመተላለፍና ሌሎች ኃላፊነት የሚያስከትሉ ጥፋቶችን በመፈፀሙ በሰራተኛው ላይ ጉዳት ከደረሰ አሰሪው ከአሰሪነቱ ከሚከፍለው የጉዳት ካሳ በተጨማሪ በጥፋቱ ካሳ የመክፈል ኃላፊነቱ የማይቀርለት መሆኑን የሚደነግግ ነው የሚል ሃሳብ አለኝ ስለዚህ የአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ አሰሪዎች እንዲያከብሩና አሰሪው ጥፋት ሰራተኞች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የተደነገገው ሕግ ለማስከበሪያነት የሚያገለግል የፍትሐብሔር ቅጣት (ኃላፊነት) (civil sanction) ነው፡፡ አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 1 ጉዳቱ የደረሰው በስራ ላይ እና ከስራው ጋር በተያያዘ እስከሆነ ድረስ ሁሉም አሰሪዎች ለሰራተኛው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት ኃላፊ የሚሆኑበትን መንገድ የሚደነግግ ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ጥፋት የፈፀመ አሰሪ ጥፋት ካልፈፀመ አሰሪ የበለጠ ኃላፊነት የሚኖርበት መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ እንጅ፣ ከንዑስ አንቀጽ 1 በአማራጭ የተደነገገ ድንጋጌ አይደለም፡፡

6. በአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ በሌላ ሰው ጥፋት ጉዳት ቢደርስበት፣ ከአዋጅ አንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 ከአሰሪው ካሳ ከተቀበለ በኋላ በፍትሐብሔር ሕጉ ጉዳቱን ካደረሰው ሰው ካሳ የሚጠይቅበትን ሁኔታ በሚያስከብር መልኩ መተርጎም አለበት የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ በአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ጥፋቱን የፈፀመው አሰሪው በመሆኑ ሰራተኛው አሰሪውን ያለጥፋትና በጥፋት ለደረሰበት ጉዳት ካሳ እንዲከፍለው ከመጠየቅ የሚከለክል ድንጋጌ አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህንን መብት ለሰራተኛው የሚጠብቅ ድንጋጌ ነው፡፡

7. በኢትጵያ የሕግ ሥርዓት ካሉት የካሳ አከፋፈሎች አንደኛው ሰራተኛው ጉዳት ሲደርስበት ከአሰሪው የጡረታ አበል ወይም ካሳ ከተቀበለ በኋላ ጉዳቱን ካደረሰበት እና ለጉዳቱ ኃላፊ ከሆነው ሰው ካሳ እንዲከፍለው የሚጠይቅ መሆኑ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2094 ተደንግጓል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች በአንድ በኩል የተጠሪ አሰሪ በመሆኑ በአዋጁ ከአንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102

በተደነገገው መሰረት ካሳ ከፍሎታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተጠሪ ላይ ጉዳቱ የደረሰው አመልካች በአዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት ለሰራተኛው የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን በማሸኑ ላይ ባለመግጠሙ ምክንያት የደረሰ ከሆነ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2094 እና ሌሎች ድንጋጌዎች መሰረት ለተጠሪ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ኃላፊነቱ በአዋጅ አንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 በተደነገገው መሰረት ካሳ መክፈል ወይም በፍትሐብሔር ሕግ መሰረት ካሳ መክፈል ነው የሚለው አተረጓጎም የሕግ ሥርዓታችን ከዘረጋው የካሳ አከፋፈል ሥርዓት ጋር የሚጣጣም አይደለም ብዬ ስለማስብ፣ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች አመልካች በአዋጅ ከአንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 በተደነገገው መሰረት ለሰራተኛው (ለተጠሪ) ካሳ መክፈሉ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 2 እና በአዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገጉትን በመተላለፍ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2035 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2094 በተደነገገው መሰረት ለተጠሪ ካሳ እንዲከፍል መጠየቁን የሚያስቀርለት አይደለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 82091

መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጠበቃ ንጋቱ ታደሰ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ለገሠ ደሣለኝ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የሥራ ግንኙነት የተቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በሥር ፍ/ቤቶች በነበረው ክርክር ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮች በመነሣት አግባብነት ያለውን የሕግ ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ሕጉ ከደነገገው ውጭ አመልካች የሥራ ውሌን አቋርጧል፤ስለሆነም ለሕገ ወጥ ስንብት በሕጉ የተፈቀደውን ልዩ ልዩ ክፍያዎች ይፈጽምልኝ በማለት የክፍያ ዓይነቶችን ዘርዝሮ ዳኝነት ሲጠይቅ፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ከየካቲት 20 እስከ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት ተከታታይ ቀናት በሥራ ገበታው ባለመገኘቱ ምክንያት የሥራ ውሉ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ለ/ በሚያዘው መሠረት እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ለሕጋዊ ስንብት ክፍያ እንድንፈጽም አንገደድም በማለት ተከራክሯል፡፡

ሆኖም የአሁን አመልካች በሁለተኛው ወሰን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለመምህራን የሚያስተምሩትን የትምህርት ዓይነቶች /ኮርሶችን/ ሲደለድል፤ ለአሁን ተጠሪ እንደ መምህርነቱ የሚያስተምረውን የትምህርት ዓይነት ለመመደብ የሚቻልበትን ምክንያት ሣይገልፅ የሚያስተምረውን ኮርስ እንዲያገኝ ስለማድረጉና የኮርስ ድልደላ ከመደረጉ በፊት የነበረውን የጥር ወር ደመወዝ እንዳይከፈለው ማገዱን፤ ለምን እንዳይከፈል እንደተደረገ ተጠሪ በጽሑፍ ከመግለጽ ጋር ይኸው ደመወዝ እንዲከፈለው የካቲት 13 ቀን 2004 ዓ.ም ሲጠይቅ በጥያቄው መሠረት ያልተከፈለው ከመሆኑም በላይ ላለመክፈል የሚያስችል በቂ ምክንያት ስለመኖሩ አመልካች በአሠሪነቱ መልስ እንዳልሰጠው የተረጋገጡ እውነታዎች ናቸው፡፡



www.chilot.me

አመልካችም እነዚህን ሁኔታዎች ይቀበልና ተጠሪው የሚያስተምረውን ኮርስ አለመደልደል መብቱ እስካልተጓደለበት ድረስ ከሥራ እንዳሰናበትነው ሊያስቆጥር አይችልም በማለት ይከራከር እንጂ አመልካች ያደረገው ተግባር ተጠሪው የሚያስተምረውን የትምህርት ዓይነት አለመስጠቱ ብቻ ሣይሆን የትምህርት ዓይነቶች ለመምህራን ከመደልደላቸው በፊት ያለውን የጥር ወር ደመወዝ ለመክፈል እምቢተኛ የሆነበትን በቂ ምክንያት አቅርቦ አላስረዳም ሰለሆነም የአሁን አመልካች እንደውላቸው ሠራተኛው የሚሠራውን ሥራ የማቅረብ በሕግ ግዴታ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አመልካች ተጠሪው የሚያስተምረውን ትምህርት ደልድሎ አለመስጠቱ ብቻ ሳይሆን በተቀጣሪነቱ ሊያገኝ የሚገባውንም የጥር ወር ደመወዝ እንዳይከፈለው አድርጓል(ነፍጐታል)፡፡ ስለሆነም የተጠሪው መብት እስካልተጓደለ ድረስ የሚያስተምረውን የትምህርት ዓይነት አለመደልደል ሠራተኛውን ለማሰናበት ተፈልጐ እንደተደረገ ተግባር ሊቆጠር አይገባም የሚለው ክርክሩ በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ያለበቂ ምክንያት ደመወዝ የማግኘት መብቱን ክልከላ ያላገናዘበ፣ በመሆኑ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች የተጠሪን የጥር ወር ደመወዝ እንዳይከፈል ለማድረግ የሚያበቃው ሕጋዊ ወይም በቂ ምክንያት ሳይኖረው የዚህኑ የጥር ወር ደመወዝ እንዳይከፈል የከለከለው መሆኑና በተከታዩም በየካቲት ወር ተጠሪው ሠራተኛ መሆኑን ተቀብሎ የሚሠራው ሥራ እንዳይሰጠው የከለከለበት ወር መሆኑ እየታወቀ እና እነዚህም ሁለት ተግባራት ድርብ ውጤት ተጠሪው የአመልካች ሠራተኛ መሆኑን ተገንዝቦ እንደማንኛውም ሠራተኛ የሥራ ቀንና የሥራ ሥዓት አክብሮ እንዲገኝ ከማድረግ ይልቅ ሠራተኛነቱን ያልተቀበለው መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ እያለ እንደገና ተጠሪው በዚህ በየካቲት ወር በነበረው የሥራ ጊዜ ከየካቲት 20 እስከ የካቲት 26 ቀን ባሉት ከአምስት ተከታታይ ቀናት በላይ ከሥራ ገበታው ስለቀረ ተሰናብቷል፡፡ ይህም ሕጋዊ ስንብት መሆኑን ያመለክታል የሚለው ክርክሩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት ያላደረገ፣ ድንጋጌውን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያበቁ ሁኔታዎችን ያላሟላ ክርክር በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት በሕጉ ከተደነገገው ውጭ እንዲሰናበት ተደርጓል፣ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት ለዚህ ዓይነት ሕገ-ወጥ ስንብት ሊከፈል የሚገባውን የክፍያ ዓይነትና መጠን ገልፀው የሰጡት ትርጉም ሕጋዊ እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 125715 በቀን 18/11/2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. የአሁን አመልካች በሰበር ደረጃ ያቀረበው ክርክር ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ብለናል፡፡
3. የአሁን አመልካች ተጠሪን በሕጉ ከተደነገገው ውጭ ከሥራ አሰናብቶታል፤ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለትና ለዚህ ሕገ-ወጥ ስንብት የሁለት ወር ደመወዝ በማስጠንቀቂያ ምክንያት፤ የሥራ ስንብት 2,125.00 /ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ አምስት ብር/ የካሣ ክፍያ ብር 9000.00 /ዘጠኝ ሺህ ብር/ ያልተከፈለው የጥር ወር ደመወዝ ብር 1500.00 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ከብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ የወጭና ኪሣራ ገንዘብ ጋር ይከፈለው መባሉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ የሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ሲከራከሩ በክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

የሰ/መ/ቁ. 84661

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ዳዊት ሸዋቀና - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ስኳር ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ አቶ ጌታቸው አክሊሉ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ የኦዲት ክፍል ሀላፊ ሆኜ እየሠራሁ የሥራ አፈጻጸምህ ዝቅተኛ ነው፣እንዲሁም በሥራ ላይ ቸልተኝነት አሳይተሃል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ/ም የሥራ ውሌን ያቋረጠብኝ በመሆኑ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ካልሆነም ካሳ፣የስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ክፍያ በዘገየበት እና የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ሰጥቷል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው መልስም፡- ከሳሽ ከሥራ የተሰናበቱበት ምክንያት በተሰጣቸው የስንብት ደብዳቤ ላይ የተገለጸ ሲሆን ወደ ሥራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄም ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፣እንዲሁም እንዲከፈላቸው ከጠየቁአቸው ክፍያዎችም ውስጥ የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የተከፈላቸው ሲሆን ሌሎች ክፍያዎች ግን ሊከፈሉአቸው አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡

የመ/ደረጃ ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ያቀረበውን መቃወሚያ ቀደም ሲል በብይን ውድቅ ማድረጉን በመግለጽ በሰጠው ፍርድ፡- ተከሳሽ ለከሳሽ በጻፈው የስንብት ደብዳቤ የሥራ አፈጻጸማቸው ሲገመገም ዝቅተኛ ስለመሆኑ የተመዘኑበትን ማስረጃ ካለማቅረቡም ሌላ በሥራቸው ቸልተኝነት አሳይተዋል ቢልም በምን ምክንያት ቸልተኝነት እንዳሳዩ አልዘረዘረም በማለት የሥራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ በአማራጭ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተም የስራ መሪ ያለበቂ ምክንያት ከሥራ አሰሪው ቢያሰናብት ወደ ሥራ

የመመለስ መብት እንዳለው በፍትሃብሔር ህጉ፣በህብረት ስምምነቱም ሆነ በሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ስላልተገለጸ ተቀባይነት የለውም ሲል ወድቅ ያደረገ ሲሆን፤እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተም፡- የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ሲወስን፤ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በሚመለከት ከሳሽ የሚሠሩበት ሥራ የእምነት ሥራ እና ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ ማስጠንቀቂያ አለመሥጠት በፍ/ህ/ቁ/2577(2) መሰረት ኪሳራ የሚያስከትል አይሆንም ሲል ያልተቀበለው ሲሆን ካሳ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሰረት ያለው አይደለም በሚል ውድቅ ሲያደርግ የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የተከፈላቸው መሆኑንም በቃል ክርክር ወቅት ከሳሽ ስላመኑ በድጋሚ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ እንዲሁም ክፍያ በዘገየበት የጠየቁትን ክፍያ በተመለከተም የሚከፈላቸው ክፍያ አይኖርም ሲል ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽም በመ/ደ/ፍርድ ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የይግባኙን መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም በዋናነት ያቀረቡት የቅሬታ ነጥብ፡-

- የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና ካሳን ፍርድ ቤቶቹ በአዋጅ ቁጥር 377/1996፣በህብረት ስምምነቱና በሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሰረት መወሰን ሲገባቸው ሳይወስኑ ያለፉት አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡-

- ኮርፖሬሽኑ በደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመ ሆኖ እያለ አመልካች የተሻሩትን የሥራ መሪዎች ደንብና የህብረት ስምምነት መሰረት በማድረግ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉአቸው ያቀረቡትን ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

አመልካችም ተጠሪው ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

- አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል የሥር ፍርድ ቤቶች ከወሰኑ በኋላ ካሳና የማስጠንቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም ያሉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? በሚል መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በተያዘው ጭብጥ መሰረት ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ወደተያዘው ጭብጥ ከመመለሳችን በፊት ተጠሪው ድርጅት በአዲስ መልክ በደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ፍርድ ለመስጠት መሰረት ያደረጉት የሥራ መሪዎች ደንብና የህብረት ስምምነት ስለተሻሩ አግባብነት የላቸውም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው መሆን አላለመሆኑ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ደንብ ቁጥር 192/2003 ተፈጻሚ የሆነው ከጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ስለመሆኑ በደንቡ አንቀጽ 12 የተደነገገ ሲሆን አመልካችም ክሱን ያቀረቡት ጥር 27 ቀን 2004 ዓ/ም በመሆኑ ክሱ የቀረበው ደንቡ ጸንቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ነው፡፡ በዚህ ደንብ ቀደም ሲል በየራሳቸው የማቋቋሚያ ደንብ ተቋቁመው የነበሩት አራት የስኳር ፋብሪካዎች የስኳር ኮርፖሬሽን በሚል መቋቋማቸውን ከደንቡ መገንዘብ



www.chilot.me

የሚቻል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪው ቀደም ሲል በደንብ ቁጥር 122/1998 እንደተሻሻለው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በሚል ሲጠራ የነበረ ሲሆን የራሱ የሆነ የህብረት ስምምነት እና የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ያለው ነው፡፡ተጠሪው የህብረት ስምምነቱና የሥራ መሪዎች የመተዳሪያ ደንቡ ተሽረዋል በሚል ክርክር ስለማቅረቡ የመ/ደ/ፍርድ ቤት ፍርድ የማያመላክት ሲሆን ክርክር አቅርበዋል ቢባል እንኳን ፍርድ ቤቱ ባለመቀበል በተሻሩ የሥራ መሪዎች ደንብና የህብረት ስምምነቱ መሰረት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሰጥቶ ከሆነ ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማቅረብ ፍርዱን ማስለወጥ ሲገባው ይግባኝ አቅርቦ አላስለወጠም፡፡ በዚህ በሰበር ደረጃ ባደረገውም ክርክር የህብረት ስምምነቱ እና የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ መሻራቸውን ከመግለጹ በስተቀር በየትኛው የህብረት ስምምነትና የሥራ መሪዎች ደንብ እንደተተኩ አልጠቀሰም፡፡ ስለሆነም የህብረት ስምምነቱና የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ የተሻሩ ናቸው ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ወደ ጭብጡ ስንመለስ፡- ተጠሪው የሥራ ውሉን ለመቋረጥ የጠቀሳቸው ምክንያቶች የአመልካች የሥራ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ ነው፣ እንዲሁም በሥራ ላይ ቸልተኝነት አሳይተዋል በሚል እንደሆነ ለሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃነት ከቀረበው የሥንብት ደብዳቤ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪውም አመልካች በሥራ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ ስለመሆኑ የተመዘኑበትን ማስረጃ ባለማቀረቡ እንዲሁም በሥራ ላይ ቸልተኝነት አሳይተዋል ላለውም ምክንያቱን በመዘርዘር ማስረዳት ባለመቻሉ ሥንብቱ ህገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የሥር ፍርድ ቤቶች ደርሰዋል፡፡ በመሆኑም የሥራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ መቋረጡ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር እስከሆነ ድረስ ተጠሪ ከሳና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል የሚገባ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር አገናዝቦ መመልከት ይገባል፡፡ ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች ሥራ መሪ ናቸው፡፡ አሰሪው የሥራ ውሉን ቀሪ በማድረግ ወይም አላድስም በማለት ይህን ውሳኔ በግልጽ የሚያረጋግጥ በቂ ምክንያት የሌለው እንደሆነ ሠራተኛው ተገቢ የሆነ ኪሳራ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ/2573 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በዚህ መልኩ በህጉ የሥራ ውሉ በቂ ባልሆነ ምክንያት የተቋረጠ ከሆነ አሠሪው ኪሳራ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተሰናበቱት ያለበቂ ምክንያት መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ካረጋገጡ በኋላ ኪሳራውን ሳይወስኑ ማለፋቸው ህጉን የተከተለ አይደለም፡፡ ኪሳራ መክፈል ተገቢ መሆኑ ከታመነ ደግሞ ስለሚከፈልበት ሁኔታም አግባብነት ያላቸውን ህጎች መመልከት የሚገባ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው የ6 ወር ደመወዝ ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁት አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አንድ የሥራ መሪ የሥራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ሲቋረጥ ሊከፈል የሚገባው የኪሳራ ልክ ሠራተኛው ባለፈው ሶስት ወር ከተቀበለው ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በፍ/ህ/ቁ. 2574 (2) የተደነገገ ሲሆን ይህንኑ የህግ አነጋገር ይዘን በታህሳስ ወር 2002 ዓ/ም ወደወጣው የተጠሪ የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ስንመለስ ፡-

በአንቀጽ 51(1) በዚህ ደንብ ውስጥ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በሌሎች ህጎች ፣ደንቦች ወይም በሌላ አኳኋን ተለይቶ የተወሰነው የተሻለና የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ ባልተጠቀሱም ሆነ በተጠቀሱ ጉዳዮች፣በህብረት ስምምነት የተደነገጉት፣በአሰራር ደንብ የተወሰኑትና የሚታወቁት ስለሥራ ሁኔታ፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት፣ የሥራ አካባቢ፣ጥቅሞች፣ግልጋሎቶች፣ሥልጠና፣የሥራ ዉጤት መለኪያ ዘዴ እንዲሁም ይህን ደንብ የማይቃረኑ አግባብ ያላቸው ሌሎች የሥራ ውል ግንኙነቶች የሚመለከቱ ዝርዝር ደንጋጌዎች የሥራ መሪው የሥራ ውል አካል ሆነው ይቆጠራሉ በሚል ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚሁ ደንጋጌ መሰረትም በፍ/ህ/ጉ ከተመለከተው የኪሳራ መጠን ይልቅ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(4)(ሀ) የተመለከተው የካሳ መጠን

የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝ በመሆኑ ለአመልካችም ተጠሪው ካሳ ሊከፍላቸው የሚገባው በዚሁ የአዋጁ አንቀጽ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

ሌላው አመልካች የጠየቁት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ነው፡፡ ተጠሪው የአመልካችን የሥራ ውል ሲያቋርጥ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶችም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለአመልካች አይገባቸውም በሚል የወሰኑት አመልካች የሚሰሩት የሥራ ባህሪ በመግለጽ ሲሆን ለዚህም መሰረት ያደረጉት የፍ/ህ/ቁ. 2577(2) ድንጋጌን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (1) የሥራው ውሉ ልዩ የሆኑ ችሎታዎችን የሚጠይቁ፣የእምነት ሥራዎች እንደሆኑ አሠሪው ውሉን ቀሪ የሚያደርግበትን ወይም የማያድስበትን ምክንያት ለማስታወቅ የማይገደድ መሆኑ የተደነገገ ሲሆን ኪሳራ ለመክፈል የሚገደደው ግን ውሉ እንዲቀር የተደረገው በማይገባ ጊዜና አንደኛውን ወገን ለመጉዳት ወይም ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ባለማሰብ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን የውሉ ያለ ማስጠንቀቂያ ቀሪ መሆን አሠሪው ለሠራተኛው ኪሳራ እንዲከፍል የሚያስገድድ አይሆንም፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ውሉ ቀሪ የተደረገው በማይገባ ጊዜ ወስጥ ስለመሆኑ፣ወይም ተጠሪው አመልካችን ለመጉዳት ወይም ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ባለማሰብ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ውሉን ቀሪ ስለማድረጉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም፡፡ አመልካች በተጠሪው ደርጅት የኦዲት ክፍል ሀላፊ የነበሩ እንደመሆናቸው መጠን የሥራ ውሉ ልዩ ችሎታን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ ሥራውም በእምነት የሚሰራ በመሆኑ አስቀድሞ የሥራ ውል የሚቋረጥ ስለመሆኑ ማስታወቅ የአሰሪውን ጥቅም ሊጎዳ የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጥር ስለሚችል ማስጠንቀቂያ አለመሥጠቱ በፍ/ህ/ቁ.2577(2) እንደተመለከተው ኪሳራ እንዲከፍል የሚያስገድደው አይሆንም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ለአመልካች ከሚሠሩት የሥራ ባህሪ የተነሳ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የሥራ ውሉን በማቋረጡ ምክንያት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለመክፈል አይገደድም ያሉት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም፡፡

ሲጠቃልል፡- የሥር ፍርድ ቤቶች ለአመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም ያሉት ከዚህ በላይ በተገለጹት ምክንያቶች የተነሳ ተገቢ በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ፍርድ ቤቶቹ የወሰኑት ተገቢ ቢሆንም የሥራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ የተቋረጠ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ግን ካሳ እንዲከፈላቸው ሳይወስኑ ያለፉት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/03537 በቀን 15/10/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/126268 በቀን 17/12/2004ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. የስር ፍርድ ቤቶች የሥራ ውሉ በተጠሪው ህገ ወጥ ድርጊት ተቋርጦ እያለ ለአመልካች የካሳ ክፍያ እንዲከፈላቸው ሳይወስኑ ያለፉት ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(4)(ሀ) መሰረት የአመልካች የቀን አማካይ ደመወዝ በ180 ተባዝቶ በሚመጣው ስሌት መሰረት እንዲከፈላቸው ወስነናል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤቶች ከካሳ ክፍያ በስተቀር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያም ሆነ ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ የሠጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
4. የካሳ ክፍያን በተመለከተ በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የአፈጻጸም ክሱን ለያዘው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይጻፍ ብለናል፡፡
5. የግራ ቀኙ ወገኖች የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የየራሳውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 79476

የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች**፡-ኢትዮ ቴሌኮም VC በትክክል ሊሥራ ሰላልቻለ መቅረብ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

**ተጠሪ**፡-

1. አቶ  ዘሪሁን ታዬ
2. አቶ ተስፋዬ አለማየሁ
3. ታየች ታደሰ
4. አቶ ያሬድ ዘውገ
5. አቶ ምስራቅ ታምራት
6. ማርሸት እንግዳወርቅ
7. አቶ ደረጀ ይልማ
8. አቶ ሚሊዮን አባይነህ
9. ለምለም አስፋው
10. ካሳሁን አንዱአለም
11. መልካሙ  ሀይሉ
12. ድርሳነ ተስፋዬ
13. ማን ታጋፍቶት አበበ
14. ሄለን ተስፋዬ
15. ስለእናት አደመ
16. መስፍን ገሰሰ
17. ብዙአየሁ ደበበ
18. እታገኘሁ ዳኜ
19. ማለፊያ በቀለ
20. ወለንሳ አስታጥቄ
21. ቴዎድርስ ክበበው
22. መሰሉ ሲራጅ
23. ፍጹም ታዬ
24. ዳንኤል ግርማ
25. እንዳልካቸው መንግስቱ
26. ወይንሸት ተፈራ
27. ተሰማ ዘውዴ
28. መዐዛ መርሻ
29. አመለወርቅ ጎሹ
30. አሕመድ ሀሰን
31. ብዙአየሁ ወንድአጥር
32. ወይንሸት ምህረተአብ
33. ምስራቅ መኮንን
34. መቅደስ ታምራት
35. ወርቅነሽ እሸቱ
36. ሳምራዊት ስዩም
37. ዘነቡ ከበደ
38. ፍስሀ አሰፋ
39. መድሀኒት አግዛ
40. ጸሐይ ቸርነት
41. ተገል ማሞ

42.እኑሽ ቤተ
43.መቅደስ ደስታ
44.ቦጋለች ተድላ
45.ተገኔ ከበረ
46.ቅድስት አየለ
47.ሄኖክ አበራ
48.ታደሱ ለማ
49.ትዝታ ሀይሌ
50.ትዕግስት ነጋሽ
51.ስመኝ ዘገየ
52.ሽብሬ ሰይፉ
53.ዳምጠው ወ/ተንሳይ
54.ከተማ ኩዩ
55.ምንዳ ጠና
56.ታምራት ደነቀ
57.ደጅይጥኑ ይልማ
58.ሮማን ነጋሽ
59.የሺጥላ  እስጢፋኖስ
60.ደስታ ገሰሰው
61.ተሾመ መልከጸዲቅ
62.መቅደስ ይልማ
63.ይታየው ጠጁ
64. ምትኩ አባይነህ
65.ሁሴን አህመድ
66.ባንተየሁ ገብሬ
67.ሐያት አብዱሰላም
68.ዝናሽ ሐይሉ
69.ዘብደር ሉልሰገድ
70.እንዳለ ሙሉጌታ
71.ሱፊያ ኢድሪስ
72.ናሆም ዮሐንስ
73.ብርሃኔ ታደሰ
74.አያለሌው ክብረት
75. ሐይሉ በቀለ
76.የሺወርቅ ቤቶኒ
77. እዮብ ደጀኔ
78.መስፍን ታደሰ
79.መሰረት ባርባ
80.ንግስቴ ደግፍ
81.ማሞ  ሽፈራው
82.ወንዱ መኩሪያ
83.አብዱላህ ሙሳ
84.  ላቀች ገበየሁ
85.ፀደቀ ዳዊት
86.ውብሸት ጀማነህ
87.ዘነበች አባተ
88.አስናቀች ሽፈራው
89.አይናለም ደነቀ
90.ስንዱ ፊይሳ
91.ዘቢደር ኃ/ጊዮርጊስ
92.አባይነሽ ኃ/ሚካኤል
93.መሠረት ፋሲል
94.ዮውብዳር ምንነህ
95.ትእግስት አሰፋ
96.ኃድራ ሽኩር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርደ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የቀረበውን የደመወዝ ጭማሪና የቦነስ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪዎች በአሁን አመልካች ላይ በድሬዳዋ ከተማ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ላይ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው የተጠሪዎች ክስ ይዘትም ከቀድሞ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙንኬሽን ኮርፖሬሽን እና በሠራተኛ ማሕበር መካከል በ1999 ዓ/ም በተፈረመ የሕብረት ስምምነት መሠረት ከሐምሌ 01 ቀን 2001 ዓ/ም አስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ለሰሩበት ከሐምሌ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ የደመወዝ ጭማሪ እንዲሁም በጳጉሜ 2002 ዓ/ም ለሰራተኛ የተደረላቸውን የቦነስ ክፍያ አመልካች እንዳልከፈላቸው ገልፀው እንዚህን ክፍያዎች እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮች አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሣቸው ነጥቦች ጉዳዩ በአዲስ አበባ አሠሪና ሰራተኛ ጉሣይ ወሣኝ ቦርድ እየታየ ባለበት ሁኔታ በድጋሚ ሌላ ቦታ ክስ መቅረቡ ያለአግባብ መሆኑን፣ ተጠሪዎች የመክሰስ መብት የሌላቸው መሆኑን እና ክሱ በስድስት ወር ይርጋ የሚታገድ መሆኑን ገለፆ የተከራከረባቸው ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ተጠሪዎች ለክሱ መሠረት ያደረጉት የሕብረት ስምምነት የተፈጻሚነት ጊዜው ያላበቃለት በመሆኑ ለደመወዝና ለሌሎች ጥቅማጥቅሞች ተፈፃሚ የሚሆንበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ተጠሪዎች የደመወዝ መጠናቸውና ይገባናል የሚሉትን ጭማሪና ቦነስ መጠኑን ለይተው ያለማቅረባቸው የአመልካችን የመከላከል መብት የሚያጣብብ ከመሆኑም በላይ ከዳኝነት አሰጣጡም አመቺ ያለመሆኑን አመልካች በበጀት አመቱ የአግልግሎት ጥራትና ምርታማነቱን ከፍ ያደረገ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ክፍያዎቹ የሚጠየቁበት አግባብ የሌለ መሆኑንና በህብረት ስምምነቱም የክፍያዎቹ ጥያቄዎች የሚፈፀሙት ከማህበሩ ጋር አመልካች በሚያደርገው ድርድር እንጂ በሰራተኞች ቀጥታ ጥያቄ ያለመሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ቦርድም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለተጠሪዎች ከሐምሌ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ የደመወዝ ጭማሪ እንዲያደርግ ክፍያውም በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 18 መሰረት እንዲፈፀም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የቦርዱ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ ሁኖ እያለ መታለፉም ሆነ የህብረት ስምምነቱ ተፈጻሚነቱ ያበቃ ሁኖ እያለ ለክፍያዎቹ ጥያቄ ተፈፃሚ እንዲሆን መደረጉ ያላግባብ መሆኑን የደመወዝ ጭማሪ የሚደረገው አመልካች የአገልግሎት ጥራት እድገትና አመታዊ የትርፍ ገቢ ከተገኘ ስለመሆኑ በህብረት ስምምነቱ በግልጽ ተቀምጦ እያለና ይህ ስለመሆኑ ተጠሪዎች አግባብነት ባለው የስነድ ማስረጃ ሳያረጋገጡ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የተጠቀሰውን የደመወዝ ጭማሪ ለተጠሪዎች ይክፈል ተብሎ በአስሪና ሰራተኛ ጉዳይ ውሳኝ ቦርድ የመወሰኑንና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የመጽናቱን አግባብነት

ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸውም 1ኛ፣2ኛ፣84ኛ እና ከ86ኛ እስከ 93ኛ፣ 6ኛ፣7ኛ 8ኛ፣27ኛ፣ 53ኛ.55ኛ፣61ኛ 69ኛ፣74ኛ 81ኛ፣ 85ኛ 94ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ቀርበው መልሳቸውን በጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን 5ኛ፣ 9ኛ፣ 19ኛ፣29ኛ፣ 31ኛ፣ 38ኛ፣46ኛ፣ 48ኛ፣ 53ኛ፣ 56ኛ፣ 69ኛ፣ 73ኛ፣ 74ኛ79ኛ 81ኛ፣ 82ኛ፣ 84ኛ፣8 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች መጥሪያ በህጉ አግባብ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ ሌሎች ተጠሪዎችም በህጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ያልቀረቡ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመውም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/1/ ስር የተመለከተው ነው? ወይስ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሶስት ስር የተመለከተው ነው? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ክስ ሊመሰረቱ የቻሉት አመልካች በ1999 ዓ/ም በወጣው የድርጅቱ የሕብረት ስምምነት መሰረት በ2001 ዓ/ም የበጀት አመት ከሐምሌ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ሊከፈል የሚገባቸውን የደመወዝ ጭማሪ በጳጉሜ 2002 ዓ/ም ለሰራተኞች ያደረገውን ቦነስ አልከፈለንም በሚል ምክንያት ሲሆን አመልካች የተለያዩ የመቃወሚያ የክርክር ነጥቦችን ከማቅረቡም በተጨማሪ የደመወዝ ጭማሪ የሚከፍልበትን ስርዓትና የህብረት ስምምነቱን የተፈፃሚነት ጊዜ ጠቅሶ ኃላፊነት የለብኝም ሲል ተከራክራል፡፡ ቦርዱም ሆነ ይግባኙን የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች ክርክር ውድቅ ያደረጉት የሕብረት ስምምነቱ በሌላ እስከሚተካ ድረስ ተፈፃሚ እንዲሆን የድርጅቱና የማህበሩ ተወካዮች ሚያዚያ 30 ቀን 2001 ዓ/ም ተስማምተው የፈረሙበትና በማህተም ያረጋገጡት ማስረጃ እንዲሁም ስምምነቱ ለሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለምዝገባ ቀርቦ ጸድቆ የተመዘገበ ስለመሆኑ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ግንቦት 02 ቀን 2001 ለሁለቱም ወገኖች በአድራሻ የፃፈላቸው ደብዳቤ ፎቶ ያስረዳል በሚል ምክንያት መሆኑንና ህብረት ስምምነቱ ተፈፃሚ እንዲሆን ግራ ቀኙ ከተሰማሙ ደግሞ ሕጋዊ አይደለም በማለት የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ እኛም ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

አመልካች የተጠሪዎች የደመወዝ ጭማሪና የቦነስ ክፍያ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የሚከራከረው የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162/3/ ስር የተጠቀሰውን ስድስት ወር ጊዜ በመጥቀስ ነው፡፡ ቦርዱም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በአዋጁ አንቀጽ 162/1/ ስር የተጠቀሰው የአንድ አመት ጊዜ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከት የተጠሪዎች ክስ ለቦርዱ የቀረበው ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ/ም ሁኖ የዳኝነት ጥያቄው መሰረት የሆነው ደግሞ የደመወዝ ጭማሪ ነው፡፡ ይህ የደመወዝ ጭማሪ የሚደረገውም አመልካች ደርጅት በ2001 ዓ/ም የበጀት አመት የአገለግሎት ጥራት እድገትና አመታዊ ትርፍ ግብ ሲመታ ስለመሆኑ አመልካች ራሱ ጠቅሶ

የሚከራከርበት የድርጅቱ የሕብረት ስምምነት በግልጽ የሚያሳየው ጉዳዩ ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ የህብረት ስምምነት ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የደመወዝ ጭማሪ የድርጅቱን የበጀት አመት የጥራት እድገትና የትርፍ ግብ መምታትን መሰረት ያደረገ መሆኑን ሲሆን የድርጅት የበጀት አመት በግልጽ አንድ አመት መሆኑ ከመጠቀሱም በላይ የድርጅቱ የጥራት እድገትና ትርፍ መኖሩ የሚረጋገጠው ደግሞ ከበጀት አመቱ መጠናቀቅ በኋላ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ስለሆነም የድርጅቱ የጥራት እድገትና ትርፍ ግብ መምታቱ የሚረጋገጠውና የደመወዝ ጭማሪውም በዚሁ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ከሆነ ተጠሪዎች ጥያቄውን ማቅረብ የሚችሉት የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ እና የደመወዝ ጭማሪውን ለማስገኘት የሚያስችለው ሁኔታ መሟላቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑ እሙን ነው፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠረው የይርጋ ጊዜ ርዝማኔ ነው፡፡ ይኼውም ጊዜው ስድስት ወር ነው ወይስ አንድ አመት ነው የሚለው የህግ ጥያቄ በአግባቡ ሊለይ ይገባል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በግራ ቀኙ የቀረበው ሙግት የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ሕግም የአዋጅ ቁጥር 377/96 ነው፡፡ ይህ የአዋጅ ቁ.377/96 በክፍል አስር ምእራፍ አንድ አንቀጽ 162-166 በሚገኙት ድንጋጌዎች ስር ስለ ይርጋ ደንብ ደንግጓል፡፡ የአዋጅ ቁ.377/96 የመብት ጥያቄዎች ለሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ በአንቀጽ 162 ስር ደንግጓል፡፡ ከመነሻው የተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ እስካልተወሰነ በስተቀር ጉዳዩን ማቅረብ ከሚቻልበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ካልቀረበ የመብቱ ጥያቄ በይርጋ እንደሚታገድ አመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ የጉዳዩ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ጉዳዩን ለማቅረብ ከሚቻልበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡ እንዲሁም በሕግ የተለየ የጊዜ ገደብ ያልተደረሰት ጉዳይ ሁሉ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ እንደሚገባው በመደንገግ አጠቃላይ የሆነ የጊዜ ገደብ አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ይኸው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162 በንዑስ አንቀጽ /2/ ፣/3/ እና /4/ ላይ ሕጉ የተለየ የይርጋ ጊዜ የወሰነላቸው የአቤቱታ አይነቶች ለይቶ አመላክቷል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 162 የተለየ ይርጋ ጊዜ ከወሰነላቸው የመብት ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያ የሆነው አንቀጽ 162/2/ "ሰራተኛው የስራ ውሉ ከሕግ ውጭ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ሥራው ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ ውሉ በተቋረጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል" በማለት ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩልም የስራ ውልን መቋረጥ ምክንያት አድርጎ ሰራተኛው በአሰሪው ላይ አሊያም አሰሪው በሰራተኛው ላይ የሚያነሳው የክፍያ ጥያቄ የስራ ውሉ ተቋረጠ በስድስት ወር ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በዚሁ አንቀጽ 162/4/ ላይ ተደንግጓል፡፡ በግልፅ እንደሚታየው የመጀመሪያው ድንጋጌ የስራ ውሉን መቋረጥ ሕጋዊነት በመቃወም ወደ ስራዬ ልመለስ ይገባል የሚል ሰራተኛ ይህን ጥያቄውን ለማቅረብ የሶስት ወር ጊዜ ብቻ እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ ሁለተኛው ድንጋጌ ደግሞ የስራ ውልን መቋረጥ መነሻ አድርገው የሚቀርቡ ማናቸውም አይነት የክፍያ ጥያቄዎች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተገደቡ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ከእነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች አቤቱታ አቅራቢው ስራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በመብቱ መጠቀም የሚችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው የአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 162 የተለየ የይርጋ ጊዜ የወሰነለት የአቤቱታ በንዑስ አንቀጽ /3/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይኸውም "ሰራተኛው የሚያቀርበው ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ መጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ...." መቅረብ እንደሚገባውና ይሄ ካልሆነ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡ ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ይህን አንቀጽ ተመስርቶ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል የተፈፀመው



www.chilot.me

የስራ ውል ፀንቶ በአለበት ሁኔታ ሰራተኛው ከአሰሪው የሚጠይቀው ክፍያ የሚመለከት እንጂ የግድ የስራ ውሉን መቋረጥ ተከትሎ የሚነሳ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የስድስት ወሩ የይርጋ ጊዜ አንደመብቱ መብሰል እየታየ ሊወሰን የሚገባው ወይም መብቱን መጠየቅ/ሊጠይቅ/ ይገባ ነበር የሚሰኝበት እለት ተመስርቶ መቆጠር የሚጀምር እንጂ ውስን መነሻ ጊዜ የተቀመጠለት አይደለም፡፡ ይኸ አንቀጽ 162/3/ ሰራተኛው አሰሪውን ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና ሌሎችም ክፍያዎችን ሊጠይቅ የሚችልበትን ውስን ጊዜ ያስቀመጠ ቢሆንም የስራ ውልን መቋረጥ ለይርጋው ጊዜ አቆጣጠር እንደመነሻ ባለመወሰዱ ከአንቀጽ /2/ እና /4/ ይለያል፡፡ እንዲሁም የድንጋጌው ይዘት ሲታይ ክፍያዎቹ ስራ በመስራት የሚገኙ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ሌሎች ክፍያዎች የሚለው የድንጋጌው ሐረግ የሚያሣየው ሰራተኛው ስራውን በመስራት ሊያገኝ የሚችላቸውን ክፍያዎች ስለመሆኑ የድንጋጌው አቀራረጽ ያሣያል፡፡ ከድንጋጌው ውስጥ "...የሌሎችም ክፍያዎች.." ወይም ".. 0thher payments ~ የሚለው ሐረግ ጠቅላላ ቃል መሆኑ ግልጽ ሲሆን እንዲህ በሆነ ጊዜ ቃሉን ሕግ አውጪው የተጠቀመው ምንን ለማመላከት ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሣቱ ተገቢ ሲሆን የሕግ አተረጓጎም መርሆዎችን መሠረት በማድረግም ምላሹን ማግኘት ይቻላል፡፡ በዚህም መሠረት ከጠቅላላው ቃል በፊት የተዘረዘሩት የቃላት ዝርያ የሚያሣዩትን ሁኔታ በመመልከት ጠቅላላ ቃል ሌሎች ያልተዘረዘሩትን ተመሣሣይ ዝርያ ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ታስቦ የተቀመጠ ነው በሚል እንደሚተረጎም ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም መርሆዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም ደመወዝ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች በመርህ ደረጃ ስራ ሲሰራ የሚከፍሉ የክፍያ ዓይነቶች ሲሆኑ በድንጋጌው የገባው የሌሎች ክፍያዎች ሐረግም ይዘቱና መንፈሱ ሲታይ በዚህ መልክ ለሰራተኛው የሚገቡትን የክፍያ አይነቶችን የሚገልጽ ነው፡፡ ይርጋውም ሠራተኛው የተጠቀሱትን ክፍያዎች ይጠይቅ ይገባው ነበር ከሚሰኝበት ጊዜ ይነሣና ምናልባትም የሥራ ውሉ ተቋርጦ እንኳ ቢሆን ይኸን ከግምት ውስጥ ያስገባና እስከ ስድስት ወር ድረስ መቆጠሩ ይቀጥላል፡፡ እንግዲህ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162 መሠረት አንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ የተለየ የይርጋ ጊዜ የተቀመጠላቸውን የመብት ጥያቄዎች የሚመለከት ከሆነ ከንዑስ አንቀጽ /2/ እስከ /4/ የተጠቀሱትን የሦስት ወይም ስድስት ወራት የጊዜ ገደብ አክብሮ የቀረበ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ሥር የማይሸፈን ከሆነ ደግሞ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተውና በአንፃሩም ሰፊ በሆነው የአንድ ዓመት የጊዜ ወሰን ውስጥ አንዲቀርብ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የይርጋ ጊዜ የተወሰነበት የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162 ሠራተኛውና አሰሪው አንዱ ከሌላቸው የመብት ጥያቄዎችን የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ብቻ በመጥቀስ የተደነገገ መሆኑን ከአንቀጾቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁት ክፍያ ስራ በመስራት የአመልካችን ድርጅት እቅድና ግብ ሲያሳኩ የሚገኙት ክፍያ የሚመለከት እንጂ አመልካች ስራ ባይሰራ ቢቀርም በህብረት ስምምነቱ መሠረት ሊፈከላቸው የሚገባውን ጥቅማ ጥቅም የሚመለከት አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/3/ ስር በተመለከተው ድንጋጌ ሌሎች ክፍያዎች በማለት የተቀመጠው ሐረግ እንደተገለፀው ሰራ በመስራት ሰራተኛው የሚያገኛቸውን የክፍያ አይነቶች የሚሸፍን እንጂ በሕብረት ስምምነቱ ስራ ከመስራት ውጪ የሚገኙትና የተጠበቁትን ክፍያዎችን የሚሸፈን አይደለም፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 162/1/ ሥር የተመለከተው የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ሣይሆን በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ ስር የተቀመጠው የስድት ወር ጊዜ በመሆኑና ይህ የስድስት ወር ጊዜ ገደብም የአመልካች የበጀት ዓመት

የተጠናቀቀበት ወይም ድርጅቱ የአገልግሎት ጥራት እድገትና ምርታማነቱን ግቡን ማሣካቱን ከአረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊቆጥር የሚገባው በመሆኑ ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአንድ አመት ይርጋ ነው በማለት ከመከራከራቸውም ውጪ ስድስት ወር ያላለፈው መሆኑን ገልጸው ያልተከራከሩ በመሆኑ ወይም የአመልካች የበጀት አመት ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተጠናቅቆ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡት ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ስለሚያሳይ አመልካቾች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በስድስት ወር የይርጋ ጊዜ የታገደ ነው፡፡

ሲጠቃለልም ቦርዱም ሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከላይ በተዘረዘረው ምክንያት አግባብ መመልከት ሲገባቸው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአንድ አመት ይርጋ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ በተጠሪዎች የተጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ ስራ ከመስራትና የድርጅቱን እቅድና ግብ ከማሳካት ጋር የተያያዘ የክፍያ አይነት መሆኑን ሳያገናዝቡ የተሰጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የፈጸሙ ሁኖ ስላአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ውሣኔ**</u>

1. በድሬዳዋ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ጥቅምት 07 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 07453 ሚያዝያ 04 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡትና እንዲከፈላቸው የተወሰነው የደመወዝ ጭማሪ ክፍያ ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 162 (3) መሰረት በስድስት ወር የጊዜ ገደብ የታገደ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ክፍያውን ሊከፍል አይገደድም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 81814

ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡- እነ ወ/ት ፌቨን የሺጌታ (12 ሰዎች) የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጠበቃ ሽዋዬ ታከለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የስራ ውላችንን በማቋረጥ ከስራ ያሰናበተን አላግባብ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተቋረጠ ማናቸውም ክፍያ ተከፍሎ ወደ ስራችን እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው በነበረው ክስ ሳቢያ ፍ/ቤቱ ክርክሩን ከሰማ በኃላ ከሳሾቹ ከተከሳሹ ጋር የነበራቸው ግንኙነት የሰልጣኝ እና የአሰልጣኝ ከመሆኑ ውጪ አግባብነት ባላቸው የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች መሰረት የተቋቋመ የስራ ውል የነበራቸው መሆኑን ስላላስረዱ ተከሳሹ የስራ ውላችንን አላግባብ አቋርጦብናል በሚል ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም በማለት የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በትዕዛዝ የጸናው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ከሳሾቹ በ07/11/2003 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ ተከሳሽ በተለያየ ቀን እና ዓ.ም. ከከሳሾቹ ጋር በተናጠል ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር የሚቆይ የስልጠና እና የብድር ስምምነት እንደፈረመ፣ስልጠናው በአራት ክፍሎች የተከፈለ ሆኖ ከሳሾቹ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች "ሰልጣኝ"፣በቀሪዎቹ ሁለት ክፍሎች ደግሞ "ሰራተኛ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶአቸው እንደነበረ፣የመጨረሻዎቹን ሁለት ክፍሎች ስልጠና ሲወስዱ መካከለኛ የበረራ አስተናጋጅ ተብለው በወር ብር 1,242 ደመወዝ እየተከፈላቸው ይሰሩ እንደነበረ፣ከሳሾቹ መብትና ግዴታ የተጠበቀላቸው ሰራተኞች ስለመሆናቸው በ23/04/2002 ዓ.ም.በተዘጋጀው ማንዋል ላይ በግልጽ እንደተቀመጠ፣በዚህ ሁኔታ ተከሳሽ እና ከሳሾች የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ያላቸው ሆኖ እያለ ተከሳሽ የቀጣሪነት የበላይነቱን ተጠቅሞ ሕገወጥ ውል በማስፈረም

3ኛ፣ከ5ኛ እስከ 8ኛ፣10ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ከሳሾችን የሁለት ዓመት ከስድስት ወር  የስልጠና ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት እንዳሰናበታቸው፣ቀሪዎቹን 1ኛ፣2ኛ፣4ኛ እና 9ኛ ከሳሾችን ደግሞ የስልጠናው ጊዜ ከተጠናቀቀ ከስድስት ወር በኃላ እንዳሰናበታቸው የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ ያልተከፈሉ ክፍያዎችን ፈጽሞ ከሳሾችን ወደ ስራቸው እንዲመልስ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ28/11/2003 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ በመካከላቸው የነበረው ውል የስልጠናና የብድር ብቻ እንደሆነ፣ከሳሾቹ ሰራተኞች እንዳልሆኑ፣መካከለኛ የበረራ ሰራተኛ በሚል ስያሜ መጠራትና መስራትም በስምምነቱ መሰረት የስልጠናው አካል እንደሆነ፣ በወር ይከፈላቸው የነበረው ብር 1,242 ደመወዝ ሳይሆን የኪስ ገንዘብ እንደሆነ፣ደመወዝ ባለመሆኑም ግብር እንደማይከፈልበት እና የሰራተኛ ማህበር መዋጮ እንደማይቆረጥበት፣የስልጠናና የብድር ስምምነቱን ወደ ጎን በመተው ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን ሌሎች ሰነዶች በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ፍ/ቤቱም ክሱን ከሰማ እና የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ከሳሾቹ  ከተከሳሽ ጋር በሕጉ አግባብ የተቋቋመ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ውል ያላቸው መሆኑን አላስረዱም በማለት ክሱን በብይን ውድቅ ያደረገው ሰራተኛ ማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ከአሰሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ማለት እንደሆነ፣በግራ ቀኙ መካከል የቅጥር ግንኙነት  የሚኖረው የስልጠናው ጊዜ ተጠናቆና ተከሳሽ ሰልጣኞቹን ለመቅጠር የሚፈልግ ሆኖ የቅጥር ውል ሲደረግ ብቻ ስለመሆኑ በስልጠናና በብድር ውሉ በአንቀጽ 8 እና 9 ላይ እንደተመለከተ፣መካከለኛ የበረራ አስተናጋጅ የሚል ስያሜ የተሰጣቸውም ከሳሾቹ ከተከሳሽ ጋር ባደረጉት ተጨማሪ ስምምነት እንደሆነ፣ክፍያውም ደመወዝ ሳይሆን የኪስ ገንዘብ ስለመሆኑ በስምምነቱ በአንቀጽ 3 እና 4 እንደተመለከተ፣ የሁለት ዓመት ከስድስት ወር የስልጠና ጊዜ ከማብቃቱ በፊትም ሆነ ካበቃ በኃላ የተሰናበቱት ከሳሾች ከተከሳሽ ጋር ከስልጠናና ብድር ስምምነት ውጪ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ውል የነበራቸው ስለመሆኑ እንዳላስረዱ፣ከሳሾቹ በተዋዋዮቹ መካከል ሕግ የሆነውን የስልጠናና የብድር ስምምነት ይዘት ወደጎን በመተው ለክርክሩ አግባብነት የሌላቸውን የተከሳሽ ድርጅት ሰነዶች በማጣቀስ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው በዝርዝር በመግለጽ ሲሆን ከሳሾቹ በብይኑ ቅር በመሰኘት ያቀረቡለትን ይግባኝ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ዘግቶ አሰናብቶአል፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካቾቹ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተጠቀሰው የሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታ የቀረበበትን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ አጠቃላይ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የስር ከሳሾች ከስር ተከሳሽ ጋር በሕጉ አግባብ ያቋቋሙት የስራ ውል መኖሩን አላስረዱም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚል ነጥብ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾች በተናጠል ከተጠሪ ጋር ያቋቋሙት ውል እና ተጨማሪ ውል ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር የሚቆይ የስልጠና እና የብድር ስምምነት መሆኑ፣በስምምነቱ መሰረት አመልካቾች በአራት ክፍሎች የተከፈለውን የስልጠና መርሐ ግብር በስኬት ካጠናቀቁ በኃላ አመልካቾችን ሰራተኛ አድርጎ በመቅጠር ረገድ የመወሰን መብት የተሰጠው ለተጠሪ መሆኑ፣ተጠሪ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከአመልካቾች መካከል



www.chilot.me

ከፊሎቹን ያሰናበተው የስልጠና መርሐ ግብሩን ከማጠናቀቃቸው በፊት መሆኑ፣ከፊሎቹ ደግሞ የስልጠና መርሐ ግብሩን በስኬት ያጠናቀቁ ቢሆንም ተጠሪው በስምምነቱ በተሰጠው መብት መሰረት ሰራተኛ አድርጎ ለመቅጠር ያልወሰነ መሆኑ በክርክሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ የስር ፍ/ቤቶችም አግባብነት ባላቸው የአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች መሰረት አመልካቾች ከተጠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ውል ያቋቋሙ መሆኑን አላስረዱም በማለት ክሱን ውድቅ ያደረጉትም ከላይ የተጠቀሱ በክርክሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን መሰረት በማድረግ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ሠራተኛ ማለት በአዋጁ በአንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ከአሠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 2(3) የተመለከተ ሲሆን የስራ ውል የሚመሰረተውም ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት ሲስማማ መሆኑ በአዋጁ በአንቀጽ 4(1) ተደንግጓል፡፡አመልካቾች ከተጠሪ ጋር በተናጠል ያቋቋሟቸው ውሎች እና ተጨማሪ ውሎች ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የስልጠና እና የብድር ውል እንጂ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ውል አይደለም፡፡ህግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት እንዳላቸው በፍ.ሕ.ቁ. 1711 የተመለከተ በመሆኑ እና በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ደግሞ ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ መሆናቸው በፍ.ሕ.ቁ.1731(1) የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪው የቀጣሪነት የበላይነቱን በመጠቀም ሕገ ወጥ ውል አስፈርሞናል በማለት አመልካቾች ያቀረቡት የክርክር ነጥብ ሕጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡አመልካቾቹ ውሉ ሕገ ወጥ ነው የሚሉበት ምክንያት ቢኖር እንኳ ይህን የውሉን ሁኔታ መሰረት አድርገው ክስ እና ክርክር ማቅረብ ይችሉ የነበረው ውሉ ፍጻሜ ከማግኘቱ በፊት እንጂ ውሉ ፍጻሜ አግኝቶ ተጠሪ የማይቀጥራቸው መሆኑን ካረጋገጡ በኃላ አይደለም፡፡በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካቾቹ ከተጠሪ ጋር በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የስራ ውል ያላቸው መሆኑን አላስረዱም ሲሉ ክሱን ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 73969 በ02/08/2004 ዓ.ም. የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 119009 በ24/09/2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ 86284

መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች ፡- ሆራይዘን አዲስ ጎማ (አ.ማ) ጠበቃ ሒሩት መለሰ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ መኮንን ዓለሙ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ሥንብት ህጋዊነት የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በተለያዩ የሥራ መደቦች ሲያሰራኝ ቆይቶ ከሕግ ውጭ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሰኝ ወይም በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ /ተጠሪ/ በድርጅቱ ላይ ጉዳት አድርሷል፤ጆንያ ተቆጣጥሮና ተከትሎ እንዲያስረክብ ትእዛዝ ተሰጥቶት ለሌሎች የቀን ሠራተኞች ኃላፊነቱን በመተው 390 /ሶስት መቶ ዘጠና/ ጆንያ ነው ተብሎ የተጫነው፣ መውጫ በር ላይ ሲቆጠር 580 /አምስት መቶ ሰማኒያ/ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ተከሣሽ 190 /አንድ መቶ ዘጠና ጆንያ/ ከድርጅቱ ሊያሰወስድ የነበረ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በወቅቱ 190 ጆንያ በትርፍ ተጭኖ በር ላይ በጥበቃ ሠራተኞች የተያዘ መሆኑን ሣይክድ ጥፋቱ የተፈፀመው አሠሪው /አመልካች/ ልምድና ክህሎት በሌለኝ የሥራ መደብ ላይ ስለመደበኝና በአንድ ጊዜ ተደራራቢ ሥራ እንድሰራ ትእዛዝ ስለሰጠኝ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪ በተመደበበት የሥራ መደብ በቂ የሆነ ልምድና ክህሎት ስለሌለውና አመልካች ተደራራቢ ሥራ እንዲሰራ ትእዛዝ ስለሰጠው 190 ጆንያ በትርፍነት ተጭኖ ሊወጣ ሲል በግቢው ጥበቃ ሠራተኞች ተይዟል፡፡ ይህንን ጥፋት የፈፀመው በልምድ ማነስና በሥራ ጉጉት ስለሆነ ጥፋቱ ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም፤ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው፤ አመልካች የስድስት ወር ደመወዙን ከፍሎ ተጠሪን ወደ ሥራው ይመልሰው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስንብቱ

ሕገ ወጥ ነው ካለ በኃላ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን በመክፈል ተጠሪን ያሰናበተው በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ ተጠሪ በኃላፊነት የተረከበውን ጆንያ በትእዛዙ መሠረት ቀንሶ እንዲጭን የማድረግና የድርጅቱ ትርፍ ጆንያ ያልተጫነ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ ይህንን ኃላፊነቱን በአግባቡ ስላለመወጣቱ 390 /ሶስት መቶ ዘጠና/ ጆንያ እንደተጫነ በመፈረም የሰጠው ማረጋገጫ እውነተኛ መሆኑና 580 /አምስት መቶ ሰማኒያ/ ጆንያ ተጭኖ የተገኘ መሆኑ ስለተረጋገጠ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ መሰናበቱ ሕጋዊ ሆኖ እያለ ሕገ ወጥ ነው መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ጥር 9 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 6 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በወቅቱ ስህተት የተከሰተው አመልካች በሁለትና ከዚያ በላይ ሰው መስራት ያለበትን ሥራ በእኔ በማሰራቱ ከፍተኛ የሥራ መደራረብ ስለነበረብኝ ነው፡፡ እኔ ንብረቱን ለግል ጥቅሜ አላዋልኩም፡፡ ስለዚህ ከሃያ አመት በላይ ስሰራ በመልካም ባህሪ የሠራሁ በመሆኑ ጥፋቱ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ በሕጋዊ መንገድ መጫን ከሚገባው ጆንያ ውጭ አንድ መቶ ዘጠና ጆንያ በትርፍነት ተጭኖ እንዲወጣ ሲያደርግ በጥበቃ ሠራተኞች የተያዘ ቢሆንም ጥፋቱ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ 390 /ሶስት መቶ ዘጠና ጆንያ/ ብቻ እንዲያስጭንና ወጭ እንዲያደርግ ትእዛዝ ተሰጥቶት የነበረ መሆኑንና ተጠሪ 390 ጆንያ ነው በማለት ያስጫነው ማረጋገጫ የሰጠበት ጭነት በጥበቃ ሠራተኞች ሲፈተሽና ሲቆጠር 580 ጆንያ ሆኖ መገኘቱ በዚህ ምክንያትም አመልካች 190 /አንድ መቶ ዘጠና ጆንያ/ ወጭ ሊደረግበት የነበረ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱም ተጠሪ 190 ጆንያ በትርፍ ተጭኖ መገኘቱን ሣይክድ የልምድ ማነስ ስለነበረብኝ የሥራ መብዛትና መደራረብ ስላለብኝ ነው ስህተቱ የተሠራው የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ ተደራራቢ የሥራ ትእዛዝ ከደረሱት ሥራዎችን በቅደም ተከተልና በአግባቡ የመፈፀምና በጊዜ አጥረትም ምክንያት ሣይሰራው የቀረውን ሥራ ኃላፊነት ሪፖርት ከሚያደርግ በስተቀር የድርጅቱ ንብረት በማስመዝበር ለሠራው ጥፋት የሥራ ብዛትና መደራረብ የይቅርታ ምክንያትና መከራከሪያ አድርጐ ለማቅረብ አይችልም፡፡ እንደዚሁም ሠራተኞች 390 ጆንያ ቆጥረው ለገዥው እንዲያስረክብ እና እንዳይጭኑ ማድረግና ይህንን ሥራ በኃላፊነት መቆጣጠር መከታተል፣ የተለየ የሥራ ልምድ ክህሎትና ችሎታ የሚጠይቅ ሥራ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ጥፋት የፈፀምኩት በሥራ ብዛት፣መደራረብና በልምድ ማነስ ነው በማለት ያቀረበው መከራከሪያ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት በአሠሪው ንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰን ሠራተኛ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ /1/ ሸ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ

በኃላፊነት የተረከበውን የአሠሪውን ንብረት /እቃ/ በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታውን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/3/ መሠረት ያልተወጣ መሆኑን የግራ ቀኙ ክርክርና ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የተጠሪ አድራጎት በአዋጅ አንቀጽ 27/1/ሽ የሚሸፈንና አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችለው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሽ መሠረት ከሥራ ያሠናበተው በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ የካሣ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 87338

ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ተሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ፋሲል አስራት ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1/ አቶ ገብሬ በላይነህ
2/ አቶ ግርማ ስንታየሁ
3/ አቶ አበጀ ካሴ
4/ አቶ መጣለም ገነት
5/ ወ/ሮ ገበያነሽ መኮንን

አልተጠሩም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የቀን ሰራተኛ ሆነው የተቀጠሩ ሰራተኞች የሳምንት እረፍት ቀናት የዓመት እረፍት ቀናት እና የህዝብ በዓላት ቀናት ክፍያ ሊያገኙ የሚችሉበት ሕጋዊ አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ የተጠሪዎች የክስ ይዘትም፡- በአመልካች ድርጅት በተለያየ ጊዜ በግንበኝነትና በአናጺነት ስራ ተቀጥረው በመስራት ላይ መሆናቸውንና ያገለገሉበትን ጊዜ ጠቅሰው በስራ ላይ በቆዩባቸው ጊዜያት ያልተጠቀሙበት የዓመት ፈቃድ የነበራቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የሳምንት እረፍት የህዝብ በዓላት የሰሩበት ታስቦ ያልተከፈላቸው መሆኑን፣ ካሌንደሩ የማይዘጋቸው ቀናትም ያላአግባብ ተዘግተው ስራ ሳይሰሩ የቀሩ መሆኑን ጠቅሰው ለእያንዳንዳቸው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ገልፆ የተከራከረው ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚገባው አይደለም፣ ይህ ከታለፈም ክሱ በይርጋ የታገደ ነው የሚሉትን ነጥቦችን በማንሳት ነው፡፡ በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪዎች በቀን የሚከፈላቸው ክፍያ በክሳቸው ላይ ያቀረቧቸው የክፍያ ጥያቄዎችን ክፍያ ከግምት ውስጥ አስገብቶና አጠቃልሎ የያዘ በመሆኑ የተለየ ክፍያ ሊኖር የሚችል ስለመሆኑ የሚሰራበት መሆኑንና በቅጥር ውሉ ላይ የተለየ እንደማይደረግ እና ክፍያ የሚፈፀምላቸው በካርዳቸው ላይ ስራ የተሰራባቸው ቀናት ተቆጥረው ስራ ለተሰራበት ቀን ብቻ እንደሚከፈል የተስማሙ ስለሆነ ጥያቄው አግባብነት የለውም በማለት

ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአመልካች በኩል የቀረቡትን መከራከሪያ ነጥቦችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ አመልካች ለተጠሪዎች የሳምንት እረፍት፣ የሕዝብ በዓላት እና የዓመት እረፍት ክፍያ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች በቀን በሰሩት ስራ መጠን ታስቦ ክፍያ የሚፈጸምላቸው በመሆኑ የጠየቁትን የክፍያ አይነቶች ሊያገኙ አይችሉም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ክርክሩ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ በመደበኛ ፍርድ ቤት መታየቱ ተገቢ መሆኑን፣ ተጠሪዎች በቀን በሰሩት ታስቦ በወር የደመወዝ ክፍያ የሚከፈላቸው መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን በምክንያትነት ይዞና የሕጉ ጥያቄ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስትም ሆነ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንፃር ሲታይ ለክሱ መሰረት የሆኑትን የሙብት ጥያቄዎች ተጠሪዎች ለመጠየቅ የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪዎች የሳምንት እረፍት ጊዜ፣ የሕዝብ በዓላትና በካሌንደሩ ላልተዘጉት ቀናት ክፍያ እንደሚገባቸው፣ የዓመት የረፍት ጊዜአት ግን የስራ ውሉ ባልተቋረጠበት ሁኔታ በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈልን በማለት ተጠሪዎች መጠየቅ የማይችሉ መሆናቸውን ዘርዝሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሠጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪዎች ጥያቄ ከራሳቸው አልፎ ሌሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተቀጥረው የሚሰሩትን በርካታ ሰራተኞችን ተመሳሳይ ጥያቄ እንዲያነሱ የሚያደርግ ሆኖ እያለ ክርክሩ የግል የስራ ክርክር መባሉ ያላግባብ ነው፣ ተጠሪዎች በስራ ላይ በቆዩባቸው ከሶስት አመታት የሚበልጥ ጊዜ ለሰሩባቸው ቀናት ብቻ እየታሰበ ሲከፈላቸው የነበረ መሆኑን፣ በቀን ታስቦ የሚከፈለው ገንዘብ የእሁድና የበዓላት ቀናትን የሚያጠቃልል መሆኑን ስራ ሲጀምሩ በተደረገው የስራ ውል ተስማምተው ክፍያው በዚሁ መልክ ሲፈፀም እና እየተሰራበት ያለ ሆኖ እያለ ለተጠሪዎች የተጠየቁት ክፍያዎች እንዲከፈሉ መወሰኑ ያለግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ የተጠቀሰው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ፡- በተጠሪዎች የተጠየቁት የበአላት፣ የሳምንት እረፍትና የዓመት እረፍት ክፍያዎች አመልካች በስራ ላይ ተጠሪዎች ላሳለፉት ቀናት ብቻ እንጂ እነዚህን ክፍያ ሊፈጸም አይገባም፣ ተጠሪዎች ከሶስት አመት በላይ በሰሩበት ጊዜም እነዚህን ጥቅማጥቅሞች ጠይቀው አያውቁም በማለት ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከዚህ ጭብጥ አንፃር ብቻ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት በኮንስትራክሽን ስራ የተሰማራና ተጠሪዎችን ቀጥሮ ሲያሰራ የነበረው በግንበኝነትና በአናጺነት ስራ መሆኑን፣ አመልካች ለተጠሪዎች ለቀን ስራ የሚያስበው የደመወዝ መጠን የተለያየ ሆኖ አከፋፈሉ ግን በወር ተጠቃልሎ በፔሮል የሚከፈል መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ሲታይ በአጠቃላይ የቅጥር ውል አይነቶች ለተወሰነ ሥራ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊደረግ የሚችሉ ናቸው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ሕጉ የቅጥር ውል አይነቱ ቋሚም ይሁን ጊዜያዊ ለሰራተኛው በሕጉ የተፈቀዱ ጥቅሞችና ከለላዎች የቅጥሩ አይነት መሰረት ተደርጎ ልዩነት ማድረግ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ጊዚያዊ ሰራተኞችም ሆነ ቋሚ ሰራተኞች በሕጉ የተጠበቁላቸውን ጥቅማጥቅሞችንና ከለላዎችን እንደሚያገኙ የህጉ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከሁሉም በላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 42(2) ድንጋጌ ሲታይ ሰራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የስራ ሰዓት እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የስራ አካባቢ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ይኼው የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ መንግስት ድንጋጌ እነዚህን ጥቅሞችና ከለላዎችን የሚያገኙትን ሰራተኞች ብሎ በጥቅሉ ከማስቀመጥ ባለፈ የቅጥር አይነቱን ለይቶ አላሰፈረም፡፡ በመሆኑም ጊዜያዊ ሰራተኞችም ቢሆኑ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡትን ጥቅሞችና ከለላዎች ተጠቃሚ የማይሆኑበት አግባብ የለም፡፡

አመልካች ተጠሪዎችን የቀጠረው በኮንስትራክሽን ስራ መሆኑ ከተረጋገጠ የቅጥሩ አይነት ለተወሰነ ስራና ጊዜ የተቀጠሩ መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ከላይ እንደተጠቀሰው ተጠሪዎች በሕጉ የተጠበቁላቸውን ጥቅሞች ከለላዎች ተጠቃሚ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች የመብቶቹ ተጠቃሚ የማይሆኑበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ሕጋዊ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሌላው አመልካች ከጊዜ ጋር በማያያዝ የሚያሳየው ክርክር ሲታይ ተጠሪዎች በአመልካች ድርጅት ከሶስት አመታት በላይ ሲሰሩ የጥቅማ ጥቅሞችን ጥያቄ አንስተው ያለማወቃቸው የሚገልፅ ሲሆን እንዲህ መሆኑ ተጠሪዎች ጥያቄውን ከእነጭራሹ እንዳይጠይቁ የማድረግ ሕጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ምክንያቱም በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ጥቅማ ጥቅሞችን ከማግኘት የሚያግዳቸው ከሚሆን በስተቀር የአመልካችን እርምጃ ሙሉ በሙሉ ሕጋዊ ሊያደርግ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 162 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪዎች ለሶስት አመታት ያህል ጥያቄውን አላቀረቡም የሚለው ክርክር ተጠሪዎች ጥያቄውን ለማንሳት አይችሉም ለማለት የማያስችል ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች በይርጋ የማይታገዱትን ክፍያዎች ለይተው የወሰኑ በመሆኑ በዚህ ረገድም የሕግ ስህተት አለ ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

የዓመት እረፍትን በተመለከተም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለተጠሪዎች እንደሚገባቸው፣ ግን የዓመት እረፍቱን መጠቀም ሲገባቸው በስራ ላይ እያሉ በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው ጥያቄ ማቅረባቸው ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 77(5) ድንጋጌ አንፃር ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልፆ መወሰኑ ሕጋዊ እንጂ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ስራ ለመስራት ዝግጁ ሆነው አመልካች ለተጠሪዎች ስራ የመስጠት ግዴታውን ያለመወጣቱ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካቹ ለተጠሪዎች ለእነዚህ ቀናት ደመወዝ የመክፈል ሕጋዊ ኃላፊነት

የሚያስከትልበት ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 12(1(ሀ))፣ 12(2)፣ 53 እና 54 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔም የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪዎች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩና ደመወዝ በቀን ሂሳብ ታስቦ በወር የሚከፈላቸው ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ለማንኛውም ሰራተኛ የተጠበቁትን ጥቅማጥቅሞችንና ከለላዎች የማግኘት መብታቸውን የሚነፈጉበት ሕጋዊ መሰረት የሌለ በመሆኑ በይርጋ ያልታገዱትን ጥቅማ ጥቅሞችን ብቻ በመለየት ተጠሪዎች እንዲያገኙ ተብሎ በተሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 24912 ጥር 06 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ተጠሪዎች በቀን ሂሳብ ታስቦ በወር ደመወዝ የሚከፈላቸው ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩ ሰራተኞች ቢሆንም የሳምንት እረፍት፣ የሕዝብ በዓላት እረፍት ደመወዝ ክፍያ የማግኘት፣ የዓመት እረፍት የማግኘትና ያለካሌንደር የተዘጉ ቀናት ክፍያ ደመወዝ የማግኘት መብት አላቸው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 87285

መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አመልካች፡- ወ/ሮ የውብዳር ንጋቱ

ተጠሪ፡- ገነት ሆቴል ኃ/ፈ.ጅ ፀጋዬ ጌታነህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የቀረበውን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች የክስ ይዘትም በተከሳሽ ድርጅት ከ1975 ዓ/ም እስከ ጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ ተቀጥረው እየሰሩ መቆየታቸው፣በደረሰባቸው የእግር በሽታ ምክንያት ከጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ጥር 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሕክምና ተከታትለው እያለና ስለሁኔታው ለስራ ባልደረቦቻቸው አቶ በላይ ተገኝ ነግረው እሳቸውም ለአቶ ታደሰ ሶልቤ ለተባሉት ኃላፊ ነግረው እያለ ድርጅቱ ይህንኑ ወደ ጎን በመተው የአመልካችን የስራ ውል ያቋረጠ መሆኑን ዘርዝረው የተጠሪ እርምጃ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ወይም ሕጋዊ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካች በተደጋጋሚ የስራ ሰዓት ባለማክበራቸው በማስጠንቀቂያ ታልፈው በመጨረሻም ከጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከስራ ስለቀሩ የተሰናበቱ መሆኑን፣ስለመታመማቸው ተጠሪ የማያውቅ መሆኑን በመግለጽ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፣ከተጠየቁት የክፍያ አይነቶች መካከልም ያልተከፈላቸው ደመወዝ፣የአመት ፍቃድ ክፍያና የሰርቪስ ቻርጅ ተገቢነት ያላቸው መሆኑና ሌሎች የክፍያ አይነቶች ግን የማይገባቸው መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ስለመታመማቸው ለተጠሪ ያላማሳወቃቸው መረጋገጡን፣አሳውቀዋል ቢባል እንኳን ሕመማቸው ተጠሪ ዘንድ ቀርበው በማግስቱ ለአሰሪያቸው ማሳወቅ/ፍቃድ ማግኘት የማይከለክላቸው ስለነበረና ይህንንም በአግባቡ ስላላሳወቁ አመልካች ከጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ለአምስት ተከታታይ ቀናትና ከዚያ በላይ የቀሩት ያለበቂ ምክንያት ነው የሚል ምክንያት በመያዝና የአዋጅ ቀጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ለ)) ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ የስራ ስንብት እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት

ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በሕመም ምክንያት የቀሩ መሆኑን የሚያሳይ የህክምና ማስረጃ ከመቅረቡም በላይ ስለሁኔታው ለተጠሪ አሳውቀው እያለ ይኼው ታልፎ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም አመልካች በሕመም ምክንያት ህክምና ላይ የቆዩና ይህንንም በስራ ባልደረባቸው በኩል ለተጠሪ አሳውቀው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስለሁኔታው በአካል ቀርበው ለተጠሪ ለማሳወቅ ህመሙ ክልከላ የማያደርግ ነው ተብሎ ከአምስት ተከታታይና ከዚያ በላይ የስራ ቀናት ከስራ ስለቀሩ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ጥር 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ በህመም ላይ ሁነው ህክምና ሲከታተሉ የነበሩ መሆኑን በሐኪም ማስረጃ የተረጋጠ ፍሬ ነገር ሲሆን አከራካሪው ፍሬ ነገር ስለህመሙ ለተጠሪ ማሳወቅ ያለማሳወቃቸው ሁኖ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ከአሰፈራቸው በርካታ ምክንያቶች ውስጥ ለውሳኔው አብይ ምክንያት ያደረገው የህመሙ አይነት አመልካችን በአካል ቀርበው ለተጠሪ ስለህመሙ ከማሳወቅና ፈቃድ በሕጉ አግባብ ከመጠየቅ አይከለክላቸውም የሚል መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ በሕመም ምክንያት ከስራ ከቀረ ስለሁኔታው ለአሰሪው ማሳወቅና ፈቃድም ማግኘት ያለበት መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 85(4) ድንጋጌ ስር ከተመለከተው ድንጋጌ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ድንጋጌው የህመም ፈቃድ ማግኘት በሕጉ የተጠበቀ መብት መሆኑና መብቱን ለማግኘት በቅድሚያ መሟላት ስለአለባቸው ሁኔታዎች በግልጽ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ስለሁኔታው ለአሰሪው ያለማሳወቅ የሚያስከትለውን ውጤት ግን በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ይሁን እንጂ ሕመም ከስራ ለመቅረት እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የሚገባው መሆኑን ሕግ አውጪው ታሳቢ አድርጎ የሕመም ፈቃድ ማግኘትን መብት የደነገገ መሆኑ ግንዛቤ ከተወሰደ በሕጉ አግባብ የሕመም ፈቃድ ያልወሰደ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሰራተኛ ከስራ የቀረው በበቂ ምክንያት ነው ተብሎ የሚገመትበት አግባብ ስለማይኖር ያለበቂ ምክንያት ከስራ ስለመቅረትና ውጤቱን የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ ለጉዳዩ ተፈፃሚ የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡አዋጁ በአሰሪና በሰራተኛ መካከል ያለውን ግንኙነት በተለይ ለመግዛት ተብሎ ታስቦ የወጣ በመሆኑ በአዋጁ ውስጥ ያሉትን ድንጋጌዎችን አስተሳስሮ ተገቢውንና የአዋጁን ዓላማና መንፈስ የሚያሳካ ትርጉም ለአንድ ድንጋጌ መስጠት በሕግ አተረጓጎም ደንቦችም የተፈቀደ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ስለመታመማቸው የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ከሚመለከተው የህክምና ተቋም የወሰዱ መሆኑና ይህንኑም በስራ ባልደረባቸው በኩል ለተጠሪ ማሳወቃቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተቀባይነት ከአገኘ አመልካችን ያመማቸው ሕመም በአካል ቀርበው ለተጠሪ ለማሳወቅ ወይም ፍቃድ ለማግኘት

የሚከለክላቸው አይደለም ተብሎ ከስራ ስለመቅረታቸው ያቀረቡት ምክንያት በቂ አይደለም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡አንድ አሰሪ የህመም ፈቃድ ለሰራተኛው መስጠት እንዲችል ስለሁኔታው እንዲያውቅ የሚደረገው መሰረታዊ አላማም ሰራተኛው ከስራ በመቅረቱ ምክንያት የሚፈጠረውን ክፍተት በተገቢው መንገድ እንዲሞላ ለማድረግ ምርትና ምርታማነቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳይፈጠርበት ነው ተብሎ የሚታመን መሆኑን አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 85 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ በመግቢያው ከተመለከተው የአዋጁ መሰረታዊ አላማ ጋር አንድ ላይ በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ተጠሪ አመልካቿ በሕመም ላይ የነበሩ መሆኑን ከአወቀ በስራው ላይ ክፍተት እንዳይፈጠር ተገቢውን ለማድረግ በሚያስችለው ሁኔታ ውስጥ የነበረ መሆኑን ተገንዘበናል፡፡ይህ ሁኖ እያለ አመልካችን ያለበቂ ምክንያት ከስራ ቀርተዋል በማለት የስራ ስንብት እርምጃ መውሰዱ የሕጉን መንፈስና ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ሕገ ወጥ ነው፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንጻር መመልከት ሲገባቸው አመልካች በአካል ቀርበው ለተጠሪ ማሳወቅ ነበረባቸው በሚል ምክንያት ላይ ትኩረት በማድረግ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ቀጥሎ የተመለከትነው ውጤቱን ነው፡፡አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ከስራው የተሰናበተው ህገ ወጥ በሆነ እርምጃ መሆኑ ከተረጋገጠ ውጤቱ ሰራተኛው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ ማድረግ ወይም በዚህ ምትክ ሕጋዊ ክፍያዎች ተከፍለውት እንዲሰናበት ማድረግ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡እነዚህ በሕጉ የተመለከቱት ውጤቶች የሚወሰኑበት ምክንያትም የአዋጁን መሰረታዊ ዓላማ ያገናዘበ መሆን ያለበት ስለመሆኑ ከድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ የእርምጃው ውጤት የሰራተኛውን የስራ ዋስትና እና የኢንዲስትሪውን ሰላም ለመጠበቅ በሚያስችል መንገድ ሊወሰን እንደሚገባው የድንጋጌዎቹ መንፈስና ይዘት ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካችን ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራ እንዲመለሱ ማድረግ ተገቢነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ምክንያቱም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ምክንያት ከመከሰቱ በፊትም አመልካች ከስራ በተደጋጋሚ ይቀራሉ በሚል ተጠሪ በማስጠንቀቂያ ያለፋቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ አመልካች ከተጠሪ 1ኛ ምስክር ከነበሩትና የቅርብ አለቃቸው ከሆኑት ሰው ጋርም በጥሩ ግንኙነት ውስጥ ያለመሆናቸውን፣ይልቁንም በመካከላቸው በተፈጠረው ፀብ የወንጀል ክስ አቤቱታ አቅርበው በሚመለከተው አካል ዘንድ በመታየት ላይ እንደሚገኝ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር የገለፁ በመሆኑ አመልካች ወደ ስራው ቢመለሱ ከተጠሪ ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት ይኖራቸዋል፣በስራ ቦታው ላይ የኢንዲስትሪ ሰላም ይሰፍናል ብሎ ለመገመት የሚያስቸግር መሆኑን የሚያሳዩ ምክንያቶች መሆኑን ክርክሩ የሚያሳይ ነውና፡፡ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(3) መሰረት አመልካች ወደ ስራ ከሚመለሱ ይልቅ በምትኩ ሕጋዊ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ማድረግ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ሲሆን ውጤቱን በተመለከተ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 43(3) መሰረት መወሰን ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ስንብቱን አስመልክቶ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04639 ነሐሴ 22 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12679 ጥር 28 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረተ ተሻሽሏል፡፡
2. የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ወደ ስራ ከሚመለሱ ይልቅ በምትኩ ሕጋዊ ክፍያዎች፤በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ፣የሚገባው በአንቀጽ 42/4/ ካሳ፤በአንቀጽ 35/1/ሀ/ መሰረት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተከፍሏቸው ይሰናበቱ ብለናል፡፡በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰኑት የጥር ወር 2004 ዓ/ም የ21 ቀን ደመወዝ፣የታህሳስ ወር እና የጥር ወር 21 ቀናት 2004 ዓ/ም የሰርቪስ ቻርጅ ክፍያና የ43 ቀናት የአመት ፍቃድ በገንዘብ ተለውጦ የሚከፈለው ክፍያ እንደፀኑ ናቸው፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ



www.chilot.me

ሰ/መ/ቁ. 90389

ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤርፖርት ድርጅት ነ/ፈጅ እፀገነት ከድር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ በሪሁን በላይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ውል መቋረጥን የሚመለከት ነው በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሣሽ /ተጠሪ/ 23-10-2002 ዓ.ም ጀምሮ በጥበቃ የሥራ መደብ ተቀጥሬ ስሰራ ተከሣሽ /አመልካች/ 27-04-2004 ዓ.ም በተፃፈ የሥራ ስንብት ደብዳቤ ከ30-05-2004 ዓ.ም ጀምሮ ከሥራ ያሰናበታቸው በመሆኑ ወደ ምድብ ሥራዬ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ ወይም የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ፍርድ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ የተመደበበት የሥራ መደብ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሆኖ እያለ ተከሣሽ /ተጠሪ/ 10-02-2004 ተረኛ ሆኖ ተመድቦ ሲሰራ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ወደውስጥ ዘልቆ እንዲገባ በማድረግ ሰውየው አውሮፕላን የሚቆምበትና የተከለከለ ቦታ ላይ ቆሞ በፖሊሶች ተይዟል፡፡ እንዲሁም ከሣሽ በተመሣሣይ ሁኔታ 27-03-2004 ዓ.ም አራት ማንነታቸው ያልታወቁ ሰዎች ወደ ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ በማድረጉ እና በድርጅቱ ላይ የከፋ ችግር በመፍጠሩ ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ተሰጥቶት የሥራ ውል በሕጋዊ መንገድ የተቋረጠ በመሆኑ የከሣሽ ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተከሣሽ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠ መሆኑንና ተጠሪ በጥበቃ ሥራ ላይ እያለ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ወደ ድርጅቱ እንዲገቡ በማድረግ ጥፋት የፈፀሙ መሆኑን ገልጿል፡፡ ነገር ግን በተጠሪ ጥፋት ምክንያት በድርጅቱ ላይ የተፈጠረ

ችግር የሌለ በመሆኑ የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ከፍሎ ተጠሪን ከሥራ ያሰናብተው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሸኘት አመልካች ይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የሰጠ በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ክፍያ መክፈል የለበትም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች በ22-09-2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ማንነታቸው የማይታወቅና ያልተፈቀደላቸውን ሰዎች ወደ ድርጅቱ ውስጥ በማስገባት ድርጅቱን ለከፍተኛ የፀጥታ ሥጋት የዳረገ መሆኑና አመልካች የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ከሥራ ያሰናበተው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ 3-11-2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚለውን ነጥብ በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡ አመልካች 11-11-2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. ከሥር የክርክር አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በተሠማራበት የጥበቃ ሥራ ላይ እያለ ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ሣይፈተሽ ወደ አውሮፕላኖች ማረፊያ ድርጅቱ እንዲገባ ያደረገና ሠውየውም አውሮፕላኖች መቆሚያ ቦታ ላይ በፖሊሶች መያዙ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ይህንን ጥፋት የፈፀመ መሆኑን በማመን በጽሑፍ ይቅርታ የጠየቀ መሆኑና በጋራዥና ትራንስፖርት በር ላይ ተመድቦ እንዲሠራ አመልካች 16-02-2004 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ግራ ቀኙ በሥርና በሰበር ደረጃ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል፡፡
6. አመልካች ተጠሪን 10-2-2002 ዓ.ም በማስጠንቀቂያ ያለፈው ቢሆንም ተጠሪ ሕዳር 27 ቀን 2004 ዓ.ም በጥበቃ ሥራ ላይ እያለ የጥበቃ ቀጠናውን ክፍት ትቶ በመሄዱ አራት ሰዎች ወደ ውስጥ ገብተው ክሊኒኩ አከባቢ ሲደርሱ በፖሊስ የተያዙ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ 27/03/2004 ዓ.ም. ይህንን ጥፋት ከፈፀመ በኃላ የጥበቃ አስተባባሪው በትራንስፖርትና ጠቅላላ አገልግሎት ቡድን ሪፖርት ያቀረበ መሆኑና የትራንስፖርት አገልግሎት ቡድን ሁኔታውን ከመረመረ በኃላ የተጠሪ የሥራ ውል ታህሣስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሚያበቃ መሆኑን ገልፆ የተጠሪ የስራ ውል ለአንድ ወር ብቻ እንዲራዘምና ይህም የቅድመ ማስጠንቀቂያ መስጫ ጊዜ ሆኖ ተቆጥሮ የሥራ ውላቸው እንዲቋረጥ ታህሣስ 23 ቀን 2004 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡
7. ተጠሪ የሚሠራበት ድርጅት የጥበቃ ሥራ በከፍተኛ ጥንቃቄ መከናወን የሚገባውና ለድርጅቱም ሆነ ለተገልጋዮና ደንበኞች ደህንነት አጠባበቅ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ይህንን የሥራ ተግባሩን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈፀሙ የድርጅቱን ደህንነት ለከፍተኛ ችግር ያጋለጠና ማንነታቸው ያልታወቀና ያልተፈተሹ ሠዎች ወደ ድርጅቱ ዘልቀው ገብተው በፖሊስ የተያዙ ስለመሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የፈፀመው

ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1/ሸ/ የሚሸፈንና የተጠሪን የሥራ ውል ያለ ማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የጥበቃ ተግባሩን በአግባቡ ባለማከናወኑና ሰዎቹ ሣይፈተሹ ወደ ድርጅቱ ዘልቀው በመግባታቸው በአመልካች ላይ የደረሰበት የፀጥታና ደህንነት ችግር /ጉዳት/ የለም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲሉ በማለት የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 17/1/ሸ እና /ቀ/ እንዲሁም አንቀጽ 14/2/ሀ/ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት መንፈስ አላማ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

8. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል በአንድ ወር በማራዘምና ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የሥራ ውል ማቋረጡ አመልካች የተጠሪን መብት ለመጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ማድረጉን የሚያሣይ እንጂ ሕገ ወጥ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕግ አግባብ በመሆኑ አመልካች የካሣ ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወሰነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 92466

ጥር 2 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ አዳነ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች፡- ሳይግን ቴክስታይል ቢዩልዲንግ ኮንስትራክሽን ትሬድ ኢንዳትሪ ኢንክ ኢትዮጲያ ብራንች ነ/ፈጅ መቅደስ ሽፈራው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ጋር ተያይዞ የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ ከሣሽ በተከሣሽ ደርጅት ውስጥ ከ22/06/02 ዓ.ም ጀምሮ በመሐንዲስነት እና በፕሮጀክት ስራ አስኪያጅነት የስራ መደብ ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ ተከሣሹ ያለአግባብ የሥራ ውላቸውን ያቋረጠባቸው መሆኑን ጠቅሰው ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ መሠረት ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲፈፀምላቸው እንዲሁም የሥራ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በሚል ዳኝነት የጠየቁ መሆናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሥር ተከሣሽም ቀርበው ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ፡- ከሣሽ ተከሣሽን በመወከል ስራዎችን የሚያቅዱ ለሠራተኞች ስራ የሚሰጡ እና የሥራ ጥራታቸውን የሚቆጣጠሩ መሆኑን፣ ስራዎችን የሚያስተባብሩ እና የስራ አፈፃፀማቸው አጥጋቢ ባልሆኑ ሠራተኞች ላይ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን ጠቅሶ ከሳሽ የሥራ መሪ እንጂ ሠራተኛ ባለመሆናቸው የሥራ ክርክር ችሎቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ነገሩ ረገድም የበኩሉን መከራከሪያ በማቅረብ መልስ መስጠቱን የሥር ፍ/ቤቱ ውሣኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙ የጽሑፍ እና የቃል ክርክር ከሰማ እና ለከሣሽ የተሰጠው የሥራ መዘርዘር በትእዛዝ አስቀርቦ መመልከቱን ከገለጸ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የከሣሽን የሥራ ተግባር የፕሮጀክቱን ስራ በኃላፊነት መምራት፣ማደራጀት፣ መቆጣጠር እና ማስተባበር መሆኑን በማስረጃ መረጋገጡን ከገለፀ በኃላ የዚህ አይነቱን ተግባራት የሚፈጽም ግለሰብ ደግሞ በአዋጁ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3 እና በማሻሻያ አዋጁ ቁ.494/98 አንቀጽ 2/ሐ/ ድንጋጌዎች እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ

ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ.42901 በሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረት የሥራ መሪ እንጂ ሠራተኛ ሊባል ስለማይችል ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ መሠረት ስለማይስተናገድ የሥራ ክርክር ችሎቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/2/ /ሀ/ መሠረት በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡

በአሁኑ ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማ በኃላ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪ የተመደበበት የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የስራ መደብ ሥራ መዘርዘር ሁኔታ ከአዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/ሐ/ ድንጋጌ ይዘት አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ ተጠሪ የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈጸም ጭምር ኃላፊነት አልተሰጠውም፣ ከነዚህ በተጨማሪም ወይም እነዚሁኑ ሣይጨምር ሠራተኞችን የመቅጠር የማዛወር የማገድ የማሰናበት የመመደብ ወይም የስነ ስርዓት እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ሣይሰጠው የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የፕሮጀክቱን ስራ በኃላፊነት ይመራሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይቆጣጠራሉ በማለት ጉዳዩን ከሰበር መ.ቁ. 42901 ገዥ ውሣኔ ጋር በማያያዝ ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው የሚል ድምዳሜ ይዞ የሰጠው ብይን የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ብይኑን ሽሮ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገሩ ክርክር ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥ ክርክሩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት መልሶለታል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይሄንኑ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሥራ መሪ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ በተሰጠው ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታልና ስህተቱ በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ ይታረመልን የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የሥራ መሪ ነው በሚል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመሻሩ አግባብነት ለተጠሪ ከተሰጠው ስራ ኃላፊነት እና ተግባር አኳያ ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም የተደረገለትን ጥሪ መነሻ በማድረግ ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን የግራ ቀኙ የሰበር ጽሑፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተጠሪ የሥራ መሪ ነው? ወይስ ሠራተኛ? የሚለው ነጥብ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እልባት ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ የሥራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደየድርጅቱ የስራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊስዎችን የማውጣት የማስፈፀም ከነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚሁኑ ሣይጨምር ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣ የማስናበት የመመደብ ወይም የስነ-ስርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወሰን ግለሰብ ስለመሆኑ በአሠሪና ሠሪተኛ አዋጁ ቁ. 377/96 3/2/ /ሐ/ እና በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2(1) (ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘትም መገንዘብ የሚቻለው አንድ ተቀጣሪ ግለሰብ የስራ መሪ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን በቅድሚያ ተቀጣሪው ግለሰብ በቀጣሪው ተቋም እንዲያከናውን የተሰጠው ተግባራት እና የሥራ ኃላፊነቶች እያንዳንዳቸው ምን ምን እንደሆኑ በጥንቃቄ ተመልክቶ በቂ ግንዛቤ መያዝ የግድ መሆኑን ነው፡፡ ከዚያ በኃላ በግለሰቡ የሚከናወኑትን የስራ

ተግባራት ወይም የሥራ ኃላፊነትቶቹን ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሕጉ ድንጋጌ ይዘት አኳያ አንድ በአንድ በጥንቃቄ አገናዝቦ መመልከቱ እና በመመርመር ተገቢ ወደ ሆነው ድምዳሜ ላይ መድረስን ይጠይቃል፡፡

ከዚህ አኳያ ወደ ተያዘው ጉዳይ ተመልስን ስንመለከተው ተጠሪ በድርጅቱ የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅነት የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ የዚህን ስራ መደብ ተግባራትን ሲያከናውን የነበረ ስለመሆኑ እና በዚሁ መነሻነትም የድርጅቱ ማኔጅመንት አባልም በመሆኑ ጭምር አጠቃላይ የሆነውን የድርጅቱ ስራ አመራር ውስጥም በመሣተፍ የበኩሉን ድርሻሲያከናውን የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ ራሱ ባቀረበው ክስ አቤቱታ ማመልከቻ፣ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አቤቱታ ማመልከቻ እና በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ቃል ክርክር የታመነ ጉዳይ ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ግልባጭ ይዘት ያስረዳል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በፕሮጀክት ስራ አስኪያጅነቱ ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና የሥራ ተግባራት እና ኃላፊነቶች በተጨማሪ በድርጅቱ የማኔጅመንት አባልነቱም በድርጅቱ የሥራ አመራር ኃለፊነት ውስጥ ተሣትፎ የነበረው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅነቱ የስራ መደብ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ብዛት የመወሰን፣ በሥሩ ያሉትን ሠራተኞች የመምራት የመቆጣጠር የሥራ አፈፃፀማቸወን የመገምገም፣ ብቃታቸውን የማሣደግ፣ የፕሮጀክቱን ስራ አመራር የማቀድ፣ የመፈፀም፣ የማስተባበር እና የመሣሰሉትን ዋና ዋና የስራ ተግባራት እና ኃላፊነቶችን ሲያከናውን የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ ተመድቦ ይስራበት የነበረውን የሥራ መደብ ስራ መዘርዝር መረጋገጡን እንዲሁ ከሥር ፍ/ቤቱ ውሣኔ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ የአመልካች ድርጅት የሥራ መሪነት የሥራ ድርሻ ወይም ሚና ነበረው ከሚያሰኝ በቀር ሠራተኛ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘንም በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሥራ መሪ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ የሰጠው ፍርድ ተጠሪ በድርጅቱ ማኔጅመንት አባልነቱም ሆነ በፕሮጀክት ስራ አስኪያጅነቱ ሲያከናውናቸው የነበረው የሥራ ተግባራት ኃላፊነቶች እና የሥራ አመራር የሥራ ድርሻነቱን በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/2/ሐ/ እና የማሻሻያ አዋጁ ቁ.494/98 አንቀጽ 2/1/ሐ/ አኳያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡



www.chilot.me

## ውሣኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኮ/መ/ቁ. 135628 በ2/11/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሥራ ክርክር ችሎት በኮ/መ/ቁ. 81696 በ15/8/2005 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው እንጂ ሠራተኛ አይደሉም ብለናል ስለዚህ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የሚስተናገድ አይደለም፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ቤ/ዮ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# ውል



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 82670

መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** 1ኛ/ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር ፅ/ቤት - የቀረበ የለም

2ኛ/ አቶ ኑስባ መሀመድ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ዋጋዬ አሰፋ - ጠበቃ እሌኒ አስራት - ቀረቡ

**መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 83247 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በንግድ ቤት በኪራይ ውል የተገኘ መብት ሊቋረጥ አይገባም የሚል ጥያቄ መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኗ ተጠሪ ከአቶ ግርማ እሸቴ ጋር በመሆን በአሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 528/ለ/ የሆነ መኖሪያ ቤት ከቀበሌ በመከራየት እንደሚኖሩበት በቤቱ ግቢ ውስጥ ሱቅ ሰርተው መነገድ እንዲችሉ ፈቃድ ጠይቀውም የአሁኑ 1ኛ አመልካች ፈቅዶላቸው የኪራይ ውል ተዋውለው በስር 2ኛ ከሳሽ በነበሩት በአቶ ግርማ እሸቴ ስም የንግድ ፈቃድ በማውጣት ሲሰሩ የቆዩ መሆኑን፣ በዚሁ ቤት ቁጥር ተጠሪ ከአሁኑ አንደኛ አመልካች ጋር ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም ለአንድ አመት የሚቆይ የኪራይ ውል ተፈራርመው የአሁኑ 2ኛ አመልካችም የንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩበት የቆዩ መሆኑን፣ የቁርስ ቤት ስራ ልምድ ካለው ሰው ጋር በጋራ ለመስራት በማሰብ ከ2ኛ አመልካች ጋር መስከረም 01 ቀን 2000 ዓ/ም በተፈረመ ውል ትርፍ እኩል ለመስራት በመስማማት በቤቱ ውስጥ ባሉ የስር ሁለተኛ ከሳሽ እቃዎች እና ንብረቶች እንዲሰሩና ውሉም እስከ መስከረም 2006 ዓ/ም ድረስ እንደሚቆይ በመስማማት በመስራት ላይ እያለ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለአሁኑ 2ኛ አመልካች ቤቱን ተጠሪ እንዳከራዩ በማስመሰል በተጠሪ ስም የነበረውን የኪራይ ውል ሰርዞ በአሁኑ 2ኛ አመልካች ስም አዋውሎ ኪራይ እየተቀበለ እንደሚገኝ፣ ከሳሾች ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር የኪራይ ግንኙነት የሌለ መሆኑን በመዘርዘር 1ኛ አመልካች ውሉን እንዲቀጥል 2ኛ አመልካችም የያዘውን ቤት ከነሙሉ ንብረቱ ለከሳሾች እንዲያስረክቡና የገቡትን ውል ያፈረሱ በመሆኑ በውሉ መሰረት ብር 3000.00 ኪሳራ ለከሳሽ እንዲከፍሉ ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት

መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የስር 2ኛ ከሳሽ የሆኑት አቶ ግርማ እሸቴ ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ተጠሪ በውሉ የተከራዩትን የንግድ ቤት ለአከራይ ሳያሳውቁና ፈቃድ ሳያገኙ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው የተገኙ መሆኑ ተረጋግጦ በመመሪያው መሰረት ለአሁኑ 2ኛ አመልካች እንዲከራይ መደረጉ የሁከት ተግባር ያለመሆኑን በመካከላቸው ያለው የኪራይ ውልም ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ከመሆኑም በላይ በፍ/ብሔር ሕጉ መሰረት የንግድ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን ማከራየት ከመፍቀዳቸው በፊት ለአከራዩ ሊያሳውቁ ይገባ እንደነበር፣ ተጠሪ ከውሉ በተቃራኒ ንግድ ቤቱን ለአቶ አምደግባ መሐመድ ያከራዩ መሆኑ እና አቶ አምደግባ መሀመድ ደግሞ ለአሁኑ 2ኛ አመልካች ያከራዩ መሆኑ ተረጋግጦ ውሉ መቋረጡን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ 2ኛ አመልካች በሰጡት መከላከያ መልስም የንግድ ቤቱን በጋራ ለመስራት ስምምነት እንደተደረገ አድርገው ያቀረቡት ሰነድ ሐሰተኛ መሆኑንና ቤቱን አከራይተዋቸው የሚጠቀሙበት መሆኑን ዘርዝረው አንደኛ አመልካች በመመሪያው መሰረት ኪራዩ ከእርሳቸው ጋር እንዲሆን ማድረጉ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም 2ኛ ከሳሽ የነበሩትን አቶ ግርማ እሸቴን ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ ገልፆ በብይን ያሰናበታቸው ሲሆን በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል ያለውን ጉዳይ በተመለከተ ግን የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ቤቱን በኪራይ ከስር 2ኛ ከሳሽ ለነበሩት ግለሰብ ይሁን ለሌላ ለሶስተኛ ወገን በኪራይ ያስተላለፉ ስለመሆኑ የሚያስረዳ የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ያለመቅረቡን ሰኔ 06 ቀን 1996 ዓ/ም የተደረገው የኪራይ ውልም ወረዳው በተከራይነት የሚያውቋቸው እና ፍርድ ቤቱ የመሆን ጥቅም አላሳዩም ሲል ባሰናበታቸው በስር ሁለተኛ ከሳሽ በነበሩት አቶ ግርማ እሸቴ የተደረገ ውል እንጂ በተጠሪ የተደረገ ውል ያለመሆኑንና አቶ ግርማ እሸቴ ደግሞ የንግድ ቤቱን ለሌላ ሰው በኪራይ የማስተላለፍ መብት በውልም ሆነ በሕግ ያላገኙና የውሉ ጊዜም ታህሳስ 6 ቀን 1997 ዓ/ም የሚቆይ ሆኖ ውሉን ያደረጉት በራሳቸው እንጂ በውክልና ስለመሆኑ ያለመግለፁን በምክንያትነት ይዞ ተጠሪ ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር እንደአደረጉት ተቆጥሮ በ1997 ዓ/ም የውሉ ዘመን መጠናቀቁ በግልፅ ተቀምጦ እያለ በ2004 ዓ/ም በወጣው መመሪያ መሰረት ተጠሪ ለአሁኑ 2ኛ አመልካች ቤቱን ባላከራዩበት እንዲሁም ሁለተኛ አመልካች በጋራ ለመስራት ውል የተፈራረሙ መሆኑን አምነው ይዘቱን ሳላነብ ነው የፈረምኩት የሚሉትን ውል ስልጣን ባለው አካል እንዲፈርስ ባላደረጉበት ሁኔታ በመመሪያው መሰረት ከ1ኛ አመልካች ጋር ያደረጉት ውል ቤቱን ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈዋል ተብሎ ኪራዩ የሚቋረጥበት አግባብ የለም በማለት ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ጋር ያላቸው የኪራይ ውል እንዲቀጥል ሁለተኛ አመልካችም ቤቱን እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ለየብቻቸው ይግባኞቻቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች በተናጠል ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን ከአከራይ ፈቃድ ውጪ አከራይተው የቆዩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ መመሪያው ቁጥር 4/2004 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ምክንያት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ የንግድ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን አሳልፈው አልተገኙም በሚል ምክንያት በመመሪያው አይሸፈኑም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ንግድ ቤቱ የአንደኛ አመልካች ሆኖ ተጠሪ ተከራይተው ይገለገሉበት የነበረ መሆኑን፣ ተጠሪ የንግድ ቤቱን በስር ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ለመክሰስ የሚያስችል መብት የለህም ተብለው በብይን ከክርክሩ ውጪ ከሆኑት ግለሰብ ጋር የኪራይ ውል አላደረጉም፣ እኚህ ግለሰብ በ1996 ዓ/ም ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር ያደረጉትና እስከ ታህሳስ 06 ቀን 1997 ዓ/ም ድረስ ቆይቷል የተባለው የኪራይ ውል መብት በሌላቸው ጉዳይ የተደረገ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት ተቀባይነት ማጣቱን እና የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያላቸው ግንኙነት በንግድ ቤቱ አንድ ላይ በመስራት ትርፉን ለመጋራት ተስማምተዋል በሚል ምክንያት የስር ፍ/ቤት ሁለተኛ አመልካችን ተከራይ አይደሉም ወደሚለው ድምዳሜ መድረሱን፣ ከዚህም በተጨማሪ በቤቱ ውስጥ አሉ የተባሉት እቃዎች ንብረትነታቸው በስር ፍ/ቤት 2ኛ ከሳሽ የነበሩት የአቶ ግርማ እሸቴ ስለመሆናቸውም ተጠሪ ክሳቸውን ሲመሰርቱ በክስ ማመልከቻው ላይ ያሰፈሩና ይህንኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 92 መሰረት ጭምር የአረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በቀላሉ ለመገንዘብ የሚቻለው የቤት ቁጥር 528/ለ በሚል በሚታወቀው የንግድ ቤት ውስጥ የአሁኑ 2ኛ አመልካች የሚኖሩ መሆኑና ይዞታውን የያዙትም ተጠሪ እያወቁ መሆኑ መረጋገጡን፣ ተጠሪ ያለ 1ኛ አመልካች እውቅና ንግድ ቤቱ በአቶ ግርማ እሸቴ አማካኝነት ለአሁኑ 2ኛ አመልካች ተሰጥቶ አመልካቹ ይዞ ባለበት ሁኔታ በመንግስት ቤቶች አጠቃቀም ላይ የተከሰተውን ችግር ለመቅረፍ ሲባል መመሪያው መውጣቱን ነው፡፡ 2ኛ አመልካች በንግድ ቤት የሚገኘውን ትርፍ በጋራ ለመጠቀም ከስር ሁለተኛ ከሳሽ ከነበሩትና የመክሰስ መብት የላቸውም ተብሎ ከክሱ ከወጡት ከአቶ ግርማ እሸቴ ጋር በተዋዋሉት መሰረት ቤቱን ይዘው መገኘታቸውም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ከክርክር ሂደት ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መመሪያ አንድ ሰው ከመንግስት የተከራየውን የንግድ ቤት ከአከራዩ እውቅና ውጪ ለሌላ ሶስተኛ ወገን አስተላልፎ መገኘቱ ከተረጋገጠ ውሉ የሚቋረጥና ቤቱን የሚያስተዳድረው አካልም በመመሪያው የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች ተሟልተው እስከተገኙ ድረስ ውሉን ቤቱን ከቀድሞው ተከራይ ከተከራየው ሰው ጋር ሊገባ እንደሚገባ ያሳያል፡፡ ይህንኑ ይዘን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የበታች ፍ/ቤቶች የ1ኛ አመልካችን እርምጃ ሁከት ነው፣ ኪራዩን ከተጠሪ ጋር ሊቀጥል ይገባል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ተጠሪዋ ከአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል የለም፣ አቶ ግርማ እሸቴ ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር ያደረጉት ሕጋዊ ውል የለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች እና አቶ ግርማ እሸቴ አደረጉ የተባለው ውል ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ በውሉ መብትና ግዴታ ባገኙት ተዋዋይ ወገኖች ላይ ተገቢውን ውጤት የሚያስከትል ከሚሆን በስተቀር ንግድ ቤቱ ለሶስተኛ ወገን ከአሁኑ አንደኛ አመልካች እውቅና ውጪ አልተላለፈም ወደሚለው ድምዳሜ የማያደርስ ነው፡፡ ይልቁንም ተጠሪ አቶ ግርማ እሸቴ ተገቢውን ውል ያደረጉ መሆኑን አምነው በአንድ የከሳሽነት ዘንግ አሰልፈው ክስ መመስረታቸው ሲታይ አቶ ግርማ እሸቴ ቤቱን ለአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ማስተላለፋቸውን የሚያሳይ እና ተጠሪዋ በቤቱ ራሳቸው ሳይሰሩበት በሌላ አግባብ ለማሰራት የፈቀዱ መሆኑን አረጋጋጭ ነው፡፡ ሲጠቃለልም የአሁኗ ተጠሪ ቤቱን ከሚመለከተው አስተዳደር አካል

ጋር ውል ገብተው ከተከራዩ በኂላ ከአከራዩ እውቅና ውጪ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው ያሉ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች አስተዳደር አካሉን የማይመለከተው የጋራ ስራ ጥቅም ስምምነት ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን መሰረት በማድረግ የ1ኛ አመልካችን እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት መወሰናቸው በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች አንድ ተግባር ሕገ ወጥ ነው ለማለት የሚቻልባቸው ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ያስፈሩትን መመዘኛ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 04938 መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 17796 ሐምሌ 17 ቀን 2004 እና በመ/ቁጥር 17696 ሚያዝያ 15 ቀን 2004 በተሰጡ ትእዛዝ፣ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18358 ነሐሴ 4 ቀን 2004 ዓ/ም እና በመ/ቁጥር 18247 ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ/ም በተሰጡት ትዕዛዛት የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ አከራካሪውን የንግድ ቤት ከአከራዩ እውቅና ውጪ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው የተገኙ በመሆኑ 1ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የኪራይ ግንኙነት አቋርጦ ከአሁን ሁለተኛ አመልካች ጋር ማድረጉ በመመሪያው መሰረት ህጋዊ ነው፣ ከተጠሪ ጋር ኪራይ እንዲቀጥል አይገደድም፣ ሁለተኛ አመልካችም ለተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመ/ቁጥር 83247 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 84330

ሚያዚያ 10 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ መንግስቱ አሾ /ቀረቡ/

ተጠሪዎች ፡-1. ወ/ሮ እመቤት ጥላሁን

2. ወ/ሮ አልማዝ ጥላሁን

3. አቶ ስዩም ጥላሁን

4. አቶ ፍቃዱ ጥላሁን

5. ወ/ሮ ትዕግስት ጥላሁን

ተወካይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን የሚመለከት ሆኖ በአሁን የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ከሳሽ ባቀረቡት ክስ፡- ከተከሳሾች ጋር በ22/10/2002 ዓ/ም ባደረግነው የጥብቅና አገልግሎት ውል በውርስ ንብረት ላይ ክርክር እንዳካሂድና ከሚያገኙት ድርሻም ብር 30,000 በቁርጥ ለመክፈል የተስማሙ ሲሆን እኔም በውሉ መሰረት በተለያዩ መዛግብት ክርክር በማድረግ ያስወሰንኩ ቢሆንም በተለያየ ጊዜ ብር 9,000 ከፍለው ቀሪውን የሚፈለግባቸውን ብር 20,000 ያልከፈሉኝ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ በውሉ ከተቀመጠው የገደብ መቀጫ ብር 6,000 ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሾችም ለክሱ በሰጡት መልስ፡- ከሳሽ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጡ መስማማታችን የማይካድ ቢሆንም በ22/10/2002 ዓ/ም በጽሁፍ ያደረግነው ስምምነት የለም፣በማስረጃነት ባቀረቡት የውል ኮፒም ላይ የተፈረመው

ፊርማ የእኛ አይደለም፣ከከሳሽ ጋር በቃል ስምምነት ያደረግን ሲሆን ስምምነቱም በፍርድ ቤት ቀጠሮ ባለበት ቀን ብቻ ቆመው እንዲከራከሩልን ሲሆን በስምምነታችን መሰረት የሚፈለግብንን ብር 4,000 የከፈልን በመሆኑ በሀሰት ያቀረበብን ክስ ውድቅ ሊሆን የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ኮፒው የቀረበው የጽሁፍ ውሉ የተካደ በመሆኑ ዋናውን ውል ከሳሽ እንዲያቀርቡ አዞ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ከጠየቁ በኋላ ዋናው ውል ከመዝገቡ ውስጥ የጠፋብኝ በመሆኑ ማግኘት አልቻልኩም በማለታቸው በቀረበው የውል ኮፒ ላይ ስማቸው የተጠቀሰውን የከሳሽ ምስክሮች እና ተከሳሾች ያቀረቡአቸውን ምስክሮች በመስማት በሰጠው ውሳኔ የከሳሽ ምስክሮች በ22/10/2002 ዓ/ም ከሳሽና ተከሳሾች ባደረጉት ውል ተከሳሾቹ ለጥብቅና አገልግሎት  ብር 30,000 ለመክፈል በከሳሽ ጽ/ቤት ውስጥ መስማማታቸውን ሲያስረዱ በተከሳሾች በኩል ከቀረቡት ምስክሮች ውስጥ 1ኛው ምስክር ከሳሽ እና ተከሳሾች እንደ ቤተሰብ የሚታዩ እና ከሳሽም ተከሳሾች በፍርድ ቤት ቀጠሮ ባላቸው ጊዜ ብቻ ፍርድ ቤት እየቀረቡ ሲከራከሩ መቆየታቸውንና ተከሳሾችም በተለያዩ ጊዜያት ገንዘቡን ሲከፍሉ ማየታቸውን ከዚያም በፐርሰንት ክፈሉ ውልም ፈርሙ በማለታቸው የተነሳ ተከሳሾቹ ስላልተስማሙ ግንኙነታቸው መቋረጡን ማስረዳታቸውን 2ኛ ምስክር ደግሞ በፍርድ ቤት በቀጠሮ ቀን ለዋሉበት ተከሳሾቹ ለከሳሽ ገንዘብ ሲከፍሉ መቆየታቸውን እንጂ ስምምነቱ በጽሁፍ ወይም በቃል ስለመሆኑ እንደማያውቁ ማስረዳታቸውን በመግለጽ፤ ተከሳሾች ብር 30,000 ለመክፈል የተስማሙ መሆናቸውን በውሉ ኮፒ ላይ ስማቸው የተጠቀሰው ምስክሮች ያስረዱ ስለሆነና ተከሳሾችም ስምምነቱ ውሸት መሆኑን ገልጸው ከመከራከራቸው በስተቀር ገንዘቡን ስለመክፈላቸው በግልጽ ክደው ባለማከራከራቸውና ባቀረቡአቸው ምስክሮችም ባለማስተባበላቸው ቀሪውን ገንዘብ ብር 20,000 ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የመቀጫ ገንዘብን በተመለከተ ግን ከሳሽ በአንድ በኩል ውሉ እንዲፈጸምላቸው እየጠየቁ በሌላ በኩል የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፈላቸው የጠየቁት ተገቢ ባለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ/1890(2) መሰረት ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዮችን አሰናብቷቸዋል፡፡

የስር ተከሳሾችም በፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በማቅረባቸው ችሎቱ የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ፡-

በጽሁፍ የተደረገ የውል ስምምነት የለም በሚል በአንደኛው ተከራካሪ ወገን በተካደ ጊዜ ውል አለ የሚለው ወገን ዋናውን ውል ወይም የግልባጩ ትክክለኛነት የተረጋገጠውን በማስረጃነት ማቅረብ የሚገባው ሲሆን በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪው ዋናውን ውል ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን የገለጹ ሲሆን ያቀረቡት የውሉ ግልባጭም (ኮፒ) ይህንኑ ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ቀርቦ ያልተረጋገጠ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የውል ስምምነት መኖር አለመኖሩን በውሉ ላይ ያሉትን ምስክሮች ሊሰሙ የማይገባ ሆኖ ሳለ ሰምተው የወሰኑት የፍ/ህ/ቁ/1719፣1726 እና 1727 ፣2001፣2003፣2005 እና 2012 ድንጋጌዎችን የሚቃረን ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች(የሥር ተከሳሾች) ገንዘቡን እንዲከፍሉ የሰጡትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታም ለዚህ ችሎት የቀረበው በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብ ሲጠቃለል፡- ተጠሪዎች የአባታቸውን እና

የእናታቸውን የውርስ ሀብት በተመለከተ እንድከራከርላቸው በቁጥር 022956 በቀን 01/10/2002 ዓ/ም የተጻፈ ውክልና ሰጥተው በዚሁ ውክልና መሰረት በ6 መዛግብት ላይ በወረዳ ፍርድ ቤት ተከራክሬ አስወስኜ እያለሁና ተጠሪዎቹም ስከራከርላቸው ስለመቆየቴ አምነው በጽሁፍ ውል አልተዋዋልንም ሲሉ በመከራከራቸው የወረዳው ፍርድ ቤት በውሉ ላይ ያሉትን የአመልካች ምስክሮችና የተጠሪዎችን ምስክሮች በመስማትና በመመዘን የአመልካች ምስክሮች ያስረዱትን የተጠሪዎቹ ምስክሮች ማስተባበል አለመቻላቸውን በማረጋገጥ የሰጠውን ውሳኔና ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ያጸናውን ሰበር ሰሚው ችሎት ዋናው ሰነድ ከጠፋ ኮፒው በፍጹም ዋጋ እንደሌለው አድርጎ የፍርድ ቤቶቹን ውሳኔ የሻረው የህግ መሰረት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- አመልካች ተጠሪዎች ያልፈረምንበትን የሐሰት ውል አዘጋጅተው ዋናው ስለጠፋ በውሉ ላይ ባሉት ምስክሮች ይረጋገጥልኝ ሲሉ ያቀረቡትን ክርክር የወረዳው እና ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተቀበለው ቢወስኑም የጠፋ ሰነድ የሚመሳከርበት ሌላ ሰነድ እስካልቀረበ ድረስ በሰው ማስረጃ ማረጋገጥ የማይቻል በመሆኑ ምክንያት ሰበር ሰሚው ችሎት ክሱን ውድቅ ያደረገው ተገቢ በመሆኑ አቤቱታቸው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ለተጠሪዎች መልስም፡- አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤቶች የሠጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪዎች ክስ የቀረበባቸውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ሲል የወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በመካከላቸው የጥብቅና አገልግሎት ውል ስለመኖሩ የሚያምኑት ጉዳይ ሲሆን የሚያለያያቸው ነጥብ ግን ውሉ የተደረገበት ሁኔታና የገንዘቡ መጠን ነው፡፡ ይሔውም አመልካች ውሉ በጽሁፍ መደረጉንና የተዋዋሉበት የገንዘብ መጠንም ብር 30,000 መሆኑን ገልጸው የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ግን ውሉ የተደረገው በጽሁፍ ሳይሆን በቃል መሆኑን እና በስምምነቱ መሰረትም የሚፈልግባቸውን ብር 4,000 ስለመክፈላቸው በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ በጽሁፍ እንዲደረጉ በግልጽ በህግ ካልተደነገጉ የውል ዓይነቶች በስተቀር ማንኛውም ውል በቃል፣በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ግዴታ ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ሊደረግ ይችላል፡፡ እንዲሁም ውሉ በጽሁፍ እንዲደረግ ህጉ ባያስገድድም ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን በጽሁፍ እንዲሆን የማድረግ መብት አላቸው፡፡ በዚህ ጉዳዩ ግን ውሉ በጽሁፍ ተደርጓል የሚሉት አመልካች ሲሆኑ ለዚህም በማስረጃነት የውሉን ኮፒ ማቅረባቸውን ከክርክሩ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ አመልካች የውሉን ኮፒ ያቀረቡት ዋናው ውል ጠፍቷል በሚል ሲሆን ይህ በማስረጃነት የቀረበው የውሉ ኮፒም አግባብ ባለው አካል ከዋናው ውል ጋር ስለትክክለኛነቱ በፍ/ህ/ቁ/2011(1) መሰረት የተረጋገጠ አይደለም፡፡ አመልካች ውሉ በጽሁፍ ተደርጎ ተፈራርመናል እስካሉ ድረስም ዋናውን ውል በተመለከተ ማስረዳት የሚጠበቅባቸው ውሉ የጠፋ ስለመሆኑ እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ/2003 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በአንድ ውል የተጠቀሱ ምስክሮችም መሰማት ያለባቸው ተዋዋዮች ውሉን ተስማምተው የፈጸሙ መሆናቸውንና የውሉ ቃል ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ/1730(1) ተመልክቷል፡፡በዚህ ጉዳይ ግን ዋናው ውል ስለመጥፋቱ አመልካች

በማስረጃ ሳያስረዱ በውሉ ኮፒ ላይ ስማቸው የተጠቀሰውን ምስክሮች እንዲሰሙላቸው ያቀረቡትን ክርክር የወረዳው ፍርድ ቤት ተቀብሎ የምስክሮችን ቃል መስማቱ ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች ዋናውን የጽሁፍ ውል በማስረጃነት ማቅረብ የማይችሉ ከሆነና ኮፒውም አግባብ ባለው አካል ስለትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ ከሆነ በሌሎች ማስረጃዎች ተጠሪዎች በውሉ ለጥብቅና አገልግሎት ብር 30000 ለመክፈል የተስማሙ ስለመሆናቸው ክሱን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ መልኩ የማስረዳት ሸክማቸውን ማስረጃን የመስማትና የመመዘን ሥልጣን ላላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ማስረጃዎቻቸውን አቅርበው አለማስረዳታቸው ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች ባቀረቡአቸው ማስረጃዎች አመልካች በቀጠሮ ቀን ብቻ ፍርድ ቤት የሚገኙ ስለመሆናቸው እና ለተገኙባቸው የቀጠሮ ቀናትም ገንዘብ የከፈሉአቸው ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር በማስረጃ ካስረዱት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች ክሱን አስረድተዋል ቢባል እንኳን ተጠሪዎቹ እንዲከፍሉአቸው የጠየቁት የአገልግሎት ክፍያ ተገቢና ሚዛናዊ መሆን ስላለመሆኑ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በመመርመር ከመጠን በላይ ተዋውለው ከተገኙም ለመቀነስ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ 2635 ከተደነገገው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ችሎት እምነት አመልካች በክሳቸው ተጠሪዎቹ እንዲከፍሉዋቸው ከገለጹት ገንዘብ መጠን እና ተጠሪዎች በቃል ውሉ አመልካች በቀጠሮ ቀን ብቻ ፍርድ ቤት እየተገኙ እንዲከራከሩላቸው ተስማምተናል በሚል በማስረጃ ካረጋገጡት ፍሬ ነገር አንጻርም የተቀበሉት ገንዘብ በቂ ነው ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ምንም እንኳን የጽሁፍ ማስረጃ በመኖሩ የሰው ምስክሮችን መስማት አይገባም ሲል በውሳኔ ላይ ያሰፈረው ትችት ከውል ጋር ተያይዞ የጽሁፍ ማስረጃ ቢኖር እንኳን ምስክሮች ሊሰሙ ስለሚችሉበት አግባብ በፍ/ህ/ቁ/1730(1) የተመለከተውን መሰረት ያደረገ ባይሆንም፤ እንዲሁም በተከራካሪዎቹ መካከል የጸሁፍ ውል ባይኖርም የቃል ውል ስለመኖሩ ተጠሪዎቹ አምነው በተከራከሩበት ሁኔታ ሰበር ሰሚው ችሎት ውል የለም ሲል በውሳኔው ያሰፈረው የፍሬ ነገር ክርክሮችን የሚመረምሩ ፍርድ ቤቶች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት ባይኖረውም በዉጤት ደረጃ በውሉ ኮፒ ስማቸው የተጠቀሰውን ምስክሮች በመስማት ከተጠሪዎች ምስክሮች ቃል ጋር በማመዛዘን በክሱ የተመለከተውን ገንዘብ ተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል ሲሉ የሥር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት ውሳኔ በመሻር ገንዘቡን ሊከፍሉ አይገባም በሚል በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/147419 በቀን 05/02/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ በመቀበል በፍ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ዋናው ውል የጠፋ መሆኑን ባላስረዱበትና በማስረጃነት ያቀረቡት የውሉ ኮፒም ከዋናው ውል ጋር ተገናዝቦ ትክክለኛነቱ አግባብ ባለው አካል ባለመረጋገጡ በተከራካሪዎቹ መካከል በጽሁፍ የተደረገ የጥብቅና አገልግሎት ውል የለም ብለናል፡፡ ሆኖም በቃል በተደረገው ውል መሰረት ተጠሪዎች ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ለአመልካች የከፈሉ ስለመሆናቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ቀደም ሲል ከከፈሉት ገንዘብ በተጨማሪ ሊከፍሉ አይገደዱም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

የሰ/መ/ቁ. 81163

የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሲሳይ ረታ ጠበቃ አቶ መዝገቡ ወልዴ ቀርቧል

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ነ/ፈጅ አቶ ሙሉጌታ ቀርቧል

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመጋዘን ኪራይ ውል ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪ በአ/ብ/ክ/መንግስት ሰሜን ጎንደር መስተደድር ዞን ከ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የተጠሪ ንብረት የሆነውና በጎንደር ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘው መጋዘን አመልካች ከመጋቢት 1 ቀን 1997ዓ.ም እስከ የካቲት 30 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ በወር ብር 5109.45 ኪራይ እየከፈለ ሲጠቀም የቆየ መሆኑን ጠቅሶ የኪራይ ውሉ ከሚያበቃበት መጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ አመልካች የመጋዘኑን ወራሃዊ ኪራይ ክፍያ ብር 13,800 እየከፈለ ውሉ በዚህ መልኩ ተሻሽሎ እንዲቀጥል ወይም በዚህ መልኩ ተስማምቶ ለመቀጠል ካልፈለጉ ደግሞ መጋዘኑን እንዲያስረክብ በተለያዩ ደብዳቤዎች ማስጠንቀቂያ ቢጻፍለትም እምቢተኛ በመሆንና ከእኛ ፈቃድ ውጪ የቀድሞውን የመጋዘኑን የኪራይ መጠን በባንክ ሂሣባችን እያስገባ በመጋዘኑ መጠቀም የቀጠለ በመሆኑ የመጋዝኑን ኪራይ ከቀን 1/7/2001ዓ.ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ18 ወራት ኪራይ ክፍያ በ13,800 ታስቦና ካለእኛ ፈቃድ የከፈለው ተቀንሶለት ባጠቃላይ ብር 156,429 እንዲከፍልና እንዲሁም ከመስከረም1 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ መጋዝኑን እስኪያስረክብ ድረስ ያለውን ብር 13,800 ወርሃዊ ኪራይ ክፍያ ታስቦ ከወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካችም ቀርቦ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ጉዳዩ ላይም ወርሃዊ የመጋዘኑን ኪራይ ክፍያ በተመለከተ በብር 13,800 እንዲከፍል የሚያስገድደው የውልም ሆነ የህግ ግዴታ አለመኖሩን በመከራከር መልስ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ከመረመረ በኋላ የቀድሞው የኪራይ ውል ጊዜ ከማለቁ በፊት ተጠሪ ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የመጋዘኑ ወርሃዊ ኪራይ መጠን ብር 13,800 መሆኑን ጠቅሶ በተለያዩ ጽሑፎች ለአመልካች በመግለጽና በዚሁ መልኩ ውሉ ተሻሽሎ እንዲቀጥል አልያም በዚህ የማይስማማ ከሆነ ደግሞ መጋዘኑን እንዲያስረክብ በተገለፀለት መሰረት አመልካች ቀርቦ ካለመዋዋሉም ባሻገር የቀድሞ ኪራይ ውል ጊዜ ከተጠናቀቀም በኋላ መጋዘኑን ሣያስረክብ ይዞ መጠቀሙን መቀጠሉ በተጠሪ የቀረበለትን ድርድር ወይም አዲሱን ወርሃዊ የኪራይ

መጠን በዝምታ የተቀበለ መሆኑን ስለሚያሳይ ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ የካቲት 15 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ወርሃዊ ክፍያ በብር 13,800 ታስቦና የተከፈለው ተቀንሶለት ብር 387,990.45 ለተጠሪ ከፍሎ መጋዘኖቹንም እንዲያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ቅሬታውን ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ቅሬታውን ሰርዞታል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አመልካች ሰኔ 25 ቀን 2004ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ማመልከቻ ይዘትም ባጭሩ አመልካች የመጋዘኑን ኪራይ በተመለከተ በወር ብር 13,800 ለመክፈል በየትኛውም መልኩ የተስማማሁት ውል ሣይኖር እና እንዲሁም አዲሱን የኪራይ መጠን እንደማልቀበል በግልጽ ለተጠሪ ምላሽ በመስጠትና ይልቁንም በመጀመሪያ የኪራይ መጠን መቀጠል እንደምፈልግ ሐሳቤን በመግለጽ አሳውቄ እያለሁ አዲሱን ዋጋ በዝምታ ተቀብሎታል በማለት የተሰጠው ውሣኔ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1684 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሣኔው ታርሞ በተዋዋልኩት ውል መሰረትና በቀድሞው የኪራይ መጠን እንዲከፍል ውሣኔ እንዲሰጥለት ዘንድ ጠይቋል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ አመልካች አዲሱን የመጋዘን ኪራይ ዋጋ በዝምታ በመቀበል ተስማምቶበታል ተብሎ በአዲሱ የኪራይ ዋጋ ስሌት መሰረት የኪራይ ገንዘቡን እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2950 አኳያ ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪም ቀርቦ የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈጠረ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለመኖሩን ጠቅሶ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ፀድቆ ከበቂ ወጪና ኪሣራ ጋር እንዲወሰንለት ዘንድ በመጠየቅ መልሱን የሰጠ ሲሆን አመልካችም የበኩሉን የመልስ መልስ ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች የቀረበለትን አዲሱን የኪራይ ዋጋ በዝምታ በመቀበልና መጋዘኑንም የቀድሞ የኪራይ ውል ጊዜ ከተጠናቀቀም በኋላ ሣያስረክብ መጠቀሙን የቀጠለ በመሆኑ በአዲሱ ዋጋ እንደተስማማ ተቆጥሮ የኪራዩን ገንዘብ በዚህ ስሌት ዋጋ አመልካች ሊከፍል ይገዳደዳል በሚል ተጠሪ የሚከራከር ሲሆን አመልካች ደግሞ በተጠሪ የቀረበውን የኪራይ ዋጋ እንደማልቀበልና እንደማልስማማበት ሐሳቤን ገልጬ ስቃወም ስለነበረ በዝምታ እንደተቀበልኩ ተቆጥሮ የሚወሰድበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ይከራከራል ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ አመልካች በተጠሪ የቀረበለትን አዲሱን የመጋዝን ኪራይ ዋጋ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1684 ድንጋጌ ስር በተመለከተው መልኩ በዝምታ ተቀብሎ እንደተስማማበት ሊቆጠር ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው መፍትሔ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጠሪ የቀረበለትን የኪራይ ዋጋ ማሻሻያ መጠን አስመልክቶ አመልካች በመቃወም ምላሽ የሰጠ ስለመሆኑና ይህንኑ ምላሽ የሰጠበትን የጽሑፍ ሰነድም በማስረጃነት ቆጥሮ ለስር ፍ/ቤት በማቅረብ የተከራከረ ስለመሆኑ ከቀረቡት ውሳኔ ግልባጮች መገንዘብ ተችሏል፡፡ ተጠሪም የኪራይ ማሻሻያውን አመልካች በዝምታ ተቀብሎታል በሚል በደፈናው መከራከሩን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1684 (2) ስር እንደተመለከተው ለምላሹ በቂ ጊዜ ተቆርጦለት በዚያው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ አመልካች መልስ ሣይሰጥ በመቅረቱ የማሻሻያ ዋጋውን እንደተቀበለ ይቆጠራል በሚል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ምላሹ የተቆረጠ የጊዜ ገደብ ስለመኖሩ የተገለፀ ነገር ካለመኖሩም ባሻገር

በዚህ ረገድ የቀረበ ክርክርም ባለመኖሩ በተጠሪ የቀረበውን የኪራይ መጠን ማሻሻያ ዋጋ ድርድር ወይም ሐሳብ አመልካች በደረሰ በወሩ ወይም ከዚህም በበለጠ ጊዜ ውስጠ አመልካች የተቃውሞ ሓሳቡን በመግለጽ ምላሹን ከሰጠ ድርድሩን በዝምታ ተቀብሎታል ተብሎ ሊወሰድ የሚቻልበት የሕግ አግባብ አይኖርም በተጠሪ የቀረበለትን የኪራይ መጠን ዋጋ ማሻሻያ ሐሳብ ከላይ በተገለፀው መልኩ አመልካች በዝምታ እንደተቀበለ የሚቆጠርበት አግባብ የለም የሚል መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ ደግሞ የኪራይ መጠኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2950(1) ስር እንደተገለፀው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ተወስኗል ለማለት አይቻልም፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ምንም እንኳ የቀድሞው የኪራይ ውል ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ አዲሱ የኪራይ ልክ በሕጉ አግባብ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ተወስኖ ያልታወቀ ቢሆንም አመልካቹ መጋዘኑን መጠቀም የቀጠለ በመሆኑ ላገኘው አገልግሎት ኪራይ ሊከፍል ይገደዳል ፡፡ ምን ያህል የኪራይ ልክ ሊወሰን ይገባል የሚለውን በተመለከተ አመልካች የቀድሞውን የኪራይ ውል መነሻ በማድረግ በወር ብር 5,109.45 መሆን አለበት ብሎ የሚከራከረውም ሆነ ተጠሪ በወር ብር 13,800 መሆን አለበት የሚለው ክርክር ከላይ በተገለፀው መልኩ የሁለቱንም ወገኖች ስምምነት መነሻ ያደረገ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2950(2) ስር በተመለከተው መልኩ የኪራይ ልኩ በተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት ሣይወሰን የቀረ እንደሆነ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት በወሰኑት በታሪፍ መሠረት ወይም ይህ በሌለ ጊዜም የአካባቢውን የወቅቱን ነፃ ገበያ ዋጋ መነሻ በማድረግ ሊወሰን እንደሚገባ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሲጠቃለል የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከ/ፍ/ቤት ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የመጋዘኑን ወርሃዊ የኪራይ መጠን እላይ በተገለፀው መልኩ በማዘጋጃ ቤቱ የተወሰነ ታሪፍ ካለ በዚያ መሰረት ይህ ከሌለ ደግሞ የአካባቢውን ልማድ ወይም ወቅታዊ ነፃ ገበያ ዋጋ መነሻ በማድረግ መወሰን ሲገባ የአመልካች ፍቃድና ስምምነት የሌለበትን ወርሃዊ ኪራይ ክፍያ ብር 13,800 በመቀበልና በዚህ አስልቶ መወሰኑና እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ይህን ስህተት ማረም ሲገባ ማፅናቱ በውሳኔዎቹ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከ/ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የመጋዘኑን ወርሃዊ ኪራይ መጠን ብር 13,800 እንደሆነ በመወሰድና ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የኪራይ ገንዘብ በዚህ በማስላት ያልተከፈለውን ብር 387,990.45 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ብቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከ/ፍ/ቤት የራሱ መ/ቁ 05667 የሆነውን በማንቀሳቀስ ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ያለውን ወርሃዊ የኪራይ መጠን እላይ በፍርዱ ክፍል ውስጥ በተገለፀው መልኩ ግራ ቀኙን በድጋሚ አከራክሮ በመስማት አጣርቶ ከወሰነ በኋላ ያልተከፈለውን የኪራይ ገንዘብ በዚያ በማስላት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ ህ/ቁ 343(1) መሰረት በመመለስ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር ምክንያት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/ጥ**

የሰ/መ/ቁ. 79794

ሚያዝያ 22 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የማይክሮሊንክ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ኃ.የተ.የግል ማህበር

ስራ አስኪያጅ ዳዲ ሁንዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ነ/ፈጅ ትቤሶ በዛብህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከኪራይ ውል ጋር ተያይዞ የተነሳውን የንብረት ጉድለትና የተቋረጠ ጥቅም ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም፡- ከአሁኑ አመልካች ጋር ሐምሌ 01 ቀን 1990 ዓ/ም በተፈረመ ውል በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11/12 የሚገኘውንና ቁጥሩ 672 የሆነውን የተጠሪን ህንጻ ለአሁኑ አመልካች ማከራየቱን፣የኪራዩ ዘመንም ተራዝሞ ከአስር አመት በላይ አመልካች ሕንጻውን ሲገለገልበት መቆየቱን፣የኪራይ ዘመኑ ሲያልቅ ሕንጻውን አድሶና ተረክቧቸው የጠፉ፣የተሰበሩና ያረጁ እቃዎችን በአዲስ ተክቶ ሊያስረክብ ተከራይ የሆነው አመልካች ግዴታ መግባቱን፣የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኂላ የርክክብ ሁኔታውን በተመለከተ ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ/ም በተፈረመ ሰነድ ሕንጻውን አድሶ የጠፉ፣የተሰበሩና የአረጁ እቃዎችን በአዲስ ተክቶ ሊያስረክብ መተማመኛ መስጠቱን፣ሕንጻውን ለማሳደስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ እድሳቱ በብር 151,725.25 እንዲከናወን አሸናፊ መመረጡን፣ለጠፉ፣ለተሰበሩና ላረጁ እቃዎች መተኪያ የብር 150,848.00 ፕርፎርማ መሰብሰቡን፣በዚህ መሰረት ሕንጻውን አሳድሶና እቃዎቹን ተክቶ እንዲያስረክብ የአሁኑ አመልካች ቢጠየቅም ፈቃደኛ ያለመሆኑን፣ተጠሪ ህንጻውን በወር በብር 20,000.00፣የህንጻውን አዳራሽ ደግሞ በወር ብር 4000.00 አከራይቶ ገቢ ሊያገኝ ይችል እንደነበር፣አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈጸሙ ተጠሪ ከመስከረም 01 ቀን 2001 ዓ/ም አንስቶ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ባሉት ሃያ ሁለት ወራት ብር 528,000.00 የኪራይ ገንዘብ ማጣቱን፣ለህንጻው ማሳደሻ ብር 302,573.25 እንደሚያስፈልግ እንዲሁም እንደውሉ ባለመፈፀሙ ደግሞ በውሉ አንቀፅ 6(12) መሰረት ብር 30,000.00 ለመክፈል ስምምነት ማድረጉን ዘርዝሮ በድምሩ ብር 860,573.25 እና ለክሱ የወጣውን ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል ዳኘነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡



www.chilot.me

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካች ህንጻውን አሳድሶ መስከረም 01 ቀን 2001 ዓ/ም ሙሉ በሙሉ መልቀቁን፣ተጠሪ ህንጻውን አመልካች እንዲረከብ በተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርብ ቆይቶና ተደጋጋሚ መፃጻፍ አድርጎ ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ/ም ህንጻውን ተጠሪ መረከቡን፣ርክክቡ የዘገዬው በተጠሪ ጥፋት በመሆኑ ለዘገዬበት ጊዜ ተጠሪ የጠየቀው የኪራይ ገንዘብ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ፣በህንጻው ያለመታደስ ምክንያት እንዴት አድርጎ የብር 528,000.00 ጉዳት እንደደረሰበት ተጠሪ ያለማስረዳቱን፣የቀረበው ስሌትም የውል መሰረት እንደሌለውና ርክክቡን ተጠሪ ለማከናወን ያልቻለው በመጠነኛ ጉድለት ምክንያት እንጂ ህንጻውን ለመጠቀም የማያስችሉ ጉድለቶች በመኖራቸው ምክንያት ያለመሆኑን፣ሕንጻውን ተጠሪ የተረከበው መልሶ ለማከራየት ሳይሆን ለራሱ ሊጠቀምበት በመሆኑ የኪሳራው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው፣ሕንፃው ለረዥም ዘመን ያገለገለ በመሆኑ በተፈጥሮ ማርጀቱንና የተጠሪ ጥያቄ ህንጻውን ማሳደስ ሳይሆን መቀየር በመሆኑ የራሱን የጨረታ ኮሚቴ አቋቁሞ ያቀረበው የእድሳት ገንዘብ ጥያቄ አግባብ ያለው እንዳልሆነ፣ህንጻውን ሲረከብ የነበረው የተፈጥሮ እርጅና ግምት ውስጥ ገብቶ ተጠሪ እዳሳት የማያስፈልገውን የሕንፃ ክፍል ለይቶ አመልካችም ለዚያ እድሳት ለምን ኃላፊ እንደሚሆን አስረድቶ ሕንፃውን ሲሰራ ወይም ህንጻ ሲሰራ ወደ ነበረበት ሁኔታ ሳይሆን በአመልካች ጥፋት እድሳት ላስፈለገው የህንጻ አካል ብቻ በገለልተኛ ወገን በሚገመተው መሰረት እንዲያሳድስ እንዲወሰንለት፣የሚተኩ እቃዎችን በተመለከተ የቀረበው ጥያቄ ግልፅ ባለመሆኑ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ፣ሕንጻው በሰጠው አገልግሎት ምክንያት ያረጁትን እቃዎች ሁሉ እንዲተካ መጠየቁ አግባብነት የሌለው መሆኑንና የቀረቡት ፕሪፎርማዎችን የተነጋነነ ዋጋ የያዙ መሆኑን እንዲሁም ዋጋውም ስምምነቱን መሰረት ያላደረገ መሆኑና የኃላፊነት መጠኑ ከብር 50,000.00 እንደማይበልጥ በውሉ መመልከቱን፣አመልካች የውል ግዴታውን ባይፈፅም የሚኖርበት የኃላፊነት መጠን የብር 30,000.00 ብቻ ስለመሆኑ ውሉ እንደሚያስረዳ ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለህንፃው ማሳደሻ የተጠቀየውን ገንዘብ ብር 302,573.25፣ተጠሪ ያጣውን የኪራይ ገቢ ብር 488,000.00 ክስ ከተመሰረተበት ከሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል፣ወጪና ኪሳራ በቁርጥ ብር 2000.00(ሁለት ሺህ) እንዲከፍል ወስኖበታል።በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ህንጻው ቢከራይ ኑሮ ሊያስገኝ ይችል በነበረው የኪራይ ገቢ መጠኑ ላይ ብቻ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ችሎቱ በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር በመመርመር አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ መባሉን በመቀበል የኃላፊነት መጠኑን በተመለከተ ግን ከብር 488,000.00 ወደ ብር 244,000.00(ሁለት መቶ አርባ አራት ሺህ ብር) ዝቅ አድርጎ አመልካች ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል መጠኑን ለይቶና ለእድሳት ያስፈልጋል የተባለውን ገንዘብ ብር 302,573.25 ለተጠሪ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማፅናት ዳኝነት ሰጥቷል።የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን የመከራከርያ ነጥቦችን በማጠናከር የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በተገቢው መንገድ ያልተመለከቱት መሆኑንና የሕግ መሰረት በሌለው አኳኋን መወሰኑን የሚጠቅስና ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው።አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ሕንጻ ተጠሪ ለጳውሎስ ሚዲካል ኮሌጅ እያከራየው የነበረ ስለመሆኑ በከፊልም ቢሆን አምኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በርትዕ አይቶ ለመወሰን የሕግ መሰረት የነበረው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከተጠሪ ህንጻውን ተከራይቶ ሲጠቀምበት የቆየ መሆኑንና የኪራይ ዘመኑ ሲያልቅ ሕንጻውን አድሶና ተረክቧቸው የጠፉ፣የተሰበሩና ያረጁ እቃዎችን በአዲስ ተክቶ ሊያስረክብ ተከራይ ግዴታ መግባቱን፣የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኂላ የርክክብ ሁኔታውን በተመለከተ ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ/ም በተፈረመ ሰነድ ሕንጻውን አድሶ የጠፉ፣የተሰበሩና የአረጁ እቃዎችን በአዲስ ተክቶ ሊያስረክብ መተማመኛ መስጠቱን፣ሕንጻውን ለማሳደስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ አድሳቱ በብር 151,725.25 እንዲከናወን አሸናፊ መመረጡን፣ለጠፉ፣ለተሰበሩና ላረጁ እቃዎች መተኪያ የብር 150,848.00 ፕሪፎርማ መሰብሰቡን፣በዚህ መሰረት ሕንጻውን አሳድሶና እቃዎቹን ተክቶ እንዲያስረክብ የአሁኑ አመልካች ቢጠየቅም ፈቃደኛ ያለመሆኑን፣ ተጠሪ ሕንፃውን በወር ብር 20,000.00፣የህንጻውን አዳራሽ በወር ብር 4000.00 ተከራይቶ ገቢ ሊያስገኝ ይችል እንደነበር ቢገልፅም የአደራሹ የኪራይ ገቢ ያለመቋረጡን፣አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈጸሙ ተጠሪ ከመስከረም 01 ቀን 2001 ዓ/ም አንስቶ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ባሉት ሃያ ሁለት ወራት ብር 528,000.00 የኪራይ ገንዘብ ማጣቱን ቢገልፅም የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ያለመቀበላቸውን፣ለህንጻው ማሳደሻ ብር 302,573.25 እንደሚያስፈልግ በጨረታ ኮሚቴ መረጋገጡንና አመልካችም በሂደቱ ሲሳተፍ የነበረ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ነው፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በኪራይ ሲጠቀምበት የነበረው ሕንጻ በተገቢው ጊዜ ለተጠሪ ያላስረከበው በአመልካቹ ጥፋት ነው? ወይስ በተጠሪው ጥፋት ነው? የሚለው ጭብጥ በስር ፍርድ ቤቶች ታይቶና የግራ ቀኙ ክርክሮችና ማስረጃዎች ተመርምረው ርክክቡ ያልተፈጸመው በአመልካች ጥፋት መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ይህ ችሎት ርክክቡ የዘገዬው በአመልካች ጥፋት ነው? ወይስ በተጠሪ ጥፋት ነው? የሚለውን በማስረጃ የሚነጥረውን የፍሬ ነገር ክርክር በመመርመር የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የደረሱበትን ድምዳሜ ለመለወጥ የሚያስችለው ስልጣን የሌለው መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ አመልካች የርክክቡ ጊዜ በተጠሪ ጥፋት የዘገዬ ነው በማለት የሚያቀርበውን ክርክር የሚቀበልበት አግባብ አልተገኘም፡፡ሌላው አመልካች ህንጻውን አድሼአለሁ፣የእቃ ርክክብም ፈፅሜአለሁ እንዲሁም ጠፉ፣ተሰበሩ የተባሉት እቃዎች በህንጻው እርጅና የተከሰቱ ናቸው በማለት የሚያቀርበው ክርክር ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶቸ ውድቅ የተደረገ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የሚያሟላ የክርክር ነጥብ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም፡፡እንግዲህ አመልካች በኪራይ የተረከበውን ህንፃ ከኪራይ ዘመኑ ማለቅ በኃላ በተገቢው ጊዜ በማደስ፣የጠፉ፣የተሰበሩና የአረጁ እቃዎችን በመተካት ለባለንብረቱ ተጠሪ ለማስረከብ በውል ስምምነት ማድረጉ ከመረጋገጡም በላይ በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት ግዴታውን ያለመወጣቱ ከተረጋገጠ ተጠሪ በሕግ አግባብ

በተቋቋመ ውል መሰረት አመልካች ግዴታውን እንዲወጣ መጠየቁና ፍርድ ቤቶቹም በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎችን በመመርመር አመልካችን ግዴታውን አልተወጣም በማለት መወሰናቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ)፣1731፣1790 እና 1757 ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል እንደውሉ ያልተፈጸመለት ወገን እንደውሉ እንዲፈፅምለት ለመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ)፣1718፣1771(1)፣1790 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በዚህ አግባብ ጥያቄ የሚያቀርበው ተዋዋይ ወገን ሌላኛው ተዋዋይ ግዴታውን ባለመፈጸሙ ውሉን በግዴታ እንዲፈጽም ወይም እንዲፈረስ ከማስደረግም በቀር ከነዚሁ ማሻሻያዎች ጋራ አጣምሮ አንዱ ወገን ለደረሰበት ጉዳት ኪሳራ መጠየቅ እንደሚችል የፍ/ሕ/ቁጥር 1790(1) ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ጥያቄም አመልካች በውሉ በገባው ግዴታ ተገቢውን እንዲፈፅምና ባለመፈፀሙ ደግሞ የደረሰውን ኪሳራ እንዲተካ ይወሰን ዘንድ የሚያሳይ ነው፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩ ሲታይ የእድሳት ወጪም ሆነ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት እቃዎች ዋጋ በጨረታ ተወዳዳሪ ተጋብዞ የዋጋ መጠናቸው የተለዩ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ከላይ እንደተገለጸው በዚህ ረገድ በሰበር አቤቱታ ላይ የቀረበው ክርክር የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጭብጥ ያልተያዘበትና የፍሬ ነገረ ክርክር በመሆኑ የመጠኑ ተገቢነት በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም፡፡የህግ ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ ከጉዳት ጋር ተያይዞ የቀረበው ነጥብ አመልካች ህንጻውን በተገቢው ጊዜ አድሶ ባለማስረከቡ ለባከነው ጊዜ ሕንፃው ቢያከራይ ኑሮ ሊገኝ ይችል የነበረ የኪራይ ገቢ መጠን ምን ይህል ሊሆን ይገባል?፣በርትዕስ መወሰኑ ተገቢነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በመሰረቱ በውል አፈፃጸም ሂደት የሚደርሰው የጉዳት ኪሳራ የሚሰላበት አግባብ በፍ/ሕ/ቁጥር 1790 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት የሚቻለውም የጉዳት ኪሳራ መጠን በጉዳዩ በሚቀርበው ማስረጃና አእምሮ ያለው ሰው ውሉ ባለመፈጸሙ ይደርሳል ብሎ በሚገምተው አስተያየት ልክ ሊወሰን እንደሚችል፣የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1800 በተለይ ሲታይም ባለገንዘቡ ከጠየቀው ዝቅ ያለ ጉዳት ያገኘው መሆኑን ባለእዳው ያስረዳ እንደሆነ ኃላፊነቱ በዚሁ ልክ እንደሚሆንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1790(2) ድንጋጌም ኪሳራው ልኩ ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነት በሚለው ምዕራፍ በተጻፉት ድንጋጌዎች መሰረት እንደሚወሰን ደንግጓል፡፡ከውል ውጪ የኪሳራ ልክ ከሚወሰንባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ ርትዕ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 2102(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ይህ ድንጋጌ ኪሳራ የሚወሰነው ያለምንም መነሻ ሳይሆን የኪሳራውን ልክ በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ የሆነ እንደሆነ ዳኞቹ የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጎጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሳራውን ልክ በርትዕ እንደሚወስኑ ያሳያል፡፡ የሚከፈለው ካሳ መጠንና የጉዳቱ መፈፀም የሚያጠራጥር በሆነ ጊዜ ግን ማናቸውንም የጉዳት ካሳ እንዲከፈል ለማድረግ የማይቻል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102(2) ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሕንጻውን በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት በተገቢው ጊዜው አድሶ ባለማስረከቡ ተጠሪ በኪራይ ያገኝ የነበረው ገቢ መቋረጡ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡መጠኑም በተመለከተም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ስሌት መሰረት ሕንፃው በወር በብር 20,000.00 አደራሹ በብር 4000.00 ሊከራይ ይችል እንደነበር ጠቅሶ ለሃያ ሁለት ወራት ብር 528,000.00 ገቢ ማጣቱን ገልጾ የተከራከረ ሲሆን የበታች ፍርድ

ቤቶች አመልካች አዳራሹን ለአስር ወራት በብር 4000.00 ሺህ አከራይቶ ገቢ ማግኘቱ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ ብር 40,000.00 የኪራይ ገቢን ተጠሪ ከጠየቀው የኪራይ ገቢ መጠን ብር 528,000.00 ተቀናሽ አድርገዋል፡፡በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነው የብር 488,000.00 የሕንፃው የወር ኪራይ ገቢ መጠን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በግማሽ ዝቅ ያደረገው ህንጻውን ተጠሪ ለጳውሎስ ሚዲካል ኮሌጅ እያከራዪ ነው በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር ተጠሪ በከፊል አምኖታል በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ህንጻውን እንደለቀቀ ወዲያውኑ ተጠሪ ሕንፃውን ሳይታደስ ለኮሌጁ አከራይቶ ጥቅም ሲያገኝበት የነበረ መሆኑን ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ኮሌጁ ዘግይቶም ቢሆንም ህንፃው ባልታደሰበት ሁኔታ መከራየቱ ሕንጻው ሊከራይ ይችል የነበረ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው የሚል በመሆኑና ሕንፃው ኮሌጁ ከተከራየው በኋላ ስለመታደሱ ማስተባበያ ክርክር በአመልካች በኩል ያልቀረበበት በመሆኑ በተጠሪ ላይ ጉዳት አልደረሰበትም ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ይልቁንም ተጠሪ ሕንጻው ለኮሌጁ አከራይቶ ብር 60,000.00 በወር ገቢ ማግኘቱን አመልካች የሚያምነው ሐቅ መሆኑ ሲታይ ተጠሪ ሕንጻው ሳይታደስ ቆይቷል ለተባለበት ጊዜ በወር ብር 24,000.00 ገቢ ያስገኝ ነበር በማለት ክስ ማቅረቡ ጉዳዩን በርትዕ ለመወሰን መሰረት ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡በሌላ አገላለጽ ተጠሪ ህንጻው ባለመታደሱ ምክንያት ያጣውን የገቢ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1799(1) ድንጋጌ አስረድቶ እያለና አመልካች በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1800 ድንጋጌ መሰረት በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ዝቅ ያለ ነው በማለት ማስረጃ አቅርቦ ባላስረዳበት ሁኔታ ተጠሪ ህንፃው ሳይታደስም ማከራየት ይችል ነበር በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡በተጠሪ ላይ የደረሰ ጉዳት በማስረጃ ተረጋግጦ እያለና አመልካች ህንጻውን ለማሳደስ በውሉ ግዴታ ከመግባቱም በላይ ግዴታውን ለመወጣት በጨረታ አወጣጡ ሂደት ሁሉ ሲሳተፍ ቆይቶ የጨረታውን ውጤት ከአወቀ በኋላ ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ስላለመሆኑ በማስረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሕንፃው ሳይታደስም ቢሆን መከራየት ይችል ነበር የሚል እንድምታ ባለው ምክንያት ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የካሳውን መጠን በርትዕ መወሰኑ ግራ ቀኙ በጉዳት መጠኑ ላይ በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ከመወጣት አንጻር ታይቶ የተወሰነ ነው ሊባል ከሚችልና በውጤቱም አመልካችን የጠቀመ ነው ከሚባል በስተቀር ውሳኔው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1790(2)፣1799፣1800፣1802 እና 2102 ድንጋጌዎችን የጣሰ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 97396 ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 65129 መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ/ም ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ለህንፃው ማሳደሻ የተጠቀየውን ገንዘብ ብር 302,573.25(ሶስት መቶ ሁለት ሺ አምስት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም)፣ተጠሪ ያጣውን የኪራይ ገቢ ብር 244,000.00(ሁለት መቶ አርባ አራት ሺህ ብር) እንዲከፍል፣ወጪና ኪሳራ በቁርጥ ብር 2000.00(ሁለት ሺህ) እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሮ/ዛ**

የሰ/መ/ቁ. 83674

ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ እቴነሽ ካሳ - ጠበቃ አስቴር ዓለማሁ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሀጂ ጀማል ይማም - ጠበቃ ተሰማ ዘርፉ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውልን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ ክስ ይዘትም፡- ከአመልካች ጋር ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም በተጻፈ የሽያጭ ውል በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ቁጥሩ 3798 የሆነው ቤት በብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺ.ህ) ከአመልካች በመግዛት በእለቱ ብር 55,000.00 አመልካች ከተጠሪ ተቀብለው ቤቱን ማስረከባቸውን፣ ቀሪውን ብር 145,000.00 (አንድ መቶ አርባ አምስት ሺ. ብር) በገዥ ስም ካርታ አስርተው ለአመልካች ካስረከቡ ከአንድ ዓመት በኂላ ሊከፍሉ መስማማታቸውና በስምምነቱ መሰረት አመልካች ካርታውን አሰርተው ለማስረከብ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ዘርዝረው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ካርታውን እንዲያስረክቡና ውሉን ለማፍረስ በመሞከራቸውም ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺ.ህ) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኗ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል በባዶ ቦታ እንጂ በመኖሪያ ቤት ያልተደረገ ሕገወጥ መሆኑና በእለቱም ብር 5000.00 (አምስት ሺ.) እንጂ ብር 55,000.00 (ሃምሳ አምስት ሺ.) ያለመቀበላቸውን ጠቅሰው ብር 5000.00 ከፍለው ሌላው የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኂላ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ስምምነት በመኖሪያ ቤት ሳይሆን በባዶ ቦታ የተደረገ ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡንና ስምምነቱም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40(3) ድንጋጌን የሚጻረር መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የተጠሪን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰው ምስክሮችን መስማቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005 ድንጋጌን የሚጥስ መሆኑን በመጥቀስ በሰነዱ ላይ የተሸጠው



www.chilot.me

መኖሪያ ቤት እንጂ ባዶ ቦታ ያለመሆኑ ተረጋገጧል በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔን በመሻር የአሁኗ አመልካች በውሉ በገቡት ግዴታ መሰረት ሊፈጽሙ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላና እስከቦታው ድረስ በመሄድ ጉዳዩን በማጣራት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የሸጡት መኖሪያ ቤት እንጂ ባዶ ቦታ መሆኑን ሊያረጋግጡ አልቻሉም የሚል ምክንያት ይዞ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል በባዶ ቦታ ስለመሆኑ የሰነዱ ይዘት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ቁጥሩ 3798 የሆነውን ቤትና ቦታውን እንዲረከቡ የተሠጠው ውሳኔ አመልካች በሕጉ አግባብ ያገኙቱን 647 ካ.ሜትር ሁሉ አጠቃልሎ እንዲወሰድ የሚያደርግ እንዲሁም ሽያጩ በመኖሪያ ቤት አልተደረገም እንጂ ተደርጓል እንኳ ቢባል አመልካች መሐይም በመሆናቸውም በሕግ ፊት የማያስገድዳቸው ሁኖ እያለ በበታች ፍርድ ቤቶች መታለፉ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርመሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ በሰጡት መልስ አመልካች መሓይም ነኝ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳና ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ መሆኑን እንዲሁም ጉዳዩ ይግባኙን በሰማው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚገባ ተጣርቶ የተወሰነ መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል ፡፡እንደመረመረውም ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ስምምነት አመልካችን በሕግ ፊት የማስገደድ ሃይል አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ተፃፈ በተባለውና በ200 ካ.ሜትር ስፋት ቦታ ላይ የሰፈረው የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል አፈፃጸም መሰረት አድርገው መሆኑን፣ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል በውልና ማስረጃ ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ አመልካች መሓይም ሁነው ያደረጉት መሆኑና በሰነዱ ላይ ለአመልካች ተሰጠ የተባለው የቤት ስፋትና የገንዘብ መጠን በውሉ ላይ በተገለፀው አኳኋን ያለመሆኑን በምስክሮች ቃል የተረጋገጠው የተለያየ መሆኑን፤አመልካች በቦታው ላይ ቁጥር 3798 ተብሎ የተጠቀሰው ቤት የሰፈረው በ200 ካ.ሜትር ብቻ ሳይሆን በ647 ካ/ሜትር መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ ተጠሪ ግን በዚህ ረገድ ግልጽ መከራከሪያ ያላቀረቡ መሆኑን፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዳኞች እስከ አከራካሪው ቦታ ድረሰ ሂደው ተሸጠ የተባለው ባዶ ቦታ መሆኑን አመልካች ሊያሳዩ ያልቻሉ መሆኑንና ይልቁንም መኖሪያ ቤት የሸጡ መሆኑን ማስተባበያ ሊያቀርቡ አልቻሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱ መሆኑን ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ ክስ ያቀረቡት እንደውሉ እንዲፈጸምላቸው ሲሆን አመልካች ደግሞ ውሉ የቤት ሽያጭ ውል ያለመሆኑንና ሕጋዊ ያለመሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ አመልካች መሓይም ነኝ በማለት ስለ ውሉ ሕጋዊነት የሚያቀርቡት ክርክር በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ነው ከማለት ውጪ ሌላ ማስተባበያ

ክርክር ያላቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በዚህ ረገድ መከራከሪያ ነጥብ አንስተው የተከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የሽያጭ ሰነዱም በማስረጃነት የቀረበበትና የመኖሪየ ቤት ሽያጭ የለም በማለት የተከራከሩበት ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ይቻል ዘንድ የሰነዱን ምንነት መለየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም የተፈረመው ሰነድ ርእሱ የ "**መኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት** " የሚል ሲሆን የገዢና ሻጭ እንዲሁም የምስክሮች ፊርማ የያዘ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ወደ ይዘቱም ሲገባ ሻጭ ተብለው የተጠቀሱት የአሁኗ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 ክልል ወስጥ ቁጥሩ 3798 የሆነውን፣የቦታው ስፋት 200 ካ/ሜትር ሁኖ በካርታ ቁጥር ቦሌ/10/02/93-4208/22572/01 የሆነውን በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘወን የመኖሪያ ቤታቸውን ለአሁኑ ተጠሪ በብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺ.ህ) ሸጠው ብር 55,000.00 ሌላ ደረሰኝ ሳያስፈልጋቸው በስምምነቱ እለት የተቀበሉና ቤቱን ያስረክቡ መሆኑን፣የመጨረሻውን ክፍያ ደግሞ ገዥ በሚፈልጉበት ቦታ ላይ በገዥ ስም ካርታ ሻጭ ከሚመለከተው ክፍል በስማቸው አሰርተው ካስረከቧቸው ከአንድ አመት በኂላ ብር 145,000.00(አንድ መቶ አርባ አምስት ሺ.)አጠቃልለው ሊከፍሏቸው መስማማታቸውን፣ የሸጡትን ቤት በቆርቆሮ አጥር አጥረው፣በር ገጥመው፣ውሃ፣መብራት፣ስልክ አስገብተው እንዲሁም ጊዜያዊ ሽንት ቤት ሰርተው ሊያስረክቧቸው መስማማታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪም በውሉ በሰነዱ በተገለጸው አኳኃን ክፍያውን የፈፀሙና ለመፈጸም የተስማሙ ሁነው ቤቱን የተረከቡ መሆኑን በመግለፅ መስማማታቸው በሰነዱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በሰነዱም ላይ ሁሉም ተዋዋዮችና ምስክሮች ፈርመውበታል፡፡

ከላይ እንደተገለፀውም አመልካች ለክርክራቸው መሰረት ከአደረጓቸው ነጥቦች አንዱ መሓይምነት ሲሆን ክርክሩ ስለመነሳቱ ግንዛቤ ከተወሰደ ጉዳዩ በፍ/ሕ/ቁ.1728/3/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚመለከት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1728(3) ድንጋጌ አንድ ስምምነት በጽሁፍ እንዲሆን ሕግ ሲያስገድድ ውሉ በጽሁፍ መሆንና ግዴታ ባለባቸው ሰዎች ሁሉና በሁለት ምስክሮች ተፈርሞ ሊረጋገጥ እንደሚገባ፤ማየት የተሳናቸው ወይም የመሐይማን ፊርማ የነሱ ለመሆኑ ውል አዋዋይ ወይም የፍርድ ፀሐፊ ወይም አንድ ዳኛ በስራው ላይ ሆነው ካላረጋገጧቸው እንደማያስገድዷቸው ከፍ/ሕ/ቁ. 1727 እና 1728/3/ መረዳት ይቻላል፡፡እንግዲህ ተዋዋዮች ንብረታቸውን አስመልክቶ ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት መብት ለማቋቋም፤ለመለወጥ፤ወይም ለማስቀረት በሚደረግ ስምምነት ሁለቱም ግዴታ የሚገቡበትን ነገር አውቀውትና ተገንዝበውት ነፃ ፈቃዳቸውን ሊሰጡ ስለሚገባ ማንበብና መፃፍ ለማይችሉ ወይም ማየት ለተሳናቸው ተዋዋዮች ህጉ ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ በመሆኑም በጽሁፍ የሰፈረውን ውል ገለልተኛ በሆኑ 3ኛ ወገኖች ፊት ካልፈረሙ በውሉ ሊገደዱ አይችሉም፡፡አመልካችና ተጠሪ በ30/05/2000 ዓ/ም አደረጉ የተባለው ስምምነት ደግሞ በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት እንዲደረግ ህጉ የሚያስገድደው ነው፡፡በመሆኑም አመልካች መሃይምነታቸውን ምክንያት በማድረግ የሽያጭ ውል ስምምነቱ በዳኛ ወይም በአዋዋይ ፊት አልተደረገም በሚል ምክንያት እንደማያስገድዳቸው ያቀርቡት ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶች መታለፉ የግራቀኙን የክርክር አቀራረብና የሰነዱን ይዘት ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰነዱ የመንደር ውል ሁኖ እያለ በሰነዱ የሠፈሩት ነጥቦች ሁሉ ደምዳሚ ናቸው በማለት ውሉ እንዲፈፀም መወሰኑም ሆነ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካች ውሉን አላስተባበሉም በማለት ውሉ እንዲፈጸም የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005፣ 1723 እና 1728(3) ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው

ውሳኔ ውጤቱ ሲታይ ግን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ከላይ በተጠቀሱት ህጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 103872 ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71988 ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 166591 ህዳር 20 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎቱ አመልካችና ተጠሪ ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ያደረጉት ስምምነት ሕጋዊ አይደለም ብሎ የሰጠው የውሳኔ ክፍል በተለወጠ ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 342 እና 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የፈረሙት ስምምነት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1728(3) መሰረት ያልተደረገ በመሆኑ አመልካችን በሕግ ፊት የማስገደድ ሓይል የለውም ብለናል፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ከተጠሪ ብር 5000.00(አምስት ሺ ብር) መቀበላቸውን ያልካዱ በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ(9%) ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል ብለናል፡፡እንዲሁም ተጠሪ ለአመልካች የከፈሉት ሌላ ገንዘብ ካለ በሕጉ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ል/ተ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 90862

ታህሳስ 14 ቀን 2006ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች- ወ/ሮ ተዋበች ኃይሌ ቀረቡ

ተጠሪ- ወ/ሮ አያንቱ በዬቻ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በሽያጭ ምክንያት ተይዞ በቆየው ይዞታ ላይ ለተሰራ ቤት የወጣው ወጪ /ገንዘብ/ ይተካልኝ የሚል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኗ ተጠሪ እና በአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ላይ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አቶ በዬቻ ሆርዶፋ ሕዳር 10 ቀን 1992 ዓ/ም በተጻፈ የብድር ውል ነሐሴ 30 ቀን 1992 ዓ/ም የሚመለሰውን ብር 10,000.00 (አስር ሺ ብር) ተበድረው መውሰዳቸውን፣ይህንኑ ገንዘብ በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ካልመለሱ ደግሞ በአለምገና ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና በ147 ካ/ሜትር የቦታ ስፋት ላይ የሠፈረውን ባለአስራ ስድስት ሉክ/ዚንጎ/ ቆርቆሮ ፣በመያዣነት መስጠታቸውንና ስምም ለማዞር ግዴታ ገብተው የነበሩ መሆኑን፣በዚህ የውል ስምምነት መሰረት ግዴታቸውን እንዲወጡም በመ/ቁጥር 07334 በሆነው ክስ አቅርበው አቶ በዬቻ ወርዶፋ የውል ግዴታቸውን አምነው መልስ በሰጡበት ሁኔታ የአሁኗ ተጠሪ በብድር ገንዘቡ ምክንያት ለመያዣነት የተሠጠው ቤት የአቶ በዬቻ ወርዶፋ የግል ቤት ሳይሆን ከሟች እናታቸው ከወ/ሮ ጌጤ በዳኔ ጋር በጋብቻ የተፈራ የጋራ ንብረት በመሆኑ ስምምነቱ ሕጋዊ አይደለም በሚል ምክንያት ወደ ክርክሩ ገብተው ክርክሩ ከተካሄደ በኋላ በቤቱ ላይ የተደረገው ስምምነት ሕጋዊ አይደለም ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት ቢሆንም ይህንኑ ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት አመልካች በብድር ስምምነቱ መነሻ ያወጡትን ወጪ የመጠየቅ መብታቸውን የጠበቀላቸው መሆኑን፣አመልካች ለአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ከብድር ገንዘቡ በተጨማሪ ብር 20,800.00(ሃያ ሺ ስምንት መቶ ብር) በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት ሊለቁላቸው በአገር ሽማግሌ ፊት ተስማምተው የሰጡ ቢሆንም ይህ ስምምነትም በአሁኗ ተጠሪ ተቀዋሚነት በወራሽነታቸው ድርሻ ላይ ስምምነታቸውን ያልሰጡበት ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገ መሆኑን፣በቦታው ላይ የሰሩት ባለሰባ ስምንት ሉክ/ዚንጎ/ቆርቆሮ መኖሪያ ቤትም ግምቱ ብር 88,330.00(ሰማንያ ስምንት ሺ ሶስት መቶ ሰላሳ ብር)መሆኑን ጠቅሰው በድምሩ ብር109,130.00(አንድ መቶ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ብር) ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም አመልካች ውል የፈፀሙት ከአቶ በዬቻ ጋር መሆኑን፣ውሉም ፈርሶ ወደ ነበሩበት ይመለሱ ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ ውጤቱን በተመለከተ ክስ ማቅረብ የሚችሉት ውሉን ከተዋዋሉት ሰው ጋር መሆኑን፣በቦታው

ላይ የተሰራ ቤት ካለመኖሩም በላይ ቤት እንዲሰሩበት ስምምነት የሌለ መሆኑን፣ከባለይዞታው ፈቃድ ውጪ ለተሰራ ቤት የሚጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት ያለመኖሩንና የግንባታ ወጪ መጠኑም በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አቶ በዬቻ ወርዶፋ በበኩላቸው ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ማለቁንና በአፈጻጸም ሂደት ላይ እንደሚገኝ እንዲሁም በቦታው ላይ የተሰራ ቤት ያለመኖሩን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም  የቤቱን ግምትም በተገቢው ባለሙያ እንዲገመት ከአደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርምር ተጠሪንና አቶ በዬቻን ለክሱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን የኃላፊነት መጠኑን በተመለከተ ግን አቶ በዬቻ ከብድሩ በኋላ በሽማግሌዎች ፊት የወሰዱትን ብር 20,800.00 እና የቤቱን ግምት ግማሽ ብር 41,507.87(አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) በድምሩ ብር 62,307.87(ስልሳ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ሰባት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ የቤቱን ግምት ግማሽ ብር 41,507.87(አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ወጪና ኪሳራን በተመለተከም ብር 600.00 በቁርጥ፣የዳኝነት ብር 3,487.95 ተጠሪና አቶ በዬቻ ወርዶፋ ለአመልካች እንዲተኩላቸው በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው አመልካች ጋር እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ አመልካች ከባዬቻ ሆርዶፋ ጋር ባደረጉት ውል የወጣውን ወጪ የሚተኩበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ሲል ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠውን የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ የክሱ ምክንያት የሆነውን ጠቅላላ ገንዘብ ብር 103,815.75(አንድ መቶ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ አምስት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም) አቶ በዬቻ ሆርዶፋ ለአመልካች ሊተኩላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተተ የለበትም ተብሎ ፀንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በቦታው ላይ በተሰራው አዲስ ቤት የግማሽ ባለመብት ሁነው እያለ የቤቱን ግምት ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ከአላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ፡- ተጠሪ የአከራካሪውን ቤት ግምት ግማሽ ለአመልካች ለመክፈል ይገደዳሉ ወይስ አይገደዱም የሚለው ነጥብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪና በአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ላይ ክስ የመሠረቱት አቶ በዬቻ ሆርዶፋ ለገንዘብ ብድር በዋስትና ውል አሳልፈው በሰጧቸው ቦታ ላይ አዲስ ቤት ሰርተው ቤትና ይዞታውን በመያዝ በመጠቀም ላይ እያሉ ይሄው የመያዣ ውል ሕጋዊ አይደለም፣ሊፀና አይገባም የሚል ክርክር በተጠሪ በኩል ቀርቦ ውሉ ሊፈርስ እንደሚገባና ይፈርሣል ከተባለም ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ተብሎ በመ/ቁጥር 07334 በስር ፍርድ ቤት ከተወሰነ በኋላ ለአሁኑ የሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ መቅረቡን፣በዚህ ክስም አመልካች ዳኝነት የጠየቁት ለአዲስ ግንባታ ያወጡት ወጪ አቶ በዬቻ ሆርዶፋና ተጠሪ እንዲከፍሉ

ይወሰንላቸው ዘንድ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪም የመያዣ ውሉ የተደረገው ከአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ጋር በመሆኑ ተጠሪን የሚያስጠይቅበት ህጋዊ ምክንያት ያለመኖሩንና ከባለይዞታው እውቅናና ፈቃድ ውጪ ለተሰራ ግንባታ ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ አግባብ ያለመኖሩን ጠቅሰው ውሉ  በተጠሪ ላይ ተጠያቂነት የሚያስከትል አይደለም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአመልካችና በአቶ በዬቻ ሆርዶፋ መካከል የተደረገው የመያዣ ስምምነት በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የተደረገ ነው ተብሎ ሕጋዊ የሆነ የቤት መያዣ ውል እንደሌለ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተረጋገጠ ሲሆን ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ሲወሰንም አመልካች አለኝ የሚሉትን መብት በክስ ማስጠበቅ የሚችሉ መሆኑ ተገልጾ መወሰኑን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ያቀረቡትም የቤት መያዣ ውል ሕጋዊ አይደለም፤ ፈራሽ ነው፣ ቤቱን ለተጠሪና ለአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ ሲሆን ተጠሪ በይዞታው ላይ በአመልካች ገንዘብ የተሰራ አዲስ ግንባታ መኖሩን በተመለከተ ያቀረቡት የማስተባበያ ክርክር በማስረጃ ያልተደገፈ ሁኖ በመገኘቱ በስር ፍርደ ቤት ውድቅ የሆነ ሲሆን የበላይ ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ የተለዬ ድምዳሜ ላይ አልደረሱም፡፡አመልካች አዲስ ግንባታ መኖሩን ጠቅሰው ይህንኑ ለማስረዳት የቆጠሩት ማስረጃ በስር ፍ/ቤት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን የቤቱ ግምትም በሚመለከተው አካል ተገምቶ ብር 83,015.75 ነው ተብሎ መረጋገጡን የስር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያሣያል፡፡ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተጠሪን የተሰራውን ቤት የግንባታ ወጪ ግማሹን ተጠሪ ሊጠየቁ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ለመያዣ ውሉ ስምምነት ምክንያት የሆኑት ተጠሪ ሳይሆኑ አቶ በዬቻ ሆርዶፋ ናቸው በሚል ምክንያት ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ የተመለከቱት ነጥቦች በስር ፍ/ቤት የተረጋገጡ ሲሆን ከላይ እንደተገለጸው ምንም እንኳን የመያዣ ውሉ የጋራ ባለንብረቶችን ስምምነት ሳያገኝ የተደረገ ነው ተብሎ ፈራሽ ቢሆንም ውሉ በመፍርሱ ወይም በመሰረዙ ምክንያት ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰው ንብረቱን ለውጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ 1818 ያመለክታል፡፡ ስለሆነም አመልካች ይዞታውንና ቤቱን እንዲለቁ ሲደረግ ቤቱንና ቦታውን እንዲረከቡ ዳኝነት ያገኙት ሰዎች በቦታው ላይ የሰፈረውን ቤት ግምት ሊከፍሉ የማይገባበት ምክንያት የለም፡፡ምክንያቱም አመልካች በቦታው ላይ አዲስ ቤት ሲገነቡ ተቃውሞ የቀረበባቸው መሆኑ በፍሬ ነገር ያልተረጋገጠ ሲሆን ይዞታውን ለመያዝም የቻሉት ሕጋዊ ውል አለኝ በሚል እምነት መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ይህ ድንጋጌ የወጪውን መመለስ በተመለከተ ያላግባብ ስለመበልፀግ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንደሚኖራቸውም ያስገነዝባል፡፡ ከውል መፍረስ ጋር ተያይዞ ለሚነሳ የወጪ ክርክር ወጪውን አውጣሁ የሚለው ወገን በሕጉ ያለው መፍትሔ ምን እንደሆነ ሕጉ ያስቀመጠው ሁኔታ ይህ ከሆነ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት አለኝ የሚሉት በሟች እናታቸው በወ/ሮ ጌጤ በዳኔ ድርሻ በመሆኑ እና አዲስ የተሰራውንም ቤት እንዲረከቡ መብት የተጠበቀላቸው ስለሆነ በአመልካች ጥሬ ገንዘብ የተሰራውን ቤት ሲወስዱ ገንዘቡን የማይመልሱበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1818 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚታይ ነው እንጂ ተጠሪን በውሉ ስምምነት ያልሰጡ መሆኑን ብቻ መሰረት አድርጎ የሚታይ አይደለም፡፡ ያላግባብ የመበልጸግ ጥያቄ የውል ግንኙነትን መሰረት በማድረግ የዳኝነት መፍትሔ የሚሰጥበት አለመሆኑ ግልጽ ሁኖ እያለ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን

ከተጠሪ የውሉ ተካፋይ ያለመሆን ጋር በማያያዝ የሰጡት ዳኝነት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1818 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 እና ተከታይ ቁጥሮች ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ባለገናዘበ መልኩ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም አመልካች በቤት መያዣ ውል ምክንያት በያዙት ይዞታ ላይ በራሳቸው ገንዘብ ለሰሩት ግንባታ ተጠሪ የቤቱን ግማሽ ድርሻ እንዲረከቡ ከተደረገ ቤቱ የተሰራበትን ወጪ ለአመልካች የማይተኩበት ህጋዊ ምክንያት ያለመኖሩን ከፍ/ሕ/ቁጥር 1818፣2162 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው በመሆኑ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 113645 የካቲት 06 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 147924 መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01302 ሐምሌ 22 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ አመልካች የሰሩትን ቤት ዋጋ ግምት ግማሽ ብር 41,507.87 (አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠቀሰው አግባብ ለክርክሩ ከወጡ ወጪዎች ጋር የመክፈል ግዴታ አለባቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 86847

ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፀጋዬ አማን ተወካይ ዘነበች አበራ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. አቶ መሐመድ ነጋሽ } ጠበቃ ሽምስ ከድር ቀረበ

2. ወ/ሮ ከድጃ ሚፍታህ

3. በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 8 አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ልማት ፅ/ቤት

ነ/ፈጅ አንዋር ሙስጠፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከመንግስት የንግድ ቤት ኪራይ ውል ጋር ተያይዞ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡በአመልካች የቀረበው የክስ አቤቱታ ይዘትም በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ቁጥሩ 4-078/879/ የሆነውን ንግድ ቤት ከወረዳው በሕጉ አግባብ ተከራይተው እና የንግድ ፈቃድ በማውጣትና የዳግም የንግድ ምዝገባ አካሂደው በመነገድ ላይ እያሉ ያለባቸውን የስራ ጫና ለማቃለል ሲሉ ከአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ የስራ ውል በማድረግ ለተጠሪዎቹ ደመወዝ እየከፈሉ በቤቱ እየሰሩበት እያለ ተጠሪዎች ወደ ወረዳው አስተዳደር በመሄድ ተቀጣሪዎች አይደለንም፣ተከራይተን ነው በማለት አስመዝገበው በመገኘታቸው አመልካች ከእነዚህ ተጠሪዎች ጋር የነበራቸውን የሥራ ቅጥር ከጥቅምት 25 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ያቋረጡ መሆኑን፣ከዚህ በኋላም ቤቱን እነዚህ ተጠሪዎች እንዲለቁ አመልካች ቢጠይቋቸውም ሊለቁ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን፣ቤቱንና ግምቱ ብር 15,000.00 የሆነውን አታክልት ይዘው እንደሚገኙ፣3ኛ ተጠሪም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ከንግድ ቤቱ እንዲያስለቀቅላቸው ቢጠየቅም በመመሪያ ቁጥር 3/2004 እና 4/2004 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሊፈጽም ያልቻለ መሆኑን በመዘርዘር ቤቱና አታክልቱ እንዲለቀቅላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡



www.chilot.me

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቀርበው በሰጡት መልስም ከአመልካች ቤቱን በብር 18,000.00 ወርሃዊ ኪራይ መከራየታቸውን፣የስራ ቅጥር ውል የሌላቸውና የተከራይ አከራይ መመሪያ ሲወጣ አመልካች ፈርተው ተጠሪዎችን ፍጹም በሆነ የሞራል መገደድ ያስፈረሙ መሆኑንና ቅጥሩም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ስለ ስራ ቅጥር ውል ፎርም የሚደነግገውን ፎርማሊቲ የማያሟላ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ክሱ እንደማይመለከተውና አመልካች ቤቱን ያለአከራይ ፈቃድ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው መገኘታቸው በሚመለከተው ኮሚቴ ተጣርቶና ተረጋግጦ በመመሪያው መሰረት ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ኪራዩ መደረጉን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ወ/ሮ ዘነበች አበራ የንግድ ድርጅቱን በሕጉ አግባብ የገዙትና ስመ ሃብቱ እንዲዞርላቸው ሊወሰን እንደሚገባ ጠቅሰው ማመልከቻ በማቅረባቸው ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን በመስማት ጉዳዩን በመመርመር በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል በመመሪያ ቁጥር 3/2004 እና ቁጥር 4/2004 መሰረት የተደረገ ነው፣የቅጥር ውሉ አሳማኝነት የለውም የሚል ምክንያት ይዞ 3ኛ ተጠሪ ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረገው ውል ተቋርጦ የአመልካች ተከራይነት መብት ሊረጋገጥ አይገባም፤1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቤቱንና አታክልቱን ለቀው ለአሁኑ አመልካች ሊያስረክቡ አይገባም፣ እንዲሁም የጣልቃ ገቧ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካችና ወ/ሮ ዘነበች አበራ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለየብቻቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዛግብቱን አንድ ላይ አጣምሮ በመመርመር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ተቀጣሪ ሰራተኛ መሆናቸው ተረጋግጧል የሚል ምክንያት ይዞ በእነዚህ ተጠሪዎችና በአሁኑ አመልካች መካከል የኪራይ ውል የለም፣ወ/ሮ ዘነበች አበራ የንግድ መደብሩን የገዙት ስለመሆኑ ያላስመዘገቡ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም የሚሉትን ምክንያቶችን ይዞ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል በወ/ሮ ዘነበች አበራ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ግን ከአመልካች ጋር ያላቸው ግንኙነት የቅጥር ውል ነው በማለት 3ኛ ተጠሪ ከአሁኑ አመልካች ጋር ያለውን ውል ማቋረጡ ያላግባብ ነው ብሎ ደምድሟል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ይህን ውሣኔ በከፊል በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማ አስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ  የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በድምፅ ብልጫ በመሻር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት የወሰነ ሲሆን ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም አመልካችንና ተጠሪዎችን በድጋሚ አከራክሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቷል፡፡ከዚህ በኋላ ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት የአሁኑ አመልካች ሲሆኑ ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱም በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እና በአመልካች መካከል የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ስለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት በሚገባ ተረጋግጦ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቀድሞ የሻረውን ውሳኔ ጉዳዩ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ሲመለስለት ያለምንም ምክንያትና ትችት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማፅናቱ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ሰበር

ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የሰበር ፅሑፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባው ነጥብ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የከተማው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአሁኑ አመልካች እና ወ/ሮ ዘነበች አበራ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት በመ/ቁጥር 18210 እና 18209 በሆኑት ላይ ይግባኙን አቅርበውለት እነዚህን መዛግብት አጣምሮ በመመርመር ነሐሴ 03 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04905 በሆነው በ07/10/2004 ዓ/ም የሠጠውን ውሳኔ የሻረ ቢሆንም የአሁኑ ተጠሪዎች ጉዳዩን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ሰበር ሰሚ ችሎቱ በጉዳዩ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለመታየቱን ደምድሞ የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሮ ጭብጡን ለይቶ ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከመለሰለት በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመ/ቁጥር 18210 በድጋሚ ተመልክቶ በመመርመር የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04905 ሰኔ 07 ቀን 2004 የሠጠውን ውሳኔ ጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት ያጸናው መሆኑን፣በዚህም ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የአመልካች ተቀጣሪ ሰራተኞች ሳይሆኑ ተከራይ መሆናቸውን የስር ፍርድ ቤት የያዘውን መደምደሚያ ሙሉ በሙሉ የተቀበለ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ የተከራዩትን የንግድ ቤት ያለአከራዩ ፈቃድ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያከራዩ ስለመሆናቸው ማስረጃዎችን የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር በመሆኑ አመልካች ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር ውጪ በመሆኑ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን ስር የማይወድቅ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በፍ/ሕ/ቁ/2957(1) ተከራይ የተከራየውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል ለ3ኛ ወገን ሊያከራይ የሚችል ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን ይህንኑ የማከራየት መብቱን ሊጠቀም የሚችለው ደግሞ በዚሁ ቁጥር በንዑስ ቁጥር ሁለት በተነገረው መሰረት አስቀድሞ ተከራዩ አሳቡን ለአከራዩ አስታውቆ አከራዩ በዚሁ ጉዳይ ላይ ሊኖረው የሚችለውን አቋም ካወቀ በኋላ መሆን እንዳለበት ህጉ በአስገዳጅ ሁኔታ አስቀምጧል፡፡በመሆኑም አመልካች አከራይ ከሆነው ከአሁን 3ኛ ተጠሪ ፈቃድ ሳያገኙ የንግድ ቤቱን ለ3ኛ ወገን ያከራዩት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2957 በንዑስ ቁጥር 2 የተቀመጠውን አስገዳጅ ሁኔታ የሚቃረን ነው፡፡

በመሆኑም አመልካች የተከራዩትን ቤት ከ3ኛ ተጠሪ የተሰጣቸው ፈቃድ ሳይኖር ለ3ኛ ወገን አከራይተው የተገኙት የፍ/ህ/ቁ 1731(1)፣2957(2) ድንጋጌዎችንና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት

ቢሮ በንግድ ቤቶችና ወደ ንግድ ቤት በተቀየሩ የመኖሪያ ቤቶች ላይ የተፈጠሩ ችግሮችን ለማስወገድ ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 3/2004 እና 4/2004 የሚጥስ ሆኖ በመገኘቱ የሥር ፍርድ ቤቶች 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል ሊቋረጥ አይገባም፤ ቤቱንና አታክልቱን ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 04905 በቀን 07/10/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/18210 በቀን 30/02/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ውሳኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 19016 በቀን 12/04/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የንግድ ቤትና አታክልክት ይለቀቅልኝ ጥያቄ በበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 86813

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች**:- የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድረጅት ነ/ፈጅ ታደሰ በቀለ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**: 1. ሰሚር መላኩ አልቀረበም

2. አቶ መላኩ በቀለ ቀረቡ

3. አቶ ንብረቱ ምትኩ ወኪል 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጎደለ ገንዘብን ከማስከፈል ክርክር ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት ቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ በአመልካች የቀረበው የክሱ ይዘትም በአመልካች ድርጅት ውስጥ 1ኛ ተጠሪ ፖስተኛ ሆኖ በሚሰራበት ጊዜ ግምቱ ብር 54,150 የሆነ ቨውቼር ካርድና ብር 6,338 የሆነ ቴምብር ቀረጥ በድምሩ ብር 61,088 የጎደለ ስለመሆኑ በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠበት መሆኑን ጠቅሶ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ሲቀጠሩ እያንዳንዳቸው ብር 30,000 ዋስ ስለሆኑ ሶስቱም ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነ ወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን 1ኛ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ የስራ ድርሻው ፖስተኛ ስለሆነ ጎደለ የተባለው ገንዘብ እሱን እንደማይመለከትና ተደርጓል የተባለው የኦዲት ስራም እሱ በሌለበት መሆኑን ጠቅሶ ለክሱ ኃላፊ ሊሆን እንደማይገባ በመከራከር መልሱን ሰጥቷል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ዋስትና የገቡት 1ኛ ተጠሪ ለ6 ወራት ብቻ በጊዜያዊ ቅጥር በፖስተኛነት ለተቀጠረበት ስራ ነው እንጂ ከዚያ በኋላ በ1ኛ ተጠሪና አመልካች መካከል በአዲስ መልክ የቅጥር ውሉ ለታደሰው ስራ አለመሆኑን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ማጉደሉ ተረጋግጦበታል በማለት ገንዘቡን ለዳኝነት ከተከፈለው ገንዘብና ወጪና ኪሳራ ብር 1500 ጋር ለአመልካች



www.chilot.me

እንዲከፍል ሲወስንበት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ ግን እነዚህ ተጠሪዎች ዋስትና የገቡበት የ1ኛ ተጠሪ ጊዜያዊ ቅጥር ውል ጊዜው አልቆ ውሉ በአዲስ መልክ በሌላ ስራ መደብ ላይ በ1ኛ ተጠሪና አመልካች መካከል ሲደረግ የዋስትና ውሉ አብሮ ያልተደሰ በመሆኑ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡

በአመልካች ጠያቂነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመሰረዝ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ያፀና ሲሆን አሁን የቀረበው ሰበር አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሆኖ መሰረታዊ ይዘቱም የዋስትና ውሉ በጊዜ ያልተገደበና እንዲሁም የ1ኛ ተጠሪ ጊዚያዊ የስራ ቅጥር ውል መታደስ በራሱ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በመጀመሪያ ቅጥር ጊዜ የገቡትን የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሊያደርገው እንደማይችል እየታወቀ የበታች ፍ/ቤቶች 2ኛና 3ኛ ተጠሪዎችን ከኃላፊነት ውጭ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ በገቡት ዋስትና መጠን ከነወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የገቡት የዋስትና ውል በጊዜ አለመገደቡ እየታወቀ የስር ፍ/ቤት ዋሶቹ ለታደሰው 2ኛ ቅጥር ውል ዋስትና ግዴታ ስላልሰጡ ለእዳው ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት ከኃላፊነት በነጻ የማሰናበቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ በአመልካችና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የጽሑፍ ክርክር የተደረገ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ግን ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው 2ኛና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ የገቡበት የ1ኛ ተጠሪ የመጀመሪያ ጊዜያዊው የስራ ቅጥር ውል ጊዜው አልቆ በሌላ ሰራ ቅጥር ውል እንዲተካ ወይም  በአዲስ መልክ ተሻሽሎና የስራ መደቡም ከፖስተኛነት ወደ ክለርክነት እንዲቀየር በተደረገበት ጊዜ የዋስትና ውሉም አብሮ አለመታደሱ ወይም ዋሶቹ ፈቃዳቸውን አለመስጠታቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ለዋስትና ውል መሰረት የሆነው የመጀመሪያ ውል ተለውጦ በሌላ ውል በሚተካበት ጊዜ ዋስትና ግዴታው ለተለወጠው ቅጥር ውልም ቀጣይነት ኖሮት እንዲቆይ በግልጽ ካልተሰማሙ በስተቀር ወደ ተለወጠው ውል ሊተላለፍ እንደማይችል ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1827/1/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይም ተፈርሞ የነበረው የዋስትና ግዴታ ወደ ተለወጠውና 2ኛ ቅጥር ውል እንዲተላለፍ በግልጽ የተሰማሙ መሆናቸውን አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎቹ ተጠያቂነት የለባቸውም ተብለው በስር ፍ/ቤት ከኃላፊነት በነፃ መሰናበታቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በዚህ ጉዳይ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. የሰበር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 86187

ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ዳንኤል ዘሚካኤል - ጠበቆች ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ እና አቶ ፊሊጶስ አይናለም ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ቢሃሪ ባቡላል ሞዲ - ጠበቃ አቶ አምሃ በድሉ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የግራ ቀኙን የገንዘብ ጉዳይ ክርክር ሰምቶ በመወሰን ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች ከተከተሉት የጉዳዩ አካሄድ አንፃር ተመልክቶ የሠጡት ዳኝነት አግባብነትን ለማየት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ሲሆን ይዘቱም ተከሳሽ ለንግድ እንቅስቃሴው ባጋጠማቸው የገንዘብ እጥረት ምክንያት ለንግድ ሥራቸው የሚውል ገንዘብ እንዲያበድሯቸው ከሳሽን በጠየቋቸው መሰረት ከሳሽ የተከሳሽን ችግር በመመልከት ከ1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም ድረስ በተለያዩ ጊዜያት ከሳሽ ለተከሳሽ ላበደሯቸው ገንዘብ ተከሳሽ ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም የተፈረመ የገንዘብ ብድር መተማመኛ ውል መሰረት ብር 7,079,604.86 (ሰባት ሚሊዮን ሰባ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ አራት ብር ከሰማንያ ስድስት ሳንቲም) ይፈለግባቸዋል፡፡ ከታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም በኋላም በተከሳሽ ፈቃድ መሰረት በተለያዩ ጊዜያት ለተከሳሽ የንግድ ሥራ ያወጡላቸውን ወጭዎች ብር 946,270.06 (ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ብር ከስድስት ሳንቲም) በብድር የወሰዱ ለመሆኑም ተከሳሽ በኢሜይል ደብዳቤዎች በፅሁፍ አረጋግጠዋል፡፡ በአጠቃላይ ብር 8,025,874.92 (ስምንት ሚሊዮን ሃያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ አራት ብር ከ$^{92}/_{100}$ ሳንቲም) በዕዳ እንደሚፈለግባቸውና ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ ሲጠየቁ የ6 ወራት የመክፈያ ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ከዚህ ጊዜ በኋላ ገንዘቡን እንዲከፍሉ በተደጋጋሚ ቢጠየቁም እከፍላለሁ በማለት የተስፋ ቃል ከመስጠት በቀር ሊከፍሉ አልቻሉም፡፡ ስለሆነም የ6 ወሩ የዕዳ መክፈያ ከተጠናቀቀበት ከግንቦት 03 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ የወለድ ተመን ጋር በአንድ ጊዜ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም በሰጠው የመከላከያ መልስ ከከሳሽ ጋር የቆየ መልካም የጓደኝነትና የንግድ ግንኙነት አልነበረኝም ተከሳሽ የገንዘብ እጥረት ያጋጠማቸው መሆኑን ለከሳሽ ገልፀው አያውቁም፣ ከከሳሽ ጋር ያለኝ የአሰሪና ሰራተኛ እንዲሁም የወካይና ተወካይ ግንኙነት ያለን በመሆኑ ገንዘብ ሊያበድሩኝ የሚችሉበት ምክንያታዊ መነሻ የላቸውም፤ ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም በእኔ ተፈረመ የተባለውን ሰነድ አላውቀውም፡፡ ይህ ሰነድ ተፈረመ ከተባለበት ከ1999 ዓ/ም በፊትም ሆነ በኋላ ተከሳሽ በኢትዮጵያ ውስጥ አልኖሩም፤ ለአድዋ ዱቄት ፋብሪካ ሲባል ገባ የተባለውን ዕዳ ተከሳሽ በግለሰብ ደረጃ መተማመኛ ወይንም ማንኛውም ውል ሊያደርጉ ስለማይችሉ በሰነዱ ልገደድ አልችልም፡፡ ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም ተፃፈ በተባለው ሰነድ እንደተመለከተው ከሳሽ ለወደፊት ወጭ ያወጡ ከሆነ ተከሳሽ መተማመኛ ይሰጡ ዘንድ ብር 946,270.06 ወጭ ያደረጉ ስለመሆኑ የሚያመለክት ማስረጃም ያልቀረበ ስለሆነ የተጨማሪውም የገንዘብ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፡፡ ከብር 500.00 በላይ የሆነን የብድር ዕዳ ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን የቀረበ የሰነድ ማስረጃም አልቀረበም፡፡ የኢሜይል ሰነዶችንም በተመለከተ በተከሳሽ ያልተፃፈ ተከሳሽ የማያውቃቸው በሐሰት ተቀናብረው የተዘገጁ ናቸው ታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ተከሣሽ በከፍተኛ የአእምሮ ጭንቀት በሽታ ምክንያት በሆስፒታል ተኝተው የነበረ በመሆኑ ሰነዱን ሊፈርሙት አይችሉም፡፡ በአጠቃላይ በከሣሽ በኩል የቀረበው ክስና ማስረጃ የህግ መሠረት የለውም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ይህ የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ ፍ/ቤቱ የቃል ክርክር ካደረገና በተከሣሽ የተካደውን ታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ተፈረመ የተባለው ሰነድ ላይ የተቀመጠው ፊርማ በተከሣሽ የተፈረመ መሆኑን እና አለመሆኑን ለማረጋገጥ በፎረንሲክ ሳይንሳዊ ምርመራ ሁለት ጊዜ እንዲመረመር ካደረገና ውጤቱን ከተቀበለ በኋላ ግራ ቀኙን ያከራከራቸውን ነጥቦች ለይቶና ከግራ ቀኙ ማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ መርምሮ በመ/ቁ. 87441 ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት፡-

ከሣሽ ለቀረበው ክስ በማስረጃነት ያቀረበው ታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈው ሰነድ በተከሣሽ ያልተፈረመ ለመሆኑ ሁለት ጊዜ በተደረገው የፎረንስክ ምርመራ ውጤት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ሰነድ ተከሣሽ ለከሣሽ ብር 7,079,604.86 የተበደረ ለመሆኑ አያረጋግጥም ፡፡

በማስረጃነት የቀረበውም በኢሜል እና በፋክስ የመልእክት ልውውጥ የተደረገ በመሆኑ የብድሩ ስምምነት መኖሩን ያስረዳል በማለት የቀረቡት ሰነዶች ሲሆኑ በተከሣሽ የተደረጉ ሳይሆን ሰለሞን ቢሀሪ ሞዲ በተባለ ግለሰብ የተደረገ ስለመሆኑ ሰነዱ ያስረዳል ሰለሞን ቢሀሪ የተከሣሽ ልጅ ነው የሚባል ቢሆን እንኳ ስለተከሣሽ ሆኖ ገንዘብ ለመበደር የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ተከሣሽ እስካልሠጠ ድረስ ማስረጃው ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡ እንዲሁም የኢሜል የመልእክት ልውውጥ ሁልጊዜም በባለአድራሻው የሚደረግ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይደለም በዚህ ሁሉ ምክንያት ማስረጃው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

በተጨማሪነት ስለቀረበው የብር 946,270.06 የንግድ ሥራ ወጭ በሚመለከት ከሣሽ ይህንኑ ወጭ አወጣው የሚለው በውክልና ሠራው በሚለው ሥራ እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ የገንዘብ ወጭ እያደረገ የተከሣሽን ሥራ ለመሥራት የማያስችለው ግልጽ የሆነ የውክልና ሥልጣን አልተሰጠውም ከብር 500.00 በላይ ተሰጠ ለሚል የገንዘብ ብድርም በሰው ማስረጃ ማስረዳት የሚቻል አይደለም በመሆኑም ከሣሹ ለተከሣሹ የንግድ ሥራ ውል በብድር መልክ ለተከሣሽ ይህንኑ የንግድ ሥራ ወጭ ያደረገ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚሉት ምክንያት ራሱ

ከሣሽ ለብር 8,025,874.92 /ስምንት ሚሊዮን ሃያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ አራት ብር ከ ዘጠና ሁለት ሣንቲም/ የብድር ገንዘብ ክስ በማስረጃ አስደግፎ አላረገገጠም ተከሣሹ ከክሱ ነፃ ነው በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የቀረበውን የይግባኝ ጉዳይ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የመጨረሻ ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውም የአሁን አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ክርክር የመከራከሪያ ነጥቦች በመጥቀስ በቀረበው የሰበር አቤቱታ ምክንያት ሲሆን ተጠሪውም ይኸው በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት በሕግ አግባብ መሠረት ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት አመልካች በቀረበው የክርክር ነጥቦች አንፃር የጽሑፍ ክርክሩን አቅርቧል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን በጽሑፍ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠይቋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭር ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው አይደሉም? የሚለውን ጉዳይ ለማስረዳት ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ ያቀረቡትን የመከራከሪያ ነጥቦች ለእነዚሁ በበታች ፍ/ቤቶች ከተሰጡት ውሣኔዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአሁን አመልካች ላቀረበው ክስ በማስረጃነት ያቀረበውን ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተደረገውን የገንዘብ መተማመኛ ሰነድ ተከሣሹ በሰጠው መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 234/1/ሠ/ እንደተመለከተው በግልጽና በዝርዝር ክዶ የተከራከረ ለመሆኑ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከተሰጠው የፍርድ ሐተታ በግልጽ ተመልክቶ እያለ በዚሁ ሰነድ ላይ የተቀመጠውን ፊርማ ተከሣሹ በግልጽ አልካደውም በሚል የአመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ያቀረበው ክርክር የተከሣሽን የመልስ ይዘት ያገናዘበ አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2001 እና 2005 በተደነገገው መሰረት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ካቀረባቸው ማስረጃዎች መካከል ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በተከሣሽ ፊርማ ተረጋግጦ ተሰጥቷል የተባለው የሰነድ ማስረጃ አንዱ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2007 መሰረት ይህንኑ የሰነድ ማስረጃ እንደማያውቀው ፊርማውም የእርሱ አለመሆኑን ክዶ ተከራክሯል፡፡ ይህ ሰነድም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ አይደለም፡፡ ይህንኑ ዓይነት ሰነድ አስመልክቶ በማስረጃነት የቀረበበት ወገን ጽሑፉቱን ክዶ የተከራከረ ከሆነ ሰነዱ ወይም ፊርማው በካደው ወገን የተደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት የጽሕፈት ምርመራ እንዲደረግ ፍ/ቤቱ ማዘዝ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2008 ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሰረት የጽሕፈት ምርመራው ስራ እንዲከናወን ፍ/ቤቱ በክርክር ሂደት ለፌደራል ፖሊስ ፎረንሲክ ምርመራ ክፍል ትዕዛዝ ሰጥቶ በመጀመሪያው የምርመራ ውጤት በሰነድ የተቀመጠው ፊርማ በተከሣሽ የተደረገ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህ የምርመራ ውጤት ከታወቀ በኋላ የአሁን አመልካች የሰነድ ምርመራ ስራው በውጭ ሀገር እንዲደረግለት አመልክቶ ፍ/ቤቱ እንደ አመልካች ጥያቄ የሰነድ ምርመራው በውጭ ሀገር እንዲደረግ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ እንደገና በሌላ ጊዜ ይህ በውጭ ሀገር በኩል ሰነድ ተመርምሮ እንዲቀርብ በሚል ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ አግባብ አለመሆኑን ጠቅሶ ለማመሳከሪያነት የሚያገለግሉ ሰነዶች የሚመጡበትን ስፍራ እና እንዴት መምጣት እንዳለባቸው አመልካች ባመለከተው መሰረት በተጨማሪነት ከሚመጡት የፊርማ ምርመራ ማመሳከሪያ ሰነዶች

ጋር ተገናዝቦ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ በፎረንሲክ የምርመራ ክፍል ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በትዕዛዙም መሰረት የምርመራ ስራው ተጠናቆ ለሁለተኛ ጊዜ ፊርማው በተከሣሽ የተፈረመ አለመሆኑን የሚገልጽ ውጤት ቀርቧል፡፡

ከዚህ ከሰነድ ምርመራ ስራ ሂደት ጋር በተያያዘ አመልካች ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ አንዱ ፍ/ቤቱ ሰነዱ በውጭ ሀገር እንዲመረመር ካዘዘ በኋላ ዳኛ ሰለተለያየ ብቻ እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያው ችሎት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ መሻሩ ከፍ ያለ የስነ ስርአት ጉድለት የፈፀመበት ነው በዚህ ጉልህ ስህተት ምክንያት ፍትህ ተጓድሎብኛል የሚለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ይህ ክርክር ያስነሳውን ሰነድ በኢት/ያ የሚገኘው የፎረንሲክ ክፍል መርምሮ ትክክለኛ ውጤቱን ለመግለጽ ብቃት፣ ችሎታ እንደሌለው አልገለፀም፡፡ ይልቁንም ይህንኑ ዓይነት ሰነድ አስመልክቶ የምርመራ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የፌዴራል ፖሊስ ፎረንሲክ ክፍል ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን እንደ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰነድ ምርምራ ሥራ በሳይንሳዊ መንገድ እያከናወነ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሰረት በአገሪቱ በሚከናወነው የወንጀልም ሆነ የፍ/ብሔር የፍትህ አስተዳደር የፍርድ ስራ ሂደት ሙያዊ ግዴታውን የሚወጣ ክፍል ነው፡፡

በዚህም ማረጋገጫ መሰረት ፍ/ቤቶች በቀረበላቸው ጉዳይ እንደ ህጉ ፍትህ ያገናዘበ ዳኝነት ሲሰጡ ቆይተዋል ይህ ሆኖ እያለ አመልካች የመጀመሪያ የሰነድ ምርመራ ውጤት በፎረንሲክ ምርመራ ክፍል ተደርጎ ለአመልካች ተቃራኒ የሆነ ውጤት መቅረቡን ካረጋገጠ በኋላ ይኸው መርማሪ ክፍል የዚህኑ ሰነድ ምርመራ ስራ በአጥጋቢ ሁኔታ ለማከናወን ለምን እንደማይቻል ከብቃት ከችሎታ ወይም ከገለልተኛነት የመነጨ አሳማኝ ምክንያትና ክርክር ባልተጠቀሰበት ሁኔታ በደፈናው አመልካች እንዳቀረበው ጥያቄ ፍ/ቤቱ ሰነድ በውጭ ሀገር ተመርምሮ ይቅረብ ማለቱን ችሎቱ በሌላ ጊዜ ተገንዝቦ ቀደም ሲል በክርክር ሂደት የሰጠው ትዕዛዝ ሥነ-ሥርዓታዊ ጉድለት የፈፀመበት መሆኑን በተገነዘበ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 207 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ለማረም ስልጣኑ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው አከራክሪ ነጥብ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ አመልካች የክርክር ነጥብ ፍ/ቤቱ ስነ-ሥርዓታዊ ጉድለት ፈፅመዋል፤ ስህተት አድርጓል እንኳ ቢባል ይህንኑ ስህተት በሰበር ማረም የሚቻለው ስህተቱ መሠረታዊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑ በህገ- መንግስቱ አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 እና 22 ተደንግጓል፡፡

"መሠረታዊ" የሚለውም ህጋዊ ትርጉሙ ይኸው ስህተት ሳይታረም በመቅረቱ ምክንያት ውጤቱ ሊለወጥ ያልቻለ ወይም በተከራካሪው ወገን ፍትህ የማግኘት መብት ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን የሚያመለካት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ይህንኑ ጉዳይ እንደተመለከትነው ከላይ እንደተገለፀው አመልካቹ ድሮውንም ቢሆን በውጭ ሀገር ሰነዱ ይመርምርልኝ በማለት ያቀረቡት የጥያቄ አግባብነት በምክንያት በማስረጃ ሳይደገፍ የቀረበ በመሆኑ ይህም ጥያቄ የቀረበው የመጀመሪያው የምርምራ ውጤት ከታወቀ በኋላ ከመሆኑ ይህም ሆኖ እራሱ አመልካች ባመለከተው መሰረት የማመሳከሪያ ሰነዶች እንደገና ይምጡ ከተባለበት ስፍራ እና ሲመጡም በተከሳሹ እጅ ሳይሆን ሰነዱን ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው ገለልተኛ መንግስታዊ አካል አማካኝነት እንዲመጡ እና በድጋሚ የሰነድ ምርምራ እንዲደረግ ከታዘዙ በኋላ በቀረበ የማረጋገጫ ውጤት እንዲቀርብ የተደረገበት የጉዳይ አካሄድ እንደመሆኑ መጠን ይህ በስር ፍ/ቤት ተፈጸመ የተባለው ስነ ስርዓታዊ ጉድለት መሠረታዊ ስህተት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የሥር ፍ/ቤትም በዚሁ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት ብቻ ተመስርቶ ለጉዳዩ ፍርድ እንዲሰጥ ተቆጥሮ ሰበር ሰሚው ችሎት የፎረንሲክ የሰነድ ምርምራ ውጤት ስለማስረጃነቱ ያለውን የማስረዳት ብቃት ሙሉ በሙሉ እምነት የሚጣልበት አባሪ ማስረጃ ነው ወይስ አይደለም? በሚል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት የሰጠውን ትርጉም በማጣቀስ የቀረበው ክርክር ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም የሥር ፍ/ቤቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለጉዳዩ በሙግት የክርክር ደረጃ ጊዜ የአሁን አመልካች ላቀረበው ክስ በማስረጃነት ዘርዝሮ ያቀረባቸውን የሰነድ የሰው ማስረጃዎች ሁሉ አንድ በአንድ በማየት ማስረጃዎቹ ለጉዳዩ ያላቸውን አግባብነት እና የማሳመን የማስረዳት ብቃት እየመረመረ እና እየለካ ማስረጃዎችን መዝኖ ፍርድ የሰጠበት ጉዳይ ስለመሆኑ የፍርድ ይዘት አስረጂ ነው፡፡

በከሳሽ የተቆጠሩት ምስክሮች እንደ ክሱ ጭብጥ ያስረዳሉ የተባለበትን ነጥብ አስመልክቶ ተከሳሹ ሰነዱን በኢት/ያ ሀገር ሊፈርም የማይቻልበትን ምክንያት በመጥቀስ ላቀረበው ክርክር አመልካች ሰነዱ የተደረገው ኢት/ያ ውስጥ ሳይሆን ጅቡቲ ሀገር ነው የሚል ክርክር አላቀረበም ይልቁንም ፍ/ቤቱ እንደ ክሱ ጭብጥ ምስክሮች በማስረዳት ረገድ የሚሰጡትን ቃል ታማኝነት ከተከሳሹ ክርክር ጋር አጣቅሶ ለመለካት እንዲያስችለው ተከሳሹ ወደ ኢትዮጵያ ሀገር መቼ መቼ እንደገባ ሁሉ ለሚመለከተው በኢምግሬሽን ጽ/ቤት ማረጋገጫ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ ጅቡቲ ሀገር ነው የተደረገው እንዳይባልም ምስክሮች ወደ ጅቡቲ ሀገር ወጥተው አያወቁም ለሚለው የክርክር ነጥብም ማስተባበያ እንዳላቀርበ በስር ፍ/ቤቶች ፍርድ የተረጋገጠ የፍሬ ጉዳይ ነጥብ ነው፡፡ እንግዲህ የአሁን አመልካች በእያንዳንዱ የክርክር ደረጃ የተደረሰበትን ዳኝነታዊ ውጤት እየተከተለ በማፈራረቅ ከሚያቀርበው ክርክር አንፃር የሰው ማስረጃዎች ስለጉዳዩ ቃላቸውን ሳይሰጡ በመታለፋቸው የመደመጥ መብታችን ታልፎብናል የሚለው ክርክሩ ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

ስለጉዳዩ ያስረዳል በሚል የአሁን አመልካች ያቀረበውን የኢሜል እና ፋክስ መልዕክት ልውውጥ በማን የተደረገ ነው ይዘቱስ ለጉዳዩ ያለው አግባብነት ምንድን ነው፡፡ ክርክር ከቀረበበት የገንዘብ መጠን አንፃር በማስረጃነቱ ያለውን ተቀባይነት ሁሉ በመዳሰስ የማስረጃውን አግባብነት ተቀባይ እና የማስረጃነቱን ዋጋ አይቶና መዝኖ የሰጠውም ዳኝነት የማስረጃ አቀባበል ስርዓትን መሰረት ያደረገ ከመሆኑ በቀር ጉድለት ያለበት አይደለም፡፡

ከዚህም በቀር በተጨማሪ ማስረጃነት ቀርቦ እንዲታይልን ጠይቀን ጉዳዩን በተጨማሪ ማስረጃነት የማስረዳት ዕድሉን ተነፍገናል በማለት ያቀረቡትን ክርክር ይቅረብ ከተባለው የማስረጃ ስርአት አንፃር ሲታይም ሁለቱን ወገኖች ያለያያቸውን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን የማስረጃነት አግባብነትና ብቃት የሌለው መሆኑን ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍርዱ ምክንያት ሰጥቶ ያለፈው በመሆኑም በይግባኝ ሰሚነቱ ስልጣን ስር የወደቀውን በተከራካሪ ወገን የሚቀርብ ማስረጃ ለጭብጡ አመሰራረት ሆነው የተያዙትን ፍሬነገሮች በማስረዳት በኩል ማስረጃው በትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ያለውን ዋጋ ሁሉ በማየት የሰጠው ዳኝነት በመሆኑ የተጨማሪን ማስረጃን አቀባበል ስርዓት የጣሰ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከሁሉም በላይ ክርክር እንዳስነሳው ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በተከሣሽ ተደረገ እንደተባለው የፅሑፍ ማስረጃ ላይ ተከሣሹ ይህንኑ መተማመኛ ሰነድ የፈረመው ከሳሹ በተለያዩ ጊዜ ተከሣሹ ላጋጠመው የገንዘብ እጥረት ማቃለያ ሲባል "7,079,604.86 ያበደሩኝ መሆኑን ከሰነዶች ያረጋገጥኩ በመሆኑ ወደፊትም ለንግድ ስራዬ

ለሚያመጡልኝ ገንዘብ አባሪ ሰነዶች ኮፒ ተደግፎ ሲመጡልኝ የሚል ይዘት እንዳለው በግልፅ የተመለከተ በመሆኑ ከሳሹ የዚያን ማስረጃ መኖርና አለመኖር በስር ፍ/ቤት ሆነ በይግባኝ ሰሚው በትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ መስፈርት እነዚህን ደጋፊ ሰነዶች በሙሉ ወይም በከፊል በማቅረብ እንዲታይለት በማድረግ ከማስረጃው አግባትነትም ሆኖ የማስረጃ ብቃት አንፃር ጉዳዩ ታይቶ እንዲወሰን ማድረግ እየቻለ ይህ ዓይነት ሰነድ በየትኛውም ደረጃ ባለው ፍ/ቤት አለማቅረብና ለማቅረብ የአለመጠቀሱ ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ዳኝነት አግባብነት የሚያመለክት እንጂ ከጉዳዩ አካሄድ አኳያ የመከራከር መብቱ የተገደበ መሆኑን አያሳይም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 78275 ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ክሱ ለቀረበበት ገንዘብ የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ለመመለስ ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ ግዴታ የለበትም መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ



www.chilot.me

# የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ. 77983

መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** 1. አቶ እንድሪስ አደም - የቀረበ የለም

2. ወ/ሪት ዚነት እንዲሪስ
3. አቶ አንዋር እንድሪስ
4. አቶ ካሚል እንድሪስ
5. ወ/ሮ ብርቱካን በላይ

} ጠበቃ ወርቁ አበበ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አስናቀች ጥላሁን ጠበቃ ይልማ አቻሜ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በጋብቻ ውጤት በሆኑ ንብረቶች ላይ በአንደኛው ተጋቢ የተደረጉ የሽያጭ ውሎች የሚፈርሱበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት ከሣሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ናቸው፡፡ ተከሣሽ ደግሞ የአሁኑ አመልካቾች ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካቾች በመሰረቱት ክስ ከአሁኑ አንደኛ አመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው ቆይተው በመካከላቸው በተፈጠረው ያለመግባባት ጋብቻው እንዲፈርስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው የጋብቻ ውጤት የሆኑት ንብረቶችን ለማስከበር የፍርድ ቤት ትእዛዝ ይዘው ወደሚመለከታቸው አካላት ሲሄዱ ንብረቶቹ በሶስተኛ ወገኖች ስም የሚታወቁና በሽያጭ የተላለፉ መሆኑን የእግድ ትእዛዙን ይዘውላቸው የሄዱባቸው አካላት እንደገለፁላቸው ንብረቶቹን ባል የሆኑት አንደኛ አመልካች ከሕግ ውጪ ለብቻ ልጆቻቸው ከተጠሪ እውቅና ውጪ ያስተላለፉ መሆኑንና የተላለፉትን ንብረቶችንም፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ በአ/ክ/ከተማ በቀበሌ 19/20 የቤት ቁጥር 816 በሆነው ቤት በ1ኛ አመልካችና ከወ/ሮ ብርቱካን በላይ ጋር፣
- በአዲስ አበባ ከተማ በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 01/02 በሚገኘውና ቁጥሩ KH-B2 B104 በሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት ከወ/ሪት ዜኒት ኢድሪስ ጋር፣



www.chilot.me

- በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 2 የሚገኘውና ቁጥር GEB1 Co/04 ከሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት ከአቶ አንዋር ኢድሪስ ጋር፣
- የሰሌዳ ቁጥር 2-52682 በሆነችው የቤት መኪና ላይ ከወ/ሪት ዜኒት ኢድሪስ ጋር፣
- የሰሌዳ ቁጥር 3-46778 ኢት በሆነው የጭነት መኪና ከወ/ሮ ዜኒት እንድሪስ ጋር
- የሠሌዳ ቁጥር 2-42462 አ.አ በሆነችው የቤት መኪና ከካሜል ኤድሪስ ጋር እና

የሰሌዳ ቁጥር 3-06469 የሆነ ከባድ መኪና ከአቶ አንዋር ኢድሪስ ጋር በተደረጉት የማስመሰያ የሽያጭ ውል እንደተላለፉ በገዥነት የተመዘገቡት የትኞቹ የባል ልጆች እንደሆኑ ለይተው ስማቸውን ገልፀው በንብረቶቹ የተደረጉ ውሎች እንዲፈርሱና ንብረቶቹ በቀድሞው ሁኔታ እንዲመዘገቡ እና ውጪ ኪሣራ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መኖሩን አምነው ተፈጠረ የተባለውን ያለመግባባት ወይም ጠብ ግን እንደማያውቁትና ተጠሪ ጋብቻው እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ክስ መሥርተው ያሉ መሆኑን ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ንብረቶች በሽያጭ ውሉ ለሌሎች አመልካቾች ያስተላለፉት ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ወደ መጥፎ ሁኔታ ከመቀየሩ በፊት ከተጠሪ በቁጥር 5904/13/2000 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት መሆኑንና የሽያጭ ውሎቹ መደረጋቸውንም ተጠሪ ያውቁ እንደነበር ገልፀው የሽያጭ ውሎችም ሊፈርሱ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ 2ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ አመልካቾች በጋራ በሰጡት መልስም ለክርክሩ ምክንያት የሆኑነት ንብረቶችን ተጠሪ በወኪላቸው አንደኛ አመልካች አማካኝነት በሽያጭ ውሉ ላይ ፈቃዳቸውን የሰጡ በመሆኑ የተሻሻለውን የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 68 እና 69 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ክርክር ሊያደርጉባቸው እንደማይችሉ ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ 4ኛ አመልካች በበኩላቸው በግል የመከላከያ መልሣቸውን ያቀረቡ ሲሆን በአቀረቡት መልስም አመልካቹ ገዙ የተባለውን መኪና ከተጠሪ ሕጋዊ ወኪላቸው የአሁኑ አንደኛ አመልካች የገዙትና የሽያጭ ውሉ ገዢው የወኪሉ ልጅ በመሆናቸው ብቻ ሊፈርስ እንደማይገባ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ንብረቶቹ የጋብቻ ውጤት መሆናቸውና የአሁኑ አንደኛ አመልካች ከተጠሪ በተሰጣቸው ውክልና መነሻ ገቢና መተዳደሪያ ለሌላቸው ለአሁኑ አንደኛ አመልካች የብቻ ልጆች ለሆኑት ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ ተራ ቁጥር አምስት ድረስ ለተጠቀሱት አመልካቾች መሸጡ መረጋገጡንና አንደኛ አመልካች አንድ ወኪል በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ አክብረው ሽያጩን አከናውነዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ መገንዘቡና እንዲህ አይነት የወኪል ተግባር ደግሞ ሕጋዊ ያለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 2208፣ 2209 እና 2188 ድንጋጌዎች እንደሚያስረዱ በመጥቀስ በንብረቶቹ ላይ የተደረጉት ሽያጮች እንዲፈርሱና ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመላክቾች ቅር በመሰኘት የአሁኑ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱት በይ/መ/ቁጥር 70423 የአሁኗ 5ኛ አመልካች ደግሞ በይ/መ/ቁጥር 70623 ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ መዝገቦችን አጣምሮ ከተመለከተና ከመመርመረ በኂላ አከራካሪ ንብረቶችን አንደኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር ወደ አለመግባባት ከገቡ በኂላ መተዳደሪያ ለሌላቸው ተማሪ ለሆኑት አንዳንዶቹ ለአቅመ አዳም እንኳን ላልደረሱ ልጆቻቸው በአፋጣኝ የሸጡ መሆናቸውን መገንዘቡን በውሳኔ ላይ ከአሰፈረና ይህም አንደኛ አመልካች ንብረቶቹን ከቅን ልቦና ውጪ ለብቻቸው ለመጠቀም በማሰብ ያደረጉት ዘዴ መሆኑን ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ መሆኑን ጠቅሶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ተገቢ ነው ብሎ ሙሉ በሙሉ

አንፅንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አንደኛ አመልካችና ተጠሪ ወደ አሜሪካ ሀገር ለመሄድ ለመኖር በማሰብ በአደረጉት ስምምነት መሰረት ተጠሪ ከአመልካቹ ውክልና ሰጥተው ንብረቶቹን አመልካች በውክልና ስልጣናቸው መሸጣቸው የማይካድ ሀቅ ሆኖ እያለ ሐቁ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ በተገቢው የክርክር አመራርና ማስረጃ ሳይጣራ ንብረቶቹ ለአንደኛ አመልካች ልጆች በመሸጣቸው ምክንያት ብቻ የሽያጭ ውሎቹ እንዲፈርሱ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳይ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አንደኛ አመልካችን ተጠሪ ለረዥም አመታት በባልና ሚስት ሲኖሩ በሽያጭ ውሉ ተላለፉ የተባሉትን ንብረቶችን በጋራ ያፈሩ መሆኑን፣ በመካከላቸው በተፈጠረው ያለመግባባትም ተጠሪ የፍቺ ጥያቄ ለፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ እንዳለ ንብረቶችን ለማስከበር እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ንብረቶቹ ከፍቃዳቸው ውጪ መሸጣቸውን አውቀው ሽያጭ ውሎቹ እንዲፈርሱላቸው ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸውን፣ ንብረቶቹን ከአንደኛ አመልካች ገዙ የተባሉት የአሁኑ ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ አምስት ያሉት አመልካቾች ደግሞ የአሁኑ የብቻ ልጆች ሆነው የራሳቸው መተዳደሪያ የሌላቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ለአቅመ አዳም እንኳን ያልደረሱ መሆኑን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በውሳኔ ላይ መግለፁን፣ ንብረቶቹን የተጠሪ ባል የሆኑት የአሁኑ አመልካች ለልጆቻቸው ለመሸጥ ስልጣን ያገኙት ከተጠሪ ግንቦት 25 ቀን 2005 ዓ/ም በተሰጠው ስልጣን ቢሆንም ንብረቶቹ የተሸጡት ከተጠሪ ጋር ያለመግባባት ከተፈጠረ በኂላ በአፋጣኝ ስለመሆኑ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ማረጋገጡን ነው፡፡ አንደኛ አመልካች በዚህ የክርክር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩት ከተጠሪ ጋር አሜሪካን አገር ለመኖር በማሰብ ንብረቶቹ መሸጣቸውንም ተጠሪ ያውቁ እንደነበር ገልፀው ተከራክረው ከአመልካች ልጆች ውስጥ የራሳቸው ገቢና መተዳደሪያ ያላቸው ሁሉ እያሉ ይሔው ሳይጣራ ተገቢ ያልሆነ የክርክር አመራር በስር ፍ/ቤት ተከናውኖ ውሳኔ መሰጠቱ ሐቁ እንዳይወጣ ሆኗል፣ ተጠሪ ባሁኑ ጊዜ የሚኖሩት አሜሪካን አገር መሆኑም ከአመልካቹ ጋር የነበራቸውን የቀደመ ሐሳብ የሚያረጋግጥ ነው በሚል ሲሆን ሌሎች አመልካቾች ደግሞ ሽያጩ በተጠሪ እውቅና የተደረገ ሆኖ እያለ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ ያለግባብ ነው በሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ችሎት ሲሆን ንብረቶቹ አንደኛ አመልካችና የአሁኗ ተጠሪ በመካከላቸው ያለመግባባት ከተፈጠረ በኂላ በአፋጣኝ ለአሁኑ አንደኛ አመልካች ልጆች ለሆኑትና የራሳቸው መተዳደሪያ ገቢ ለሌላቸው ጭምር መሸጣቸው ከክርክሩ ሂደት መገንዘቡን በውሳኔ ላይ አስፍሯል፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍሬ ነገር ድምዳሜ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከደረሰበት ድምዳሜ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ

ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ የበታች ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ድምዳሜ የያዙት ጉዳይ የሚለወጥበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አንደኛ አመልካች ንብረቶቹን ከተጠሪ ጋር ያለመግባባት ከተፈጠረ በኂላ በአፋጣኝ መሸጣቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ ንብረቶቹን ሸጥኩ የሚሉበት ምክንያት አሜሪካን አገር ለመኖር ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ስምምነት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በማስረጃ እንዲነጥር ያለመደረጉ ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረታዊ ጠቀሜታ የሌለው ነው፡፡ በአንድ የፍትሃ ብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲነጥር የሚደረገውም በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣ 137፣ 138፣ 246፣ 247፣ 248፣ 256፣ እና ሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ማንኛውም የክርክር ነጥብ ሁልጊዜ በማስረጃ እንዲነጥር የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሆኖ ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩባቸውና ዳኝነት በሚሹ ነጥቦች ላይ ከሚሰማ በስተቀር በማንኛውም ፍሬ ነገር ላይ እንዲሰማ የግድ የሚል የማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን ደንብ የለም፡፡ ከሁሉም በላይ ማስረጃ እንዲሰማ የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን ማስረጃው የሚሰማበት ነጥብ ለይቶ የማስረጃውን አይነትና የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በመጥቀስና በእጁ ላይ ያለውን ማስረጃውም አያይዞ ማቅረብ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 223፣ 234፣ 137(3)፣ 145፣ 256 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም 1ኛ አመልካች በስር ፍ/ቤት የመከላከያ ማስረጃ ጥር 25 ቀን 2003 ዓ/ም ዘርዝረው ሲያቀርቡ በመልስ ማመልከቻው ውስጥ የዘረዘራቸው ፍሬ ነገሮችን የሚያውቁና የሚያስረዱ ሶስት የሰው ምስክሮችን ዘርዝረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ምስክሮቻቸው የተሰሙ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ የማያሳይ ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ንብረቶቹ የተሸጡበት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ወደ ያለመግባባቱ ከገቡ በኂላ በተፋጠነ ሁኔታ መሆኑ ከረጋገጡ አንፃር ሲታይ የአመልካች ምስክሮች ያለመሰማት መሠረታዊ የመሰማት መብትን አጣብቧል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አላኘነውም፡፡ ተጠሪ የውክልና ውሉን መሠረት አድርገው ክስ ያለመመስረታቸውም በክርክሩ ሂደት አመልካቾች በመከላከያነት ክርክር እስካቀረቡ ድረስ ፍ/ቤቱ ውክልናውን ተከትሎ የተፈፀመውን ተግባር ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ከመመርመርና ተገቢውን ዳኝነት ከመስጠት የሚያገደው አይደለም፡፡ ይልቁንም ውክልናው መኖሩን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን በመለየት ዳኝነት መስጠታቸውን የክርክሩ ሒደት የሚያሳይ በመሆኑ ተጠሪ ክስ ሲመሰርቱ ውክልናን ጠቅሰው ያለማቅረባቸው በክርክር አመራሩና ዳኝነት አሰጣጥ ውጤት ላይ መሠረታዊ የሕግ ግድፈት አስከትሏል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ሌላው አንደኛ አመልካች ንብረቶቹን ለብቻ ልጆቻቸው የሸጡ መሆኑን ሳይክዱ አንድ ተወካይ ሊወጣ የሚገባውን ሕጋዊ ግዴታ ተወጥተው ንብረቶቹን የሸጡ ስለመሆኑ ጠቋሚ ሊሆኑ የሚችሉትን የንብረቶቹን የገበያ ዋጋ ለንጽጽር እንኳን ጠቅሰው እሰከዚህ ሰበር ደረጃ በአቀረቡት ክርክር ያለመጥቀሳቸው ሲታይም የአመልካቾች የማስረጃ ያለመሰማት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል አስፈላጊ ፍሬ ነገር አልተሟላም ለማለት የማያስደፍር መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አንደኛ አመልካች ንብረቶቹ ተሸጡ በተባለባቸው ጊዜያት የተጠሪ ባልና ተወካይ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ተወካዩ ከወካዩ ጋር የሚያስተሳስረው ግንኙነት ውስጥ ጥብቅ የሆነ ቅን ልቦና ሊኖረው እንደሚገባ በፍትሐብሄር

ሕግ ቁጥር 2208(1) ስር ተደንግጓል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተወካዩ የተወካይነት ሥራውን የሚፈጽመው በተለይ የወካዩን ጥቅም ሊሰጥ በሚችልበት መንገድ ብቻ መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2209 (1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተወካዩ በውክልና ሥራው ላይ በሚገኝባቸው ጊዜዎች ሁሉ በውክልና በተሰጠው አደራ አንድ መልካም የቤተሰብ አባት ቤተሰቡን ለመጠበቅ እንደሚያደርገው ሁሉ በትጋትና በጥንቃቄ መጠበቅ ያለበት መሆኑን በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2211(1) ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ አንደኛ አመልካች ከላይ በጠቀስናቸው አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት ያልተወጡ መሆናቸውን ከዚህ በሚቃረን አኳኋንና የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2187(1) ባላገናዘበ መልኩ ለብቻ ልጆቻቸውና የራሳቸው የሆነ መተዳደሪያ ለሌላቸው ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ አምስት ለተጠቀሱት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለመግባባት ከተፈጠረ በኋላ በአፋጣኝ አከራካሪ ንብረቶችን መሸጣቸው ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመወሰን ሥልጣን ባላቸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ በሆነው ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ለአንደኛ አመልካች በውክልና ከተጠሪ የተሰጣቸውን አደራ በመጣስና ንብረቶቹን ከጋብቻ የጋራ ውጤት ከመሆን ለማሸሽ ክፉ ልቦና የፈፀሙት የንብረት ሽያጭ ስለመሆኑ ንብረቶቹ በአፋጣኝ መሸጣቸው የሚያስገነዝብ መሆኑን ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከአረጋገጠ ደግሞ የአንደኛ አመልካች ተግባር በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2188(1) ድንጋጌ መሠረት የጥቅም ግጭት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በተጠቀሱት ሕጋዊ ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99766 ግንቦት 01 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 70423፣70632 ታህሳስ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በአከራካሪ ንብረቶች የተደረጉ ውሎች እንዲፈርሱ፤ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>**

በዚህ ችሎት መጋቢት 21 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ ብልናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 81275

ሰኔ 5 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች:-** ወ/ሮ ዘምዘም ወንድሙ - ከጠበቃ አትሙት አሰፋ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ:-** አቶ አብዲሰቡር አብዱሰመድ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ተመሳሳይ የሆኑ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ክሶችን በአንድ ፍ/ቤት በመቅረባቸው የተነሳ አንደኛው ወገን ይህን ተገንዝቦ ጉዳዮች ተጣምረው እንዲታዩለት ለፍ/ቤቱ ባመለከተ ጊዜ ፍ/ቤቱ ሊፈፅመው የሚገባውን ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፤ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ የሆኑበትን የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺ) የብድር ገንዘብ ክርክር ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቂራ ምድብ ችሎት ተመልክቶ በኮ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ ላይ በቀን 25/06/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ላቀረቡት የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ) የገንዘብ ብድር ክስ መሰረት አድርገው የጠቀሱት በሁለቱም መካከል ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደርጓል የተባለውን የገንዘብ ብድር ውል ሲሆን በዚህ ውል ተበዳሪ ገንዘቡን እስከ መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ/ም ድረስ በመመለሱ በን/ስ/ላፍቶ ክ/ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኘውንና በቤት ቁጥር B6/14 የተመዘገበውን የኮንዶሚኒየም ቤት በመያዣነት አስይዘዋል፡፡ ይሁን እንጂ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ገንዘቡን አልከፈለም፡፡ ስለሆነም የብድር ገንዘቡን ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ህዳር 05 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የክስ ምክንያታቸውን ገልፀው ዳኝነት የጠየቁበት ሲሆን፤

የአሁን አመልካችም በተከሳሽነታቸው በዚህ የብድር ውል በተባለው ሰነድ ሊገደዱ የማይችሉበትን የፍሬ ነገርና የህግ ክርክር በመጥቀስ ዝርዝር መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች መስከረም 02 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ለዚሁ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቂራ ምድብ ችሎት በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ የኮ/ቁ 45441 የሆነውን መዝገብ አስከፍተው በኂላም መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ/ም የተሻሻለ ክስ እንዲቀርብ ተደርጎ የክርክሩ መሰማት በዚሁ ፍ/ቤት ቀጥሏል፡፡ የአሁን አመልካች በኮ/ቁ 45441 በሆነው መዝገብ ላይ ባቀረቡት ክስ የጠቀሱት ዝርዝር

ምክንያት የአሁን ተጠሪ ከላይ በአድራሻና በቁጥር የተጠቀሰውንና በዕዳ የደረሰኝን የኮንዶሚኒየም ቤት አስመልክቶ በማስላት ሐምሌ 12 ቀን 1998 ዓ/ም እና ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን የሽያጭ ውል፤ ሐምሌ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን የሥጦታ ውል እና ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) የብድር ውል ያስፈረመኝ ስለሆነና እነዚህም ውሎች በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል ለመያዝ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች አሟልቶ የተደረጉ ባለመሆኑ ሊፈርሱ ይገባል የሚል ነው፡፡

ለዚህም ክስ የአሁን ተጠሪ የፅሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱ የታለፈ ቢሆንም፤ ክርክር በሚሰማበት ዕለት ቀርቦ ከአሁን አመልካች ጋር ያደረጉት የብድር ስምምነት በህግ ፊት የፀና ነው የሚሉበትን ምክንያት በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡

እነዚህ ሁለት ክሶች በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ፍ/ቤት ቀርበው እየተሰሙ ባሉበት ጊዜ በአሁን አመልካች እነዚህ ተመሳሳይ ጭብጥ የሚያስነሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ተጣምረው ሊታዩ ይገባል በሚል በማመልከታቸው ፍ/ቤቱ በኮ/መ/ቁ 45441 በሆነው መዝገብ ላይ ተከሳሽ የነበሩትን የአሁን ተጠሪን ምስክሮች ዝርዝር ቃል ከተቀበለ በኋላ በቂራ ምድብ 1ኛ ፍ/ብ/ችሎት እየታዩ የሚገኘው የኮ/ቁ 37363 የሆነው መዝገብ ቀርቦ ከመ/ቁ 45441 ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ ሆኖም የኮ/መ/ቁ "37363" ተብሎ መፃፍ ሲገባው የመጨረሻዋ "3" የምትለው ቁጥር ተሰርዞና ተደልዞ "6" በሚል በመፃፉ ምክንያት እንደ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ይኸው መዝገብ እንዲጣመር አልተደረገም፡፡ በዚህም የተነሳ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ሁለቱንም ጉዳዮች ጐን ለጐን ሲያይ ከቆየ በኋላ በኮ/መ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪ ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገው የብድር ውል መሰረት ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ለአበዳሪ ለአሁን ተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት ሲወስን፤ በኮ/መ/ቁ 45441 በሆነው ጉዳይ ደግሞ ይኸው ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለው የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) የብድር ውል እና የመያዣ ውል በህግ ፊት የፀና ውል ሆኖ ባለማግኘቱ ፈራሽ ነው የሚለውንም ጭምር ያካተተ አስቀድሞ ከሰጠው ፍርድ ጋር በተቃራኒ አኳኋን ሰኔ 10 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡

በዚህ አኳኋን የተቃረነ ፍርድ መስጠቱን እንደተረዳ በኮ/መ/ቁ 45441 የሆነውን መዝገብ ከተዘጋ በኋላ እንደገና በማንቀሳቀስ ቀደም ሲል በክርክር ሂደት ተከስቶ የነበረውን የመዝገብ ቁጥር አፃፃፍ ስህተት ታርሞ ቁጥር "6" በሚል የተፃፈው የመዝገብ ቁጥር የመጨረሻ አኃዝ ቁጥር "3" በሚል ሊስተካከል ይገባል በማለት በሰጠው እርስ በእርሱ የተቃረነ ፍርድ ላይ አንዳችም ውጤት ሊያስከትል የማይችል ትዕዛዝ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ/ም እንደሰጠበትም ከሰጠው የትዕዛዝ ዳኝነት ግልባጭ ተረድተናል፡፡

የአሁን አመልካችም ተከሳሽ በነበሩበት በኮ/መ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ተመልክቶ በመ/ቁ 119226 በቀን 04/08/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ይኸው በኮ/መ/ቁ 37363 የተሰጠው ፍርድ በፍሬ ነገርም ሆነ በህግ ረገድ ጉድለት የተገኘበት አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት የሆነውም በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን የክርክር ነጥቦች በመጥቀስ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሲሆን የአሁን ተጠሪም ይኸው ፍርድ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው ሊፀና ይገባል በማለት ከእነምክንያቱ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

እንግዲህ የዚህ ጉዳይ መነሻና አመጣጡ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻና ምክንያት የሆነው ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ግራ ቀኙ አድርገውታል የተባለው የብድር ውል ስምምነት ህጋዊ ውጤትን ያስከትላል ወይስ አያስከትልም? የሚለውን አከራከሪ ነጥብ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የመሰረተ ህጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን ከማየታችን በፊት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 347(4) እና 182(3) እንደተደነገገው በቅድሚያ ከዚሁ ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ ከተባለው የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ) የብድር ውል እና የመያዣ ውል በመነሳት እነዚሁ ሁለት ተከራከሪ ወገኖች በከሳሽነትና በተከሳሽነት በመፈራረቅ አንድ ዓይነት የፍሬ ነገርና የህግ ክርክሩ ጭብጥ በሚያስነሳ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በአንድ ፍ/ቤት በተለያዩ ክሶች እየተከራከሩ የነበሩ መሆኑ ሲታወቅ በስር ፍ/ቤቶች ሊከተሉት የሚገባው ስርዓት ምን ሊሆን ይገባ ነበረ? የሚለው ጭብጥ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንደዚህ ባለ ተመሳሳይ ጉዳይ ተመሳሳይ የሆኑ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ፍ/ቤት በተለያዩ ክሶች መከራከራቸው ሲታወቅ ጉዳዩን በመጀመሪያም ሆነ በይግባኝ ደረጃ የተመለከቱት ፍ/ቤቶች እንዚህ ሁለት ጉዳዮች ተጣምረው እንዲታዩ ካላደረጉ በቀር በአንድ ጉዳይ ላይ በተለያዩ አኳኋን ፍርድ ሊሰጥ ስለሚችልና በተመሳሳይ ተከራከሪ ወገኖች በሚከራከሩበት ተመሳሳይ ጉዳይ አንድ ፍ/ቤት በተለያዩ ክስ ተቀብሎ በማስተናገዱ ምክንያት የተለያየ ፍርድ መስጠቱ በየትኛውም መለኪያ ቢሆን ፍትሐዊ እና ህጋዊ ካለመሆኑም በላይ በዚህ አኳኋን የተሰጡትንም ፍርዶች ለማስፈፀም አዳጋች ሆኖ ይገኛል፡፡

ይህንንም በመገንዘብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ እንደዚህ ያለ ሁኔታ እንዳያጋጥም ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ ይኸውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8(1) ላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ምላሽ የሚያስፈልገውም የሥረ - ነገር ጭብጥና ተከራከሪ ወገኖችም ተመሳሳይ ሆነው ጉዳዩ በቅድሚያ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ እያለ ሌላው ፍ/ቤት ይህንኑ አንድ የሆነውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመከራከር አይችልም በማለት ተመሳሳይ የሆነው ጉዳይ በአንድ ፍ/ቤትም ሆነ በሌላ ፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ክርክሩ ሊቀጥል እንደማይገባ አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ደንግጓል፡፡ ምናልባትም ይኸው ሥርዓት ሳይፈፀም ተመሳሳይ የሆነውና በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች የተነሳው ጉዳይ በተለያየ ክስ አማካኝነት በተለያየ ፍ/ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ የሚገኝ መሆኑ ከታወቀም የክርክሩ ተነጣጥሎ መታየት ለዳኝነት ሥራ አመራር ወይም ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ የማይመች ወይም የማይገባ ሆኖ ስለሚገኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 11 መሰረት ተጣምሮ መታየት እንደሚኖርበት ወይም በቁጥር 244 እና 245 በተነገረው መሰረት አስፈላጊው ብይን ሊሰጥበት እንደሚገባም ተከታይ የሆነውን የማረሚያ ሥርዓት አበጅቷል፡፡

ከዚህም ድንጋጌ ሥር ከተመለከተው "... ለዳኝነት ሥራ አመራር..." የማይመች..." የሚለው ሐረግ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማው አንድ ክርክሮችን ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአፋጣኝ እንዲታዩ በማድረግ ጊዜን፣ ጉልበትን እና ገንዘብን ለመቆጠብ እንደመሆኑ መጠን ተመሳሳይ ጉዳይ በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች

በአንድ ፍ/ቤትም ሆነ በተለያዩ ፍ/ቤቶች ማቅረብና ቀርቦ እንዲታይ ማድረጉ ከዚሁ መሰረታዊ ከሆነው የሥነ-ሥርዓት ህጉ ዓላማ ጋር የማይስማማ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን፤ "... ወይም ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ የማይመች ወይም የማይገባ...." የሚለው ሐረግ ደግሞ ተለያይተው ክሶች የመቅረባቸው ውጤት በክርክር አመራር አመቺነት ወይም ጊዜን ወጭንና ድካምን በማስቀረት ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመጨረሻ በሁለቱም ክሶች ላይ የሚሰጠው ፍርድ ከቶውንም ቢሆን ተመሳሳይ ሊሆን ስለማይችል ውጤቱ ትክክለኛ ፍርድ ሊሆን የማይችል መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

የዚሁ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 8 ን ድንጋጌ ሙሉ ለማድረግ በተቀመጠውም በቁጥር 11 ላይ የተመለከተውም ድንጋጌ ይዘትና ሀሳብ ይህንኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉን ዓላማ የተንተራሰ ነው፡፡ በተለይም በቁጥር 11(1) ላይ ከአንድ ጉዳይ የመነጩት ክሶች በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ፍ/ቤት የቀረቡ መሆኑ ከተረጋገጠ የክርክሩ ደረጃ ምንም ይሁን ምን ክሶች ተጣምረው መታየት እንደሚገባቸው በግልፅ ያመለከተ ሲሆን፤ በቁጥር 11(2) ላይም "…. ማስረጃ መቀበልና ማከራከር ከመጀመሩ በፊት…" በሚል መቼ መጣመር እንደሚገባቸው ጊዜን አስመልክቶ የተቀመጠው ሐረግ በተቻለ መጠን ተከራካሪ ወገኑ ይህንኑ እንደተረዳ ወዲያውኑ ማቅረብ ያለበት መሆኑን ለማስገንዘብ ነው ከሚባል በቀር የአሁን ተጠሪ በዚህ የሰበር ደረጃ ባቀረቡት የፅሁፍ ክርክር እንደገለጹት ምንም እንኳ ክሶች ተለያይተው የቀረቡ መሆኑ ቢታወቅም በሁለቱም ክሶች ላይ የማስረጃ መስማቱ ሥራ ካለቀ ሁለቱም ጉዳዮች ተነጣጥለው ለየብቻ ታይተው ፍርድ እንዲሰጣቸው ሥርዓቱ ይፈቅዳል ከሚለው ትርጉም የሚያደርስ አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 እና 11 መሰረት የሚነሱት ክርክሮች በይዞታቸው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ሥር የሚታቀፉ በመሆናቸው መቼ መቅረብ እንዳለባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 234 እንደተደነገገው ማስረጃ ከመስማቱ በፊት የመከላከያ መልስ በሚቀርብበት ጊዜ ለመሆኑ መደንገጉና፤

ሆኖም በዚህ ጊዜ መቅረብ ሲገባቸው ያልቀረቡት የመቃወሚያ የክርክር ነጥቦች በይዞታቸው ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያሰናክሉ ሆነው ከተገኙ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሊቀርቡ እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(3) ከተደነገገው አንፃር የቁጥር 11(2) ድንጋጌ ይዘት ሲታይ ከላይ የተመለከተውን ትርጉም የሚደግፍ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ሁለታችንም በሌላ ፍ/ቤት እየተከራከርን እንገኛለን ይህ ለሁለተኛ ጊዜ በዚያው ፍ/ቤትም ሆነ በሌላ ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ከዚህ በፊት ቀርቦ እየተከራከርን ከምንገኝበት ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ስለሆነም ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም ወይም ተጣምሮ ሊታይ ይገባዋል የሚለው በቁጥር 8 ሆነ 11 መሰረት የሚቀርበው ክርክር ማስረጃ ከመስማቱ በፊት ያልቀረበ ስለሆነ ክርክርን በአፋጣኝ እና በአነስተኛ ወጭ ለማየት አያስችልም ስለሆነም ጊዜው ካለፈበት በኋላ የቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም የሚያሰኝ የክርክር ዓይነት ሳይሆን ይህ ዓይነት ክርክር መኖሩ እየታወቀ ከታለፈ ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የማያስችል በመሆኑ ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ እንዲቀርቡ ከሚድረጉት የመቃወሚያ ክርክሮች ዘርፍ የሚመደብ ነው፡፡

የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ቢሆን እነዚህን ሁለት ክሶች ይዘታቸውን ተመልክቶ ተጣምሮ እንዲታዩ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ የሰጡበት እንጂ ማስረጃ ከመስማቱ በፊት ያልቀረበ ስለሆነ ሊጣመሩ አይገባም በሚል ዳኝነት አልሰጡበትም፡፡

በመዝገብ አፃፃፍ ስህተት ሁለቱም ጉዳዮች በተናጠል ታይተው የተለያየ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ እራሱ የሰጠውን ፍርድ እንደይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቱ የመሻር ስልጣን የሌለው በመሆኑ በክርክር ሂደት በመዝገብ አፃፃፍ ጊዜ የተፈፀመውን የቁጥር አፃፃፍ ዝንፈት በማረም ተገድቧል፡፡

ሆኖም የሥር ፍ/ቤት በቁጥር አፃፃፍ ስህተት ምክንያት እንጂ ድሮውንም ተጣምረው ሊታዩ የሚገባቸው ተመሳሳይ ጉዳዮች መሆናቸውን ተገንዝቦ ቀደም ሲል ተጣምረው እንዲታዩ በሚል የሰጠውን ትዕዛዝ ተከትሎ ፍርድ ከሰጠም በኋላ ቢሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 208 መሰረት የእርማት ዳኝነት የሰጠበት ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ/ም ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዳኝነት አልሰጠበትም፡፡ የመጨረሻ ዳኝነት የሠጠበት ከ6 ወር በኋላ ነው፡፡

በመሆኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 እና 11 ድንጋጌዎች አፈፃፀም በሚመለከት በአሁን አመልካች አማካኝነት የይግባኝ መዝገብ ከተከፈተም በኋላ ክርክሩ ሲቀርብለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345፣ 32(2) እና 244(3) ድንጋጌ አንፃር በማየት የቀረበለትን የይግባኝ መዝገብ ከመዝጋት ይልቅ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 11(3) መሰረት ተገቢውን መፈፀም ይቻል ዘንድ በመ/ቁ 45441 የተሰጠው ውሳኔ ደረጃውን ጠብቆ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መቅረብና አለመቅረቡን መጠባበቅ ይገባው እንደነበረም ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በኮ/መ/ቁ 45441 በሆነው ጉዳይ ላይ የአሁን አመልካች በሁለቱም ጉዳዮች ተመሳሳይ ሆነው እያለ በአንድ ፍ/ቤት የተለያየ ፍርድ ሊሰጥ የቻለበትን ምክንያት በመግለፅ የተፈፀመው የሥነ - ሥርዓታዊ ግድፈት በይግባኝ ደረጃ እንዲታረም በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 116629 ማስከፈታቸውን ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲረዳ አስቀርበን ከተመለከትነው መዝገብ የተረዳን ከመሆኑ በቀር የአሁን ተጠሪ በዚህ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለው የብድርና የመያዣ ውል ፈራሽ ነው በሚል በመ/ቁ 45441 በሆነው መዝገብ ላይ ከታች ወደ ላይ ያቀረቡት ክርክር የለም ክርክር ያቀረቡበትም ለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር አልተገኘም፡፡ ይህም በመሆኑ ምክንያት በመ/ቁ 45441 የተሰጠው ፍርድ ደረጃውን ጠብቆ በቀረበ ክርክር እንደገና ታይቶ ሥልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች እስካልተለወጠ ወይም እስካልተሻሻለ ድረስ የፀና እና ተፈፃሚነት ያለው ፍርድ ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በይግባኝ መ/ቁ 119226 በቀረበለት የይግባኝ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት በአንድ ጉዳይና በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች የተነሳውን ሁለት የተለያዩ ክሶች ከጉዳዩ አመራር ሥርዓት ውጭ ነጣጥሎ በማየቱ ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8፣ 11፣ 244(3) የተመለከቱትን ሥነ - ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች የጣሰ መሆኑንና በማየትና በመ/ቁ 45441 የተሰጠውን ፍርድ የአሁን አመልካች ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ በይግባኝ ደረጃ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 345 የተመለከተውን ሥነ - ሥርዓታዊ ድንጋጌ ምርኩዝ ያደረገና አቤቱታው ከድንጋጌው ትክክለኛ አፈፃፀም ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሁሉ ተገንዝቦ በይግባኝ መዝገቡ ላይ ተገቢውን ፍርድ መስጠት

እየቻለ በመ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ ላይ ብቻ ተወስኖ ሚያዝያ 04 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም በመ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ ለተነሳው ክርክር መሰረት የሆነው ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው የብድር እና የመያዣ ውል በህግ ፊት ሊፀና የማይችል፤ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል መሆኑ ተገልፆ ፈራሽነቱ በመ/ቁ 45441 የተወሰነ በመሆኑና ይህም ውሳኔ ከታች ወደ ላይ ባለው የክርክር መስመር ታይቶ ያልተለወጠ ያልተሻሻለ ሆኖ በመገኘቱ የመጨረሻ ፍርድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም አንፃር ለብር 400,000.00 ብር (አራት መቶ ሺ) ክርክር መሰረት የሆነው የብድር ውል ፈራሽ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውና በመ/ቁ 37363 የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ/ም በዚሁ መዝገብ ላይ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 400,000 (አራት መቶ ሺ) ይክፈሉ በሚል የተሰጠውም ፍርድ ዋጋ ያለው እና ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 119226 ሚያዝያ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በጉዳዩ ላይ የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል ግዴታ የለባቸውም ብለናል፡፡
3. የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዝገቡ የመ/ቁ 116629 በመጣበት አኳኋን ይመለስ፡፡
4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 83007

ሰኔ 3 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካቾች፡-1. ወ/ሮ አልማዝ ገመቹ } ጠበቃ አቶ ገናናው ተሾመ ቀረቡ

2. አቶ ዮሐንስ ገመቹ

ተጠሪ፡- አቶ ፋዩ ገመቹ ጠበቃ አቶ ተስፋዬ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳይ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 147083 ሰኔ 4 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ንብረት በአንደኛው ወራሽ ስም እንዲመዘገብ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በስዮ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ የደንቢ ዶሎ ማዘጋጃ ቤት ተከሣሽ ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ ተከራካሪዎች ሆነው ቀርበው ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ከአባቱ በውርስ ያገኘሁት ቤት ስመ ንብረቱን እንዲያዛውርልኝ ተከሣሹ /የደንቢ ዶሎ ማዘጋጃ ቤት/ ስጠይቀው ስም ለማዛወር እንቢተኛ ስለሆነ ስመሀብቱን እንዲያዛውር ውሣኔ ይሰጥኝ በማለት ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ በሥር ተከሣሽ የነበረው የደንቢ ዶሎ ማዘጋጃ ቤት ግብር የተከፈለው በሟች አቶ ገመቹ ገዳም ወራሾች ስም በመሆኑና አንደኛ አመልካች ወ/ሮ አልማዝ ገመቹ/ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ ተከሣሽ እንዳይዛወር ያመለከቱ በመሆኑና ስም አላዛወርኩም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካቾች ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆነው ቀርበው ቤቱ በወራሾች ስም ግብር የሚከፍልበት እና በሽማግሌ ዳኞች ወራሾች እንድንካፈለው በ1992 ውሣኔ የተሰጠበት እና በ1998 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት የፈፀምንበት የሟች ወራሾች የጋራ ሀብት በመሆኑ ወደ ከሣሽ ስም ሊዛወር አይገባም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡
2. የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪና አመልካቾች በሚከራከሩበት ቤት ላይ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ከዚህ በፊት ውሣኔ ተሰጥቶበታል ስለዚህ የቤቱ ስመሃብት ወደ ከሣሽ /ተጠሪ/ እንዲዛወር ለተከሣሹ ደንቢዶሎ ማዘጋጃ ቤት ይፃፍ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ትእዛዝ ቅር

በመሰኘት ለቁለም ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ቤቱ ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት እንደሆነ በመግለጽ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

3. ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአሁን አመልካቾች ተጠሪ የያዘውን ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 99/90 የካቲት 10 ቀን 1992 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲያካፍለን የሚል የአፈፃፀም ክስ በመዝገብ ቁጥር 12882 አቅርበው ነበረ ተጠሪ በበኩሉ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 384 የተደረገው የአስር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ በመሆኑ የአፈፃፀም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካቾች /ይግባኝ ባይዎችና/ እና መልስ ሰጭ /ተጠሪ/ በመዝገብ ቁጥር 12882 ያቀረቡትን ክርክር በመመርመር አመልካቾች ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚታገድ መሆኑን ገልፆ ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ባዮች /አመልካች/ በዚህ መዝገብ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አላቀረቡም፡፡ ይግባኝ ባዮች በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠውን ውሣኔ ለማሻር የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 323/2/ በሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ይግባኝ ሣያቀርቡ ተጠሪ የደንቢ ዶሎ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14255 ሀምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ባቀረቡት ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠውን ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሻሩ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስኗል፡፡

4. አመልካች ጳጉሜ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የቤቱ ባለቤትነትና ግብር ከ1951 ዓ.ም ጀምሮ በወራሾች ስም የሚከፈል መሆኑን ተጠሪ በማመን ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1060/1/ መሠረት የንብረቱ የጋራ ባለሃብት ናቸው፡፡ አመልካቾች በመዝገብ ቁጥር 12882 ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በአስር አመት ይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ተጠሪን ብቸኛ የቤቱ ባለሃብት እያደርገውም፡፡ አመልካቾች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1168 መሠረት ለተከታታይ አስራ አምስት ዓመት ግብር የገበሩ በመሆናቸው የቤቱ ባለሃብት ናቸው፡፡ በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የሚቀርብ ክስ በይርጋ ቀሪ እንደማይሆን ይኸ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43600 ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

5. ተጠሪ ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ቤቱን እንዲያካፍላቸው የአፈፃፀም ክስ አቅርበው ጥያቄቸው በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ በመዝገብ ቁጥር 12882 ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡አመልካቾች በሕግ በተደነገገው መሠረት ይህንን ውሣኔ በይግባኝ አላሻሩም አመልካች ይህንን ውሣኔ በይግባኝ እንዲለወጥ ወይም እንዲሻር ሣያደርጉ ቤቱ የጋራ ሃብታችን ነው በተጠሪ ስም



www.chilot.me

ሊዛወር አይገባም ብለው ለመከራከር የሚችሉበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች ታህሣስ 9 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካችና ተጠሪ የሟች አባታቸው የአቶ ገመቹ ገዳም የውርስ ንብረት ክፍል የሆነው ቤት የጋራ ወራሾች መሆናቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ እንደዚሁም በሟች ወራሾች ስም በጋራ ለቤቱ ግብር ሲከፈል የቆየ መሆኑም ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም በዚህ መዝገብ እያከራከረ ያለው ጉዳይ አመልካቾች በወራሽነታቸው በቤቱ ላይ ያረጋገጡት የወራሽነት መብት ያለ መሆኑ ወይም አለመሆኑ አይደለም፡፡ አከራካሪ የሆነው አመልካቾች በንብረቱ ላይ ያላቸውን ያልተከፋፈል የጋራ ባለሃብትነት ለማስፈፀም አቅርበውት የነበረውን የአፈፃፀም ክስና በአፈፃፀም ክሱ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ቀርቦበት ሣይሻር ፣ሣይለወጥ ወይም ሣይሻሻል መቅረቱ አመልካቾች በቤቱ ላይ የሚያነሱት የመብት ጥያቄና ክርክር ላይ ምን አይነት ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል የሚለው የሥነ ሥርዓት ጉዳይ ነው፡፡

8. አመልካቾች በተጠሪ ይዞታ ሥር የነበረው የማይንቀሣቀስ የውርስ ንብረት /ቤት/ የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 99/90 የካቲት 10 ቀን 1992 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ለሶስት እኩል እንዲያካፍላቸው ፍርድ ቤቱ የአፈፃፀም ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው በመዝገብ ቁጥር 12882 የአፈፃፀም ክስ አቅርበው የነበረ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በዚህ መዝገብ አመልካቾች ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 384 የተደነገገው የአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ ነው ስለዚህ በይርጋ ቀሪ ነው የሚል ክርክር አቅርቦ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች በመዝገብ ቁጥር 12882 ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ዘግቶታል፡፡ አመልካቾች በህጉ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን በማቅረብ ወደ ይኸ ውሳኔ እንዲሻር ፣እነዲለወጥ ወይም እንዲሻሻል አላደረጉም፡፡ ስለሆነም በመዝገብ ቁጥር 12882 ታህሳስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ አመልካቾች በቤቱ ላይ ያላቸውን የወራሽነት መብት በፍርድ ለማስፈፀም በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለማቅረባቸው ተጠሪ ቤቱን እንዲያካፍላቸው የመጠየቅ መብታቸውን በይርጋ ቀሪ የሚሆን በመሆኑ ጉዳዩ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ አስገዳጅነት ያለው ውሣኔ ነው፡፡

9. አመልካቾች በቤቱ ላይ ያላቸው መብት በፍርድ ሃይል እንዲፈፀም ለመጠየቅና ለመከራከር የማይችሉና ጥያቄያቸው በይርጋ ቀሪ እንደሆነ በመዝገብ ቁጥር 12882 ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ አንቀጽ 320/1/፣ አንቀጽ 324፣ አንቀጽ 327 እና በሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርበው ሣያሽሩ ተጠሪ በውርስ በተገኘው ቤት ላይ በፍርድ ሊፈፀም የሚችል መብት ያለኝ እኔ ብቻ ነኝ ስለዚህ የደንቢ ዶሎ ማዘጋጃ ቤት ስመ ሃብቱን እንዲያዛውር ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበውን ክስ በመቃወም ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የሚሆኑበት በሕግ ፊት የፀናና ሊፈፀም የሚችል መብትና ጥቅም የላቸውም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የአመልካቾች በቤቱ ላይ አለን የሚሉት

መብት በፍ/ቤት ውሣኔ /ትእዛዝ/ እንዲፈፀም ጥያቄ ሊያቀርቡበት የማይችሉና የይርጋ የጊዜ ገደብ ያለፈበት መሆኑ ቀደም ሲል መወሰኑን ገልፆ የአመልካቾችን ክርክር በመዝገብ ቁጥር 14255 ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም ውድቅ አድርጓል፡፡

10. አመልካቾች በዚህ መዝገብ የተሰጠውን ብይን መነሻ በማድረግ በውጤት ደረጃ በመዝገብ ቁጥር 12882 ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07355 የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ ለማሻር ወይም ለማስለወጥ የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ይግባኝ ያላቀረቡ መሆኑን ሳያገናዝብ በመዝገብ ቁጥር 14255 በተሰጠው ትእዛዝ ያቀረበውን ይግባኝ መነሻ በማድረግ በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ የሚሽርና ውጤት አልባ የሚያደርግ ውሣኔ መስጠቱ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድ በይግባኝ እና በሰበር ለማሣረም ሲውሉ የሚገቡ አስገዳጅ ሥርዓቶችን ያልተከተለና አንድ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በሕግ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት በይግባኝ በሌላ ሥርዓት ወይም በሰበር ካልታረመ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለው ውሣኔ ነው የውሣኔው አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት በባለጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን በማናቸውም አስፈፃሚ አካልና ማናቸውም ፍርድ ቤት የሚመለከት እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ፣በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 2 የተካተተውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስ ነው፡፡

11. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14255 በሰጠው ትእዛዝ መነሻ አመልካቾች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 320/1/ አንቀጽ 324፣ አንቀጽ 327 እና ሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት የይግባኝ ቅሬታ ያላቀረቡበትንና በጉዳዩ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለውን የወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12882 የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 07355 መሻሩ የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ አመልካቾች በዚህ መዝገብ የጠቀሷቸውን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1060፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1168፣ እና ሌሎች ድንጋጌዎች ይዘትና ትርጉም በመተንተን የይግባኝ ቅሬታ በማቅረብ ለማስለወጥ ወይም ለማሻር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 324 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ የነበራቸው የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12882 ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነበር፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ በማቅረብ ውሣኔውን አላስለወጡም ወይም አላሻሩም

12. በመዝገቡ ቁጥር 12882 የተሰጠው ውሣኔ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ባልተሻረበት ወይም ባለተለወጠበት ሁኔታ የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14255 ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ መነሻ በማድረግ በቀረበው ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠው ውሣኔ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የገለጽናቸውን የፍርድ ቤቶች ውሣኔ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት መርህንና አስገዳጅ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ የሚጥስ ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ከላይ የገለጽናቸውን ሥነ ሥርዓታዊ ምክንያቶችንና መሠረታዊ የዳኝነት ሥራ አካሄድ መርሆች መሠረት በማድረግ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻራቸውና የአመልካቾች ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 83169

መጋቢት 28 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ፕሮፌሰር አደም ዓሊ አህመድ ጠበቃ አስፋ ንጉሴ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አዳማ ጠቅላላ ሆስፒታልና ሜዲካል ኮሌጅ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ

አቶ በሻዳ ገመቹ ቀረቡ

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን ሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ እንዲሁም አመልካች የተከሳሽ ከሳሽ ተጠሪ የከሳሽ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በሰባት ሰዎች የተመሰረተ የንግድ ማህበር መሆኑን ገልጾ፣ የማህበሩ ጠቅላላ ካፒታል 140, 000,000/አንድ መቶ አርባ ሚሊዮን ብር/ ነው ተከሳሽ/አመልካች/ በማህበሩ ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋ ብር 35,000,000 /ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ብር/ ቁጥሩ ኤቢቲ 094872 በሆነ ቼክ አስይዘው አባል ሆነዋል፡፡ ሆኖም ይህንን ገንዘብ ባለመክፈላቸው ከሳሽ/ተጠሪ/ የገንዘብ ችግር ገጥሞት አቶ ከቢር ሁሴን ዋቆ በማህበሩ አባላት በቃለ ጉባኤ በሚወሰን ውሣኔ ሲሸፍኑ ቆይተዋል፡፡ ተከሳሽ የአክሲዮን ድርሻ ክፍያቸውን እንዲከፍሉ ቢጠየቁ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የአባልነት ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ ስለዚህ የማህበሩ አባልነታቸው ተሰርዞ ቼኩ እንዲመለስላቸው ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው እኔ ብር 35,000,000 /ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ብር/ ለመክፈሌ በቂ ማስረጃ አለኝ፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ያቀረበው ክስ ከማህበር አባልነት ይሰረዝልኝ የሚል ቢሆንም የክርክሩ መሰረታዊ ጭብጥ ተከሳሽ ብር 35,000,000 /ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ብር/ ከፍሏል ወይስ አልከፈለም? የሚለው በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ የገንዘብ መጠን ላይ አከራክሮ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡



www.chilot.me

2. አመልካች በበኩላቸው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበሩ እንዲፈርስ ለመጠየቅ የሚያስችሉኝ ምክንያቶች ናቸው የሚላቸውን በመዘርዘር ማለትም በአንደኛ ደረጃ ብር 35,000,000 የአክሲዮን ድርሻ ክፍያ እያለ አልከፈለም መባሉ፣ በሁለተኛ ደረጃ በእኔ ስም የነበረ መሆኑ ከእኔ እውቅና ውጭ ወደ ከሳሽ ስም መዛወሩ፣ በሶስተኛ ደረጃ አቶ ከበር ሁሴን ብር 78, 750,000 /ሰባ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ ብቻ ገቢ አድርገው እያለ ተጨማሪ ገንዘብ ገቢ ሳያደርጉ ገቢ እንዳደረጉ የተያዘ በመሆኑ ማህበሩ ፈርሶ በአክሲዮን ድርሻ ግምት ድርሻዬን እንዳገኝ ውሳኔ ይሰጥልኝ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ሆስፒታሉ ስራ ሲጀምር በሜድካል ዳሬክተርነት አገኝ የነበረው በወር 40,000 በ1993-2000 ዓ.ም ብር 3,360,000 እና በስራ አስኪያጅነት የሰራ ጊዜዬንና አእምሮዬን በማጥፋት ለሰጠሁት አገልግሎት አበል ብር 5,000,000 ከነወለዱ የተከሳሽ ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በሶስተኛ ደረጃ መሬቱን መካከለኛ ሆስፒታል ለመገንባት 40,600 ካሬ ሜትር በአዳማ ከተማ አስተዳደር በግሌ የተሰጠኝ ነው፡፡ ሆስፒታሉ እንዲገነባበት የተስማማሁት የመሬቱ ባለይዞታ በመሆኔ፣ ተገምቶ ወደ ፊት ጥቅም የማገኝ መሆኑን ተወያይተን ስለተስማማንበት ነው፡፡ አሁን ግን እኔ ሳላውቅ የባለይዞታነት መብቴ ተገፎ ወደ ከሳሽ ተከሳሽ የተዛወረ በመሆኑ ይዞታዬ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1179 መሰረት እንዲለቀቅ ይወሰንልኝ በማለት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ ማህበሩ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የመሬት ካርታ ይሰርዝልኝ ጥያቄ በአስተዳደር የሚታይ እንጂ በፍርድ ቤት የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሳሽ ከሳሽ የጠየቁት የገንዘብ ጥያቄ አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም የሚል መከራከሪያዎችን አቅርቧል፡፡

3. የአዳማ ልዩ ዞን በተጠሪ ክስና በአመልካች የተከሻስ ከሻስነት ክስ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያዎች ከመረመረ በኋላ ከሳሽ/ተጠሪ/ በተከሳሽ/አመልካች/ ላይ ያቀረበው ክስ የማህበርን አባልነት ግዴታውን ያልተወጣ ስለሆነ ከማህበር አባልነቱ ይሰረዝልኝ የሚል ነው፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ ብር 35,000,000 ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ብር እንዲከፍለው ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የለም፡፡ ጭብጡ ተከሳሽ ከማህበሩ አባልነቱ ይሰረዛል ወይስ አይሰረዝም የሚል በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡

• የተከሳሽ ከሳሽ የከሳሽ ተከሳሽ ብር 8,360,000 /ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሣ ሺ ብር/ እንዲከፍለው ያቀረበው ጥያቄ ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 14 ከተሰጠው ስልጣን በላይ በመሆኑ፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለኝም

• ማህበሩን መፍረስ በተመለከተ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን አለኝ፡፡

• የመሬቱ ይዞታ ከተከሳሽ ወደ ከሳሽ ተከሳሽ የተዛወረ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ለተከሳሽ ከሳሽ የተሰጠው የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝና በተከሳሽ ስም የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን የለውም፡፡ በማለት ብይን ሰጥቶ በሌሎች ነጥቦች ላይ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ለመስማት ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

4. በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት የጠየቀው ብር 8,360,000 በስር ፍርድ ቤት

የሚታይ ባለመሆኑ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪ በከሳሽነት ያቀረበው ከማህበር አባልነት ይሰርዝልኝ በማለት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስር ነገር ስልጣን አለው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ማህበሩ የተመሰረተበትን መሬት ጉዳይ  አይቶ የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች መሬቱን በተመለከተ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ማህበሩ እንዲፈርስ ካቀረበው ጥያቄ ጋር ታይቶ ውሣኔ ይሰጥበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. አመልካች መስከረም 7 ቀን 2005 ዓ.ም  በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብር 35,000,000 የተከፈለ መሆን አለመሆኑን የክርክሩ ጭብጥ የሆነበትን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለው መባሉ ስህተት ነው፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በተከሣሽ ከሣሽነት ያቀረቡት የገንዘብ ጥያቄ ተነጥሎ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በማለት የሰጠው ውሣኔ የተሣሣተ  ነው፡፡ ስለመሬቱ የሰጠውን ውሣኔም ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ታህሣስ 26 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በስልጣኔ ሥር ናቸው ባላቸው ጉዳዮች ውሣኔ ሣይሰጥ፣ የአመልካች ክርክር በይግባኝና በሰበር መስተናገዱ ስህተት ነው፡፡ አመልካች ያቀርቧቸው ክሶች ተለይተው ሊቀርቡ የሚገባቸው ናቸው ስለዚህ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ከማግኘቱ በፊት ያቀረበው ክርክር በሕግ የተደነገገውን ስርአት የተከተለ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥር 21 ቀን 2005 ዓ.ም የሥር ፍርድ ቤት የከሣሽን ክስና አራት ራሣቸውን የቻሉ የዳኝነት ጥያቄዎችን የያዙ የተከሣሽ ከሣሽነት ክሶች ቀርበውለታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤት ብይን በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን የመጨረሻ ውሣኔ ላይ ውጤት ያለው በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌውን የተከተለ ነው በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአዳማ ልዩ ዞን ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አለው፣ የአመልካች የተከሣሽነት ክስ የጠየቁት ብር 8,360,000 ተነጥሎ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቅረብ በማለት የተሰጠው ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6.1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን፣ በመጀመሪያ ለአዳማ ልዩ ዞን ተጠሪ ያቀረበው ክስና በአመልካች በኩል የቀረበው የተከሣሽነት ክስ ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቀውን የመብትና የዳኝነት ጥያቄ እና አመልካች ከተጠሪው የሚጠይቀውን የመብትና የዳኝነት ጥያቄ የያዙና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዩች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕግ አውጭው በከሣሽ በኩል ክስ የቀረበበት ተከሣሽ፣ ክሱን ለመከላከል ከሚያቀርበው መልስ በተጨማሪ ጉዳዩን እያየ ላለው ፍርድ ቤት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 30/1/ አንቀጽ 324/1/ሀ እና በአንቀጽ 215/2/ የደነገገው፣ የከሣሽ ክስና የተከሣሽ ክስ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በአንድ ላይ ተጠቃልለው ጉዳዮን የመወሰን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት መታየታቸው፣ የተከራከሪዎቹንና የፍርድ ቤቱን ጊዜና ወጭ የሚቆጥብና ትክክለኛ ፍትሕ ላይ ለመደረስ፣ ጠቀሜታ እንዳለው በመገንዘብ ነው፡፡



www.chilot.me

ተከሣሽ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ካቀረበ ፍርድ ቤት ከቀረቡለት ጉዳዮች በሥረ ነገር ስልጣኑ ሥር ያሉትን መርጦ የማየትና ክሱ ከስረ ነገር ስልጣን በላይ የሆኑትን ጉዳዮች ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቅረብ በማለት የከሣሽ ክስና የተከሣሽ ተከሣሽነት ክስ ተነጣጥለው እንዲታዩ ትእዛዝ መስጠት አይችልም፡፡ ምክንያቱም የከሣሽን ክስ ተቀብሎ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በማየት ላይ እያለ ተከሣሹ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ካቀረበ የፍርድ ቤቱ የሥረ ነገር ስልጣን የሚወሰነው አንደኛው ወገን ያቀረበውን ከፍተኛ የሃብት ግምት መሠረት በማድረግ እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን ክስና አመልካች ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አጠቃልሎ ለማየት የሚያስችለው የሥረ ነገር ስልጣን የሌለው በመሆኑና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ውስጥ የብር 8,360,000 የዳኝነት ጥያቄ የያዘውን ጉዳይ አከራክሮ የመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም፡ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቅረብ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ይህንን ጉዳዩ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነጥሎ እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የይግባኝ ቅሬታና የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የሥር ፍርድ ቤት በከሣሽ ያቀረበውን ክስና በተከሣሽ የቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አጠቃልሎ ለመወሰን የሚያስችለው የሥር ነገር ስልጣን ከሌለው መዝገቡን ዘግቶ ማስናበት እንጂ የተጠሪ ክስ እና እኔ ያቀረብኩት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተነጣጥለው ግማሹ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግማሹ በሌላ ፍርድ ቤት እንዲታይ ትዕዛዝ መስጠት አይችልም በማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ካቀረባቸው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውስጥ የተወሰኑትን የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይንና ከሳሽ ያቀረበውን ክስና አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ከጠየቃቸው የተወሰኑትን ስልጣን አለኝ ብሎ ማከራከር መቀጠሉ ተጠሪ እንዲሚለው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320 ንዑስ አንቀጽ /3/ መሰረት ይግባኝ የማይባልበት ጊዚያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ብይን ክስና የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በቀረበበት ጉዳይ የፍርድ ቤቱ ስረ ነገር ስልጣን ስለሚወሰንበት ሁኔታ የተደነገገውን አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ የሚጥስና ጉዳዩ ተነጣጥሎ በፍርድ ከማለቁ በፊት በይግባኝና በሰበር መታረም የሚገባው የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ ልዩ ባህሪና ውጤት ያለው የመጨረሻ ውሳኔ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 320 ንዑስ አንቀጽ 3ን በመጥቀስ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ተጠሪ አመልካች ብር 35,000,000 የአባልነት መዋጮ የአክሲዮን ክፍያ ያልከፈለ ስለሆነ ከማህበር አባልነት ይሰረዝልኝ በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የከሳሽ ክስ ተከሳሽ ከአባልነት ይሰረዛል ወይስ አይሰረዝም የሚል ጭብጥ የሚያስነሳ መሆኑን በመግለጽ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው በማለት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ብይን ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ተጠሪ ብር 8,360,000 /ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ ሺ ብር/ ሊከፍለኝ ይገባል የሚልና ሌሎች የዳኝነት ጥያቄዎችን የያዘ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡

የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለው ጭብጥ የሚወሰነው ከተጠሪና አመልካች ካቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ከፍተኛ የኃብት ግምት ያለውን ማለትም አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የጠየቀውን ብር 8,360,000 መሰረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን ክስም ሆነ የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችለው የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ተደንግጎ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪውን ክስና አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ካቀረባቸው የዳኝነት ጥያቄዎች የተወሰኑትን በዳኝነት አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን አለኝ ሌሎቹን ደግሞ የስረ ነገር ስልጣን የሌለኝ በመሆኑ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አመልካች ያቅርብ በማለት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የተጠሪን ክስና የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አጠቃልሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን እንዲቀርብ በመወሰን የስር ፍርድ ቤት የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 17 ንዑስ አንቀጽ 3ን በመጣስ የፈፀመውን ስህተት ሳያርም ማለፍ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11396 ግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 150799 ሰኔ 14 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበውን ክስም ሆነ በአመልካች ያቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ለማየት የሚያስችለው የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ሕግ ቁጥር 17/3/ መሰረት ወስነናል፡፡
3. ጉዳዩ መታየት ያለበት የተጠሪን ክስና የአመልካችን የተከሳሻ ከሳሽነት ክስ አጠቃልሎ ለማየትና ውሣኔ ለመስጠት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመሆኑ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያስተላልፍለት በማለት ወስነናል፡፡
4. አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን መሰረት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሲያቀርብ የከፈለው የዳኝነት ገንዘብ በደንቡ መሰረት ተቀንሶ ተመልሶለት ከሆነ፣ በሕጉ መሰረት የዳኝነት ገንዘቡን እንዲከፍል ሊደረግ ይገባል ብለናል፡፡ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሮ/ብ

የሰ.መ.ቁ. 85873

መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ኒኢማ አባድጋ አባዋጂ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጣሐ ጀማል አደም ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በውጭ አገር የተደረገ የእርቅ እና የግልግል ስምምነት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊፀድቅ የሚችልበትን ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ከአሁኗ አመልካች ጋር የነበራቸውን ጋብቻና ውጤቱን በተመለከተ በሽማግሌ ፊት ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በስምምነት በሰዑዲ አረቢያ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ቆንጽላ ጽ/ቤት በተረጋገጠው አግባብ መደረጉን ገልፀው ይኼው ስምምነት እንዲፀድቅላቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው የካቲት 17 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ ለተጠሪ ያጸደቀላቸው ሲሆን የአሁኗ አመልካች ሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ማመልከቻ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት የስምምነት ፍቺ በሌሉበትና እና ሙሉ ፍላጎታቸው ሳይጠየቅ በተጠሪ ተፅፎ የቀረበ ስለመሆኑና በውጤቱም እጅጉን የጎዳቸው መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ ክርክር አድርገው የመኽር ገንዘብ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር)፣ የቤት ንብረት፣የልጅ ቀለብ ላይ ውሳኔ እንዲሰጣቸው የመቃወም ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት አድርጎ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪና አመልካች ሰኔ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት አመልካች የተሳተፈበት መሆኑ የተረጋገጠ ነው በሚል ምክንያት ቀድሞ የእርቅ ስምምነቱን ያጸደቀበትን ውሳኔ ባለበት አጽንቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጋብቻው በስምምነት የፈረሰ ቢሆንም በንብረቱና በልጅ አስተዳደግ ላይ ግን ተገቢዉና ሕጋዊ ስምምነት ባልተደረገበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች በስምምነት መሰረት ልትጸና ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የሸሪዓ ሕጉንም ሆነ መደበኛውን ሕግ የሚጥስ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም የተደረገ ነው ያሉትን የእርቅ ስምምነት ለፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው አመልካች በሌሉበት እንዲጸድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሕጉ ተለይቶ የተሰጣቸውን ስልጣን ምን እንደሆነ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩ መሆኑን፣ ባሁኑ ደረጃ ተለያይተው እንደሚገኙና በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በሳውዲ አረቢያ ውስጥ በሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንፅላ ጽ/ቤት ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በሽማግሌዎች ፍቺ ተደረገ በተባለ የእርቅና የግልግል ስምምነት የሚል ርዕስ ባለው ሰነድ ጋብቻውን በፈቃዳቸው አፍርሰው ንብረቱንም ሆነ በጋብቻ ወቅት ያፈሯትን ሕጻን አስተዳደግ በተመለከተ ስምምነት ተደርጓል በሚል ምክንያት ተጠሪ ሰነዱን ለፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም አመልካች በሌሉበት ሁኔታ የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ስምምነቱ ፀድቋል ተብሎ የተወሰነ መሆኑንና አመልካች ይህንኑ ውሳኔ ለማስነሳት የተቃውሞ አቤቱታ ማቅረባቸውን፣ ለአቤቱታቸው መሰረት ያደረጉት ምክንያትም ተጠሪ አለ በማለት ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ስምምነት የማያውቁትና በተጠሪ ፍላጎት ብቻ ተፅፎ የቀረበ እንዲሁም የአመልካችን የንብረት መብትም ሆነ የህጻኗን አስተዳደግ የጎዳ መሆኑን መጥቀሳቸውን የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 34 (5) ስር የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሀይማኖት ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን በሕገ መንግስቱ ክልከላ እንዳልተደረገበት በግልጽ ከማስቀመጡም በላይ ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን ያሳያል፡፡ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብትም ምንጩ ይኼው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ሲሆን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሰረት ተደራጅተዋል፡፡ በዚሁ አዋጅም ስልጣናቸው ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ በአዋጁ የክርክሩን የአመራር ሥርዓት ካልሆነ በስተቀር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በስረ ነገር ስልጣናቸው ሥር የሆኑ ጉዳዮች የሚቀርብላቸውን አቤቱታና ክርክር የሚወስኑት የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/92 በአንቀጽ 6 (1) ስር በግልፅ የተደነገገ ሲሆን አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፈቃድ የሰጠ መሆኑም ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 188/1992 ዓ.ም አግባብ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ የሚገባ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 6 ድንጋጌና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 80 (3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6 ጣምራ ንባብ መሰረት ስነ ስርዓታዊ የሆነ የህግ ጥያቄን ብቻ ለማየት ስልጣን እንዳለው ግንዛቤ በመውሰድ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ሕጎችን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን ከጭብጡ አንጻር መርምሯል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የእርቅ ስምምነት እንዲፀድቅላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ያቀረቡት ሰነድ የእርቅ ግልግል ስምምነት መሆኑን በርዕሱ የሚገልፅና በይዘቱም ጋብቻንና ውጤቱን እንዲሁም የልጅ አስተዳደግን በተመለከተ ግራ ቀኙ ያደረጉትን ስምምነትን ምንነት የያዘ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስምምነቱ የተደረገው የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመጀመሪያው ለማየት በቀጥታ በተከፈተለት መዝገብ ሳይሆን በውጪ አገር ተደርጎ የመጣው የእርቅ ስምምነት እንዲፀድቅ ተጠሪ አመልካች በመሆን ባስከፈቱት መዝገብ ነው፡፡ በዚሁ

መዝገብ ላይ በአመልካችነት የአሁኑ ተጠሪ ስም የተመዘገበ ሲሆን በመዝገቡ ተጠሪ በሚል በተቀመጠው ቃል ትይዩ ግን የአሁኗ አመልካች ወይም ለጉዳዩ ተከራካሪ የሆነ ሰው ስም ያለመመዝገቡን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ አንድ እርቅ በፍርድ ቤት ሊፀድቅ የሚችለው ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በመታየት ሂደት ላይ እያለ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ መሆኑን ገልፀው ይኼው ስምምነታቸው ለሕግ እና ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ እርቁ ወይም ስምምነቱ በፍርድ ቤት ተመዝግቦ ክርክሩ እንዲቆምላቸው ሲያመለክቱ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከዚህ ውጪ ከፍርድ ቤት ውጪ በሚደረግ እርቅ ወይም ግልግል መሰረት ያለመግባባትን ያስቀሩ ወይም ለጉዳያቸው እልባት ያገኙ ሰዎች እርቁ ወይም ግልግሉ እንደተፈረደ ፍርድ ሊቆጠርላቸው የሚገባ እና በውጤቱም በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ወይም ማስፀደቅ ሳያስፈልገው ራሱን ችሎ ሊፈጸም የሚችል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3312 እና 3324 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እርቁ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲጸድቅ ያቀረቡት ማመልከቻ በሕጉ ያልተቀመጠውን ስርዓት መሰረት በማድረግና በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አግባብም ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ባልተሰጠው ሁኔታ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከላይ እንደተገለጸው የአሁኗ አመልካች በአካል ያልቀረቡ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ተወክለው ጉዳዩ ያልታዬ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ይልቁንም አመልካች ያቀረቡት የእርቅ ስምምነት ይዘት አመልካች የማያውቁት እና በተጠሪ ተፅፎ የቀረበ ነው በማለት ለመቃወም አቤቱታ ማቅረቢያ መነሻ ያደረጉ መሆኑ ሲታይ ተጠሪ ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ተደረገ የተባለውን ስምምነት በሸሪዓ ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ቀድመው ፈቃዳቸውን በአዋጁ አንቀጽ 2 (4)፣4 (5) እና 5 (1) ድንጋጌዎች አነጋገር መሰረት ሰጥተዋል ለማለት ሁሉ የማያስደፍር መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ምክንያቱም አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 5 (1) እና ከአዋጁ ጋር በተያያዘው አባሪ (ፎርም) በመሙላት ማረጋገጥ እንደአለባቸው ሕጉ ያሳያል፡፡ ይህም የመከራከር መብትን በህጉ አግባብ ለማስከበርና ለማረጋገጥ የተዘረጋ ስርዓት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ ተደረገ የተባለው የእርቅ ስምምነት በሌላ አግባብ ውጤት ከሚያገኝ በስተቀር በሸሪዓ ፍርድ ቤትም ሆነ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክርክር በሌለበት ሁኔታ ቀርቦ የሚጸድቅበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ በመሆኑ እርቁ መፅደቁ ከአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6 (1) እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277 ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## **ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 4595/04 የካቲት 17 ቀን 2003 ዓ.ም እና ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 007/05 ታህሳስ 22 ቀን 2005 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በውጪ አገር ተደረገ የተባለው ስምምነት በሸሪዓ ፍርድ ቤት በቀጥታ ቀርቦ የሚጸድቅበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው የኖሩ ከሆነ ውጤቱንም ሆነ የልጅ አስተዳደግን በተመለከተ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ከመጠየቅና መብታቸውን ከማስከበር ተጠሪ ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ተደረገ የሚሉት ስምምነት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ጸድቋል ተብሎ ሊከለከሉ አይገባም ብለናል፡፡ ተጠሪም ስምምነቱ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ጸድቋል ከሚለው ነጥብ በመለስ ይህንኑ ስምምነት መሰረት አድርገው የሚያቀርቡትን ክርክር ይህ ውሳኔ አይከለክላቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ሮ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 86551

መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ብዙነሽ ወ/ሚካኤል - ወኪል ታፈሱ አሰፋ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** እነ አቶ ሽመልስ ቦጋለ - ጠበቃ ተስፋዬ ግዛው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በቅምብቢት ወረዳ ፍ/ቤት ባሁኗ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪዎች ክስም በውርስ የሚገባቸውን የሟች አባታቸውን ቆርቆሮ ቤት የአሁኗ አመልካች ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው የቤቱን ግማሽ ግምት ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) አመልካች እንድትሰጣቸው ወይንም ቤቱን በአይነት እንድታካፍላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም የቤቱ ግምት ያላግባብ ከፍ መደረጉን ቤቱ ሶስት ክፍል ሰርቪስ ቤት ቢሆንም ብር 50,000.00 አያወጣም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም አመልካች የቆርቆሮ ቤቱን የተጠሪዎች አባት ድርሻ ሊያካፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቶ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ስንት ብር እንደሚያወጣ በባለሙያ ተገምቶ በአማራጭ በቀረበው ክስ ግምት ላይ ተመስርቶ ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት ጭብጥ ይዞ ለስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መለሰለት ሲሆን የወረዳ ፍ/ቤትም የሸኖ ከተማ አስተዳደር በባለሙያ እንዲያስገምት ትዕዛዝ ሰጥቶ ይሄው አካልም በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት በባለሙያ አስምምቶ የቤቱ ግምት ብር 93,750.00 (ዘጠና ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) መሆኑን በቁጥር 64/353/2005 በ30/01/2005 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ገልጾለት ፍ/ቤቱ ይህንኑ ግምት ከተቀበለ በኋላ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጎ አመልካች ግምቱ ትክክል አይደለም የሚል ተቃውሞ ያቀረቡ መሆኑን ከመዘገበ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ግምቱን የተቃሙበት ምክንያት በቂ አይደለም የሚል ምክንያት ይዞ በቀረበው ግምት መሰረት ተጠሪዎች የአመልካችን ድርሻ ከፍለው ቤቱን እንዲወስዱ ወይም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እኩል መካፈል የሚቻል ከሆነ እኩል እንዲካፈሉ ወይም ሸጠው ገንዘቡን እኩል እንዲከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ

ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪዎች የቤቱ ግምት ብር 50,000.00 ሆኖ ይህንኑ ግምት በመቃወም በይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታ ያቀረብኩ እኔ ሆኜ እያለና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በእኔ ቅሬታ መነሻ ግምቱ እንደገና እንዲከናወን እንዲደረግና ጉዳዩ እንዲወሰን ትዕዛዝ ሰጥቶ በዚሁ መነሻ በተገኘው የተጋነነ ግምት መሰረት ተቃውሞ እየቀረበ እያለ የወረዳው ፍ/ቤት ግምቱን ከፍ አድርጎ ተጠሪዎች ግምቱን ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ በማለት በቅድሚያ የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም የአመልካች ቅሬታ ዋናውን ውሳኔ መሰረት ያላደረገና በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር መሆኑን ዘርዝረው የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ የተከራከሩ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የተጠሪዎችን ግምት በመቃወም ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ግምቱ እንደገና እንዲገመት ሲደረግ ከፍ በማለቱ በዚሁ ግምት መሰረት ተጠሪዎች ቅድሚያ ቤቱን የማስቀረት መብት እንዳላቸው ተገልፆ ሌሎች የክፍፍል ቅደም ተከተሎች ተጠቅሰው ውሳኔ መስጠቱ ከዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተጠሪዎች የሚጠይቁት የአባታቸውን ድርሻ መሆኑን አመልካች ክርክር ያላቀረቡበት ጉዳይ ሲሆን ተጠሪዎች ንብረቱን በብር 50,000.00 ገምተው ድርሻቸውን ብር 25,000.00 አመልካች እንዲሰጧቸው፣ ይህን ማድረግ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ቤቱን በአይነት እንዲከፋፈሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የወረዳው ፍ/ቤት የቤቱን ግምት ሳያጣራ ክፍፍሉ እንዲደረግ ውሳኔ ሰጥቶ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ የተሰማቸው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የቅሬታቸው መሰረታዊ ነጥብም ቤቱ ብር 50,000.00 ግምት ሊያወጣ አይችልም የሚል የነበረ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ መርምሮ ግምቱ እንደገና እንዲከናወን ማድረጉን፣ በዚህ ውሳኔ መሰረት ግምቱ ሲከናወን ግን ተጠሪዎች መጀመሪያ ገምተው ከአቀረቡት ግምት እጅጉን የላቀ ሆኖ መገኘቱን አመልካች በድጋሚ ግምት ትክክል አይደለም በማለት ቢቃወሙም የወረዳው ፍ/ቤት የአመልካች ምክንያት በቂ አይደለም ከማለት አልፎ ተጠሪዎች በአዲሱ ግምት መነሻ ቤቱን እንዲያስሩ በማለት በመጀመሪያ አማራጭነት መወሰኑን ከክርክሩ ሂደት መረዳት ተችሏል፡፡

በመሰረቱ ክርክር በሚደረግበት ንብረት ላይ የግምት ተቃውሞ ከተነሳ ግምቱ ተጣርቶ ክርክሩ መካሄድ ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 250፣ 136፣ እና ከሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብ ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባው በተጠቀሰው መጠን ሆኖ አግባብነት ባለው ማስረጃ ነጥሮ በታወቀው ውጤት መሰረት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) ድንጋጌ መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ አንድን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍ/ቤት በሕጉ አግባብ ክስ ተሻሽሎ ከፍ ያለ

ዳኝነት ባልተጠየቀበት ሁኔታ በግምት ላይ ተቃውሞ ቀርቦ ግምቱ እንዲጣራ ሲደረግ የንብረቱ ግምት ከፍ ማለቱ በመረጋገጡ ብቻ ቀድሞ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 92፣182(1) ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 225 እና 226 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) ገምተው ድርሻቸውን ብር 25,000.00 በአመልካች እንዲሰጣቸው በመጀመሪያ ደረጃ የጠየቁት ዳኝነት ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ቤቱን በአይነት ልንከፋፈል ይገባል በማለት በሁለተኛ አማራጭ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የቤተሰብ ሕጉንና የውርስ ሕጉን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ የንብረት ክፍፍል ጥያቄቆች ላይ ክፍፍሉን በተመለከተ ውሳኔ ሲሰጥ በሕጉ የተቀመጡ ቅደም ተከተሎች ያሉ ሲሆን ተከራካሪ ወገን ይህንኑ በመተው ክፍፍሉን ሲጠይቅ ግን ሕጉን የማይፃረር መሆኑ ተረጋግጦ በተጠየቀው መሰረት ውሳኔ መስጠት የሚቻል መሆኑን አግባብነት ካላቸው ሕጎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የግምት ይከፈለኝ ጥያቄ በቅድሚያ አማራጭነት ከቀረበ ፍ/ቤቱ የግምቱን ትክክለኛነት አረጋግጦ በተጠየቀው ውሳኔ ቢሰጥ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን የጠበቀ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪዎች የቤቱን ግምት በግልፅ አስቀምጠው ግምቱን አመልካች ተቃውመው እንደገና እንዲገመት በተደረገበት ሁኔታ ግምቱ ከፍ ሲል ይህንኑ ከፍ ያለውን ግምት መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) ድንጋጌን የጣሰ ሆኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች ግምቱ እንዲቀነስ በማሰብ ይግባኝ አቅርበው ተቀባይነት አግኝተው በይግባኙ መነሻ ግምቱ ሲከናወን ከፍ በማለቱ ብቻ ይሄው መሰረት ተደርጎ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የይግባኝ ጽንሰ ሃሳብና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን የሚፃረር ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ተከራካሪ ወገን ይግባኝ የሚያቀርበው መብቱን ለማስፋት እንጂ መብቱን ለማጥበብ ያለመሆኑን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍ/ቤት ዳኝነት መስጠት ያለበት በተጠየቀውና ሕጋዊ በሆነው መጠን መሰረት ብቻ መሆኑን ከይግባኝ አቀራረብና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓቶች የምንገነዘበው ጉዳይ ነውና፡፡ ሥለሆነም የወረዳው ፍ/ቤት በይግባኙ መነሻ የቤቱ ግምቱ ከፍ ሲል ተጠሪዎች በጠየቁት ዳኝነት መጠን ተወስኖ የክፍፍል ውሳኔ መስጠት ሲገባው ይህንኑ በማለፍ ከፍ ብሎ በቀረበው ግምት መሰረት ተጠሪዎች ግምቱን ለአመልካች ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ በመጀመሪያ አማራጭነት መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1)፣ 250 እና ስለይግባኝ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን የጣሰ ሲሆን ይህንኑ ውሳኔ የክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ሳያስተካክሉ ማለፋቸውም የህግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ ሆኖ ስለአገኘን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በቅምብቢት ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 02775 ጥቅምት 22 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 35974 ጥቅምት 27 ቀን 2005 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 157217 ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ ያፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች በቅድሚያ ዳኝነት የጠየቁት ቤቱን በብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር) ገምተው ድርሻቸውን አመልካች እንዲከፍሏቸው በመሆኑ ግምቱ ላይ አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ መሰረት እንደገና በመገመቱና ከፍ በማለቱ ተጠሪዎች ከፍ ያለውን ግምት መሰረት አድርገው ለአመልካች ድርሻቸውን ሰጥተው ቤቱን ያስቀሩ በማለት መወሰኑ ያላግባብ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች የቤቱ ግምት 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) መሰረት አድርገው ግማሹን ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ለተጠሪዎች እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስቀሩ፣ ይህንን ማደረግ የማይችሉ ከሆነ ቤቱን በአይነት እኩል እንዲከፋፈሉ፣ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ቤቱን በስምምነት እንዲሸጡ፣ ካልተቻለም በሀራጅ ተሸጦ የሽያጩን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት አፈፃፀሙን የወረዳው ፍ/ቤት እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ተጠሪዎች በብር 93,750.00 (ዘጠና ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) ላይ በታሪፉ መሰረት የከፈሉት የዳኝነት ገንዘብ እንዲመለስ እንዲያደርግ የስር ፍ/ቤት ታዝዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 79871

የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ የውብዳር ባንቱ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ መአዛ ጥበቡ - ተወካይ አዜብ ጥበቡ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ሎሚ ተሊላ

2. ወ/ሮ ብርቄ ተሊላ

3. ወ/ሮ ትርንጎ ተሊላ

4. ወ/ሮ ቀበኒ ተሊላ

5. አቶ ደሴ ተሊላ

ጠበቃቸው አቶ ብርሃኑ ተሊላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በአሁን የሰበር አመልካቾች የመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢነት በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አቤቱታውም፡- በ04/05/1994 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል አቶ ደሴ ተሊላ ለወ/ሮ የሺ ወ/መድህን የሸጡትን ቤት ወ/ሮ የሺም በ24/07/1994 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ለአመልካቾች ለእያንዳንዳችን አንድ አንድ ክፍል ሸጠውልን ይዘን እያለ በመቃወም ተጠሪዎች ፍርድ ቤቱን በማሳሳትና ባዶ ቦታ በማስመሰል በውርስ የተላለፈልን ነው በሚል የወራሽነት ውሳኔ ያሰጡ ስለሆነ ውሳኔው እንዲሰረዝ ይወሰንልን ብለዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- የሚያከራክረውን ቤትና ቦታ ከሟች አባታችንና እናታችን በውርስ ያገኘነው ነው፣ ወ/ሮ የሺ ወ/መድህን ከወንድማችን ደሴ ተሊላ እንደገዙና አመልካቾችም ከግለሰቧ እንደገዙ በመጥቀስ ያቀረቡት ማስረጃ የሐሠት ነው፤ማስረጃው አለ ቢባል እንኳን በህግ ፊት የሚጸና አይደለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማትና በመመዘን በሰጠው፡- ውሳኔ የግራ ቀኙ ምስክሮች ቤቱ የተጠሪዎች አባት እና እናት መሆኑን ያስረዱ በመሆናቸው በመቃወም አመልካቾች ወ/ሮ የሺ ወ/መደህን ከተባሉት ግለሰብ ገዝተናል ቢሉም ግለሰቧ እነዚህን ሰዎች በመወከል ሊሸጡ አይችሉም፣ እንዲሁም የሽያጭ ውሉ የተመዘገበ ባለመሆኑ በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም፣ ስለሆነም አመልካቾች ከፈለጉ ግለሰቧን በመክሰስ መብታቸውን ከሚያስጠብቁ በስተቀር ለተጠሪዎች የተሰጣቸው የወራሽ ማስረጃ ሊሰረዝባቸው አይገባም በሚል የመቃወም አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

በመቃወም አመልካቾችም በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ ክርክር ያስነሳው ቤት በ1990 ዓ/ም ከመልስ ሰጪዎች እጅ መውጣቱን ከአዳማ ከተማ አስተዳደር እና ከደቤ ሶለቄ ቀበሌ አስተዳደር ከተጻፉት ደብዳቤዎች ከመረጋገጡም ሌላ መልስ ሰጪዎች (በመቃወም ተጠሪዎች) በ26/09/2002 ዓ/ም ለወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ አባታቸው በ1976 ዓ/ም፣እናታቸው ደግሞ በ1990 ዓ/ም መሞታቸውን የገለጹ ሲሆን የወራሽነት ማስረጃውን የያዙት ደግሞ በመ/ቁ/38843 በቀን 28/05/2002 በመሆኑ ማስረጃውን የወሰዱት 10 ዓመት  ካለፈ በኋላ ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤት በቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ ማለፉ ተገቢነት የለውም በሚል መልስ ሰጪዎች የወራሽነት ማስረጃ ያወጡት በፍ/ህ/ቁ 1845 የተደነገገው 10 ዓመት ይርጋ ካለፈው በኋላ ነው ሲል የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

በመቃወም ተጠሪዎች ይግባኝ ጠያቂነት ጉዳዩን የመረመረው የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ በሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ባዮች እናት እጅ የነበረው ቤት ፈርሶ  5ኛ ይግባኝ ባይ (አቶ ደሴ ተሊላ) በቦታው አራት ክፍል ቤት መስራታቸው የተረጋገጠ በመሆኑና ቤቱ ወደ መልስ ሰጪዎች የተላለፈው በ5ኛ ይግባኝ ባይ በመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃውን ይግባኝ ባዮች ያወጡት የ10 ዓመት ይርጋ ካለፈ በኋላ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው በሚል የጠቀሰው ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን የሚነቀፍ አይደለም ሲል አጽንቷል፡፡

በመቃወም ተጠሪዎችም በከፍተኛው እና በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ በሠጠው ውሳኔ፡- ተጠሪዎች አቤቱታ ያቀረቡት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 358 ሲሆን ይዘቱም ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ ለአመልካቾች የተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሻር ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ የሚያቀርብ ሰው ደግሞ መብቱን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣ በከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ ቤት ደግሞ ባለንብረት ለመሆን የባለይዞታነት ማረጋጫ ማስረጃ (ካርታና ፕላን) መኖር ግዴታ ነው፣ይህ በመሆኑ ግዥ እና ሽያጭ መፈጸም ብቻ የቤቱ ባለቤት ማድረግ እንደማይችል የፍ/ህ/ቁ/1185 ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ ተጠሪዎቹ መብት በሌላቸው ንብረት ላይ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358ን ጠቅሰው ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ የሚሆን ነው ሲል የከፍተኛውን እና የክልሉን ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾችም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- የተጠሪዎች አባት ከሞቱ ከ26 ዓመት በኋላ እንዲሁም እናታቸው ከሞቱ 12 ዓመት በኋላ ተጠሪዎች በቦታውና ቤቱ ላይ ወራሽነት ይገባናል በሚል የያዙት የወራሽነት ማስረጃ በፍ/ህ/ቁ/1000(1) እና 1845 የተደነገጉት ይርጋ ጊዜያት ካለፉ በኋላ የተሠጣቸው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በሚል ያቀረብነው የመከራከሪያ ነጥብ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዝምታ ማለፉ ተገቢነት የለውም፤
- ክርክር ያስነሳውን ቤትና ቦታ የተጠሪዎች ወላጆች ከሞቱ በኋላ በ5ኛ ተጠሪ እጅ ገብቶ ተጠሪውም ቀደም ሲል የነበረውን ቤት አፍርሶ በአዲስ መልክ ሰርቶ ለወ/ሮ የሺ ወ/መድህን የሸጠ ሲሆን ግለሰቧም አስፋፍታ ግንባታዎችን በማካሄድ በጽሁፍ በተደረገ የሽያጭ ውል ለአመልካቾች ሽጣ እያለ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ወጪ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት የፍሬ ነገር ጉዳዮችን ለማጣራት ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ካርታ እና ፕላን በተመለከተ ክርክር ያልተነሳውን በራሱ ጊዜ በማንሳት የከፍተኛውንና የክልሉን ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- የሚያከራክረው ቤትና ቦታ የወላጆቻችን የነበረ ሲሆን ወላጆቻችን በሞት ከተለዩ በኋላ በእጃችን የሚገኝ ሆኖ እያለ አመልካቾች በሽያጭ አግኝተው በእጃቸው መግባቱን በመጥቀስ በሐሰት በተቀነባበረ ማስረጃ የሚከራከሩ ቢሆንም የሽያጭ ውሉ አመልካቾች እንደሚሉት ተፈጽሟል ቢባል እንኳን የጋራ የውርስ ንብረት አንዱ ወራሽ ብቻ አደረገ በተባለው የሽያጭ ውል መነሻ ሌሎች ወራሾች የመውረስ መብታችንን የምናጣበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፤እንዲሁም ተጠሪዎች የውርስ ንብረት ይለቀቅልን በሚል ያቀረብነው ክስ በሌለበት የይርጋ ክርክር ሊነሳ የማይችል ከመሆኑም ሌላ ይርጋን መከራከሪያ ሊያደረግ የሚችለው ተከሳሽ የሆነ ወገን እንጂ ከሳሽ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾችም ተጠሪዎች ለሠጡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት ሊቀርብ የሚገባ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካቾች ካቀረቡት ክርክር መረዳት የተቻለው ተጠሪዎች ወላጅ አባታቸውና እናታቸው በሞት የተለዩ መሆናቸውን በመግለጽ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለፍርድ ቤቱ አመልክተው ወራሽ ናቸው በሚል በተሰጠ ውሳኔ መነሻ የውርስ ሀብት ነው በሚል በግዥ ያገኘነውን ቤት ስለያዙ የተሰጣቸው ማስረጃ እንዲሠረዝባቸው ሲሉ መጠየቃቸውን ነው፡፡

በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው በክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው ወይም ጠበቃው ወይም ነገረ ፈጅ መሆኑን ከድንጋጌው መረዳት የሚቻል ሲሆን መቃወሚያውም ሊቀርብ የሚገባው ለመቃወሚያው መሰረት የሆነው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የሟች እናታቸው እና አባታቸው ወራሾች መሆናቸው እንዲወሰንላቸው ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት

ወራሾች ናቸው በሚል በመ/ቁ/38843 በቀን 28/05/2002 ዓ/ም ፍርድ/ውሳኔ የተሠጠ መሆኑን መዝገቡ ያመላክታል፡፡ በዚህ በተጠቀሰው መዝገብ ተጠሪዎች ወራሾች ስለመሆናቸው ባቀረቡት አቤቱታም ሆነ በሚደረገው ክርክር እንዲሁም በሚሠጠው ፍርድ ወይም ውሳኔ የሚያከራክረውን ቤት ስለገዛን ፍርዱ ወይም ውሳኔው መብታችንን ይነካል በሚል ምክንያት የተጠሪዎች የወራሽነት ማስረጃ እንዲሠረዝባቸው አመልካቾች መቃወሚያ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ህጋዊ ሁኔታ አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪዎች የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ከጠየቁት ዳኝነትም ሆነ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር አመልካቾች የውርስ ሀብቱን በሽያጭ ውል አግኝተናል በሚል ያቀረቡት የንብረት መብት ጥያቄ የሚገናኝ ባለመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በሚያከራክረው ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉ ከሆነ ተገቢውን ዳኝነት ክፍለው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው መብታቸውን ከሚጠይቁ በስተቀር በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 358 መሰረት የፍርድ/የውሳኔ መቃወሚያ ሊያቀርቡ አይገባም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት ሊቀርብ የማይገባውን መቃወሚያ ተቀብለው በማከራከር ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ ባይሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጡትን ውሳኔ በመሻር የመቃወሚያ አቤቱታቸውን ውድቅ ያደረገው በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/131390 በቀን 06/09/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ውሳኔ ምክንያቱን ለውጠን በውጤት ደረጃ በመቀበል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካቾች የውርስ ሀብት የሆነውን የሚያከራክረውን ቤትና ቦታ በግዥ ስላገኘን ለተጠሪዎች የተሠጣቸው የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልን ሲሉ ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት ሊቀርብ የሚገባ አይደለም ብለናል፡፡ ይህ ውሳኔ አመልካቾች ለሚያከራክረው ንብረት ተገቢውን ዳኝነት ከፍለው መብታቸውን በሚጠይቁት ወገን ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ አቅርበው መብታቸውን ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይሆንም ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ት/ዘ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 80202

የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ሐጎስ ሽጎዕ የቀረበ የለም } መቀሌም በፕላዝማ አልቀረበም

2. አቶ ተስፋዬ ጥጋቡ ሽጎዕ የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የመሸነ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከቦታ ማስለቀቅ ጋር ተያይዞ የተነሳ የካሳ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁኖቹ አመልካቾች በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ ተከሳሽ በሚተዳደርበት የከተማ ቦታ ኪራይ ደንበ መሰረት ለሆቴል አገልግሎት የሚውል 3250 ካ.ሜ ቦታ ለ1ኛ ከሳሽ እና የ2ኛ ከሳሽ አባት ለሆኑት ለአቶ ጥጋቡ ሽጎዕ በውል ሰጥቶ እንደነበረ በዚሁ ቦታ ላይ ግንባታውን በከፊል አከናውነው ከፊሉ ደግሞ በግንባታ ኦዲት ላይ እያለ ተከሳሽ አቅም ስለሌላችሁ ቦታውን አስረክቡ በማለት በ18/05/01 በተፃፈ ደብዳቤ እንዳስታወቀቸው እነርሱም ጉዳዩ የተጓተተው በአቶ ጥጋቡ ሽጎዕ ሞት ምክንያት ከውርስ ማጣራት ጋር ተያይዞ መሆኑን ለተከሳሽ እንደገለጹ እና በተጠየቁት መሰረት የፋይናንስ አቅማቸውን የሚያመለክት ማስረጃ ለተከሳሽ እንዲያቀርቡ ለግንባታው ከብር አንድ ሚሊዮን በላይ ወጪ እንዳደረጉና ተከሳሽ ተገቢውን ምላሽ ሊሰጧቸው እንዳልቻሉ የሚገለፅ ሆኖ በሂደት እያለሙት የነበረውን ቦታ ተከሳሽ እንዲመልስላቸው የማይመልስ ከሆነ ደግሞ ያወጡትን ወጪ ብር አንድ ሚሊዮን ከተዛማጅ ወጪዎች ጋር እንዲመልስላቸው ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት የተጠየቀባቸው ነው፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ የቦታ ማስለቀቅ እና የካሳ ጉዳይን ፍ/ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ማየት ስለማይችል መዝገቡን ዘግቶ ያስናብተን በማለት መቀወሚያ ከቀረበ በኋላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሳሾቹ ሆቴል እና የነዳጅ ማደያ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ገንብተው አገልግሎት ላይ ለማዋል ውል ገብተው ቦታውን በ1994 ከተረከቡ በኋላ እስከ 1999 ዓ.ም ደረስ የተወሰኑ ክፍሎችን ከመስራት በስተቀር በገቡት ግዴታ መሰረት ግንባታውን አጠናቀው ስራ ላይ ባለማዋላቸው በ1999 ስራውን እንዲያቆሙ እንደታዘዙ እና ቀጥሎም

እንዲያስረክቡ እንደተደረገ ይህ እርምጃም የተወሰደው ለከተማ አስተዳደሩ በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንደሆን እና ቦታው በጨረታ ለሌሎቹ ባለሀብቶቹ ሊተላለፍ እንደሆነ በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡

ፍ/ቤቱም መቃወሚውን ውድቅ አድርጎ የግንባታው ዋጋ በባለሙያ እንዲገመት ካደረገ በኋላ ተከሳሽ የግንባታውን ወጪ ብር 618,815.93 ለከሳሾች ይክፈል ከዚህ በኋላ ቦታውን ከነግንባታው ይረከብ በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ሁለቱም ወገኖች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የመረመርው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው የከተማ ቦታን በኪራይ ስለመያዝ እንደገና ለመደንገግ በክልሉ በወጣው ደንብ ቁጥር 19/1995 አንቀጽ 13/2/ መሰረት የቦታ ማስለቀቅ እና የካሳ ክፍያ ጉዳይን በመጀመሪያ ደረጃ ለማየት የሚያስችል ስልጣን ሳይኖው ነው በማለት ውሳኔውን በሁለቱም መዝገቦች የሻረው ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ ዘግቶ አስናብቶአል፡፡

አመልካቾች አቤቱታ ያቀረቡት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት ሲሆን ይህንኑ ክርክራቸውን በ12/11/04 አዘጋጅተው ባቀረቡት የተሻሻለ አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠው በሌለው ስልጣን ነው ተብሎ በበላይ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት በክርክሩ ከተጠቀሰው ደንብ ቁጥር 19/1995 አንቀጽ 13/2/ አንፃር ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ለማየት ስልጣን ሳይኖረው ነው በሚል የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የሰጠው ውሳኔ እና ከዚህ ውሳኔ የቀረበለትን አቤቱታ ዘግቶ በማስናበት የጠ/ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ከላይ እንደተጠቀሰው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ጉዳይ በይግባኝ ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ በፍ/ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ለሰጡት ውሳኔ መሰረት ያደረጉት የከተማ ቦታን በኪራይ ስለመያዝ እንደገና ለመደንገግ በክልሉ የወጣውን ደንብ ቁጥር 19/1995 ሆኖ በተለየም የደንቡን አንቀጽ 13/2/ ድንጋጌ ነው፡፡ ተጠሪው ይዞታውን ለአመልካቾቹ በኪራይ የሰጠው ሆቴል እና ነዳጅ ማደያ ገንብተው በሁለት ዓመት ውስጥ አገልግሎት ላይ እንዲያውሉ ግዴታ በማስገባት መሆኑ እና የተጀመረውን ግንባታ አቁመው ይዞታውን እንዲያስረክቡ ያደረገው ደግሞ ግንባታውን በተባለው ጊዜ አጠናቀው አገልግሎት ላይ አለማዋላቸውን እና የአቅም ውስንነት የታየባቸው መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ መሆኑ በክርክሩ ተረጋግጦአል፡፡ የተጠሪ እርምጃን በመቃወም በመሆኑ የደንቡ አንቀጽ 13 ድንጋጌ በተያዘው ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆን አለመሆኑ ሊጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ በመሰረቱ ደንቡ የሚደነግገው ሁለቱ ጉዳዮችን ነው፡፡ የመጀመሪያው አስተዳደሩ የከተማ ቦታ በኪራይ ስለሚሰጥበት ሁኔታ እና ከኪራይ ይዞታ ጋር ተያይዞ በአስተዳደሩ እና በኪራይ በለይዞታዎች መካከል ስለሚኖረው አጠቃላይ ግንኙነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የከተማ ቦታን ስለማስለቀቅ ሆነ ቦታ እንዲለቁ በሚደረጉ ባለይዞታዎች እና በአስተዳደሩ መካከል ስለሚኖረው አጠቃላይ ግንኙነት ነው፡፡ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የከተማ ቦታውን እንዲለቅ የማስቀለቀቂያ

ትዕዛዝ የተሰጠው ባለይዞታ በማስለቀቅ ትዕዛዙ ላይም ሆነ በክሳ ጉዳይ ላይ ቅሬታ የሚኖረው ከሆነ የዚህ ዓይነቱ ቅሬታ የሚስተናገድበትን ስርዓት ጨምሮ ከቦታ ማስለቀቅ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በደንቡ ተደንግገው የሚገኙት ከአንቀጽ 13 ጀምሮ ነው፡፡ የደንቡ አንቀጽ 13/2/ የሚደነግገውም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የከተማ ቦታን ከማስለቀቅ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቅሬታዎን በቀጥታ ለፍ/ቤት ክስ ሊቀርብባቸው የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾቹ ቦታውን እንዲያስረከቡ ተጠሪ የወሰነው ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ተፈልጉአል በማለት ሳይሆን አመልካቾቹ በገቡት ግዴታ መሰረት ግንባታውን በተገቢው ጊዜ አጠናቀው ለአገልግሎት አላበቁም የፋይናንስ አቅም ችግርም ታይቶባቸዋል በማለት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በደንቡ ከአንቀጽ 13 እስከ 16 ያሉት ድንጋጌዎች በጉዳዮ ላይ ተፈፃሚ ሊደረጉ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም፡፡ የተያዘው ጉዳይ የኪራይ ይዞታ ማቋረጥን የሚመለከት በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ደንቡ አንቀጽ 10 እና 11 ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ደግሞ የኪራይ ይዞታ ማቋረጥን አስመልክቶ አስተዳደሩ በሚወስዳቸው እርምጃዎች ላይ ባለይዞታው ቅሬታ ሲያድርበት ጉዳይ ሊታይ ስለሚችልበት የደኝነት መድረክ የሚገልጹት ነገር የለም፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ሊወስን የሚገባው እስከሆነ እና ጉዳዩን ለማየት በሕግ በግልጽ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ሌላ አካል እስከሌለ ደረስ ደግሞ አመልካቾቹ ጉዳያቸውን በቀጥታ ለፍ/ቤት አቅርበው ፍትሕ ከማግኘት የሚታገዱበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ የኢ.ፊ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 37/1/ እና 79/1/ እንዲሁም የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 4 ድንጋጌዎችም ይህንኑ የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩ በቀጥታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ አይችልም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መስረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የት/ብ/ክ/ከመንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 47481 በ04/04/04 እና በመ/ቁ 47436 በ04/04/04 የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 49966 በ03/08/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ጉዳዩ በቀጥታ ለፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት የሚችል መሆኑን እና የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን አስተናግዶ ውሳኔ የሰጠው በዚሁ አግባብ መሆኑን በመገንዘብ ሁለቱን የይግባኝ መዝገቦች አንቀሳቅሶ በዋና ጉዳይ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341/1/ መሰረት ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 83915

የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ዩሐንስ በቀለ ጠበቃ መረሣ ፍስሃ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት 1. ዐ/ህግ ታመነ ታደሰ ቀረቡ

2. ዐ/ህግ ኬሮ ወ/ሚካኤል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የከተማ ክልል ይዞታ ለማስለቀቅ የተወሰደውን እርምጃ በመቃወም ለፍርድ ቤት የቀረበ ክስ ተጠሪ ሳይጠራ ውድቅ በመደረጉ ምክንያት የቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በከፋ ዞን ቦንጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ በቦንጋ ከተማ ካላቸው ይዞታ ውስጥ ተጠሪ ትርፍ ይዘሃል በሚል ምክንያት እንዲለቁ እያደረጋቸው መሆኑን ጠቅሰው ይህንኑ እንቅስቃሴ ተጠሪ በፍርድ ኃይል እንዲያቆሙ እንዲደረግላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአሁኑ ተጠሪ ሳይጠራ የአመልካች ክስ በትርፍነት የያዙትን ቦታ እንዲለቁ ሲጠየቁ ይህንኑ ለማድረግ አልችልም በሚል የቀረበና ከማዘጋጃ ቤቱ ስልጣን ውጪ ነው በሚል ምክንያት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸው ለከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ሳይጠራ አመልካችን ብቻ በመስማት ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ንብረታቸው ከሕግ ውጪ መውደሙን ቤት፣ ቡና፣ አታክልት፣ ባህር ዛፍ፣ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል ይህንን ያጠፋው ማዘጋጃ ቤቱ ነው ከስር ክሱን ንብረቱን ገምቼ አላቀረብኩም ከስር የከሰስኩት በሁከት ይወገድ ነው የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አላይም በማለት የዘጋው ያላግባብ ነው እየተጠየቀ ያለው በህጋዊ መንገድ ሰርቼ ላገኘሁት ግምት ሊከፈለኝ ይገባል ብዬ ነው በማለት ጉዳዩን አመልካች እንዳብራሩት በመመዝገብ ይግባኛቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ዘግቶባቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ጠርተው ጉዳዩን በማስረጃ ሳያጣሩ መዝጋታቸው



www.chilot.me

ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጉለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ሳይጠሩ የአመልካችን ክስ መዝጋታቸው ስነ ስርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለው በጭብጥነት የሚታይ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ በሁከት ይወገድልኝ ስለመሆኑ በይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስመዘገቡ ሲሆን በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ደግሞ በንብረት ግምት መሰረት የካሳ ይከፈለኝ ክስ ሳያቀርቡ ጥያቄአቸው ለንብረታቸው ካሳ ይከፈለኝ በማለት አቤቱታ እያሰሙ ያሉ መሆኑን ያረጋገጡ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ክስ ለፍርድ ቤት የሚያቀርብ ሰው ክሱን የሚያቀርበበት ስርዓት በሕጉ የተዘረጋ ሲሆን ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሌላኛውን ወገን ከመጥራቱ በፊት ክሱ ህጋዊ ፎርማሊቲ ያሟላ መሆን ያለመሆኑ መመርመር ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33፣80፣222፣225፣226፣ እና 231 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በህጉ መሰረት ያልቀረበ ክስ ተከሳሽ የሆነውን ተከራካሪ ወገን መጥራት ሳያስፈልግ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ መኖሩን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በህጉ አግባብ መቅረቡ ከተረጋገጠ ደግሞ የግራ ቀኙ የመስማት መብት በሕጉ አግባብ መጠበቅ ያለበት መሆኑን 223፣234፣241 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ክስ ሲመሰርቱ ትርፍ ቦታ መያዛቸውን ተረድተው ለመልቀቅ ፈርመው ለማዘጋጃ ቤቱ ማሳወቃቸውን የከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን ይህም በትርፉ ቦታ ጥቅም ወይም መብት የሌላቸው መሆኑን በመነሻነት የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ቦታውን ልለቅ አይገባም ሲሉ ቆይተው ጥያቄአቸው የካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ መሆኑን በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አረጋግጠዋል፡፡ የካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ ደግሞ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 225 መሰረት የዳኝነት ተከፍሎበት ያልቀረበ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካች የክስ አቀራረባቸውን በሕጉ በተዘረጋ ስርዓት መሰረት አስተካክለው ሳያቀርቡ ወጥነት በሌለው አኳኋን የጠየቁትን ዳኝነት እየቀሩ የመሰማት መብቴ ሳይከበር ክሴ ተዘግቷል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ የዘጉት አግባብ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/፣222፣225፣226 እና 231/1/ሀ// አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ባለመሆኑ በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ትዕዛዝ በማጽናት በመ/ቁጥር 50332 ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች ክስ ውድቅ የተደረገው የክስ አቀራረብ ሰርዓቱን አሟልቶ ባለመቅረቡ በመሆኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ሕጋዊ መብታቸውን መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት የካሳ ክፍያ ጥያቄ ካለ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/ጥ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 42501

የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ታደሠ ታፈሠ ቀረበ

ተጠሪ ፡- የአስር አለቃ ደምሴ ዳምጤ ወራሾች (ሶስት ሰዎች) - ለራሣቸውና ለሌሎች ወኪል - ደጀኔ ደምሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት መፋለም ክስ በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከታየና የመጨረሻ ፍርድ ካረፈበት በኃላ ጉዳዩ ለአፈፃፀም ተይዞ ባለበት ሁኔታ ለፍርዱ መሠረት የሆነውና በአስተዳደር አካሉ የተሰጠ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በአስተዳደር አካሉ ሲመክን በፍርድ አፈፃፀም ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን ሕጋዊ ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የተያዘውና ለአሁኑ ክርክር መነሻ በሆነው የአፈፃፀም ጉዳይ የፍርድ ባለመብቶች የሆኑት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ አመልካችና አቶ ክፍሉ ዮሴፍ የፍርድ ባለእዳ ነበሩ፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ባሁኑ አጠራር በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 305 የሆነውን ቤት ፍርድ ያረፈበት መሆኑን ጠቅሰው ቤቱን በፍርድ ሃይል እንዲረከቡ ትእዛዝ እንዲሰጣቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፍርድ ባለእዳነት ቀርቦ በሰጠው መልስ የቤቱ ደብተር መሰረዙን ገልፆ የሚፈፀም ውሣኔ የለም ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካችን ምክንያት ባለመቀበል ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የፍርድ አፈፃፀም ትእዛዝ የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀረብም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የተጠሪዎች የባለቤትነት ደብተርና ካርታው ተሰርዟል፣ ፍርዱ ሊፈፀም የሚችል አይደለም የባለቤትነት ማረጋገጫው የተሰረዘበትን ደብዳቤ እስካላሻሩ ድረስ ቤቱን ልናስረክብ አይገባም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 280 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ የባለቤትነት ማረጋገጫው ደብተር ተሰርዟል እየተባለ አመልካች ቤቱን ሊያስረክብ ይገባል ተብሎ የመታዘዙን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀረበው መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪዎች በጽሑፍ በሰጡት መልስም የባለቤትነት ማስረጃውን አምክኗል የተባለው ደብዳቤ ከዚህ ቀደም በነበረው ክርክር ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቀርቦ ክርክር ተደርጎበት ውድቅ መደረጉን የመሬት ልማት አስተዳደር መምሪያው ማስረጃውን ያመከነው አምኖበት ሣይሆን ፍትሕ ሚኒስቴር በሕግ ከተሰጠው ስልጣን ውጪ ባስተላለፈው ትእዛዝ መሰረት መሆኑን ጉዳዩ እስከ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ውሣኔ ካረፈበት በኃላ ሊሻር፣ ሊሻሽል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች በአፈፃፀም ጉዳይ የሰጡት ትእዛዝ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም አመልካች የባለቤነት ማረጋገጫ ደብተሩ ተሰርዟል በማለት የሚያቀርበው ምክንያት እንደ ፍርዱ ላለመፈፀም የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክር መሠረት የሆነው ቤት ተጠሪዎች ሕጋዊ ባለቤትነታቸው በፍርድ ቤት ውሣኔ ተረጋግጦላቸው እንዲረከቡ እስከ የአገሪቱ የመጨረሻ የዳኝነት አካል ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደርሶ የሰበር ችሎቱ የመጨረሻ ዳኝነት ያሰረፈበት መሆኑን ተጠሪዎች ክርክሩ በዚህ አግባብ የመጨረሻ መፍትሔ ከአገኘ በኃላ የፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ እንዲፈጸምላቸው የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው ተገቢውን መዝገብ በሕጉ አግባብ ከፍተው አመልካች እንደ ፍርዱ እንዲፈጽም የማይፈጽምበት ሕጋዊ ምክንያት ካለም ቀርቦ እንዲያስረዳ ሲደረግ አመልካች ፍ/ቤት ቀርቦ እንደ ፍርዱ ላለመፈፀም ያቀረበው ምክንያት ለፍርዱ መሠረት የሆነውና የተጠሪዎችን የባለቤትነት መብት የማያረጋግጠው ደብተር በአስተዳደር አካሉ ከፍርድ ቤቱ ውሣኔ በኃላ መክኗል የሚል መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈፀም ያለበትም ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በተዘረጋው ስርዓት አግባብ በመመራት ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሌላ አካል ዋጋ የሚያጣበት አግባብ አይኖርም፡፡ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያስገነዝቡት አቢይ ነጥብ የፍርድ አፈፃፀም ስርዓት ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለወጥበት ሥርዓት መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ ሲታይም የፍርድ አፈፃፀም ስለፍርድ አፈፃፀም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርዱን በተግባር መተርጐም እንደመሆኑ መጠን የአፈፃፀም ስርዓቱ ሕጉን መሠረት ማድረግ ያለበት እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉን መሠረታዊ አላማ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአንስተኛ ወጪ ጊዜና ጉልበት በተፋጠነና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም በሚያስችል አግባብ ሕግ አውጪው ያስቀመጣቸው መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

እንዲሁም በሕግ አግባብ የተሰጠ ፍርድ ዋጋ እንዳይኖረው የሚደረግው የዳግም ዳኝነት ወይም የፍርድ መቃወሚያ ጥያቄ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ቀርቦ ከታየና ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ስለመሆኑ ከፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 እና 358 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አንድ የአስተዳደር አካል በፍርድ ቤት ክርክር መረታቱን ከተረዳ በኃላ በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን መነሻ በማድረግ ለፍርዱ መሰጠት መሠረት የሆነውን ማስረጃ ዋጋ በማሣጣቱ ምክንያት የፍርድ አፈፃፀም ዋጋ እንዲያጣ የማድረግ ውጤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78/1/ እና 79/1/ እና /4/ ስር የተረጋገጠውንና የተከበረውን የነፃ ፍርድ ቤት መኖርንና የዳኝነት ስልጣን ትርጉም

አልባ የሚያደርገው ነው፡፡ ይህ ብቻ ሣይሆን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ሥር የተረጋገጠው የዜጎች ፍትህ የማግኘት መብትም ውጤት ባለው መልኩ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ጠባብ እንዲሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ክርክሮች መቋጫ እንዳይኖራቸው የሚጋብዝ የፍርድ ቤትን ጊዜ ጉልበትና በጀት ለብክነት የሚዳርግ እንዲሁም ሕዝቡ በፍርድ ቤት አመኔታ እንዳይኖረው የሚያደርግ ነው፡፡ የነፃ ፍርድ ቤት መገለጫው ደግሞ የሕግ የበላይነት መኖሩና መረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ውጤታማ የሚሆነው አንዱ የመንግሥት አካል ሌላኛውን ሲቆጣጠረው ከመሆኑ በተጨማሪ ፍርድ ቤት የራሱን ውሣኔ ዋጋ የማያሣጣና የሕግ መሠረት የሌለውን የአስተዳደር አካል እርምጃ ውድቅ ሲያደርገው መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ፍርድ ቤት በሕገ መንግስቱ አንዱ የመንግስት አካል እንደመሆኑ መጠን የመንግስት የስልጣን አጠቃቀም የተወሰነና የተገደበ መሆኑ ሊያረጋግጥ እንደሚገባ ይህ ሊከወን ከሚያስችሉት መንገዶች አንዱ ደግሞ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ትርጉም እንዲኖረው በማድረግ ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱ ስለፍርድ ቤቶች ስልጣን ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እና በአገሪቱ የሕግ አካል ከሆኑ አለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ ከሰፈሩት መርሆዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ከላይ እንደተጠቀሰው ሕገ መንግስቱ ከተመሠረተባቸው መርሆች አንዱ የሕግ የበላይነት ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱ መግቢያው ላይ የሰፈረ ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤት ለሁሉም ወገኖች እኩል ተፈፃሚነት ባለው ሕግ መመራት ያለበት ስለመሆኑም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 25 እና 13/1/ ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ በማየት መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሕግ አግባብ የተቋቋመ ፍርድ ቤት አከራክሮ መወሰን ብቻ ሣይሆን የወሰነው ውሣኔ ውጤት ባለው መልኩ ወደ ተግባር መለወጡን ጭምር ማረጋገጥ አብይ ሀላፊነትና ተግባር በመሆኑ ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ስልጣን አንድ የመንግስት አካል የሚዘረጋው አሠራር ወይም የሚወስደው እርምጃ በፍርድ ቤቶች የፍርድ ስርዓት ላይ /በዳኝነት አካሉ ላይ/ የሚያመጣው ውጤት በሕግ የተመሠረተና የሚገዛ ስለመሆኑ ማየት የግድ ይላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድ የአስተዳደር አካል የቤት ባለቤትንት ማስረጃ በፈለገው ጊዜ ከሕግ ውጪ እንዲሰረዝ ማስቻል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1ና2/ ድንጋጌ ሥር የተከበረውን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሣጣው ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲነበቡም የአስተዳደር አካል በባለቤትን ማረጋገጫ ማስረጃ አሰጣጥ ላይ ፍጽም የሆነ አስተዳደራዊ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ አያሣዩም፡፡ ይልቁንም ድንጋጌዎች እርስ በእርሣቸውም ሆነ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1198 ድንጋጌ ጋር ተዛምደው ሲታዩ የባለቤትን ማረጋገጫ ደብትር የሚሰርዘው በሕጉ በተመለከቱት ምክንያቶች ብቻ መሆኑን ከሕጉ ውጪ ተግባሩ ተከናውኖ ከተገኘም መብቱ የተነካው ሠው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣78 እና 79 ድንጋጌዎች መሠረት ጉይዩን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ አቤቱታው እንዲታይለት የሚያርግበት ጉዳይ እንጂ አስተዳደር አካሉ የሰጠው ውሣኔ በፍርድ ቤት እንዳይታይ የሚገደብበት ስርዓት የሌለ መሆኑን የምንገነዘበው ነው፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ቀድሞ በፍርድ ቤት በነበረው ክርክሩ ተሣታፊ ሁኖ በፍርድ ኃይል ከተረታ በኃላ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሕጉ አግባብ እንዳይፈጽም በሚል እሣቤ በዋናው ክርክር ጊዜ የተጠሪ ባለቤትነት የተረጋገጠበትን ማስረጃ በመሠረዝ ፍርዱን አከራካሪውን ቤት አላስረክብም ማለቱ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የአመልካች ክርክር ውድቅ በማድረግ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64032 ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75215 ታህሣስ 24 ቀን 2001 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ቀድሞ የክርክሩ ተሣትፊ ሁኖ እስከ በላይ ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ተረቺ መሆኑ ከተረጋገጠ በኃላ ለቀድሞው ውሣኔ መሠረት የሆነውን የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በማምከን አዲስ ክስ የሚመሰርትበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 82234

የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ አየለ መኮንን /ከጠበቃ አቶ ምናሴ ዘሪሁን ጋር ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ ወ/ሮ ጦቢያው ወንድም ገዛው

2ኛ ወ/ሮ ውቢት በየነ

3ኛ አቶ ብሩክ በየነ

4ኛ ወ/ት ሰናይት በየነ

5ኛ ወ/ት እጥፍወርቅ በየነ

6ኛ ወ/ት መሰረት በየነ

} 5ኛ ተጠሪ እና የሁሉም ጠበቃ አቶ አበበ ማስረሻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ግራ ቀኙን ካከራከረው ጉዳይ አንፃር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231/1/ሀ/ የተመለከተው ስነ ሥርዓታዊ ድንጋጌ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ለማየት ሲባል ነው፡፡

የአሁን አመልካች በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ የጉዳዩ መነሻ ሲሆን የዚህም ክስ ይዘት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 696 የሆነው ቤት  አካል የሆነውን  ሰርቪስ ቤት ከ2ኛ እስከ 6ኛ ተራ ቁጥር ከተጠቀሱት ተጠሪዎች አባት ከአቶ በየነ ወልደሚካኤል እና ከባለቤታቸው ከአሁን 1ኛ ተጠሪ ጋር ህዳር 27 ቀን 1990 ዓ.ም ባደረግነው የሽያጭ ውል ገዝቼ ተረክቢያለሁ ሻጮችም ቀደም ሲል ቤቱን የገዙበትን ውል እና የግብር ደረሰኝ አስረክበውኛል፡፡ በቤቱም ላይ ያለውን ካርታ ተከታትዬ እንዲሰጣቸው አድርጌያለሁ አስረከቢያቸዋለሁ፡፡ ሆኖም ከዚህ በፊት በሽያጭ ውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት በገዛሁት ሰርቪስ ቤት ላይ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጠኝ ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆኑም ስለሆነም የገዛሁት ሰርቪስ ቤት  ስመ ሀብትነት በስሜ እንዲዞር ተከሳሾች ስመ ሀብትነትን በሚያዛውር አካል በመቅረብ የመለያ ውል በመፈረምና አስፈላጊ ሰነዶችን ይዘው በመቅረብ ሰመ ሀብቱ እንዲዛወር ያደርጉ ዘንድ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎችም በመካከላችን የተደረገ የሽያጭ ውል የለም፡፡ ቢኖርም እንኳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2879 መሰረት ቤቱንና ሰነዶችን ለገዥ ማስረከብ እንጂ ውል እንድንዋዋል አንገደድም፡ ፍ/ቤቱም ውል ተዋዋሉ ብሎ ውሣኔ

ለመስጠት አይችልም፡፡ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም የሚለውን ክርክር ካስቀደሙ በኋላ ስለዋናው ጉዳዩም ዝርዝር መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባቱ በፊት በአሁን አመልካች አማካኝነት የቀረበው ክስ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ መስርቶ እና ጉዳዩን ተመልክቶ በኮ/መ/ቁ 37513 በሆነው በቀን 25/7/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሳሽ የጠየቁት ዳኝነት ተከሳሾች የሸጡልኝን ቤት ካርታ እና የሽያጭ ውሉን በክ/ከተማው መሬት አስተዳደር በማቅረብ የመለያያ ውል እንዲፈርሙ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ሆኖም ውል  በሁለት ተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ የሚቋቋም እንጂ ሁለቱም ቀርበው ውል ሊያደርጉ ይገባል በሚል ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የሚደረግ አይደለም፡፡ ከሳሽ በጠየቀው ዳኝነት መሰረት የሚሰጠው ውሣኔ ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሣኔ መሠረት የሚደረግ አይደለም ከሳሽ በጠየቀው ዳኝነት መሰረት የሚሰጠው ውሣኔ ፍ/ቤት ለሁለት ወገኖች ውል የመፍጠር ያህል ውጤት የሚያስከትል ስለሆነ ጥያቄው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1679 ከተመለከተው ደንጋጌ ዓላማ ውጭ ሆኖ ስለተገኘ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም በማለት በይኗል፡፡

ይግባኙን የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ የአሁን ተጠሪዎቹን መጥራት ሳያስፈልገው ይግባኙን ሰርዞ የአሁን አመልካችን ያሰናበተ የመጨረሻ ዳኝነት በመስጠቱ በዚህ የመጨረሻ ዳኝነት የቀረበ የሰበር ጉዳይ ነው፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ የሰበር ደረጃ በየፊናቸው ያላቸውን የጽሁፍ ክርክር ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ብይኑን በሚመለከት በየግላቸው ያቀረቡትን ክርክር የያዘ ከመሆኑም በላይ የዋናውን ጉዳይ ዝርዝር ክርክርንም ሁሉ አካቶ መያዙን የሚያሳይ ነው፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የአሁን አመልካች በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብት የለውም በሚል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዳኝነት አግባብነት ለግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ይዘት እና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

አመልካቹ ባቀረበው ክስ ላይ ግራ ቀኙ ካደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የመነጨ በተሸጠው ንብረት ላይ መብት አግኝቻለሁ በዚሁ ባገኘሁት መብት መገልገል እችል ዘንድ ሻጭ በሸጠው ነገር ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት ለገዥው ለማስተላለፍ በህግ ይገደዳል ስለሆነም የእኔ እና የሻጩ መብትና ግዴታ ታይቶ ሻጭ የሚጠበቅበትን ግዴታ እንዲወጣ ይወሰንልኝ የሚል፤የአሁን ተጠሪዎችም ለአሁን አመልካች መብት ከእኛ ላይ ደግሞ ግዴታ ሊፈጥር የሚችል ህጋዊ ተግባር አልፈፀምንም የቤት ሽያጭ ውል አላደረግንም አድርገናል እንኳ ቢባል የእኛ የግዴታ ውሉን ከሳሹ የሚለውን ሁሉ አይጨምርም በከሳሹ የተጠየቀው ዳኝነት በእኛ አማካኝነት የሚፈፀም አይደለም ከሚለው ጀምሮ በህግ ረገድ ግዴታ ሊፈጥር የሚችል ከከሳሹ ጋር የፈጠሩት  ግንኙነት ሁሉ እንደሌለ ገልፀው የተከራከሩበት ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች በየቅላቸው ያቀረቡት ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ እንደተደነገገው ከውል ወይም ከህግ የመነጨ መብትና ግዴታ ያለ መሆኑን ለማመልከት የሚያበቃ ክርክር እንዳቀርቡ አስረጂ ነው፡፡ ይህ መብትና ግዴታ በእርግጥም አለ ወይስ የለም በክርክር ሂደት የሚረጋገጥ ነው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማው በዋናው ህግ የተቀመጡትን መብትና ግዴታዎች ወደ ተግባር ለመለወጥ እንዲያስችል ታስቦ የተዘረጋ ስርዓት እንደመሆኑ መጠን በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት



www.chilot.me

ተሰይመው ለመከራከር በቅድሚያ ክርክሩ ቀጥሎ እንደ ክርክራቸው ሁለቱም ወገኖች በማስረጃ አስደግፈው ቢያስረዱ ለህግ ወይም ከውል የመነጨ መብትና ግደታ ያላቸው መሆኑን ለማመልከት በሚያስችል ደረጃ ክሱ ተብራርቶ እና ተዘጋጅቶ መቅረብ እንዳለበት በሚያስገነዝብ አኳኋን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ መደንገጉ እና የእነዚህ ድንጋጌዎችን መስፈርት ባላሟላ ክስ ተከሳሹን መጥራት እንደማያስፈልግ እና ክርክሩም በጅምር ደረጃ ሊቋረጥ እንደሚገባ ተገልፆ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231/1/ሀ/ መደንገጉም ክርክር ውጤት ኖሮት በመሰረተ ህጉ የተቀመጡትን መብትና ግዴታ ሊያስከብር መቻሉን ለማረጋገጥ ነው፡፡

ከዚህም አንፃር አሁን በግራ ቀኙ መካከል የተነሳውን ክርክር እንዳየነው የአሁን አመልካች ካቀረበው ክስ መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቀኛችን ካደረግነው የሽያጭ ውል የመነጨ የንብረት መብት አለኝ፤ ተከሳሾችም ከዚህ ውል የተነሣ ግዴታ አለባቸው ግዴታቸውም የተሸጠውን ነገር ስመ ሀብትነት በሚመለከተው ክፍል ቀርበው ለማዛወር ግዴታ ገብተዋል፡፡ እንደገቡት ግዴታ ይፈጽሙልኝ የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን የክስ ዝርዝር ጥቅል በማየት የክስ ምክንያቱ እና የሚጠይቀው ዳኝነት ምንድን ነው የሚለውን ከእነ ሙሉ ይዘቱ መውሰድ ሲገባው የመለያያ ውል እንዲያደርጉ የሚለውን ሐረግ ብቻ መውሰዱ በፍ/ብ/ሥ//ሥ/ህ/ቁ 222 እና 224 የተመለከቱትን ድንገጌዎች ግብና ዓላማ መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡

ተከሳሾችም ቀርበው በሰጡት የመከላከያ መልስ ከከሳሽ ጋር የፈፀምነው የሽያጭ ውል የለም የሚለውንና የመሳሰለውን ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ በቅድሚያ ተለይቶ ሊረጋገጥ የሚገባው ጉዳይ ለከሳሽ መብት ለተከሳሾች ደግሞ ግዴታ ሊፈጥር የሚችል ህጋዊ ተግባር ተከናውኗል ወይስ አልተከናወነም? የሚለው እንደመሆኑ መጠን የግራ ቀኙን ክርክር ተመልከቶ እንደ ስነ ስርዓት ህጉ ዓለማ ትርጉም እና ውጤት ያለው ዳኝነት በመስጠት ረገድ በጭብጥ አያያዝ ረገድም ስነ ስርዓታዊ ጉድለት የታየበት ዳኝነት ነው፡፡

ስለሆነም ከሳሽ የአሁን አመልካች ያቀረበው የክስ አቤቱታ ከእነ ሙሉ ይዘቱ ሲታይ ሻጮች ስመ ሀብትነቱን በሚመለከተው ክፍል ቀርበው ሸጠውታል በተባለው ቤቱ ላይ ስመ ሀብትነት ለማዞር የሚያስችል ውል እንዲያደርጉ ሳይሆን የተሸጠውን ንብረት ስመ ሀብትነት ስልጣን ያለው አካል ወደ ገዥው ማዞር እንዲችል አስቀድመው በውሉ ላይ የገቡትን ግዴታና ህጉ በሻጭ ላይ የሚጥለውን ግዴታ እንዲፈፀሙ የሚል በመሆኑ ይኸው የክስ አቀራረብ እና የዳኝነት ጥያቄ ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ አንፃር ሲታይ ክርክሩ ቀጥሎ በግራ ቀኙ ማስረጃ ከመለየቱ በፊት ከወዲሁ ከሳሹ ድሮውንም ቢሆን የክስ ምክንያት የለውም ብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231/1/ሀ/ መሰረት ዳኝነት ለመስጠት የሚያስቻል አይደለም፡፡

በመሆኑም ከግራ ቀኙ ክርክር እና ክርክራቸውን ለማስረዳት ካቀረቡት ማስረጃ አንፃር በቅድሚያ ሊታዩ የሚገባቸው የክርክር ነጥቦች እያሉ የአሁኑ አመልካች ያቀረበው የክስ ምክንያትና የጠየቀውን ዳኝነት ሙሉ ይዘቱ እና ሀሳቡ ሳይታይ በስር ፍ/ቤቶች ክሱ የክስ ምክንያት ያለው አይደለም በሚል የሰጡት ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/፣33/3/ እና 231/1/ሀ/ ደንጋጌዎች ትክክለኛ አፈፃፀም የተከተለ ሁኖ ስላላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 37513 በቀን 25/7/2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 118522 ግንቦት 06 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የክርክሩን ቅደም ተከተል ጠብቆ በግራ ቀኙ መካከል የተነሱት ሌሎች አከራካሪ ነጥቦች በማስረጃ እንዲለዩ በማድረግ የአሁን አመልካች በህግ ፊት ከፀና ውል ወይም ከህግ የመነጨ መብት የለውም ካልተባለ በስተቀር የግራ ቀኙ ክርክር ከደረሰበት የክርክር ደረጃ አንፃር የአሁን አመልካች የክስ ምክንያት የለውም ሊባል አይችልም ብለናል ስለሆነም የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ክርክሩን ቀጥሎ አስፈላጊውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 72980

ሐምሌ 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ይርገዱ አዲሱ - ጠበቃ ይርጉ ሰንበቶ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ሕጻን ምስጋናው ዘሪሁን ሞግዚት - ወ/ሮ ጠጋ ሙሉይ

2. ሕጻን መስከረም ዘሪሁን ሞግዚት ወ/ሮ የሺ ባልቻ

3. ቤቴልሔም ዘሪሁን ሞግዚት ወ/ሮ ሰናይት ሰንደቁ

} ጠበቃ የምስራች ደሣለኝ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሚስትነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች የሟች አቶ ዘሪሁን ብርሃኑ ሚስት ናቸው ተብሎ ማስረጃ እንዲሰጥላቸው አመልክተው ፍርድ ቤቱን የአመልካችን በቃለ መሃላ ተደግፎ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ከሟቹ ጋር በአገር ባህል የተጋቡ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ሚስትነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሰጠ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ሟቹ ከተለያዩ ሴቶች ልጆችን የወለዱና አመልካች በ1996 ዓ/ም ከሟቹ ጋር አብረው ከመኖር ውጪ በሀገር ባህል ተጋብተው የኖሩ ያለመሆኑን ገልፀው ለአመልካች የተሰጣቸው የሚስትነት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱንም ግራ ቀኙን በመቃወሚያ አቤቱታው ላይ ከአከራከረ እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በቀበሌ የቤተሰብ ቅፅ ላይ ሚስት ተብለው የተመዘገቡ ቢሆንም በቤተዘመድና በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ ባልና ሚስት የተቀበሏቸው መሆናቸውን በበቂ ሁኔታ አስረድተዋል ለማለት ስለማይቻል አመልካች ጋብቻ ለመፈጸማቸው የትዳር ሁኔታ እንዳላቸው በማረጋገጥ አላስረዱም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ቀድሞ የሰጠውን የሚስትነት ማስረጃ ሰርዞታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የይግባኝ አቤቱታቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ባል ወይም ሚስት በቀበሌ ፎርም ላይ ሞልተው ማረጋገጣቸው ራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት እየቆጠሩ የሚኖሩ መሆኑ እና ማህበረሰቡም በዚህ መልኩ የተቀበላቸው መሆኑን እንደሚያመላክት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 20036 ግንቦት 16 ቀን 1998 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል የሚል ምክንያት በመያዝ ከመቃወሚያው በኋላ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ አመልካች የሟች አቶ ዘሪሁን ብርሃኑ ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ከሟች ጋር በባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ስርዓት ጋብቻ የፈጸሙ እና ይህንኑ የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ በመጥፋቱ ምክንያት ማቅረብ ያልቻሉ ቢሆንም በ1996 ዓ/ም ከሟች ጋር ባደረጉት ስምምነት በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ጽ/ቤት ሁለታቸውም ቀበሌ ቀርበው በቀበሌው ጽ/ቤት ውስጥ በሚገኘው  በሟች የግል ማህደር ላይ ባልና ሚስት ፎርም ቅፅ ላይ በባልና ሚስትነት ስማቸው መመዝገቡንና እስከ እለተሞቱ ድረስ አንድ ላይ በመሆን ንብረት ሁሉ ያፈሩ ስለመሆኑ እየታወቀ አመልካች ከሟች ጋር የመሰረቱት ሕጋዊ ግንኙነት የለም ተብሎ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የሟች ሚስት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከሰ/መ/ቁጥር 20036 አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠው ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ከሰ/መ/ቁጥር 20036 አንፃር መታየት ያለበት ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከሟች ጋር ሕጋዊ ጋብቻ መስርተናል የሚሉት በባህላዊ የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት ሲሆን ይህንኑ ያሳያል የሚሉት ሰነድም የጠፋባቸው ስለመሆኑ ገልፀው ከመከራከራቸውም በላይ በ1996 ዓ/ም ግን ከሟች ጋር በክፍሉ ቀበሌ ጽ/ቤት ቀርበው በባልና ሚስት ፎርም ላይ ቅጹን የሞሉ መሆኑንና ከሟች ጋር በባልና ሚስትነት ይኖሩ እንደነበር በመዘርዘር መሆኑን፣ ተጠሪዎች የአመልካችን ከሟች ጋር ጋብቻ አልፈፀሙም በማለት የሚከራከሩት ለአንድ ወር ከሟች ጋር ከመኖራቸው ውጪ ጋብቻ አልመሰረቱም፣ በባልና ሚስትነትም የሚታወቁ አይደሉም፣ ሟች ሌሎች ሴቶች ጋር ህጋዊ ግንኙነት የነበራቸው በመሆኑ ከአመልካቻቸው ጋር በጋብቻ ውስጥ አልነበሩም በማለት መሆኑንና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው አመልካች ቀድመው ማስረጃ ሲወስዱ ከሟች ጋር በአገር ባህል እንደተጋቡ አድርገው ገልፀው ቆይተው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ በ1996 ዓ/ም ቀበሌ ፅ/ቤት ቀርበን ቅፁን ሞልተናል ማለታቸው ቀድሞውንም ጋብቻ ያልፈጸሙ መሆኑን እንደሚያጠራጥር፣ ይልቁንም እንደ ባልና ሚስት ሁነው ይኖሩ እንደነበረ መግለፃቸውን እንደሚያሳይ ጠቅሶ ጋብቻ መኖሩ ተገልጾ ክርክር ባልቀረበበት ሁኔታ ደግሞ ጋብቻ መኖር ያለመኖሩን ማስረዳት አለማስረዳትን መመርመሩ አስፈላጊ አይደለም የሚሉ ምክንያቶችን በመያዝ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተመለክተናል፡፡

ከዚህ አንፃርም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን ተጠሪዎች በተቃዋሚነት በጉዳዩ ቀርበው የተከራከሩት የአሁን አመልካች የሟች ሚስት አይደሉም የሚሉበትን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህንኑ ክርክር ለማቅረብ የሚያስችላቸውን የእራሳቸው የሚስትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አላቀረቡም፣ ወይም ህጋዊ ሚስቶች የተባሉትም ቀርበው አልተከራከሩም፡፡  ስለሆነም በዚህ በግራ ቀኙ መካከል በተነሳው ክርክር ለጉዳዩ እልባት መስጠት በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ነጥብ የአሁን አመልካች የሟች አቶ ዘሪሁን ብርሃኑ ሚስት ሊሆኑ

የማይችልበትን ፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ባሁኑ ተጠሪዎች በኩል በሕጉ አግባብ ቀርቧል ወይስ አልቀረበም?፣ ፍርድ ቤቱስ ጉዳዩን በሕጉ አግባብ ማጣራት ነበረበት ወይስ አልነበረበትም? የሚለው ነው፡፡ ከዚህ ነጥብ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከት ተጠሪዎች ሟች ከሌሎች ሴቶች ጋር ጋብቻ መስርቶ ነበር በሚለው ነጥብ ላይ አትኩረው የተከራከሩ ከመሆኑ በቀር የአሁን አመልካች ሚስት ሊሆኑ ያልቻሉበትን ክርክርና ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ምንም እንኳ የእርሷ ሚስትነት ከክርክሩ አካሄድ አኳያ ጥያቄ ውስጥ የገባ ቢሆንም ይህ ግን ፍርድ ቤቱ ራሱ በሚያጣራው ማስረጃ ነጥሮ ሊወጣ ይችል የነበረ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የሟች ዘሪሁን ብርሃኑ ሚስት መሆን ያለመሆናቸው ጉዳይ መታየት የነበረበት በቀበሌው ውስጥ ተሞልቷል የተባለው ቅጽ አሞላሉ እንዴት እንደነበር (ሟችና አመልካች በግንባር ቀርበው መሆን ያለመሆኑ፣ የባልና ሚስት ሁኔታን ሊያረጋግጥ የሚችል ማስረጃ በቀበሌው ጽ/ቤት ቀርቦ ታይቶ መሆን ያለመሆኑና ሌሎች የቀበሌ ጽ/ቤቱ የሚከተላቸው አሰራሮች ምን ምን እንደሆኑ) ከተጣራ በኋላ መሆን እንደነበረበት ተረድተናል፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኸው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣137፣ 272፣ 327(3)፣ 345 እና ከሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች ክርክር ወጥ ያለመሆኑን በመግለጽ ውሳኔ መስጠቱም አጠቃላይ የክርክሩን ይዘትና ፍርድ ቤት እውነትን ለማውጣት በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት ተግባር ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ሊወሰን የቻለው በክርክሩ ሂደት ሊጣራ የሚገባቸው ነጥቦች ባልተሟሉበት ሲሆን የክርክር ሂደት ሳያሟላ ዳኝነት መስጠት ደግሞ የፍርድ አካሄድ ስርዓት የሚቀበለው ጉዳይ ባለመሆኑ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው አመልካች ከሟች አቶ ዘሪሁን ብርሃኑ ጋር በሕግ አግባብ ጥበቃ ሊደረግ የሚችል ግንኙነት መኖር ያለመኖሩን በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንዲሁም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 20036 በተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለመወሰን በቅድሚያ አመልካች የአገር ባህል የጋብቻ ስርዓት የፈፀሙ ስለመሆኑ ያሳያል ያሉት ሰነድ የጠፋ መሆኑን የገለፁ ስለሆነ ይኸው ፍሬ ነገር ተገቢ ነው በተባለው መንገድ ሁሉ እንዲጣራ፣ በ1996 ዓ/ም አመልካች ሟች አቶ ዘሪሁን በቀበሌው ጽ/ቤት ፎርም ሲሞሉ ባልና ሚስት ናቸው ተብሎ እንዴት ሊሞላ እንደቻለና በቅጽ ባልና ሚስት ተብሎ መሞላቱ ስላለው ውጤት የክፍሉ ቀበሌ መግለጫ እንዲያቀርብ ማድረጉ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓቱ የግድ የሚለው ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1879/02 መጋቢት 08 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 16359 ጳጉሜ 01 ቀን 2003 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15639 ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔም ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፡፡

3. የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1879/02 ክርክሩን ቀጥሎ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተመለከተው አግባብ ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(2) መሰረት መልሰንለታል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ሮ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 82679

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ / አክሊሉ አበባው ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** ወ/ሮ እንዳገር ጌቱ - ጠበቃ ጌታሁን ተስፋዬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በጋብቻ የተፈራ የጋራ ሀብት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ተጠሪና ወ/ሮ እብስቴ በልስቲ አመልካች የአሁን አመልካችና እነ ጤናዬ በልስቲ ተጠሪዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ የተነሳው የሟች በልስቲ አወቀ ውርስ በሚጣራበት ወቅት ነው፡፡ አመልካች 1960 ዓ.ም ጀምሮ ሟች ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለየበት ድረስ በህጋዊ ጋብቻ ተሳስረን ኖረናል፡፡ በጋብቻ ስንኖር በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/15 የቤት ቁጥር 487 የሆነውን ቤት አፍርተናል፡፡ ስለዚህ ይህ ቤት ግማሹ የሟች በልስቲ አወቀ ግማሹ ደግሞ የአመልካች ማለትም የከበቡሽ ሸዋረገድ መሆኑ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/15 የሚገኘው የቤት ቁጥር 457 ሟች አቶ በልስቲ አወቀ ከእኔ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበረበት ጊዜ ያፈሩት ንብረት ነው፡፡ ስለዚህ የቤቱ የጋራ ባለሀብት እኔ ነኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሟች አቶ በልስቲ አወቀን ውርስ እንዲያጣራ የተመደበው ውርስ አጣሪ በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 08/15 የቤት ቁጥር 487 ሟች አቶ በልስቲ አወቀ ከማንኛቸው ጋር እንዳፈራው አከራካሪ በመሆኑ ፍ/ቤቱ መርምሮ ውሳኔ ይስጥበት በማለት አስተያየት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ፣ አከራከሪውን ቤት ሟች በልስቲ አወቀ ከወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ ጋር ያፈራው ንብረት ነው፡፡ ስለዚህ የቤቱ ግማሽ ባለሀብት ወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ (አመልካች) ናት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርባለች፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የቤቱ ግማሽ ባለሀብት ወ/ሮ አንዳገር ጌቱ (ተጠሪ) ናት በማለት የሥር ፍ/ቤት

የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች ይህንን በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባለች፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች (ይግባኝ ባይ) ተጠሪ (መልስ ሰጭዋ) ከሚች ጋር ከተለያየች አስር ዓመት ካለፈው በኋላ ያቀረበችው የጋራ ንብረት ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረብኩትን መከራከሪያ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አላግባብ ውድቅ አድርጎብኛል፡፡ ቤቱም የጋራ ንብረቴ ሆኖ እያለ የጋራ ሀብትሽ አይደለም መባሉ ስህተት ነው በማለት ያቀረበችውን የይግባኝ ቅሬታ ለማጣራት ጭብጥ ይዞ፣ መልስ ሰጭ (ተጠሪን) በማስቀረብ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይርጋውን ክርክር አመልካች አንስተው ቢሆን እንኳን፣ ይህንን የይርጋ መከራከሪያ ሁለቱ ፍ/ቤቶች ያልተቀበሉት በመሆኑ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለሶስተኛ ጊዜ ይህንን መከራከሪያ ሊመረምር እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 የተደነገገ በመሆኑ ይህንን መከራከሪያ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ መርምሮ የመወሰን ሥልጣን ስለሌው አልፈነዋል፡፡

ቤቱ የይግባኝ ባይ (የአመልካች) የጋራ ሀብት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ መልስ ሰጭ (ተጠሪ) የሚች ሚስት መሆኗን በማረጋገጥ የደብረ ኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ቤቱም ይግባኝ ባይ (አመልካች) ከሚች በልስቲ አወቀ ጋር በጋብቻ ስትኖር ያፈራችው ስለመሆኑ ያስረዳል ተብሎ የቀረበው ማስረጃ ቤቱን ይግባኝ ባይ ከሚች ጋር ያፈሩት መሆኑን የማስረዳት ብቃት የለውም፡፡ ስለዚህ አከራካሪው ቤት ሚች አቶ በልስቲ አወቀ ከመልስ ሰጭ( ተጠሪ) ጋር ያፈሩት ሀብት ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሠጡትን ውሳኔ ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የሚች በልስቲ አወቀ ሚስት መሆኗን አረጋግጣ ያቀረበችው የሚች መደበኛ የመኖሪያ ቦታ ባልሆነው ምስራቅ ጎጃም ዞን በሚገኘው ደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ይህንን ማስረጃ በመቃወም ማስረጃው ትክክለኛውን ፍሬ ጉዳይ የማያሳይ መሆኑን ያቀረብኩትን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመጀመሪያ የደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ አላሻረም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው የሕግ ስህተት አለበት፡፡

ተጠሪ ከሚች ጋር ከተለያየች አስር ዓመት ያለፋት መሆኑን በመግለፅ የተጠሪ ክርክር በይርጋ ይታገዳል የሚለውን ክርክር ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት አቅርቤያለሁ፡፡ ይህ የይርጋ መከራከሪያ መታለፉ ተገቢ አለመሆኑን በመግለፅ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተከራክሬያለሁ፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማጣራት እንዲወስንልኝ ያቀረብኩትን ክርክር በይግባኝ ደረጃ እንደተነሳ አዲስ ክርክር አድርጎ በመውሰድ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ ሚች በልስቲ አወቀ 1954 ቦታውን የተመራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከማቅረቧ ውጭ ቤቱ 1954 የተሰራ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበችም፡፡ ስለዚህ ቦታው የተመራበትን ጊዜ ቤቱ እንደተሰራበት ጊዜ በመውሰድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክታለች፡፡

ተጠሪ በበኩሏ ታህሳስ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ቤቱ እኔና ሚች ከተጋባን ከአራት አመት በኋላ የተፈራ ነው፡፡ አመልካች ቤቱ ሲሰራ አልነበሩም፡፡ የይርጋ ክርክር ለስር ፍ/ቤት አላቀረቡም፡፡ የሚስትነት ማስረጃ ከሚች መደበኛ መኖሪያ ውጭ በሚገኝ ፍ/ቤት አስወስኖ በመቅረብ የጋራ ሀብት መጠየቅ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ ስለዚህ

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ተጠሪ ከሟች ጋር የነበራት ጋብቻ ከሃምሳ ዓመት በኋላ ያቀረበችውን ጥያቄ በመቀበል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አከራከሪው ቤት የሟች በልስቲ አወቀና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ባህሪና ሕጋዊ ውጤት እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችና ይኸ ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ግራ ቀኙ በስር ፍ/ቤት በይግባኝና በሰበር ያቀረቧቸውን ክርክሮችና በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካችና ሟች በልስቲ አወቀ 1960 ዓ.ም ጋብቻ ፈፅመው በትዳር ፀንተው የኖሩና ጋብቻቸው በሟች መሞት ምክንያት የተቋረጠ መሆኑን በስር ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ ከአመልካች ጋር 1950 ዓ.ም ጋብቻ ፈፅመው የነበረ መሆኑና ተጠሪ የሟች ሚስት መሆኗን በማረጋገጥ የደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የሚስትነት ማስረጃ እንደሰጣት ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክርና የበታች ፍ/ቤቶች ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተረድተናል፡፡

ተጠሪ የሟች ሚስት መሆኗን ለማስረዳት የደብረ ኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጣትን የሚስትነት ማስረጃ ብታቀርብም ተጠሪ ከሟች በልስቲ አወቀ ጋር ተለያይታ የኖረች መሆኑን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ፅፋ ባቀረበችው አቤቱታዋ ያመነች መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍ/ቤት በውሳኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ተጠሪ ከሟች ጋር የነበራት ጋብቻ የፈረሰ መሆኑን ጋብቻው ከፈረሰ ከሃምሳ ዓመት በኋላ የጋራ ንብረት አለኝ በማለት የክፍያ ጥያቄ ማቅርቧ ተገቢ አለመሆኑን ለዚህ ሰበር ችሎት ነሐሴ 7 ቀን 2004 ዓ.ም ፅፋ ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ በግልፅ በማስፈር ተከራክራለች፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ የሟች ሚስት መሆኔ በውሳኔ ተረጋግጧል ከማለት ውጭ ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ ሟች ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩ ጊዜ ድረስ ከሟች ጋር የነበረን ጋብቻ አልፈረሰም በማለት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 234(1) በሚደነግገው መሰረት በግልፅ ክዳ ያቀረበችው ክርክር የሌለ መሆኑን ተጠሪ ለዚህ ሰበር ችሎት ታህሳስ 4 ቀን 2005 ዓ/ም ፅፋ ያቀረበችውን መልስ የዘት በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ተጠሪ ከሟች ጋር ከተለያየች ሃምሳ ዓመት ሆኖታል በማለት አመልካች በሰበር አቤቱታዋ ያቀረበችውን ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 235(2) መሰረት እንዳመነች የሚያስቆጥራት ነው፡፡

ተጠሪ የሟች ሚስት ስለመሆኗ የደብረ ኤልያስ ወረዳ የሰጣትን የሚስትነት ማስረጃ ብታቀርብም በፍሬ ጉዳይ ደረጃ አመልካችና ተጠሪ ተለያይተው የኖሩ መሆኑንና አመልካች ከሟች ጋር ከ1960 ዓ.ም ጀምሮ በፀና ጋብቻ የኖረች መሆኑን ተጠሪ በክርክር ሂደት ለስር ፍ/ቤት ካቀረበችው የፅሁፍ አቤቱታና ለዚህ በሰበር ችሎት ከሰጠችው መልስ በመሸሽ መልክ ካቀረበችው ክርክር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ አከራከሪው ቤት በሚች አቶ በልስቲ አወቀና በአመልካች ስም የተመዘገበና አመልካች የቤቱ የጋራ ባለሀብት መሆኗን የሚያሳይ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ያላት መሆኑን ተጠሪም የምትክደው አይደለም፡፡ ተጠሪ የምትከራከረው ቤቱ የተሰራው ሚች አመልካችን ከማግባቱ በፊት ነው በማለት ነው፡፡

2. ከላይ የገለጽናቸው ፍሬ ጉዳዮች የአመልካችና የተጠሪን የማስረዳት ኃላፊነት በማቅለል ወይም በማክበድ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ናቸው፡፡ አመልካች ከሚች በልስቲ አወቀ ጋር ከ1960 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚች ህልፈተ ህይወት በፀና ጋብቻ መኖራቸው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62(1) በአንደኛው ተጋቢ ስም ቢመዘገብም ማንኛውም ንብረት የባልና የሚስቱ የጋራ ሀብት ናቸው ተብለው ይገመታሉ በማለት በግልፅ የደነገገው የህግ ድንጋጌ ተጠቃሚ የምትሆነው አመልካች መሆኗን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ከሚች ጋር ተለያይታ የኖረች መሆኑ ለስር ፍ/ቤትና ለሰበር ያቀረበችው ክርክር ስለሚያሳይ የአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62(1) የተደነገገው የሕግ ግምት ተጠቃሚ አትሆንም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ከሚች በልሰቲ አወቀ ጋር የቤቱ የጋራ ባለሀብት ሆና የማይንቀሳቀሰው ንብረት መዝገብ ውስጥ መመዝገቧና አመልካች ከሚች ጋር ባለሀብት መሆነኗን በአስተዳደሩ ክፍል የተመዘገበ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቤቱ ባለሃብት እንደሆነች የሚያስገምት እንደሆነ ከህጉ ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ አመልካች የቤቱ የጋራ ባለሀብት መሆኗ ከላይ የገለፅናቸው የሕግ ድንጋጌዎች የህሊና ግምት የሚወስድበት በመሆኑ በሕጉ የተደነገገውን ግምት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ የማፍረስ ወይም የማስተባበል ግዴታው ያለባት ተጠሪ ናት፡፡ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62(1) የተደነገገውንና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195(1) የተደነገገውን የአመልካችን የቤቱን የጋራ ባለሀብትነት ግምት ለማፍረስና ለማስተባበል የሚያስችል ማስረጃ የማቅረብ ኃላፊነት አለባት፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው ተጠሪ ሚች ቦታውን 1954 ዓ.ም መመራቱን የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ ከላይ በተገለፁት የሕግ ድንጋጌዎች የተደነገገውን የአመልካችን የቤቱ የጋራ ባለሀብትነት ግምት የማፍረስ ወይም የማስተባበል ግዴታና ኃላፊነት ለመወጣት አትችልም፡፡ በተለይም ተጠሪ አመልካች ከሚች ጋር የቤቱ ባለሀብት መሆኗ የቤቱ ዕርስተ መዝገብ የተመዘገበች መሆኗንና በቤቱ ባለቤትነት የአስተዳደሩ ክፍል መዝገብ ላይ ስሟ በባለሀብትነት መገለፀን፣ ለማስተባበል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ከተደነገጉት ሁኔታዎች አንደኛውን በማስረጃ በማረጋገጥ የማስተባበል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195(1) የተደነገገውን የአመልካችን የቤቱ የጋራ ባለሀብትነት ግምት የማስተባበልና የማፍረስ ኃላፊነቷን ባልተወጣችበት ሁኔታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ቤቱ የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሚች ሚስት ስለመሆኗ በደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጣት ማስረጃ (ውሳኔ) እውነታውን የሚያንፀባርቅ አይደለም በማለት አመልካች ተቃውሞ ብታቀርብም የወረዳው ፍ/ቤት ሚስትነቷን በመግለፅ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 360(2) መሰረት ካላሰረዘ ተጠሪ የሚች ሚስት ናት ወይስ አይደለችም የሚለውን ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ስልጣን የለኝም በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንዳለፈው ከውሳኔው

ተረድተናል፡፡ የደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የተጠሪን አቤቱታና ማስረጃ ብቻ በመቀበል የሰጠው የሚስትነት ማስረጃ በማስረጃነት በቀረበበት በማናቸውም ጊዜ ተዓማኒነትና ክብደት የሌለው ማስረጃ መሆኑን ለማሳየት ክርክር ሊቀርብበትና ተቃራኒ ማስረጃ ተሰምቶ ውድቅ ሊደረግ የሚችል (Declaratory Judgment) ነው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪን ሚስትነት በመግለፅ የሰጠውን የሚስትነት ውሳኔ አመልካች ካላሻረች ውሳኔውን መቃወምም ሆነ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እውነትነት የሌለው መሆኑን መከራከር አትችልም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠው የሚስትነት ማስረጃ ትክክል መሆን አለመሆኑን የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የለውም በማለት የተሰጠው ትርጉም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 14290 እና የሰ.መ.ቁ 17058 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

4. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበችውን የይርጋ ክርክር መነሻ በማድረግ ለአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 የሰጠው ትርጓሜ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ስልጣን የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 25/1988 ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው የተለየ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣን እንዳለው በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ስልጣኑ አይቶ በመሻር ቤቱ የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምራ የይርጋ መከራከሪያ እንዳነሳች ገልፃ የከፍተኛው ፍ/ቤት ጥያቄው በይግባኝ ደረጃ እንደተነሳ በውሳኔው የገለፀውና መከራከሪያውን ውድቅ ያደረገው ስህተት ስለሆነ በይግባኝ ታይቶ ይሻርልኝ በማለት ጠይቃለች፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9(2) አንድ ተከራካሪ ያነሳው የህግ መከራከሪያና ምክንያት በስር ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከታለፉ የክርክሩ ውጤት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቢለውጠውም በሁለቱም ፍ/ቤቶች የታለፈውን የሕግ መከራከሪያ በይግባኝ የማየት ስልጣን እንደሌለው በመግለፅ የሰጠው ትርጓሜ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ይዘት ዓላማና ተግባራዊ ተፈፃሚነት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራካሪው ቤት የአመልካች ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመለወጥ አከራካሪው ቤት የተጠሪ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9(2) በተጠበቀላት የይግባኝ መብት ተጠቅማ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ለማሳረም ያቀረበቻቸውን የፍሬ ጉዳይና የሕግ ክርክሮች የመመርመርና ውሳኔ የመስጠት የስረ ነገር ሥልጣን ብቻ ሣይሆን ኃላፊነትና ግዴታ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ተጥሎበታል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መከራከሪያ በሁለቱ ፍ/ቤቶች የታለፉ በመሆኑ በይግባኝ የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው የህግ ትርጉም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው የሕግ ምክንያቶች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አከራካሪው ቤት የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/15 የሚገኘው ቁጥሩ 487 የሆነው ቤት የአመልካችና የሟች በልስቲ አወቀ የጋራ ሀብት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 83582

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ውብነህ አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ አልማዝ ዓለሙ
2. አቶ አለባቸው አሰፋ ጠበቃ ብርሃኑ ቀረቡ
3. አቶ ታደሰ ገብሬ በሌሉበት ታይቷል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ያፀደቀው የእርቅ ስምምነት ያስረዝልኝ በሚል መንገድ የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቅራቢ /አመልካች ተጠሪዎች የፍርድ መቃወሚያ ተጠሪዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍል ከተማ ወረዳ 7 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥር ያልተሰጠውን አዲስ ቤት ከሶስተኛ ተጠሪ እኔ በሕጋዊ ውል ገዝቼና ተጨማሪ ግንባታ በማካሄድ እየተገለገልኩበት እገኛለሁ፡፡ ሆኖም አንደኛ የመቃወም ተጠሪና ሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ በመካከላቸው በፍርድ ቤት ሲያደርጉት የነበረው ክርክር ለማቋረጥና ቤቱ በሐራጅ ተሽጦ ለእዳ መክፈያ እንዲሆን በመግለጽ በመስማማት ይህንን ስምምነታቸውን ፍርድ ቤቱ እንዲያውቅና እንዲመዘግበው በማድረግ እኔ ተካፋይ ባልሆንኩበት ክርክር ንብረቴን ለማሸጥ በማንቀሣቀስ ላይ ናቸው፡፡ ስለዚህ እኔ በክርከሩ ገብቼ ውሣኔው እንዲሰረዝልኝ በማለት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቀርባለች፡፡ ተጠሪዎች የእዳ መክፈያ እንዲሆን የእርቅ ስምምነት ያደረጉበትን ቤት፣ እኔ ከእዳና እገዳ ነፃ መሆኑን አረጋግጪ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በተደረገ ውል ከሶስተኛው ተጠሪ ገዝቼ ቤቱንና ይዞታውን ተረክቤያለሁ፡፡ ቤቱን በግዥ ከተረከብኩ በኃላ በከፍተኛ ወጭ ተጨማሪ ግንባታ ሥራ ሠርቻለሁ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት 06-04-2002 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ቤቱ በፍርድ አፈፃም መምሪያ ሊሸጥ የሀራጅ ማስታወቂያ በግድግዳው ላይ ሲለጠፍበት ሁኔታውን በማወቄ በመጀመሪያ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 418 መሠረት በአፈፃፀም ጣልቃ ገብቼ መቃወሚያየን አቅረብኩ፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ችሎት በመጀመሪያ የእርቅ ስምምነቱን የመዘገበው ችሎት በእርቁ መሠረት

እንዲፈፀም የሰጠውን ትእዛዝ ሣይሰረዝ ጥያቄሽ ተቀባይነት የለውም በማለት መቃሚያን ውድቅ አደረገብኝ የሥር ፍርድ ቤት መዝግቦና በፍርድ ቤቱ ማህተም አረጋግጦ ያስተላለፈው በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል እየተፈፀመ ያለውን ከፍርድ ቤቱ የፀደቀው የአፈፃፀም ስምምነት እኔ ባለሁበት ታይቶ እንዲሰረዝ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቤለት ውድቅ አድርጎብኛል፡፡ ስለዚህ ውሣኔው የእኔን መብትና ጥቅም የሚነካና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምለኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በበኩላቸው አንደኛ ተጠሪና 3ኛ ተጠሪ በጋብቻ ተሣስረን የኖርን ባልና ሚስት ነበረን በ1996 ዓ.ም ጋብቻችንን በስምምነት ስናፈርስ የጋራ ሃብት የሆነውን ክርክር የተነሣበትን ቤት እኩል እንድካፈል የትግራይ ክልል ማህበራዊ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ በኃላ ሁለተኛው ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት አለኝ በማለት በመያዙ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቤ ተጠሪዎች በስምምነትና በእርቅ ጉዳዩን በመጨረሣችን፣ የሥር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182 መሠረት የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ አመልካች ፍርድ ቤት ያልሰጠውን ውሣኔ እንዲሰረዝላት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ ከሚያዘው ውጭ ያቀረበችው የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ የአንደኛ አንደኛ ተጠሪ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ ባቀረቡበት ቤት ላይ ክርክር ተካሂዶ በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ የለም፡፡ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው ሶስተኛው ተጠሪ እንጂ አመልካች አይደለም፡፡ ማመልከቻቸው ውድቅ ይደረግ በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን፣ ሁለተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ የተለየ ምላሽ የለኝም ብሏል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ መልስ አላቀረበም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ቤቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ መዝገቡ የተዘጋው ተከራካሪ በነበሩት ተጠሪዎች ጥያቄ ነው፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ የሰጠው ውሣኔ ባለመኖሩ የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ የሕግ መሠረት የሌለው ነው በማለት የአመልካችን የመቃሚያ ማመልከቻ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ባልና ሚስት የሆኑት አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የጥቅም ተካፋያቸው ከሆነው ሁለተኛ ተጠሪ ጋር በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 18281 የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበው ክርክር ካደረጉ በኃላ፣ በመጀመሪያ ሕዳር 3 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የእርቅ ስምምነት በማጽደቅ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን እንዲዘጋላቸው ጠየቁ በማስከተል ሕዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት በማድረግ ፍርድ ቤቱ እንዲያፀድቅላቸው ሲያቀርቡ በመዝገቡ የተያዘው ጭብጥ የሁከት ይወገድልኝ ሆኖ እያለ ቤቱ ተሸጦ የእዳ እንዲሆን በማለት ተስማምተው መቅረባቸውን በመዘርዘር የእርቅ ስምምነቱን ሣያፀድቅ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪዎች ለሶስተኛ ጊዜ የእርቅ ስምምነት አቅርበው ፍርድ ቤቱ 06-04-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 377 መሠረት መዝግቦና በፍርድ ቤቱ ማህተም አረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎችም በሀራጅ ተሸጦ የእዳ መክፈያ እንዲሆን የእርቅ ስምምነት ያደረጉበትን ቤት ቤቱ ከእዳና እገዳ ነፃ መሆኑ ተረጋግጦና በሶስተኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑንና ሶስተኛ ተጠሪም ሚስት የሌለው መሆኑን ማስረጃ

አቅርቦ በሰነዶች ምዝገባ ጽ/ቤት በተደተገ የቤት ሽያጭ ውል አመልካች ገዝቼዋልሁ፡፡ ቤቱን ከሶስተኛ ተጠሪ በውል ከገዛው በኃላ ቤቱንና ይዞታውን ተረክቤ በከፍተኛ ወጭ ተጨማሪ ግንባታ አከናውኛለሁ፡፡ ተጠሪዎች ባደረጉት የእርቅ ስምምነትና የሥር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18281 ታህሣስ 6 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መነሻ ቤቱን በአፈፃፀም በሐራጅ ለማሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ተሰጥቷል፡፡ እኔም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 ጣልቃ ገብቶ ያቀረቡኩትን መቃወሚያ የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት ትእዛዝ ሣታሽሪ በአፈፃፀም ጣልቃ ልትገቢ አትችይም በማለት አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ውድቅ አድርጎብኛል ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ የተጠሪዎች የእርቅ ስምምነት ላይ ተቃውሞ እንዳላቀርብ የሚገድብና የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

አንደኛ ተጠሪ ታህሣስ 1 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱ ከሶስተኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ሲኖሩ ያፈራው የጋራ ሃብት ነው ጋብቻችን ሲፈርስ ቤቱን እንድንካፈል በማሕራዊ ፍርድ ቤት ተወስኗል፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ መደበኛ መኖሪያው መቀሌ ሆኖ እያለ ከባህር ዳር ሚስት የሌለው መሆኑን የሚገልጽ የሐሰት ማስረጃ በማቅርብ ከአመልካች ጋር ያደረገው የሽያጭ ውል እኔ በቤቱ ላይ ያለኝን መብት የሚጎዳ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ በመቀበል ፍሬ ጉዳዩን በማጣራ መወሰን ነበረበት፡፡ ይህንን በማድረጉ እኔን በተጨማሪ ክርክር ማለት ባለሃብትነት የመፋለም ክስ በመዝገበ ቁጥር 24007 እንዳቀርብ አስገድዶኛል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ ተመልሶ ሁለቱ መዛግብት ተጣምረው ተጣርቶ እንዲወሰንልኝ በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ ታህሣስ 22 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ እኔና ሶስተኛ ተጠሪ በሶስተኛ ተጠሪ ስም ቤት በጋራ ገዝተን ለመሸጥ በነበረን ስምምነት ቤቱ በሶስተኛ ተጠሪ ስም ሲገዛ ገንዘብ አዋጥቻለሁ፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ ከእኛ በመደበቅ ቤቱን ለመሸጥ ሲንቀሣሰቅ ስለደርስንበት አንደኛ ተጠሪና እኔ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበንበታል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪም በእርቅ ለመጨረስ ስለተስማማ፣ ጉዳዩ በእርቅ አልቋል ስለዚህ የአመልካች አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሶስተኛ ተጠሪ መልስ የመስጠት መብት በብይን ተልፏል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክና ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበችውን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ውድቅ ማድረጋቸው ሕጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18281 አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ከሣሾች ሶስተኛው ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ይከራከሩ ነበር፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን መዝገብ ከዘጋው በኃላ ተጠሪዎች ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በመካከላቸው ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በመመዝገብ ለሚመለከተው ክፍል እንዲያስተላልፍላቸው በመጠየቃቸው የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 18281 በማንቀሣቀስ ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት የፍርድ ቤቱ ማህተም ተደርጎበት ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ በማለት ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት በፍርድ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለሚመለከትው ክፍል እዲተላለፍ ትእዛዝ የተሰጠበትና ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደጉት የእርቅ ስምምነት በይዘቱ አመልካች በሕጋዊ ውል ገዝቻዋለሁ የምትለውን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት በሶስተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቁጥር ያልተሰጠው አዲስ ቤት ተጠሪዎች ባለበት ሁኔታ ሸጠው፣ ዋጋውን ለሶስት እኩል ለመካፈል ያደጉት የእርቅ ስምምነት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በፍርድ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝና ከዚሁ ትእዛዝ ጋር የተያያዘውን በሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት መሠረት በማድረግ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪዎች የፍርድ ባለመብቶች ሶስተኛው ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ሆኖ የሚከራከሩት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 184598 ተከፍቶ ቤቱ በባለሙያ ተገምቶ የሀራጅ ማስታወቂያ ወጥቶበታል፡፡

2. አመልካች ፍርድ ቤቱ ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በፍርድ ቤቱ ማሕተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላፍ ያደረው ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነትና በሶስተኛው ተጠሪ ቤት ላይ የተደረገ የእርቅ ስምምነት አይደለም፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ ቤቱን ለእኔ የሸጠልኝ በመሆኑ የእርቅ ስምምነቱ መጽደቁና በፍርድ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ መተላለፉ የእኔን መብን የሚነካ ነው፡፡ ስለዚህ ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ተጠሪዎች ያደጉት የእርቅ ስምምነት በመመዝገብ የተሰጠውን ትእዛዝ ይሰረዝልኝ የሚል የመቃወሚያ ማመልከቻ አቅርባለች፡፡

የሥር ፍ/ቤት ታህሣስ 06 ቀን 2003 ዓ.ም ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ በማለት የሰጠው ትእዝዛ በይዘቱም ሆነ በሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት የእርቅ ስምምነቱ ሕግና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን በመቀበልና በማረጋገጥ የመዘገበው መሆኑ የሚያሣይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 377 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተቀብሎ አጽድቄዋለሁ ብሎ በዝርዝር ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ውስጥ አለመፃፉ ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉትን የእርቅ ውል ተቀብሎ አላፀደቀውም፣አልመዘገበውም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት ህጋዊ ውጤትና አስገዳጅነት በሚያገኝበት መንገድ ትእዛዝ ከሰጠ፣ ተጠሪዎች በፍርድ ቤቱ በማህተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ትእዛዝ የሰጠበትን የእርቅ ስምምነት እንዲፈፀምላቸው መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች በክርክሩ ተካፋይ ሣልሆን የሥር ፍርድ ቤት ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ እውቅና በሰጠውና ባፀደቀው ተጠሪዎች ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በእኔ ንብረት ላይ የተደረገ ነው፡፡ ክርክሬንና ማስረጃዬን አቅርቤ ፍርድ ቤቱ ለተጠሪዎች ስምምነት እውቅና ለመስጠትና ለመመዝገብ የሰጠው ትእዛዛ ሊሰረዝልኝ ይገባል በማለት ያቀረበችው የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ

ትእዛዝ ማለት ውሣኔ የተለያና በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማናቸውም አይነት እንደ ብይን የሚቆጠር ተፈፃሚ ትእዛዝ ማለት እንደሆነ የተሰጠው ትረጓሜ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የእርቅ ስምምነት መጽደቁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር. 227 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤትና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ያገናዘበና መሠረት ያደረገ ጥያቄ ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ለተጠሪዎች የእርቅ ስምምነት እውቅና የሰጠበትንና የመዘገበበትን ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝና ከዚሁ ትእዛዝ ጋር ሕጋዊ ተፈፃሚነት ያገኘው የሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት በመቃወም ተከራካራ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ካላስረከበች መብቷን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 ሆነ በሌላ መንገድ ለማስረከብ የማትችል መሆኑን አልተረዱትም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 የሰጡት ትርጉም የጠበበ ነው፡፡ እንደዚሁም የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤት ትእዛዝ ተረጋግጦና ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ መባሉ የፍርድ ያህል አስገዳጅነት ያለው መሆኑና አስገዳጅነቱን ለማስቀረት እርቁን ያፀደቀው ፍርድ ቤት እርቁ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም እርቁን የፀደቀው ፍርድ ቤት እርቁ ለሕግና ለሞራል ተቀራኒ አይደም በእርቁ መሠረት ይፈፀም በማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሰጠውን ትእዛዝ መሰረዝ አስፈላጊ መሆኑን ሣያገናዝቡ አመልካች ያቀረበችውን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጋቸው ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18281 የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 118786 ነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደጉት የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤቱ እውቅና ሊሰጠውና ሊመዘገብ አይገባም በማለትና ፍርድ ቤቱ ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት ያቀረበችውን ማመልከቻና ማስረጃ እንደዚሁም ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በመቀበልና በመመርመር በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360 መሠረት የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ጉዳይ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 84446

ሚያዝያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አደነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ጠበቃ አንበርብር ዓባይነህ አልቀረቡም

**ተጠሪ፡** የፍትሕ ሚኒስቴር አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች የጠበቆችን ስነ ምግባር ደንብ ተላልፎ ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቷል በሚል በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24/3 መሰረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች የዲስፐሊን ጉባኤ ውሳኔ ተሰጥቶ በፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር የጸደቀው ውሳኔ አግባብነት በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ክርክር ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በመነሳት ለጉዳይ አግባብነት ካለው ከዚህ ህግ አንፃር ለማየት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በጥብቅና ተወክሎ የሚከራከርበት ጉዳይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተወስኖ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በይግባኝ ታይቶ የፀናውን እና በፍርድ ያለቀ ጉዳይ መሆኑን እያወቀ እንደገና በዚያው በፍርድ ያለቀው ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንደገና አቤቱታ ከማቅረብ በፊት በፍርድ ባለቀው ጉዳይ የተለየ ዳኝነት እንዲሰጥ በማድረጉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 ከተወሰነው ድንጋጌ አንፃር ይኸው ተግባሩ የሙያ ጥፋት ሆኖ ስለተገኘ በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24/3/ መሰረት ጥፋተኛ ለዚህም ጥፋቱ ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቃጮ እንዲቀጣ በአዋጅ መሰረት በፈዴራል ጠበቆች የዲስፐሊን ጉባኤ ተወስኖ ሚኒስቴር ሚኒስትር በመጽደቁ እና ጉዳዩንም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በማጽናቱ ምክንያት የአሁን አመልካች ይህንኑ የመጨረሻ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲል ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በማቅረብ ነው::

የፍትሕ ሚኒስቴርም በተጠሪነቱ በጉባኤው የተሰጠው ውሳኔ በህጉ አግባብ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለትም በጽሁፍ መልሱን አቅርቧል፡፡

ከላይ በጭሩ እንደተመለከተው አሁን አመልካች ጉዳዩን በጥብቅና ይዞ ክርክር ያደረገበት የአፈፃፀም ጉዳይ ነው ለአፈፃፀም መሰረት የሆነው ዋናው ፍርድ በመ/ቁ 05802 በቀን 09/10/2002 የተሰጠው ሲሆን የፍርዱም የተፈፃሚ ክፍል ‹‹… የሚቻል ከሆነ በዓይነት …. ይህ ሁሉ ካልተቻለ ንብረቱ በሐራጅ ተሸጦ በፍርዱ በተመለከተው የድርሻ መጠን መሰረት ይከፋፈሉ የሚል ነው፡፡



www.chilot.me

ይህንንም ፍርድ ለማስፈፀም ሲባል ለተከፈተው በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 173354 የሆነው የአፈፃፀም መዝገብ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲመለከት ቆይቶ እንደ ፍርዱ ንብረቱን በዓይነት ለማካፈል የሚቻል መሆኑን በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በባለሙያ ተረጋግጦ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ከባለሙያ በቀረበው ማረጋገጫ መሰረት ንብረቱን በዓይነቱ ለማከፋፈል አይቻልም ከሚል መነሻ ተነስቶ ንብረቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጠበት መሆኑና በዚህም ትዕዛዝ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞ ስለማሰናበቱ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

እንዲሁም የፍርድ አፈፃፃም መመሪያው ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ንብረቱን በማየት ቦታውን በዓይነት ማካፈል የሚቻል ሲሆን ቤቱን በተመለከተ ግን ከቤቱ አተማመን አኳያ እኩል በእኩል ለማካፈል እንደማይቻል ሆኖም ትንሹንም ድርሻ ቢሆን አሁን አመልካች የወከሏቸው በአፈፃፀም መዝገቡ ላይ 1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የነበሩት ጠይቀዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ማስፈፀም ይቻል እንደሆነ ማብራሪያ ይሰጥበት በሚል ገልፆ እያለ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ግን ከዚሁ ከፍርድ አፈፃፀም መመሪያ የተሰጠን ሙያዊ መግለጫ ከደረሰው በኋላ እንደ ፍርዱ ንብረቱን በዓይነት ለማካፈል የልቻል አይደለም ከሚል መደምደሚ ደርሶ በመጨረሻው የፍርድ አማራጭ መሰረት ንብረቱ በሐራጅ እንዲሸጥ በሚል ትዕዛዝ የሰጠበት ስለመሆኑም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ በሐራጅ ይሸጥ በተባለው ትዕዛዝ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ ተቀባይነት ካጣ በኋላ አሁን አመልካች አፈፃፀሙን በመጀመሪያ ደረጃ ለያዘው ፍ/ቤት ደንበኛቸው ንብረቱ በሐራጅ ከሚሸጥ ይልቅ በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል እንደተረጋገጠው ቢጎዳም አነስተኛው ድርሻ ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል ስለሆነም በዚሁ መሰረት እንዲፈፀም ይታዘዝልኝ በማለት በመጠየቃቸው ፍ/ቤቱ እንደጥያቄው ተቀብሎ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በዚህ አኳኋን ቀድሞ ሰጥቶት የነበረውን የሐራጅ ሽያጭ አማራጭ ትቶ አመልካች እንዳቀረበው አቤቱታው በዓይነት ይካፈሉ ብሎ ካዘዘ በኋላ እንደገና መዝገቡን አንቀሳቅሶ ከዚህ በፊት በሐራጅ ተሸጦ ይከፋፈሉ በሚል የሰጠው ዳኝነት በይግባኝ ታይቶ የጸና መሆኑን የ1ኛ ፍርድ ባለዕዳ እያወቀ እንደገና በፍርዱ ባለቀ ጉዳይ ላይ አዲስ ጥያቄ በማቅረብ የተለየ ዳኝነት እንዲሰጥ አስደርጓል፡፡ ይህም አግባብ አይደለም በማለት በዓይነት ክፍያውን አማራጭ አንስቶ የአሁን አመልካች ፍ/ቤቱን በማሳሳት ለፈፀመው ተግባር ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው አመልካች የጥብቅና ሙያ ስነ ምግባር ከሚያዘው ውጭ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ አቤቱታ በማቅረብ በሚል ጉዳይ ላይ መጉላላቱንአስከትሏል፡፡ ይህም አድርጊቱ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 አንፃር ሲታይ ሙያዊ ጥፋት መፈፀሙን ያረጋግጣል በማለት ጥፋተኛ ብሎ የገንዘብ መቀጮ የቀጣው ስለመሆኑ ሁሉ የተረጋገጡ ጉዳዮች ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭር ባጭሩ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም የጉባኤውን ውሳኔ አግባብነት እንደሚከተለው መረምረናል፡፡

በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 ተፈፃሚነቱ ከታች ወደ ላይ የተዋቀሩት ፍ/ቤቱ ዋናውን ጉዳይ አከራካሪው ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ብቻ የተወሳነ ስለመሆኑ ከአፈፃፀም ቢመለስ በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ የቀረቡት ጉዳዮች አካሄድ

የሚመሩበት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌዎች ያላቸውን የተፈፃሚነት ውስን በሚደነግገው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 32 ተመልክቷል፡፡

ይህ ለዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የአፈፃፀም እንደመሆኑ መጠን ይኸው በቁጥር 5 የተመለከተው ስነ ሰርዓታዊ ድንጋጌ በዚህ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው አይደለም፡፡

ይልቁንም የተፈረደ ፍርድን በማስፈፀም ሂደት የጉዳዩ አካሄድ የሚጣራው ስለፍርድ አፈፃፀም በተመለከቱት እራሳቸውን ችለው በተዘረጉት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ነው በዚህም የአፈፃፀም ጉዳይ የሚመለከትን ስርዓት አስመልክቶ በተደረገው ስነ ስርዓታዊ ዝርዝር የህግ ክፍል ማየት እንደሚቻለው የአፈፃፀም ጉዳዩን የያዘ ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ በማስፈፀም ረገድ ከፍርዱ ይዘት ሳይወጣ እንደፍርዱ ተቋጭቶ መዝገቡ እስኪዘጋ ድረስ በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ ፍርድ የማስፈጸሚያ ስልትና ዘዴ በመከተል የተለያዩ ትዕዛዞችን ለመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል

በዚህ ጉዳይ በአፈፃፀም መዝገቡ ላይ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ንብረቱ በሀራጅ ተሸጦ እንዲከፋፈሉ ይደረግ ብሎ ካዘዘበት ጊዜ ጀምሮ ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ ችሎት ደርሶ ከፀናና እንደገና አሁን አመልካች እንደገና የአፈፃፀም ችሎት ቀደም ሲል ንብረቱ ተሸጦ ይከፋፈሉ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ አግባብነቱ እንደገና ይታይልኝ በማለት እስከጠየቀበት ድረስ ፍርዱ ፍፃሜ ያገኘ ጉዳይ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

ከዚህ በላይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡትን ጉዳዮች በተጠቀሰበት በዚህ ፍርድ ላይ እንደተገለፀው ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ የሰጠው ሙያዊ ማረጋገጫ ይዘት ንብረቱን በዓይነት ለማካፈል የሚቻል አይደለም በሚል ሳይሆን አንደኛውን ወገን ጠቅሞ ሌላኛውን ወገን ካልጎዳ በቀር ማካፈል ይቻላል በዚህም መሰረት 1ኛ የፍርድ ባልዕዳ ቢጎዳም ልጎዳ በማለት እነስተኛው ድርሻ ተሰጥቷቸው ክፍፍሉ በዓይነት እንዲደረግ ጠይቀዋል ይኸው ታይቶ አስፈላጊው ዳኝነት ይሰጥበት የሚል ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ በዘፈቀደ ንብረቱ በሐራጅ ይሸጥ በማለት ማዘዙ ስህተት የፈፀመ መሆኑን ያስገነዘበው ጉዳዩም ፍፃሜ አግኝቶ ባለጉዳዮች የተሰናበቱ እስካልሆነ ድረስ ፍርድን ተገቢ በሆነ መንገድ በማስፈፀም ረገድ ለአፈፃፀም ፍ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተስተካከለ ዳኝነት እንዲሰጥ የአሁን አመልካች ለደንበኛው ተገቢን ሙያዊ ድጋፍ ማሰጠት ካለበት ግዴታ አንፃር ለፍ/ቤቱ አመልክቷል ከሚባል በቀር የፈፀመው መያዊ ጥሰት አልተሰተዋለበትም፡፡

በፍርዱ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ድርሻ ግማሽ ቀሪው የሌሎች ተከራካሪዎች እንደመሆኑ መጠን ንብረቱን በዓይነት ለማካፈል ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለውን ለመለየት ይኸው የፍርድ ባለዕዳ ግማሽ ድርሻ መነሻ ከሚሆን በቀር የቀሪውን ግማሽ ድርሻ ቀሪ ተከራካሪዎች በዓይነት ሊከፈሉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ነጥብ ሊሆን አይገባም በዚህም ምክንያት ግማሹ ድርሻ ለቀሪ ሶስት ወገኖች የሚከፈፈል የመሆኑ ጉዳይ የአፈፃፀሙን አካሄድ ሊያስቀይረው የሚችል ሆኖም አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የዲስፕሊን ጉባኤ ለጉዳዩ አግባብነት ከሌለው ድንጋጌ አንፃር እንጂ ፍርድን እንደ ፍርዱ በተገቢው መንገድ በሚስፈጽም ረገድ ፍ/ቤቱ ሊከተለው ከሚገባው ስርዓት አንፃር ባለማየቱ ምክንያት የአሁን

በአመልካች ሙያዊ ጥፋት ፈጽሟል ሲል የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቀጠይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ መነሻ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁ ነው 125177 ጳጉሜ 01 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች በወሰነበት መሰረት የገንዘብ መቀጮውን ክፍያ ፈፅሞ ከሆነ ለገንዘብ መቀጮው ምክንያት የሆነው ውሳኔ የተሻረ ስለሆነ ገንዘቡ እንዲመሰለት ታዟል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ
3. በዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 85718

ሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ቴዎድሮስ አማረ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አዲሱ ፍሰሃ ጠበቃ አቶ አባቡ ሞላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአላማጣ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02693 ህዳር 19 ቀን 2005ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲሽርልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አላማጣ ምድብ ችሎት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ሟች ወ/ሮ አስካለ አርአያ መስከረም 10 ቀን 1993ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይታለች፡፡ ሟች ተወላጅና እናትና አባታቸው የሌሉ በመሆኑ በእናት መስመር የተከሣሽ/ አመልካች/ እናት የሆነችው ወ/ሮ አረጋነሽ አርአያ በእናት መስመር የእናቷ ልጅ የሆነችው ወ/ሮ ብርታንን ፋንታዬ ወራሾች መሆናቸው በወፍላ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 0793 02-06-1993ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ ወ/ሮ ብርታንን ፋንታዬ የሟች አስካለ አርአያ ወራሽ መሆኑን ካረጋገጠች በኂላ ከዘጠኝ ዓመት በኂላ ህዳር 28 ቀን 2001ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፡፡ እኔ የሟች ብርታንን ፈንታዬ ተተኪ ወራሽ መሆኔ የሰቆጣ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 4609 ታህሣስ 16 ቀን 2001ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አውራሽ ወ/ሮ ብርታንን ፈንታዬ ከሟች አስካሉ አርአያ በኮረም ከተማ 01 ቀበሌ ከሰራችው ሁለት ክፍል ቤት የሚደርሳት አንድ ክፍል ቤት ተከሣሽ እንዲያስረክበኝና ስመ ንብረቱ እንዲዛወርልኝ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡
2. አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ ተጠሪ ከዚህ በፊት በኮረም ወረዳ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦብኝ የወረዳው ፍ/ቤት ጥር 2 ቀን 2004ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡
ስለዚህ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ስለሆነ በድጋሚ ሊቀርቡብኝ አይገባም የሚል ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርቧል፡፡ የአላማጣ ምድብ ችሎት የኮረም ከተማ ፍርድ ቤት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የተጠሪንና



www.chilot.me

የአመልካችን ክርክር ከሰማ በኃላ የተከሣሽን /የተጠሪን/ ክስ ውድቅ በማድረግ ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ገልፆ የከሣሽ /ተጠሪ/ መኖሪያ አማራ ክልል ሰቆጣ ከተማ የተከሣሽ መኖሪያ ትግራይ ኦፍላ ወረዳ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/1985 አንቀጽ 5/2/ መሠረት ስልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሆኑ የኮረም ወረዳ ፍርድ ቤት በሌለው የዳኝነት ስልጣን የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ እንዳይወሰን የሚገድብ አይደለም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአመልካቾችና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች አንድ ክፍል ቤት ለተጠሪ እንዲያካፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ፀንቷል፡፡

3. አመልካች ታህሣስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የኮረም ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ሣይሻር የአላማጣ ምድብ ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/1/ ድንጋጌ በተዛባ መንገድ በመተርጐም ያቀረቡኩትን የመጀመሪያ የፍርድ መቃወሚያ በማለፉ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ በሟች አስካለ አርአያ ጋር ምንም አይነት ዝምድና የሌለው በመሆኑ የውርስ ንብረት እንዲካፈል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 27 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አውራሽ ቀደም ብላ ሟች አስካለ አርአያን ወራሽ መሆኗን አረጋግጣለች የኮረም ወረዳ ፍርድ ቤት ጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም ከሥር ነገር የዳኝነት ስልጣኑ ውጭ በማየት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አለመሆኑን በማየት ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአላማጣ ምድር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. የሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አላማጣ ምድብ ችሎት ቀደም ሲል በኮረም ወረዳ ፍርድ ቤት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ አይደለም በማለት ተጠሪ ያቀረበለትን ክስ በማየት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ማፅናታቸው የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች የሟች አስካለ አርአያ የውርስ ንብረት የሆነውንና በኮረም ከተማ የሚገኘውን ቤት እንዲያካፍለው በኮረም ከተማ ምድብ ችሎት ክስ አቅርቦ፣ የኮረም ከተማ ምድብ ችሎት የተጠሪን /የከሣሽንና/ የአመልካችን /የተከሣሽን/ ክርክር ህዳር 10 ቀን 2004 ዓ.ም ከሰማ በኂላ የከሣሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ጥር 2 ቀን  ዓ.ም ብይን የሰጠ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአላማጣ ምድብ ችሎት ያረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የዳኝነት ስልጣን ያለው የኮረም ከተማ ምድብ ችሎት ተጠሪ አመልካች ቤቱን እንዳካፍለው ያቀረበውን ክስ በማየት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320/1/፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 314፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 327 እና ሌሎች አስገዳጅ የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበት አልተሻረም ወይም አልተለወጠም፡፡ ተጠሪ የኮረም ወረዳ

ምድብ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ፣ በሁለት ክልል ኗዋሪዎች መካከል የተነሣውን ክርክር በማየት ውሣኔ መስጠቱ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 4 የሚቃረን ስለሆነ በይግባኝ ታይቶ እንዲሻርለት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ፣ የኮረም ምድብ ችሎት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ያላሻረ በመሆኑ ውሣኔው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለው መሆኑ የሚቀርበት ምክንያት የለም፡፡

6. የኮረም ምድብ ችሎት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በሕግ ከተሰጠው የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ውጭ የሆነ ጉዳይ በማየት የሰጠው ቢሆንም፣ ይህ ውሣኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልተደረገ በስተቀር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212 በጉዳዩ ላይ አስገዳጅነት ያለውና የመጨረሻ ውሣኔ ነው፡፡ በመሆኑም የኮረም ምድብ ችሎት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በይግባኝ ወይም በሰበር ታይቶ ባልተሻረበት ሁኔታ በዚያው ጉዳይ ተጠሪ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አላማጣ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02693 ያቀረበው ክስ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ የአላማጣ ምድብ ችሎት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ የተዛባ ትርጉም መስጠት የኮረም ምድብ ችሎት ቀርቦ ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርድ ባለቀና ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ያልተሻረ ሆኖ እያለ ተጠሪ ያቀረበውን ክስና ክርክር በማየት ሚያዝያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የአላማጣ ምድብ ችሎት የፈፀመውን የሕግ ስህተት ሣያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአላማጣ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02693 የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26210 የሰጠው ትዕዛዝ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 56287 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በኮረም ከተማ ምድብ ችሎት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርድ ያለቀ በመሆኑ ተጠሪ ይህንን ውሣኔ ለይግባኝ ወይም በሌላ የፍርድ ማረሚያ ሥርዓት ሣያሽር ሌላ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 511 መሠረት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ማ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 86454

ግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሪታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ት ፍሬወይኒ አለም በ VC ቀርባለች፡፡

2. ወ/ት ሣምራዊት አለም
3. አቶ በረከት አለም፡ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ አለም መሐሪ ጠበቃ አቶ ምናስቦ ገብሩ ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከንብረት ግምት ክፍያ ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በት/ብ/ክ መንግስት አዲግራት ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከወ/ሮ አለምነሽ ተ/ብርሃን ጋር በትዳር ተሳስሮ በመኖር ላይ ሳሉ በመካከል ለስራ ወደ ምዕራብ ትግራይ ሄዶ በቆዩበት ወቅት አመልካቾች የተጠሪን የመጥፋት ውሣኔ በማሳወጅና ከዚያ በኂላም ውርስ እንዲጣራ በማድረግ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረው ግምቱ ብር 80,000 የሆኑ 4 ክፍል ቤቶች ግማሹ ድርሻ ወደ ባለቤታቸው ስም ቀሪውን የተጠሪ ግማሽ ድርሻ ደግሞ ወራሾች ለሆኑት ወደ አመልካቾች ስም በማዘጋጃ ቤት በኩል ተላልፎ እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ አሁን ለስራ ከሄድኩበት ተመልሼ አመልካቾች የሰጡትን የመጥፋት ውሣኔም ስላስነሳው በዚህ ምክንያት ተወርሶና ወደ አመልካቾች ስም ተላልፎ የነበረው የቤቱ ግማሽ ድርሻዬ ወይም ንብረቴን እንዲመልሱልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ ያሁኑ አመልካቾች /የስር ተከሣሾች/ በበኩላቸው ቀርበው ለክሱ በሰጡት መልስ የቤቱ ግምት ብር 80,000 ሳይሆን ከ200,000 በላይ መሆኑንና ከመጥፋቱ በፊት በተጠሪ ስም የነበረው ባዶ መሬት ብቻ መሆኑንና የባዶ መሬት ባለቤት ደግሞ መንግስት እንጂ ተጠሪ ባለመሆኑና ተጠሪ ከጠፋ በኂላ በባዶ መሬቱ ላይ ሀብታችን አፍስሰን የሰራነውን ቤት ከ 18 ዓመት በኂላ መጥቶ ሊጠይቅ እንደማይገባ በመጀመሪያ መቃወሚያነት የተከራከሩ ሲሆን ፍሬ-ጉዳዩን በተመለከተም ቤቱ በባዶ መሬት ላይ በእኛ በአመልካቾች መሰራቱ ታውቆ በህጋዊ መንገድ ወደ ስማችን የተዛወረ

በመሆኑ የተጠሪ አይደለም፡፡ ሆኖም ግን ባዶ መሬቱ ለተጠሪ ሲሆን ይገባል ከተባለም ቤቱ በባለሙያ ተገምቶና በግምቱ መሰረት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ወረዳ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር 5 የአመልካቾች ምስክሮች ሰምቶ በተጠሪ በኩል ከቀረቡት ሰነድ ማስረጃዎች ጋርም በማገናዘብ ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ ምንም እንኳ ቤቱን የሰሩት አመልካቾች ስለመሆናቸው በእነሱ በኩል ቀርበው በተሾሙት ምስክሮች ቢነገርም ከዚህ ቀደም ውርሱ በአመልካቾች እንዲጣራ ሲደረግ ቤቱ የተጠሪ እንደሆነ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ የተገለፁ በመሆኑና አሁን ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ቤቱ የአመልካቾች ነው በማለት የቀረበው ክርክር እርስ በራሱ የሚጣረስ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ለክርክሩ መነሻ የሆነውና ወደ አመልካቾች ስም የተላለፈው ሁለቱ ክፍል ቤቶች ለተጠሪ ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካቾችም በተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለምስራቃዊ ዞን ማዕከላይ ፍ/ቤት አቅርበውና ግራ ቀኙም ቀርበው እንዲከራከሩ ከተደረገ በኂላ ክርክር የተነሳበት ቤት በአመልካቾች መሰራቱ ተረጋግጦ ሳለ አመልካቾች ያለ ምንም ግምት ክፍያ ቤቱን ለቀው ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሣኔ አለአግባብ መሆኑን ከገለፁ በኂላ ተጠሪ በባለሙያ ተገምቶ በቀረበው ግምት መሰረት የቤቱን ግምት ብር 160,482.765 ለአመልካቾች ከከፈሉ በኂላ ቤቱ ተመልሶለት በስሙ እንዲመዘገብ በማለት የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ይህንን ውሣኔ በመቃወም የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ቀርበው እንዲከራከሩ ከተደረገ በኂላ አመልካቾች የቤቱ ግምት እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ክስ ወይም የተከሣሽ ከሳሽነት ክስ በሌለበትና እንዲሁም በአመልካቾች የተከፈለ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሳይኖር ተጠሪ ራሱ ዳኝነት ከፍሎ ባስከፈተው መዝገብ ላይ ብር 160,482.765 እንዲከፈላቸው በዞኑ ፍ/ቤት መወሰኑ ስነ-ስርዓታዊ አይደለም በማለት ይህንን በሚመለከት የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል ሽሮ ሆኖም ግን ንብረቱ ለተጠሪ ሊመለስ ይገባል በማለት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ /የውሣኔ ክፍል/ በማፅናትና አመልካቾችም በቦታው ላይ ሀብታቸውን አፍስሰናል የሚሉ ከሆነ ይህንን በህጉ አግባብ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን በመግለፅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ደግሞ በተራቸው በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታው በድምፅ ብልጫ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተወስኖና በክልሉ ሰበር ችሎት ድምፅ ብልጫ የፀናውን በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም በአንድ በኩል ንብረቱ ለተጠሪ ይመለስ እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ እኛ አመልካቾች የንብረታችንን ግምት ከሳችሁ ጠይቁ በማለት የተሰጠው ውሣኔ ጊዜና ጉልበት ከማባከን ውጪ ሌላ ለውጥ ስለሌለው ውሣኔው ተሽሮ በፍ/ብ/ህ/ቁ 171/1/ ድንጋጌ መሰረት ያፈሰስነው ሀብት ግምታችን እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠበት ሲሆን አመልካቾችም የመ/መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የሰበር አቤቱታ በቀረበበት ውሣኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ ሊመረምር የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ እንደሚቻለው ከሳሽ የነበረው የአሁን ተጠሪ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዳኝነት ጠይቆ እየተከራከረ ያለው ወደ አመልካቾች ዞሮ የነበረው ንብረቴ ይመለስልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካቾችም በበኩላቸው ንብረቱ ለተጠሪ የሚመለስ ከሆነ በቦታው ላይ ያፈሰስነው ሀብት በባለሙያ ተገምቶ ግምቱ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል መከራከሪያ ነጥብ በማቅረብ እየተከራከሩ ያሉ መሆናቸውን መገንዘብ ችለናል፡፡ ሆኖም ግን አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ተከሳሾች እንደመሆናቸውና እነሱም በበኩላቸው ከተጠሪ የሚጠይቁት መብት ካላቸው በህጉ አግባብና በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 234/1/ /ረ/ መሰረት ከመከላከያ መልሳቸው ጋር የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 215/2/ ስር እንደተመለከተው በመፈፀም በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የተጠቀሰው የቤቱ ግምት እንዲከፈላቸው በሚል የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ የለም፡፡ በዚህ አግባብ ተሟልቶ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ በለሌበት ደግሞ ዳኝነቱ ሊሰጥ አይችልም፡፡

በሌላ በኩል ከፍ ሲል እንደተገለፀው የአመልካቾች ክርክር የቤቱ ግምት እንዲከፈላቸው ይወሰንልን በማለት ከመከራከር ውጭ ጨርሶ ቤቱንም ልናስረክብ አይገባም የሚል አይደለም፡፡ ጥያቄያቸው ይህ ከሆነ ደግሞ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ችሎቱ ግምቱ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ውሣኔ የሰጡ ሣይሆን ይህ የዳኝነት ጥያቄቸው በዳኝነት አካሉ ተቀባይነት አግኝቶ ሊስተናገድ የሚገባው መጀመሪያውኑ በህጉ አግባብ ስርዓቱን ጠብቆ ሲቀርብ መሆኑን በማለት ነው፡፡ አመልካቾችም እራሳቸው ይህንኑ መሆኑን ተረድተው ይህ አከራካሪው የቤቱ ግምት እንዲከፈላቸው በተጠሪ ላይ ስልጣን ሳለው ፍ/ቤት አዲስ ክስ ማቅረባቸውን ተጠሪ ለሰበር አቤቱታ መልሱን ሲሰጥ ጠቅሶ ባቀረበው ክርክር ላይ ምንም ያሉት ነገር የለም ይህ ደግሞ እርግጥም እንደተባለው በዚህ ጉዳይ አዲስ ክስ ያቀረቡ መሆናቸውን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 234/1/ /ሠ/ እና 235 /2/ ስር እንደተመለከተው እንደመሆኑ ተቆጥሮ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል ከፍ ሲል በተገለፁት ምክንያቶች የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የዳኝነት አገልግሎት ፈፅመው ዳኝነቱንም በስርዓቱ ባላቀረቡበት ሁኔታ ይህ የተጠቀሰው የቤቱ ግምት ብር 160,482.765 ተጠሪ ራሱ ዳኝነት ከፍሎ ባስከፈተው መዝገብ ላይ ሊወሰንላቸው አይገባም በማለት ተወስኖ በሰበር ችሎቱም በድምፅ ብልጫ እንዲፀና በማለት በተሰጠው ትእዛዝ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መ/ቁ 54034 ጥቅምት 26 ቀን 2005 በዋለው ችሎት ተወስኖ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 55375 ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡
3. በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 86510

ሰኔ 18 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ሙሉ ኤሌክሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ ታደሠ ጉርሙ ቀረቡ

**መልስ ሰጪ፡-** ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል /አ.አ/ ነ/ፈጅ ዳንኤል ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከውል አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የተነሳውን የክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም የአሁኑ አመልካች ለልብ ሕመማን አገልግሎት የሚውል ECLO car diagram ultra sound GE modele VIVID of system የተባለ የልብ ህክምና መመርመሪያ መሳሪያ ለተጠሪ ለማስረከብ ውል ተዋውሎ ቅድሚያ ክፍያ 30% ብር 702,000.00 /ሰባት መቶ ሁለት ሺ ብር/ ተቀብሎ መሳሪያውን ሊያቀርብ ያለመቻሉን ገልፆ መሳሪያውን በአስቸኳይ እንዲያቀርብ ካልሆነም በቅድሚያ የወሰደውን ገንዘብ እጥፍ አድርጎ ብር 1,404,000.00 ከነወለዱ እንዲከፍለን ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር ውል መዋዋሉንና የቅድሚያ ክፍያ መቀበሉን ሳይክድ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሳሪያ ለተጠሪ ያላስረከበው መሆኑን ገልፆ መሳሪያውን ለማምጣት ኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የግዥ ውል ከጠቅላላ ሰነድ ጋር ቀርቦለት እንዲፀድቅ መጠየቅ እንዲሁም መሳሪያው ከውጪ እንደሚመጣ በመሆኑ ባንክ ምንዛሬ እንዲፈቅድ መጠየቅ ስለነበረበት ተጠሪም ትብበር እያደረገ ስምምነቱ ከተደረገበት ባንክ እስከ ተፈቀደበት ሚያዚያ 12 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ አስራ አንድ ወራቶች መቆጠራቸውን መሳሪያው ወደ አገር እንዲገባ የሚፈቅደው አካል ደግሞ ያልፈቀደለት በመሆኑ እየተጠባበቀ የሚገኝ መሆኑንና በዚህ ችግር ምክንያት ውሉን ያልፈጸመ ስለመሆኑ ገልጾ መሳሪያውን እንዲያስረክብ እንዳደረግ ይህ የማይፈቀድ ከሆነ ተጠሪ የቅድሚያ ክፍያ እጥፍ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ በውሉ ከተቀመጠው ግዴታ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከተሰማ በኋላ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በውሉ በተመለከተው ግዴታ መሰረት መሳሪያውን ማስረከብ ከሚገባበት ከሐምሌ 12ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ሲታሰብ 437 ቀናት ማለፋቸውንና ለእያንዳንዱ ቀን 0.1% መቀጮ የግዥ ዋጋ ከሆነው ብር 2,340,000 .00 ሲታሰብ ብር 999, 180. 00 /ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰማንያ ብር/ የሚመጣው ገንዘብ በመቀጮነት አመልካች ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው መሆኑን ገልፆ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል እንዲሁም የቅድሚያ ክፍያ ብር 702,000.00 /ሰባት መቶ

ሁለት ሺህ ብር/ ክሱ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በተጠሪ የተጠየቀውን ዳኝነት ይዘት ያላገናዘበና በጉዳዩ ላይ ሊመሰረት ይገባው የነበረውን ጭብጥ በአግባቡ ያልለየ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው እንዲለወጥ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም አመልካች ብር 999,180.00 በመቀጮነት እንዲከፈል የተወሰነው በተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ቀርቦ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ተደርጓል በሚለው ስምምነት አከራካሪውን እቃ በወቅቱ አመልካች ያላስረከበ መሆኑን ገልጾ እንዲወሰንለት ዳኝነት የጠየቀው የህክምና መሳሪያውን በአስቸኳይ እንዲያስገባ መስሪያውን በውሉ መሰረት ማስገባት ካልቻለ በቅድሚ የወሰደውን ገንዘብ በእጥፍ አድርጎ በድምሩ 1,404,000.00 /አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አራት ሺ ብር/ መሳሪያውን ማስገባት ከነበረበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ገንዘቡን እንዲከፍልና ወጪና ኪሳራም ዝርዝር የማቅረብ መብቱ እንዲጠበቅለት መሆኑን ጥቅምት 02 ቀን 2004 ዓ.ም ተጠሪ ያቀረበው የክስ ማመልከቻ የሚያሳይ መሆኑን አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጠው መልስም ውሉ መኖሩንና ከተጠሪ ቅድመ ክፍያ መቀበሉን ሳይክድ ለውሉ አለመፈጸም ሕጋዊ ምክንያት ናቸው ያላቸውን ምክንያቶችን አንስቶ መከራከሩን ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች ውሉን ለመፈፀም አላስቻለኝም በማለት አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ የልብ መመርመሪያ መሳሪያውን ለማስመጣት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ያለማግኘቱን ጠቅሶ ነው ይሁን እንጂ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ማስረጃ ያለመኖሩንና እቃውን ሳያስገባ ያለፉት ቀናት ብዛት ሲታዩ ፈቃድ ያለማግኘቱን ያሳያል ወይም ውሉን ለመፈፀም ተገቢውን ጥረት አድርጓል ለማለት የሚቻል አለመሆኑን ደምድመዋል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የበታች ፍርድ ቤቶች የልብ መመርመሪያ መሳሪያው ወደ አገር ውስጥ ያልገባው ፈቃድ ከሚሰጠው አካል ፈቃድ ሳይገኝ መቅረቱን አረጋግጠዋል በማለት የተያዘው ፍሬ ነገር ድምዳሜ በበታች ፍርድ ቤቶች የተደረገውን የግራ ቀኙን ክርክርና የማስረጃ ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች መሳሪያውን ለማስገባት የሚመለከተው አካል የከለከለው ስለመሆኑ በማስረጃ ያለማስደገፉ ከተረጋገጠ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1792 ድንጋጌን ጠቅሶ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሚገኝበት አግባብ የለም፡፡

ወደ ዋናው ጭብጥ ስንመለስም ከላይ እንደተገለፀው በተጠሪ ከተጠየቁት ዳኝነቶች መካከል አንዱ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ እጥፍ ሁኖ እንዲመለስ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ዳኝነት የሰጠው ግን አመልካች እቃውን ማስገባት

ከነበረበት ከሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ በሚታሰብ 427 ቀናት ማለፋቸውንና ለእነዚህ ቀናትም የውሉን ጠቅላላ ዋጋ ብር 2, 340,000. 00 0.1% ሲታሰብ የሚመጣውንና ከውሉ ዋጋ 10% ያልበለጠውን መቀጮ አመልካች በውሉ አንቀጽ 2.3/ለ/ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731 ለመክፈል ይገደዳል የሚል ምክንያት ይዞ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አመልካች የቅደም ክፍያ የከፈለ ሁኖ እያለ ቀብድ አድርጎ እጥፍ መጠየቁ ስህተት መሆኑን አምኖ ክሱ ሊመሰረት የጠየቀው ዳኝነት የቅድመ ክፍያ እጥፍ ቢሆንም ክሱ በተሰማበት ወቅት የመቀጫ ገንዘብ መጠየቁ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናቱን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ ክርክር የሚመራውና ዳኝነት የሚሰጠው በህጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡ በህጉ ከተዘረጋው የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣት ስርዓት ውጪ ክርክር የመምራትና ዳኝነት የመስጠት አካሄድ የዳኝነት ሰጪ አካሉን ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚሰጠው በተከራካሪ ወገን የተጠየቀ ሁኖ በሕጉና በውሉ የተፈቀደ መሆኑን በጥንቃቄ አረጋግጦ ሲሆን ተከራካሪ ወገን በሕጉ ወይም በውሉ የተፈቀደለትን መፍትሔ ለማግኘት በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ የሚገባው መሆኑን ስለክስ አመሰራረትና የመከላከያ መልስ አቀራረብን የሚደነግጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 222፣234፣235፣236 እና 83 ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 224 እና 182 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር ተዳምረው ሲታዩ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የዳኝነት ጥያቄ አይነትና መጠኑን በክሱ ማመልከቻ በግልጽ መስፈር ያለበት መሆኑን ያሳያል ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 224 ድንጋጌ ጠቅላላ ይዘቱ ሲታይም ከሳሹ በጉዳዩ ላይ የሚጠይቀው ዳኝነት ጠቅላላ ፍርድ ቤቱ የክሱን ጭብጥና የማስረጃውን አከባቢ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ትክክለኛ መስሎ የታየውን ፍርድ ሊሰጥ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 241 ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ ተከራካሪ ወገኖች/ በጽሑፍ ያቀረቡትን ክርክር ለማብራራትና በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 246-248 ድንጋጌች አግባብ ጭብጥ ለመመስረት እንዲያገዝ ሲሆን በጽሑፍ ማመልከቻው ላይ ያልሰፈረን ዳኝነት ለመጠየቅ የሚስችል ያለመሆኑን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያስረዳል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ከመጀመሪያው ክረክር ላይ ካቀረቡት በቀር ሌላ ተጨማሪ ሙግት ወይም ሌላ ማስረጃ ማስቀረብና መመርመር የሚያስፈልግ ከሆነ ወይም ቀድሞ የተያዘው ጭብጥ የሚሻሻል ወይም ተጨማሪ ጭብጥ የሚያዝ መሆኑ ከታመነም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 255 እና 251 አግባብ የሚፈፀም እንጂ ያለህጋዊ ምክንያት በማናቸውም የክርክር ደረጃ የቀረበ ክርክር ሁሉ ተቀባይነት የሚያግኝበት የክርክር አመራር የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የጠየቀው ዳኝነት ቅድመ ክፍያ አጥፍ ሁኖ እንዲከፈል ሲሆን በውሉ በተመለከተው አግባብ መቀጫ እንዲከፈለው በግልጽ አልጠየቀም የቅድመ ክፍያው እጥፍ ሁኖ እንዲከፈለው ጥያቄ ያቀረበው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1883 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተቀመጠውን የቃብድ መሰረተ ሐሳብ ይዞ ስላለመሆኑ የክስ ማመልከቻው ያሳያል እንዲህ ከሆነ አመልካች ለተጠሪ የቅድመ ክፍያውን እጥፍ አድርጎ ለተጠሪ የሚከፍልበት አግባብ መኖር ያለመኖሩ በጭብጥነት ተይዞና የክሱን ጭብጥና የማስረጃውን አካባቢ ሁኔታ መሰረት አድርጎ ዳኝነት ከሚሰጥበት በስተቀር የመቀጫ ገንዘብ በጭብጥነት የሚያዝበት አግባብ የለም፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለቀብድ የያዘው ጭብጥ ተገቢነት ያልነበረው ሲሆን ውጤቱ ሲታይ ተጠሪ በውሉ አለመፈፀም ከአመልካች የሚጠይቀውን ኪሳራ ከመጠየቅ ሊከላከለው የማይገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ አመልካችን የጠየቀው የቅድመ ክፍያ እጥፍ ክፍያ ለጉዳቱ ተገቢ ነው ብሎ ያሰበውና ጠቅላላ አገላለጽ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 224 መሰረት ግንዛቤ የሚወሰድበት ነውና፡፡ ይህ የተጠሪው የክስ ዳኝነት ጥያቄ ዝርዝር ይዘት

ደግሞ ግራ ቀኙ በውሉ ከአቋቋመበትና በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር በመነሳት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በውሉ የተጠቀሰው ስሌት መሰረት ተደርጎ የሚመጣው መጠን በማናቸው ምክንያት ተጠሪ በግልጽ መጠኑን ለይቶ ከአቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ሊበልጥ የሚችልበት የዳኝነት አሰጣጥ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የቅድመ ክፍያውን እጥፍ ሲጠይቅ በውሉ የተቀመጠው መሆኑን ገልፆ ባለመሆኑና አመልካችም የቅድመ ክፍያውን መወስዱን ያልካደው በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ሊገደድ የሚገባው የክፍያ መጠን ቅድመ ክፍያውንና ተጠሪ በመቀጫነት ሊታሰብ ይገባል ያለው የዚሁ ገንዘብ መጠን ነው፡፡ ተጠሪ ውሉን መሰረት አድርጎ ስሌቱን ቢሰራ ኖሮ የመቀጫው ገንዘብ የሚመጣው ብር 999, 180.00 ሲሆን ይህን ባለማድረጉና ቅደመ ክፍያው እጥፍ ነው ሊከፈል የሚገባው ብሎ ዳኝነት በመጠየቁ የመቀጫ ገንዘቡ ከብር 702,000.00 /ሰባት መቶ ሁለት ሺ ብር/ ሊበልጥ የሚችልበት አግባብ የለም በመሆኑም የተጠሪ ክስ ማመልከቻ ጠቅላላ ይዘት ሲታይ ለውሉ ያለመፈፀም የጠየቀው የመቀጫ ገንዘብ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደረሰን በመሆኑ መጠኑን በተመለከተ ግን ተጠሪ በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ የመቀጫ ገንዘቡ 999,180. 00 ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከቅድመ ክፍያ ገንዘብ ጋር ተዳምሮ ሲታይ አመልካች በግልጽ ከጠየቀው ከብር 1, 404,000.00 / አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አራት ሺ ብር/ የብር 297,180. 00 /ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ አንድ መቶ ሰማንያ ብር/ ብልጫ ያለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182/2/ ድንጋጌን በግልጽ የሚጻረር በመሆኑ ከዚህ አንጻር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ አሰጣጥ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 111482 የካቲት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 78582 ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ አመልካች በውሉ ላይ በተመለከተው መሰረት የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፈለው ዳኝነት ያልጠየቀ በመሆኑ በውሉ በተመለከተው ስሌት መሰረት መቀጫውን አመልካች ለተጠሪ ሊከፈል አይገደድም ብለናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የቅድመ ክፍያውን እጥፍ መሰረት አድርጎ የመቀጫ ገንዘቡ እንዲከፈል የተጠየቀ በመሆኑ ለመቀጫ ብር 702,000.00 /ሰባት መቶ ሁለት ሺ/ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች የቅደመ ክፍያው ብር 702,000. 00 /ሰባት መቶ ሁለት ሺ/ በተመለከተ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ከፍል በሙሉ ጸንቷል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪ ክፍሎ ከሆነ በአፈፃፀም ጊዜ እንዲታይለት ከማድረግ ይህ ውሳኔ አያግደውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

ሐ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 87190

ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ቄስ ዳንኤል አርኬ ከጠበቃ ሙሉጌታ ዱላ ጋር ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የኮልፌ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ - አልቀረበችም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የይግባኝ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ አልፏል ወይስ አላለፈም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ክርክር ከተረጋገጠውና ይህንኑ የተረጋገጠውን ጉዳይ መነሻ አድርጎ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዚሁ ጭብጥ ከሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በዋናው ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16273 ፍርድ ሰጥቶ ግራ ቀኙን ካሰናበተ በኋላ የአሁኗ ተጠሪ ግንቦት 21 2004 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 208 መሠረት በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ፍርድ ቤቱ የአሁን አመልካችን ሳይጠራ ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ግንቦት 22 ቀን 2004 በጥያቄው መሠረት ዳኝነት የሰጠበት ስለመሆኑ፣

እንዲሁም ይህ መዝገብ ከተዘጋ በኋላ ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ የአሁን አመልካች በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም የደረሰው ስለመሆኑ የአሁን ተጠሪ ማስተባበያ ያቀረበበት በመሆኑና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም እነዚህኑ ፍሬ ነገሮች መነሻ አድርጎ ዳኝነት የሰጠበት እንደመሆኑ መጠን እነዚህ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ፍሬነገሮች የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የቀረበለትን የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ በይግባኝ ከተመለከተ በኋላ ለአሁን አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ዳኝነት ከደረሳቸው ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ከማለፉ በፊት 9 ቀን የነበራቸው ከመሆኑ አንፃር በዚህ በዘጠኝ ቀን ጊዜ ውስጥ የይግባኝ አቤቱታ አዘጋጅቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለማቅረብ በቂ ጊዜ የነበራቸው ሆኖ እያለ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሳያቀርቡ ምክንያት አለኝ ይፈቀዳልኝ በሚል ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው የይግባኝ አቤቱታ ሊቀርብልኝ ይገባል በማለት የአሁን አመልካች ጥያቄ ያቀረቡበት ዳኝነት የተሰጠው መዝገብ ከተዘጋ በኋላ እንደገና ከተንቀሳቀሰ በኋላ ስለሆነ፤

በዚህ አኳኋን ተንቀሳቅሶ በታየው ጉዳይ ላይ የአሁን አመልካች የበኩላቸውን ክርክር ማቅረብ ይችሉ ዘንድ የመደመጥ መብታቸው እንዲከበር ጥሪ ያልተደረገላቸው ከመሆኑም በላይ መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ተንቀሳቅሶ ዳኝነት የተሰጠበት ስለመሆኑ እርሷ በጊዜው እንዲያውቁት አልተደረገም፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የተቀመጠው የ60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ታሳቢ የሚያደርገው ተከራካሪው ባሉበት ውሳኔ መስጠቱን ወይም ለውሳኔ የሚያበቃ ክርክር የተደረገ መሆኑን ተረድቶ ቀርቦ ለመከታተል እና የዳኝነቱን ውጤት ለመስማትም ሆነ ለማወቅ ያልፈለገውን ወይም ደግሞ የተከራካሪው የመደመጥ መብት ይከበር ይቻል ዘንድ በሕጉ በተዘረጋው መረዳት መሠረት በአግባቡ ጥሪ ተደርጎለት በጥሪው መሠረት ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት ያልቻለ እንደሆነ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ይህ የ60 ቀን ጊዜ መታሰብ ያለበት ስለመሆኑ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን አመልካች ሳይጠሩ ዳኝነት የተሰጠ በመሆኑ አመልካች ሳይጠሩ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም የተዘጋው መዝገቡ ተንቀሳቅሶ ዳኝነት የተሰጠ መሆኑን እንዲያውቀው በጊዜው ያልተደረገ መሆኑ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ ይህ በሕጉ በተቀመጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ተጠቃሚ ሊሆን እንዳልቻለ ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ሕጉ ታሳቢ አድርጎ ባስቀመጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚቻል ከተረጋገጠ ደግሞ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው በቂ ነበረ ወይስ አልነበረም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ዳኝነቱ መሰጠቱን ከተረዳበት ጊዜ ጀምሮ ከቀረው ዘጠኝ ቀን አንፃር በማየት ዘጠኝ ቀን የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ ያስችል ነበር አልነበረም ከሚለው አንፃር ሊታይ የሚገባው አይደለም፡፡

አመልካች በሕጉ ከተሰጠው የ60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ 51 ቀን በፍርድ ቤቱ በተፈፀመው ሥነ ሥርዓት ጉድለት ሳቢያ የባከነበት መሆኑ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ አመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ የቀረው የዘጠኝ ቀን ጊዜ በቂ መሆኑና አለመሆኑ መለኪያ ሊሆን የሚገባ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ የአሁን አመልካች ስለመንቀሳቀሱም ሆነ የመደመጥ መብቱ እንዲከበር ሳይጠሩ ዳኝነቱ መስጠቱ እየታወቀ በዚህም ምክንያት በሕጉ በተሰጠው የ60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ ሊጠበቅ እንዳልቻለ እየታወቀ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንኑ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በቀረው የዘጠኝ ቀን ጊዜ ብቻ ተወስኖ ይህ ዘጠኝ ቀን በጉዳዩ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ በቂ ነበር ወይስ አልነበረም? ከሚለው ማነፃፀሪያ አኳያ ብቻ ተመልክቶ ማስፈቀጃው ተቀባይነት የለውም በሚል የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡



www.chilot.me

**ው ሣ ኔ**

1. ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ማስፈቀጃውን ጉዳይ ተመልክቶ በኮ/መ/ቁ 126464 በቀን 7/5/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች በሕጉ በተሰጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ለመጠቀም በሚያስችላቸው ደረጃ የተሰጠ ዳኝነት በመሆኑ ይህ ዳኝነት መሰጠቱን ከተረዳበት ጊዜ ከሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የይግባኝ አቤቱታ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ ሲሰላ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው እንዳለፈባቸው ስለማይቆጠር በጉዳዩ ላይ የይግባኝ አቤቱታቸውን አቅርበው እንዲያሰሙ ሊፈቀድ ይገባል ብለናል፡ ተፈቅዷል፡፡
3. በዚህ በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ሀ**

የሰ/መ/ቁ. 85102

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሰንደቁ አበበ - ጠበቃ ወንድአወክ አየለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሐብታሙ ቃበቶ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ኑዛዜን መሰረት አድርጎ የቀረበውን የውርስ ንብረት ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ/ም በአቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በመሰረቱት ክስም ተጠሪውና የአሁኑ አመልካች በሞግዚትነት የሚያስተዳድሯት እህታቸው ስመኝ ቃበቶ የአንድ እናትና አባት ልጆች መሆናቸውን፣ከእናታቸው ከሟች ወ/ሮ ነጠር አስፋው የተላለፈላቸው መኖሪያ ቤት በባህርዳር ከተማ ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ እንደሚገኝና አመልካች፣ ተጠሪውና እህቱ ህፃን መሆናቸውን ተገን በማድረግ እንደ አንድ ወራሽ በመሆን በመኖሪያ ቤቱ ላይ የውርስ ማስረጃ በማውጣት ከ1989 ዓ/ም ጀምሮ ባለድርሻ ሁነው የቤቱን ኪራይ ተካፋይ ሲሆኑ መቆየታቸውን፣ተጠሪም ይህንኑ የአሁኑ አመልካች ድርጊት በመቃወም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ያገኘውን የውርስ ማስረጃ እንዲሰረዝ፣የእህታቸው ሞግዚትነትና አስተዳዳሪነት እንዲነሳ ለፍርድ ቤት አመልክተው ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች የያዘውን የውርስ ማስረጃ ሕግ በሚደግፈው መንገድ ያልተገኘ ስለሆነ ተሽሯል፣ነገር ግን የሞግዚትነት ስልጣንን በተመለከተ ግን የሟች ኑዛዜ ቃል ሊከበር የሚገባው በመሆኑ ህፃኗ አካለ መጠን አድርሳ የበኩሏን መብት እስከምታስጠብቅ ድረስ የጸና ነው በማለት መወሰኑንና በይግባኝም ውሳኔው ያለመለወጡን ዘርዝረው አመልካች በተሳሳተ የውርስ ማስረጃ ለአስራ ሶስት አመታት የተጠቀሙበትን የገንዘብ መጠን ብር 139,900.00 መሆኑን በመዘርዘርና የተጠሪውን የድርሻ መጠን በመለየት በጠቅላላው ብር 23,316.20 እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም የመጀመሪያ ወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው ጉዳዩ በይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እየታየ መሆኑን፣ስመኝ ቃበቶን በተመለከተ የውክልና ስልጣን ስለሌላቸው ክስ ለማቅረብ የማይችሉ፣ጉዳዩ ከዚህ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ በመሆኑ በድጋሚ ሊቀርብ እንደማይገባ፣ክሱ በይርጋ የታገደ በመሆኑ ክሱ ሊቀጥል እንደማይገባ፣የአመልካች የወራሽነት ማስረጃ የተሰረዘው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሊሆኑ አይችሉም በሚል እንጂ የኑዛዜ ወራሽነትን በሚመለከት ያለመሆኑን የሚመለከቱ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡ ሲሆን

በፍሬ ነገር ክርክር ረገድ ደግሞ ተጠሪ በክሱ ላይ የጠቀሱት ገንዘብ ብር 139,900.00(አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር)፣የተጠሪ ድርሻ ተብሎ የተገለፀውን ብር 23,316.60 ለብቻቸው ያልተጠቀሙበት በመሆኑ ሊከፍሉ የማይገባ መሆኑን፣ከ1989 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ ወር1998 ዓ/ም ድረስ ቤቱ ተከራይቶ ይገኝ የነበረውን የተለየ መጠን ያለውን የኪራይ ገቢ ተጠሪ በየወሩ ድርሻቸውን እየተረከቡ ምግባቸውን ከአመልካችና ከስመኝ ቃበቶ ጋር ሁነው ሲጠቀሙ የነበረ መሆኑን፣ተጠሪ በ1996 ዓ/ም የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ አቤቱታ አቅርበው ስለነበር አመልካች ቀርበው መልስ ከሰጡ በኋላ ሽማግሌዎችን መርጠው ድርድር ጀምረው ተቋርጦ ከቆየ በኋላ እንደገና ድርድሩ ጀምሮ ስምምነት ላይ ተደርሶ ድርሻቸውን ተከፋፍለው እየተጠቀሙ እንደሚገኙ ዘርዝረው በክሱ ላይ የተገለፀውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካች የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ከተጠሪ ጋር እንደ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ሁነው ንብረቱን እኩል የሚካፈሉ ናቸው የሚል ምክንያት ይዞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915(1) ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካችና ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰውን የኪራይ ገንዘብ በጋራ የተጠቀሙ ስለሆነ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም፣የስመኝ ቃበቶ ሞግዚትነት ስልጣንን በተመለከተ ግን አካለ መጠን ያደረሰች በመሆኑ ራሷ ከምትጠይቅ በስተቀር ተጠሪ ሊጠይቅ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምእራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄ ኑዛዜው ስለግልጽ ኑዛዜ አደራረግ ሕጉ ያስቀመጠውን መስፈርት የማያሟላ ሁኖ ተገኝቷል በሚል ምክንያት ማስረጃውን ውድቅ ያደረገውና የሚች ወ/ሮ ነጠር አስፋው ሕጋዊ ወራሾች ተጠሪና እህታቸው ስምኝ ቃበቶ ናቸው ሲል የደመደመ ሲሆን ውጤቱንም በተመለከተ የቤቱን ኪራይ ገቢ አመልካች ሕጋዊ ወራሽ ነኝ በሚል እምነት ከተጠሪ ጋር በጋራ የተጠቀሙበት በመሆኑ ሊከፍሉ አይገባም፣ቤቱን በተመለከተ ግን ለሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ለተጠሪና ለወ/ሮ ስመኝ ቃበቶ አመልካች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በድምጽ ብልጫ ተሰርዞባቸዋል፡፡

ከዚህም በኋላ የሰበር አቤቱታቸው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን ከይርጋ መቃወሚያ አንፃር ብቻ በመመልከት ጉዳዩ የጋራ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ስለሆነ በማናቸውም ጊዜ ሊጠየቅ የሚችል ነው የሚል ምክንያት ይዞ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ሁኖ እያለ ስለኑዛዜው ሕጋዊነት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በማንሳት በዚህ ረገድ የተሰጠውን የወረዳውን ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻራቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ወ/ሮ ነጠር አስፋው ሰኔ 03 ቀን 1988 ዓ/ም ባደረጉላቸው ኑዛዜ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውና ኑዛዜውም በወቅቱ በፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99/89 ፀድቆ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መፅናቱ እየታወቀ ባሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት በመ/ቁጥር 19749 የተጀመረውን ክርክር በመቀበል ኑዛዜው በፍርድ ቤት መጽደቅ አይገባውም ነበር፤ኑዛዜው በሕግ የተቀመጠውን መስፈርት አያሟላም በማለት ጉዳዩን ዳግም በማየት ኑዛዜውን የመሻራቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪና ስመኝ ቃበቶ የሚች ወ/ሮ ነጠር አስፋው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው መረጋገጡን፣አመልካቸ የሚቿ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በመ/ቁጥር 99/89 መጋቢት 15 ቀን 1994 ዓ/ም ከወረዳው ፍርድ ቤት አግኝተው የነበረ መሆኑን፣ተጠሪ ይህ ማስረጃ በአመልካች የተገኘው ያላግባብ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ለወረዳው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው የወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16107 ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ አመልካች ከሚች የተወለዱ ባለመሆኑ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሊያደርጋቸው የሚችል ሌላ ሕጋዊ ግንኙነት የሌለ በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉበት የሕግ መሰረት የለም በማለት ማስረጃውን ሰኔ 03 ቀን 2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰረዘው መሆኑን፣ይህ ውሳኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦም በመ/ቁጥር 33024 በሆነው ግራ ቀኙ ተከራክረውበት ህዳር 21 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተቀባይነት አግኝቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ አመልካች የሚቿ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉበት የህግ መሰረት የለም፣የአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ በሚል በተጠሪ ቀርቦ  በታየውና በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝ ዳኝነት ላይ አመልካች ስለኑዛዜ ክርክር የሚያቀርቡበት አግባብ የለም በማለት የመ/ቁጥር 05200 በሆነው ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአጸናው መሆኑንና ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የተጠሪ ክስ በወረዳው ፍርድ ቤት የተመሰረተውም መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ/ም መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠሪና አመልካች በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በጋራ የመ/ቁጥር 99/89 በሆነው በአስከፈቱት መዝገብ በኑዛዜው ላይ የነበሩ ምስክሮች ቀርበው መስክረው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ኑዛዜው የሕግን ፎርማሊቲ ያሟላ ነው በማለት ኑዛዜውን  መጋቢት 14 ቀን 1994 ዓ/ም ያፀደቀው መሆኑን፣የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ አመልካች ኑዛዜው ቀድሞ ፀድቋል፤በፍርድ ያለቀ ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ያደረጉት ኑዛዜው በፍርድ ቤት መፅደቁንና ተጠሪ የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ መሆኑን በማመን ኑዛዜው ቀድሞውንም የሕጉን መስፈርት የማያሟላ ሁኖ እያለ በፍርድ ቤት መጽደቁ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባቸው ስርዓቶች በፍ/ሕ/ቁ.881 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ፣ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡በሚች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ሰነዱ ሲታይ አራት ምስክሮች ያልፈረሙበት፣ኑዛዜው በምስክሮች እና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ የማይገልጽ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42623 በቀረበው ክርክር ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም ሚች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ሕ/ቁ. 881 ሥር የተመለከቱትን

ስርዓቶችን ያላሟላ ነው ተብሎ ውሳኔ የተሠጠው አመልካችና ተጠሪ ቀድሞ በመ/ቁጥር 99/89 በቀረበው ክርክር ከተከራከሩና ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ከፀደቀ በኋላ ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት የወሰነው ቀድሞውኑም ስርዓቱን ሳያሟላ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 99/89 ማፅደቁ ተገቢ አልነበረም በሚል ምክንያት ነው፡፡ይሁን እንጂ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17058 የሠጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በፍርድ ቤት ኑዛዜው የፀደቀ ነው ተብሎ ሲወሰን ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ይህንኑ ከማቅረብ የማይከለከሉ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የኑዛዜውን ሕጋዊነት መሰረት አድርጎ ተከራክሮ ተቀባይነት ያጣና ኑዛዜው በፍርድ ቤት የፀደቀበት ሰው በሌላ ጊዜ ስለኑዛዜው ሕጋዊነት ክስ መመስረት ወይም መቃወሚያነት ማቅረብ የሚችል መሆኑን የሚያሳይ አንድምታ የሌለው ነው፡፡በመሆኑም በሕግ አግባብ የተደረገን ኑዛዜ በፍርድ ቤት ማስጸደቅ ያስፈልጋል? ወይስ አያስፈልግም? የሚል ጭብጥ ተይዞ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበትን የሰ/መ/ቁጥር 17058 ጉዳይ መሰረት አድርገን ጉዳዩን ስንመለከተው አንዴ በፍርድ ቤት ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ የፀደቀ ኑዛዜ ቀድሞውንም መፅደቅ አልነበረበትም ተብሎ ፈራሽ እንዲሆን የሚደረግ የሕግ ምክንያት የለውም፡፡አግባብነት ያላቸው ተከራካሪ ወገኖች ስለኑዛዜው ሕጋዊነት ክርክር አቅርበው ኑዛዜው ሕጋዊ መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በጉዳዩ ላይ በድጋሚ ክስ ማቅረብና ፍርድ ቤቱም መቀበል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚጥስ ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ አግባብ ጉዳዩ በፍርድ ቀደሞ ያለቀ ነው ተብሎ ተቀባይነት እንዲያገኝ ካልተደረገ በስተቀር ክርክሮች መቋጫ እንዳይኖራቸው የሚያደርግና ተከራካሪ ወገኖችን ለአላስፈላጊ የገንዘብ፣ጊዜና ጉልበት ብክነት የሚዳርግ፣ከስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ አላማም ውጪ ነው፡፡አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባውም በስርዓቱ መሰረት የቀረበለትን ይግባኝ መሰረት አድርጎ ነው እንጂ ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ተገቢ አልነበረም በሚል ምክንያት እንዳልሆነ ስለይግባኝ ስርዓት ከተደነገጉት ድንጋጌዎችና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 ድንጋጌ ጣምራ ንባብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ተጠሪ  የኑዛዜን ወራሽነት አስመልክቶ አመልካች የሚያቀርቡትን ክርክር በመ/ቁጥር 99/89 ያልተካሄደ ነው ወይም በወቅቱ በጉዳዩ ላይ ክርክር ለማቅረብ የማያስችሉ ሕጋዊ ምክንያት የነበራቸው ስለመሆኑ ገልፀው ያልተከራከሩ ከመሆናቸውም በላይ አመልካች የሚች ነጠር አስፋው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ አይደሉም ተብሎ ማስረጃው እንዲሰረዝ በቀረበው ክርክር አመልካቹ ስለኑዛዜው ሕጋዊነት እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር አቅርበው ችሎቱ በመ/ቁጥር 05200 ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በመዝገቡ የተያዘው ክርክር ስለመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነት እንጂ ስለኑዛዜ ተጠቃሚነት ያለመሆኑን ጠቅሶ በዚህ ነጥብ ላይ ዳኝነት ሳይሰጥበት ማለፉ በዚህ ረገድ አመልካች ወደፊት የሚያቀርቡትን ክርክር ያልገደበው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡በአንድ ጉዳይ በጭብጥነት ተይዞ እልባት ያላገኘ ነጥብ ደግሞ ቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት የማይቻል መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም አመልካች ኑዛዜውን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ክርክር የመጨረሻ ፍርድ ያላገኘ ሲሆን የተጠሪ ግን በመ/ቁጥር 99/89 በተሰጠው ፍርድ መሰረት የመጨረሻ ዳኝነት ያገኘ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለለም አመልካች በፍርድ ቤት የፀደቀው ኑዛዜ ተጠቃሚነትን መሰረት አድርገው ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ቤት ያለቀ ነው በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የታለፈው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ውጪ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በምእራብ ጎጃም ዞን መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42623 ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01-32078 ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 18331 ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ሚች ወ/ሮ ነጠር አስፋው አደረጉት የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያላሟላ በመሆኑ ፈራሽ ነው ተብሎ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ የተሰጠ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌንና በፍርድ ቤት በጸደቀ ኑዛዜ ተቃውሞ የሚቀርብበትን አግባብ ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡
3. በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር በ19749 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፤አመልካች ሚች ወ/ሮ ነጠር አሰፋው ሰኔ 03 ቀን 1988 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚነታቸው በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99/89 በተሰጠ ውሳኔ የተረጋገጠ ነው ብለናል፡፡
4. ተጠሪ እና ስመኝ ቃበቶ በአከራካሪው ቤት ላይ ከአመልካች ጋር እኩል መብት አላቸው ብለናል፡፡አመልካች ለተጠሪ የሚከፍሉት የኪራይ ገንዘብ የለም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 86133

ጥቅምት 20 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-**

1. አቶ ፍቅሩ ከበደ
2. አቶ ገብረወልድ በርጋ
3. አቶ ከበደ አርጋው
4. አቶ ኃይሉ ግዛው
5. አቶ መህዲ መሐመድ
6. አቶ ግንባሩ አረጋው
7. አቶ ሳዲቅ አውል
8. አቶ ከድር ረሺድ
9. አቶ ፈድሉ ኑረዲን
10. አቶ ወልዴ ብዛ
11. አቶ መንግስቱ ኃ/ማሪያም

} ጠበቃ ታፈሰ ይርጋ ቀረቡ

ተጠሪ፡ 1. ወ/ሮ አስቴር አርአያ - አልቀረቡም

2. ወ/ሮ ፋንታዬ መኮንን - ጠበቃ ዮሴፍ ደስታ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥቷል፤**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ በአንድ ንብረት ላይ አፈጻጸሙ ሲመራ በንብረቱ ላይ ሕጋዊ መብት አለን የሚሉ ሰዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት አቤቱታ ሲያቀርቡ አቤቱታቸው ሙሉ የክርክር አመራር ስርዓትን መሰረት አድርጎ ሊከናወን የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡የአፈፃፀሙ ክርክር የተጀመረው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ባሁኗ 2ኛ ተጠሪ ላይ የጥብቅና አበል አልተከፈለኝም በሚል ያቀረቡት የዋና ክርክር ጉዳይ ታይቶ የፍርድ ባለመብት መሆናቸው በመረጋገጡ ይኼው ፍርድ ቤት እንዲፈፅምላቸው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባስከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ ነው፡፡1ኛ ተጠሪ ለፍርዱ ማስፈፀሚያ ይሆንላቸው ዘንድም 2ኛ ተጠሪ በውርስ መብት አግኝተውባቸዋል ባሏቸው፤በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ አጠራር በወረዳ 3፣ቀበሌ 32 ክልል ውስጥ በሚገኙትና ቁጥራቸው ከ803 እስከ 805 በሆኑ ቤቶች እንዲሁም በወረዳ 5፣ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ በሚገኙትና ቁጥራቸው ከ936 እስከ 953 በሚል ተመዝግቦ በሚገኙ ጋራዥ ቤቶች ላይ ለፍርድ ቤቱ የገለፁ ሲሆን የአሁኑ አመልካቾች በወረዳ 5 ቀበሌ 06 ክልል በሚገኙትና ቁጥራቸው ከ936 እስከ 953 ተብሎ የተመዘገቡ የመኮንን ነጋሽ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅትና ጋራዥ በድርጅትነት እንደሚታወቅና ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገ የንግድ ቤት ድርጅት ሽያጭ ውል የሟች አቶ መኮንን ነጋሽ ሚስት ወ/ሮ የሺወርቅ ግዛው ከልጆቻቸው እነ ፋሲል መኮንን ነጋሽ (ሰባት ራሳቸው) እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን ሽጠውላቸው ነሐሴ 08 ቀን 1999 ዓ/ም የተረከቧቸው መሆኑን ገልፀው 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የፍርድ ይፈፀምልኝ ጥያቄ በንብረቶቹ ላይ ሊቀጥል እንደማይገባ፣በወረዳ 3 ቀበሌ 32 በቤት ቁጥር 803 እስከ 805 በሚታወቁት ቤቶች ላይ አፈፃጸሙ ቀጥሎ በእነዚህ ንብረቶች ላይ የፍርድ ባለእዳዋ ድርሻ እዳውን የሚሸፈን ካልሆነ የአሁኑ አመልካቾች ሻጮች ባደረጉት ውል መሰረት ተፈጽሞ 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ቀሪ ድርሻ እንዳላቸው ቀሪውን በፍርድ ባለእዳዋ ድርሻ ልክ ይዘው ለመክፈል የሚችሉ መሆኑን ገልጸው አፈፃጸሙ በዚህ መልክ እንዲመራ አመልክተዋል፡፡የአሁኗ ተጠሪ ለአመልካች አቤቱታ በሰጡት መልስም አመልካች አለን የሚሉት ውል ሕጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ ያልተደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ጥያቄአቸው ሙሉ በሙሉ ውድቅ እንዲሆን ያመለከቱ ሲሆን 2ኛዋ ተጠሪም አመልካቾች በወረዳ 5 ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ የሚገኙትንና ቁጥራቸው 936/2/፣947 እስከ 952፣953/2/ ፣954 እና 954/2/ የሆኑትን በውል ገዝተው የተረከቧቸው መሆኑን ጠቅሰው እንደውሉ ተጠብቆ እንዲፈፀምላቸው ቢደረግ የማይቃወሙ መሆኑን፣የቤት ቁጥር 803 የተባለውን ግን እንደማያውቁት፣የቤት ቁጥር 936/3/፣938/1/፣946 እና 947/2/ ለአመልካቾች ያልተሸጡላቸው፣ገንዘብ ያልተቀበሉባቸው እና ያላስረከቧቸው በመሆናቸው የፍርድ ባለመብት ፍርዱን ሊያስፈጽሙባቸው የሚችሉ በመሆኑ የአመልካቾች ጥያቄ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣የቤት ቁጥር 937/1/፣938፣940፣941፣943፣944፣945 የሆኑት ደግሞ የመንግስት ቤቶች በመሆናቸው ፍርዱ ሊፈጸምባቸውም ሆነ መቃወሚያ ሊቀርብባቸው የማይችልባቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

አፈጻጸሙን የያዘው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካቾች ያቀረቡት ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723(1) ስር እና በንግድ ሕጉ ቁጥር 127 እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1432(1) ድንጋጌዎችን ይዘት የሚያሟላ አይደለም በማለት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የአሁኑ አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 አግባብ ያቀረቡት በመደበኛ የሙግት ስርዓት ከግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ባለመሆኑና ይህንኑ እድል ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421

ክስ አቅርቦ መጠቀም እንደሚቻል፣ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37214 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን ዘርዝሮ የሥር ፍርድ ቤትን የአፈጻጸም ትእዛዝ ምክንያቱን ለውጦ በማፅናት የአመልካቾችን አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸውን ጠብቋል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 እና 421 ድንጋጌዎች አተገባበር የሰጠው ትርጉም የሕጉን መንፈስና አላማ ያላገናዘበና ትርጉሙ ውጤት የሌለው መሆኑን እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤት ሽያጩ በሕጉ የተዘረጋውን የሽያጭ አደራረግ ስርዓት ያልተከተለ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ለድርጅት ሽያጭ የተመለከቱትን የሕግ ድንጋጌዎችን ባግባቡ ያላገናዘበ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች በንብረቶቹ ላይ ያላቸው መብት እንዲጠብቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡እንደመረመርነውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ መደበኛ የሙግት ስርዓት ተከትሎ የሚከናወን አይደለም፣አቤቱታው ውድቅ የሆነበት አካል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 አግባብ ሌላ ክስ አቅርቦ መብቱን ማስጠበቅ ይችላል በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ እንደተቻለው የአሁኑ አመልካቾች በወረዳ 5 ቀበሌ 06 ክልል በሚገኙትና ቁጥራቸው ከ936 እስከ 953 ተብሎ የተመዘገቡ የመኮነን ነጋሽ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅትና ጋራዥ በድርጅትነት እንደሚታወቅና ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገ የንግድ ቤት ድርጅት ሽያጭ ውል የሟች አቶ መኮነን ነጋሽ ሚስት ወ/ሮ የሻሸወርቅ ግዛው ከልጆቻቸው እነ ፋሲል መኮነን ነጋሽ (ሰባት ራሳቸው) እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን ሸጠውላቸው ነሐሴ 08 ቀን 1999 ዓ/ም የተረከቧቸው መሆኑን ገልፀው 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የፍርድ አፈጻጸም ጥያቄ በእነዚህ ንብረቶች ሊቀጥል እንደማይገባ ገልፀው በሽያጭ ያገኙት መብት እንዲጠብቅላቸው ዳኝነት ጠይቀው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉ ሕጉን የማያሟላ ነው በማለት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉና የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግን የአመልካቾች አቤቱታ በመደበኛ ሙግት አመራር ስርዓት መሰረት ሊከናወን የማይችልና መብታቸውን በአዲስ ክስ ማስከበር የሚችሉ መሆኑን ዘርዝሮ የስር ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ምክንያቱን ለውጦ በውጤት ደረጃ የተቀበለው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 እና 419 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር የመቃወሚያ አቤቱታ ሲቀርብ ወይም በዚሁ ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ የሚል ተቃዋሚ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በሚያዘው ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው በመቁጠር የሚያቀርቡትን መቃወሚያና አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር እንዳለበት እንዲሁም በመጨረሻ ላይም የቀረበለትን አቤቱታና ማስረጃውን ከመረመረ በኋላ ንብረቱ እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የሚያደርግ በቂ ምክንያት ያለመኖሩን

የተረዳ እንደሆነ ንብረቱ እንደሁኔታው በሙሉ ወይም በከፊል እንዲለቀቅ ወይም ንብረቱ በፍርዱ አፈጻጸም መያዙ ተገቢ ሆኖ ካገኘው ደግሞ አቤቱታውን እንደሚሰረዝ ያስገነዝባሉ፡፡ሆኖም ግን እነዚህ ድንጋጌዎች በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 419 መሰረት ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ሲሰጥ የሌላውን ተከራካሪ ወገን ህገ መንግስታዊ የመስማት መብቱ ሣይከበርለት እና እንዲሁም አግባብነት ባለው መሰረት የተከበሩለትን መብቶች አንስቶ መከራከሪያ ሣያደርግባቸው ሊፈጸም የሚችል አይደለም፡፡በሌላ አነጋገር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 419 ድንጋጌ ይዘት የሌላውን ተከራካሪ ወገን የመስማት፤የመደመጥ እና በህጉ አግባብ ክርክሩን የማቅረብ መብቱን የሚከለክል ያለመሆኑን ከላይ በተገለጸው አግባብ በመተንተን ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 87833 በቀረበው ጉዳይ ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 37214 በቀረበው ጉዳይ ይህ የመሰማትና የመደመጥ መብት የማይከበር ስለመሆኑ በግልጽ አቋም ያልተያዘበት የሕግ ትርጉም ሲሆን በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የሚያሳያው የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል መቃወሚያ አቅርቦ ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 መሰረት በድጋሚ ክስ ለማቅረብ  የተፈቀደለት በአፈፃፀም ችሎቱ የንብረቱ ባለመብትነት በጭብጥነት ተይዞ በመደበኛው የሙግት ስርአት አይነት የአመልካቹ ጥያቄ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ባለመሆኑ ይህንን እድል ለመስጠት ነው በሚል ነው፡፡ሆኖም ችሎቱ ድንጋጌው የመደበኛ ሙግት ስርዓትን በመከተል መቃወሚያ አቤቱታውን ለማስተናገድ ሕጉ በግልጽ ክልከላ አድርጓል ወደሚለው ድምዳሜ ያልደረሰ ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 87833 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡በመሆኑም በሕጉ አግባብ የቀረበን መቃወሚያ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት የፍትሓብሄር ስነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ አላማ ያሳካል ከሚባል በስተቀር ሌላ አሉታዊ ውጤት በክርክር አመራር ስርዓት ላይ የሚያስከትል አይደለም፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት አቤቱታ ያቀረበ ወገን በሕጉ አግባብ ማስረጃ ቆጥሮ ተቃውሞውን ከአቀረበ ጉዳዩ በአፈጻጸም መዝገብ እንዲከናወን ማድረግ ጊዜን፣ጉልበትንና ወጪ የሚቆጥብ መሆኑ የሚታመን ሲሆን ክርክሩ የመደበኛ መግት ስርዓትን ተከትሎ እንዲከወን ለማድረግ የሚያስችል አቤቱታ መቅረቡ እስከተረጋገጠ ድረስ የግራ ቀኙን የመከራከር መብት ጠብቆ በጉዳዩ ላይ ዳኝነት መስጠት ተገቢ አይደለም፣የሕጉን አላማ አያሳካም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 አግባብ የተሟላ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበ ወገን አቤቱታው በመደበኛ ሙግት እንዲከናወን እንዳይጠይቅ ሕጉ ግልጽ ክልከላ ያላደረገበት ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 ስር የተጠበቀው መብትም በሕጉ አግባብ የሚቀርቡ መቃወሚያዎች እንደተጠበቁ ሁነው አመልካቹ በምርጫው እንዲጠቀምበት የተቀመጠ እንጂ ይህንኑ ስርዓት እንዲከተል የግድ የሚደረግበት ያለመሆኑ ድንጋጌው በፈቃደኝነት የአቀራረፅ ስርዓት መቀመጡ አስረጂ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በአፈጻጸም ሊያዙ የማይችሉበትን ሕጋዊና በቂ ምክንያት ካላቸው ይህንኑ አንስተው ሙሉ በመደበኛው የሙግት ክርክር አቅርበው መብታቸው ሊከበርላቸው የማይገባበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በእርግጥም ሽያጭ ውሉ በህጉ አግባብ የተደረገ መሆን አለመሆኑንና ወይም በንብረቶቹ ላይ አመልካቾች ያቋቋሙት መብት መኖር ያለመኖሩና አመልካቾች በሽያጭ ንብረቶቹን አስተላልፈዋል የሚሏቸው ወገኖች ተግባሩን ለመፈፀም ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት ያላቸው መሆኑና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የሕግና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በጭብጥነት ይዞና በግራ ቀኙ ማስረጃዎችም ሆነ ፍርድ ቤቱ በሚያስቀርባቸው ሌሎች አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች በማንጠር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

አመልካቾች አለ የሚሉት የሽያጭ ውል ሕጋዊ አይደለም በማለት የሰጠው ትእዛዝ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሊወስንበት የሚገባው ሁኖ ሳላ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418፣419 እና 421 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ በመውጣት ጉዳዩ በመደበኛ የሙግት ስርዓት ሊከናወን የሚችል አይደለም፣አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚቻልበት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ፣ የፍታብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አይነተኛ አላማ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 87833 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ ላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 81670 ታህሳስ 23 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁ 81670 ቀጥሎ የግራ ቀኙን አስቀርቦ የአመልካቾች አቤቱታ በህጉ አግባብ በተቀመጠው ሙሉ የመስማት መብት ጠብቆ እና ጉዳዩ በግራ ቀኝ ክርክር እና አግባብነት ባለው ማስረጃ እንዲጣራ ከተደረገ በኂላ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341 መሰረት ክርክሩን መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

የሰ/መ/ቁ. 89494

ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዩጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ሠናይት በዳሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የሚች ዘካሪያ ኢብራሂም ባለቤት ሳዲያ ኢብሮሽ /ጠበቃ ወረደ ፀሐይ ወ/ዮሐንስ - ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በመድን ውሉ መሰረት የተከፈለ ገንዘብ ይተካልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ እና በአቶ ቶፊቅ ኡስማን ላይ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች ክስ ይዘት፡-ንብረትነቱ የአቶ ዘነበ ተካን፤የአመልካች ደንበኛ የሆነውንና በሰሌዳ ቁጥር 3-52129 የሚታወቀው ሚኒባስ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ ጅጅጋ አስር ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ ንብረትነቱ የአሁኑ ተጠሪ የሆነውና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-00947 ሐረር በሚል የሚታወቅ መኪና በስር ሁለተኛ ተከሳሽ በነበሩት አቶ ቶውፊቅ ኡስማን ሲሽከርከር ከመንገድ በመውጣት በ23/11/2003 ዓ/ም በመግጨት ጉዳት ያደረሰበት መሆኑንና በጉዳቱም በተሳፋሪዎች የመቁሰል አደጋ ከመድረሱም በተጨማሪ መኪናው ከስራ ውጪ የሆነ መሆኑን፣ለተሳፋሪዎች የተከፈለውንና መኪናው ከስራ ውጪ በመሆኑ በድምሩ የብር 287,003.40 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ሶስት ብር ከአርባ ሳንቲም) ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፣ከዚህ ገንዘብ ውስጥ የመኪናውን ሳልቬጅ በብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ ብር) የሸጠ እና ገቢ ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ቀሪውን ብር 187,003.40 ግን ተጠሪና የተጠሪን መኪና ሲያሽከርክር የነበሩት ግለሰብ አቶ ቶፊቅ ኡስማን እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ለማስረጃነትም የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዞ አቅርቧል፡፡የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ቶውፊቅ ኡስማን በሌሉበት ጉዳዩ የታየ ሲሆን የአሁኗ ተጠሪ ግን ቀርበው በሰጡት የመከላከያ መልስ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣ለአደጋው መድረስ የተጠሪ መኪና ጥፋት ያለበት መሆኑ አለመረጋገጡን፣የጉዳቱን መጠን ለማስረዳት የቀረቡት ደረሰኞችም ስርዝ ድልዝ ያለባቸው በመሆኑ በሕጉ ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን፣ስለመከፈሉ ያስረዳል ተብሎ በቀረበው የሰነድ ማስረጃም የጉዳቱ መጠን በአኀዝና በፊደል የተቀመጠው የተለያየ በመሆኑ ሊወሰድ የሚገባው የፊደል መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው አደጋ ያደረሰው የተጠሪ መኪና መሆኑ ያለመረጋገጡን ጠቅሶ ለጉዳቱ መድረስ

ሁለቱም ተሸከርካሪዎች የራሳቸው አስተዋጽኦ እንደነበር በመደምደም ሁለቱም ተሸከርካሪዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2084(3) ድንጋጌ መሰረት የጋራ ኃላፊነት አለባቸው በማለት የወሰነ ሲሆን የጉዳቱን መጠን በተመለከተ ደግሞ በአመልካች በኩል ከቀረቡት የተወሰኑት ደረሰኞች እምነት የማይጣልባቸው መሆኑን ለይቶ ውድቅ አድርጎ በድምሩ ብር 245,588.25 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺ አምስት መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም) ጉዳት መደረሱን፣ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺ ብር) ሳልቬጅ ሲቀነስ ቀሪው ብር 145,588.25 መሆኑን በመግለፅ ይኼው የጉዳት መጠን ለሁለት ሲካፈል ተጠሪ ብር 72,794.12. (ሰባ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአስራ ሁለት ሳንቲም) ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲያቀርብ ተጠሪ ባሉበት ጉዳዩ እንዲጣራ በመደረጉ ተጠሪም በስርኣቱ መሰረት የመስቀልኛ ይግባኝ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪን መኪና ሲያሽከርከሩ የነበሩት አሽከርካሪ ለጉዳቱ ሙሉ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በወንጀል ተቀጥተው እያለና ይኼው ውሳኔ በማስረጃነት በፍርድ ቤቱ እገዛ እንዲቀርብ አመልካች ጠይቆ እያለ ማስረጃው ሳይቀርብ ጉዳቱ የደረሰው በሁለት ተሽከርካሪዎች ግጭት ነው ተብሎ አግባብነት የሌለው ሕግ ተጠቅሶ ኃላፊነቱ የጋራ ተደርጎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ የተጠሪን መኪና ሲያሽከርክር የነበረው አሽከርካሪ በወንጀል ያለመቀጣቱን፣አመልካችም የወንጀል ችሎት የሰጠውን ውሳኔ አለ ከማለት ውጪ በየትኛው ፍርድ ቤትና በየትኛው መዝገብ ቁጥር ስለመሆኑ ለይቶ ባልጠቀሰበት ሁኔታ ማስረጃው ሳይቀርብ ቀርቷል በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 ድንጋጌ አተገባበርን ያላገናዘበ መሆኑን በመጥቀስና ተጠሪ ያላግባብ ለጉዳቱ የጋራ ሃላፊነት አለባቸው ተብሎ መወሰኑ ተጠሪን የጎዳና አመልካችን የጠቀመ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡የአሁኑ አመልካች በሰጠው የመልስ መልስም የወንጀል ውሳኔ የተባለውን ማስረጃ ውሳኔውን የሠጠውን ፍርድ ቤትና መዝገቡን ለይቶ ሳይጠቅስ የሰበር አቤቱታውን ይዘት በመድገም ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገውን የአደጋ ቦታ ፕላንና መግለጫ ይዘት ታልፎና በፍርድ ቤት እገዛ እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ ሳይቀርብ በበታች ፍርድ ቤቶች ኃላፊነቱ የጋራ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ከእነዚህ ነጥቦች አንጻር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው መኪና ሐምሌ 23 ቀን 2003 ዓ/ም በተጠሪ መኪና ግጭት የደረሰበት መሆኑን አመልካች ገልጾ ጉዳት በደረሰበት መኪና ለነበሩት ተሳፋሪዎች የተከፈለውን ወጪ፣መኪናውን ከስራ ውጪ በመሆኑ ምክንያት የታጣውን ገቢ መጠን ዘርዝሮና የሳልቬጁን ዋጋ መጠን ለይቶ በድምሩ ብር 187,003.40 ለደንበኛው የከፈለው የጉዳቱ ወጪ

መሆኑን ገልፆ ይሔው ገንዘብ እንዲተካ ጥያቄ አቅርቦ የአሁኗ ተጠሪም በኃላፊነቱም ሆነ በመጠኑ ላይ የቀረቡት ክርክሮች ያላግባብ የቀረቡ ናቸው የሚል ክርክር አቅርበው የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክሮችና ማስረጃዎችን መርምሮ በአመልካች የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና ከተጠሪ መኪና ጋር ሐምሌ 23 ቀን 2003 ዓ/ም መጋጨቱን፣ለግጭቱ ምክንያት የሆነውን ጥፋት የፈፀመው አሽከርካሪ ግን የትኛውን መኪና ሲያሽከርክር የነበረ አሽከርካሪ እንደሆነ በጉዳዩ የቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች እንደማያሳዩ ገልጾ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር በከፊል ያለፈው መሆኑን ነው፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ደንበኛ መኪና እና የተጠሪ ንብረት በሆነው መኪና ግጭት መድረሱንና ለጥፋቱ ሙሉ ኃላፊነቱን ሊወስድ የሚገባው አሽከርካሪ ግን ያለመለየቱን ፍሬ ነገሩን አጣርቶና ማስረጃን መርምሮ ድምዳሜ ላይ የደረሰበት ጉዳይ ሲሆን ይኸው የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

እንግዲህ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው መኪና ከተጠሪ መኪና ጋር ተጋጭቶ ጉዳት የደረሰበት ከመሆኑ ውጪ በተጠሪ አሽከርካሪ ሙሉ ጥፋት ግጭቱ ስለመድረሱ በጉዳዩ ላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች ይዘትና መንፈስ የስር ፍርድ ቤት መገንዘብ ያለመቻሉን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣኑን ተጠቅሞ ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡አሁን አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት በዚህ ረገድ ያቀረበው ቅሬታ የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 መሰረት እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ ሳያስቀርብ አልፏል የሚል ነው፡፡በእርግጥ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 መሰረት የተጠየቀ ማስረጃ ሳይቀርብ ፍርድ መስጠት የፍርድ ኣካሄዱ በተሟላበት ሁኔታ የተሰጠ ነው ለማለት የማይቻል መሆኑ የሚታመን ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 መሰረት የፍርድ ቤቱን እገዛ በመጠየቅ ማስረጃ ማስቀረብ የሚቻለው ግን ጠያቂው ወገን እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ ትክክል ግልባጭ በቅርብ ጊዜ ለማምጣት የማይችልበትን ወይም ማስገልበጫ የሚያስፈልገውን ወጭ ለመክፍል የማይችል መሆኑን እንዲሁም እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ ለክርክሩ ምን ያህል ጠቃሚነት እንዳለው፤ትክክለኛን ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን በፅሁፍ ገልፆ ማስረዳት እንዲሚጠበቅበት የተጠቃሹ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡በመሆኑም ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤት እገዛ ማስረጃ እንዲቀርብለት ሲጠይቅ በሕጉ የተመለከቱትን መስፈርቶችን በግልጽ ገልፆ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች በፍርድ ቤት እገዛ እንዲቀርብለት የሚጠይቀው የፅሑፍ ማስረጃ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሆን ውሳኔው በየትኛው ፍርድ ቤትና በየትኛው የመዝገብ ቁጥር እንደተሰጠ ካለመግለፁም በላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 ስር የተመለከተውን የሕጉን አገላለፅ ለማስረዳት የጠቀሳቸው ምክንያቶችም የሉም፡፡እንዲሁም አመልካች የወንጀል ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በየትኛው ፍርድ ቤትና መዝገብ ቁጥር እንደተሰጠ ያለመግለጹን፣በስር ፍርድ ቤትም ፍርድ ቤቱንና የመዝገብ ቁጥር እንዲጠቅስና ማስረጃውንም እንዲያቀርብ እድል ተሰጥቶት በእድሉ ሊጠቀም ያለመቻሉን ተጠሪ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጡት መልስ በግልጽ ጠቅሰው ተከራክረውም አመልካች በዚህ ረገድ ባቀረበው የመልስ መልስ ለተጠሪ የክርክር ነጥብ ማስተባበያ ክርክር አላቀረበበትም፡፡በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት እድሉ ተሰጥቶ ተገቢውን ሊፈፅም ያለመቻሉን አመልካች እንዳመነ የሚያስቆጥረው መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 235 እና 83 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ሲሆን በዚህ የሰበር የክርክር ደረጃ እንኳን አመልካች አለኝ የሚለውን የወንጀል ውሳኔ የሠጠውን ፍርድ ቤትና የመዝገቡን ቁጥር በግልጽ

ጠቅሶ ያለመከራከሩ በማስረጃው አቀራረብ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቱ ተገቢውን እገዛ እንዲያደርግ  አመልካች በራሱ በኩል ተገቢውን ያለመፈፀሙን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች በትራፊክ መርማሪ ፖሊስ ጥፋቱ የተጠሪን መኪና ሲያሽከርክር የነበረ አሽከርካሪ መሆኑ ተገልጾ እያለ በበታች ፍርድ ቤቶች ይኼው ታልፏል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ደግሞ ማስረጃው በስር ፍርድ ቤት ተመዝኖ የታለፈ በመሆኑና ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን መዝኖ የራሱን ድምዳሜ ከመያዝ የሚከልክል ሕግ የሌለ ስለመሆኑ፣ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንደዚህ አይነት ማስረጃ እንደማንኛውም ማስረጃ ሊመዝን የሚችል እንጂ ደምዳሚ ማስረጃ ያለመሆኑን ገልጾ በሰ/መ/ቁጥር 14981፣43453 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን ያላገናዘበ በመሆኑ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር ከመሆኑም በላይ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ይዘት ውጪ በመሆኑ አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ማጣራትና በማስረጃ ምዘና ሂደት ሰርተውታል የሚለውን ስህተት የማጣራትና የማረም ስልጣን ይኽ ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ያልተሰጠው ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ክርክር ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ግጭቱ በሁለት ተሽከርካሪዎች የደረሰ ከሆነና ጥፋቱ የየትኛው ተሽከርካሪ እንደሆነ በማስረጃ መለየት ካልተቻለ አንዱ ባንዱ ላይ አደጋ እንደአደረሰ እንደሚቆጠር፣ለየእንዳንዱ ተሽከርካሪ ባለሃብት ወይም ለአደጋው አላፊ የሆነው ሰው በአደጋው ምክንያት ከደረሰው ጠቅላላ ጉዳት ገሚሱን መክፈል ያለበት መሆኑን ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2084(1) እና (2) ድንጋጌዎች በግልጽ ያሳያሉ፡፡

በአጠቃላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 ድንጋጌ መሰረት እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የቀረው አመልካች በሕጉ በተመለከተው አኳኋን ማስረጃውን ለማቅረብ ያልቻለበትን ሕጋዊ ምክንያትና ማስረጃው የሚገኝበትን ፍርድ ቤትና የመዝገቡን ቁጥር ለይቶ ባለማቅረቡ ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት መረጋገጡን የተገነዘብን ስለሆነና በትራፊክ ፖሊስ ማስረጃ ላይም አመልካች  በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተፈጽሟል የሚለው ስህተት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት በመሆኑና ይህ ደግሞ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛ ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ ስለሌለ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 940/03 ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 185/2004 የካቲት 08 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ለአደጋው የአመልካች ደንበኛ መኪና እና የተጠሪ መኪና የጋራ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የጉዳት መጠኑን እኩል እንዲጋሩ ተደርጎ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

ቤ/ዮ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 90543

ጥቅምት 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-1.አቶ ተሾመ አሰፋ
2.ማርሸት አሰፋ
3.ፍቅረዓለም አሰፋ
} የጠበቃ ወኪል ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት መስታወት አሰፋ/ቀረበች

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ከወ/ሪት ቦንቱ አሰፋ ጋር በመሆን በሀዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የስር ከሳሾች ያቀረቡት ክስ ይዘትም የከሳሾችና የተከሳሾች ወላጅ አባት የሆኑት አቶ አሰፋ በዳሳ የካቲት 15 ቀን 1994 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውንና ንብረቶቻቸውም በተከሳሾች እንደሚተዳደሩ ገልፀው የሚቹ የውርስ ንብረቶች እንዲጣሩ ይደረግላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም ጉዳዩ በይርጋ የታገደና ቀድሞ በፍርድ ያለቀ መሆኑን ጠቅሰው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መቃወሚያ መነሻ አድርጎ ጉዳዩን የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ መሆኑ መረጋገጡን ገልጾ ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ መሰረት ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ብይን ከሳሾች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ያጡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ከሳሾች በመ/ቁጥር 01110 አቅርበውት የነበረው ክስ ሟች አቶ አሰፋ በዳሳ በተውት የቁም ኑዛዜ ከሰጧቸው ብር 20,000.00 ውስጥ ቀሪውን ብር 10,000.00 የአሁኑ 1ኛ አመልካች እንዲከፍል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የጠየቁበት ሁኖ በጉዳዩ ላይ 07/7/2004 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔም ይህንኑ ጥያቄአቸውን በመቀበል በኑዛዜው መሰረት ቀሪው ገንዘብ እንዲከፈላቸው የሚገልፅ በመሆኑና በአዲሱ ክስ ከሳሾች ክስ የመሰረቱት የውርስ ንብረት ይጣራልኝ በሚል እንጂ በኑዛዜ የተሰጣቸውን ገንዘብ እንዲሰጣቸው የሚጠይቅ ባለመሆኑ፤በሁለቱ መዛግብት የተነሱት የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክሮች ተመሳሳይ ባለመሆናቸው ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት የሚቻል አይደለም በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶችን ብይን በመሻር ፍሬ ጉዳዩ በስር ፍርድ ቤት ታይቶ ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥበት ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ ቀድሞ በኑዛዜ ክርክር ጊዜ ያለቀ ሁኖ እያለ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄና በኑዛዜው መሰረት ይፈፀምልኝ ጥያቄ ተመሳሳይነት የላቸውም ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰጠቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ አይደለም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪና ወ/ሪት ቦንቱ አሰፋ የካቲት 08 ቀን 2004 ዓ/ም ለሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ባቀረቡት ማመልከቻ ሟች አባታቸው አቶ አሰፋ በዳሳ መስከረም 16 ቀን 1994 ዓ/ም በተውት ኑዛዜ ላይ ለእያንዳንዳቸው ብር 10,000.00 በአቶ ተሾመ አሰፋ በኩል እንዲሰጣቸው የተናዘዙላቸው መሆኑንና ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 10,000.00 በአቶ ተሾመ አሰፋ ተሰጥቷቸው ቀሪው ብር 10,000.00 ያልተሰጣቸው መሆኑን ገልጸው ይኼው በኑዛዜ የተሰጣቸው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ እንዲከፈል ዳኝነት እንዲሰጣቸው የጠየቁ መሆኑንና ክርክሩም ከአቶ ተሾመ አሰፋ ጋር ብቻ ቀጥሎ አቶ ተሾመ አሰፋ በክሱ ኃላፊ ተደርገው ገንዘቡን እንዲከፍሏቸው ዳኝነት የተሰጠበት ጉዳይ መሆኑን፣እኔ ወ/ሪት መስታወት አስፋ ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ደግሞ አቶ ተሾመንና ሌሎች ሁለት እህቶቻቸውን በአንድ ላይ አድርገው፣በተከሳሽነት ሰይመው ዳኝነት እንዲሰጣቸው የጠየቁት ጉዳይ የአቶ አሰፋ በዳሳ የውርስ ንብረት እንዲጣራላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የፍትሐ ብሔር ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ እንዲኖረው በማሰብ ከተደነገጉ የስነ ስርዓቱ ድንጋጌዎች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍኑ መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣በውሣኔ፣በትእዛዝ፣ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ መንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ አቅፎ የያዘ፣ክርክር አንድ ቦታ ላይ እንዲቆም ታስቦ በሕግ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካላባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡
ሕጉ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ስለመሆኑም ያስገነዝባል፡፡ ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን ያስነዝባል፡፡

በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው ፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5(1)እና (2) ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2(ለ)) እና 245(2) ድንጋጌ ጋር ተጣምረው ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/2/ ድንጋጌ በግልጽ ሲታይም በቀድሞው ክርክር ላይ የማስረጃ ወይም የመከላከያ ወይም የመቃወሚያ መሰረት መሆን ይገባቸው ነበር ወይም ለመሆን ይችሉ ነበር የሚባሉት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለሥረ ነገሩ መሰረት በመሆን ከቀድሞው ውሳኔ ጋር ተቀላቅለው እንዳለቁ የሚቆጠሩ ናቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 216 ድንጋጌ ጋር ተዛምዶ ሲታይም ክርክሮች ተጠቃልለው እንዲታዩ የግድ የሚል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡በመሆኑም በተከራካሪ ወገኖች በግልጽ የሚታወቁና በቀዳሚው ክርክር ሊነሱ ይችሉ የነበሩት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለሌላ ክስ ምክንያት ሁነው ሊቀርቡ እንደማይገባና ፍርድ ቤቱም ተቃውሞው በስርዓቱ መሰረት ሲቀርብለት በመቀበል ክርክሩ እንዲቆም ማድረግ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ከላይ ከተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በተጨማሪ በቀድሞው ክርክርና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ የታለፈ እንደሆነ የተጠየቀው ዳኝነት እንደተከለከለ እንደሚቆጠር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(3) ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጧል፡፡በአጠቃላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ሲታይ በቀዳሚው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑ የተከራካሪ ወገኖች አንድነት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ከላይ የተመለከቱት መመዘኛዎች በተሟሉበት ሁኔታ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት በመሆኑ ድጋሚ ክስ የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ያስረዳል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከእህታቸው ቦንቱ አሰፋ ጋር ሁነው ቀደም ሲል በአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ መስከረም 16 ቀን 1994 ዓ/ም በተደረገው ኑዛዜ መሰረት ጥሬ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ሲሆን ይኸው የዳኝነት ጥያቄአቸው በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ገንዘቡ በ1ኛ አመልካች እንዲከፈል ተወስኗል፡፡ይህ የተጠሪና የእህታቸው የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ያደረገው ኑዛዜውን ሲሆን ኑዛዜው ለተጠሪና ለእህታቸው ምን ያህል ገንዘብ እንደሚሰጥ በግልጽ አስቀምጦ በኑዛዜው ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ውጪ ሌላ ገንዘብም ሆነ ንብረት ሊጠይቁ እንደማይችሉ ተናዛዡ መግለጹ በኑዛዜ ላይ የተቀመጠ ጉዳይና ተጠሪና እህታቸው ስለኑዛዜው ሰነድ ይዘት እውቀት የነበራቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ከዚህ በኋላ ተጠሪና እህታቸው ለፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ 1ኛ አመልካችን ጨምሮ በሌሎች ሁለት እህቶቻቸው(2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች) ላይ የቀረበ ከመሆኑ ውጪ ጠቅላላ የዳኝነት ጥያቄው የውርስ ንብረት ይጣራልኝ የሚል ነው፡፡እንግዲህ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 944 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ የሚፈፀም ሲሆን የኑዛዜ መኖርና ያለመኖር እንዲሁም ተጠቃሚዎች የሚለዩበት አግባብ እንደሆነ ከሕጉ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ኑዛዜን መሰረት አድርጎ የሚቀርበው የኑዛዜ ተጠቃሚነት መብት ይረጋገጥልኝ ጥያቄና የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆነ የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ተጠሪና እህታቸው ከኑዛዜው ጋር ተያይዞ የሚነሱትን ማናቸውንም የሕግ ጥያቄዎች በኑዛዜው መብት ተጠቃሚነት ይከበርልኝ በማለት ክስ በመሰረቱበት ጊዜ ሊያቀርቡ የሚችሉት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በኑዛዜው ላይ

የተቀመጠውን የገንዘብ መጠን ብቻ ጠይቆ መውሰድ ደግሞ በኑዛዜው የተደረገውን ክልከላንም ጭምር እንደመቀበል የሚያስቆጥር ነው፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ሟች በተውት ኑዛዜ መሰረት ጥሬ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ክስ አቅርበው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ከተሰጠ በኋላ የሟች ውርስ ንብረት ይጣራልኝ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ቀድሞ በቀረበው ክስ ጊዜ ሊያቀርቡ ይችሏቸው የነበሩትን ነገሮችና ምክንያቶችን ከተዉ በኋላ ያቀረቡት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ተቀባይት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ አይደለም፡፡ተጠሪ የኑዛዜውን ሰነድ ይዘቱን እንደሚያውቁም የሚታመን ሲሆን በኑዛዜው ላይ ሌላ ማናቸውንም ገንዘብ ወይም ንብረት ከሟቹ እንዳይጠይቁ ክልከላ ተደርጎባቸው እያለ ይኼው የኑዛዜው ክፍል ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን በቀድሞው ክስ ክርክር አቅርበው እልባት ማግኘት ሲገባቸው ኑዛዜውን ተቀብለው በኑዛዜው መሰረት ተጠቃሚነታቸው ከተረጋገጠላቸው በኋላ ሌላ የውርስ ንብረት መብት እንዳላቸው በመቁጠር የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ማቅረባቸው በቀድሞው ክርክር ላይ የማስረጃ ወይም የመከላከያ ወይም የመቃወሚያ መሰረት መሆን ይገባቸው ነበር ወይም ለመሆን ይችሉ ነበር የሚባሉት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለሥረ ነገሩ መሰረት በመሆን በቀድሞው ውሳኔ ጋር ተቀላቅለው እንዳለቁ የሚቆጠሩ ናቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(2) የተደነገገውን የሚጥስ ነው፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪና እህታቸው በቀደመው ክስ መሰረት ያደረጉት ኑዛዜ ሁኖ እያለና በኑዛዜው ደግሞ ሌላ ገንዘብ ወይም ንብረት ለመጠየቅ የማይችሉ መሆኑ በግልፅ ተመልክቶ እያለ በዚህ ረገድ ተገቢው ክርክር ቀርቦ መፍትሔ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ጉዳይ ተጠሪ በኋላ ያቀረቡት ክስ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ነው በማለትና ይህ ተግባር ኑዛዜን ማፈላለግና ተጠቃሚዎችን የመለየት ስራዎችን ጭምር የሚይዝ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገባ የኑዛዜ ተጠቃሚነትና የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ የተለያዩ ነገሮች ናቸው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5፣244(2(ለ)) እና 245(2) ድንጋጌዎችን እንዲሁም አጠቃላይ የስነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማ ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በደ/ብ/ብ/ሕ/ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 57725 የከቲት 28 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01280 ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 12576 ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ የአባታቸውን የአቶ አሰፋ በዳሳ ኑዛዜን መሰረት አድርገው ክስ አቅርበው ተጠቃሚነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄ ክስ የሚመሰረትበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
4. *በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ና ኪሳራ የየራሰሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡*

***መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡***

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 92459

ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፍፁም ብርሃን ገ/ክርስቶስ

ተጠሪ፡- የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው አመልካች ፍርድ ቤትን የመድፈር የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል ተብሎ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 አግባብ የጥፋተኝነትና የአምስት ቀን ቀላል እስራት መወሰኑም ሆነ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይኼው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መፅናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልካች ስለአመለከቱ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2005 ዓ/ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ የነበረውን ሂደትና ጉዳዩ በችሎት መድፈር የማያስጠይቃቸው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተተ ያለበት በመሆኑ እንዲሻርላቸው ወይም የእስራት ቅጣቱ በገንዘብ መቀጮ እንዲቀየርላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡እኛም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተተ ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካችን በፍርድ ቤት መድፈር የወንጀል ድርጊት እንዲቀጡ ትዕዛዝ ሊሰጥ የቻለው ፍርድ እየተነበበ ባለበት ሰዓት ትዕዛዙ በተሰጠበት መዝገብ ቁጥር 72908 ተከሳሽ የሆነው ድርጅት ካሌብ ሆቴል ጠበቃ የሆኑት የአሁኑ አመልካች ስልክ በማስጮህ እንደሁም ከሳሽ ከሆኑት ግለሰብ ከአቶ ሀብታሙ በላይ ጋር ያልተገባ ክርክር በመፍጠር ፍርድ ቤቱ ስነ ስርዓት እንዲይዙ ቢያሳውቃቸውም ስነ ስርዓት ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው፣እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በስነ ስርዓት ያናግረን በሚል ያልተገባ ባህርይ ማሳያታቸውን፣ከዚህም በተጨማሪ በችሎት ውስጥ ስልክ ማስጮህ እንደማይቻል ተገቢው ማስታወቂያ ተለጥፎ እያለና አመልካችም የሕግ ባለሙያ ሁነው እያለ የችሎቱን ስርዓት ያወኩ መሆኑን በመግለፅ ሲሆን እነዚህ የፍሬ ነገር ነጥቦች መኖራቸውን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ ተቀብሎአቸዋል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በችሎት መድፈር ወንጀል ሊቀጡ የቻሉት ስልክ

በማስጮሃቸው ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ ስነ ስርዓት እንዲይዙ አሳውቆአቸው ስነ ስርዓት ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረትና ፍርድ ቤቱ በስነ ስርዓት ያናግረን በሚል ያልተገባ ባህርይ ሁሉ ለችሎቱ በማሳየታቸው መሆኑን ጭምር ነው፡፡ትዕዛዙን የሰጡት ዳኛም በጊዜው በፍርድ ማንበብ ስራ ላይ እንደነበሩ በመዝገቡ ላይ የሰፈረ ጉዳይ ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ችሎት በኢ.ፌ..ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ጉዳይ ያለመሆኑ የሚታወቅ በመሆኑ ከላይ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮችን እንዳሉ የምንቀባላቸው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ደግሞ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ አመልካች በችሎት ውስጥ ሞባይል ስልክ አስጨኸዋል ተብለው በዚህ ድርጊት መነሻነት ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን ጋር በተደረገ የቃላት ልውውጥ መነሻነት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 449(1(ሀ)) እንዲቀጡ መደረጉ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ የተያዘው ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከችሎቱ ዳኛ ስነ ስርዓት እንዲይዙ የተነገራቸውን ትዕዛዝ ሳያከብሩ መቅረታቸውን እንዲሁም ችሎቱንም በስነ ስርዓት ያናግረን በማለት ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸውን የስር ፍርድ ቤት የመዘገበውን ፍሬ ነገር ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች ፍርድ ቤቱ ፍርድ በሚያነብበት ጊዜ ስነ ስርዓት እንዲይዙ የተነገራቸውን ትዕዛዝ ያለማክበራቸውንና "ፍርድ ቤቱን በስነ ስርዓት ያናግረን" በሚል ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸው የፍርድ ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱን ማወካቸውን የሚያሳይ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 አግባብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 449(1(ሀ)) ድንጋጌ ስር ተጠያቂነት የሚያስከትል ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡በመሆኑም የአመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘትና የሰበር አጣሪ ችሎት ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አሰጣጥ መነሻ የሆኑትን ፍሬ ነገሮችን ሙሉ በሙሉ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተገቢነት የሌለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም አመልካች በገንዘብ መቀጮ እንዲቀየርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የመሰረታዊ ሕግ መመዘኛን የሚያሟላ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ፍርድ እየተነበበ ባለበት ጊዜ የችሎቱን ስነ ስርዓት ባለማክበርና ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸው ተረጋግጦ ፍርድ ቤቱን በመድፈር የተቀጡ በመሆኑ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበበ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

**ል/ተ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 91103

ታህሳስ 16 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች:-** ዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር - ጠበቃ ረዳኢ ባራኪ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** 1. የአቶ ፉአድ መሃመድ እናት ወራሽ ወ/ሮ ማሪያም አብዱላሂ -

2. የአቶ አልፍሬዶ ፌሪርቶ ዶመኒኮ ወራሾች እነ አቶ ሚሊዩኝ አልፍሪዶ (5 ሰዎች) በሌሉበት የሚታይ ነው

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ ጉዳይ የወጭና ኪሣራ አወሣሰን ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ ለወጭና ኪሣራው መነሻ የሆነ የውሳኔ ክፍል ከመስጠቱ በፊት የአሁን 1ኛ ተጠሪ አውራሽ በሆኑት አቶ ፉአድ መሃመድ እና በአቶ አልፍሬድ ፌሪሬቶ መካከል ሐምሌ 26 ቀን 1991 ዓ/ም በብር 350,000.00(ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) የተደረገን የቤት ሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ክርክር በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተደርጎ ሻጭ አቶ አልፍሬድ ፌሪሬቶ ቤቱን ለገዥ አቶ ፉአድ መሃመድ እንዲያስረክቡ ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውሳኔ አግኝቶ የነበረ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ቤቱን ህዳር 30 ቀን 2001 ዓ/ም በሕጋዊ የሽያጭ ውል በብር 2,000,000.00(ሁለት ሚሊዩን ብር) ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪዎች አውራሽ የገዛው መሆኑን ጠቅሶ ውሳኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ተቃውሞ ቀርቧል፡፡ተቃውሞ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ሻጭ ከአሁኑ አመልካች ጋር ሕጋዊ ሽያጭ ውል አድርጎ እያለ ከቅን ልቦና ውጪ ከአቶ ፉአድ መሃመድ በድጋሚ መሸጣቸው ያላግባብ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የቀድሞውን ውሳኔ በመሻር ቤቱን የአሁኑ አመልካች ሊለቅ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች ያልተለወጠ ሲሆን ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ደግሞ የአቶ ፉአድ መሃመድ ወራሽ ዝርዝሩን የማቅረብ መብታቸውን ሲጠብቅ የአሁኑን አመልካች ጥያቄ ግን በዝምታ አልፎታል፡፡ አመልካች የወጪና ኪሳራ ይተካልኝ ጥያቄ በተመለከተ በዝምታ በመታለፉ ምክንያት ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ከቅን ልቦና ውጪ ለተደረገ የሽያጭ ውል ለክርክር የተዳረገ መሆኑ እየታወቀ የበታች ፍርድ ቤቶች የወጪና ኪሳራ ዝርዝሩን ማለፋቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አንደኛ ተጠሪን በተመለከተ ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስቀርብ የሕግ ነጥብ የለውም ተብሎ የተዘጋ ሲሆን 2ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ ግን ያስቀርባል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች በሕጉ አግባብ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ጭብጥ አመልካች በ2ኛ ተጠሪዎች አውራሽ ቅን ልቦና ውጪ በሆነ ተግባር ለክርክር የተዳረገ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የወጪና ኪሳራ ጥያቄው በዝምታ መታለፉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ ክርክር ተጠናቆ በፍርድ እንዲቋጭ ሲደረግ ለዚህ ፍርድ ምክንያት የሆነው ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሣራ ጉዳይ በፍርድ ተካቶ ሊወሰን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 183 ሥር ተመልክቷል ፡፡ ዝርዝር አወሣሰኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462-464 ተደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 እንደተመለከተው በክርክር ምክንያት የወጣን ወጭና ኪሣራ ማን እንደሚከፍልና ምን ያህል እንደሚከፍል ፍ/ቤቱ በመሰለው ሊወስን እንደሚችል ፈቃደ- ስልጣን እንዳለው በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የዚሁ ድንጋጌ ተከታይ የሆነው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 463 ደግሞ በዚሁ ሕግ የተሰጠው ፈቃደ ስልጣን ተጠቅሞ ፍ/ቤቱ ማን ይክፈል? የሚለውን በመለየት ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ጉዳዩች ሁሉ ተመልክቶና አረጋግጦ ተረቺ ለረቺ ይክፍል ብሎ ሊያዝ እንደሚችል ያሳያል፡፡የወጪና ኪሳራ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማም ሰዎች ያላግባብ ለክርክር እንዳይዳረጉ መከላከል መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ክርክሩ ከሕግ ውጪ የቀረበ መሆኑ ከታወቀ ደግሞ ለክርክሩ ያላግባብ የተዳረገ ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪና ኪሳራ ለዚሁ የዳረገው ወገን ሊተካለት ይገባል ፡፡በእርግጥ የክርክሩ ረቺ የሆነ ወገን ሁሉ ወጪና ኪሳራ ይተካለት ማለት እንዳልሆነ ከድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ሆኖም አንድ ተከራካሪ ወገን በሌላኛው ተከራካሪ ወገን ቅን ልቦና ውጪ በሆነ ተግባር ለክርክር ተዳርጎ መገኘቱ ከተረጋገጠ የወጪና ኪሳራ ጥያቄ ውድቅ ማድረግ የስነ ስርዓት ሕጉ ሊያሳካ ከአሰበው ዓላማ ውጪ በመሆኑ የሕግ መሰረት የሌለው ነው፡፡በመሆኑም

የውጪና ኪሳራ ጥያቄን አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ በመጠኑ ላይ በሕጉ ስልጣን የተሰጠው መሆኑና ረቺ ሁልጊዜ ወጪና ኪሳራ እንዲተካለት መደረግ የሌለበት መሆኑ ግንዛቤ የሚወሰድበት ቢሆንም ከቅን ልቦና ውጪ ለክርክር የተጋበዘውን ወገን በተመለከተ ግን የክርክሩ ረቺ መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ቅን ልቦና ከሌለው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት ማድረግ ክርክሮች ያላግባብ እንዳይፈጠሩ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣም አመልካች በ2ኛ ተጠሪዎች አውራሽ ከቅን ልቦና ውጪ በሆነ ምክንያት ለክርክሩ መዳረጉን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው በሚገባ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ የተለየ ድምዳሜ የሌለው መሆኑን የትዕዛዙ ድምዳሜ አስረጅ ነው፡፡በመሆኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 463 እና 464 በተመለከተው መሠረት የግራ ቀኙ ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሣራ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪዎች ለአመልካች የመተካት ግዴታ ሊኖርባቸው ይገባል፡፡ተጠሪዎች ሊተኩ የሚገባው የወጪና ኪሳራ መጠን ደግሞ አመልካች ዝርዝሩን አቅርቦ ግራ ቀኙ ክርክር አድርገውበትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 “………… ምን ያህል ይክፈል………” የሚለውን በሚመለከት በሕጉ ለፍ/ቤቱ የተሰጠውን ፈቃደ ስልጣን ሁሉ በመጠቀም የሚወሰን ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት አመልክች በ2ኛ ተጠሪዎች አውራሽ ቅን ልቦና መሰረት ባላደረገ ሁኔታ ለክርክር የተዳረገ መሆኑ አረጋግጠው እያለ የወጪና ኪሳራውን ጥያቄ በዝምታ ማለፉም ሆነ

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ክፍል ሳያርም መቅረቱ ወጭና ኪሣራ አወሣሰን ትክክለኛ አፈፃፀም የተከተለ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81591 የካቲት 14 ቀን 2005 ዓ/ም በአመልካች የቀረበውን ወጪና ኪሳራን አስመልክቶ የሰጠው የውሳኔ ክፍልና በዚሁ የውሳኔ ክፍል አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በመ/ቁጥር 89064 ሚያዚያ 29 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የወጪና ኪሳራ ዝርዝሩን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የማስወሰን መብት አለው ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡
3. የዚህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

***መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 90452

ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ትዕግስት አሸናፊ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገ/ሥላሴ በርሄ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በውሉ በተመለከተው መሰረት አልተከፈለም የተባለን በብድር የተሰጠ ገንዘብ ከማስመለስ ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ ባለመክፈላቸው ከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ያቀረበውን ክስ ተከሳሽ ቀርበው ባለመከላከላቸው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ተከሳሽ በሌሉበት አይቶ ዋናውን ገንዘብ እና ወለዱን ጨምሮ በድምሩ ብር 300,109.15 ከ 29/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ በ26/02/2001 ዓ.ም. ውሳኔ በመስጠት እና በ19/11/2002 ዓ.ም. ደግሞ የብር 6,294.30 የወጪና ኪሳራ ውሳኔ በመስጠት መዝገቡን ከዘጋ በኃላ ተከሳሽ ክርክሩ በሌሉበት ተሰምቶ ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው በመደበኛ መኖሪያ አድራሻቸው በአግባቡ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ መሆኑን ገልጸው ውሳኔው ተነስቶ ክርክራቸውን ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት በማግኘቱ ውሳኔው ተነስቶ የጽሁፍ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶአቸው የነበረ መሆኑን፣ይሁን እንጂ ተከሳሽ በቀጠሮው ዕለት መልስ ባለማቅረባቸው መብታቸው ታልፎ ክሱን ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ የተያዘ መሆኑን፣ክሱን ለመስማት በተያዘው ቀጠሮም ሳይቀርቡ በመቅረታቸው ጉዳዩ በድጋሚ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑን ፣ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በህግ ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ክርክርን ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ግምቱን ፍ/ቤቱ በራሱ ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚገባው፣እስከ ሁለት ዓመት ያልተከፈለ የወለድ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠር ስለመሆኑ በፍ.ሕ.ቁ. 2024(1) ስር የተመለከተው ግምት በባንክ በሚሰጥ ብድር ጉዳይም ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 29181 በ20/04/2002 ዓ.ም. አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንደሰጠ እና ይህንን የሕሊና ግምት ለማፍረስ ከሳሽ በፍ.ሕ.ቁ. 2473(2) መሰረት ያቀረበው ማናቸውም ዓይነት ማስረጃ እንደሌለ ገልጾ ተከሳሽ ከዋናው ዕዳ ያልተከፈለውን ብር 41,391.50 እና ለኢንሹራንስ የተከፈለውን ብር 19,586.87 ከወለድ እና ከቅጣት ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ እና የወጪና ኪሳራ መጠኑንም ከቀድሞው ዝቅ በማድረግ በ22/02/2004 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣በከሳሽ ጠያቂነት የይግባኝ ክርክሩን የሰማው ፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ የስር ተከሳሽ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ቢሆንም በጽሁፍም ሆነ በቃል ያቀረቡት ክርክር በሌለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የቀድሞ ውሳኔውን እራሱ በመለወጥ የሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ አይደለም

በማለት ውሳኔውን ሽሮ በቀድሞው ውሳኔ መሰረት አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ውሳኔ መስጠቱን እና በመጨረሻም በስር ተከሳሽ ጠያቂነት የይግባኝ ክርክሩን የሰማው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የቀድሞው ውሳኔ የተነሳ በመሆኑ ጉዳዩን እንደገና ከመመርመር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትን የሚያግደው ነገር እንደሌለ ገልጾ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የፍሬ ነገር ክርክሩን መርምሮ ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 343(1) መሰረት ለፌከ/ፍ/ቤት በመመለስ ውሳኔ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ብር 300,109.15 ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ በማለታቸው ውሳኔው ቢነሳም ተጠሪ የጽሁፍም ሆነ የቃል ክርክር ሊሰማ በተቀጠረበት ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በድጋሚ በሌሉበት አይቶ ተጠሪ በፍ.ሕ.ቁ. 2024(1) በተመለከተው የሕሊና ግምት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል በማለት የወለድ ጥያቄውን ውድቅ አድርጎ ዋናውን ዕዳ ብቻ እንዲከፍሉ ሲወስን ቀደም ብሎ አመልካች የወለድ አሰላሉን በተመለከተ ያያዘውን ሰነድ ሳይመለከት የማለፉን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብ ተከሳሽ በሌሉበት በመጀመሪያ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 78(2) መሰረት ተነስቶ ተከሳሽ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ የጽሁፍ መልስ ሳያቀርቡና ክሱ ሊሰማ በተያዘው በቀጠሮም ሳይቀርቡ ከቀሩ በድጋሚ በሌሉበት ታይቶና ተመርምሮ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ከሚሆን በስተቀር የተነሳው ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸና የሚደረግበት አግባብ የለም ሲል የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት በመመለስ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚል ጭብጥ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ውሳኔው ወይም ትእዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሳኔው እንዲነሳለት ሊያመለክት እንደሚችል እና ፍ/ቤቱም የሌላኛውን ወገን አስተያየት ከሰማ በኃላ የአመልካቹን አቤቱታ ተገቢ አድርጎ ከተቀበለው ውሳኔውን በማንሳት ክርክሩ እንደገና የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ እንደሚሰጥ በፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 78 ተመልክቶአል፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በሌሉበት ታይቶ የተሰጠባቸው ውሳኔ ተነስቶ ክርክራቸውን ለማቅረብ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ውሳኔው ከተነሳ እና ክርክሩን እንደገና ለመቀጠል ቀጠሮ ከተያዘ በኃላ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ለሁለተኛ ጊዜ ተጠሪ በሌሉበት የአመልካችን ክስ እና ማስረጃ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት የቻለው ተጠሪ በጽሁፍም ሆነ በቃል ክርክራቸውን ለመስማት በተሰጠው ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ክርክሩን በድጋሚ በሌሉበት በማየት ነው፡፡በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩን ለማሰማት እንዲፈቀድለት ጠይቆና ተፈቅዶለት ለጹፍም ሆነ ለቃል ክርክር በተያዘው ቀጠሮ በድጋሚ ሳይቀርብ ከቀረ ፍ/ቤቱ ክርክሩን መምራት የሚገባው በምን ዓይነት ስርዓት እንደሆነ የስነ ስርዓት ሕጉ በግልጽ ያስቀምጠው ነገር

የለም፡፡ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ ተጠሪ ክርክሩን እንደገና ለማየት የሚያስችል በቂ ምክንያት ያቀረቡ መሆኑን አረጋግጦ የቀድሞውን ውሳኔ ያነሳው እስከሆነ ድረስ ተጠሪ ክርክራቸውን እንዲያቀርቡ በድጋሚ በተሰጣቸው ዕድል ተጠቃሚ ሳይሆኑ ከቀሩ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 70(ሀ) በተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እና ክርክሩን እንደገና ለመስማት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የአመልካች ክስ እና ማስረጃ እንደገና ተመርምሮ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚደረግ ከሚሆን በስተቀር እንዲነሳ አስቀድሞ ትዕዛዝ የተሰጠበት የቀድሞ ውሳኔ በቀጥታ ተመልሶ እንዲፀና ሊደረግ የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡የከሳሽ ወገን ክስ እና ማስረጃ እንደገና ተመርምሮ የሚሰጠው ውሳኔ ደግሞ እንደነገሩ ሁኔታ ከበፊቱ ውሳኔ ጋር ተመሳሳይ ወይም የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡በመሆኑም ተከሳሽ ወገን የቀድሞውን ውሳኔ ለማስለወጥ የሚችል የጽሁፍም ሆነ የቃል ክርክር ያላቀረበ እስከሆነ ድረስ የከሳሽ ወገንን ክስ እና ማስረጃ እንደገና መመርመር ሳያስፈልግ  የተነሳው የቀድሞ ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸና መደረግ ነበረበት በማለት አመልካች ቀረበውን ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በሌሉበት በመጀመሪያ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 78(2) መሰረት ተነስቶ ተጠሪው ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ የጽሁፍ መልስ ሳያቀርቡና ክሱ ሊሰማ በተያዘው በቀጠሮም ሳይቀርቡ ከቀሩ በድጋሚ በሌሉበት ታይቶና ተመርምሮ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ከሚሆን በስተቀር አስቀድሞ የተነሳው ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸና የሚደረግበት አግባብ አለመኖሩን ገልጾ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር እና የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት በመመለስ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የስር ተከሳሽ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ በጽሁፍም ሆነ በቃል ያቀረቡት ክርክር በሌለበት ሁኔታ የስር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀድሞ ውሳኔውን እራሱ በመለወጥ በመቁ.114956 በ22/02/2004 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት ውሳኔውን ሽሮ በቀድሞው ውሳኔ መሰረት አፈጻጸሙ እንዲቀጥል የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.118042 በ08/12/2004 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪው ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ የጽሁፍ መልስ ሳያቀርቡና ክሱ ሊሰማ በተያዘው በቀጠሮም ሳይቀርቡ ከቀሩ በድጋሚ በሌሉበት ታይቶና ተመርምሮ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ከሚሆን በስተቀር አስቀድሞ የተነሳው ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸና የሚደረግበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን ገልጾ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የይግባኝ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 343(1) መሰረት ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት በመመለስ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 82803 በ21/06/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 91968

ታህሳስ 15 ቀን 2009.ም.

**ዳኞች:** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች**:- አቶ ግርማ ሰንበት አልቀረቡም

**ተጠሪ:-** ወ/ሮ አልማዝ ገብረየስ ጠበቃ ወንድወሰን ይልማው ቀረቡ

**ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37983 ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰረት በድጋሚ በማየት እንዲያርምልኝ ያቀረብኩትን ማመልከቻ በቂ ህጋዊ ምክንያት የለውም ብሎ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

1. ከዚህ በፊት የአሁን አመልካች/ከሳሽ/ በመሆን ተከራክረዋል አመልካች ተጠሪ የራሳቸው መጸዳጃ ቤት የላቸውም ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር የመፀዳጃ ቤት በጋራ በመጠቀም ላይ እያለን ከሳሽ መፀዳጃ ቤቱን በጋራ ለመጠቀም ባለመቻሉ የራሴን መፀዳጃ ቤት ለመገንባት የእድሳት ፈቃድ አውጥተን ከሰራተኞች ጋር ተዋውዬ ቤቱን ማፍረስ ላይ እያለሁ ስራውን እንዳቆም የተደረግሁ በመሆኑ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድና የመፀዳጃ ቤቱን በማደስ ስራውን እንዳጠናቅቅ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርባ መፀዳጃ ቤቱን የሰራሁት እኔ ነኝ መፀዳጃ ቤቱ የሚገኘው በእኔ ይዞታ ስር ነው በማለት ተከራክራለች ፍርድ ቤቱም የክፍሉን አስተዳደር መፀዳጃ ቤቱ በማን ይዞታ ስር እንደሆነ አረጋግጦ እንዲልክለት ጠይቆ መፀዳጃ ቤቱ በተጠሪ ይዞታ ስር መሆኑን በማረጋገጡ ይዞታው የተጠሪ ነው በማለት ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
2. አመልካች በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 09 አስተዳደር ከዚህ በፊት የሰጠው የባለሙያ ማስረጃ ተገቢነት የሌለው መሆኑን አሳግባብ የቤት ቁጥር 417 /አመልካች ቤት የጋራ መገልገያ የሆነውን መፀዳጃ ወደ ቤት ቁጥር 418 ያጠቃለላ በመሆኑ ከዚህ በፊት የተፃፈው ደብዳቤ መሻር ያለበት ነው በማለት ጽፏል ስለዚህ ቀደም ተብሎ ተጠሪ የውሳኔ ባለመብት የሆነችው ሀሰተኛን መረጃ መሰረት በማድረግ በመሆኑ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰረት ፍርድ በድጋሜ ተይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09

የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት በቁጥር7/ክ/ከ/ወ0 የሰአ/363/105 ታህሳስ 23 ቀን 2005 ዓ/ም የተፃፈውን ደብዳቤ በመጥቀስ የሰጠውን ማስረጃ በማያያዝ ጥያቄ አቅርቧል የስር ፍርድ ቤት አመልካች ፍርድ እንደገና እንዲታረምለት ያቀረበውን ጥያቄ ለማስረዳት ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ቀደም ብሎ የተሰጠው ውሳኔ በሀሰተኛና ወንጀል ነክ ተግባሮች በተገኙ የሰነድ ማስረጃዎች መሆኑን የሚያሳይ አይደለም ፍርዱ በድጋሚ የሚታይበት ምክንያት የለም በማለት ሚያዚያ 18 ቀን 2005 ዓ/ም ብይን ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች ሀምሌ 12 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የመጀመሪያው ውሳኔ የተሰጠው በሀሰት ተዘጋጅቶ በተሰጠ ማስረጃ መሰረት መሆኑን የሚሳይ ሰነድ አቅርቤአለሁ ይህም የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰፈርት አያሟላም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት አመልክቷል ተጠሪ መስከረም 13 ቀን 2005 ዓ/ም የመጀመሪያ ውሳኔ የተሰጠው ሀሰተኛና በተጭበረበረ የወንጀል ተግባር መሆኑን የአመልካች ማስረጃ አያሳይም የስር ፍድ ቤት ብይን ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች አመልካች ጥቅምት 4 ቀን 2006 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡
4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የስር ፍድ ቤት አመልካች ከጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር ያቀረበው ማስረጃ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ አንቀጽ 6/1/ መስፈርት አያሟላም በማለት ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው የስር ፍድ ቤት ይዞታው የተጠሪ ነው ብሎ ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ለሰጠው ውሳኔ መሰረት የሆነው በጉለሌ ክፍለከተማ የወረዳ 9 የመሬትናፕሮሰስ ካውንስል የፃፈው ደብዳቤ ቀደም ሲል በሚመለከተው ክፍል በGIS ላይ 9997 ተብሎ የተገለፀው ቦታ የማን ይዞታ እንደሆነ ለማየት የሚያስቸግርና የጋራ መገልገያ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠውን ውሳኔና የተፃፈውን ደብዳቤ  ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሬት ላይ ይዞታውን /መጸዳጃ ቤቱን/ አመልካችና ተጠሪ በጋራ የሚገለገሉበት መሆኑን የሚደብቅና በቀድሞው የወረዳ 8 ቀበሌ 11 የቤት ቁጥር 417 ነዋሪ የሆነውን አመልካችን የመፀዳጃና የማብሰያ ቤት ለቤት ቁጥር 418 በማጠቃለል በካርታ ቁጥር 20/11/26812/00 እንዲሰጥ  ያደረገ መሆኑን የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር አረጋግጦ በደብዳቤ የገለፀ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡
6. ይህም ይዞታው የተጠሪ ነው ተብሎ ውሣኔ ለመስጠት መሰረት የሆነው መረጃ እውነታውን የማያሳይና ከዚህ በፊት የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችንና የተፃፉ ደብዳቤዎችን አላግባብ በማለፉ የተሰጠ ሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑን የሚያሳይ ነው አንድ የመንግስት አካል /ባስልጣን/ እወነተኛውን ሳያጣራ መስጠት የማይገባውን ሀሰተኛ ማስረጃ ለፍርድ ቤት በመስጠቱ ውሳኔ የተሰጠበት ወገን ማስረጃው ሀሰተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እስካቀረበ ድረስ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/1/ መስፈርትን ያላሟላሀ ስለሆነ ፍርድ በድጋሚ አይተይልህም መባሉ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ አንቀጽ 6/1/ መሰረታዊ ዓላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘውም ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ በደጋሚ እንዲታይ የጠየቀው ሰው ሀሰተኛ መረጃ የተሰጠው መንግስት በኃላፊነት ቦታ ላይ ባስቀመጠው ባለስልጣን እና በመንግስት አካል መሆኑን ከማስረዳት አልፎ የመንግስት ባለስልጣን ይህንን ህገወጥ ተግባር የፈፀመበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ሊጠይቅ የሚገባው እንዳልሆነ

ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 403 እና አንቀጽ 405 ድንጋጌዎች ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/1/ ድንጋጌ ጋር በማጣመር በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም ለሰጠው ውሳኔ መሰረት ያደረገው ለክፍሉ አስተዳደር የተፃፈ ደብዳቤ እውነታውን የማያሳይና ሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑን የጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 አስተዳደር በፃፈው ደብዳቤ የተገለፀ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት ፍርዱን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/1 መሰረት እንደገና ለማየት በቂና ህጋዊ ምክንያት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ፍርዱን በድጋመ ለማየት በቂ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37483 ሚያዚያ 15 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰረት ጉዳዩን በድጋሚ በማየት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመቀበልና በመስማት እንደዚሁም አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ፧ወደ መዝገብ ቤት ይመስለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 85468

መስከረም 24 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ሣባ ኢንጂንሪግ ኃ.የተ.የግል ማህበር ጠበቃ ምስጋናው ካሴ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጂንሲ ነ/ፈጅ መስፍን በሻህ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በሽያጭ ውል መሠረት ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባውን ቀሪ የሽያጭ ገንዘብና የተጣራ ትርፍ ክፍያ እንዲከፍል ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ክስ መሥርቶ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ በመስጠቱና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይሄው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌዴራል ከፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የቦሌ ቡልቡላ ጠጠር ማምረቻ አክሲዮን ማህበርን ለመሸጥ ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት ከተወዳዳሪዎች መካከል አመልካች የአክሲዮን ማህበሩን ሙሉ ድርሻ ለመግዛት ባቀረበው ዋጋና ቢዝነስ ፕላን መሰረት አሸናፊ በመሆኑ ሀምሌ 08 ቀን 1999 ዓ/ም በተፈረመ የሽያጭ ውል በብር 17,020,570.00 ለመግዛት ስምምነት ማድረጉን፣የሽያጭ ውሉ አንቀጽ 4(2) መሻሻል በማስፈለጉ ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም ማሻሻያ የተደረገለት መሆኑን፣በዚሁ መሰረትም አመልካች የሽያጩን ጠቅላላ ዋጋ 35% ብር 5,957,060.00 ከፍሎ ቀሪውን 65% የሽያጭ ዋጋ ደግሞ በየዓመቱ በእኩል ክፍያ ወለድን ጨምሮ አመልካች ለተጠሪ እየከፈለ ሐምሌ 08 ቀን 2004 ዓም ድረስ ለማጠናቀቅ ስምምነት መደረጉን፣ክሱ እስከቀረበበት ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም እና እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ መክፈል የነበረበትና ያልተከፈለ የሽያጭ ቀሪ ገንዘብ ብር 5,129,494.00፣ወለድና ቅጣት ብር 735,637.00 በጠቅላላው ብር 5,865,131.00 እንደሚፈልግበት፣በሽያጭ ውሉ አንቀጽ 6(2) መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ ርክክቡ እስከተጠናቀቀበት እለት ድረስ ያለውን የተጣራ ትርፍ አመልካች ለተጠሪ መክፈል ያለበት መሆኑ በግራ ቀኙ ስምምነት የተደረገበት መሆኑና አመልካች ያልከፈለው ብር 2,821,490.00



www.chilot.me

ሁኖ ይህም አክሲዩን ማህበር ላይ የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ያረጋገጡት የሂሳብ መጠን መሆኑን፣ተጠሪ ገንዘቡ እንዲከፈለው በተለያዩ ጊዜአት ለአመልካች ማስጠንቀቂያና ማሳሳቢያ ቢልክለትም አመልካች የተለያየና አጥጋቢ ያልሆነ ምክንያት እያቀረበ ለመክፈል ፈቃደኛ ያለመሆኑን ዘርዝሮ ከዋናው የሽያጭ ገንዘብ ቀሪ እና የተጣራ ትርፍ ክፍያ በጠቅላላው ብር 8,686,621.00 (ስምንት ሚሊዩን ስድስት መቶ ሰማንያ ስድስት ሺ ስድስት መቶ ሃያ አንድ ብር) እና በውሉ ላይ የተመለከተውን ወለድ(7.5%) ገንዘቡን ከፍሎ እስከሚያጠናቅቅበት ጊዜ ድረስ ታስቦ አመልካች እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የተጠሪ ክስና ማስረጃ ለአመልካች ደርሶ በሰጠው መልስ የሽያጭ ውሉ መኖሩና 35% መክፈሉን፣ እንዲሁም ቀሪው 65% የሽያጭ ገንዘብ ተከፍሎ የሚጠናቀቅበት ጊዜ ሐምሌ 08 ቀን 2004 ዓ/ም መሆኑን ሳይክድ ክሱ በውሉ የተመለከተው የጊዜ ገድብ ሳያልቅ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣አመልካች ድርጅት የገባውን ውል ግዴታ የሚያፈረስ አንዳችም ጥፋት ያለመፈጸሙን፣ለመክፍል እምቢተኛ ያለመሆኑን፣ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት አለመክፈሉም እንደ እምቢተኛ ያስቆጥረዋል የሚባል ከሆነም በተለያየ ጊዜ የተከሰተውን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች አስመልክቶ የተሰጡት የጽሁፍ መልሶችና ማስረጃዎች መቅረባቸውን፣የማሻሻያ ውሉም የመክፍያ ጊዜ ገደቡን ያልነካው መሆኑን፣የመጀመሪያ ውል ከተደረገ በኋላ በየዓመቱ እኩል ክፍያ የሚል ሐረግ ተጠሪ በማስገባት ውሉ እንዲሻሻል ያደረገው አመልካች ያጋጠመውን የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥና በፈረቃ ሥራ እንዲሰራ የመደረጉን ሁኔታ ያላገናዘበና በወቅቱ በተፈጠረው ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች ምክንያት ጥያቄዎችን ለተጠሪ ሲያቀርብ ውሉ ተሻሻለ እንጂ ቀደም ሲል የነበረውን ውል በየዓመቱ በእኩል ክፍያ ትከፍላለህ የሚል ስምምነት ያለመደረጉን፣አመልካች በኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ለሁለት አመታት ያህል ማምረቱን ማቆሙን፣ለ150 ሰራተኞች ደመወዝ ከብር 200,000.00 በላይ መክፍሉንና ይህንን ችግር ለተጠሪ ማሳወቁን፣በዚህም መሰረት ውይይት ተደርጎ የሽያጭ ዋጋና ወለዱ በረዥም ጊዜ ክፍያ ተከፍሎ እንዲያልቅ በውሉ ላይ የተቀመጠው ቅጣት ደግሞ እንደማይከፈልና እንደሚነሳ የድርጅቶቹን ሕልውናና የሰራተኞችን ቀጣይ ሕይወት ለመታደግ ሲባል ስምምነት ላይ የተደረሰና በኤጄንሲው ቦርድም እንዲጸድቀና ተቀባይነት እንዲያገኝ መደረጉን፣አመልካች ድርጅት ከሚፈልግበት እዳ ላይ በቅድሚያ ብር 5,957,060.00 እና በተለያዩ ሰነዶች የተከፈለ ብር 3,732,622.00 በአጠቃላይ ብር 9,689,682.00 ከነትርፍ ድርሻው የመክፍያውን የጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ መከፈሉን፣ተጠሪ ከሚያዚያ 30 ቀን 2003 ዓ/ም በኋላ ያለውን እንዳልፈለገው ተቆጥሮ እዳው ከመክፈል ቀሪ ይሆናል ስለሚል ሕጉ ተጠሪ መስሪያ ቤት የጠየቀው ወደፊት የመክሰስ መብት በሕግ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣አመልካች የጠጠር ማምረቻ ቦታ ሚያዚያ 03 ቀን እና ሚያዚያ 26 ቀን 2003 ከቦሌ ክፍል ከተማ አስተዳደር የወረዳ 12 ዋና ስራ አስኪያጅ ፅ/ቤት በተፃፈ ደብዳቤ ቦታውን እንዲለቅ በመደረጉ ድርጅቱ ስራውን ማቆሙንና ይህም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑን ዘርዝሮ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በውሉ መሰረት ለክሱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን፣የኤሌክትሪክ መቋረጥም ሆነ የቦታው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መወሰድ የውል ግዴታውን ለመፈፀም የማያስችሉ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው ሊባሉ የማይችሉ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ በዚህ ረገድ  የቀረበውን የአመልካችን ክርክርም ውድቅ ያደረገው ሲሆን አመልካች በሽያጭ

ውሉ መሰረት ሊከፈለው የሚገባውን ቀሪ ገንዘብ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ መክፈል የነበረበትን ብር 5,129,494.00፣በመጀመሪያው ውልና በተሻሻለው ውል መሰረት መክፈል የነበረበትን ገንዘብ ባለመክፈሉ በውሉ አንቀጽ 8(3) መሰረት ቅጣት ብር 735,637.00፣ በዋናው ውል አንቀጽ 6(2) መሰረት ከሐምሌ 1ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ ርክክቡ እስከተጠናቀቀበት እለት ድረስ ያለውን የተጣራ ትርፍ ብር 2,821,490.00፣በውሉ አንቀጽ 4(4) መሰረት ደግሞ ላልተከፈለው ቀሪ የሽያጭ ገንዘብ ለተጣራ ትርፍ ክፍያ ወለድ ብር 7.5% ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያለውን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በውሉ የተመለከተው የመክፈያ ጊዜ ሳይጠናቀቅና ውሉ የተሻሸለ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በፍርድ ቤቱ እገዛ እንዲቀርብ ተጠይቆ ማስረጃው ሳይቀርብ መቅረቱ እንዲሁም የውል ግዴታውን አመልካች ከኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥና ተጠሪ የሸጠው የጠጠር ማምረቻ ድርጅት ያለበትን ቦታ መንግስት ለኮንዶሚኒየም መስሪያ በመፈለጉ በአስቸኳይ ቦታው እንዲለቀቅ ተጠይቆ ቦታውን አመልካች በመልቀቅ ስራውን ያቆመ መሆኑ የውል ግዴታውን ለመወጣት የማያስችሉ ምክንያቶች ሁነው እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ሁኔታዎቹ ስለመፈጠራቸው እንኳ በአግባቡ ሳይመረምሩ ማለፋቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስ ይቻል ዘንድም በአመልካች የቀረቡትን መሰረታዊ የቅሬታ ነጥቦች አንድ ባንድ መመልከቱ ተገቢ በመሆኑ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች አጥብቆ ከሚከራከርባቸው መሰረታዊ ነጥቦች አንዱ ስለውሉ መሻሻል እንደሚያስረዳ ተገልፆ በፍርድ ቤት እገዛ እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ውሳኔ መሰጠቱ ያላግባብ ነው የሚል ይገኝበታል፡፡አመልካች ይህ ማስረጃ ቃለ ጉባኤ ስለመሆኑ ጠቅሶ ማስረጃው ቢቀርብ የሚያስረዳው አመልካቹ ከወለድና ከቅጣት ነጻ መሆኑን ስለመሆኑ የገለፀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በተጠሪ እጅ የሚገኘው ቃለ ጉባኤ ለማስረጃነት መቅረቡን፣ወለድና ቅጣትንም ነፃ ለማድረግ ስምምነት የሌለ መሆኑን ጠቅሶ መልሱን ሰጥቷል፡፡

በመሰረቱ ከሳሽ ክሱን ሲያቀርብ አስፈላጊ ማስረጃዎችን በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ ሊያቀርባቸው የማይችላቸውን ደግሞ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሰረት በፍ/ቤቱ እገዛ እንዲቀርቡለት መጠየቅ የሚችል መሆኑን በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ ስር የተደነገጉት የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች ያሳያሉ፡፡ይህ የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ለተከሳሽም የሚሰራ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 234(1) ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ከሳሹ ወይም

ተከሳሹ ሊያቀርባቸው ሲችል ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኛነት ያላቀረባቸውን ማስረጃዎች በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠበ ሊያቀርብ ወይም የማስረጃ ማሰባሰብ ስራውን ፍርድ ቤት እንዲያከናውን ሊጠይቅ የሚችልበት የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት የሌለ ሲሆን ከሥነ ስርዓት ህጉ አላማ ጋርም አብሮ የማይሄድ ጉዳይ በመሆኑ ሕጉ የሚፈቅደው አካሄድ አይደለም፡፡በፍርድ ቤት እገዛ ማስረጃ የሚቀርበው ተከራካሪ ወገን አጠቃልሎ ማቅረብ የማይችላቸው መሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፍርድ ቤት ማስረጃ እንዲቀርብ ጥያቄ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ ማስረጃው ለጉዳዩ ያለውን አግባብነትም በመመልከት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት የሚችል መሆኑን ከማስረጃ አቀራረብ ደንቦች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች አልቀረበልኝም የሚለው ማስረጃ ስለመቅረቡ ተጠሪ የገለፀ ከመሆኑም በላይ አለ የተባለው ማስረጃ ደግሞ ቃለ ጉባኤ ሁኖ በወለድና በቅጣት ኃላፊነት ላይ በይዘቱ ከዋናው ውልና ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ/ም ተደረገ ከተባለው የማሻሻያ ውል የተለየ መሆኑን አመልካች ጠቅሶ የሚከራከር በመሆኑ አመልካች የውሉ ቅጂ የራሱን ድርሻ ከተጠሪ ሳይወስድና ሳይኖረው የሚቀርበት ሕጋዊ ምክንያትና አግባብ ይኖራል ተብሎ ስለማይታሰብ ማስረጃውን ራሱ ማቅረብ ይገባው የነበረ ከመሆኑም በላይ ሰነዱ ቃለ ጉባኤ ብቻ ነው ከተባለ ደግሞ በፅሑፍ የተደረገውን ውል ማሻሻል የሚቻለው የመጀመሪያው ውል በተደረገበት የጽሑፍ አግባብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1722(1) ድንጋጌ የሚያስገነዝበን ጉዳይ በመሆኑ ማስረጃው ቢቀርብም በሕግ ፊት ዋጋ የሚሠጠው ነበር ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም አመልካች ማስረጃውን ለማቅረብ የማይችል የነበረ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበትና ማስረጃውም በሕጉ አግባብ ውሉ መሻሻሉን የሚያሳይ ሳይሆን ቃለ ጉባኤ መሆኑን ጠቅሶ በሚከራከርበት አግባብ የማስረጃ ማቅረብ መብቱ ሳይጠበቅ ውሳኔ እንደተሰጠ አድርጎ የሚያቀርበው ቅሬታ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ በውሉ የተመለከተው የመክፈያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ክስ መቅረቡ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡በእርግጥ አንድ ተዋዋይ በውሉ የተመለከተውን ግዴታ እንዲወጣ የሚጠየቀው በውሉ በተመለከተው የክፍያ የጊዜ ገደብ ግዴታውን ሳይወጣ መቅረቱ ሲረጋገጥ መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731(1)፣1740፣1756፣1846 እና ከሌሎች ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም የሽያጭ ገንዘቡን አመልካች ከፍሎ ለማጠናቀቅ በውሉ ተቆርጦ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሐምሌ 08 ቀን 2004 ዓ/ም መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጊዜ በሕጉ አግባብ ተሻሽሏል የሚል ክርክር አመልካች የሌለው መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡እንግዲህ በውሉ የተመለከተው የገንዘቡ መክፍያ ጊዜ ሐምሌ 08 ቀን 2004 ዓ/ም ሁኖ እያለ ተጠሪ አመልካች ግዴታውን አልተወጣም በሚል ክስ ያቀረበው ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም፤በውሉ ከተመለከተው ጊዜ ቀድሞ ነው፡፡ይህ ተገቢ ያልነበረ መሆኑን ይህ ችሎት የሚቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ይሁን እንጂ አሁን የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሰጠበት እስከ ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስም ሆነ ክርክሩ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ባለበት ሁኔታ በውሉ የተመለከተው የሽያጭ ገንዘቡን ከፍሎ የማጠናቀቂያ የጊዜ ገደብ አልፎ ከአንድ ዓመት በላይ ተጨማሪ ጊዜ ማለፉን የክርክሩ ሂደት የሚያስገነዝበን ፍሬ ነገር ነው፡፡በመሆኑም በውሉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ አልደረሰም የሚለው የአመልካች የክርክር ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጥም ሆነ ባሁኑ ጊዜ ቀሪ የሆነ በመሆኑና በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ

ደግሞ አመልካች ግዴታውን የተወጣ መሆኑን ወይም እየተወጣ የሚገኝ መሆኑ ገልፆ ያቀረበው ክርክር ስለሌለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 280 አግባብ የገንዘቡ መክፍያ ጊዜ አልደረሰም የሚለው መከራከሪያ ነጥብ የክርክሩ ምክንያት ሊሆን የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች መከራከሪያ ነጥብም ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች የሚከራከርበት ነጥብ የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥና ከተጠሪ የገዛው የጠጠር ማምረቻው ድርጅት የነበረበት ቦታ ለኮንዶሚኒየም መስሪያ በመንግስት መወሰዱ ግዴታውን ለመወጣት የማያስችሉ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው ተብሎ የቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች የታለፈው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መፈጠር አለመፈጠሩ እንኳ በአግባቡ ሳይመረመርና ቦታውን አመልካች እንዲለቅ ያደረገው የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ባንክና ከተማ ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሳይደረግ ነው የሚል ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት የነበረ መሆኑና ድርጅቱ የነበረበት ቦታ ለኮንዶሚኒየም መስሪያ ተፈልጎ በአስቸኳይ እንዲለቀቅ ሚያዚያ 03 እና 16 ቀን 2003 ዓ/ም በሚመለከተው የመንግስት አካል ለአመልካች ደብዳቤ መፃፉ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ሲሆን የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረቱ ግን አመልካችን ድርጅቱን ከተጠሪ ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከ ቀረበበት ጊዜ ድረስ ሙሉ በሙሉ እንዳይጠቀም ያደረገው ስለመሆኑ ተገልጸ በአመልካች ክርክር ያልቀረበበት ከመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤት ችግሩ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ለማለት የማያስችል ነው በማለት ውድቅ ያደረገው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር በአግባቡ ሳይመረመር አልፏል የሚለው የአመልካች ቅሬታ የስር ፍርድ ቤትን የውሳኔ ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ እውነት የሌለው ነው፡፡ስለሆነም በሕግ ጭብጥነት መታየት ያለበት የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል? ወይስ አይችልም? የሚለው ነው፡፡

በዚህ መሠረትም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻለው መቼ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1792 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ድንጋጌ ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው ባለአዳው ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍፁም መሰናክል በሆነ አይነት የሚደግፈው ነገር ባጋጠመ ጊዜ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለአዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈፃፀም ከባድ የሆነ ወጭ በባለአዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለእዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለአዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊያስብና ጥንቃቄ ሊያደረግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረጉት የክሱ ምክንያት የሆነውን እዳ ለመክፈል የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም በማለት

ነው፡፡በመሆኑም አመልካች የገዛው ድርጅት የጠጠር ማምረቻ እና ይህንኑ ስራ የሚሰራውም በኤሌክትሪክ ኃይል መሆኑ ቀድሞ የሚታወቅ ሲሆን ለስራው ቀጣይነት የኤሌክትሪክ ኃይል አስተማማኝ መሆኑን ለሥራ በሚሰማራበት ጊዜም ሆነ በወቅቱ በአገሪቱ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አጣርቶ የክፍያ ምንጬ የድርጅቱ ስራና በስራው የሚገኘው ገቢ ከመሆኑ ጋር አገናዝቦ የክፍያ ጊዜውን በተመለከተ ከተጠሪ ጋር ስምምነት ሊያደርግበት ይችል የነበረ መሆኑ የሚታመን ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጎ ግዢውን ከፈፀመ በኋላም ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚችልበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ሣያደርግ ቀርቶ ጉዳት ቢደርስ እንደሕጉ አነጋገርና መንፈስ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም አመልካች ከላይ እንደተመለከተው በድርጅቱ ግዢ ወቅትም ሆነ ከግዢ በኋላ የኃይል ችግር እንዳይደርስበት አስቀድሞ ሊገምተውና ሊከላከለው ሲገባ ይህንን የመከላከልና የጥንቃቄ ዕርምጃ አስቀድሞ ሣይወስድ በመቅረቱ እዳውን ለመክፈል ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ሊባል የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡በተጨማሪም አመልካች ስራውን በፈረቃ ይሰራ የነበረ መሆኑን በክርክሩ ሂደት የገለፀ በመሆኑ ፍጹም በሆነ መሰናክል ውስጥ ነበር ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡

ሌላው ከአቅም በላይ ምክንያት ጋር አያይዞ አመልካች የሚያነሳው ነጥብ በግዥ ያገኘው ድርጅት ያለበት ቦታ ለኮንዶሚኒየም መስሪያ የመንግስት አካል ተረክቦታል የሚለው ነው፡፡በእርግጥ ቦታው እንዲለቀቅ ሚያዚያ 03 እና 16 ቀን 2003 ዓ/ም የተጻፉ ደብዳቤዎች የሚያሳዩና ተጠሪም ያልካደው ፍሬ ጉዳይ ሲሆን አመልካች የጠጠር ማምረቻ ስራውን የሚሰራበት ምትክ ቦታ የተሰጠውና ስራውንም እየሰራ የሚገኝ መሆኑንና ተገቢውን ካሳም አመልካች እንዲያገኝ ተጠሪ የበኩሉን ስለማድረጉ ገልጾ በሰጠው መልስ ግን አመልካች የማስተባበያ ክርክር አላቀረበበትም፡፡ይህም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 235 እና 83 ድንጋጌዎች መሰረት የሚያሳየው አመልካች የገዛው ድርጅት እስከ ሚያዚያ 16 ቀን 2003 ዓ/ም በቦታው የነበረ መሆኑንና በምትክም ሌላ ቦታ አመልካች ወስዶ ስራውን የቀጠለ መሆኑን አመልካች በግልጽ ያልካደው፣ይልቁንም እንዳመነ የሚቆጠር ፍሬ ነገር መሆኑን ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ይህ ምክንያት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1791,1792 እና 1793 (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች አግባብ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ብሎ ለመወሰድ የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያስገነዘበን ነው፡፡ቦታው እንዲወሰድ ትዕዛዝ ያስተላለፈው አካልም የክርክሩ ተካፋይ በመሆን የሚያስጠብቀው መብት ወይም ጥቅም እንዲሁም እንዲወጣ የሚገደድበት ግዴታ የሌለ በመሆኑ የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ውሳኔ ተሰጥቷል የሚለው የአመልካች ክርክር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39 እና 40 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች በሕጉ አግባብ ማቅረብ የሚችለውን ማስረጃ ማቅረቡ ስለተረጋገጠና ያለፍርድ ቤት እገዛ ደግሞ ማስረጃውን ማቅረብ የማይችል መሆኑ ያልተረጋጠ በመሆኑ፣የእዳው መክፍያ ጊዜም በክርክሩ ሂደት የደረሰና አመልካችም ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ እንዲሁም ግዴታውን ለመፈፀም ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ተከስተዋል ለማለት የሚቻል ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ውጤቱ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 108074 ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 82501 በ17/03/2005 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ ውጤቱ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

በዚህ ችሎት መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 87834

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አቶ ግርማ አበራ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ ፀዳለ ካሣ

2ኛ/ ገነት ካሣ } ሁለቱም ቀርበዋል

3ኛ/ ጌጤ ካሣ - ከጠበቃ አቶ ከፈለኝ ካሣ ቀረቡ

**መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 የተመለከተው ድንጋጌ በግራ ቀኙ መካከል ለተነሳው ክርክር ያለውን አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪዎች በመካከላቸው የተነሳው የውርስ ክርክር ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እየታየ እያለ፤ ጉዳያቸውን በእርቅ/ በስምምነት የጨረሱ መሆኑን በመግለፅ በደረሱበት የእርቅ ስምምነት መሰረት ጉዳዩ እንዲቋጭ ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ሰኔ 29 ቀን 1993 ዓ/ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን በመ/ቁ 27/93 ተመልክቶ የእርቅ ስምምነቱን በማጽደቅ በስምምነቱ መሰረት ጉዳዩ የተቋጨ መሆኑን ሚገልጽ ዳኝነት ሰጥቷል፡፡

በዚህ አኳኋን በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው የአሁን ተጠሪዎች በአፈፃ/መ/ቁ 178781 እንደጠየቁ የአሁን አመልካች በእርቅ ስምምነቱ እንዲከፋፈሉ የተስማሙበት ንብረት የይዞታ ማረጋገጫ የሌለው መሆኑን ይህንኑ ዓይነት ንብረት በስምምነት እንድንከፋፈል ተስማምተናል በማለታቸው ምክንያት የእርሱን መብትና ጥቅም የነካ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለበትን ዝርዝር የፍሬ ነገር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማጣቀስ አቤቱታውን ዋናውን ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም ቀደም ሲል በውሳኔ የዘጋውን የመ/ቁ 27/93 የሆነውን መዝገብ ካንቀሳቀሰ እና የአሁን አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ቀደም ሲል ውሳኔ የሰጠው ግራ ቀኙ ያደረጉትን ስምምነት ተቀብሎ በማጽደቁ ምክንያት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተከራከሪ ወገኖች የእርቅ ስምምነት መሰረት

የተሰጠው ውሳኔ በሶስተኛ ወገን ላይ ውጤት እንደማያስከትል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3311 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ይህ በእርቅ ስምምነት መሰረት የተሰጠው ውሳኔ በአመልካች ላይ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም የሚል ዳኝነት በመስጠቱና ይህም ዳኝነት በበላይ ፍ/ቤቱ በመፅደቁ የተነሳ ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ እንደቻለ ከጉዳዩ አመጣጥ ተገንዝበናል፡፡

እኛም በዚህ አኳኋን በተሰጠው ዳኝነት ላይ ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡትን የጽሁፍ ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3311 ድንጋጌ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ወገኖች በሙግት ምክንያት ሊሆን የሚችለውን ጉዳይ ወይም ደግሞ ያከራከራቸውን ጉዳይ በእርቅ በጨረሱ ጊዜ ይህ የእርቅ ስምምነት በሶስተኛ ወገን ላይ ውጤት አያስከትልም በሚል የተመለከተው የድንጋጌ ይዘት ግብና ዓላማ የእርቅ ስምምነቱ ግቡ ታራቂዎች በየግላቸው ያላቸውን መብትና ግዴታ እንደሁኔታው በማስተካከል ለክርክር መንስኤ ሊሆን የሚችለውን ወይም የሆነን ጉዳይ በስምምነት ማስቀረት እንደመሆኑ መጠን በዚህ የእርቅ ስምምነት ላይ ቀሪ የሆነን መብት እና ግዴታን ወይም የተፈጠረን መብትና ግዴታን ሊመለከት የሚችለውና ተፈጻሚነቱ በእነዚያው በታራቂ ወገኖች ላይ ብቻ ተገድቦ የሚቀር፤ የሌላ ሰውን መብትና ግዴታ ሁሉ በማካተት የእነዚህ ሶስተኛ ወገኖች መብትና ግዴታ አብሮ በእርቅ እንዳለቀ ሊቆጠር እንደማይችል የእርቅ ስምምነቱ አንፃራዊ ውጤቱ በተስማሚ ወገኖች ላይ ብቻ የተገደበ መሆኑን የሚያመለክት እንደመሆኑ መጠን ይህ ክርክር የተነሳበት የእርቅ ስምምነት ጉዳይ የማንም ሦስተኛ ወገን መብትና ግዴታን ሳይነካ በእራሱ ችሎ ሊፈፅም የሚችል የመሆኑ ጉዳይ ሊረጋገጥ ይገባል አሁን በተያዘው ጉዳይ ግን የእርቅ ስምምነት እንደ ታራቂዎች ሀሳብ በስምምነቱ ላይ የተገለፀው መብትና ግዴታ ተፈፃሚነቱ በተስማሚዎች መብትና ግዴታ ላይ ብቻ ተወስኖ ሊቀር ያልቻለ መሆኑን የማያመለክት የፍሬ ነገርና የህግ ክርክር የአሁን አመልካች አቅርቧል፡፡ የአሁን አመልካች ይህንኑ ከመጥቀሱም በላይ እንደፍርዱ እንዲፈፀምላቸው በፍርድ ኃይል ዕገዛ የአሁን አመልካች ግዴታውን እንዲፈጽም የአፈፃጸም ክስ ማቅረባቸውም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3311 ከተመለከተው አንፃር ይታይ እንኳ ቢባል ተጠሪዎች የደረሱበት ስምምነት ወይም እርቅ ከእራሳቸው መብትና ግዴታ አልፎ 3ኛ ወገን የአሁን አመልካችን መብትና ጥቅም የነካ ስለመሆኑ አመልካች ክርክር ያቀረበ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የእርቅ ስምምነቱ የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት በታራቂዎች ላይ ብቻ ተወስኖ እንዳልቀረ እየታወቀ የሥር ፍ/ቤቱ ለድንጋጌው የሰጠው ትርጉም መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪዎች እርስ በእርሳቸው ያደረጉት የእርቅ ስምምነት እና በፍ/ቤት የፀደቀው ውሳኔ እና የስምምነቱ አካል ሳልሆን ክርክሬ ሳይሰማ መብትና ጥቅሜን ያስቀረ እኔን የጎዳ ውሳኔ ሊሰጥ በመቻሉ መብትና ጥቅሜን በክርክር ማስከበር እንድችል የክርክር ተካፋይ ልሁን በማለት ያቀረበው ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 አፈፃፀም ማሚያ የሚሆኑትን የፍሬ ነገር ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማጣቀስ የተደገፈ መሆኑ እስኪታወቅ እና ለዚህም ማስተባበያ እስካልቀረበበት ጊዜ ድረስ አመልካች በጉዳዩ ላይ የክርክር ተካፋይ ሊሆን ሲገባ እንዲሁም የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ ያቀረበው አቤቱታ በፍ/ሕ/ቁ 3311 ከተመለከተው ድንጋጌ አፈፃፀም ጋር ተደጋጋፊ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ከእነዚህ ድንጋጌዎች

ትክክለኛ አፈፃፀም እና ትርጉም በመራቅ የአሁን አመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በጉዳዩ ላይ በመ/ቁ 27/93 ነሐሴ 29 ቀን 2004 ዓ/ም እና በኮ/መ/ቁ 127958 ታህሳስ 02 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ አማካኝነት የሰጡት ዳኝነት ሁሉ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27/93 ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ/ም በተጠሪዎች መካከል የቀረበውን የእርቅ ስምምነት ተቀብሎ ያፀደቀበት ውሳኔ የአመልካች መብትና ጥቅም የነካ ስለመሆኑ ሊያመለክት የሚችል የክርክር መነሻ በአሁን አመልካች በኩል የቀረበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ፍ/ቤቱ በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ጉዳዩን የአሁን አመልካች ባለበት እንደገና በማየት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 89893

መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ኮንቴክ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አለልኝ ምህረቱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ወልዱ ህሉፍ - ጠበቃ ሰለሞን ገ/ሚካኤል ጋር ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮም ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከስነ-ስርዓት ክርክር ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ድርጅትና የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች በሆኑት ሌሎች 2 ሰዎች ከሳሽነት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ጥር 24 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ አመልካችና የአመልካች ድርጅት ባለአክሲዮኖች በሆኑት አቶ ሳልህ ሁሴንና ወ/ሮ አለም ካሣ በጋራ በመሆን በተጠሪ ላይ ያቀረቡት የክሱ ይዘት ባጭሩ ተከሳሽ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ሆኖ በሰሩበት ወቅት ያለአግባብ ያባከኑት የድርጅቱን ገንዘብ ብር 3,641,052.04 እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸውና እንዲሁም ተከሳሹ በድርጅቱ ባለአክሲዮንነት ማዋጣት ከሚጠበቅበት የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ ገቢ አድርገው የተገኘው ብር 516,744.56 በመሆኑና በዚህ የተነሳም የማህበሩ ካፒታል ወደ ብር 4,442,616.36 ብቻ ቀንሶ በመገኘቱ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ድርሻ እያንዳንዳቸው ባደረጉት ካፒታል ልክ እና እንዲሁም የማህበሩ ጠቅላላ ካፒታልም በተከፈለው ልክ ብቻ ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ የተለያዩ መከራከሪያ ነጥቦችን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የማህበሩን ካፒታል እና የባለአክሲዮኖቹን የአክሲዮን ድርሻ መጠን ጋር በተያያዘ የተጠየቀው ዳኝነት በፍ/ቤት የሚወሰን አይደለም በማለት በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ ወይም መከራከሪያ ነጥብ በመቀበል ያለፈ ሲሆን ተጠሪ በስራ አስኪያጅነት ኃላፊነታቸው አባክነዋል የተባለውን የድርጅቱን ገንዘብ በተመለከተ ግን ምክንያቶቹን በበለጠ በመተንተንና ግልፅ በማድረግ ክሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ሌሎች ከሳሾች ከክሱ በመቅረት የአሁኑ አመልካች ብቻ ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ ክሱን አሻሽያለሁ በማለት ለፍ/ቤቱ ያቀረበ ሲሆን ይህ ተሻሽሎ የቀረበ ነው የተባለው የክሱ ይዘትም ባጭሩ ተከሳሹ ያልከፈሉትን የአክሲዮን ድርሻ ወይም ዋጋ ብር 2,438,255.44 ና እንዲሁም በስራ አስኪያጅነታቸው ዘመን ያባከኑትን የድርጅቱን ገንዘብ ብር 5,488,693.84 ከህጋዊ ወለድ ጋር ታስቦ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን

ተጠሪም በበኩሉ ክሱ በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት ተሻሽሎ አለመቅረቡንና ሌሎች ክርክሮችንም በማንሳት መልሱን ሰጥቷል፡፡ ቀጥሎም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በ15/8/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሻሽሎ የቀረበው ክስ ፍ/ቤቱ በ8/10/2003 ዓ/ም ከፈቀደው ውጪ መሆኑን ፍ/ቤቱ ለመገንዘብ ችሏል በማለት የተከሳሽን መቃወሚያ በመቀበል ከሳሽ ፍ/ቤቱ በ8/10/2003 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ክሱን አሻሽሎ ያቅርብ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁኑ አመልካች በ15/8/2004 ዓ/ም የተሰጠው ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(2) መሰረት እንዲታረምለት ጉዳዩን እንዲያይ ለተመራለት ሌላ ችሎት አቤቱታ በማቅረቡና ችሎቱም በቀረበው አቤቱታ ላይ ተጠሪም የበኩሉን መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ/ም አሻሽሎ ባቀረበው ክስ የካፒታል መጠን ይወሰንልኝ የሚለውን ጥያቄ ያስቀረ ከመሆኑም በላይ በሌላ በኩል ከተከሳሽ የሚጠይቀውን ዳኝነትም በዝርዝር አብራርቶ ያቀረበ በመሆኑና የገንዘብ መጠኑም ቢሆን ጨምሮ መቅረቡ ፍ/ቤቱ ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ ሲሰጥ የገንዘብ መጠኑ ከፍ ብሎ እንዳይቀርብ የገደበው ባመሆኑና ይህም ወደፊት ተከሳሹ ይጠየቅበታል? ወይስ አይጠየቅበትም? ተብሎ የሚመረመር እንጂ ከወዲሁ ክሱ እንደገና ይሻሻል ተብሎ ትዕዛዝ የሚሰጥበት ሆኖ ባለመገኘቱ ቀድሞውንም ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ተሻሽሎ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ሚያዝያ 15 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠውን ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(2) መሰረት ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ መሰል ስህተቶችም ለማረም እንደሚቻል የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 17352 የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ በአመልካች ተሻሽሎ የቀረበው ክስ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ተሻሽሎ በቀረበው ክስ ክርክሩ ይቀጥል ሲል ትዕዛዘው ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረቡና ችሎቱም ግራ ቀኙ ቀርበው በጉዳዩ ላይ እንዲከራከሩ ካደረገ በኋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በ15/8/2004 ዓ/ም እራሱ የሰጠውን ብይን ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(2) ድንጋጌን መነሻ በማድረግና ያለስልጣኑ መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት ለይግባኝ አቤቱታ መቅረብ መነሻ የሆነውን ትዕዛዝ በመሻር ክርክሩ ሚያዝያ 15 ቀን 2004 ዓዓም በዋለው ችሎት በፍ/ቤቱ በተሰጠው ብይን መሠረት ይቀጥል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341 መሠረት ወደ ፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟልና ስህተቱ ይታረምልን የሚል ሲሆን አቤቱታውም ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠበት ሲሆን አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት አጠር ባመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ አስቀድሞ ሚያዝያ 15 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት እራሱ ሰጥቶ የነበረውን ብይን መለወጡ ወይም መሻሩ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ መመልከቱ አስፈላጊ ሳይሆን መጀመሪያውኑ ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በመሠረቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(4) ስር የተመለከቱትን የሰው መታሰርና የንብረት ማጣት ጉዳይ የሚመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር በማናቸውም ፍ/ቤት ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜና ከስረ-ነገሩ ፍርድ በፊት በጉዳዩ ላይ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ማናቸውም ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ በትዕዛዙ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደማይቻል ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(3) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳዩም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በባህሪው የሰውን መታሰርና የንብረት ማስተላለፍን ወይም ማዛወርን የሚመለከት ትዕዛዝ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(4) ስር የተደነገገው ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት እና ግንኙነት የሌለው በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ድምዳሜ ላይ ደርሶ በውጤት ደረጃ የሰጠው ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች (የስር ከሳሽ) ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ/ም አሻሽሎ ባቀረበው ክስ መሠረት በፍሬ-ጉዳይ ላይ ክርክሩ በግራ ቀኙ መካከል ቀጥሎ ክሱ ይሰማ የሚል ሲሆን ይህ ትዕዛዝም ከስረ-ነገር ፍርድ በፊትና የጉዳዩ መሰማት በግራ ቀኙ መካከል ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ የተሰጠ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ (interlocutory order) ነው ከሚባል በስተቀር በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ወይም እልባት የሰጠ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የትዕዛዙ ይዘትና ባህሪይ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ በትዕዛዙ ላይ ቅሬታ ካለውም በስረ-ነገሩ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ይህንን ቅሬታም ጨምሮ በአንድ ላይ በማጠቃለል ይግባኙን ያቀርባል እንጂ ክርክሩ ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ በየጊዜው በሚሰጠው ጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(3) መሠረት የተከለከለ ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዙ ላይ በተጠሪ የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ በዚህ ምክንያት ውድቅ ማድረግ ሲገባው ይህንን አልፎ ይግባኙን በመቀበል ማስተናገዱና ወደ ክርክር ጉዳዩ ገብቶ ውሳኔ መስጠቱ የስነ-ስርዓት ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 81511 በ21/8/2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 99819 ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው (interlocutory order) በመሆኑ በትዕዛዙ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል አይደለም ብለናል፡፡
3. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩ ከቆመበት ጀምሮ እንዲታይ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/ትዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 93137

የካቲት 11 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ብጥር ታገለ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አገር ተሰማ - የቀረበ የለም

***መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡***

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ማስረጃ መመዘንን የሚያስከትል በመሆኑ እና ሰበር ችሎቶች የማስረጃ ምዘና ተግባር የሚያስከትሉ ጥያቄዎችን የማስተናገድ ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ አመልካች ለሰበር ችሎቱ ያቀረቡት የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ሲል የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ከሟች ወ/ሮ አብንደጅ አምባው የተላለፈልኝን የእርሻ ይዞታ አላግባብ ይዘውብኛል በማለት የአሁኗ አመልካች የሰበር ክርክሩ ተካፋይ ባልሆኑት በእነ አቶ የሻምበል ተሰማ ላይ በሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ መመስረታቸውን፣ ተከሳሾቹም ቀርበው መሬቱን ይዘው የሚገኙት ስለ አሁኗ ተጠሪ መሆኑን በመግለጻቸው ተጠሪ በጉዳዩ በጣ/ገብነት መከራከራቸውን፣ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል እና በሟች የቤተሰብ አባልነት የተመዘገቡት ከሳሽ ስለመሆናቸው ከሚመለከተው አካል ተጣርቶ የተላከለትን ማስረጃ መሰረት በማድረግ እና ጣ/ገብ በማስረጃነት ያቀረቡት በቀበሌው ማህበራዊ ፍ/ቤት በ15/09/1995 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በጉዳዩ ተከራካሪ ወገን ባልነበሩት የአሁኗ ከሳሽ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ባለመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ክርክር ያስነሳውን የእርሻ ይዞታ ጣ/ገብ ለከሳሽ ለቀው እንዲያስረክቡ በ19/08/2002 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣ይ/ሰሚው ፍ/ቤትም ጣ/ገቧ ያቀረቡለትን ይግባኝ በ26/08/2002 ዓ.ም. ዘግቶ ማሰናበቱን እና በጣ/ገብ ጠያቂነት ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ጣ/ገብ መሬቱን የያዙት ከሳሽ ተከራካሪ ወገን በነበሩበት በማህበራዊ ፍ/ቤት በ15/09/1995 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ መሰረት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ጣ/ገብ መሬቱን ለከሳሽ እንዲለቁ የተሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ ጣ/ገብ መሬቱን ለከሳሽ ለመልቀቅ

አይገደዱም በማለት በ15/02/2004 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች አቅርበውት የነበረው የሰበር አቤቱታ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ.ቁ.75679 በ27/04/2004 ዓ.ም. መዘጋቱን፣ አመልካች ይህ በ15/02/2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝላቸው በፍ.ስ.ስ.ህ.ቁ. 6 ድንጋጌ መሰረት የዳግም ዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡትም ሰበር ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ለመሻር መሰረት አድርጎት የነበረው በ15/09/1995 ዓ.ም. በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠ ነው የተባለው ውሳኔ ሀሰተኛ መሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ተረጋጦአል መባሉን መሰረት በማድረግ መሆኑን እና ቀደም ሲል በመግቢያው እንደተገለጸው የክልሉ ሰበር ችሎት ይህንን የአመልካች ጥያቄ ባለመቀበል በ17/11/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አቤቱታ የቀረበበትን ብይን የሰጠው አቤቱታው ማስረጃ የመመዘን ተግባርን የሚያስከትል በመሆኑ በሰበር ሊታይ አይችልም በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ችሎት ክርክር የተነሳበት መሬት በ1995 ዓ.ም. ለተጠሪ የተወሰነ ነው በማለት ቀደም ሲል ለሰጠው ውሳኔ መሰረት አድርጎት ለነበረው የማህበራዊ ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት የሆነው ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ስለተረጋገጠ ዳኝነቱ በድጋሚ ይታይልኝ በማለት አመልካች በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 ድንጋጌ መሰረት ያቀረቡት ጥያቄ ማስረጃን በሰበር ችሎት የመመዘን ዕድል ይፈጥራል በማለት ጥያቄውን ውድቅ የማድረጉን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የእርሻ መሬት የይዞታ ክርክር ሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሰጡት ለአሁኗ አመልካች ጥቅም ሲሆን የሁለቱን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ በመሻር ጉዳዩን ለአሁኗ ተጠሪ ጥቅም የወሰነው የክልሉ ሰበር ችሎት ነው፡፡የክልሉ ሰበር ችሎት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውም ከሳሽ ተካፋይ ባልሆኑበት ክርክር የተሰጠ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶች ውድቅ ያደረጉትን 15/09/1995 ዓ.ም. በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠ ነው የተባለውን ውሳኔ ነው፡፡በመሰረቱ ማንኛውም ውሳኔ የተሰጠበት ሰው በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6(1)(ሀ) እና (ለ) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ወይም ከእነዚህ አንዱን መሰረት በማድረግ የዳግም ዳኝነት አቤቱታውን ማቅረብ የሚችለው ፍርዱን ለፈረደው ወይም ትዕዛዙን ወይም ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6(1) ስር በግልጽ ተመልክቶአል፡፡አመልካቿን ተረቺ የሚያደርግ ውሳኔ የሰጠው የክልሉ ሰበር ችሎት እስከሆነ ድረስ የዳግም ዳኝነት ጥያቄው በቀጥታ ለሰበር ችሎቱ መቅረቡ ከድንጋጌው አነጋገር አንጻር ሲታይ ተገቢነት የለውም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡የዳግም ዳኝነት ጥያቄን የሚያስተናግድ ፍ/ቤት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች የማጣራት እና የግራ ቀኙን ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን ማከናወን የሚጠበቅበት መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡በሌላ በኩል በክልሎችም ሆነ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ውስጥ የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት ዓይነተኛ ዓላማ አንድ ወጥ የሕግ አተረጓጎም ስርዓትን ለማስፈን ይቻል ዘንድ በመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተትን ማረም ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3)(ሀ) እና(ለ)፣በብ/ክ/መንግስታት ሕገ መንግስቶች እንዲሁም በፌዴራልና በክልሎች ዝርዝር ሕጎች በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ይህም አግባብነት ባላቸው የስረነገር እና የስነ ስርዓት ሕጎች መሰረት ፍሬ

ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጠው ለመጀመሪያ ደረጃ እና ለይ/ሰሚ ፍ/ቤቶች መሆኑን እና በዚህ ረገድ ለሰበር ችሎቶች የተሰጠ ስልጣን አለመኖሩን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ ለተያዘው የክርክር ጭብጥ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ይቻል ዘንድ የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 ድንጋጌን ዓላማ እና ይዘት የሰበር ችሎቶችን የስልጣን ወሰን ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የሰበር ክርክር  የሚመራበት የተዘረጋ የተለየ ስነ ስርዓት ባለመኖሩ አጠቃላይ የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች በሰበር ክርክር ጉዳይም  እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡በመሰረቱ የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 ዓይነተኛ ዓላማ ተገቢ ሁኔታዎችና ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸው ሲረጋገጥ በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በመደለያና በመሰል ወንጀል ጠቀስ ድርጊቶች ምክንያት የተዛነፈውን ፍትሕ ወደነበረበት መመለስ ነው፡፡ይህ ሂደት ከሰበር ችሎቶች የስልጣን ወሰን ውጪ የሆነው ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ምክንያት በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ የተጠቀሰውን የስነ ስርዓት ድንጋጌ ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ የሚኖረው አማራጭ የዳግም ዳኝነት አቤቱታው ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን የማከናወን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች እንዲስተናገድ ማድረግ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጉዳዩ የሚመራለት የስር ፍ/ቤትም የዳግም ዳኝነት ጥያቄው የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው በፍ/ቤቶች የስልጣን ተዋረድ መሰረት የበላይ የሆነው ሰበር ችሎት የመሆኑን ጉዳይ ከግምት ሳያስገባ ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን አከናውኖ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ በመስጠት ረገድ በስነ ስርዓት ድንጋጌው መሰረት ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል፡፡ የተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብት እንዳይጣበብ ለማድረግ ያስችል ዘንድም ጉዳዩ ለወረዳው ፍ/ቤት እንዲመራ መደረጉ የተሻለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ችሎት የዳግም ዳኝነት ጥያቄውን እራሱ ማስተናገድ እንደማይችል የያዘው አቋም ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን የማከናወን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች እንዲታይ መምራት ሲገባው የአመልካች የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ተንጠልጥሎ እንዲቀር ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 09404 በ17/11/2005 ዓ.ም. የሰጠው ብይን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ከላይ በተ.ቁ.1 ከተጠቀሰው ብይን ውስጥ የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ምክንያት በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም በሚል የተሰጠው የብይኑ ክፍል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
3. ከላይ በተ.ቁ.1 ከተጠቀሰው ብይን ውስጥ አቤቱታው በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በሚል የዳግም ዳኝነት አቤቱታው በእንጥልጥል እንዲቀር በማድረግ የተሰጠው የብይኑ ክፍል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሮአል፡፡

4. በአመልካቿ የቀረበውን የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ተቀብሎ በማስተናገድ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 ድንጋጌ መሰረት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 341(1) መሰረት ለሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲላክ ወስነናል፡፡
5. በዚህ ውሳኔ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት ይላክ፡፡
6. እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ሰበር ችሎትም ይላክ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

*ት/ዘ*

የሰ/መ/ቁ 83771

መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ አቶ ሰለሞን ፍቅሬ

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ ዘነበች አለማየሁ - ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ቀርቧል

2. አቶ አዱኛ ደምሴ -ቀርቧል፡፡

**መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በባንክ የቁጠባ ሂሣብ ውስጥ ያለው ገንዘብ ለማንም ሣይከፈል ታግዶ እንዲቆይ ተብሎ በፍ/ቤቱ የተላለፈው የእግድ ትእዛዝ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ በገንዘቡ ላይ ወለድ ይታሰብበታል? ወይንስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በዚህ ሰበር ችሎት ተመርምሮ ተገቢው ምላሽ እንዲሰጥበት በማለት የቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 እና 359 መሠረት ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባቀረበው የመቀወሚያ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ የመቃወሚያ ማመልከቻ ይዘቱም የይግባኝ መ.ቁ. 58449 በሆነው ላይ በተጠሪዎች መካከል በነበረው የንብረት ክፍፍል ክርክር መነሻነት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በ2ኛ ተጠሪ ስም በተከፈተው የቁጠባ ሂሣብ 34951 ውስጥ ያለው ገንዘብ ለማንም ሣይከፈል እንዲቆይ በሚል አረጋግጠው የእግዱ ትእዛዝ መነሻነት ባንኩ ገንዘቡን በዝግ ሂሣብ ውስጥ እንዲቀመጥ አድርጓል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ችሎቱ በተጠሪዎች መካከል ሲካሄድ በነበረው ክርክር ላይ ታህሣስ 8 ቀን 2003 ዓ.ም ውሣኔ ሲሰጥ ከሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ፍ/ቤቱ የእግድ ትእዛዝ መሠረት ወደ ዝግ ሂሣብ ውስጥ የገባው ገንዘብ ላይ ጭምር ወለድ ታስቦበት ከነወለድ እንዲከፈላቸው በሚል የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ስለነካው በዝግ ወይም ተካፋይ ሂሣብ ውስጥ በተቀመጠ ገንዘብ ላይ ወለድ ስለማይታሰብ ገንዘቡ ወደ ዝግ ሂሣብ ከገባበት ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ጀመሮ ባለው ጊዜያት ወለድ ሣይታሰብበት ዋናው ገንዘብ ብቻ ይከፈላቸው በሚል ውሣኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360 /2/ ስር በተመለከተው መልኩ ተሻሽሎ ወይም ታርሞ እንዲሰጥ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎ ሁለቱም ተመሣሣይነት ባለው መልኩ በገንዘቡ ላይ ወለድ የማይታሰብበት በቂና ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ የቀረበው መቃወሚያ ማመልከቻ ውድቅ እንዲደረግላቸው በመከራከር መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ፍ/ብ/ይ/ሰሚ ችሎቱም ግራ ቀኙን ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመር በኃላ ቁጠባ ሂሣብ ውስጥ ያለው ወጪ ሆኖ ለጊዜ እንዳይከፈል የእግድ ትእዛዝ ከመስጠት በስተቀር አመልካች እንደሚለው

ገንዘቡን ከቁጠባ ሂሣብ ወጥቶ በዝግ ወይም ተከፋይ ሂሣብ ውስጥ እንዲቀመጥ በሚል የሰጠሁት ትእዛዝ ስለሌለ በገንዘቡ ላይ ወለድ የማይታሰብበት ምክንያት የለም በማለት የቀረበውን የመቃወም ማመልከቻ ሣይቀበል ቀርቷል፡፡ አሁን በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ ሲቀመጥ በገንዘቡ ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ በውጤት ደረጃ ገንዘቡ በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ እንደማለት መሆኑ ግልጽና የማያሻማ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካችም ይህንኑን በመረዳት ገንዘቡን በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ በማድረጉና በዝግ ሂሣብ በተቀመጠ ገንዘብ ላይ ደግሞ አመልካች ወለድ አስቦ ለመክፈል የሕግም ሆነ የውል ግዴታ ሣይኖርበት በዝግ ሂሣብ የተቀመጠ ገንዘብ ከነወለዱ ታስቦ ይከፈል ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሣኔው ታርሞ በጥያቄያችን መሠረት ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በመባሉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ቀርበው የበኩላቸውን መልስ የሰጡበት ሲሆን አመልካችም የመ/መልስ ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም በገንዘቡ ላይ የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠበት ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ጊዜያት አመልካች ከነወለዱ አስቦ ገንዘቡን ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው አከራካሪ ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ ምላሽ ሊሰጥበት የሚባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
እንግዲህ ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ እንደተቻለው በ2ኛ ተጠሪ ስም በአመልካች ባንክ በተከፈተ የቁጠባ ሂሣብ ቁጥሩ 34951 ውስጥ ያለው ገንዘብ ለማንም ሣይከፈል ታግዶ እንዲቆይ ተብሎ የእግዱ ትእዛዝ መተላለፍ የተረጋገጠ ፍሬ-ነገር ከመሆኑም በሻገር ይህ ስለመሆኑ በግራ ቀኙም አይካድም፡፡ አመልካችም ይህንኑ የተረጋገጠውን ፍሬ-ነገር መነሻ በማድረግ በአጽኖት እየተካራከረ ያለው በፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ አጠቃላይ ይዘቱ ከፍ ሲል እንደገለፀው ቢሆንም ወይም ቃል በቃል ሲነበብ ገንዘቡ ወደ ዝግ ሂሣብ ተዛውሮ እንዲቀመጥ በሚል የሰፈረ ባይሆንም ገንዘቡ ለማንም ሣይከፈል ታግዶ ይቆይ በሚል አገላለጽ መተላለፉ በራሱ ገንዘቡን ማንም እንዳያንቀሣቅሰው ወይም ማንም እንዳይጠቀምበት ወይም በተለመደው አባባል በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ የሚያደርግ ወይም ውጤት ያለው ትእዛዝ በመሆኑና ይህንኑ መነሻ አድርገን በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ በተደረገ ገንዘብ ላይ ወለድ ሊታሰብ አይገባም በሚል ይከራከራል፡፡
ተጠሪዎችም በበኩላቸው ገንዘቡ ወደ ዝግ ሂሣብ ተዛውሮ እንዲቀመጥ በፍ/ቤቱ የእግድ ትእዛዝ ያልተሰጠ በመሆኑና አመልካች በራሱ በተሣሣተ ትርጉም በተከፋይ ሂሣብ /payable account/ እንዲቀመጥ ያደረገውን በፍ/ቤቱ የእግድ ትእዛዝ መነሻነት ወለዱን ለመክፈል አስመሰሎ የሚያቀርበው ክርክር ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል ይከራከራሉ፡፡
እንዲህ ከግራ ቀኙ እየቀረበ ያለው ክርክር አንድ ቁጠባ ሂሣብ ውስጥ ያለው ገንዘብ እንዴትና በምን አይነት ሁኔታዎች ወደ ዝግ ወይም ተከፋይ ሂሣብ እንዲቀመጥ ሊደረግ ይችላል የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ላይ መፍትሔ ከመስጠቱ በፊት ሙያዊ አስተያየት ወይም ማብራሪያ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥበት ማድረጉ የግድ ይላል ተከራካሪ ወገኖች የሚከራሩበት ነጥብ ከክርክሩ ልዩ ባህሪይ የተነሣ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና የባለሙያን ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በዚህ አኳኃን እንዲጣራ ማድረግ እንደሚገባው

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 136/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በያዝነው ጉዳይም ከፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ገንዘቡን በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ ውጤት ያለው ነው ወይም አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ የባንክ ባለሙያዎች አስተያየት ሙያዊ ማብራሪያ የሚያስፈልግ በመሆኑ እንደሁኔታው ከብሔራዊ ባንክና እንዲሁም በዚህ ረገድ ያለው የሌሎች የግል ንግድ ባንኮች የታወቀና የተለመደ ልማድ ባካተተ መልኩ ተገቢው ሙያዊ አስተየየት እንዲሰጥበት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ታልፎ መወሰኑ ወይም በክርክሩ ሂደት አግባብነት ያላቸው ፍሬ-ነገሮች ሣይጣሩ ታልፎ በመወሰኑ በጉዳዩ ላይ የተሟላ ዳኝነት ተሰጥቷል ለማለት አልተቻለም በመሆኑም በክርክር አመራር ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 58449 ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መዝገቡን አንቀሣቅሶ ግራ ቀኙን በማስቀረብ ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ቁጠባ ሂሣብ ውስጥ የነበረው ገንዘብ ወደ ዝግ ወይም ተከፋይ ሂሣብ ተዛውሮ እንዲቀመጥ የማድረግ ውጤት ያለው መሆን አለመሆኑን እንደሁኔታው በብሔራዊ ባንክ ባለሙያና ተገቢ ሆኖ ከተገኘም ከሌሎች ንግድ ባንኮችም ሙያዊ አስተያየት ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥበት በማድረግና ጉዳዩን በሥነ-ሥርዓት ሕጉ አግባብ በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት በመመለስ ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 90298

የካቲት 10 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ኃይሉ ዴሬሳ - ከጠበቃ ጅሬኛ ለሜሳ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሱፊ አለሙ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ ከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች የቀረበ የንብረት ክፍፍል ጥያቄን አስመልክቶ የተደረገ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተ ጉዳዩ ተጣርቶ በስር ፍ/ቤቶች በውሳኔ የተቋጨ ሲሆን አከራካሪ ሆኖ የቀጠለው እና በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክርም ምክንያት የሆነው በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ በቀበሌ 01 ውስጥ በአሁኑ አመልካች ስም በባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ቁጥር AM/691/89 ተመዝግቦ የሚታወቀው ቤት ነው፡፡ይህንኑ ቤት በተመለከተ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተፈራ የአሁኑ አመልካች የግል ንብረት ነው በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በአሁኗ ተጠሪ ጠያቂነት ይግባኙን የተመለከተው የምዕራብ ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ሰርቪስ ቤቶቹ ከጋብቻ በፊት፣ዋናው ቤት ግን ከጋብቻ በኃላ የተሰሩ መሆኑ ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ መገንዘብ እንደተቻለ ገልጾ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ዋናው ቤት በጋብቻው ጊዜ የተፈራ በመሆኑ ግራ ቀኙ እኩል ሊካፈሉት ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ሰርቪስ ቤቶቹ የአመልካች የግል ንብረት ናቸው በመባሉ በዚህ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔም ቅር ተሰኝተው ይግባኝ በማቅረባቸው እና የአሁኑ አመልካች ደግሞ ዋናው ቤት የጋራ ነው በመባሉ ቅር ተሰኝተው መስቀልኛ ይግባኝ በማቅረባቸው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ጉዳዩ እንደገና በተጨማሪ ማስረጃ እንዲጣራ ካደረገ በኃላ በጋራ የተፈሩ መሆናቸው እንደተረጋገጠ ገልጾ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ዋናውንም ሆነ ሰርቪስ ቤቶቹን ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

ዋናውን እና ሰርቪስ ቤቶቹን አስመልክቶ በአሁኑ አመልካች ጠያቂነት ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ሰርቪስ ቤቶቹን በጋራ ያፈሩት ነው በማለት ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለክልሉ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ሶስት ዳኞች የተሰየሙበት

አጣሪ ችሎት በመ.ቁ. 158167 በ21/06/2005 ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡትም የክልሉ ሰበር ችሎት ሰርቪስ ቤቶቹን ብቻ ነጥሎ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱ ዋናውን ቤት በተመለከተ ለክልሉ ሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት እንዳጣ የሚያስቆጥር ነው በማለት ነው፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ከመገባቱ በፊት በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ ለሰበር ብቁ የመሆን አለመሆኑ ጉዳይ በቅድሚያ እልባት ማግኘት የሚገባው መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በቀጥታ ወደ ተያዘው ጭብጥ ከመገባቱ በፊት በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለክርክር እንዲቀርብ የተያዘው ጭብጥ ከአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት እና የዳኝነት ጥያቄ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑ በቅድሚያ መታየት የሚገባው ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሰርቪስ ቤቶቹን በተመለከተ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት ዋናውን ቤት በተመለከተ ስለመሆኑ በ19/09/2005 ዓ.ም. አዘጋጅተው ካቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር መቅረብ የሚገባው መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ተገቢው ትዕዛዝ ሊሰጥበት ይገባው የነበረው ዋናውን ቤት በተመለከተ ብቻ ሆኖ እያለ ሰርቪስ ቤቶቹ የጋራ ናቸው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት በሚል በዚህ መዝገብ ለክርክር ተይዞ የቀረበው ጭብጥ የአመልካቹን የሰበር አቤቱታ ይዘት መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ዋነኛ ጭብጥ በተመለከተ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው በአምቦ ከተማ በቀበሌ 01 ውስጥ በአሁኑ አመልካች ስም በባለቤትነት ማረጋገጫ ቁጥር AM/691/89 ተመዝግቦ የሚታወቀው ቤት ነው፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት ዋናው ቤት የጋራ ነው መባሉን በመቃወም ሲሆን በሌላ በኩል የዚሁ ቤት ሰርቪስ ክፍሎች ጉዳይ በክልሉ ሰበር ችሎት በክርክር ላይ ይገኛል፡፡ጉዳዩ አምስት ዳኞች ለሚሰየሙበት የክልሉ ሰበር ችሎት የተላለፈው ሰርቪስ ቤቶቹን በተመለከተ ቢሆንም በሰበር ችሎቱ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ አልታወቀም፡፡አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት የክልሉ ሰበር ችሎት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው በአጣሪው ችሎት በተያዘው ጭብጥ ሳይገደብ በሌሎች ነጥቦች ላይም ጭምር ጭብጥ በመመስረት ክርክሩ እንዲሰማ አድርጎ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ መስጠት የሚችል በመሆኑ ሰርቪስ ቤቶቹን አስመልክቶ የቀረበውን የአቤቱታ ነጥብ ለማጣራት ጉዳዩ ለክልሉ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ሶስት ዳኞች የተሰየሙበት አጣሪ ችሎት በመ.ቁ. 158167 በ21/06/2005 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ነው ከሚባል በቀር የመጨረሻ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ትዕዛዙ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ነው ከተባለ ደግሞ አመልካች ዋናውን ቤት በተመለከተ አቤቱታቸውን ለዚህ ሰበር ችሎት ማቅረብ የሚገባቸው በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 320(3) ድንጋጌ መሰረት በክልሉ ሰበር ችሎት የተያዘው ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኃላ ነው፡፡በመሆኑም ሰርቪስ ቤቶቹን የሚመለከተው የክርክሩ ክፍል በሂደት ላይ ባለበት እና የመጨረሻ ውሳኔ ባላገኘበት ሁኔታ ዋናውን ቤት አስመልክቶ አመልካች በዚህ መዝገብ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአሁኑ የክርክር ደረጃ ሊስተናገድ የሚችል ሆኖ ባለመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. ሰርቪስ ቤቶቹን የሚመለከተው የክርክሩ ክፍል በክልሉ ሰበር ችሎት በሂደት ላይ ባለበት እና የመጨረሻ ውሳኔ ባላገኘበት ሁኔታ ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት በመ.ቁ. 158167 በ21/06/2005 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ አመልካች በዚህ መዝገብ ያቀረቡት አቤቱታ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
2. አመልካች በክልሉ ሰበር ችሎት በመ.ቁ.158167 የተያዘው ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኃላ ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነውን ዋናውን ቤት አስመልክቶ ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ የሚያግዳቸው አይሆንም በማለት ወስነናል፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ



www.chilot.me

# የንግድ ህግ

የሰ/መ/ቁ. 79561

የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ፀጋዬ አማን ለጃ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አንዋር ሙስጠፋ አህመድ ቀረቡ

***መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡***

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የኪራይ ውል ግንኙነት እንዲቀጥል የቀረበውን ጥያቄ መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ እና በወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም ንብረትነቱ የአሁኑ ተጠሪ የሆነ የንግድ ቤት በ18/12/1998 ዓ/ም በተፈረመ ውል ከቀድሞው የንግድ መደብሩ ባለቤት ከአቶ አቦቸር ሁንዴ በመግዛት የንግድ ቤቱ ኪራይ ውሉን በስማቸው እንዲዛወር በማስደረግ መደብሩን ከገዙበት ጊዜ አንስቶ የንግድ ስራውን ሲያከናዉኑ ቆይተው የንግድ መደብሩን ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ለሆኑት ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ያከራዩ መሆናቸውን፣ ወ/ሮ አስካለም አመልካች በአወጡት የንግድ ፈቃድ መሰረት የንግድ ሰራቸውን በማከናወን እንዳሉ የአሁኑ ተጠሪ የአመልካችን ተግባር እንደ ሕገወጥ ተግባር በመቁጠር ከአመልካች ጋር ያለውን የንግድ ቤት ኪራይ ውሉን በማቋረጥ ከወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ጋር የኪራይ ውል ማድረጉን ዘርዝራ ተጠሪ ከወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ጋር ያደረገው የኪራይ ውል ተሰርዞ አመልካች ጋር የነበረው የኪራይ ውል ግንኙነት እንዲቀጥል እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካች የንግድ ቤቱን ከተጠሪ እውቅና ውጪ ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ አከራይተው በመገኘታቸው ችግሩን ለማስተካከል በወጣው መመሪያ መሰረት ከአመልካች ጋር የነበረው ውል ተቋርጦ ከወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ጋር ኪራይ ውል መደረጉን ገልጾ እርምጃውን ሕጋዊ ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆኑት ወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ በሌሉበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ያከራዩት የንግድ መደብሩን መሆኑንና ይህም ተግባር በንግድም ሕጉም ሆነ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ተገቢ መሆኑን ዘርዝሮ እና አግባብነት አላቸው ያላቸውን ድንጋጌዎችንም በመጥቀስ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የኪራይ ውሉን ሊቀጥል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ያከራዩት የንግድ ቤቱን መሆኑ ያልተካደ ፍሬ ነገር መሆኑን፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የንግድ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን አሳልፈው ሲያከራዩ የአከራዩን ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው መሆኑ በከራይ ውሉ መመልከቱንና ሕጉም ግዴታ የሚጥልባቸው መሆኑን በምክንያትነት ይዞና አግባብነት ያላቸውን

ድንጋጌዎችን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል እንዲቀጥል ሊገደድ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት የሰበር አቤቱታቸው ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ የንግድ ሕጉ ስለንግድ መደብር ኪራይ ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪ ባሉበት እንዲታይ የታዘዘ በመሆኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሑፍ በሰጠው መልስ አመልካች ለሶስተኛ ወገን ያከራዩት የንግድ መደብሩን ሳይሆን የንግድ ቤቱን ስለመሆኑ ማስተባበያ ክርክር ያልቀረበበት መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑና ይህም የአመልካች ተግባር በንግድ ሕጉ ስለንግድ መደብር ኪራይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የሚታይበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙኝ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለውው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውን የንግድ ቤት ተከራይተው የንግድ ፈቃድ በስማቸው አውጥተው ሲሰሩበት ከቆዩ በኃላ ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ የንግድ መደብሩን አከራይተው የንግድ መደብሩን ተከራይ የሆኑት ግለሰብ ቤቱን ሲጠቀሙ መቆየታቸውና ይህ ተግባር በንግድ ሕጉ የተፈቀደ ሁኖ እያለ በተጠሪ በኩል ሕገ ወጥ ነው በሚል ምክንያት አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የኪራይ ውል እንዲቋረጥ ተደርጎ አመልካች የንግድ መደብሩን ከአከራያቸው ግለሰብ ጋር ተጠሪ ሌላ የኪራይ ውል ተዋውሏል በሚል ምክንያት መሆኑን፣ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ያከራዩት የንግድ መደብሩን ሳይሆን የንግድ ቤቱን ሁኖ ይህንን ለማድረግም ደግሞ የአከራዩን ፈቃድ አመልካች ማግኘት ይገባቸው የነበረ መሆኑን ጠቅሶ በወቅቱ በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ባለው መመሪያ መሰረት ሕጉን ተከትሎ ተግባሩን መፈፀሙን አምኖ የተከራከረ መሆኑን፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የንግድ ቤት ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ያከራዩ መሆኑን ያልካዱ መሆኑን በውሳኔው ላይ ያሰፈረ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ውሳኔ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ሳይሆን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ማረም ነው፡፡ በመሆኑም ችሎቱ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡን ፍሬ ነገር እንደ ተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመቀበል በሕጉ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈፀመ መስረታዊ ስህተት መኖሩን በማረጋገጥ ይህንኑ ስህተት ማቃናት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን

ነጥብ ባለመቀበል የሚቀርበውን ክርክር የሚመለከትበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያከራዩት የንግድ ቤቱን ስለመሆኑና ቤቱን ሲያከራዩ ለአከራዩ አስቀድሞ የማሳወቅ የውል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ማስተባበያ ክርክር አላቀረቡም፡፡ ይልቁንም አመልካች ይህንኑ ተግባር ሕጋዊ ነው በማለት የሚከራከሩት የን/ሕ/ቁጥር 127(ሐ) እና 145(1) ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ነው የንግድ ቤት ከንግድ መደብሩ የተለየ ሊሆን አይችልም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ለአመልካች ያከራየው የንግድ መደብር ካለመሆኑም በላይ የንግድ ቤቱን በተመለከተ ግን አመልካች ለሶስተኛ ወገን ሲያስተላልፉ ለአከራዩ የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በውሉ ሰነድ ያረጋገጠ በመሆኑና የን/ሕ/ቁጥር የአከራይን ፈቃድ ተከራይ አስቀድሞ እንዲያገኝ በሕግ ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንዲሁም በዚህ ረገድ ውል ተገብቶ ከሆነ እንኳ ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን የሚያስቀምጠው የንግድ መደብር ከራይን በሚመለከት እንጂ የንግድ ቤትን ኪራይ በሚመለከት አይደለም፡፡ አንድ ውል በሕጉ አግባብ ከተቋቋመ ደግሞ የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ) እና 1731 ድንጋጌዎችን በአንድ ላይ በማጣመር ስናነብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የንግድ ቤትን ኪራይ የተከራየ ሰው ያለአከራዩ ፍቃድ ለሶሰተኛ ወገን አስተላልፎ መስጠት የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል ስለመሆኑ በውሉ ላይ ከተመለከተ ይህ ስምምነት በሕግ ጥበቃ የማይደረግለት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ከተጠሪ ያተከራየው የንግድ መደብሩን ሳይሆን የንግድ ቤቱን ስለመሆኑና የንግድ ቤቱን ደግሞ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው ሲሰጡ የአከራዩን ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው መሆኑን በውሉ ላይ ግዴታ ገብተው ይህንኑ ግዴታቸውን ሳይወጡ የንግድ ቤቱን ለሶሰተኛ ወገን አስተላልፈው መስጠታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ከአመልካች ጋር የነበረውን የኪራይ ግንኙነት ተጠሪ እንዲቋረጥ ማድረጉ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ)፣1731 እና 2959 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከን/ሕ/ቁጥር 127 እና 145 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17579 በ12/08/2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 17782 በ25/08/2004 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ የተከራዩት የንግድ መደብሩን ሳይሆን የንግድ ቤቱን በመሆኑና በንግድ ቤቱ ያላቸውን ኪራይ መብት ለሶስተኛ ወገን ሲያስተላልፉ ለአከራይ ለማሳወቅ የውል ግዴታ የገቡ ሁነው ይህንኑ ግዴታቸውን ሳይወጡ የንግድ ቤቱን ማከራየታቸው ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በተወሰነው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 82503

ሚያዚያ 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡- 1.ወ/ሪት ቤዛ ዱጉማ
2.አቶ ብሩክ ዱጉማ } ጠበቃቸው አቶ ዮሴፍ አእምሮ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ዘሚሊ ቀለም ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ አለሙ ገበየሁ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን የሰበር አመልካቾች እንደየቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ከሳሾች፤ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- በአጭር ሥነ ሥርዓት የቀረበ ሲሆን፡- ፍሬ ቃሉም ከአባታችን በውርስ ያገኘናቸው የ1ኛ ከሳሽ 840 አክሲዮኖች፣ የ2ኛ ከሳሽ ደግሞ 841 አክሲዮኖች በተከሳሽ ድርጅት ያለን ሲሆን ተከሳሽ በ2001ዓ/ም ከተገኘው ትርፍ ሊከፍለን የሚገባንን ድርሻ የከፈለ ቢሆንም በ2002 ዓ/ም ፋብሪካው ብር 24,340,165.11 ከግብር በኂላ ማትረፉ በውጪ ኦዲተር የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ከኦዲት ሪፖርት 11,036,538.97 ለባለ አክሲዮኖች ሳይከፈል የተቀመጠ መኖሩ ስለተረጋጠና በአጠቃላይ ማህበሩ ብር 35,376,704.08 የሚከፈል ትርፍ ስላለው ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ የመንግስት ግብርና ታክስ እንዲሁም በድርጅቱ ያለብን ብድር ተቀንሶ ለእያንዳንዳችን ብር 1,206,057.76 ስለሚደርሰን ለሁለታችን ሊደርሰን የሚገባውን ብር 2,412,115.52 ገንዘቡን መክፈል ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ክሱን እንዲከላከል ተፈቅዶለት ባቀረበው መልስ፡- ከሳሾች በኦዲት ሪፖርት ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ የመንግስት ግብርና ታክስ ተቀንሶ ድርሻቸው እንዲሠጣቸው የጠየቁ ቢሆንም የኦዲት ሪፖርት ከካሽ ፍሰው ስቴትመንትና (cash flow statement) እና ከባላንስ ሽት (Balance sheet) ጋር አብሮ መናበብ ይገባዋል፡፡ ክስ የቀረበበት ገንዘብ በዋነኛነት በጥሬ ገንዘብ የተገኘ አይደለም፣ የኦዲት ሪፖርት ካሽ ፍሰው ስቴትመንት እንደሚያመለክተው ከብር 35,376,704.08 ውስጥ በጥሬ ገንዘብ የተገኘው 107,181.78 ብቻ ሲሆን ቀሪው ከሳሾች

ትርፍ ነው ብለው የመዘገቡት ገንዘብ ከተከሳሽ ድርጅት እህት ኩባንያዎች የሚሰበሰብ ነው፣ከትርፍ ክፍፍል በፊት ከሳሾችን ጨምሮ ባለአክሲዮኖች ያላዋጡት መዋጮ ብር 25,311,616.61 ስላለ ትርፉ ሊከፈላቸው የሚገባው ገንዘቡን ለዲ.ኤች. ገዳ ዳይንግ ኤንድ ብሊቺንግ ፋብሪካ ባለአክሲዮኖች በቅድሚያ ከከፈሉና ከእህት ኩባንያዎች ላይ ገንዘቡ ከተሰበሰበ በኋላ ነው፡፡ እንዲሁም ትርፍ ገንዘብ በጥሬ ገንዘብ ቢኖር ትርፉ ለባለአክሲዮኖች ከመከፋፈሉ በፊት ከድርጅቱ የሚፈለጉ ሁሉም ወጪዎች እና በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት መቀነስ ያለባቸው ሌሎች ወጪዎች ከተቀነሱና ክፍያዎችም ከተከፈሉ በኋላ የሚተርፍ ቀሪ ገንዘብ ካለ ብቻ ነው፣በኦዲት ሪፖርቱ የተገለጸው ትርፍ ዋና ዓላማ በአዋጅ ቁጥር 286/1996 መሰረት መክፈል ያለበትን ታክስ ለመወሰን ነው፣የኦዲት ሪፖርትም መጽደቅ ያለበት በጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን ትርፍ የሚከፋለውም በጠቅላላው ጉባኤ ሲወሰን ነው፣ከሳሾች ለእህት ኩባንያዎች ሊከፍሉ የሚገባ የካፒታል መዋጮ ብር 6,958,221.21 መኖሩን የኦዲት ሪፖርት ስለሚያመላክት ይህ ገንዘብ ከሳሾች ከሚያገኙት ትርፍ ሊቀነስ የሚገባ ነው በሚል ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የጋራ ምስክር የሆኑት ኦዲተር የሰጡትን የምስክርነት ቃል ከሰማ በኋላ በሰጠው ፍርድ ከሳሾች አለ የሚሉት ትርፍ ገና ያልተሰበሰበ ከመሆኑም ሌላ የተለያዩ ወጪዎች፣ብድሮች፣ የካፒታል መዋጮዎች ያልተከፈሉበት እና ስለትርፍ አከፋፈልም ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ለከሳሾች የሚከፈላቸው የትርፍ ክፍያ የለም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

የሥር ከሳሾችም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ስላሰናበታቸው የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡

በሰበር አቤታቸውም በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦች፡-

- የሽርክና ማህበሩ ዋና አላማ የኢኮኖሚ ሥራ በመሥራት ትርፍ ማግኘት ሲሆን እያንዳንዱ ባለአክሲዮንም በየዓመቱ ከተጣራ ትርፍ ላይ ድርሻውን የማግኘት መብት እንዳለው በንግድ ህግ አንቀጽ 345(1) ከመደንገጉም በላይ በድርጅታችን የመመሥረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7 ሥር የድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች እንደሚከፋፈል የተደነገገውን ተጠሪው በመጣስ የ2002 ዓ/ም ትርፍ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ እንዲከፍል እንዲወሰንልን ያቀረብነውን ክስ ፍርድ ቤቶቹ የድርጅቱን ያልተሰበሰበ ገንዘብ ሰብስቦ የማስገባት እንዲሁም በድርጅቱ አለበት የተባለውንም የብድር ገንዘብ በወቅቱ በመክፈል በድርጅቱ ወጪዎች ማስያዝ የተጠሪ ሀላፊዎች ሥራ ሆኖ ሳለ ተጠሪው እነዚህን ነጥቦች በተመከለተ ያቀረበውን ክርክር እንደ በቂ ምክንያት የተቀበሉት ያለአግባብ ነው፡፡
- ተጠሪው የድርጅቱ ወጪዎች አልተከፈሉም ብሎ ቢከራከርም የኦዲት ሪፖርቱ ወጪዎች ሁሉ የተከፈሉ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ነው፣
- በተጠሪ የመተዳደሪያ ደንብ እና የመመሥረቻ ጽሁፍ የማህበሩ ካፒታል ሙሉ በሙሉ የተከፈለ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ሰነዶቹ አግባብ ባለው አካል ፊት ተመዝግበው እያሉ ፍርድ ቤቶቹ የካፒታል መዋጮ አልተከፈለም ያሉት ተገቢነት የለውም፣

- በመመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7 የደርጅቱ የተጣራ ትርፍ ለባለቤቶቹ እንደሚከፍል እንጂ ለትርፍ ክፍፍል የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ እንደሚያስፈልግ የማይገልጽ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶቹ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለትርፍ ክፍፍል ያስፈልጋል ያሉት ተቀባይነት የለውም  የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡-

- በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11(1) የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ መሰበሰብ የሚገባ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የጠቅላላ ጉባኤ ዋና አላማም የዉጪ ኦዲተር ሪፖርት ሰምቶ ማጽደቅና ስለትርፍ ክፍፍል መወሰን ሲሆን በዚህ ጉዳይ ጉባኤው ተሰብስቦ የትርፍ ክፍፍል እንዲደረግ የኦዲት ሪፖርቱን አላጸደቀም፤
- በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 7 የተጣራ ትርፍ ለአባላት የሚከፈል መሆኑን የሚደነግግ ቢሆንም አንቀጹ የትርፍ ክፍፍሉ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሳያስፈልግ ክፍፍሉ ይፈጸማል አይልም፤
- አመልካቾች ለትርፍ ክፍያ ጥያቄ መነሻ ያደረጉት በኦዲት ሪፖርቱ ላይ የተገለጸውን የተጣራ ትርፍ ቢሆንም በሪፖርቱ የተጣራ ትርፍ ነው የተባለው በዋናነት የተዘጋጀው ለግብር ዓላማ እንጂ ለትርፍ ክፍፍል በሚል የተዘጋጀ አይደለም፣
- በኦዲት ሪፖርቱ የተጣራ ትርፍ ነው የተባለውም አመልካቾችን ጨምሮ ከባለአክሲዮኖች ወደ ፊት የሚሰበሰበውን የካፒታል መዋጮን የሚያካት በመሆኑ አመልካቾችም በኦዲት ሪፖርቱ የተጣራ ትርፍ ነው የተባለውን ትክክል ነው ብለው የሚወስዱ ከሆነ ትርፉ ያልተከፈለ የካፒታል መዋጮን የሚጨምር መሆኑን ሊቀበሉት ይገባል፤
- በምስክርነት ቀርበው ቃላቸውን የሰጡት ኦዲተርም ብር 107,181.78 ትርፍ መሆኑን ቢገልጹም ከብር ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን በላይ አመልካቾች ባለአክሲዮኖች ከሆኑባቸው እህት ኩባንያዎች የሚሰበሰበው መሆኑን፣ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ ብር ሃያ ሁለት ሚሊዮን የሚሰበሰበው ከባለአክሲዮኖች ሲሆን የተወሰኑት እናት ኩባንያዎችም የተዘጉና ሥራ ያቆሙ በመሆናቸው ሊሰበሰብ የማይችል መሆኑን አረጋጠዋል፤ በመሆኑም ለትርፍ ክፍፍሉ ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት አመልካቾች ያቀረቡትን የትርፍ ክፍፍል ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

አመልካቾችም ለተጠሪው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ማንኛውም በሽርክና ስምምነት መሰረት የሚቋቋም ማህበር የንግድ ማህበር እንደሚባል ከንግድ ህጉ ቁጥር 210(1) መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የሽርክና ስምምነቱም ተሻራኪዎች በህብረት ሆነው የኢኮኖሚ ተግባር ያለውን ሥራ ለመሥራትና ከሚገኘው ትርፍም ሆነ ዕዳ ተካፋይ ለመሆን የሚደረግ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 211 ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ ማህበር ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን በንግድ ህጉ ቁጥር 517 እና 518 መሰረት የራሱ የሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ያለው ነው፡፡ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ በአንቀጽ 7 ለማህበሩ አባላት ዓመታዊ ትርፍ የሚከፈል መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን፣ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ሲባልም በመተዳደሪያ

ደንቡ የተመለከተውን ህጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ ከተከፈለና ሌሎችም ወጪዎችና ክፍያዎች ከተፈጸሙ በኂላ የሚቀረው ገንዘብ ስለመሆኑ ያመላክታል፡፡ እንዲሁም በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10(2) እያንዳንዱ አባል ማህበሩ ከሚያገኘው ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ የመካፈልና ማህበሩ ሲፈርስም ከሚገኘው ገንዘብ የመካፈል መብት ያለው መሆኑንና የትርፍ አከፋፈሉም በመመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7 መሰረት እንደሚሆን የደንቡ አንቀጽ 15 ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በመመስረቻ ጽሁፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ አባላት የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ የመካፈል መብት ያላቸው ስለመሆኑ የተደነገገ ከሆነ ተጠሪው የትርፍ ክፍፍሉን ለማድረግ በጠቅላላ ጉባዔ የኦዲት ሪፖርት ቀርቦ አልተወሰነም፣የማህበሩ ገንዘብ ከባለአክሲዮኖችና እንዲሁም ከእህት ማህበሮች አልተሰበሰበም ፣የማህበሩ እዳና የተለያዩ የወጪዎችና ክፍያዎች አልተከናወኑም በሚል ያቀረባቸው እና በስር ፍርድ ቤትም ሆነ በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ደረጃ ተቀባይነት ያገኙትን እነዚህ ምክንያች አግባብነት ያላቸው መሆን አለመሆኑን መመርምር የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ እነዚህ ተጠሪ ያቀረባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች በሶስት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው፡፡ አንደኛው ለማህበሩ አባላት የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ ለመከፈል የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የሚፈልግ ነው? ወይስ አይደለም? ሲሆን የንግድ ህጉ ቁጥር 532(1) ከ 20 በላይ የሆኑ ማህበረተኞች ባሉባቸው ማህበሮች ውስጥ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው ቀን አንድ ጠቅላላ ጉባኤ መደረግ አለበት ሲል በአስገዳጅ ሁኔታ ያስቀመጠ ሲሆን የማህበርተኞቹ ቁጥር ከ20 በታች በሆኑባቸው ማህበሮች ግን ጠቅላላ ጉባኤ በየዓመቱ የሚደረግ ስለመሆኑ በህጉ የተቀመጠ ግዴታ የለም፡፡ ሆኖም በዚህ ጉዳይ ተጠሪው ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ በየዓመቱ የሚደረግ መሆኑን በደንቡ አንቀጽ 11(1) የተመለከተ ሲሆን የማህበሩ ትርፍ በተመለከተ ግን በጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን ብቻ ለአባላት የሚከፋፈል ስለመሆኑ ደንቡ የሚያመላክት አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪው ትርፍ ለባለአኪሲዮኖች ሊከፈል የሚችለው የኦዲት ሪፖሪቱ ላይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሲሰጥበት ነው ሲል ያቀረበው የመከራከሪያ ሀሳብ ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡

ሁለተኛው የተጠሪው ክርክር ከማህበሩ ባለ አክሲዮኖችና ከእህት ማህበሮች የሚሰበሰብ ገንዘብ ገቢ ባልሆነበት የተጣራ ትርፍ ሊከፋፈል አይገባም የሚል ሲሆን ይህ ተጠሪው ያቀረበው በቅደመ ሁኔታነት በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ የተቀመጠ ካለመሆኑም ሌላ የማህበሩ ሥራ አስኪያጆች በንግድ ህጉ አንቀጽ 528(1) እንደተመለከተው ከማህበሩ ዓላማና ወሰን ሳያልፉ በማንኛውም ሁኔታዎች ሁሉ በማህበሩ ስም ለመሥራት ሙሉ ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን በመተዳደሪያ ደንቡም በአንቀጽ 8 የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የማህበሩን አመራር በሚያካሂዱበት ወቅት ከአንድ ወኪል እንደሚጠበቀው ጥንቃቄ በማድረግ እንዲሁም በታታሪነትና በቅንነት መስራት እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን በመመሥረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 9 ፊደል (ሀ)ም ሥራ አስኪያጁ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን መሥራት እና ማህበሩን መምራት እንዲሁም ከፊደል (ለ-ቀ) ያሉትን የማህበሩን ሥራዎች የማከናወን ግዴታ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ከድንጋጌዎቹ መንፈስ መረዳት እንደሚቻለውም ሥራ አስኪያጁ የተጣለበትን ሀላፊነት በታታሪነትና በቅንነት መወጣት የሚጠበቅበት መሆኑን ሲሆን ከባለአኪሲዮኖች ያልተሰበሰበ የካፒታል መዋጮ ካለም በወቅቱ እንዲሰበሰብ የማድረግ እንዲሁም ከእህት ማህበሮችም የሚሰበሰብ ገንዘብ ካለ በተያዘለት ጊዜ መሰረት ገንዘቡ ለማህበሩ ገቢ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህን በንግድ ህጉም ሆነ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንብ የተጣለበትን ግዴታ የተጠሪው ሥራ አስኪያጅ አልተወጣም ቢባል እንኳን የማህበሩ ባለአኪስዮኖች ለሚጠይቁት የትርፍ ክፍፍል እንደቅድመ ሁኔታ ሊቀመጥ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ ስለሆነም ተጠሪው የትርፍ ክፍፍል ለማድረግ

የካፒታል መዋጮና ከእህት ማህበሮች የሚሰበሰብ ገንዘብ ለማህበሩ ገቢ አልተደረጉም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሶስተኛው የተጠሪው ክርክር የማህበሩ እዳና የተለያዩ ወጪዎችና ክፍያዎች አልተከናወኑም የሚል ሲሆን በእርግጥ ከማህበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7 መገንዘብ እንደሚቻለው የተጣራ ትርፍ ሲባል በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 13 የተመለከተው የመጠባበቂያ ገንዘብ ከተቀመጠ በኋላ እንዲሁም ለሌሎች ወጪዎችና ክፍያዎች ከተፈጸሙ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የመጠባበቂያ ገንዘብ ፣የመንግስት ግብርና ታክስ ጨምሮ ሌሎች ወጪዎችን ክፍያዎችም እንዲሁም ማህበሩ ያለበት ዕዳም ካለ ዕዳው በመቅድሚያ ሊከፍል የሚገባ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ክፍዎች በተገቢው ጊዜ ማህበሩ ሒሳቡን በማስመርመር ክፍያዎቹ መኖራቸው ሲረጋገጥ ከትርፍ ክፍፍል በፊት ከፍሎ ማጠናቀቅ የሚገባ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ባለማድረግ ዕዳዎች እና የተለያዩ ወጪዎች እንዲሁም ክፍያዎች አልተከፈሉም በሚል አመልካቾች በንግድ ህጉም፣በመመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ያገኙትን ትርፍ የመካፈል መብት ሊያዘገይ ወይም ሊያሳጣ አይገባም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በንግድ ህጉ፣እንዲሁም በማህበሩ በመመስረቻ ጽሁፉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለአመልካቾች ከማህበሩ የተጣራ ትርፍ ድርሻቸውን እንዲከፍላቸው ላቀረቡት ክስ ተጠሪ የዘረዘራቸውን አግባብነት የሌላቸውን ምክንያቶች ፍርድ ቤቶቹ ተቀብለው ክሱን ውድቅ ያደረጉት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/108018 በቀን 19/06/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/78730 በቀን 18/11/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡትን የትርፍ ክፍፍል ክስ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ያደረጉት ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡
3. በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የማህበሩ የመጠባበቂያ ገንዘብ፣ እንዲሁም ዕዳዎች፣ወጪዎችና የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለው የተጣራ የ2002 ዓ/ም ትርፍ መኖሩ በአግባቡ ከታወቀ በኋላ አመልካቾች በማህበሩ ባላቸው አክሲዮኖች መጠን መሰረት የትርፍ ድርሻቸው ተሰልቶ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም በዚሁ ውሳኔ መሰረት የፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሂሳቡ እንዲሰራ በማድረግ ተጣርቶ ሲቀርብ ውሳኔ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

የሰ/መ/ቁ. 85009

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ሃጅ ፈዬ ገመቹ ሄዳአ ከጠበቃ አቶ በሽር ወያ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1.አቶ ዓለሙ በቀለ
2. አቶ ክፍለ ማሪያም ከበደ
3. አቶ አሰፋ ጥላሁን
4. አቶ አሰፋ ይመር
5. አቶ ታደሰ ደምሴ
6. አቶ ገስጥ ይነሱ
7. አቶ ንጉሴ ነሲቡ
8. ፶ አለቃ ለማ በየነ
9. አቶ ደበሌ ማርም
10. አቶ ማስረሻ ገ/ሚካኤል
11 አቶ እንዳለ ጭልቆ
12. አቶ ብርሃኑ ዙርጋ
13. አቶ ወርቁ ባሆ
14. አቶ አባተ በቀለ
15 አቶ በየነ አማረ

ተወካይ አቶ አለሙ በቀለ እና አቶ ክ/ማሪያም ከበደ ቀረቡ

***ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፤***

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በኦሮሚያ ክልል የአሪሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06633 የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63806 የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 134880 የሰጠው ውሳኔ፣ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው። ጉዳዩ የንግድ ድርጅት ቤት ሽያጭ የሚመለከት ነው። በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች በወኪሎቻቸው በኩል በአመልካች (አንደኛ ተከሳሽ) በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ በሆነው አየለ ኃይለስላሴ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው። በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በከሳሽነት ቀርበው በአርሲ ዞን በአሰላ ከተማ በቀበሌ 07 ውስጥ በ4000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሚገኝ ስማኒያ አራት አባላት ያሉት የልብስ ሰፊዎች የህብረት ሥራ ማህበር ንብረት አለ። ይህንን የልብስ ሰፊዎች የህብረት ሥራ ማህበር የማይንቀሳቀስ ንብረትና ግምቱ ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) በላይ የሆነውን

ሁለተኛ ተከሳሽ ከማህበሩ አባላት ፈቃድ ውጭ በአነስተኛ ዋጋ ለአንደኛው ተከሳሽ በመሸጥ በከሳሾች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶብናል፡፡ ስለዚህ አንደኛ ተከሳሽ ከሁለተኛ ተከሳሽ ጋር 30/09/97 ያደረጉት የንግድ ቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ ውሳኔ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

2. አመልካች በአንደኛ ተከሳሽ በመሆን ቀርቦ በክሱ የገለፀውን ንብረት፣ የንብረቱ ባለሀብት ከሆነው የልብስ ሰፊዎች የህብረት ሥራ ማህበር ሕጋዊ ወኪሎች 30/9/1987 ዓ/ም በተፃፈና በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ውል በብር 110,000 (አንድ መቶ አስር ሺህ ብር) ገዝቸዋለሁ አንደኛ ተከሳሽ የማይነቀሳቀሰውን ንብረት ዋጋ የንብረቱ ባለሃብት ለሆነው የልብስ ሰፊዎች የህብረት ሥራ ማህበር ሙሉ በሙሉ በመክፈል የማይነቀሳቀሰው ንብረት በስሜ አዛውሬአለሁ፡፡ የንብረቱም ባለኃብት አንደኛ ተከሳሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ካርታና ፕላን በአስተዳደሩ ክፍል ተዘጋጅቶ ተሰጥቶኛል፡፡ ስለዚህ ውሉ ሊፈርስ የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ ከሳሾች የማህበሩ አባላት ናቸው፡፡ የአከራካሪው ንብረት ባለሃብት የሆነው የልብስ ሰፊዎች የህብረት ስራ ማህበር ሰማኒያ አራት አባላት እንደነበሩት ተረጋግጧል፡፡ ከሰማኒያ አራቱ አባላት ንብረቱን እንዲሸጡ ለሁለተኛው ተከሳሽና ለሌሎች ሶስት ማህበሩ አመራር አባላት የውክልና ሥልጣን የሰጡት ሰላሳ አምስት አባላት ብቻ ናቸው፡፡ የማይነቀሳቀሰውን ንብረት የአባላቱ ያልተከፋፈለ የጋራ ሀብት የሚቆጠር በመሆኑ ንብረቱ ለመሸጥ የሁሉም አባላት ሥምምነት አስፈላጊ ነው፡፡ የንብረቱም ግምት ብር 200450 (ሁለት መቶ ሺ አራት መቶ ሃምሳ ብር) እንደሆነ በባለሙያዎች ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ስለዚህ ውሉ ፈርሶ - ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ጸንቷል፡፡
4. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 25/3/2005 ዓ/ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ጉዳዩ መታየት ያለበት ከአዋጅ ቁጥር 147/91 እና ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 106/1996 አንፃር መሆን ሲገባው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍ/ብሔር ሕጉ ስለ ጋራ ንብረት የተደነገጉትን መሰረት በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ እኔ የገዛሁት የማህበሩ ንብረት የሆነ ቤት በመሆኑ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ከሰማኒያ አራቱ አባላት በሞት የተለዩትን ተተኪ የሌላቸው ሰላሳ ዘጠኝ ሰዎች የማህበር አባልነታቸው ቀሪ ሆኗል፡፡ አመልካች ቤቱን በምገዛበት ወቅት ማህበሩ የነበሩት አርባ አምስት አባላቶች ብቻ ነበሩ፡፡ አርባ አምስቱ ማህበሩ አባላት ንብረቱ እንዲሸጥ አርባ አባላት ተገኝተው ተወያይተው ውሳኔ አሳልፈዋል፣ ውክልና ሥልጣን ሰጥተዋል፡፡ ይህም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አስገዳጅ ውሳኔ ለማሳለፍ የሚችሉ የማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተገኝተው ፎርም ተሟልቶ በተሰጠ ውሳኔና ውክልና መሰረት የገዛሁት ሆኖ እያለ ውሉ እንዲፈርስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪዎች በ2/7/2005 ዓ/ም በተፃፈ መልስ የማህበሩ አባላት በማህበሩ ውስጥ ያላቸው መብት እኩል ነው፡፡ ማህበሩ 84 አባላት ያለው ሆኖ እያለ ከሰላሳ ዘጠኝ የማይበልጡ አባላት ብቻ ባስተላለፉት ውሳኔና በሰጡት ውክልና አመልካች ቤቱን መግዛታቸው ውሉን የጸና አያደርገውም፡፡ ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤት

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ከማህበሩ አባላት 50 ፐርሰንት በላይ ተገኝተውና ምልዕተ ጉባኤ ተሟልቶ በተሰጠው ውሣኔ ገዝቻለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍታብሔር ሕጉ ስለ ጋራ ንብረት የተደነገጉትን መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ተገቢና መሰረተዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡ ስለዚህ የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንድስናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ07/08/2005 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም በታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ቤቱን ለመግዛት የተዋዋለው ውል ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሰረትና ድጋፍ ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች አሰላ ከተማ ሸማኔዎች አገልግሎት የህብረት ሥራ ማህበር፣ በአሰላ ከተማ ከፍተኛ ቀበሌ 07 የሚገኘውን ድርጅት ቤት የገዙት አቶ ተስፋዬ በሻህ (የማህበሩ ሊቀመንበር) አቶ ሲሳይ ጅራቱ የማህበሩ ፀኃፊ አቶ አየለ ኃይለ ስላሴ እና አቶ ኃይለማሪያም ደምሴ የተባሉት የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ (ስራ አስኪያጅ) ኮሚቴ አባላት በተገኙበት ሌሎች የማህበሩ ሰላሳ አምስት አባላት ማህበሩ መንግስት ግብርና የዘበኛ ደመዎዝ ለመክፈል ባለመቻሉ ንብረቱን ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው አራቱ የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ (ስራ አስኪያጅ) ኮሚቴ አባላት ንብረቱን ለአመልካች በብር 110,000 / አንድ መቶ አስር ሺ ብር / በመሸጥ ገንዘቡን እንዲቀበሉ ግንቦት 29 ቀን 1987 ዓ.ም የሰጡትን ውሳኔ እና የውክልና ስልጣን በመመልከት ነው ፡፡

8. አቶ ተስፍዬ በሻ (የማህበሩ ሊቀመንበር) ፣ አቶ ሲሳይ ጅራቱ የማህበሩ ፀኃፊ አቶ አየለ ኃ/ለስላሴ እና አቶ ኃ/ማሪያም ደምሴ የተባሉት የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ (ስራ አስኪያጅ) ኮሚቴ አባላት እነሱን ጨምሮ ሰላሳ ዘጠኝ የማህበሩ አባላት ግንቦት 29 ቀን 1987 ዓ.ም ባስተላለፉት ውሳኔ እና በሰጧቸው ውክልና ስልጣን መሰረት የአሰላ ከተማ ሸማኔዎች አገልግሎት የህብረት ስራ ማህበርን በመወከል ግንቦት 30 ቀን 1987 ዓ.ም አከራካሪውን የማህበሩን ንብረት አመልካች በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡ የሽያጭ ውሉን በወቅቱ የውልና ምዝገባ አገልግሎት የመስጠት ስልጣን በነበረው አርሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውልና ምዝገባ ክፍል ቀርቦ ተመዝግቧል፡፡ የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ (ስራ አስኪያጅ) ኮሚቴ አባላት ቤቱን ለአመልካች የሸጡት ማህበሩን በመወከል ፣ በማህበሩ ስምና /የአሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የህብረት ስራ ማህበር ጽ/ቤት/ የሚል የማህበሩን ማህተም በመጠቀም ነው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የሽያጭ ውሉ የተደረገው የአሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የህብረት ስራ ማህበር እና በአመልካች መካከል ነው፡፡

9. የህብረት ስራ ማህበራት የራሳቸው የሆነ ልዩ አላማ ያላቸው ፣ የራሳቸው ባህሪያትና ሕጋዊ ሕልውና ያላቸው ናቸው ፡፡ እያንዳንዱ አባል በማህበሩ ውስጥ ያለው መብትና ግዴታ የሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ፣የሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅን ለማስፈፀም በወጣው ደንብና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ነው፡፡ ተጠሪዎች የማህበሩ አባላት ሰማኒያ አራት ናቸው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ቤቱ ሲሸጥ ማህበሩ ሰማኒያ አራት አባላት የነበረው መሆኑን የማስረዳት ግዴታቸውን እንዳልተወጡ ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይዘት

ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማህበሩ ቤቱ እንዲሸጥ ውሳኔ ሲያስተላልፍ ያልነበሩ ሌሎች አባላት አሉ ቢባል እንኳን ተጠሪዎች ሌሎቹም አባላት ወክለው ክስ ማቅረብ ስልጣን የላቸውም፡፡

10. የሕብረት ስራ ማህበራት ንብረት ላይ መወሰን የሚችለው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀፀ 21 የተደነገገ ሲሆን የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ እንደሚካሄድ  በደንቡ ቁጥር 106/1996 አንቀጽ 20/2/ የተደነገገ ሲሆን ውሳኔ የሚተላለፈው በድምጽ ብልጫ መሆኑ በደንቡ አንቀጽ 23 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ያአሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የሕብረት ስራ ማህበር ሰላሳ ዘጠኝ አባላት ያስተላለፉትን ውሳኔና የሰጡትን ውክልና በማየት ቤቱን ገዝተዋል፡፡ ተጠሪዎች ይህንን የሚያስተባብል ማስረጃ ያላቀረቡ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት የማህበሩ ንብረት እንደ አባላቱ የጋራ ሀብት ሊቆጠርና ንብረቱን ለመሸጥ ሁሉም አባላት ስምምነት በፍታብሕር ሕግ ቁጥር 1266 መሠረት አስፈላጊ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ የአመልካቾች ክርክር በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 32፣ አንቀጽ 18 ፣ አንቀጽ 19 እና ደንብ ቁጥር 106/1996 አንቀጽ 20 እና አንቀጽ 23 የሚጥስና የሕግ መሠረት የሌለው ነው ፡፡

11. የበታች ፍርድ ቤቶች የአሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የሕብረት ስራ ማህበርና በአመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 1266 መሠረት በማድረግ የማህበሩ ንብረት የአባላቱ የጋራ ሀብት በመሆኑ ንብረቱን ለመሸጥ የሁሉም አባላት ስምምነት ያስፈልጋል በማለት ውሉ እንዲፈርስ መወሰናቸው ከላይ የጠቀስናቸውን የአዋጅ ቁጥር 147/1991 እና የደንብ ቁጠር 106/1996 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ክልል የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06633 የሰጠው ውሳኔ ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጠር 63806 የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 134880 የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል ፡፡
2. በአሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የሕብረት ስራ ማህበርና በአመልካች መካከል ግንቦት 30 ቀን 1987 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ይህ ውሳኔ ተጠሪዎች ከቤቱ ሽያጭ የሚደርሳቸው ድርሻ ካለ የአሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የሕብረት ስራ ማህበርን ወይም ገንዘቡን ተካፍለው ወሰዱ የተባሉ አባላትን ከመጠየቅ የሚገድባቸው አይደለም በማለት ወስነናል ፡፡
4. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ 83489

ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** የኢትዩጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ አልሣቤጥ ጌታቸው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዩጵያ  መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ሀሮን ካሣዬ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለመድን አረቦን ኃላፊ መሆን የሚገባው ወገንን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ ክስ ይዘትም አመልካች ደንበኛ ለሆነው አቶ መኮንን ጸጋው የሰ.ቁጥር 3-40259 ኢት የሆነ የጭነት መኪና አጠቃላይ የመድን ዋስትና ሽፋን ተጠሪ እንዲሰጥላቸው በውል እድሳት ማሳወቂያ ሰነድ ማዘዙን፣የኢንሹራንስ ውሉም ለአንድ አመት የሚቆይ መሆኑና ተጠሪ ውሉን አድሶ አመታዊ አርቦን ብር 12,154.75(አስራ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም) እንዲከፍል ጠይቆ አመልካች ደንበኛው ወይም ባንኩ ይከፍላችኋል የሚል ምላሽ ሰጥቶ ከቆየና የመኪናው ባለንብረትም ውሉ እንዲታደስ ጥያቄ አላቀረብኩም በማለታቸው ለባለንብረቱም ሆነ ለባንኩ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን እንዲሰረዝ ማድረጉን በመጥቀስ አመልካች ውሉ እንዲታደስ ትዕዛዝ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ውሉ እስከተሰረዘበት ጊዜ ላለው ብር 6,079.88 እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር በሕጉ አግባብ የገባው ግዴታ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የመድን ውሉ እንዲታደሰ አመልካች ጥያቄ ማቅረቡ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት አመልካችን ከውል የመነጨ ግዴታ አለብህ በማለት ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ሲሆን የኃላፊነቱን መጠን በተመለከተም ውሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ነው በማለት ጊዜውን ሶስት ወር አድርጎ በመለየት ለዚሁ ጊዜ ብር 3,453.30(ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከሰላሳ ሳንቲም)ነው በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች የመድን ውሉ ተጠቃሚ እንጂ ገቢ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበትና የእድሳት

ጥያቄውን አመልካች አቅርቧል ተብሎ ለአረቦን ክፍያው አመልካች ኃላፊ መደረጉ የን/ሕ/ቁጥር 657 እና 675 እንዲሁም አስገዳጅነት ያለውን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከለተው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ  ነጥብ አመልካች ለመድን አረቦን ክፍያው ኃላፊ ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ  ይዘት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የአቶ መኮንን ፀጋው የሆነ የጭነት ተሽከርካሪ አመልካች በመያዣነት ይዞ የመድን ሽፋን የተገባለት መሆኑን በመግለፅ ለመኪናው የመድን ሽፋን እድሳት ጥያቄ በአመልካች በኩል ቀርቦ እድሳቱ ከተደረገ በኂላ ለአንድ አመት የመድን ሽፋን መከፈል የነበረበት የአረቦን ክፍያ በድምሩ ብር 12,154.75 የሚፈለግባቸው ስለሆነ አመልካች  እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡አመልካች ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

 በመሰረቱ አንድ ሰው ግዴታው የሚመነጨው ከውል ወይም ከሕግ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር በንግድ ህግ ቁጥር 657 ወይም በንግድ ህግ ቁጥር 675 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገው የመድን ውል ያለ መሆኑ አንደኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠው እና በሰበር ካደረገው ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች መያዣው አስተማማኝ ዋስትና እንዲኖረው በማሰብ አቶ መኮንን ፀጋው የተባለ ደንበኛው በመያዣነት በተያዘው መኪና ላይ ለሚደርስ ጉዳት የመድን ውል እንዲገቡ ሲያደርግ በመድን ውሉ ፖሊሲው ላይ በተበዳሪውና በአመልካች ስም መፃፉን፣በተለይም መጀመሪያ የተደረገው የመድን ሽፋን ጊዜ ሲያበቃ አመልካች በራሱ ጠያቂነት ለተጠሪ ባቀረበው የእድሳት ጥያቄ ተጠሪ ጥያቄውን ተቀብሎ ውሉን በማድስ ለአንድ አመት እንዲቆይ ከአደረገ በኂላ የመድን አረቦን ክፍያውን ጥያቄ አመልካች ራሱ ወይም ደንበኛውም ለመክፈል የሚችል መሆኑን ለተጠሪ ሲገልፅለት ከቆየ በኃላ የመኪናው ባለንብረትም ሆነ አመልካች ክፍያውን ሊፈጽሙ ያልቻሉ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን ይህንኑ የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ ደግሞ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሙሉ በሙሉ ተቀብሎታል፡፡ይህ ችሎት እነዚህን ፍሬ ነገሮች  ማጣራት ወይም ማስረጃውን መመዘን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡አመልካች የእድሳት ጥያቄውን  ራሱ ማቅረቡና የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለትም ባንኩ ወይም ደንበኛው የሆኑት አቶ መኮንን ፀጋው እንደሚከፍሉ ለተጠሪ ሲገልጽለት የቆየ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ አመልካች ከውል የመነጨ አረቦን የመክፈል ኃላፊነት የለበትም የሚባልበት አግባብ የለም፡፡አመልካች የሰበር መዝገብ ቁጥር 43886 በመጥቀስ በጉዳዩ ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ምክንያቱም

በሰ/መ/ቁጥር 43886 መያዣ ያዥ የሆነው ባንክ ለመድን አረቦን ክፍያ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የተወሰነው የእድሳት ጥያቄው ባንኩ አቅርቦ ካለመሆኑም በላይ መድን ገቢውም ከስር ጀምሮ እስከ ሰበር በተደረገው ክርክር ኃላፊነቱ የራሱ መሆኑን ገልፆ ተከራክሮ ነው፡፡በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን የመኪናው ባለንብረት የሆነው ግለሰብም የክርክሩ ተሳታፊ ያልሆነ ከመሆኑም በላይ  ተጠሪ ወደ ክሱ ያመራውም ግለሰቡን ማስንጠቀቂያ ሰጥቶ ግለሰቡ የእድሳት ጥያቄውን ባለቀረቡበት ሁኔታ የሚጠየቁበት አግባብ የለም በማለት ከገለፁለት በኋላ በመሆኑ በመዝገቡ ያሉት የክርክሩ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች በሰ/መ/ቁጥር 43886 ካሉት የክርክሩ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ጋር የሚገናኙ አይደሉም፡፡ የክርከሩ መሰረታዊ ነጥቦች የተለያዩ ከሆነ ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጠ የሕግ ትርጉም በሌላ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚደረግበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከአስገዳጅ የህግ ትርጉም ፅንሰ ሐሳብና ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ጉዳዩ በሰ/መ/ቁጥር 43886 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ታይቶ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ባለመሆኑ እና አመልካች ከውል የመነጨ ግዴታ ያለበት በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር በገባው የመድን ውል መሠረት ውሉ እስከተሰረዘበት ጊዜ ድረስ ያልከፈለውን የአረቦን ክፍያና ተያያዥ ወጪውን ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት



www.chilot.me

# ቤተሠብ

የሰ/መ/ቁ. 80920

የካቲት 25 ቀን2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ተሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ውድነሽ እሸቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፍቅረማሪያም ወርቁ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ክርክር ሲሆን የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በሻሽመኔ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ ሁለቱም ወላጆች በሞት መለየታቸውን እና በውርስ ንብረቱን ሁለቱ ተከሳሾች ይዘው እንደሚገኙ የሚገልጽ ሆኖ ክርክሩ ከቀረበው ንብረት ውስጥ ድርሻው የሆነውን አንድ ስድስተኛ እንደያስከፍሉ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የነበረው ሰው ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል በመባሉ ከክርክሩ ውጭ የተደረገ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው የአሁኗ አመልካች በበኩሏ ከሳሽ የውርስ ሀብት ናቸው ሲል ከዘረዘሯቸው መካከል ወፍጮ እና ወፍጮው የሚገኝበትን ቤት ሟች እናታችን በህይወት እያሉ በስጦታ አስተላልፈውልኝ የቤቱ ባለቤትነቱም ሆነ የወፍጮው ንግድ ፍቃድ በስሜ ተዛውሮ የሚገኝ በመሆኑ የውርሱ አካል አይደለም ቀሪዎቹን ንብረቶች በተመለከተ ግን እኔም ወራሽ ስለሆንኩኝ እንዲከፋፈለን ቢደረግ ተቃውሞ የለኝም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ ፍ/ቤቱም ከቤቱ ማህደር ጋር ተያይዘዋል የተባሉትን ሰነዶች ከኩየራ ከተማ አስተዳደር አስቀርቦ ከተመለከተ በኃላ ሰነዶች በፍ.ስ.ቁ.2443 እና 881 መሠረት ስጦታ መደረጉን ማስረዳት የማይችሉ በመሆኑ የተከሳሽ ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ከውርስ ንብረቶቹ ውስጥ አንድ ስድስተኛው ለከሳሽ ይሰጥ ሲል ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የምዕራብ አሩሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የይግባኝ ክርክሩን ከሰማ በኃላ ሟች በሂወት እያሉ ለስር 1ኛ ተከሳሽ በስጦታ አስተላልፈው በስሟ የተዛወረው የወፍጮ ቋት እና ቤቱ የውርስ ንብረቱ አካል ነው የተባለው አላግባብ ነው ሲል በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡

የስር ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በተራው ባቀረበው ይግባኝ መነሻ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ክርክሩን ከሰማ በኃላ የወረዳው ፍ/ቤት ለውሳኔው የተሰጠውን ምክንያት በመደገፍና በማጠናከር የከፍተኛውን ሽሮ የወረዳ ፍ/ቤትን ውሳኔ ያፀና ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ውርሱን የሚቀበለው የሟቹ ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ የሆነ ሰው መመለስ የለብህም ተብሎ ከሟቹ ያገኘው ችሎታ ስለሆነ በስተቀር አስቀድሞ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ተሰጥቶት የነበረውን ንብረት መልሶ ከውርሱ ንብረት ጋር መቀላቀል እንዳለበት

በፍ.ሕ.ቁ.1065 እና 1067 (1) እና (2) ተደንግጐ የሚገኝ መሆኑን በተጨማሪ ምክንያትነት በመጥቀስ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ አፅድቋል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረበችው ከከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በስተቀር ቀሪው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን በ 20-10-04 አዘጋጅታ ያቀረበችው አቤቱታ ተመርምሮ ሟች በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ቀድሞውኑ በኑዛዜ ያስተላለፉት ስመ ሀብቱን ያዛወሩት እና በሞቱበት ጊዜ የራሳቸው ያልነበረው ንብረት የሟች የውርስ ንብረት አካል ነው ተብሎ ለወራሾች ይከፋፈል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጣዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ  የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ከስር ጀምሮ በአንድ በኩል የወፍጮውን ቋት እና ወፍጮው የተቋቋመበትን ቤት ሟች በሕይወት እያሉ በስጦታ ያስተላለፈልኝና በስሜ ተዛውሮ የሚገኝ በመሆኑ የውርስ አካል ተደርገው ሊወሰድ አይገባም በማለት ስትከራከር መቆየቷ እና በሌላ በኩል ደግሞ በስጦታ ተላልፎልኛል ከምትለው ንብረት ውጪ ያለውን ውርስ እንደ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ለመካፈል ዝግጅ ወይም ፍቃደኛ መሆኗ እንዲሁም በስጦታ ተላልፎልኛል የምትለውን ንብረት ወደ ውርሱ መልሶ ከማግባት በሟች ነፃ ተደርጌአለሁ በሚል ያቀረባቸው ክርክርና ማስረጃ አለመኖሩ በስር የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጠዋል፡፡ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እነዚህን የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና በክርክር ለተረጋገጠው ፍሬ ነገር አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመለየት አመልካች በስጦታ የተላለፈላትን ንብረት መልሳ በውርሱ ውስጥ ማግባት እንዳለባት የሰጠው ውሳኔ በመሰረቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ይሁን እንጅ ሰበር ችሎቱ የዚህ አይነቱ ንብረት ወደ  ውርሱ መልሶ እንዲገባ የሚደረግበትን ስርዓት ጭምር በውሳኔው ውስጥ በግልጽ ሳያሰፍር የቀረው በአግባቡ መሆኑ  አለመሆኑ ሊጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቶአል በዚሁም መሠረት የጋራ ወራሾች ስለሚመለሱት ንብረት እና መመለሱ ስለሚፈፀምበት ስርዓት ተደንግጐ የሚገኘው በፍ/ሕጉ አንቀጽ 5 በምዕራፍ 3 በክፍል 2 ቁጥር 1065 እስከ 1078 ድረስ ሲሆን ከሟች በስጦታ ወይም በኑዛዜ  የተሰጠውን ንብረት ወደ ውርስ መለሶ የማግባት ግዴታ ያለበት ወደታች የሚቆጠር የሟች ተወላጅ ከውርሱ መልሶ ማግባት ያለበት ንብረቱን ራሱን ሳይሆን የንብረቱን ዋጋ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ.1065 እና 1074 (1) በግልጽ ተደንግጋል የንብረቱ የዋጋ ግምት የሚታወቅበት ስርዓትም በቁጥር 1077 ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ንብረቱን መልሶ ወደ ውርስ በማግባት ስርዓት መፈፀም የሚገባው ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተከትሎ መሆኑን በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈር ሲገባው አላስፈለጊ የሆነ ተጨማሪ ሙግት በሚጋብዝ አኳኃን አመልካች በስጦታ የወሰደችውን ንብረት መልሳ ከውርስ ጋር መቀላቀል አለባት በማለት በደፈናው የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሻሸመኔ ወረዳ ችሎት በመ.ቁ.29205 በ19/09/2003 ዓ.ም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.119303 በ24/04/2004ዓ.ም እና የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ.135371 በ04/10/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ.348 (1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ወደ ውርሱ መልሳ ማስገባት ያለባት ንብረቱን እራሱን ሳይሆን የዋጋ ግምቱን ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የንብረቱ ግምት ጉዳዩ ከላይ በተጠቀሰው የፍ.ሕ.ቁ.1077 መሠረት በሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.36929 በተያዘው የአፈፃፀም ክርክር ታይቶ የሚወሰን ይሆናል በማለት ወስነናል፡፡
4. የሰበር ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ፡፡
5. የአፈፃፀም ዕግድ ተነስቷል፡፡
6. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
7. ውሳኔ ያገኙ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ



www.chilot.me

የሰ/መ/ ቁጥር 82585

የካቲት 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካቾች**፡-1. ወ/ሮ ሱዛን ሞንታልባን
2. ወ/ሮ ለይላ አሊ
3. ወ/ሪት ሜሪያም አሊ
ስለ ሶስቱም ጠበቃ ያለለት ተሾመ ቀረቡ

**ተጠሪዎቹ**፡- 1. አቶ ሙራድ አሊ
2. ዶ/ር ሰሚር አሊ
ስለ ሁለቱም ጠበቃ ሙሉጌታ ገበሩ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ኑዛዜን የማስፈረስ ክስ ወይም አቤቱታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የሚገባበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኖቹ አመልካቾች ሟች አቶ አሊ አህመድ ታህሳስ 4 ቀን 2001ዓ.ም አደረጉት የተባለውን ኑዛዜ ለአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው ውሣኔ በማስጠት የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ከወሰዱ በኋላ የአሁኖቹ ተጠሪዎች የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሆነን እያለ በኑዛዜው የተደረገው ድልድል መብታችንን የሚነካ በመሆኑ ኑዛዜው ሊሻር ይገባል በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 358 መሰረት መቃወሚያ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመ/አመልካቾቹ ኑዛዜው ሲነበብ ያልነበሩ እና ወኪልም ያልነበራቸዉ ቢሆንም ኑዛዜ መኖሩን ስለኑዛዜው ስልጣን በተሰጣቸው 3ኛ በመ/ተጠሪ እንዲያውቁ የተደረገ እና በክፍፍሉ ረገድም ሀሳባቸውን ሲሰጡ የነበሩ ስለመሆኑ የመ/ተጠሪዎች ካቀረቧቸው የሰነድ ማስረጃ መገንዘብ ስለተቻለ እና ስለድልድሉ ከ3ኛ የመ/ተጠሪ ከሰሙበት ጊዜ ጀምሮ አቤቱታቸውን በ15 ቀን ውስጥ ስላላቀረቡ አቤቱታቸው በፍ/ሕ/ቁ 973 እና 974 መሰረት በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት በብይን አሰናብቶአቸዋል፡፡

ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር የመ/ተጠሪዎች ውርስ አጣሪው በአግባቡ ተሰይሞ ስለውርስ ክፍፍልም ሆነ ድልድል ለስር የመ/አመልካቾች የገለፀላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዳላቀረቡ ከስር የመ/አመልካቾቹ ጋር ሲጻጻፍበት ነበር የተባለውም ማስረጃ የመ/አመልካቾች ኑዛዜ ስለመኖሩ ያውቁ ነበር የሚለውን ከሚያስረዳ በስተቀር አሁንም ስለውርስ ክፍፍልና ድልድል የሚገልፀው ነገር እንደሌለ በዚህም ምክንያት አቤቱታው በፍ/ሕ/ቁ 973/1/ መሰረት በይርጋ ይታገዳል የተባለው በአግባቡ እንዳልሆነ በዝርዝር ገልጾ ብይኑን በመሻር የውርስ ክፍፍልን አስመልክቶ በኑዛዜው ላይ የቀረበውን ክርክር መርምሮ ውሣኔ ይሰጥበት

ዘንድ ጉዳዩን ወደስር ፍ/ቤት የመለሰው ሲሆን የአሁኖቹ አመልካቾች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት ያቀረቡለትን አቤቱታ ዘግቶ በማሰናበቱ ነው፡፡

አመልካቾቹ በ17/12/04ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር የተለዋወጡ ሲሆን እኛም የይ/ሰሚው ችሎት ውሣኔ እና የሰበር ችሎቱ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ኑዛዜ ፈራሽ ነው በሚል ስለሚቀርብ መግለጫ እና ክስ እንዲሁም መግለጫው እና ክሱ ሊቀርብ ስለሚገባበት የጊዜ ገደብ በፍ/ሕ/ቁ 973 እና 974 ተደንግጐ ይገኛል፡፡ ቁጥር 973 ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ኑዛዜው ሲነበብ በነበሩ ወይም በተወከሉ ሰዎች ጉዳይ ሲሆን ቁጥር 974 ድንጋጌ ደግሞ በኑዛዜው ስነስርዓት ባልነበሩ ወይም ባልተወከሉ ሰዎች ጉዳይ ነው፡፡ የፍ/ሕ/ቁ 973 እና 974 ድንጋጌዎች አቤቱታ አቅራቢው ኑዛዜው ሲነበብ የነበረ ወይም የተወከለ የመሆን አለመሆኑን መስፈርት መሰረት በማድረግ ይርጋው መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ እና ፍጹም የሆነ የይርጋ ጊዜ /974 ንዑስ ቁጥር 2/ በተለየ ሁኔታ ከመደንገጋቸው በስተቀር ሁለቱም ድንጋጌዎች ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል ክስ የሚቀርብበትን ስርዓት የሚደነግጉ በመሆናቸዉ በመሰረቱ ተያይዥነት አላቸው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነበብ ያልነበሩ ወይም ያልተወከሉ መሆኑ አላከራከረም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ቢያንስ ሁለቱንም ድንጋጌዎች አጣምሮ መጥቀስ ሲገባው በውሣኔው ውስጥ ቁጥር 973 ድንጋጌን ብቻ ነጥሎ መጥቀሱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህ አንጻር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ቁጥር 973 ድንጋጌ በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ የተሳሳተ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ከድንጋጌው አጠቃቀስ አንጻር ብቻ ተገቢነት ያለው ቢሆንም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ ተመርምሮ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ አቋም የሚወሰድበት ከድንጋጌው አጠቃቀስ አንጻር ብቻ ሳይሆን በሙሉ ይዘቱና መንፈስ ነው፡፡

ዋናውን ፍሬ ጉዳይ በተመለከተ ተጠሪዎቹ ኑዛዜውን ያውቁ የነበረ መሆኑን ይ/ሰሚው ፍ/ቤት አረጋግጦ እያለ እና አጣሪውም በኑዛዜው ከተመለከተው ውጪ የሚያቋቁመው የተለየ የንብረት ድልድል በማይኖርበት ሁኔታ ተጠሪዎቹ ስለንብረት ድልድሉ እንዲያውቁ መደረጉን አመልካቾች አላስረዱም ሲል ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የተሳሳተ ነው በማለት አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ተከራክረዋል፡፡ በመሰረቱ ኑዛዜ መኖሩን ማወቅ እና የኑዛዜውን ሙሉ ይዘት ማወቅ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ተጠሪዎቹ የኑዛዜውን ቅጂ እንዲያገኙ ተደርጕአል የሚል ክርክር አመልካቾቹ በስር ፍ/ቤቶችም ሆነ በሰበር ደረጃ አላቀረቡም፡፡ አመልካቾቹ ያቀረቡት ማስረጃ የኑዛዜውን መኖር እንጂ በኑዛዜው የተደረገውን የንብረት ድልድል ተጠሪዎች እንዲያውቁት መደረጉን የሚያስረዳ አይደለም በማለት ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጠው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በማስረጃ ምዘና ረገድ የሰጠውን ውሣኔ አግባብነት መመርመር ደግሞ በዚህ ሰበር ችሎት የስልጣን ወሰን ውስጥ የሚካተት አይደለም፡፡

በመጨረሻም ተጠሪዎቹ በኑዛዜው የተደረገውን የሀብት ድልድል ያወቁት በ13/03/04 ዓ.ም መሆኑን በሰበር መልሳቸው ያመኑ በመሆኑ እና የመቃወም አቤቱታቸውን ያቀረቡት ግን 15 ቀናት ካለፋ በኋላ በ03/05/04 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ውድቅ መደረግ ነበረበት በማለት አመልካቾች በመ/መልሳቸው ተከራክረዋል፡፡ በመሰረቱ በፍ/ሕ/ቁ 973/1/ የተመለከተው የ15 ቀን የጊዜ ገደብ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ሳይሆን የመግለጫ ማቅረቢያ ጊዜ ነው፡፡ በኑዛዜው የተሰየሙ አጣሪ ናቸው የተባሉት የአሁኗ 3ኛ አመልካች ስለንብረት ድልድሉ ለአሁኖቹ ተጠሪዎች ያሳወቁት ነገር አለመኖሩን ይ/ሰሚው ፍ/ቤት አረጋግጦአል፡፡ ተጠሪዎቹ የንብረት ድልድሉን

እንዲያውቁ አልተደረገም ከተባለ ደግሞ መግለጫ የማቅረብ ግዴታ አይኖርባቸውም፡፡ የዚህ ዓይነቱ ግዴታ ከሌለባቸው ደግሞ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ተጠሪዎቹ በኑዛዜው የተደረገውን የንብረት ድልድል ማወቃቸውን ከገለጹበት ከ13/03/04ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ በ03/05/04 ዓ.ም ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ በፍ/ሕ/ቁ 973/3/ በተመለከተው አነስተኛው የሶስት ወር የይርጋ ዘመን እንኳ የይርጋ ጊዜው ያለፈበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቶአል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአ/አበባ ከተማ ይ/ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 17753 በ17/09/04 ከሰጠው ውሣኔ ውስጥ ይርጋን የሚመለከተው የውሣኔው ክፍል እና የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በመ/ቁ 18053 በ06/11/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. በአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 1944/03/ የተያዘው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡
4. የውሣኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
5. ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

የሰ/መ/ቁ 89641

ጥቅምት 21 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ ሐረገወይን ብርሃኑ

2. አቶ ፀጋዬ ከድር የህጻን ቤቤቶ ፀጋዬ እና የህጻን ናትናኤል ፀጋዬ ሞግዚት

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ አዜብ ብርሃኑ

2.አቶ እስክንድር ኮከቤ

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር አመልካቾች የክስ አቤቱታ አቅራቢነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካቾች የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም አሻሽለው በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ አመልካቾችና 1ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ብርሃኑ ገ/ማሪያም እና የወ/ሮ ፀዳለ በዳዳ ወራሾች መሆናችን በድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የወራሽነት ማስረጃ ወስደን የውርስ ንብረቶች ተጣርተው ሪፖርቱም ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ የጸደቀ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ቀደም ሲል እውነተኛ ወራሽና ተወላጅ ሳይሆኑ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ከህግ ውጪ አሳስተው የወሰዱ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰረዘ በመሆኑ በተሰረዘ ወራሽነት ማስረጃ ከሟቾች ወራሾች ጋር የውርስ ሀብት ሊከፋፈሉ ስለማይገባ የውርስ ሀብቶችን ከወራሾች ጋር እንዲከፋፈሉ የተሰጠው ትዕዛዝ ይሰረዝልን ብለዋል፡፡

ተጠሪዎችም በሰጡት መልስ፡- አመልካቾች 1ኛ ተጠሪ የሟቾች ልጅ መሆኗን አምነው የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸውም ሆነ የውርስ ሀብቶች እንዲከፋፈሉ ለፍርድ ቤት ሲያመለክቱ ቆይተው የሟቾች ልጅ እና ወራሽ አይደለችም በሚል ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6(1)(ሀ)የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ስለማያሟላ ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በሰጠው ብይን፡- አመልካቾችና 1ኛ ተጠሪ የሟች ብርሃኑ ገ/ማሪያም እና ወ/ሮ ጸዳለ በዳዳ ልጆች ስለመሆናቸው አንድ ላይ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ የውርስ ንብረቶች ተጣርተው የአጣሪው ሪፖርት ቀርቦ ስለትክክለኛነቱ ወራሾቹ በሰጡት አስተያየት በመስማማታቸው ከጸደቀና የፍርድ ቤቱ የውሳኔ አካል ሆኖ እንዲፈጸም ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 ስር ከተደነገጉት ሁኔታዎች ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡



www.chilot.me

አመልካቾችም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከራቸው በኋላ በሰጠው ፍርድ፡- ይግባኝ ባዮች ቀርቦ የነበረውን ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ/91 መሰረት በማሻሻል በ12/08/2004 ዓ/ም የተጻፈ የክስ አቤቱታ ቢያቀርቡም የክስ አቤቱታቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያመላክትም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ አቤቱታቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ሳይፈቅድላቸው ያቀረቡት የክስ አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ/91 ስለአቤቱታ አቀራረብ ከተደነገገው ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣በሌላ በኩል ይግባኝ ባዮች በ25/04/2004 ዓ/ም እና በ12/06/2004 ዓ/ም ያቀረቡኣቸው አቤቱታዎች ጥቅምት 09/2004 ዓ/ም የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲሻሻልላቸው የጠየቁባቸው ቢሆንም አቤቱታዎቹ በመዝገቡ ላይ የመጨረሻ ውሳኔና ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከተዘጋ በኋላ የቀረቡ በመሆናቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ/6 አንጻር የሚታዩ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በዚሁ የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር መሰረት በማየት ውደቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ሲል አጽንቷል፡፡

አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በሥር ፍርድ ቤቶች ብይን/ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የቅሬታ ነጥቡም ሲጠቃለል፡-አመልካቾች በህጉ አግባብ ተገቢውን የዳኝነት ክፍያ ከፍለን በ12/06/2004 ዓ/ም ባቀረብነው ቀጥታ የክስ አቤቱታ ተጠሪዎች በተሰረዘ የወራሽነት ማስረጃ መሰረት የያዙትን የውርስ ንብረቶች እንዲመልሱ እንዲወሰንልን ዳኝነት ጠይቀን ሳለ ፍርድ ቤቶቹም የክሱን አርዕስት፣ተከራካሪ ወገኖችንና የክሱን ማስረጃ ዝርዝር እንዲሁም በክሱ አቤቱታ የተጠየቀውን ዳኝነት በማየት በፍ/ሀ/ቁ/ 999 መሰረት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው ጉዳዩ እንደገና ዳኝነት እንዲታይ በሚል እንደቀረበ በመቁጠር የክስ አቤቱታችንን በፍ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ/6 መሰረት መርምረው ውድቅ ያደረጉት ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- ጉዳዩ እልባት አግኝቶ በተዘጋ መዝገብ ላይ የፍ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ/ 91(1)ን በመጠቅስ አመልካቾች የውርስ ሀብቱ ይመለስልን ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ/ 6(1) መሰረት በመመርመር ውድቅ ያደረጉት ህግን መሰረት ያደረገ ነው፣አመልካቾች ያቀረብነው አቤቱታ ሊታይ የሚገባው በፍ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ/6(1) ሳይሆን በፍ/ሀ/ቁ/999 መሰረት ነው ቢሉም በፍ/ሀ/ቁ/999 መሰረት የሚቀርብ ጉዳይ አዲስ ክስ ቀርቦ አዲስ ዳኝነት የሚሰጥበት እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት መዝገብ ተንቀሳቅሶና በፍ/ሥ/ሥ/ሀ ቁ 91 መሰረት የክስ አቤቱታ ተሻሽሎ የሚወሰን ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾችም ለተጠሪዎች መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-አመልካቾች ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካቾችና 1ኛ ተጠሪ የሁለቱም ሟቾች ወራሾች ስለመሆናቸው እንዲወሰንላቸው በጋራ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ወራሽነታቸው በፍርድ ቤት ተረጋግጦ መወሰኑንና የሟቾች የውርስ ሀብቶች እንዲጣሩ ተደርጎ ተጣርተው ከቀረቡ በኋላ የአጣሪው ሪፖርት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ ስለመጽደቁና ክፍፍሉም እንዲፈጸም ታዞ መዝገቡ ጥቅምት 09 ቀን 2004 ዓ/ም መዘጋቱን የስር ፍርድ ቤቶች በውሳኔያቸው ካሰፈሩት መገንዘብ ተችሏል፡፡

አመልካቾችም መዝገቡ ከተዘጋ በኂላ በታህሳስ ወር 2004 ዓ/ም ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጻፉት አቤቱታ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጣቸው የወራሽነት ማስረጃ የተሰረዘ በመሆኑ ተጠሪዋ ከውርስ ሀብቱ ¼ኛ እንዲካፈሉ የተሰጠው ትዕዛዝ ተሽሮ ለአመልካቾች እንዲደርሳቸው በተወሰነው የውርስ ሀብት ድርሻ ላይ እንዲጨመርላቸው ጠይቀው የተጠሪዋን መልስ ፍርድ ቤቱ ከተቀበለ በኂላ መዝገቡ ለምርመራ ተቀጥሮ ባለበት አሁን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የክሱን አርዕስት በፍ/ህ/ቁ/999 መሰረት የአመልካቾችን የውርስ ድርሻ ለማስለቀቅ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/91 መሰረት ተሻሽሎ የቀረበ የክስ አቤቱታ የሚል አቅርበዋል፡፡ ይህን ተሻሽሎ ቀረበ የተባለውን የክስ አቤቱታ ፍርድ ቤቶቹ የመረመሩት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6(1) መሰረት መሆኑንም ከውሳኔያቸው መገንዘብ ችለናል፡፡

የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 ተከራካሪ ወገኖች አቤቱታቸውን ወይም የመከላከያ መልሳቸውን ሊያሻሽሉ ወይም ሊለውጡ ስለሚችሉበት አግባብ የሚደነግግ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር 1 እንደተመለከተው አቤቱታ ወይም ክርክር ለመሻሻል ወይም ለመለወጥ የሚቻለው በተካራከሪ ወገኖች ጥያቄ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ሲያዝ ሲሆን ተከራካሪ ወገኖቹም አቤቱታቸውን ወይም ክርክራቸውን አሻሽለው ወይም ለውጠው ሊያቀርቡ የሚችሉት የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን በይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ይረዳል ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲገምት ብቻ ነው፡፡ አቤቱታውን ለማሻሻል ወይም ክርክሩን ለመለወጥ የሚቻለውም በጉዳዩ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ስለመሆኑ በዚሁ በንዑስ ቁጥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካቾች አቤቱታቸውን አሻሽለው ለማቅረብ እንዳልተፈቀደላቸው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍርድ የሚያመላክት ከመሆኑም ሌላ አቤቱታቸውን ያቀረቡትም በጉዳዩ ላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥቅምት 09 ቀን 2004 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቶ መዝገቡ ከተዘጋ በኂላ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ አቤቱታው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 መሰረት የሚስተናገድ አይሆንም፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ይህን አቤቱታ የመረመሩትም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 መሰረት ሲሆን ድንጋጌው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆን አለመሆኑን መመርመር ይገባል፡፡

በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 (1)(ሀ) መሰረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረው የመጨረሻው ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሰነድ ወይም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት በማድረግ ሲሆን አቤት ባዩም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጎ ለማወቅ አለመቻሉን ማስረዳት የሚጠበቅበት ከመሆኑም በላይ በፊደል (ለ) እንደተጠቀሰውም እነዚህ የተዘረዘሩት ተግባሮች መፈጸማቸው ቢገለጽ ኖሮ ለተሰጠው ፍርድ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር አቤት ባዩ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች በክስ አቤቱታቸው የገለጹት 1ኛ ተጠሪ እውነተኛ ወራሽ ሳይሆኑ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰረዘባቸው በመሆኑ የተቀበሉትን የውርስ ሀብት ድርሻ ለአመልካቾች እንዲለቁ በፍ/ህ/ቁ/999 መሰረት ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ ከዚህ የክስ አቤቱታው ይዘትም መረዳት የሚቻለው አቤቱታው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6(1)(ሀ) እና (ለ) የተመለከቱትን ሁኔታዎች አለመያዙንና በውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት መቅረቡን ነው፡፡ በፍ/ህ/ቁ 996 (1) ወራሽ የሆነ ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑንና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመላክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፍርድ ቤት ማመልከት የሚችል

ሲሆን የተሰጠው የወራሽነት ምስክር ወረቀትም በፍ/ህ/ቁ/998(1) በተመለከተው ሁኔታ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በፍ/ህ/ቁ/999 በተደነገገው መሰረት አንድ ሰው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ ያደረገ እንደሆነ እውነተኛው ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት የወራሽነት ጥያቄ ክስ ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ የአመልካቾች አቤቱታም 1ኛ ተጠሪ እርግጠኛ ወራሽ ሳይሆኑ የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ የውርስ ሀብት ድርሻ ስለያዙ እንዲመልሱ ይወሰንልን የሚል እስከሆነ ድረስ የዳኝነት ክፍያ በታሪፉ መሰረት ከፍለው በፍ/ህ/ቁ/999 እንደተጠቀሰው አዲስ ክስ ከሚያቀርቡ በስተቀር የውርስ ሀብት ተጣርቶ ክፍፍሉ እንዲፈጸም ተወስኖ የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ እንዲከራከሩ የሚፈቅድ የፍ/ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌ የለም፡፡

በመሆኑም አመልካቾች የውርስ አጣሪ ሪፖርት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከጸደቀና የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ታዞ ድርሻቸውን ወስደው መዝገቡ ከተዘጋ በኂላ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 መሰረት ቀደም ሲል የቀረበውን የክስ አቤቱታ አሻሽለን አቅርበናል በማለት የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም ያቀረቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤቶቹ ተቀብለው በማከራከር አቤቱታውን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 6 መሰረት መመርመራቸው የፍ/ሥነ ሥርዓት ህግን የተከተለ ባለመሆኑ ምክንያቱን ለውጠን በውጤት ደረጃ ግን የክስ አቤቱታውን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 38608 በቀን 12/08/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ብይን/ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 07907 በቀን 03/08/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ ምክንያቱን ለውጠን በውጤት ደረጃ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. የአመልካቾች አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 6 መሰረትም ሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 መሰረት ሊስተናገድ የሚገባ አይደለም፡፡ ይህ ውሳኔ አመልካቾች ተገቢውን የዳኝነት ክፍያ ከፍለው አግባብነት ባላቸው የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት መብታቸውን በሚጠይቁት ወገን ላይ የሚያቀርቡትን ቀጥታ ክስ የሚያግድ አይሆንም፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ.መ/ቁ. 93779

ታህሳስ 30 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ጂአቶ ያሲን ሺበሺ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ሐሰን መሐመድ - በሌሉበት የሚታይ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጋብቻ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፋንቲ ረሱ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ነው፡፤ ፍርድ ቤቱ ለአሁኗ ለአመልካች በቁጥር ፋ/ሸ/577/05 በቀን 21/06/2005 በአድራሻቸው በፃፈው ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የተፋቱ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረቡም፣ከአቶ አደም አንባዬ ጋር ተጋባሁ ስለሚሉት ጋብቻ ያቀረቡት ማስረጃ የማጭበርበሪያ ወረቀት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት አመልካቿ የተጠሪው ሚስት እንጂ የአቶ አደም አንባዬ ሚስት አይደሉም ሲል መወሰኑን አረጋግጧል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታም መሰረታዊ ይዘትም በያሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ከተጠሪ ጋር በነበራቸው የጋብቻ ይፍረስልኝ ክርክር የወረዳው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ/ቁጥር 14/2003 በቀን 04/06/2003 በሰጠው ውሳኔ ጋብቻው መፍረሱን አረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ በሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲታይ መደረጉ ስነ ስርዓቱን የተከተለ አይደለም፣በአገሪቱ ሕገ መንግስት የተረጋገጠውን ጋብቻን በፈቃደኝነት የመመስረት መብትም የጣሰና የእኩልነት መብትን ያላስከበረ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታቸው ተመርምሮም የግራ ቀኙ ጋብቻ በመደበኛ ፍርድ ቤት በክልሉ ከፈረሰ በኋላ የክልሉ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ዳግም የማስተናገዳቸውን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡



www.chilot.me

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር  በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ጉዳዩን በያሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍቺ ጉዳይ ተከራክረው በመካከላቸው ያለው ጋብቻ የፈረሰ መሆኑ በመ/ቁጥር 14/2003 በቀን 04/06/2003 ከተወሰነ በኃላ የጋብቻው ጉዳይ ተመልሶ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የታዬና አመልካች ያለፍላጎታቸው ከተጠሪ ጋር በጋብቻ እንዲቀጥሉ ተብሎ የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34(1) ስለ ተጋቢዎች በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን በአንቀጽ 35(2) ድንጋጌም ሴቶች በሕገ መንግስቱ በተደነገገው መሰረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ሕገ መንግስቱ በሕግ በተለይ በሚዘረዝረው መሰረት በሐይማኖት፣ በባህል የሕግ ስርአቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ እንደሚችል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 34(4) ከማስቀመጡም በላይ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር አምስት ድንጋጌ ስር ሕገ መንግስቱ የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሀይማኖታቸው ወይም በባህሎቻቸው ሕጎች መሰረት መዳኘትን እንደማይከለክል፣ዝርዝሩም በሕግ እንደሚወሰን አስቀምጧል፡፡ በዚህም አግባብ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 188/1992 የተቋቋሙ ሲሆን በቤተሰብ ጉዳይ ላይ ያላቸው የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ተለይቶ ተቀምጦላቸዋል፡፡ አሁን የተያዘው ጉዳይም በሕገ መንግስቱና በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሰረት ለሸሪዓ ፍ/ቤቶች በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንዲታይ በተጠሪ በኩል የቀረበ ሲሆን አመልካች ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሰረት በተዘረጋው ስርዓት እንዲታይ ፈቃድ የሰጡ ስለመሆኑም የክርክሩ ሂደት የማያሳይ ቢሆንም አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በመደበኛ ፍርድ ቤት ከፈረሰ በኂላ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚታይበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት ጉዳዩ ሊታይ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 5(4) እና 6(2) በተደነገገው መሰረት የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ሲመሩ የፈፀሙት የስነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት ካለ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ሐይማኖትን መሰረት በማድረግ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ይህ ችሎት የመመርመር ስልጣን የለውም፡፡ከዚህ አንጻር የሸሪዓ ፍርድ ቤት አመልካች ያለፍላጎታቸው ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ሊቀጥሉ ይገባል በማለት የደረሰው ድምዳሜ በዚህ ችሎት የሚታይበት አግባብ የሌለ በመሆኑ አመልካች በሕገ መንግስቱ የተከበረላቸውን በፍላጎት ጋብቻ የመመስረት መብት መሰረት አድርገው የሚያቀርቡትን ክርክር አልፈነዋል፡፡

አመልካች በተያዘው ጉዳይ ተፈፀመ የሚሉት የስነ ስርዓት ሕግ ግድፈት በመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ የፍቺ ውሳኔ እያለ ዳግም በሸሪዓ መታየቱ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ በክልሉ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ስልጣን በፌዴራል በአዋጅ ቁጥር 188/1992 ከተዘረጋው የተለየ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ያልቀረበ ሲሆን በተጠቃሹ የፌዴራሉ አዋጅ አንቀጽ 4 ስር የተመለከተ ሲሆን አዋጁ ፍርድ ቤቶቹ ስለሚሰሩባቸው ሕጎችም በአንቀጽ 6 ስር ደንግጓል፡፡በዚህ አንቀፅ ስር ከተመለከቱት ሕጎች መካከል ስራ ላይ ያለውና በ1958 ዓ/ም የወጣው የፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ አንዱ ስለመሆኑ የተጠቃሹ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህ

አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም የፍትሐ ብሔር ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ እንዲኖረው በማሰብ ከተደነገጉ በ1958 ዓ/ም በወጣው የስነ ስርዓቱ ድንጋጌዎች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ እልባት ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍኑ መሆናቸውንና እንዲህ አይነት እልባት አግኝተዋል የሚባሉት ጉዳዮች ደግሞ በፍርድ፣ በብይን፣ በውሣኔ፣ በትእዛዝ፣ ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ መንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ አጠቃልሎ የያዘ መሆኑንና መሰረታዊ አላማውም ክርክር አንድ ቦታ ላይ እንዲቆም ታስቦ በሕግ የተዘረጋ ስርዓት የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካላባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ሕጉ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ስለመሆኑም ያስገነዝስባል፡፡ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ለይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው ፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 (1) እና (2) ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2(ለ)) እና 245(2) ድንጋጌ ጋር ተጣምረው ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ሲታይ በቀዳሚው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑ የተከራካሪ ወገኖች አንድነት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ከላይ የተመለከቱት መመዘኛዎች በተሟሉበት ሁኔታ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት በመሆኑ ድጋሚ ክስ የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይህ ድንጋጌ ጉዳዮችን በአግባቡ ለመመራትና ተከራካሪ ወገኖች ለአላስፈላጊ ወጪና እንግልት እንዳይዳረጉ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑም ይታመናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በያሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ከተጠሪ ጋር በነባራቸው የጋብቻ ይፍረስልኝ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ በ1952ቱ የፍትሃ ብሔር ሕግ ስለቤተሰብ በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ ጉዳዩን በመመራት ጋብቻው መፍረሱን መወሰኑን በመ/ቁጥር 14/2003 በቀን 04/06/2003 የተሰጠው ውሳኔ ያሳያል፡፡ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ የሚያውቁት መሆኑን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ተጠሪ ጉዳዩን ወደ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመውሰድ አሁን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ይኸ የተጠሪ የክርክር ስልት በአገሪቱ ሰዎች በፈቃዳቸው በሀይማኖት ወይም በባህል ህግ መሠረት የመዳኘት መብት እንዳላቸው በህገ

መንግስቱ አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 የተረጋገጠውን መብት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሞከሩ መሆናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ተጠሪ በያሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ ታይቶ እልባት ያገኘውን የፍቺ ጉዳይ ከውሳኔ በኋላ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ያቀረቡት ጥያቄ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 34(5)፣የአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6(2) እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(1) የሚጥስ ነው፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የፋንቲ ረሱ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የአፋር ክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪ ሚስት ናቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የስነ ስርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፋንቲ ረሱ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በቁጥር ፋ/ሸ/577/05 በቀን 21/06/2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በአፋር ክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00012/05 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ጋብቻ በያሎ ወረዳ መደበኛ ፍርድ ቤት የፈረሰና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(1) አግባብ ፍርድ የተቋጨ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6(2) መሰረት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳግም የሚዳኝበት ስነ ስርዓት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ አመልካቾ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

***መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 95995

የካቲት 10 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ወ/ት ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአባት ስም ይስተካከልልኝ ጥያቄን የሚመለት ሲሆን የተጀመረውም አመልካች ከአሁን ቀደም በወላጅ አባታቸው ስም ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ተብለው እና በአሳዳጊ አባታቸው ስም ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው በሁለት የአባት ስም ይጠሩ እንደነበረ እና አሁን ግን በትክክለኛው አባታቸው ስም መጠራት እንደፈለጉ በመግለጽ ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው መጠራታቸው ቀርቶ ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ብቻ ተብለው እንዲጠሩ ይወሰንላቸው ዘንድ በመጠየቅ ለአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ነው፡፡ፍ/ቤቱም አቤቱታውን እና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካች አሁንም ቢሆን ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ተብለው የሚጠሩ መሆኑን ከሰነድ ማስረጃዎቹ መገንዘብ መቻሉን ገልጾ አመልካች እየተጠሩበት ባለው የአባት ስም እንድጠራ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም በማለት መዝገቡን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 231(1)(ሀ) መሰረት በብይን ዘግቶአል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡትም ለከተማው የበላይ ፍ/ቤቶች ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በሁለት የአባት ስሞች እንደሚጠሩ በሰነድ ማስረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ ያቀረቡት የአባት ስም ይስተካከልልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የአመልካች ክርክር ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን የክስ አቤቱታ ተቀብለው ክርክሩን መስማት ከመጀመራቸው በፊት በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ጉዳይ የሚያስከስስ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚገባቸው መሆኑ እና በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ጉዳይ የማያስከስስ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የክስ አቤቱታው ተቀባይነት እንደሌለው ገልጸው

መመለስ የሚገባቸው መሆኑ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 231(1)(ሀ) ስር ተደንግጎ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነው፡፡ይሁን እንጂ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጉዳዩ የሚያስከስስ አይደለም ተብሎ ተቀባይነት ከማጣቱ በፊት በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ጉዳይ በርግጥም የማያስከስስ መሆኑ በአግባቡ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው የአመልካቿ የዳኝነት ጥያቄ ከአሁን ቀደም በወላጅ አባታቸው ስም ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ተብለው እና በአሳዳጊ አባታቸው ስም ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው በሁለት የአባት ስም ይጠሩ እንደነበረ እና አሁን ግን በትክክለኛው አባታቸው ስም መጠራት እንደፈለጉ በመግለጽ ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው መጠራታቸው ቀርቶ ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ብቻ ተብለው እንዲጠሩ እንዲወሰንላቸው ሲሆን ይጠሩበት በነበሩት ሁለቱም የአባት ስሞች የተዘጋጁ ወይም ከመንግስታዊ ተቋማት የተሰጡ ሰነዶችንም በማስረጃነት ማቅረባቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ እያንዳንዱ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞች እና የአባት ስም እንደሚኖረው፣እንዲሁም ለልጁ የአባት ስም የሚሆነው የአባቱ የግል ስም እንደሆነ በፍ.ሕ.ቁ.32(1) እና 36(1) ድንጋጌዎች ተመልክቶአል፡፡አንድ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች በአባቱ ብቻ ሳይሆን በአሳዳጊው ስም ጭምር ሊጠራ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው የሚታወቅ ሲሆን እንዲህ ዓይነቱ ሰው ተገቢ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በአሳዳጊው ስም ጭምር መጠራቱ ቀሪ ሆኖ ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ መሰረት በአባቱ ስም ብቻ እንዲጠራ የመወሰን መብት ያለው በመሆኑ ይህንኑ መብቱን በፍርድ ለማረጋገጥ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡አመልካች ክሱን ያቀረቡት በሚጠሩበት የአሳዳጊያቸው ስም የተሰጡ ሰነዶችን ወደሚጠሩበት አባታቸው ስም በሕግ አግባብ ለማስቀየር እና እነዚሁ ሰነዶች በሚሰጡት መብት ለመገልገል ጭምር መሆኑን ከክርክራቸው ይዘት መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው መጠራታቸው ቀርቶ ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ብቻ ተብለው እንዲጠሩ ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ሊሰጥ የሚችለው ውሳኔ በአመልካቿ መብት ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አይኖርም ሊባል የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል ክሱ የቀረበለት የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበለትን የክስ ማመልከቻ እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት የሚገባው ሆኖ እያለ በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ጉዳይ የሚያስከስስ አይደለም በማለት ሲል የሰጠው እና በከተማው የበላይ ፍ/ቤቶች በትዕዛዝ የፀናው ብይን የክስ ማመልከቻውን እና የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 231(1)(ሀ) ድንጋጌን ይዘትና ዓላማ በአግባቡ ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ የክስ ምክንያት የለውም ሲል መዝገቡን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 231(1)(ሀ) መሰረት በመዝጋት የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 2908 በ07/12/2005 ዓ.ም. የሰጠው እና በከተማው ፍ/ቤቶች ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ እና በመ.ቁ. 20742 በ27/12/2005 ዓ.ም.እና በመ.ቁ.21123 በ27/02/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1)መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ላይ የተገለጸው ጉዳይ የክስ ምክንያት ያለው መሆኑን ተገንዝቦ ጉዳዩን በማንቀሳቀስ የቀረበለትን የክስ ማመልከቻ እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 341(1)መሰረት ወደ አ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. በዚሁ መሰረት ይፈጸም ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 87420

ሚያዚያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች** ፡- ወ/ሪት ማህሌት ልዑለቃል ጠበቃ በፈቃዱ ተሲላ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የለም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረጉና በየደረጃው ያሉ የከተማው አስተዳደር የበላይ ፍርድ ቤቶችም የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናታቸው ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ/ም ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ቃሉ ፡- ከአባቴ ከአቶ ፈለቀ ደንበልና ከእናቴ ከወ/ሮ ፋንቱ ገብረሕይወት ተወልጄ ማህሌት ፈለቀ በሚል ስም በላፎንቴን መዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ቤት እየተጠራሁ ትምህርቴን የጀመርኩ ቢሆንም መደበኛ ትምህርቴ ሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ሲቀጥል በት/ቤቱ መምህር በሆኑት አሳዳጊዬ በአቶ ልዑለቃል ገብረየሱስ ስም በመመዝገብ ተምሬ እስከ ዩኒቬርሲቲ ያጠናቀቅኩ ቢሆንም አሁን ግን በሥጋ ወላጆቼ ስም መጣራት ስለምፈልግ ማህሌት ፈለቀ ደንበል ተብዬ እንዲጠራ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የመ/ደረጃ ፍርድ ቤትም፡- አመልካች አቤቱታቸውን ለማስረዳት ያቀረቡት የሰው ምስክሮች የሰጡትን ቃልና የጽሁፍ ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን በሰጠው ውሳኔ፡- አመልካች በፍ/ህ/ቁ/32(2) መሰረት ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የቤተዘመድ ስም የሚገልጽ ማስረጃ ካለማቅረባቸውም ሌላ የተሰሙት ምስክሮችም ‹‹ ልዑለቃል ገብረየሱስ ›› በሚል ስትጠራበት የነበረው የአሳዳጊ አጎቷ ስም መሆኑን እንጂ የቤተዘመድ ስም አለመሆኑን ስላስረዱና እንዲለወጥላቸው የፈለጉት ስም የቤተዘመድ ስም ስለመሆኑ ተገቢውን ማስረጃ በማቅረብ ስላላስረዱ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህ ውሳኔም ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተገለጸው በበላይ ፍርድ ቤቶች በመጽናቱ ምክንያት ለዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብም ሲጠቃለል፡- አንድ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞችና የአባት ስም እንደሚኖረው በፍ/ህ/ቁ/32(1) የተደነገገ ሲሆን በቁጥር 33(1) ደግሞ የልጁ የቤተዘመድ ስም ማለት የአባቱ የቤተዘመድ ስም እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ስሙ እንዲለወጥለት በሚጠይቅ ሰው አቤቱታም የአቤቱታ አቅራቢውን የቤተዘመድ ስም ዳኞች ሊለውጡ እንደሚችሉ ቁጥር 42 ተመልክቷል፡፡ በአሁን በአገራችን ባለው ተጨባጭ የስም አሰጣጥ ባህል መሰረትም የቤተዘመድ ስም የሚባል የለም፡፡ የቤተዘመድ ስም ሳይኖርው ሲቀር ደግሞ የቤተዘመድ ስም ነው ተብሎ የሚወሰደው የአባት ስም እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ/ 33 (2) ተደንግጎ እያለና አመልካችም የቤተዘመድ ስሜ በወላጅ አባቴ ስም እንዲሆን እንዲወሰን በቂ የሰውና ጽሁፍ ማስረጃዎችን አቅርቤ ሳለሁ ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም ብለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች በወላጅ አባቴ ስም እንድጠራ ይወሰንልኝ ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመርህ ደረጃ አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም( family name)፣አንድ ወይም ከዚያ በላይ የግል ስሞች( first names) እና የአባት ስም( patronymic ) እንደሚኖረው በፍ/ህ/ቁ/32(1) የተደነገገ ሲሆን ለልጁ የአባት ስም የሚሆነው ደግሞ የአባቱ የግል ስም እንደሆነ በቁጥር 36 ተመልክቷል፡፡
የልጁን መወለድ መግለጫ ሊሰጥ የሚገባው ሰው ደግሞ ልጁ ከተወለደበት ቀን አንስቶ ባለው ተከታዩ ዘጠና ቀናት ውስጥ ለልጁ የተሰጠውን የግል ስም ልጁ በተወለደበት ቀበሌ(አጥቢያ) ለሚገኘው የክብር መዝገብ ጽህፈት ቤት መግለጫ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በቁጥር 37 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ የመወለድ ጽሑፍም ከሚያካትታቸው መስፈርቶች አንዱ በአንቀጽ 99(መ) ሥር የተመለከተው የቤተዘመድ ስም ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው የቤተ ዘመድ ስም እንዲለወጥ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በቁጥር 42 የተመለከተ ሲሆን በዚህ ረገድ የሚቀርበውን ጥያቄ ዳኞች ተቀብለው ስሙ እንዲለወጥ መወሰን የሚችሉት ስሙን ለመለወጥ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያረጋግጡ ሲሆን የስሙ መለወጥም በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ አንድም ጉዳት እንዳያስከትል ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባቸው ስለመሆኑም ህጉ ያመላክታል፡፡ እንግዲህ በክብር መዝገብ ሊሰፈር የሚገባው የመወለድ ጽሑፍ ቃል የቤተዘመድ ስምንም የሚያካትት እስከሆነ ድረስ በጊዜው ልደትን፣ጋብቻና ሞት የሚመዘግበው የክብር መዝገብ ሹም ባለመኖሩ በፍ/ህጉ በቁጥር 3361(1) ስር ስለ ክብር መዝገቦች የተዘረዘሩት የፍ/ህግ ቁጥሮች በሥራ ላይ የሚውሉበት ቀን ተወስኖ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ እስከሚወጣ ድረስ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው የተደነገገ ሲሆን በንዑስ ቁጥር 2 ልደትን፣ጋብቻን እና ሞትን የሚገልጽ ማስረጃ በጊዜው በነበረው አጠራር የአገር ግዛት ሚኒስቴር የመረጣቸው ሰዎች ያዘጋጁትን የታወቁ ጽሁፎች በማቅረብ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የተመለከተ ቢሆንም በይበልጥ ከዚህ ከሚያከራከረው ጉዳይ ጋር ተያይዞ የቤተዘመድ ስም የግል ስም እንዲሁም የአባት ስም( patronymic) በተደራጀ መልኩ የሚመዘግብ አካል የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በተወለዱበት በ1979 ልደትን በአግባቡ መዝግቦ ማስረጃ የሚሰጥ የክብር መዝገብ ሹም ወይም አካል በሌለበት ሁኔታ አመልካች እንዲለወጥላቸው የጠየቁት ስም የቤተዘመዳቸው ስም ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ

(ሰነድ) አለቀረቡም በሚል አቤቱታቸውን ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ያደረጉት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ህጋዊ ምክንያች ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደ ፍሬ ጉዳዩ ስንመለስ አመልካች ላፎንቴን መዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ቤት በ23/12/1991 ዓ/ም በተሰጣቸው የተማሪ ውጤት መግለጫ(ካርድ) ላይ ማህሌት ፈለቀ በሚል ስማቸው መመዝገቡን ፤ሊሴ ገብረማርያም 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ሲማሩ ደግሞ ማህሌት ልዑለቃል ገ/የሱስ  በሚል ተመዝግበው መማራቸውን እንዲሁም በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የንግድ ትምህርት ቤት ሲማሩም ማህሌት ልዑለ ቃል ገብረየሱስ ተብለው እንደሚጠሩ በመ/ደ/ፍርድ ቤት ከቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋጠ ሲሆን፤ ቀርበው ከተሰሙት የአመልካች አባት እና እናት ከሆኑት ምስክሮች ቃልም፡- አቶ ልዑለ ቃል ገብረየሱስ የአመልካች እናት ወንድም መሆናቸውን እና በት/ቤቱም መምህር ስለነበሩ አመልካችን ት/ቤቱ እንዲቀበላቸው በሚል የወላጅ አባታቸው ስም ተለውጦ በመምህር ልዑለ ቃል ገብረየሱስ ስም እንዲመዘገብ መደረጉን ካስረዱት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡

እነዚህን ማስረጃዎችን የመመዘንና የመመርመር ሥልጣን ባለው የሥር የመ/ደ/ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ቀደም ሲል ሲጠሩበት የነበረውን የአባታቸውን ስም በመለወጥ ማህሌት ልዑለቃል ገ/የሱስ ስም የተጠሩት መደበኛ ትምህርታቸውን ለመማር በሚፈልጉበት ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር እንዲያስችላቸው በሚል ምክንያት ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶቹ በተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች መሰረት ጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው ልዑለ ቃል ገብረ የሱስ የቤተዘመዳቸው ስም ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም ሲሉ ውድቅ ያደረጉት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/2827/2004 በቀን 20/10/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/18469 በቀን 23/12/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የከተማው አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/19021 በቀን 24/03/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች በወላጅ አባታቸው በአቶ ፈለቀ ደንበል ስም እንዲጠሩ በጠየቁት መሰረት ቀደም ሲል ሲጠሩበት የነበረው ስም ማህሌት ልዑለቃል ገብረየሱስ ተቀይሮ ማህሌት ፈለቀ ደንበል በሚል እንዲጠሩ ወስነናል፡፡
   **መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

# ጉምሩክ/ግብር/ታክስ

የሰ/መ/ቁ. 79189

መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** የኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ወ/ሕይወት ደምሰው ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** ጂ.ኤም.ቲ ኢንዱስትሪያል ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር በተጀመረበት ፌ/ከ/ፍ/ቤት ተጠሪ እና አመልካች እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የነበሩት ደግሞ የሰበር ክርክሩ አካል ያልሆኑት እንደቅደም ተከተላቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የማረሽ፣ የወገልና የቢላዋ ስ/አ/ህብረት ስራ ማህበር ናቸው፡፡ በ06/07/02 ተሻሽሎ የቀረበው ክስ ይዘትም ከሳሽ በ1ኛ ተከሳሽ ስር ከሚገኘው የፍ/አ/መምሪያ የ3ኛ ተከሳሽ ንብረት የነበረ ድርጅት በጨረታ ገዝቶ መረከቡን፣ ይሁን እንጂ ከ3ኛ ተከሳሽ የሚፈለግ የካፒታል ዕድገት ግብር ካለ እንዲገለፅ ከ1ኛ ተከሳሽ ለተፃፈለት ደብዳቤ 2ኛ ተከሳሽ በወቅቱ ምላሽ ባለመስጠቱ፣ 1ኛ ተከሳሽም የ2ኛ ተከሳሽን መልስ ሳይጠብቅ እና ግብሩን ሳይቀንስ ተራፊውን ገንዘብ በሙሉ ለ3ኛ ተከሳሽ በመመለሱና የ3ኛ ተከሳሽ ካርታ ሳይቀርብ ከሳሽ በንብረቱ እንዲበደር ለባንክ ማረጋገጫ በመስጠቱ 3ኛ ተከሳሽ ከግብር ነፃ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃና ካርታ ሳያቀርብ ሙሉ ገንዘብ በመቀበሉ በአጠቃላይ ተከሳሾቹ በአንድነትና በመመሳጠር በፈጸሙት ተግባር ከሳሽ ስሙን አዛውሮ በንብረቱ ለመጠቀምና ብድሩን ለመክፈል አለመቻሉን የሚገልጽ ሆኖ በከሳሽ ላይ የታሰበውን የብድር ወለድ ብር 1,785,539.20 ተከሳሾቹ ለከሳሽ እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ክስ የቀረበበትን የወለድ ገንዘብ ለመክፈል ተከሳሾቹ የሕግም ሆነ የውል ግዴታ የለባቸውም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፍ/ባለመብት አሰፋ አርጋው እና የፍ/ባለዕዳ በነበረው 3ኛ መ/ሰጪ መካከል በነበረው አፈፃፀም ይ/ባይ የ3ኛ መ/ሰጪ ንብረት የነበረውን ድርጅት በ22/03/99 ዓ/ም በብር 6,700,000 በጨረታ ገዝቶ ገንዘቡን አጠቃሎ ገቢ በማድረግ ድርጅቱን እንደተረከበ

ድርጅቱን ለመግዛት ይ/ባይ ከወጋገን ባንክ ጎፋ ቅርንጫፍ ብር 4,265,100 ሲበደር የስም ዝውውሩ ወደ ይ/ባይ ሲፈፀም ካርታውን በቀጥታ ለባንኩ እንዲልክ ለ2ኛ መ/ሰጪ በደብዳቤ የሚያሳውቅ መሆኑን በመግለፅ የፍ/አ/መምሪያ ለባንኩ ማረጋገጫ እንደሰጠ፣ ከ3ኛ ተከሳሽ የሚፈለግ የካፒታል ዕድገት ግብር እንዲገለጽለት 1ኛ መ/ሰጪ ለ2ኛ መ/ሰጪ ደብዳቤ የፃፈው በ09/09/99 ዓ/ም ሆኖ 2ኛ መ/ሰጪ ብር 803,997.33 የካፒታል ዕድገት ተቀንሶ እንዲሰጠው በመጠየቅ ምላሽ የሰጠው ከዘጠኝ ወራት በኋላ በ06/06/2000 ዓ/ም እንደሆነ፣ በዚህ ጊዜ መሀል 3ኛ መ/ሰጪ ተራፊውን ገንዘብ በሙሉ እንደወሰደ፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 37 መሰረት የካፒታል ዕድገት ግብር የመክፈል ግዴታ የሻጭ በመሆኑ ግብሩ እንደሚፈለግብኝ አላውቅም ነበር በማለት 3ኛ መ/ሰጪ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው 1ኛ መ/ሰጪ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ አይገባውም ወይም ግብሩ ሊኖር እንደሚችል መገመት የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም ባይባልም ግድፈቱ ሚዛን የሚደፋ እንዳልሆነ በፍ/ቤቶች የሚፈፀም ስህተት በይግባኝ ከሚታረም በስተቀር ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው የሚባል ከሆነ በሀገሪቱ ምስቅልቅል የሚፈጠር እንደሆነ፣ 2ኛ ከዘጠኝ ወር በኋላ ግብሩ ገቢ እንዲደረግለት ጠይቆ ገንዘቡ ለ3ኛ መ/ሰጪ መለቀቁ ሊገለጽለት ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት እና ለፌዴራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን ደብዳቤ መፃፉ የራሱን ስህተት ግምት ውስጥ እንዳያስገባ ስህተቱን ሌሎች መ/ሰጪዎች እንደፈፀሙት በማድረግ መሯሯጡ ተገቢነት እንዳልነበረው በዝርዝር ከገለፀ በኋላ ይ/ባይ ድርጅቱን የተረከበው በመሆኑ መ/ሰጪዎች የባንክ ብድር ወለድ ይክፈሉኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው ይሁን እንጂ ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው ይ/ባይ ግዴታውን ሙሉ በሙሉ ተወጥቶ እያለ ስሙ እስካሁን ያልተዛወረለት በመሆኑ 2ኛ መ/ሰጪ የድርጅቱን ባለቤት ስም ወደ ይ/ባይ ያዘውር የካፒታል ዕድገት ግብሩን ብር 803,997.33 ገንዘቡን ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር 3ኛ መ/ሰጪ ለ2ኛ መ/ሰጪ ገቢ ያድርግ 2ኛ መ/ሰጪም ተከታትሎ ገቢ ያስደርግ ይ/ባይ ለዳኝነት የከፈለውን ገንዘብ 2ኛ እና 3ኛ መ/ሰጪዎች በታሪፉ መሰረት ግማሽ ይክፈሉት፣ ቀሪውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የጠ/ፍ/ቤቱ ይ/ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን በ24/08/04 አዘጋጅቶ ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በጨረታ አሸንፎ የተረከበውን ድርጅት በአመልካችና በሌሎች የስር ተከሳሾች ጥፋት ወደስሙ ማዛወር ባለመቻሉ ከባንክ ለወሰደው ብድር ለብር 1,785,539.20 የወለድ ክፍያ የተዳረገ በመሆኑ ወለዱ ሊተካልኝ ይገባል የሚል ሆኖ አመልካች ስም እንዲያዘውር የካፒታል ዕድገት ግብር ከነወለዱ ከስር 3ኛ መ/ሰጪ ተከታትሎ ገቢ እንዲያደርግ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ከክሱ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በ06/07/02 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ አሻሽሎ ባቀረበው ክስም ሆነ ለይ/ሰሚው ፍ/ቤት ባቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ የጠየቀው ዳኝነት የወለድ ክፍያ መሆኑን እና በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ዳኝነት ደግሞ የስም ዝውውር እንዲፈፀም መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ በከ/ፍ/ቤትም ሆነ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ዳኝነት ለጠየቀበት የወለድ ክፍያ ዋንኛ መንስኤ

የሆነው በስር ተከሳሾች (መ/ሰጪዎች) ድርጊት ሳቢያ የስም ዝውውሩ ሊፈፀም አለመቻል መሆኑን በግልጽ ሲከራከርበት የነበረ በመሆኑ የድርጅቱ የስም ዝውውር ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶች ዳኝነት ከጠየቁበት ጉዳይ ውጪ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን የስም ዝውውሩን እና የካፒታል እድገት ግብሩን ክፍያ መፈፀም ቅደም ተከተል አስመልክቶ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ከገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑ መጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ግብር የተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ ማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው ሰው ግብሩ መከፈሉን ሳያረጋግጥ ዝውውሩን እንደማይቀበል እንደማይመዘግብ እና እንደማያፀድቅ በአዋጅ በአንቀጽ 37(7) ስር በግልጽና በአስገዳጅነት ተደንግጐ ይገኛል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ግልጽ የሕግ ክልከላ ባለበት ሁኔታ ደግሞ የስም ዝውውሩ ከግብር ክፍያው አስቀድሞ ሊፈጸም የሚችልበት አግባብ ስለማይኖር በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው የአፈፃፀም ቅደም ተከተል ከአዋጁ ድንጋጌ አንፃር መስተካከል የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ከስር 3ኛ መ/ሰጪ የካፒታል እድገት ግብሩን ተከትሎ ገቢ እስኪያስደርግ ድረስ የስም ዝውውሩ መዘግየት ጉዳት ያስከትልብኛል የሚል አቋም ኖሮት ተጠሪው ግብሩን ከፍሎ የስም ዝውውሩን የሚያስፈፅም ሆኖ ከተገኘም የከፈለውን የካፒታል ዕድገት ግብር ከስር 3ኛ መ/ሰጪ የማስተካት መብት እንዲኖረው መደረጉን ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 69181 በ30/06/04 የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ካፒታል እድገት ግብሩን ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በውሳኔው መሰረት ከስር 3ኛ መ/ሰጪ ተከታትሎ ገቢ ካስደረገ በኋላ የስም ዝውውሩን ያስፈጽም በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ የጉዳዩ መዘግየት ሊያስከትልበት የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ያስችለው ዘንድ ግብሩን እራሱ ከፍሎ ከስር 3ኛ መ/ሰጪ ለማስተካት የሚፈልግ ከሆነ የካፒታል እድገት ግብሩን ብር 803,997.33 (ስምንት መቶ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ከ33/100) ከፍሎ የስም ዝውውሩን እንዲያስፈፅም እና የስር 3ኛ መ/ሰጪም ይ/ሰሚው ችሎት በወሰነው መሰረት ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ ለተጠሪ እንዲተካ ወስነናል፡፡
4. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው የወጪና ኪሳራ ውሳኔ አልተነካም፡፡
6. የአፈፃፀም እግዱ ተነስቷል፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 84623

ሰኔ 04 ቀን 2005 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** 1. ጅ. አግሪ ፖክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

2. አቶ ጌታሁን አስፋው ጠበቃ ገ/እግዛብሔር ሙናቸው ቀረቡ

**ተጠሪ፡** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ

**መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታርምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ታክስ አለመክፈልን የሚመለከት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ተጠሪ በስር አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አንደኛው አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና በአዋጅ ቁጥር 255/94 አንቀጽ 26/1/ለ/2 አንቀጽ 56/1/2/ እና አንቀጽ 49 የተደነገገውን በመተላለፍ የታክስ ከፋይነት መለያ ቁጥርና የተጨማሪ እሴት ታክስ መለያ ቁጥር ተስጥቶት እያለ ከመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2001 ዓ.ም በሚያከናውነው የንግድ እንቅስቃሴና ሽያጭ በየወሩ ተጨማሪ እሴት ታክስ በመሰበሰብ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ማሳወቅና መክፈል ሲገባው የንግድ ማህበሩ የማስታወቅ ግዴታውን ብቻ በመወጣት የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ በሶስተኛ ወገን በተሰጠ ጥቆማ መነሻ በተደረገው ማጣራት መክፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስና አስተዳደራዊ መቀጫ ብር 9 ,065,777.59 /ዘጠኝ ሚሊየን ስልሳ አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከሃምሳ ዘጠኝ ሳንቲም/ ያልከፈለ በመሆኑ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል የሚል ነው፡፡

2. የአንደኛ ተከሳሽ ዋና ስራ አስኪያጅ የሆነው ሁለተኛው ተከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 26/1/ለ/2/ አንቀጽ 56/1/2 እና አንቀጽ 49 የተደነገገውን በመተላለፍ አንደኛው ተከሳሽ/አንደኛ አመልካች/ የአክስዮን ባለድርሻና ባለንብረት እንዲሁም በመመስራቻ ጽሁፍ የተሾመ ስራ አስኪያጅ ሆኖ እያለ ከላይ መጠኑ የተገለፀውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የመክፈል ግዴታውንና ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል የሚል ይዘት የለው ነው፡፡
3. አንደኛ ተከሳሽ በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 53 ንዐሱ አንቀጽ 1፣2 እና 3 አንቀጽ 102 እና አንቀጽ 96 የተደነገገውን በመተላለፍ ከዕቃ ገዥዎች በቅድሚ ክፍያ ተቀንሶና ተሰብስቦ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ማስገባት የነበረበትን ብር 374,818. 81 /ሶስት መቶ ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም/ ያልከፈለ በመሆኑ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል
4. ሁለተኛ ተከሳሽ ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የአንደኛው ተከሳሽ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ በቅድመ ክፍያ ቀንሶና ሰብስቦ መክፈል የሚገባውን መጡኑ በሶስተኛው ክስ የተገለጸውን ገንዘብ የልከፈለ በመሆኑ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል የሚል ይዘት የላቸው አራት የወንጀል ክሶችን አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምንም ጥፋተኛ አይደለመንም በማለት ተከራክረዋል፡፡
5. ተጠሪ ክሱን የሚያስረዱልን ምስክሮች አሉ በማለት ሶስት ምስከሮችን በማቅረብ አሰምቷል፡፡ የመጀመሪያው ምስክር አንደኛ ተከሳሽ ተጨማሪ እሴት ታክስና የደመወዝ ግብር ገቢ በሕግ አግባብ እያሰበሰበና እየከፈለ አይደለም የሚል ጥቆማ ድርሰን፡፡ የደመወዝ ግብር ገቢ ለክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን እንዲያውቀው አድርገን የተጨማሪ እሴት ታክሱን በኦዲት እንዲጣራ ተደርጎ በአንደኛው የክስ ማመልከቻ መጠኑ የተጠቀሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ አንደኛው ተከሳሽ እንዳልከፈለ ተረጋግጧል ከዚያ በኒላ አንደኛ ተከሳሽ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አመልክተው ጥያቄው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ሁለት ፐርሰንት ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ እያደረገ ለግብር አስገቢ መስሪያ ቤት ያልከፈለ መሆኑንና በሶስተኛው ክስ መጠኑ የተገለጸውን ገንዘብ እንዳልከፈለ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የግብር ገንዘቡን ለማስከፈል እንቅስቃሴ ቢያደርግም አንደኛ ተከሳሽ ከዳሽን ባንክ ለወሰደው ብድር ባንኩ መደባውን በመሸጡና በባንኩ እዳ የተረፈ ገንዘብ የሌለ መሆኑ ስለተነገረን ሌሎች ንብረቶችን በማፈላለግ ላይ እንገኛለን በማለት እንደመሰከሩ የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልጽ አስፍሮታል፡፡
6. ሁለተኛዋ የተጠሪ ምሰክር አንደኛ ተከሣሽ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሣወቂያ ቅጽ መሠረት በየወቅቱ ለተጠሪ ያሣወቀ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ነገር ግን አመልካች ተጨማሪ እሴት ታክስ ከፍሎ አያውቅም፡፡ የድርጅቱን /አንደኛ/ ተከሣሽን ኦዲት ሠርቻለሁ፡፡ ኦዲት ስንሰራ እኛ ድርጅቱ በሣምንት አንድ ቀን ማለትም እሁድ ቀን ምርት እንደማያመርትና በወር አራት ቀናት እንደማያመርት በመቀነስ በወር ሃያ ስድሰት ቀናት እንደሚያመርት በመያዝ ሂሣቡን ሠርተናል፡፡ አንደኛ ተከሣሽ በወር ሃያ ስድስት ቀናት የማምረት አቅሙን ተጠቅሞ የሚያመርተውን በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሣወቂያ ቅጽ አላሣወቀም የዊዝ ሆልድግ ታክሱም አለበት በማለት እንደመሰከረች ከስር ፍ/በት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

7. ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር የአንደኛ ተከሣሽ ሒሣብ ኦዲት ሲደረግ አንደኛው ተከሣሽ የተሟላ መረጃ ይዞ አለመገኘቱንና የቀን ግምቱን መነሻ በማድረግ የግብሩን መጠን የሰሩ መሆኑን@ የድርጅቱን ትክክለኛ የሽያጭ መጠን ለማወቅ የተሟላ ሪከርድ የሌለ መሆኑንና አስቸጋሪ እንደሆነ፣ የቀን ግምት በመውሰድ በወንጀል ክሱ የተገለፁት የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድመ ተከፋይ ተቀናሽ /ዊዝሆልድግ/ ታክስ የሚፈለግበት መሆኑን በመግለጽ ሪፖርት አቅርበናል የሚል ይዘት ያለው የምስክርነት ቃል እንደሰጠ ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ይዘት ተረድተናል፡፡

8. አመልካቾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የስር ፍ/ቤት ብይን ሰጥቶ ሁለተኛው ተጠሪ የመከላከያ የምስክርነት ቃሉን የሰጠ ሲሆን፣ በቂ እውቀትና ክህሎት ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ባለማግኘታችን የምርት ብልሽትና ብክነት ተከስቷል፡፡ ከመጋቢት 1999 እስከ 2001 መብራት ይቆራረጥ የነበረ በመሆኑ ድርጅቱ በአንድ ፈረቃ ብቻ ለማምረት ከመገደዱም በላይ ለቀናትና ለወራት ጭምር የምርት ስራ የቆመበት ሁኔታ ነበር፡፡ ለዙሁም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተፃፈልን የጽሑፍ ማስረጃ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከወር ሃያ ስድስት ቀናት በሶስት ፈረቃ እንደሚያመርት በመገመት የተሰራው የኦዲት ስራ እውነታውን የሚያሣይ አይደለም በማለት የምስክርነት ቃሉን የሰጠ ሲሆን ሌሎች የአመልካቾች ሁለት ምስክሮችም ከመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም የመብራት መቋረጥ ምክንያት የምርት ስራ ተቋርጧል የሚሉበትን ሁኔታ በዝርዝር የመሰከሩ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

9. ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የሃዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩልና በአመልካቾች በኩል የቀረቡትን ማሰረጃዎች ከመረመረ በኂላ አንደኛ ተከሣሽ /አንደኛ አመልካች/ ተጠሪ ባቀረበው በአንደኛውና በሶስተኛው የወንጀል ክሶች ውስጥ የጠቀሣቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ፣ በተጠሪ ክስ የተገለፁትን የወንጀል ድርጊቶች የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ተከሣሽ/ሁለተኛ አመልካች/ ተጠሪ በሁለተኛውና በአራተኛው የወንጀል ክስ የጠቀሣቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በክሱ የተገለፁትን የወንጀል ድርጊቶች የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተ አንደኛው አመልካች በብር አርባ ሺ ብር/ብር 40,000/ መቀጮ እንዲከፍል ሁለተኛው አመልካች ከሐምሌ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ አምስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ይግባኝ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/1/ መሠረት ሰርዞታል፡፡

10. አመልካቾች ጥቅምት 9 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በወንጀል ክሱ የጠቀሣቸው የአዋጅ ቁጥር 285/94 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 ድንጋጌዎች የታክስ ስወራ ወንጀል የሚፈጸሙ ሰዎችን በወንጀል ኃላፊ እንዲሆንና እንዲቀጣ ለማድረግ ታስበው የታወጁ ናቸው፡፡ አመልካቾች በወቅቱ ለግብር ሰብሣቢው መስሪያ ቤት የማሣወቅ ግዴታችንን የምንወጣ መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስና አቅርቦ ባሰማቸው ምሰክሮች ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ኦዲተሮች በወቅቱ የነበረውን በኤሌክትሪክ ሀይል እጥረት ምክንያት ምርት የሚቋረጥባቸውን ጊዜዎች ሣያገናዝቡ ድርጅቱ በሶስት ፈረቃ ሃያ ስድሰት ቀናት እንደሚያመርት የህሊና ግምት በመያዝ የሰሩት ሒሣብና ያቀረቡት ሪፖርት በግምት ላይ

የተመሰረተና የተመረተውን እርግጠኛ ምርትና የተደረገውን ግብይት መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ@ በዚህ ማስረጃ መነሻ የወንጀል ክስ መቅረቡም ሆነ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትም ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በዊዝሆልዲንግ ታክስ ጥሰት ቢፈፀም እንኳን የወንጀል ተጠያቂነትና ቅጣት የሚያስከትል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/94 ያልተደነገገ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ሶስተኛውና አራተኛው የወንጀል ክስ የሕጋዊነት መርህን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር እንዲያሰናብተን በማለት አመልክተዋል፡፡

11. ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 285/94፣ በአዋጁ ቁጥር 286/94 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/94 የተጣለባቸው የተጨማሪ እሴት ታክስና የዊዝሆልዲንግ ታክስ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች የማሣወቅ ግዴታቸውን መወጣታቸው መክፈል የሚገባቸው ታክስ ባለመክፈላቸው የሚደርስባቸውን የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስቀርላቸው አይደለም፡፡ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ግብር በግምት እንዲወሰን የሚፈቅድለት የሕግ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ስለዚህ በግምት የተወሰነው የግብር ውሣኔ በወንጀል ጉዳይ እንደማስረጃ መቅረቡን በመቃወም አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ በአጠቃላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 16 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

12. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

13. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስና ክሱን የወንጀል መሠረታዊ ይዘት ያለው መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 285/96 ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሚፈፀው ወንጀሎች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በመተላለፍ የሚፈፀው በመሆኑ ክሱ የሚመሠረተው የሚታየውና በይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት እንደሆነ በአንቀጽ 48 የሚደነገግ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 94 ተመሣሣይ ይዘት ያለው እንደሆነ እንረዳለን ይህም በመሆኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 111 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 112 መሠረት የተዘጋጀን አመልካቾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሕግ የሞራልና የግዙፍ ተግባር ሁኔታ በተሟላበት ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በተለይ የሕግ ጥሰት በመፈፀም ታክስ ያለመክፈል ወንጀል የፈፀመ መሆኑን የሚያሣይ የወንጀል ክስ ይዘትና ባህሪ ያለው ሊሆን ይገባዋል፡፡

14. የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ድንጋጌዎች ሕግን በመጣስ ተክስን አለመክፈል ወይም በእንግሊዘኛው "Tax Evasion" የሚል ርእስ ያላቸው ሲሆን ይዘታቸው ተመሣሣይነት ያለው ነው፡፡ የድንጋጌዎቹ ይዘት ቃል በቃል ሲነበብ ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ግብር ያላሣወቀ ወይም የሚፈለግበትን ግብር ያልከፈለ ወይም መንግስትን ለማጭበርበር በማሠብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ማናቸውም ሰው ወንጀል አንደፈፀም ይቆጠራል በመሆኑም በዚህ አዋጅ ክፍል አሥራ አንድ መሠረት ከሚጣልበት መቀጮ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ሲረጋገጥ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት ይቀጣል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

15. አመልካቾች ግብር የማሣወቅ ግዴታቸውን የፈፀሙ መሆኑን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ባቀረባቸው የወንጀል ክሶች በግልጽ ያሰፈረው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንደኛ አመልካችን ሂሣብ ለማጣራት የተመደቡት የተጠሪ ምስክሮች አመልካቾችን በየወቅቱ በሂሣብ በግብር ማሣወቂያ ቅጾችን በመሙላት ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ያሣውቁ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በተደነገገው መሠረት ግብር የማሣወቅ ግዴታቸውን በመተላለፍ ታክስ ባለመክፈል የፈፀሙት ግዙፍ የወንጀል ተግባር የሌለ መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስና ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

16. አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 285/96 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በተደነገገው መሰረት መንግስትን ለማጭበርበር በማሰብ የማይገባቸውን የታክስ ተመላሽ በመጠየቅ ግዙፍ የወንጀል ተግባር የፈፀሙ መሆናቸውን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረባቸው የወንጀል ክሶች አይገልጽም፡፡ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረቧቸው ምስክሮችም አመልካቾች የማይገባቸውን የታክስ ተመላሽ በመጠየቅ መንግስትን የማጭበርበር ስራ ስለመስራታቸው የሰጡት የምስክርነት ቃል የለም፡፡

17. ተጠሪ አመልካቾች የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል በማለት ክስ ያቀረበው አመልካቾች ከመጋቢት ወር 1999ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ በግምት የተወሰነባቸውን ብር 9,065,577.59 ተጨማሪ እሴት ታክስ ከነመቀጫውና ብር 374,818.81 ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ በወቅቱ አልከፈሉም በማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት አመልካቾች አንደኛ አመልካች ያመረተውን የምርት መጠንና ያከናወኑትን ግብይት ከግብይቱ የሰበሰቡትን ገቢ በየወቅቱ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ያቀርቡ የነበረ መሆኑ በተጠሪ ክስና ማስረጃ የተገለፀና የተረጋገጠ በሆነበት ሁኔታና አመልካቾች በየወቅቱ ባቀረቡት የግብር ማሳወቂያ ቅጽ በመጀመሪያ አንደኛ ተከሣሽ ዕቃዎችን ሲያስገባ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ እና አንደኛ ተከሣሽ የፋብሪካ የምርት ውጤቱን ሲሸጥ የሰበሰበው ተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናንሰው ባላንሱ ዜሮ መሆኑንና ለመንግስት የሚከፍሉት የግብር ገንዘብ የሌለ መሆኑን በየወሩ መጨረሻ ሲያሳውቁ መኖራቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ኦዲተሮች ሂሣቡን ኦዲት ሲያደርጉ ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ ማለትም በሶስት ፈረቃ በወር ሃያ ስድስት ቀናት ሊያመርት ይችላል የሚለውን የህሊና ግምት በመያዝ የወሰኑት ግብር ባለመክፈላቸው በወንጀል የቀረበባቸው ክስ እና የተሰጠባቸው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 162 መስፈርት የማያሟላ መሆኑን ነው፡፡

18. በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ግብር አለመክፈል የወንጀል ተግባር ተደርጎ የተደነገገው ግብር ከፋዩ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ባሳወቀና ባልከፈለው ግብርና ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ግብር ከፋዩ የያዛቸውን የሂሣብ ሰነዶችና ማስረጃዎች በተለያየ ምክንያት በመጣል በግምት በወሰነው ግብር መካከል ልዩነት ሲፈጠር ግብር ከፋዩን በወንጀል ለመጠየቅና ለመቅጣት በማሰብ አይደለም፡፡ ይልቁንም መክፈል የሚገባውን የግብር ገንዘብ ላለመክፈል በማሰብና ግብር አስገቢው መስሪያ ቤትም ንብረቶችን በመያዝና በመሸጥ የግብር ገንዘቡን ገቢ እንዳያደርግ ለማድረግና ግብር ከመክፈል ኃላፊነቱ ለማምለጥ ንብረቶቹን የማሸሽና የመሰወር እና ሌሎች ተመሣሣይነት ያላቸውን ህገወጥ ተግባራት በመፈፀም ግብር ያልከፈለ ግብር ከፋይን ተጠያቂ ለማድረግ እንደሆነ ይኸ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 53544 በቀን 11/10/02 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

19. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካቾች በየወቅቱ ግብር የመስጠት ግዴታቸውን ሲወጡ ቆይተዋል፡ አመልካቾች በየወቅቱ ባቀረቡት የሂሣብ ሪፖርት ለመንግስት የሚከፈል ገንዘብ የሌለ መሆኑን ያሳወቁ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በወንጀል ክሱ የተጠቀሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የዊዝ ሆልዲንግ ታክስ ገንዘብ ከአንደኛው አመልካች የሚፈለግ መሆኑን በመወሰን የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ከሰጣቸው በኂላ አመልካቾች በህጉ መሰረት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በኂላ አመልካቾች በግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የተወሰነውን ግብር ያልከፈሉት የአንደኛው አመልካች ንብረት በዳሽን ባንክ ዕዳ ምክንያት በመሸጡና የባንክ ዕዳ ተከፍሎ ቀሪ ገንዘብ ባለመኖሩ መሆኑን አንደኛው የተጠሪ ምስክር በስር ፍ/ቤት ባስመዘገበው የምስክርነት ቃል እንደተገለፀ ተረድተናል፡፡

20. ማናቸውም ሰው የፍታብሄር ዕዳ ለመክፈል ባለመቻሉ ምክንያት በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ እንደማይቀጣ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 11 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ድንጋጌዎችም ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 13(2) እና ከላይ ከጠቀስነው ዓለም አቀፍ ድንጋጌ ጋር በማጣጣም ሁኔታ መተርጎምና ተፈፃሚ መሆን ያለባቸው መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 53544 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ፣ አመልካቾች ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በግምት የወሰነውን የግብር ገንዘብ ለመክፈል ባለመቻላቸው ምክንያት በወንጀል ተጠያቂና ጥፋተኛ ሊባሉ የሚችሉበት የህግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም በህጉ የተደነገጉት መስፈርቶች ሳይሟሉና በወንጀል ህግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የሃሳብና የግዙፍ ተግባር ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካችን ህግን በመተላለፍ ግብር ያለመክፈል ወንጀል ፈፅመዋል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 11768 የሰጠው ፍርድ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57769 የሠጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(1) *ሀ* መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ አንደኛው አመልካች ብር 40,000 (አርባ ሺ ብር) መቀጮ ከመክፈል በነፃ ተሰናብቷል፡፡ አንደኛው አመልካች የመቀጮውን ከፍሎ ከሆነ ይመለስለት፡፡
3. የበታች ፍርድ ቤቶች የሠጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ ሁለተኛው አመልካች ከእስር እንዲለቀቅ በክፍሉ ማረሚያ ቤት መፍቻ ይፃፍ፡፡

*መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 86388

ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች፡- አቶ ባዘዘው ይሁን የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የአ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ የቀረበ የለም

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ በሕግ የፀና ንግድ ፍቃድ ሣይኖረው መነገድ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ጃዊ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በተጠሪ የቀረበበት ክስም አመልካች የንግድ ምዝገባ ፈቃድ አዋጅ ቁ. 686/2002 አንቀጽ 60/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ሚያዚያ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ከለሊቱ በግምት 11፡30 ሲሆን ፈንደቀ ከተማ ልዩ ስሙ መናኸሪያ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ አመልካች ባልታደሰ የንግድ ፈቀድ ሁለት ማደበሪያ የፍየልና የበግ ቆዳ በሕዝብ ማመላለሻ መኪና በኪስ ውስጥ ይዞ ሊወጣ ሲል የትያዘ ስለሆነ በፈፀመው የፀና የንግድ ፈቃድ ሣይኖረው መስራት ወንጀል ተከሷል የሚል ሲሆን አመልካችም ቀርቦ ክሱ ከተነበበለት በኃላ ቆዳውን ይዤ ተገኝቻለሁ ነገር ግን ሕጋዊ ፈቃድ ስላለኝ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ዐ/ሕግም እንደ ክሱ ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም የቀረበውን የሰው ምስክር ሰምቶ ጉዳዩን ከማስረጃ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኃላ አመልካች እንደ ክሱ ባልታደሰና በማያገለግል ንግድ ፊቃድ ተጠቅሞ የበግ እና የፍየል ቆዳ ሲነግድ በመያዙ የተመሠከረበት በመሆኑ ክሱን ሊከላከል ይገባል በማለት ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ አመልካቹም በበኩሉ ክሱን ለመከላከል አቅርቦ ያሰማቸው የመከላከያ ምስክሮች አመልካች ንግድ ፈቃድ የነበረው መሆኑ እንጂ ንግድ ፈቀዱ የታደሰ ይሁን አይሁን ለይተው የማያቁ መሆናቸውን በመግለጽ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመጨረሻም ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት ጉዳዩን

ከመረመር በኃላ አመልካች ወንጀሉን አለመፈፀሙን በመከለከያ ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻሉ በተከሰሰበት የሕገ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት ከወሰነ በኃላ ቅጣትን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት ሃሣብ ተቀብሎ ከመረመር በኃላ በ7 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 150,000 የገንዘብ መቀጮ ይቀጣ ሲል ውሣኔ ሰጥቷል እንዲሁም ቆዳው የተሸጠበት ገንዘብም ብር 2,432 ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

አመልካችም በተሰጠው ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለአዊ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/1/ መሠረት ተቀባይነት አላገኘም በመቀጠልም አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርቦ ችሎቱም ግራ ቀኙ ቀርበው እንዲሰሙ ካደረገ በኃላ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ በማጽናት ቅጣቱን በተመለከተ ግን በ3 ዓመት ተኩል ጽኑ እስራት እና 5000 ብር መቀጮ በማሻሻል ወስኗል፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ ላይ የሕግ ግድፈት መፈፀሙን በመግለጽ እስከ አሁን የታሰርኩት ራሱ ከበቂ በላይ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከጥፋቱና ቅጣቱ በነፃ አንድሰናበት ይወሰንልኝ የሚል ነው አቤቱታውም ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም የመ/መልሱን ሰጠቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክር ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች የፀና የንግድ ሥራ ፈቀድ ሣይኖረው በቆዳና ሌጦ ንግድ ሥራ ተሰማርቶ ተገኝቷል በሚል የተከሰሰበትን ድርጊት መፈፀሙን ሣይክድ ነገር ግን ድርጊቱን ሊፈጽም የቻለው የተጠቀሰውን የንግድ ሥራ ሊያሰራ የሚችል የንግድ ሥራ ፈቀድ ያለው በመሆኑ ጥፋተኝነት እንደሌለበት በመግለጽ የተከራከረ መሆኑን ተረድተናል ሆኖም ግን አመልካች አለኝ የሚለው የቆዳና ሌጦ ንግድ ሥራ ፈቃድ በአዋጅ ቁ. 686/2002 አንቀጽ 2/10/ እና 36 ድንጋጌዎች ይዘት አኳያ በሕግ በተቀመጠው የግዜ ገደብ ውስጥ ያልቅጣትም ሆነ በቅጣት የታደሰ ባለመሆኑ /የማያገልግል ፈቃድ በመሆኑ/ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም በሕጉ አግባብ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሣይኖረው በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ ሰው ደግሞ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ በወንጀል ኃላፊ ሆኖ እንደሚቀጣ በአዋጅ አንቀጽ 60/1/ ስር ተደንግጓል በመሆኑም በዚህ ረገድ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ቅጣትን አስመልክቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የቀጣት ውሣኔም ቢሆን አመልካች ተላልፏል ተብሎ ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከ7 ዓመት እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት እና እንዲሁም በብር 150,000 እስከ 300,000 የገንዘብ መቀጫ ቢሆንም ችሎቱ የአመልካቹን የግል ሁኔታ የቀድሞ ባህሪውን የወንጀሉን አፈፃፀም እና እንዲሁም የወንጀሉን ክብደት እና ቅለት በማገናዘብ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሣሰን መመሪያ አኳያ በማስላት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ቅጣት በማሻሻል በ3 ዓመት ተኩል 3½/ ጽኑ እስራት እና በብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑ የሚነቀፍ እና መሠረታዊ



www.chilot.me

የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የሰበር አቤቱታም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

1. በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔም ሆነ ቅጣት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/2//ለ//2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ መጽናቱን አመልካች በሚገኝበት ማረሚያ ቤት በኩል ይገለጽለት፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 86597

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** በትግራይ ገቢዎች ልማት ባለስልጣን ዐ/ህግ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ በርሀ ረዳ ኪዳኑ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ሕጎች ጋር ተያይዞ የተነሳውን የወንጀል ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በዞኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከአክሱም ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ሳይፈቀድላቸው የቅዱስ ገብርኤል ማተሚያ ቤት መሳሪያ መደብር ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩ ሃያ አንድ ፓድ ደረሰኝ አትመዋል፣ በሁለት ኮፒ የሚታተም ደረሰኝ በአንድ ገፅ 100 ፓድ አትመው ደግሞ ተራፊ የሌለው አድርገው አትመዋል በዚህ አድራጎታቸው መንግስት ሊያገኘው ይገባ የነበረ ገቢ አሳጥተዋል፣ እንደዚሁም ማህተም ብቻ በማድረግ ብር 1,908.00 ያለ ቫት ክፍያ ተጠቅመዋል በማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ 609/2001 አንቀጽ 19፣ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 22(1)(2)፣ 50(ሐ) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ተላልፈዋል በሚል የቀረበባቸው መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪ ክደው ተከራክረው አቃቤ ህግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ተጠሪ እንዲከላከሉ ተደርጎም የመከላከያ ማስረጃዎች የተሰሙላቸው ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪን መከላከያ ማስረጃዎች ቃል ውድቅ አድርጎ ተጠሪን በአቃቤ ህግ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ በማድረግ በስድስት ወር እስራትና በብር 15,000.00 (አስራ አምስት ሺ ብር) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሙሉ በሙሉ የፀና ሲሆን ጉዳዩ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ግን ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ህትመቱን ሰራ የተባለው አካል በሕጉ ድርጅት የሚለውን መስፈርት የማያሟላና ተጠሪም የግል ባለሃብት እንጂ በድርጅት መሪነት የሚሸፈኑ አይደሉም የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ የስር ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነትና ቅጣት ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ የድርጅቱ ባለቤትና ስራ አስኪያጅ ሆነው እያለና ሕጉ ደግሞ ማንኛውንም ሰው ተጠያቂ እንደሚያደርግ ደንግጎ ባለበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባልቀረበለት የፍሬ ነገር ክርክርና ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ውጪ ተጠሪ በወንጀል አይጠየቁም በማለት

መወሰኑ ያለግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ተጠሪ የወንጀል ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ክስ የቀረበበት አካል ድርጅት መሆኑን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት ክስ የቀረበው በድርጅት ያለመሆኑን፣ አመልካች የግል ባለሃብት መሆናቸውን ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ለ)) እና በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 64(2(ሐ)) እንዲሁም በክልሉ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/1994 አንቀጽ 16 እና 17 ስለ ሰበር ችሎት ዳኝነት ስልጣን ከሚደነግጉት ስርዓት ውጪ ነው፡፡ ተጠሪ የማተሚያ ቤቱ ንግድ ፈቃድ በራሳቸው መሆኑና ግብርም በስማቸው የሚገብሩ መሆኑን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በሕጉ የተሰጣቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያረጋገጧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

ይህንኑ ይዘን ወደ ሕጉ ስንመጣም ተጠሪ በስራ አስኪያጅነት የሚመሩትና የግል ሃብታቸው በሆነው የንግድ ድርጅት በአመልካች በክሱ የተመለከቱትን ድርጊቶች ድርጅቱ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኝ ተገቢ ያልሆኑ ፓዶችን ማሳተሙን፣ ብር 1908 ያለ ቫት ደረሰኝ መጠቀሙ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በመርህ ደረጃ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 2(11) እና 56(1) እንዲሁም በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 19(50(ሐ)) ድንጋጌዎች መሰረት ጥፋተኛ የሚባሉ መሆኑ በህጉ ተደንግጓል፡፡

ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከቱትን ልዩ ሁኔታዎች በማስረዳት ከተጠያቂነት ነፃ ለመሆን ይጠቅመኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር በሌላ ቦታ የነበሩ መሆኑን ያሳያሉ ያሉት የመከላከያ ማስረጃ ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ በሌላ ቦታ የነበሩ መሆኑ ከወንጀል ተጠያቂነት የሚያድናቸው አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 3/ለ/ በተደነገገው መሰረት ማንኛውም በጎ አሳቢ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ጥንቃቄ ያደረጉና ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ድርጅቱን በመምራት ኃላፊነታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያለማቅረባቸውን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ከሰጡት የውሣኔ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3/1/ሀ/ መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ተመዝግበውና የድርጅቱ ባለሃብትና ስራአስኪያጅ  ሁነው ያልተፈቀደ ደረሰኝ በማተምና ብር 1908 ያለ ቫት የተጠቀሙ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ስራ አስኪያጅ ሳይሆኑ የግል ባለሃብት ስለሆኑ የወንጀል ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሻሩ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 2/11/፣3/1/ሀ/፣56 እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 2፣19/50/ሐ/

ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ባላገናዘበ ሁኔታ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 52605 ታህሳስ 23 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/2/ለ-1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17403፣ በቀን 24/7/2004 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51850 ሚያዝያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሰረት ጸንቷል፡፡

3. ተጠሪ በጉዳዩ ላይ የታሰሩበት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሆኖ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነባቸውን የስድስት ወር ቀላል እስራትና የብር 15,000.00 የአክሱም ማረሚያ ቤት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ታዟል፡፡ የዞኑ ፖሊስም ተጠሪን ይዞ ለማረሚያ ቤቱ እንዲያስረክብ ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 82061

መስከረም 20 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱልቀድር ሁሴን ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዐ/ሕግ ሜሮን ግርማ ቀረቡ

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ መስራዊ የህግ ሥህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ይታይልኝ በማለት የቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በተጠሪ የተወሰነው የገቢ ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብርን የሚመለከት ነው፡፡በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው አመልካች ይግባኝ ባይ፣ተጠሪ መልስ ሰጭ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ ያቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ ነው፡፡ ይግባኝ ባይ ( አመልካች) የተዘጋጁ ልብሶችና ቦርሳዎችን በችርቻሮ የመሸጥ የንግድ ሥራ የተሰማራሁ ግብር ከፋይ ነኝ፡፡ የይግባኝ ባይ ድርጅት ካለፈው ዓመት ያሳየው እድገት የለም፡፤ መልስ ሰጭ ገቢዬንና የንግድ ሥራዬን በአግባቡ ሳያጠናና በቂ ማስረጃ ሳይኖረው ባለፈው ዓመት የከፈልኩትን ገቢ ግብር እጥፍ እንድከፍል ወስኖ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶኛል፡፡ እንደዚሁም ይግባኝ ባይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሳልሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶኛል፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ባይ ከሕግ ውጭ የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ ባለፈው ዓመት በከፈልኩት መሰረት በቁርጥ እንድከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ መልስ ሰጭ በበኩሉ የይግባኝ ባይ የቀን ገቢ በኮሚቴ ተጠንቷል፡፤ ገማች ኮሚቴ ባጠናው የጥናት ውጤት መሰረት ገቢ ግብሩ ተስተካክሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው፡፡ የይግባኝ ባይ የቀን ገቢ ከብር 1700 (አንድ ሺ ሰባት መቶ ) በላይ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት ከሀምሌ ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት በመሆኑ

ከሚያዚያ ወር 2003 እስከ ሰኔ 2003 ዓ.ም መክፈል ያለበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር እንዲከፍል ውሳኔው ማስታወቂያ በነሀሴ ወር 2003ዓ.ም እንዲደርሰው የተደረገው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ይግባኝ ባይ መልስ ሰጭ በይግባኝ ባይ ላይ ገቢ ግብር ጨምሮ የወሰነው በገማች ኮሚቴ የይግባኝ ባይን የቀን ገቢ በማስጠናት በመሆኑ ተገቢ ነው፡፡ ለይግባኝ ባይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የደረሰው የቀን ገቢው ብር 1700( አንድ ሺ ሰባት መቶ) በመሆኑ ነው፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኛ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል ፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ገቢ ግብር በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶ፣የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ ሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ሰበር አቤቱታ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የከተማው ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

3. አመልካች 2/11/2004 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የቁርጥ ግብር ከፋይ ነኝ፡፡ ተጠሪ ገቢ ግብር አስተካክሎ መወሰን የሚችለው በየ አምስት ዓመቱ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሥከረም ወር 2002 ዓ.ም በሰጠው ግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ቅር ተሰኝቸ ይግባኝ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርቤ ተሻሽሎ ተወስኖልኛል፡፡ ተጠሪ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ግብሩን አሻሽሎ ውሳኔ ከሰጠ ከሥምንት ወራት በኋላ በእጥፍ አሳድጎ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አመልካች የምሰራው የችርቻሮ ንግድ ስራ ሆኖ እያለ ጅምላ አከፋፋይ ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ አመልካች ተጨማሪ አሴት ታክስ እንድመዘገብ የተወሰነ መሆኑን ሳያሳውቅ በህጉ መሰረት አሳውቀኝ የሶስት ወር ተጨማሪ አሴት ታክስ እድከፍል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በ04/06/2005 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ስለ ገቢ ግብር ውሳኔና ተጠሪ አመልካች የሶስት ወር ተጨማሪ አሴት ታክስ እንድከፍል የሰጠው ውሳኔ ማስታወቂያ ተገቢ ነው በማለት የሰጠው ትርጉምና ውሳኔ የሕጉን መንፈስ የተከተለ ነው የሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በ14/06/2005ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር ክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የገለፅነው ሲሆን እኛም የአዲስ አበባ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ገቢ ግብር ጨምሮ የወሰነው በመጋቢት ወር 2003 ዓ/ም በገማች ኮሚቴ የአመልካችን የቀን ገቢ በማስጠናት መሆኑ እና የቀን ገቢው ብር 1700( አንድ ሺ ሰባት መቶ ብር) መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው የግብር ይግባኝ ሰሚ

ጉባኤ ተረጋግጧል፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ፍሬ ነገርና ማስረጃ ምዘና የሚመለከት በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

6. የአመልካች የንግድ እንቅስቃሴ በዓመት ከብር 500,000 ( አምስት መቶ ሺ ብር) እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 መሰረት በፈቃዱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ሲገባው እንዳልተመዘገበና አመልካች የቀን ገቢ ብር 1700 ( አንድ ሺ ሰባት መቶ ብር) እንደሆነ ተጠሪ በገማች ኮሚቴዎች በኩል ባደረገው ጥናት ተረጋግጧል ፡፡ ይህም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(1) ከነሀሴ 1 ቀን 2002 እስከ ነሃሴ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ማመልከቻ አቅርቦ መመዝገብ የነበረበት መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(1) ከነሀሴ 1 ቀን 2002 እስከ ነሃሴ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ማመልከቻ አቅርቦ መመዝገብ የነበረበት ሰው ካልተመዘገበ ፣ ለመመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብ ከሚጀምርበት የሂሳብ ጊዜ አንስቶ ታክስ ከፋይ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(3) ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚቀጥለው የሂሳብ ጊዜ ማለትም መስከረም 2003 ዓ.ም ጀምሮ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ተጠሪ ከመጋቢት ወር 2003 ዓ/ም በገማች ኮሚቴ የአመልካችን የቀን ገቢ በማስጠናት መሆኑ እና የቀን ገቢው ብር 1700( አንድ ሺ ሰባት መቶ ብር) መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ከሚያዚያ 2003 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2003 ዓ.ም አመልካች ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ . በመሆኑም ተጠሪ የሰጠው ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(1) ፣ አንቀጽ 3(3) እና አንቀጽ 16(1) /ለ/ መሰረት ያደረገ በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ ፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ማጽናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 86672

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ መቅደስ ብሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ በቀለ ተሰማ ቀረቡ

2. ዝናሽ ዘየደ በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ባአሁኑ ተጠሪዎች እና በሐናን በላይ ላይ በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡

ተጠሪዎች የተከሰሱት በሁለት ምድብ በተከፈለ ክስ ሲሆን አንደኛው ክስ ባአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበ ሁኖ ይዘቱም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 50(ለ) እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 22(11) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የንግድ ፈቃድ ቁጥር 06/64213/01/00000040 መሰረት በሬስቶራንት ንግድ ላይ ተሰማርቶ ከሕዳር 16 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ በመሆኑ በቁጥር 3313860032 በሆነ ተመዝግቦ እያለ የካቲት 11 ቀን 2004 ዓ/ም ከቀኑ በግምት 6፡05 ሰዓት በአዳማ ከተማ ቀበሌ 05 ክልል ውስጥ በሚገኘው የቤት ቁጥር 840 በሆነ የኬሮድ ባርና ሬስቶራንት ውስጥ ይታገስ አሸናፊ፣ግርማ ሚኮሬና ኮንስታብል ኢብራሂም አማን የተባሉ ሰዎች ሁለት ቅቅል ምግብና እና ሶስት ለስላሳ በአሁኗ ሁለተኛ ተጠሪና በስር ሶስተኛ ተከሳሽ በነበረ ሐናን በላይ በከል ብር 67.00 የሆነ ዋጋ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መሸጣቸውን ዘርዝሮ ተጠሪው የግል ባለንብረት በመሆናቸው የወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው በማለት ክስ ማቅረቡን የሚያሳይ ሲሆን 2ኛው ክስ ባሁኗ 2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበ ሁኖ ዝርዝር ይዘቱም ተከሳሾቹ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 55 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 609/01 አንቀጽ 50(ለ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ እንዲሁም ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የብር 67.00 ሽያጭ ደረሰኝ መቁረጥ ሲገባት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሽያጩ እንዲፈፅም በማድረጓ 1ኛውን ተጠሪ የመርዳት ወንጀል ፈፅማለች የሚል ነው፡፡ 3ኛው ክስ በስር ሶስተኛ ተከሳሽ በነበረችው ሐናን በላይ ላይ የቀረበ ሁኖ በ1ኛው ክስ በተመለከተው ጊዜና ቦታ እንዲሁም ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች ደረሰኝ ቆርጣ መስጠት ሲገባት ይህንኑ ባለመፈፀሟ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 55 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 50(ለ) ስር የተመለከተውን ተላልፋለች የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ተጠሪዎች የወንጀል አፈፃፀሙን ክደው ተከራክረው ዐ/ሕግ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን በማቅረብ አስምቷል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ መከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአቃቤ ህግ ምስክሮች ከፍለው የነበረው ገንዘብ ደረሰኝ አልተሰጠንም በሚል ምክንያት መልሰው መውሳዳቸው ሽያጭ ያለመፈፀሙን እንደሚያሳይ፣ሽያጭ ተፈጽሟል ከተባለም 1ኛ ተጠሪ የቫት ደረሸኝ አሳትሞ ለተገልጋዮች እየቆረጠ የሚሰጥ መሆኑ መረጋጡን፣ተጠሪው የሽያጭ ማሽኑን በ25/05/04 ዓ/ም ገዝተው በ01/06/2004 ዓ/ም የተረከቡ መሆኑንና ወንጀሉ የተፈጸመበት ጊዜ በ11/06/2004 ዓ/ም አንፃር ሲታይ ስልጠና እስከሚያገኙ ድረስ ጊዜው አጭር መሆኑን፣ክሱ ለአቃቤ ሕግ ምስክሮች ደረሰኝ አልተሰጠም የሚል ሁኖ በማስረጃ የተረጋገጠው ግን ምስክሮቹ በእጅ የተፃፈ ደረሰኝ ተሰጥቷቸው በማሽን የተፃፈ ደረሰኝ ካልሆነ አልንቀበልም ማለታው መሆኑን፣ደረሰኞቹ በተጨማሪ ታክስ ምጣኔው ላይ ልዩነት የሌላባቸው መሆኑንና በእጅ የሚፃፈው ደረሰኝም በተገቢው አካል ጥያቄ ቀርቦ 1ኛው ተጠሪ ያሳተሙትና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ ተጠሪዎች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው የአቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ጥርጣሬ ውስጥ ከተዋል በማለት ተጠሪዎችን በነፃ አሰናብቷዋል፡፡

በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በስር ፍርድ ቤቶች የተሠጠው የተጠሪዎች ነፃ መለቀቅ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ሲሆን የአመልካች መስሪያ ቤት አቃቤ ህግ ጥር 03 ቀን 2005 ዓ/ም የተፃፈ የሠበር ማመልከቻ ስላቀረቡ ነው፡፡ የሠበር አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪዎች ሽያጩ አልተከናወነም በሚል ነፃ ተብለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር በፅሑፍ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክከርክር ለሠበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ፈፅመዋል ተብለው የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ለማስረዳት ዐ/ሕግ ያቀረቧቸው ሁለት ምስክሮች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ኬሮድ ምግብ ቤት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ውጪ ሽያጭ መፈፀሙ የሚያሳይ ሪፖርት ደርሷቸው መስሪያ ቤቱ ወደ ቦታው በክስ በተገለጸው ጊዜ የላካቸው መሆኑን፣ወደ ቦታው ደርሰውም ሶስት ምግብና ሶስት ለስላሳ በማዘዝ ከተጠቀሙ በኋላ ብር 100.00 ሂሳብ ክስር 3ኛ ተከሳሽ ለነበረችው አስተናጋጅ ሰጥተው እሷም ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ከሰጠች በኋላ መልስ ብር 33.00 ያለደረሰኝ የመለሰችላቸው መሆኑን፣1ኛ ተጠሪም በጊዜው በቦታው ላይ እንዳልነበርና በኋላ ከመጣ በኋላ ምስክሮቹ ሲጠይቁትም ለጠየቀን እንሰጣለን ብሎ እንደመለሰላቸውና ከዚህ በኋላ ተከሳሾችን በቁጥጥር ስር ያዋሏቸው መሆኑን ነው፡፡ተጠሪዎች ያቀረቧቸው መከላከያ ምስክሮች ደግሞ ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ምግብ ቤት በአስተናጋጅነት የሚሰጡ ሁነው በክሱ በተጠቀሰው ጊዜ ሶስት ሰዎች ወደ ምግብ ቤቱ መጥተው ምግብና ለስላሳ አዝዘው ከተጠቀሙ በኋላ የማሽን ደረሰኝ 3ኛ ተከሰሽ የሆነችውን አስተናጋጅ አምጪልኝ በማለት ሲጠይቋት ማሽኑ ስራ ስላልጀመረ በእጅ የሚሞላ ደረሰኝ አመጣላችኋለሁ ስትል በእጅ የሚፃፍ ደረሰኝ አንፈልግም፣የማሽን ነው እንጂ በማለት እምቢ ብለው ሄደው ከሶስት ደቂቃ በኋላ ተመልሰው በመምጣት ለአገልግሎቱ የከፈሉትን ብር

100.00 መልስ መውሰዳቸውን፣ቤቱ በእጅ የተጻፈ ደረሰኝ እንደሚጠቀምና ይህንኑ ደረሰኝ ምስክሮቹ ወስደው ቤቱን ያሸጉና ስራው የተከለከለ መሆኑን ሲሆን የሰነድ ማስረጃዎች ደግሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ አስመልክቶ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በህዳር 30 ቀን 2004 ዓ/ም ማስታወቂያ መውጣቱን፣1ኛው ተጠሪ በ08/05/2004 እና 09/06/2004 ዓ/ም ለተፈፀሙ ሽያጮችም ደረሰኝ መቆረጣቸውን፣ተጠሪው ማሽኑን በ25/05/2004 ዓ/ም ገዝተው በ01/06/2004 ዓ/ም መረከባቸውን እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ፍቃድ ከምስራቅ ሸዋ ዞን ገቢዎች ፅ/ቤት አግኝተው ደረሰኙን አሳትመው ወደ ስራው የገቡ መሆኑ በሰውና በሰነድ ማስረጃዎች መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሯል፡፡

እንግዲህ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አጣርቶና ማስረጃን መዝኖ የደረሰባቸው ድምዳሜዎች ከላይ የተጠቀሱት ሲሆን ተመሳሳይ ስልጣን ያለው የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤትን የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ መቀበሉን የክርክሩ ሂደት ያስገነዝባል፡፡በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ስለሌለው ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ስለመረጋገጣቸው የተጠቀሱትን ነጥቦች እንዳሉ የሚቀበላቸው ይሆናል፡፡እዚህን ይዘን ወደ ሕጉ ስንመጣም ተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ የሚገዛው ራሱን በቻለ ሕግ ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 285/1994 እና ከማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 609/2001 ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡እነዚህ ሕጎች የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ተግባራትን ዘርዝረው ማስቀመጣቸውን ድንጋጌዎቹ ያሳያሉ፡፡አዋጆቹን የማስፈፀም ስልጣንና ተግባርም የፌዴራል መንግስት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 99 እና ይህንኑ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 03 ቀን 1994 ዓ/ም ባደረጉት ሁለተኛ መደበኛ የጋራ ስብሰባ መወሰኑ የሚታወቅ ነው፡፡በመሆኑም የአዋጆችን የአፈጻጸም የመቆጣጠር ስልጣንን መሰረት አድርጎ የተጠሪዎች ጠበቃ ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡የተጨማሪ እሴት ሽያጭ ተከናወነ የሚባልበትን አግባብም በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 11(1)(2)፣ 22(1) እና (3) በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው በግልጽ ተመልክቷል፡፡የአዋጁ አንቀጽ 11(1) በመርህ ደረጃ ሽያጭ ተከናወነ የሚባለው ለግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሲሰጥ ነው በሚል የሚያስቀምጥ ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ እቃዎቹ ለተረካቢው ዝግጁ ሁነው መቀመጣቸው፣የእቃዎቹ ርክርብ ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ መፈፀም ወይም የአገልግሎት መስጠት፣እንዲሁም የእቃዎችን ርክክብ ማጓጓዝን የሚያካትት ሲሆን የእቃዎችን ማጓጓዝ ሲጀመር ሽያጭ ተከናወነ ብሎ ለመደምደም የሚቻል መሆኑን በልዩ ሁኔታነት ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ መረዳት የሚቻለው ሽያጭ ተከናወነ ለማለት ለተከናወነው ግብይት ሂሳብ መክፈሉ ወይም አለመከፈሉ በቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ ሳይሆን ሕጉ ትኩረት የሚያደረገው እቃዎቹ ለተረካቢው ዝግጁ ሁነው በተቀመጡ ጊዜ አገልግሎቶች በሚሰጡበት እና የመሳሳሉት ተግባራት መፈጸማቸው ላይ ነው፡፡በመሆኑም እነዚህ ተግባራት በሚፈጽሙበት ጊዜ የተጨማሪ እሴት ደረሰኝ ባይቆረጥም እንኳን ሽያጩ እንደተከናወነ ሕጉ እንደሚቆጥር የድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ማእቀፍ ሽያጭ ተከናወነ የሚባልባቸውን ሁኔታዎችን ለይቶ አስቀምጦ እያለ በዚህ ረገድ ልዩ ሕግ የደነገገው ነገር እንደሌለ በመቁጠር በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለሽያጭ የሚገዙትን ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ተፈጻሚ ማድረጉ አግባብነት ያልነበረው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ቀጥሎ የተመለከትነው ተጠሪዎች ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ናቸው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ውጤቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑ ነው። በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልፅ ደንግጓል።እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል።በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎችን ነፃ በማድረግ ሊወሰን የቻለው ሽያጩ አልተከናወነም በሚል ብቸኛ ምክንያት ሳይሆን የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በእጅ የተፃፈ የቫት ደረሰኝ አንቀበልም ማለታቸው በተጠሪዎች የመከላከያ ማስረጃዎች መረጋገጡን ተቀብሎ 1ኛው ተጠሪ ለቫት ከተመዘገበበት፣ማሽኑን ከገዙበትና ከተረከቡት ጊዜ አንፃር ሲታይ ድርጊቱ ተፈጸመ የተባለበት ጊዜ አጭርና ለማሽኑ አጠቃቀም ስልጠና የሚያስፈልግ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ጭምር ነው።ከዚህም መረዳት የሚቻለው ማሽኑ እያለ ሕጋዊነቱ በተረጋገጠው ደረሰሠኝ በእጅ ተፅፎ ለአቃቤ ሕግ ምስክሮች የሽያጭ ደረሰኙ ሊሰጥ የነበረ መሆኑ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች መረጋገጡን ነው።እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች በወቅቱ ሽያጩን ያለቫት ደረሠኝ ለማከናወን ፍላጎትና ዝግጁነት የነበራቸውና የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም የሓሳብ ክፍላቸው ተሟልቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም።በእርግጥ ለቫት የተመዘገበና ማሽኑን የተረከበ የቫት ተመዝጋቢ ሽያጩን ማከናወን ያለበት በማሽኑ ደረሰኝ መሆኑ በሚንስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 139/1999 የተደነገገ ሲሆን ማሽኑ ጋር ተገቢውን ስልጠና መውሰድም ግዴታ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ማሽኑ ገብቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከማሽኑ አሰራር ጋር ባለመታዋወቅ በእጅ በተፃፈ ሕጋዊ ደረሰኝ ሽያጩን ያከናወነ ሰው በአቃቤ ሕግ በኩል በቀረበው ክስ አቀራረብ አይነት በወንጀል እንዲጠየቅ ማድረግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (2)፣58 (3) ስር የተመለከቱትን መርሆዎች የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል አይደለም።በመዝገቡ ከተያዘውና በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠው የጉዳዩ ልዩ ባህርይ ስንነሳ ተጠሪዎች የወንጀል መስራት ሓሳብ ነበራቸው ለማለት የሚያስችል የፍሬ ነገር ምክንያት አላገኘንም።ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ያረጋገጧቸው ነጥቦች በዚህ ችሎት የሚለወጡበትን አግባብ ስላላገኘንና በዚህ ረገድ የቀረቡት የአመልካች የቅሬታ ነጥቦች የማስረጃ ምዘና እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የማያሟሉ ሁነው ስለአገኘናቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎችን በነፃ በማሰናበት የሰጡት የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል።

## ው ሣ ኔ

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13453 መስከረም 10 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 152242 ህዳር 27 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ጸንቷል።
2. ተጠሪዎች በነፃ እንዲሰናበቱ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 89640

መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን-የሐረር መቆጣጠሪያ ጣቢያ- ዐ/ሕግ ጌቱ ቀዎች ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሰይፈዲን አብዱልቃድር ጠበቃ ሻምበል ተሾመ ደምሴ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጉምሩክ ሕግንና አፈጻጸሙን መሰረት ባላደረገ መንገድ መኪናው ተይዞ ለቆየበት ጊዜ ይገኝ የነበረውን ገቢ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረቱት ክስ ይዘቱ ባጭሩ፡- ኮድ 3-00700 ሐረ ላንድ ክሩዘር የጭነት መኪና የሆነ ተሽከርካሪያቸውን በቆመበትና ምንም የኮንትሮባንድ ድርጊት ሳይፈፅም ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም አመልካች ከሕግ ውጪ መያዙንና ሊለቅ ባለመቻሉ በፍርድ ቤት ክስ መስርተው መኪናው የተያዘው ከሕግ ውጪ መሆኑ ተረጋግጦላቸው መኪናው እንዲለቀቅ እስከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተወሰነላቸውና መኪናውን መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ/ም በፍርድ ኃይል መረከባቸውን፣በዚህ ጊዜ ውስጥ ሊያገኙ ይችሉ የነበረው የቀን ገቢ ብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) ሁኖ በድምሩ የሁለት አመት ከስድስት ወራት ብር 450,000.00 (አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ገቢ የቀረባቸው መሆኑን ገልጸው ይህንኑ የተቋረጠባቸውን ገቢ አመልካች ከተለያዩ ወጪና ኪሳራ ጋር ጭምር እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርቧል፡፡በክርክሩም ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑና መኪናው የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያከናወነው ተግባር መሆኑን፣የመኪናው ገቢም ቢሆን በተጠሪ የተገለጸው ሳይሆን ከክፍሉ ገቢዎች ባለስልጣን የተሰጠው ማስረጃ የሚያረጋግጠው ብር 3000.00 በአመት የሚያገኘው መሆኑንና በዚህ ሂሳብ ሲሰላም መኪናው ለቆመበት ጊዜ ከብር 10,500.00 (አስር ሺህ አምስት መቶ ብር) በላይ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል

ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አመልካች አለኝ የሚለውና ከክፍሉ የገቢዎች ባለስልጣን የመኪናው አመታዊ የተጣራ ገቢ ብር 3000.00 ስለመሆኑ የሚገልጸውን ማስረጃ ውድቅ ከአደረገ በኋላ የተጠሪ ምስክሮች የሰጡትን ቃል መሰረት በማድረግ ገቢው በቀን ብር 500.00 መሆኑን ተቀብሎና መኪናው ስራ ሊሰራባቸው የማይችላቸውን የእሁድ ቀናት ቀንሶ በጠቅላላው ብር 349,500.00 (ሶስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ብር) ተጠሪ የተቋረጠባቸው መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ይህንኑ ገንዘብ በታሪፉ መሰረት ከዳኝነት ገንዘብና ከ10% የጠበቃ አበል ጋር አመልካች እንዲከፍላቸው ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለሐረሪ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሚያዚያ 10 ቀን 2005 ዓ/ም በጻፉት አስር ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ይዘቱም ባጭሩ፡- የተጠሪ ክሱ የተመሰረተው በሕጉ አግባብ የውክልና ስልጣን ለተጠሪ ጠበቃ ሳይሰጥ መሆኑን፣አመልካች በሕጉ አግባብ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የፈፀመው ድርጊት ስለመሆኑ ገልፆ ከመከራከሩም በተጨማሪ መኪናው የሚያስገኘው አመታዊ ገቢን የሚያሳየው ማስረጃ ከሚመለከተው የገቢዎች ባለስልጣን ቀርቦ እያለ ማስረጃው ውድቅ መደረጉና የተጠሪ የሠው ምስክሮች ቃል ተቀባይነት አግኝቶ በቀን ብር 500.00 መሰረት ተደርጎ ካሳው መሰላቱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 እና 2011 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተድርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ የአመልካች የሰነድ ማስረጃ ውድቅ ተደርጎ በተጠሪ የሰው ምስክሮች ብቻ ካሳው መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም ? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ ያላግባብ በአመልካች ተይዟል በሚል ክስ አቅርበው አመልካች ከሕግ አግባብ ውጪ የያዘው መሆኑ በፍርድ ተረጋግጦ መኪናው እንዲለቀቅላቸውና መኪናው ተይዞ ለቆመበት ጊዜ ገቢ እንዲከፈላቸው ተጠሪ ወደፊት ክስ አቅርበው የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው መኪናው እንዲለቀቅላቸው እና የጉዳት ኪሳራውን የመጠየቅ መብታቸው ተጠብቆ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሰጥቶ ውሳኔው እስከዚህ ሰበር ችሎት ደርሶ የጸና መሆኑን የሰ/መ/ቁጥር 75913 የሚያረጋግጠው ጉዳይ መሆኑን፣አመልካች አሁን አጥብቆ የሚከራከረው የጉዳት ካሳ መጠን የተሰላበት አግባብ ከሕግ ውጪ የተጠሪ የሠው ምስክሮች ቃል ብቻ መሰረት ተደርጎና ከሚመለከተው አካል የቀረበው የአመልካች የሰነድ ማስረጃ ግን ውድቅ ተደርጎ ስለመሆኑ ዘርዝሮ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለጉዳቱ ሀላፊ ነው ያሉት ቀድሞ በፍርድ ያለቀውን ጉዳይ መሰረት በማድረግ በመሆኑና አመልካችም የተጠሪን ክስ ነጣጥሎ በማቅረብ ላይ ግልጽ ቅሬታ ያላቀረበበት ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብም በጭብጥነት ያልተያዘ በመሆኑ የኃላፊነት ጭብጥ በዚህ ችሎት አሁን የሚታይበትን አግባብ አላገኘንም፡፡በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ነጥብ የጉዳት ካሳ መጠኑ የተወሰነበት

መንገድ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ስለሆነ ይህንኑ ጭብጥ ግንዛቤ ውስጥ አስገብተን ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመለክተናል፡፡በመሰረቱ ለደረሰው ጉዳት አላፊ መሆኑ በህግ የታወቀ ሰው የጉዳት ኪሳራ መክፈል ያለበት ሲሆን ጉዳት የደረሰበት ሰው የሚካሰውም ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሳራ በመክፈል እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ/ 2090(1) ተመልክቷል፡፡ የኪሳራው ልክም ሀላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ በመመዛዘን መሆን እንደሚገባ የፍ/ህ/ቁጥር 2091 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በሚቀርቡለት ማስረጃዎች የጉዳቱን መጠንና ሊከፈል የሚገባውን ካሳ መጠን አመዛዝኖ በህጉ መሰረት መወሰን የሚገባው ስለሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141፣2152 እና 2153 ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ሲሆን ጉዳቱ ያስከተለውን ኪሳራ በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነም በፍ/ህ/ቁ/2102 በተመለከተው አግባብ በርትዕ ለመወሰን እንደሚቻል ሕጉ ያስቀምጣል፡፡ እንዲህ ሲደረግ ግን ለጉዳዩ የቀረቡት ማስረጃዎች ለጉዳዩ አግባብነት፣ጥንካሬና ክብደት ያላቸው መሆኑን በቅድሚያ ማረጋግጥን የግድ ይሏል፡፡በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ማስረጃዎቹ በሕጉ አግባብ ከቀረቡለት ደግሞ ማስረጃዎችን የማይቀበልበትን ሕጋዊ ምክንት በግልጽ ማስፈር ያለበት መሆኑን የሚሰጠው ምክንያትም ሕጋዊ መሰረት ያለው መሆን ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 138፣ 180 (1) እና ሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ከሚደነገጉት የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የጉዳት ካሳ ግምቱን የወሰነው በተጠሪ በኩል የቀረቡትን የሰው ምስክሮች ቃል ተቀብሎ በአንጻሩ ግን አመልካች በሕጉ አግባብ በመኪናው የአመታዊ ገቢ ግብር ተጠሪ እንደሚከፍሉበት ያሳያል የተባለውን የሰነድ ማስረጃ በማለፍ ነው፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበዉ ይህ ማስረጃ በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያጣበት ሕጋዊ ምክንያት ግን በግልጽ በውሳኔው ላይ አልሰፈረም፡፡በአንድ የመንግስት ባለስልጣን የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ ደግሞ የማስረጃነት ዋጋ ሳይሰጠው የሚታለፍበት አግባብ በሕጉ መሠረት ተቃውሞ ቀርቦበት ዋጋ የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2010 እና 2011 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 140 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ጉዳዩ በመኪና ገቢ የግብር መጠን የሚጣልበትን አግባብ የሚያስረዳ ሙያዊ ምስክርነት ማስቀርብን የሚያስፈልግ መሆኑንም የክርክሩ ባህርይ ያስገነዝባል፡፡እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 ድንጋጌ አኳያ ከሚመለከተው አካል የሙያ ምስክር አስቀርቦ ከተጠሪ ምስከሮች ቃል፣አመልካች አለኝ ከሚለው የሰነድ ማስረጃ ይዘት ጋር ማመዛዘንና ዳኝነት መስጠትን የግድ የሚል ነው፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎችን ትክክለኛና ሕጋዊ ያለመሆናቸውን በተገቢው መንገድ ሳያረጋግጥ ለተጠሪ ምስክሮች ቃል ብቻ ክብደት ሰጥቶ የጉዳት ካሳ መጠኑን መወሰኑ የማስረጃ አቀባበል መርህንና  የጉዳት ካሳ መጠን መወሰን ያለበት ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሁኖ ተመዛዝኖ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 እና 2091 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን መርህ የሚጥስ ሁኖ አግኝተናል፡፡በሌላ በኩል የተጠሪ መኪና ለበርካታ ወራት ያለስራ በአመልካች ሕገ ወጥ ተግባር መቆሙ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ የተቋረጠባቸው ገቢ የለም ብሎ ለማለት የሚቻልበት አግባብም የለም፡፡ስለሆነም ለካሳው መጠን አወሳሰን ይረዳ ዘንድ በተጨማሪነት ሊጣሩ የሚገባቸው ፍሬ ነገሮች ያሉ ሁነው አግኝተናል፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም፡-

1. አመልካች የተጠሪን መኪና አመታዊ የተጣራና ግብር የሚከፈልበትን የገቢ መጠን ያሳያል በማለት ያቀረበው ሰነድ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2010 መሰረት ተቃውሞ የሚቀርብበትና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2011 አግባብ የማስረጃነት ዋጋ የማይሰጥበት ሕጋዊ ምክንያት አለ? ወይስ የለም?
2. የተጠሪ መኪና አመታዊ የተጣራ ገቢ ብር 3000.00 ተብሎ የተወሰነበት አግባብ ሕጋዊ መሰረት አለው? ወይስ የለውም? ፤የሚመለከተው የክፍሉ የገቢዎች ባለስልጣን የተጠሪን አይነት መኪና ላይ ግብር የሚያስከፍልበት አሰራር ምንድው?
3. አመልካች የተጠሪ የመኪና የተጣራ አመታዊ ገቢ በማለት የገለፀው ብር 3000.00 የሆነው ተጠሪ በሕጉ አግባብ ባሳወቁት የገቢ መጠን ነው? ወይስ ባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተገቢውን ማጣራትና አሰራር ተከትሎ በሰጠው ውሳኔ ነው? የሚሉትና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የፍሬ ነገር ነጥቦች በተገቢው መንገድ በፍርድ ቤቱ ሊቀርቡ በሚገባቸው ማስረጃዎች ሊጣሩ የሚገባቸው ሁነው አግኝተናል፡፡

እነዚህ ፍሬ ነገሮች በሕጉ አግባብ ሳይጣሩና ሳይሚሉና የጉዳት ካሳ መጠኑ መወሰን የጉዳት ካሳ አወሳሰን መሰረታዊ ዓላማና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን የሚጥስ መሆኑን ተረድተናል፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ ስላላገኘነው ውሳኔው በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወሰንናልወ፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 09627 በቀን 22/04/2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 02400 መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች በተጠሪው መኪና ላይ በፈፀመው ሕገ ወጥ ተግባር ለደረሰው ጉዳት ሀላፊ ነው በሚል የሠጡት የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብለናል፤ጸንቷል፡፡
3. የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ ግን በተገቢው መንገድ ለጉዳዩ አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ሳይጣራ የተሠጠ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡በመሆኑም የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 09627 ቀጥሎ በፍርደ ሐተታው ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 የተጠቀሱትን ነጥቦችንና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ነጥቦችን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች ከሚመለከተው የክፍሉ የገቢዎች ባለስልጣን እንዲቀርቡ በማድረግና የባለሙያ አስተያየት ሁሉ በመስማት በጉዳዩ ላይ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገወ ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

# ንብረት

የሰ/መ/ቁ. 85979

መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የሐረር (ደ/ሳ) ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን - አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** ወ/ሮ ማንያህልሻል አበራ - አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው በሐረር ክልል የከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የመቃብር ቤት ግምት ይከፈለኝ በማለት የቀረበን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሐረሪ ሕዝብ ክልል የከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በሐረር ከተማ በሚገኘው ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስትያን ግቢ ውስጥ የመቃብር ቤት ለመስራት እንዲፈቀድልኝ ጠይቄ የመቃብር ቤት እንድሰራ ስለተፈቀደልኝ ለእኔና ለዘመዶቼ የቀብር ስርዓት የሚፈፀምበት ቤት የመቃብር ቤት በብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ሰርቻለሁ፡፡ ሆኖም ቤተክርስቲያኗ ኃይማኖትሽን የለወጥሽ በመሆኑ በመቃብር ቤቱ ለመጠቀም አትችይም በማለት በግልፅ ደብዳቤ አሳውቆኛል፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃይማኖት ተከታይ በነበርኩበት ጊዜ የሰራሁትን የመቃብር ቤት ያለምንም ካሳና ግምት ለመልቀቅ የውል ግዴታ ያለገባሁ በመሆኑ የመቃብር ቤቱን ለመስራት ያወጣሁትን ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) እንድከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል መቃወሚያው በብይን ታልፏል፡፡ አመልካች ተጠሪ የመቃብር ቤት ሰርታለች፡፡ ተጠሪ በሰራችው የመቃብር ቤት የዘመዶቿ ስርዓተ ቀብር ተፈፀሞ የዘመዶቿ አጽም አርፎበት ይገኛል፡፡ ተጠሪ (ከሳሽ) ኃይማኖቷን የለወጠች በመሆኑ በመቃብር ቤቱ የመጠቀም መብት የላትም፡፡ የመቃብር ቤት ግምት የመክፈል ያደረግነው ውል የሌለ በመሆኑ ክሱ የእምነቱን መሰረታዊ ቀኖናና አሰራር የሚፃረር በመሆኑ የመቃብር ቤት ግምት የመክፈል ኃላፊነት የለብንም፡፡ ተጠሪ የሰራችው ቤት ግምትም ከብር 13,000 (አስራ ሶስት ሺህ ብር) የሚበልጥ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራቀ ኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካች ተጠሪ የሰራችውን የቤት ግምት የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በመቃብር ቤቱ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ መጋቢት 26 ቀን 2003 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ መቃብር ቤቱ በባለሙያ ብር 50,153.40 (ሃምሳ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከአርባ

ሳንቲም) የተገመተ በመሆኑ አመልካች ይህንን የመቃብር ቤቱን ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል። የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 ሰርዞታል።

አመልካች ታህሳስ 25 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በነበረችበት ወቅት ስሞት ስርዓተ ቀብሬ መፈፀሚያ ይሆናል በማለት መቃብር ቤት እንድትሰራ ፈቃድ ጠይቃ ተፈቅዶላታል። ተጠሪ በመቃብር ቤቱ ስርዓተ ቀብሯ ሊፈፀም የሚችለው የእምነቱ ተከታይ ሆና ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ ነው። ተጠሪ ኃይማኖቷን ከቀየረች በቤተክርስቲያኑ የመቃብር ሥፍራ የሌላ እምነት ተከታይ የሆነ ሰው የማይቀበር በመሆኑ በመቃብር ቤቱ ስርዓት ቀብሯ ሊፈፀም አይችልም። አመልካች ይህንን ለተጠሪ ማሳወቁ ተገቢ ነው። ነገር ግን ፍ/ቤቱ ቦታው የመቃብር ቦታና የእምነቱ ጋር የተያያዘ መሆኑን ሳያገናዝብ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ሕ/ቁጥር 1179 በመጥቀስ የመቃብር ቤት ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

ተጠሪ የካቲት 4 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ መልስ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ከሰራችው የመቃብር ቤት ውስጥ የቀብር ስርዓት ያልተፈፀመበት ቦታና ክፍል ግምት አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠው 26-1-2003 ዓ/ም ነው። ይህ ውሳኔ አመልካች ይግባኝ ብሎ አላሻረም። ስለዚህ ቤቱ ከተገመተ በኋላ ያቀረበው ይግባኝ በአፈፃፀም እንደቀረበ ይግባኝ መታየት ያለበት ስለሆነ መዝገቡ ይዘጋልኝ። ተጠሪ የገነባቸውን የመቃብር ቤት እንዳትጠቀም አመልካች የከለከለ በመሆኑ፣ የቤቱን ግምት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ሰበሰር በጽሁፍና በቃል ባደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ተጠሪ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሰራችውን የመቃብር ቤት ግምት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይም አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ተጠሪ አመልካችን የሰበር አቤቱታ በመቃወም ያቀረበውን ክርክር ህጋዊነት ተመልክተናል። አመልካች የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ አመልካች ተጠሪ የሰራተኛውን የመቃብር ቤት ግምት የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብሎ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የስር ፍ/ቤት በዚያው መዝገብ ንብረቱን አስገምቶ አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው የመቃብር ቤት ግምት ብር 50,153.40 (ሃምሳ ሺህ አንድ መቶ አምሳ ሶስት ብር ከሰርባ ሳንቲም ነው) በማለት መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በማጠቃለል ይግባኝ ማቅረቡና ይግባኙ ውድቅ ሲሆንበት የሰበር አቤቱታ ማቅረቡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 327 ንዑስ አንቀጽ 3 የመጀመሪያውን ፓራግራፍ መሰረት ያደረገ ነው። ተጠሪ ይግባኙ የአፈፃፀም ይግባኝ ነው በማለት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካች ለክሱ ኃላፊ መሆኑንና ለተጠሪ መክፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን የወሰነው የተጠሪንና የአመልካችን ክስ ባስተናገደበት የመዝገብ ቁጥር 06816 መሆኑን ተረድተናል። በሌላ በኩል ተጠሪ ፍርዱን ለማስፈፀም ያስከፈተችው የአፈፃፀም መዝገብ

ቁጥሩ 20166 መሆኑን ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ያቀረበውን መቃወሚያ አልተቀበልነውም፡፡

2. ዋናውን ጭብጥ በተመለከተ፣ ተጠሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ተከታይ በነበረችበት ወቅት የኃይማኖቱን መሰረታዊ ቀኖና ስርዓት መሰረት በማድረግ በምትሞትበት ጊዜ የእሷና የዘመዶቿ አስክሬን የሚያርፍበትና ሥርዓተ ቀብር የሚፈፀምበት የመቃብር ቤት በአመልካች ግቢ ውስጥ ለመስራት እንዲፈቀድላት ጠይቃ የመቃብር ቤት እንድትገነባ ልዩ ፈቃድ በመስጠት የተጠሪን "privilege" ጠብቆላታል፡፡ ተጠሪም በአመልካች በተሰጣት ልዩ ፈቃድ መሰረት መቃብር ቤቱን በአመልካች ግቢ ውስጥ በራሷ ወጭ የሰራች መሆኑ ግራ ቀኙ የሚተማመኑበት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ እንደዚሁም ተጠሪ በሰራችው የመቃብር ቤት ውስጥ የኢትዮጲያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ የተጠሪ ዘመዶች አስክሬን የተቀበረ መሆኑና አሁንም በመቃብር ቤቱ ውስጥ የተጠሪ ዘመዶች አፅም ያረፈበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

አመልካችና ተጠሪን የሚያከራክረው ጭብጥ በአሁኑ ወቅት የተለየ ኃይመኖት ተከታይ የሆነችው ተጠሪ በአመልካች በተሰጣት ልዩ ፈቃድ መሰረት በሰራችው የመቃብር ቤት ስትሞት የመቀበር መብት ይኖራታል ወይስ አይኖራትም? ተጠሪ በመቃብር ቤቱ የመቀበር መብት የላትም ከተባለ አመልካች የመቃብር ቤቱን ግምት ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነጥብ ነው፡፡

ማንኛውም ሰው የማሰብ የሕሊናና የኃይማኖት ነፃነት ያለው መሆኑንና ይህም መብት የመረጠውን ኃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ የመቀበል ኃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎቹ ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን እንደሚያካትት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ማንኛመው ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል የማይቻል መሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይህ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠው የእምነትና የኃይማኖት ነፃነት፣ ማናቸውም ሰው በሚያምንበት እምነትና በሚከተለው ኃይማኖት ቀኖና ስርዓት መሰረት በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ መንፈሳዊ ፀጋ አገኝባቸዋለሁ የሚላቸውን የበጎ አድራጎት ተግባራቶችንና ሌሎች ስራዎችን የማከናወን ነፃነትን ጭምር የሚመለከት ነው፡፡

በዚህ መሰረት ተጠሪ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃይማኖት ተከታይ በነበረችበት ወቅት በአመልካች ግቢ ውስጥ የመቃብር ቤት እንድትገነባ ልዩ ፈቃድ የተሰጣት እሷም የመቃብር ቤቱን በግል ወጭዋ የገነባችው አመልካች የሚያረምደውን ኃይማኖታዊ ቀኖና ሥርዓት በማመንና ተገዥ በመሆን እንደነበር ከግራ ቀኙ ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች የመቃብር ቤቱን እንድሰራ ልዩ ፈቃድና ክብር የተሰጣት የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ተከታይ አማኝ ስለነበረች ነው፡፡ አመልካች ትከተለው የነበረው የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃይማኖታዊ ቀኖና ሥርዓት የመለወጥና የመረጠችውን ኃይማኖት የመያዝና የማምለክ የመተግበር ነፃነት ያላት መሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1ና ንዑስ አንቀጽ 3 እንደዚሁም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች ሁለተናዊ መግለጫ አንቀጽ 18 እና ዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 18(1) ድንጋጌዎች

የተረጋገጠላት በመሆኑ ኃይማኖቷን በመለወጥና የምታምንበትን ኃይማኖት የመያዝ መብቷን ማረጋገጧ የሚገድብ አይደለም፡፡ አመልካችም ይህንን የተጠሪን መብትና ነፃነት የሚገድብ ደብዳቤ ያልፃፈና ሌሎች የተጠሪን መብት የሚገድቡ ተግባሮችን ያልፈፀመ መሆኑን ተረድተናል፡፡

3. ተጠሪ የአመልካችን ኃይማኖታዊ ቀኖና ሥርዓት መከተሏን አማኝ መሆኗን በማቆም የሌላ ኃይማኖት ወይም እምነት ተከታይ መሆኗን በመካድ ያቀረበችው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ የአመልካችን የሚያራምደውን ኃይማኖትና መንፈሳዊ አስተምሮት በመተው የሌላ ኃይማኖት ወይም እምነት ተከታይ መሆኗ ካልተካደ ተጠሪ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታይ አማኝ የነበረች በመሆኑ ምክንያት አመልካች ሰጥቷት የነበረው ክብር መብትና ጥቅም በነበረው ሁኔታ እንዲቀጥልላት ለመጠየቅ አትችልም፡፡ ተጠሪ የሌላ እምነትና ኃይማኖት ተከታይ መሆን ስትጀምር ከአመልካች ጋር የነበራት ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ ትስስርና ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ይቋረጣል፡፡ አመልካች በቅጥር ግቢው ውስጥ በሚገኘው የመካነ መቃብር ቦታ ተጠሪ የመቃብር ቤት እንድትሰራ ልዩ ፈቃድ የሰጣት ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራትን የኃይማኖትና የእምነት ትስስር መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በአመልካች ቅጥር ግቢ ውስጥ ተጠሪ የመቃብር ቤት የገነባችው ከአመልካች ጋር በነበራት ጥብቅ የሆነ ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ ግንኙነት ምክንያት እንጂ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በገንዘብ የሚተመን የኢኮኖሚያዊ ውልና ስምምነትን መሰረት በማድረግ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች በቅጥር ግቢው የሚገኘው የመካነ መቃብር ቦታ ላይ ተጠሪ ቤት እንድትሰራ የሰጠው ልዩ ፈቃድና ተጠሪም በዚህ ፍቃድ መሰረት የሰራችው የመቃብር ቤት ከኃይማኖቱና ከእምነቱ ተለይቶ የሚታይ የሚፈፀምና የሚተገበር ተራ የሆነ የውል ወይም የንብረት ግኑኝነት ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የኃይማኖቴና የእምነቴ ተከታይ ናት በሚል ምክንያት የሰጣትን ልዩ ፈቃድ መሰረት በማድረግ በአመልካች ቅጥር ግቢ ውስጥ በሰራችው የመቃብር ቤት ላይ ያላት መብትና ጥቅም፣ ተጠሪ ኃይማኖቷን ከለወጠችና የሌላ እምነት ተከታይ ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ይቋረጣል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲመዘን አመልካች ትከተለው የነበረውን ኃይማኖትና እምነት በመለወጥ ሌላ ኃይማኖት ተከታይ በመሆነሽ በአመልካች ግቢ ውስጥ በሰራሽው የመቃብር ቤት የመጠቀምና ስትሞችም በመቃብር ቤቱ የመቀበር መብት የለሽም በማለት ለተጠሪ የፃፈው ደብዳቤ የህገ-መንግስቱን አንቀፅ 11 አንቀፅ 27 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና ተገቢነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. ከላይ በተለፁት የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎችና በሌሎች ዓለም አቀፍ የስብዓዊ መብቶች ህግጋት ድንጋጌዎች የተረጋገጠለትን ሃይማኖቱን የመለወጥና የሚያምንበትን ኃይማኖት የመያዝ የማመለክና የመተግበር መብቱን ዕውን ያደረገ ሰው በፊት ሲከተለው የነበረውን ኃይማኖትና እምነት መሰረት በማድረግ ለሰራቸው ተግባራት እንዲፈርሱለት እንዲመለሱለት ወይም ለሰራቸው ተግባሮች ግምት እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም? የሚለውን ነጥብ መታየት አለበት፡፡ የኃይማኖትና የእምነት ነፃነትና ኃይማኖትንና እምነትን የመለወጥ መብት አንድ ሰው በፊት ይከተለው የነበረውን ኃይማኖትና እምነት መሰረት በማድረግ ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ ግዴታውን ለመወጣትና መንፈሳዊ ፀጋና ቡራኬ ለመጎናፀፍ በማሰብ የሰጣቸው ስጦታዎች ወይም ወጪቸውን በመሸፈን የሰራቸው የኃይማኖትና የእምነት ማምለኪያና ኃይመኖሮታዊ ትምህርት ማስተማሪያ ቤቶች ወይም በእምነቱ መሰረት የቀብር ስርዓት መፈፀሚያ እንዲሆን በማሰብ የሰራው

ቤት እንዲመለስለት ወይም እንዲፈርስ ወይም ግምታቸው እንዲከፈለው የመጠየቅ መብትን የሚያስከትል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የአመልካች ኃይማኖታዊ አስተምሮትና እምነት ተከታይ በነበረችበት ወቅት ለእሷና ለዘመዶቿ ስርዓተ ቀብር ማስፈጸሚያ ይሆናል በሚል ዕምነት የሰራችውን የመቃብር ቤት ግምት አመልካች እንዲከፍላት ለመጠየቅ የሚያስችላት ህጋዊ መሰረት የለም፡፡ አመልካችም ተጠሪ የኃይማኖቱ ተከታይ በነበረችበት ጊዜ የኃይማኖቱን መሰረታዊ  ቀኖና ስርዓት መሰረት በማድረግ ለስርዓተ ቀብሬ ማስፈፀሚያ ይሆናል በሚል ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ እምነት ወጭውን ችላ በቅጥር ግቢው ውስጥ የሰራችውን የመቃብር ቤት ዋጋና ግምት የመክፈል ኃላፊነት የለበትም፡፡

የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለውሳኔቸው መሰረት በማድረግ የጠቀሱት የፍታብሄር ህግ ቁጥር 1179 ድንጋጌዎች ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ እምነት መሰረት በአንድ ኃይማኖታዊ ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ የተገነባ የመቃብር ቤት ላይ ተጠቃሽም ሆነ ተፈፃሚ የሚሆኑ አይደሉም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1179 ድንጋጌዎች ይዘት ፣ ዓላማና ተፈፃሚነት ወስጥ፣ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 11 እና አንቀፅ 27 ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር ሳይተረጉሙ፣ አመልካች ተጠሪ ለእኔና ለዘመዶቼ ስርዓተ ቀብር ማስፈፀሚያ ይሆናል በማለት የሰራችውን የመቃብር ቤት ግምት ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሐረሪ ክልል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06816 መጋቢት 20 ቀን 1983 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔና መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02332 የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ በቅጥር ግቢው ውስጥ የገነባችውን የመቃብር ቤት ግምት የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 88798

ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡ አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች**፦ አቶ ሙሉ አብርሃ ገ/ሕይወት ጠበቃ ብናልፈው ነጋ ቀረቡ

**ተጠሪ**፦1. በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል

2.አቶ ወንድሙ አይፈዬ

3.አቶ ዳንኤል ገብሩ

ጠበቃ በላቸው ታደሠ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ ከተማ ክፍል ከተማ፣ወረዳ 8 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 911 የሆነውን ንግድ ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ላይ ተከራይተው ሕጋዊ የሆነ የንግድ ፈቃድ በማውጣት ሰራተኞችን በመቅጠር የንግድ ስራ ሲሰሩበት የቆዩ መሆኑን፣1ኛ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኞች የሆኑት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ተከራይ ነን በማለታቸው የኪራይ ውሉን በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት ያቋረጠው መሆኑንና ተግባሩም ሁከት መሆኑን በመግለፅ የሁከት ተግባሩ እንዲወገድላቸው፣የኪራይ ውሉ ያላግባብ በመቋረጡ ምክንያት ያጡትን የቀን ገቢ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም ክርክሩ መሰረት ያደረገው የመንግስት ቤትን መሆኑን በምክንያት ጠቅሰው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ አመልካች በወኪላቸው አቶ ዳዊት አብርሃም አማካኝነት ሚያዚያ 17 ቀን 2001 ዓ/ም ከተጠሪዎቹ ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል በመፈፀም በወር ብር 2350፣በኂላም ብር 3000.00 ሲሰበስቡ መቆየታቸውን፣መንግስት ያወጣውን መመሪያም ተከትሎ አመልካች የንግድ ቤቱ እንዳይወሰድ ሆነ ብለው ተጠሪዎችን በማባበል እና በማስገደድ የሰራተኝነት ውል ማስፈረማቸውን፣ሆኖም የሰራተኝነት ውሉም ተቀባይነት የሌለውና ተጠሪዎቹ ሰራተኛ ሳይሆኑ ተከራይ የነበሩ መሆኑን፣አመልካችም ቢሆኑ የስራ ገቢ ግብር በስማቸው ለመክፈላቸው ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው አመልካች የንግድ ቤቱን በከፍተኛ ዋጋ አከራይተው ሲገለገሉ በመመሪያው



www.chilot.me

መሰረት የንግድ ቤቱን ለተጠሪዎቹ መተላለፉ የሁከት ተግባር ሊባል አይችል በማለት ተከራክረዋል፡፡የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ግን በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎለት ክሱ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ጭምር ሳይቀርብ በመቅረቱ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችንና የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ክርክር ሲሰማ አመልካች ለተጠሪዎቹ ድርጅቱን እንጂ ቤቱን ያላከራዩ መሆኑን መግለፃቸውን አረጋግጦ ተጠሪዎቹ ስልጣንን መሰረት አድርገው ያነሱትን ተቃውሞ ወድቅ አድርጎ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎቹ ማስተላለፍ ያለማስተላለፋቸውን በጭብጥነት ይዞ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ሰምቶ የአመልካች ሁለቱ ምስክሮች ተጠሪዎች ሰራተኛ መሆናቸው ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን የምስክርነት ቃላቸው እንደሚያሳይ፣የተጠሪዎች ሶስቱም ምስክሮች ደግሞ ተጠሪዎች ተከራይ እንጂ ሰራተኛ ያለመሆናቸውን መመስከራቸውን፣ተጠሪዎች በሰነድ ማስረጃነት ያቀረቡት ሰነድም ተጠሪዎች ቤቱን ተከራይተው ግምቱ ብር 6000.00 የሆነ ንብረት ያላቸው መሆኑን መግለፁ የተከራዩት ቤት እንጂ ድርጅቱን ያለመሆኑን እንደሚያሳይና ያለአከራይ እውቅና አመልካች ቤቱን ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አስተላልፈው እንደአከራዩ መረጋገጡን በምክንያት ይዞ የተፈጠረ ሁከት የለም፣አመልካች የቀረባቸው የቀን ገቢም የለም፣ወጪና ኪሳራ በቁጥር ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ብር 8000.00(ስምንት ሺህ ብር) ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የአመልካች ቅጥር ሰራተኞች መሆናቸው ተረጋግጦ እያለና ውሉን ተገደው የፈረሙ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ የአመልካች ምስክሮች ቃልና የቅጥር ውሉ ሰነድ ይዘት እንዲሁም አመልካች በቃል ክርክር ጊዜ ስለድርጅት ቤት ኪራይ የገለፁት አገላለፅ በተዛባ መልኩ ተመዝግቦና መንግስት ከአወጣው መመሪያ ይዘት ውጪ ቤቱን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲነጥቁ የተደረገ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ግን ቀርበው በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት ከመንግስት ተከራይተው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በሰራተኛነት ቀጥረው በማሰራት የሚጠቀሙበት ቤት 1ኛ ተጠሪ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 ውጪ ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በኪራይ አሳልፎ ሰጥቶብኛል፣ይህም የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድልኝ ይገበል በማለት ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም ቤቱን ከአመልካች ሊያገኙ የቻሉት በሰራተኝነት ሳይሆን በኪራይ መሆኑን፣የሰራተኛነት ቅጥር ውል የተባለው ሰነድም መመሪያውን ተከትሎ የተደረገ ሽፋን እንጂ ትክክለኛ ያለመሆኑን ገልፀው ተግባራቸው ሁከት የሚሆንበት አግባብ የለም ሲሉ መከራከራቸውን ነው፡፡የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የሰማ ሲሆን አመልካች ለተጠሪዎች ያከራዩሁት የድርጅት ቤት ነው በማለት በቃል ክርክር ከመግለጻቸው በተጨማሪ አሉኝ የሏቸውን ምስክሮችን

አቅርበውም ተጠሪዎች ሰራተኛ መሆን ያለመሆናቸው ላይ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ያደረጉ መሆኑን ገልፆ ምስክሮች ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ተጠሪዎቹ የአመልካች ቅጥር ሰራተኞች መሆናቸውን ያለመመስከራቸውን፣የተጠሪዎች ምስክሮች ግን ተጠሪዎቹ የአመልካች ሰራተኞች ሳይሆኑ የንግድ ቤቱን ተከራይተው የሚሰሩ መሆኑን በተመሳሳይ ሁኔታ መመስከራቸውን እንዲሁም የኪራይ ሰንዱ ተጠሪዎች ግምቱ ብር 6000.00 የሆነ ንብረት በቤቱ አስገብተው ያሉ ስለመሆኑ የሚገልጽ መሆኑ ተጠሪዎች የተከራዩት የንግድ ቤቱን እንጂ የድርጅት ቤቱን ያለመሆኑን እንደሚያሳይ ዘርዝሮ ቤቱ ለተጠሪዎች ተላልፎ የተሰጠው በመመሪያ ቁጥር 4/2004 በመሆኑ ተግባሩ የሁከት ተግባር ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የለም በማለት ውሳኔ የሠጠ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡እንግዲህ አመልካች በዚህ የሰበር ደረጃ ባቀረቡት ቅሬታ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን በአግባቡ ያልመዘገበና ከአመልካች የክርክር ነጥብና ማስረጃዎቹ ከአረጋገጡት ውጪ መሆኑን ጠቅሰው እንደዚህ አይነት የዳኝነት አሰጣጥ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት አይደለም ሊባል የማይችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን አጥብቀው ገልጸዋል፡፡ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ስለመረጋገጣቸው የገለጻቸው ፍሬ ነገሮችን በውሳኔው ላይ በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን ይህንኑ የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ የተቀበለው በመሆኑና ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ተያይዘው የሚቀርቡት የበታች ፍርድ ቤቶች የውሰኔ ግልባጭ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 21 እና 22 ስለሚያስገነዝቡ ይህ ችሎት ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ይዘት አይቶ ተገቢውን ዳኝነት ከመስጠት በሰበር ደረጃ የቀረበው የአመልካች ቅሬታ የሚያግድው ሁኖ አልተኘም፡፡በመሆኑም ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.,ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን ማረም እንጂ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለመሆኑ  የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የያዙትን ድምዳሜ ለመለወጥ የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ከመንግስት የተከራዩትን ቤት ከአከራዩ ፈቃድ ውጪ ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አከራይተው ሲጠቀሙ የነበሩ መሆኑን፣ያከራዩትም የንግድ ድርጅቱን ሳይሆን የንግድ ቤቱን፣ተጠሪዎች የአመልካች ቅጥር ሰራተኞች ሳይሆኑ ተከራይ መሆናቸውን፣አመልካች አለ የሚሉት የኪራይ ውልም የመንግስት መመሪያን መውጣት ተከትሎ ለሽፋን የተደረገ መሆኑን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን በሕጉ ስልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ከመንግስት ተከራይተው የነበሩት ቤት ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ1ኛ ተጠሪ ተላልፎ የተሰጠውና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይዘው ለአመልካች ሊለቁ ፈቃደኛ ያለመሆናቸው የሁከት ተግባርን የሚያቋቁምበት የሕግ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 191282 ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128223 ጥር 02 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካች ላይ የተፈጠሩ ሁከት የለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

**ሐ/አ**

የሰ/መ/ቁ. 80241

የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ጽናት የሆቴል ቱሪዝም ስራዎች ኃ.የተ.የግል ማህበር -ጠበቃ ኃ/ማሪያም ተመስገን ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-1. አቶ ዳመነ ነጋ

2. አቶ አሰበ ፈቃዱ

3. አቶ ሱልጣን በደዊ - ጠበቃ በለጠ ጉራራ ቀረቡ፡፡

4. አቶ አበራ አመንሲሳ

5. ወ/ት አለምፀሐይ ሰለሞን

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክስን መሰረት አድርጎ የቀረበውን በተከራይነት የተገኘ የንብረት ይዞታ ይልቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሀኑ ተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርደ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች ክስ ይዘትም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 169 የሆነው ቤት ከሰላሳ ዘጠኝ ክፍሎች እና ከሁለት ሰርቪስ ቤቶች ጋር በ10/09/2003 ዓ/ም በተፈጸመ የኪራይ ውል ከመንግስት ቤቶች ተረክቦ ባለበት ሁኔታ ተጠሪዎች ምንም ሕጋዊ መብት ሳይኖራቸው እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ክፍል በመያዝ ጨርቃ ጨርቅ በመያዝ እየነገዱ እንደሚገኙ ገልፆ በዚህ አድራጎታቸው ሁከት የተፈጠረበት ስለመሆኑ ጠቅሶ ሁከቱ እንዲወገድለትና ክፍሎቹ እንዲለቀቁለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ጉዳዩን የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በመመሪያው መሰረት እየተመለከተው መሆኑን ጠቅሰው ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም፣አመልካችም በክፍሎቹ ላይ ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙኝ አከራክሮ አመልካች ከመንስት ቤቶች ኤጀንሲ ንብረቱን በወርሃዊ የኪራይ ገንዘብ ብር



www.chilot.me

40,000.00 ተከራይቶ ለተጠሪዎች ደግሞ ክርክር ያስነሱትን ክፍሎች እያንዳንዳቸውን በብር 15,000.00 ወርሃዊ የኪራይ ገንዘብ በማከራየት ጥቅም እያገኘበት መሆኑን የአመልካች ጠበቃ በክርክሩ ወቅት ማረጋገጣቸው፣ተጠሪዎች ወርሃዊ ኪራዩን ለመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ እየከፈሉ እንደሚገኙ ገልጾና መመሪያው ሲወጣ ደግሞ አመልካች ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረዋል ብሎ ክስ ማቅረቡ የመመሪያው አፈጻጸም እንዳይነካው በማሰብ ምክንያት ነው የሚሉትን ነጥቦችን በምክያትነት ይዞ ጉዳዩን ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብቶ የሚዳኘው አይደለም በማለት እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 231 ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች ክፍሎችን የያዙበትን አግባብ በተመለከተ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ባወጣው መመሪያ የማይሸፈን ስለመሆኑ በኤጂንሲው የተረጋገጠ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ማስረጃዎችን በአግባቡ ሳይሰሙና የጉዳዩን ክርክር በስርዓቱ መሰርት ሳይመሩ ውሳኔ መስጠታቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ክፍሎችን ከአመልካች የተከራይ አከራይ ሁኖ ተጠሪዎች ተከራይተው ይዘው ሲጠቀሙ እንደነበርና በመመሪያው መሰረትም የመንግስት ቤቶች ከተጠሪዎች ጋር የኪራይ ግንኙነት እንዲቀጥል በማድረግ ሲጠቀሙ መቆየታቸውን፣የመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ ጉዳዩ በመመሪያው እንደማይሸፈን የገለፀበት ሁኔታ ተገቢነት የሌለው መሆኑንና ባሁኑ ጊዜ ከመንግስት ቤቶች ኤጂንሰ ጋር በክርክር እንደሚገኙ ገልጸው የበታች ፍርድ ቤቶች ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ ተደርጎ የተሰጠው ብይን ውጤቱ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ተጠሪዎች ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የመሰረተው አመልካች ከመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ የተከራየውን ቤት ተጠሪዎች ምንም መብት ሳይኖራቸው ይዘው ይገኛሉ በሚል ምክንያት መሆኑን፣ተጠሪዎች በበኩላች ክፍሎችን የያዙት ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል አድርገው መሆኑን፣የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ መመሪያ ሲያወጣ ደግሞ ከአመልካች ጋር ያላቸው ግንኙነት ተቋርጦ የኪራይ ገንዘቡን ለቤቱ ባለቤት እየከፈሉ እንዲቀጥሉ መደረጉን በመግለፅ የተፈጠረ ሁከት የለም ሲሉ መከራከራቸውን ነው፡፡የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በሰማበት ወቅት የአመልካች ጠበቃ ለተጠሪዎች ክፍሎችን አመልካች አከራይቶ በወር ብር 15,000.00 ከእያንዳንዳቸው እንደሚሰበሰብና ከመንግስት ቤቶች ቤቱን ከተከራየበት ጠቅላላ ወርሃዊ ገንዘብ ብር 40,000.00(አርባ ሺኅ ብር) በላይ ብር 35,000.00(ሰላሳ አምስት ሺኅ) ማግኘቱንና ሌሎች ክፍሎችን ይዞ  በመጠቀም ላይ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን ይህንኑ

ፍሬ ነገር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀብሎታል፡፡አመልካቾች ይህንኑ ፍሬ ነገር ፍርድ ቤቱ ገለልተኛ ሁኖ ጉዳዩን አልተመለከተም ከሚሉ በስተቀር በግል የሚክዱት ጉዳይ አለመሆኑን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡እንግዲህ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጧቸው ነጥቦች ከላይ የተመለከቱት ከሆነ ይህ ችሎት እነዚህን ፍሬ ነገሮች የሚለውጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ))እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም እንዚህን ፍሬ ነገሮችን ይዘን በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ሊሰጡ ይገባ የነበረውን ዳኝነት አይነት እና የበታች ፍርድ ቤቶችን ብይን ውጤት ተገቢነት ተመልክተናል፡፡ይህንኑ ለይቶ ለመደምደምም በአመልካች የተጠየቀውን ዳኝነት አይነትና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች በስር ፍርድ ቤት እንዲሰጠው የጠየቀው ዳኝነት በተጠሪዎች የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድለት ነው፡፡ተጠሪዎች ደግሞ ይዞታውን በሕግ አግባብ የያዙት ስለመሆኑ ጠቅሰው የአመልካችን ክስ ክደዋል፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በጭብጥነት ሊመለከተው ይገባ የነበረው መሰረታዊ ነጥብ ሁከት? አለ ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡ ይህ የጭብጥ አመራረት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246 እስከ 248 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ያገናበዘ ሲሆን ዳኝነቱ መሰጠት ያለበት በከሳሽ በተጠየቀው መሰረት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) ድንጋጌ ከተቀምጠው መርህ ጋርም የተጣጣመ ይሆናል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመፍታት ደግሞ ስለሁከት የተደነገጉትን የፍትሐ ብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፍስ በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ጋር በማገናዘብ መመልከትን የግድ ይላል፡፡

በመሰረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታውን ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈፀምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ንብረቱ እንዲመለስለት ህጉ ከጠበቀላቸው መንገዶች አንዱ አማራጭ የይዞታ ክስ ማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1149/1/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ መቅረብ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረው ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም ዓይነት መብት በሌለው ሰው ላይ ስለመሆኑም የድንጋጌው መንፈስ ያስረዳል፡፡ የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅራቢ በማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ንብረቱ በይዞታው ስር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመቀጠም ወይም በሚስጢር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው፡፡ ሁከት መፍጠር የሚኖረው ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ስር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ሲፈጥርበት ወይም ረብሻ ሲፈጥርበት ነው፡፡

እንግዲህ የሁከት መፍጠር ድርጊት አጠቃላይ ትርጓሜና ይዘቱ ከላይ የተመለከተው ስለመሆኑ ከፍ/ህ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንግጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሁከት የወገድልኝ ክስ የሚያቀርበው ሰው ንብረቱ በእርሱ ግልጽ ቁጥጥር ስር መሆኑንና በዚህ ንብረት እንዳይገለገልበት ተከሣሹ ረብሻ የተነሣበት ወይም መሰናክል የተፈጠረበት ስለመሆኑ በማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ በሌላ አገላለጽ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ስለመሆኑ ማሣየት ይጠበቅበታል፡፡



www.chilot.me

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ክፍሎች አመልካች ከመንግስት ቤቶች ኤጄንሲ ባገኙት የተከራይነት መብት በቁጥጥር ስር አድርጎ ሊጠቀምበት ከተከራየ በኋላ ለተጠሪዎች ያከራየ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡የመንግስት ቤቶች ኤጄንሲም ጉዳዩን አጣርቶም የኪራይ ውሉን ተጠሪዎች ከመንግስት ቤቶች ጋር እንዲቀጥሉ ወስኖ የነበረ መሆኑና በኃላ ግን ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ ነው በሚል ምክንያት ጉዳየ በመመሪያው እንደማይሸፈን እና ኪራዩም እንደገና ከአመልካች ጋር እንዲቀጥል በማለት ደብዳቤ መፃፉን፣ተጠሪዎች ደግሞ የመንግስት ቤቶችን እርምጃ ተቃውመው በፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ ክርክር ላይ እንደሚገኙ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የአከራካሪ ክፍሎች ሕጋዊ ተከራይ ማን ነው? ወደፊት ሕጋዊ ተከራይ ሁኖ መቀጠል ያለበት አመልካች ነው ወይስ ተጠሪዎች ናቸው? የሚሉት ነጥቦች ከሚታዩ በስተቀር አመልካች ተጠሪዎችን በራሱ ተነሳሽነት አከራይቶ ቆይቶ የሁከት ተግባር ፈጥረዋል ብሎ ክስ የሚያቀርብበት አግባብ የለም፡፡ተጠሪዎች በኃይል ተግባር የአመልካችን ይዞታ እስካልያዙ ድረስ ክርክሩ የሁከት ይወገድልኝ ክስን መሰረት አድርጎ የሚታይበት አግባብ የለም፡፡በሌላ አነጋገር የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለውና መብቱ የሚከበረው የተሻለ የይዞታ መብት በማሣየት ነው፡፡እንዲሁም የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርብ ወገን የሚጠይቀው ዳኝነት የሁከት አድራጐት እንዲቆም በይዞታው ስር የነበረው ንብረት ሊያስገኝለት የነበረውን ጥቅም በኪሣራ መልክ እንዲከፈለው ሲሆን በህጉ አግባብ የተፈፀመ የኪራይ ውል አለመኖሩን ተከትሎ የሚቀርበው ጥያቄ ግን ውጤቱ ከሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ ጋር ተመሣሣይነት የለውም፡፡በመሆኑም በሁከት ይወገድልኝ ክስ ሕጋዊ ተከራይ ማን ነው የሚለው ጥያቄ ተነስቶ ዳኝነት የሚሰጥበት ሁኔታ ስለመኖሩ መሰረታዊውም ሆነ የስነ ስርአት ህግ ድንጋጌዎችን አያመላክቱም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ክፍሎች ለተጠሪዎች አከራይቶ ቆይቶ ለተጠሪዎች የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት የተከራይነት መብት ሲያስተላልፍ ሁከት ፈጥረዋል በማለት የሚያቀርበው ክርክር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 ድንጋዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ ማየትና ዳኝነት መስጠት እየተገባው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 መሰረት በመንግስት ቤቶች ኤጄንሲ ታይቶ እልባት የሚሰጥበት እንጂ ፍርድ ቤት ጣልቃ የሚገባበት ነው በማለት የሰጠው የምክንያት ክፍል የተጠቃሹን አዋጅ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከፍርድ ቤት ስልጣን አድማስ ጋር ያላገናዘበ ቢሆንም ክሱን ውድቅ ማድረጉ ግን በውጤት ደረጃ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 188655 መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118491 ሚያዚያ 11 ቀን 2004 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው ብይን በተለወጠ ምክንያት ውጤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ክፍሎችን በኪራይ ከአከራየ ከአስተላለፈ በኋላ ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረዋል ብሎ ክስ ማቅረቡ ስለ ሁከት ይወገድልኝ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ የፈጠሩት ሁከት የለም ብለናል፡፡
3. አመልካች በሌላ አግባብ መብቱን ለማስከበር ይህ ውሳኔ አያግደውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሣ/ክ



www.chilot.me

የሰበር መ/ቁ 83060

ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ገ/ማሪም ገ/መድህን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ጣዕመ ወ/ስላሴ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

***ፍ ር ድ***

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በአመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ሻለቃ ኃይለማርያም ኃ/ስላሴ ላይ የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 20 ቀበሌ 19 ክልል ቁጥር 513 የሆነውና የካርታ ቁጥር 13079 በሚል የሚታወቅ ቤት ባለቤት መሆናቸውን ለ1ኛ ተከሳሽ ቤቱን እንዲያስተዳድሩ እንዲያከራዩ በሚል የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው ቢሆንም ቤቱን ወደ ሌላ ሰው የማስተላለፍና ስልጣን እንዳልተሰጣቸው 1ኛ ተከሳሽ የተሰጣቸውን ስልጣን ሽፋን በማድረግ ሐምሌ 10 ቀን 1992 ዓ/ም በተፃፈ ውል አማካኝነት ቤቱን ለአሁኑ አመልካች በብር 148,000.00/አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ብር/ የሸጡ መሆናቸውን አሁኑ አመልካች በዚህ የመሸጥ የመለወጥና የማስተላለፍ ሥልጣን በማያካትተው የውክልና ሰነድ ወይም ህገ ወጥ ሰነድ አማካኝነት ቤቱን መግዛታቸውን ገልፀው የሽያጭ ውል ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲፈርስ እንዲሁም ውሉን ተከትሎ የተከናወኑት ተግባራት ዋጋ አልባ ናቸው እንዲባሉ ቤቱን የአሁን አመልካች ለቀው እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት ፍርድ ቤቱ ጉዳን ለማየት ሚያስችለው ስልጣን የሌለው መሆኑን ተጠሪ የክስ ምክንያት የሌላቸውና ክሱን ለማቅረብም መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን ሚገልፅ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ካርታው የተሰረዘ መሆኑን በሕጉ አግባብ የተደረገ ቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያትዬሌለ

መሆኑንና ተጠሪ የውጭ ሀገር ዜጋ በመሆናቸው የማይንቀሳቀስ ንብረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለመያዝ ህጋዊ መብት የሌላቸው መሆኑንና ሌሎች ነጥቦችን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤትም በመጀመሪ ደረጃ መቃወሚያነት ተጠሪ ያቀረቧቸውን ነጥቦች ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ አልፎ ፍሬ ጉዳዩን መርምሮ የቤት ሽያጩ ውሉ ሕጋዊ አይደለም በሚል ምክንያት ፈራሽ ነው በማለት ቤቱን ተጠሪ ሊረከቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1808 መሰረት ውል እንዲፈርስ ጥያቄ የሚቀርብባቸው ውሎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1810 መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገዱ ናቸው፡፡ ተጠሪ የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም ክሱን የመሰረቱት ሐምሌ 14 ቀን 1992 ዓ/ም የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው በመሆኑና ጊዜ ሲሰላም የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ያለፈበት በመሆኑ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ከዚህም በኃላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ችሎቱ ጉዳዩ በይርጋ የታገደ አይደለም በማለት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ሲል ጉዳዩን ለፌዴራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የፍሬ ጉዳይ ክርክርን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ውሉ ፈራሽ ነው ቤቱን አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም አመልካች በመንግስት መመሪያ መሠረት በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ በጊዜው የወጣው የመንግስት መመሪያ የውሉን ይዘትና ለጉዳዩ መቅረብ ያለባቸውን ማስረጃዎችን አይነትና የአቀራረባቸውን ስርዓት እንዲሁም ማስረጃዎቹን ይዘት ያላገናዘበና በጉዳዩ ላይ የክርክሩ የግድ ተሳታፊ ሊሆን ይገባው ነበረውን ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባ ሳይደረግ ክረክሩ የተመራበት ለተጠሪ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ያስቀመጠው መፍትሔ መሰረት ያላደረገ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ የቤትሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስም የቤት ሽያጭ ውሉ በመንግስት መመሪያ መሰረት የተደረገ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠና በመንግስት መመሪያ ተደርጓል ቢባል እንኳን መመሪያው ሕጉን ለማውጣት ስልጣን ባለው አካል የወጣ ባለመሆኑ የህግ አቋም የሌለውና የውክልና ሕግ መርህዎችን የሚፃረር በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የማየይገባ መሆኑን ዘርዝረውና የአመልካች መከራከሪያ ነጥቦች ድግግሞሽ ያለባቸው ስለመሆኑ ገልፀውና የህግ መሰረት የሌላቸው መሆኑን ያሳያሉ የሚሏቸውን ምክንያቶች ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር መልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከለይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ መርምረናል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አከራካሪው ቤት ሊሸጥ የቻለው የውክልና ሰነዱንም መሰረት አድርጎ ሳይሆን በምንግስት በወጣ መመሪያ ነው እየተባለና ይህንንም መመሪያ አመልካች ከመልሳቸው ጋር እንደማስረጃ ሳያቀርቡ በመቅረታቸው ብቻ ይሄ ታልፎ የሽያጭ ውሉ ተሰረዞ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ መልሰው ያስረክቡ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሀምሌ 10 ቀን 1992 ዓ/ም ከተጠሪ ወኪል ከተባሉት ከሻለቃ ሀብተማሪያም ሀብተስላሴ ጋር ያደረጉት መኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ መሆኑን መስከረም 25 ቀን 1993 የተደረገው ውልም በተመሳሳይ አካል ፊት የተደረገ መሆኑን የክልል መስተዳደር ጽ/ቤት በቁ/አመ/አ.አ 73 በ18/8/1992 ዓ/ም ለውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ ኤርትራዊያን ከሀገር ሲወጡ ንብረታቸውን የመጠበቅ የማስተዳደር የመሸጥ የመሳሰሉት የውክልና ሰነዶች/ማስረጃዎች/ ያሏቸው ሰዎች መሸጥ መለወጥ ይችላሉ የሚል ይዘት ያለው መሆኑን ተጠሪ ኤርትራዊ መሆናቸውና ለወኪላቸው ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ስልጣን ያልሰጡ መሆኑን የተረጋገጠ መሆኑን በቁጥር ቀ2/ጠ67/61/92 በቀን 10/10/92 በተፃፈ ደብዳቤ ተጠሪ በአከራካሩው ቤት ጥር 13 ቀን 1974 ዓ/ም የወሰዱት የካርታ ቁጥር 13079 ለተወካያቸው ሳይሰጡ ከሀገር የወቱ በመሆናቸው ከሚመለከተው አካል ተረጋግጦ በመቅረቡ ምክንያት ተጠሪ የወሰዱት ካርታ እጃቸው ላይ እንዳለ በማምከን ለአሁኑ አመልካች ቁጥሩ 39897 ሆነ አዲስ ካርታ ሰኔ 09 ቀን 1992 ዓ/ም የተሰጣቸው መሆኑን ከሚመለከተው አካል የተፃፈ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ሐምሌ 10 ቀን 1992 ዓ/ም በውልና ማስረጃ በተደረገው የስምምነት ሰነድ ይዘቱ ሲታይ የውሉን አላማ የኤርትራዊያን ቤት ወኪሎች የሆኑት ወኪል የሆኑበትን ቤት ሸጠው ገንዘቡን በዝግ ሂሳብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባንክ ገቢ እንዲያደርጉ በክልል 14 ቢሮ ቁጥር 20 የተጠሪ ወኪል ተጠርተው በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ቤቱን ለመሸጥ መሆኑንና ወኪሉ የወኪል አድራጊያቸው ባለቤት መጥተው ቢከራከሩ ወይም ያገባኛል ቢሉ ሁሉንም ነገር በኃላፊነት የሚመልሱ መሆኑን በመግለፅ ፊርማቸውን ማስቀመጣቸውንና የቤቱን ዋጋ በወቅቱ የተከፈለውን የገንዘብ መጠንና ቀሪው ገንዘብ የሚከፈልበትን ሁኔታ እንዲሁም ሌሎች የገዥንና ሻጭን መብትና ግዴታዎችን በዝርዝር የያዘ መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ የተገለጹት ነጥቦች በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡ ሲሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ሊወስኑ የቻሉት አመልካች ቤቱ የተሸጠው በመንግስት ትዕዛዝና መመሪያ መሆኑን ገልፀው ቢከራከሩም ለጉዳዩ ለማስረጃነት የቀረቡት የውል ሰነዶች አያሳም እንዲያውም ወኪሉ ቤቱ የእኔ ነው ባይ ወይም ተከራካሪ ወገን ቢመጣ የመመለስ ኃላፊነቱ የውል ሰጪው ነው በሚል የስምምነት ግዴታ የተቀመጠ መሆኑ ቤቱ የተሸጠው በመንግስት ትዕዛዝ ሳይሆን የተጠሪ ወኪል በራሳቸው ፈቃድ ተነሳስተው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው የሚል ምክንያት በመያዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሐምሌ 10 ቀን 1992 ዓ/ም የተደረገው ውል እንደከፍተኛው ፍርድ ቤት ድምዳሜ በመንደር የተደረገ ሳይሆን በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ ከመሆኑም በላይ እንደተጠቀሰው ይዘቱ ወኪሉ በክልል 14 ቢሮ ቁጥር 20 ተጠርተው በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ሽያጩን ያከናወኑ መሆኑን በግፅ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የሰነዱ ይዘት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005 እና አዋጅ

ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 2(1) ፣ 4(1) እና 5(1(ሀ) መሰረት ተቀባይነት የማያገኝበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሲሆን ውሉን ያረጋገጠው አካልም ኤርትራዊያን ከሀገር ሲወጡ ቤት ለመሸጥ የሚያስችል ስልጣን ለተወካቻቸው ባይሰጡም ተወካዩቹ የማስተዳደር መጠበቅና የመሳሰሉ የውክልና ሰነዶችን ቢይዙም ንብረቶቹን መሸጥ መለወጥ የሚችሉ መሆኑን ከአዲስ አበባ መስተዳደር ሚያዝያ 18 ቀን 1992 ዓ/ም የተላለፋትን መመሪያ መሰረት አድርጎ ስምምነቱን ማረጋገጡን ሁለቱም ሰነዶች አንድ ላይ ሲታ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲታይም የተጠሪ ወኪል ተግባሩን የፈፀሙት ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችላቸው ሕጋዊ ውክልና አለኝ በሚል ሳይሆን በጊዜው በነበረው ነባራዊና አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ሁነው መሆኑንና አመልካች ደግሞ ይህንኑ በማየትና በመገንዘብ ስምምነቱ ውስጥ የገቡ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ የተጠሪ ነባር የባለቤትነት ካርታ በሚመለከተው አካል መሰረዙ ከላይ ከተጠቀሰው የክልል 14 መስተዳድር መመሪያና ውሉ በውልና ማስረጃ ፊት ቀርቦ ከመደረጉና ሕጋዊ ነው ተብሎ ከመረጋጡ ጋር ተዳምሮ ሲታይ አመልካች ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ግዢውን የፈፀሙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የመንግስት መመሪያ ስለመኖሩ አመልካች ማስረጃ አላቀረቡም በማለት የያዙት ድምዳሜ ከላይ የተጠቀሰውን ውል ይዘት ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ከሆነም በራሳቸው አነሳሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145(1) እና 345(1)(ለ) ድንጋጌዎች አግባብ ማስቀረብ ይችሉ የነበረ ጉዳይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን የውሉ ሰነድ ይዘት በግልፅ ሽያጩ በመንግስት አስተዳደር አካል ትዕዛዝ የተከናወነ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ይሄው የሰነዱ ይዘት ለጉዳዩ ተቀባይነት ያለውና ተግባሩ በአስተዳደር አካሉ ትዕዛዝና መመሪያ የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች ሽያጩ በመንግስት አስተዳደር አካል ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መሰረት የተከናወነ መሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ሐምሌ 10ቀን 1992 ዓ.ም. እና መስከረም 25 ቀን 1993 ዓ.ም. የተደረጉትን ውሎችን ይዘትና መንፈሳቸውን ለውሎች መደረግ ከሚመለከተው አካል ለዚሁ ውል አረጋጋጭ አካል ሲተላለፉ የነበሩትን ደብዳቤዎችን ይዘት ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ወኪል ውክልናውን መሰረት አድርገው ሸጠዋል በማለት በአመልካች ክርክር ባልቀረበበትና በወቅቱ በነበረው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት በመንግስት አስተዳደር አካል በተወሰደው እርምጃ መሰረት ወደ ግብይት የገቡት ዜጎች አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ የፈፀሙት ተግባር መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ጉዳዩ በወቅቱ ከነበረው ልዩ ሁኔታ ታይቶ በራሱ ዳኝነት ከሚያገኝ በስተቀር የውክልና ህግ መርህዎች መሰረት ተደርገው ተግባራቸው ህጋዊ ጥበቃ የሚነፈግበት አግባብ ሊኖር አይገባም፡፡ በወቅቱ የተወሰደውን እርምጃ በመገንዘብም በወቅቱ የተከናወኑትን ተግባራትና መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ/ም ወጥቶ ስራ ላይ መዋሉም መንግስት በማመን የግዥ ተግባር ያከናወኑትን ዜጎች ዋስትና ለመስጠት ነው ተብሎም ይታሰባል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ከሀገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራዊያ በመንግስት አስተዳደር ንብረታቸው ተሸጦ በዝግ ባንክ አካውንት የተቀመጠ ገንዘብ ካላቸው ማስረጃ ሲያቀርቡ ካለወለድ ገንዘባቸውን በብር እንዲያገኙ እንደሚደረግ በአንቀፅ 4(2) ስር በግልፅ ሰፍሯል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከሀገር ወጥተው የነበሩ ኤርትራዊ መሆናቸውንና አመልካች ለቤቱ የከፈሉት ገንዘብ ብር 148,000.00(አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ) በኢትጵያ ንግድ ባንክ ፊኒፊኔ ቅርንጫፍ በዝግ ሂሳብ መቀመጡና የባንክ ደብተሩም በአዲስ አበባ መስተዳደር መቀመጡን አመልካች ጠቅሰው ላቀረቡት ክርክር በተጠሪ በኩል ማስተባበያ ክርክር ያልቀረበበትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሐ/ቁጥር 234(1(ሠ)፤235 እና 83 ድንጋጋዎች እንደታመነ የሚቆጠር በመሆኑ ተጠሪ ያላቸው መፍትሔ ይህንኑ ገንዘብ መቀበል እንጂ የቤት ሽያጩ እንዲፈርስ

ማስደረግና ቤቱን የመረከብ መብት አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም አመልካች በመንግስት አስተዳደር አካል በተላለፈው መመሪያ መሰረት ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው የገዙትና ለበርካታ አመታት ሲጠቀሙበት የነበረውን ቤት ውሉ ፈርሶ ለተጠሪ ሊያስረክቡ የሚገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን የበታች ፍርድ ቤቶች የክርክሩን ልዩ ባህርይና በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የውል ሰነዶችን ይዘታቸውን በአግባቡ ሳይመለከቱ ለጉዳ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት የሌለለውን ውክልና ሕገ መርህዎችንና በአመልካች ላይ መመሪያውን ለማስረጃነት ማቅረብ ግዴታን ሕጉ ባልጣለበት አግባብ የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40449 ህዳር 04 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87379 ነሐሴ 18 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አከራካሪው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ሊገደዱ አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ያላቸው መፍትሄ የቤቱን ሽያጭ ገንዘብ ብር 148,000.00(አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ብር) በኢትጵያ ንግድ ባንክ ፊኒፊኔ ቅርንጫፍ ከሚገኘው የዝግ የሂሳብ አካውንት መውሰድ ነው ብለናል፡፡
4. ለክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአመስት ዳኞች ፊርማ አለበት፤

እ/ኢ

የሰ/መ/ቁ 83665

ግንቦት 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ እታፈራሁ ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. ወ/ሮ መሰረት ግርማ ወኪል ሁለተኛ ተጠሪ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፍሬህይወት ግርማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32817 ታህሳስ 5 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 118115 መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ሀብትና የጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪዎች ወላጅ አባታችን አቶ ግርማ ብሩ መጋቢት 24 ቀን 1988 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ እኛም ወራሽነታችን በፍርድ በማረጋገጥ ውርስ እንዲጣራልን አድርገናል፡፡ የውርስ አጣሪው ሪፖርት በመዝገብ ቁጥር 30327 ህዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፀድቋል፡፡ አባታችን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ቁጥሩ 076/ሀ/ የሆነ ቤት አላቸው፡፡ ተከሳሽ /አመልካች/ ቤቱን ይዛ ግማሹን እያከራየች ትገኛለች፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ ቤቱን እንዲለቁና የኪራይ ገንዘብ ብር 20400 /ሃያ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡
2. አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ከሳሾች ክስ ያቀረቡበት የውርስ ንብረት ጥያቄ በአስር ዓመት የይርግ ጊዜ ገደብ ቀሪ ይሆናል፡፡ የቤት ቁጥር 076 የሆነው ቤት ባለቤቱ /የከሳሾች አውራሽ/

ከሞተ በኋላ በእርጅና ምክንያት በመፍረሱ በአዲስ መልክ ሃምሳ ሁለት ቆርቆሮ ጣራውን በአዲስ መልክ ሰርቼ የምጠቀምበት የግል ንብረቴ ነው በማለት ተከራክራለች

3. የስር ፍርድ ቤት በውርስ ማጣራቱ ቤቱ የአቶ ግርማ ብሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የቤቱ ስመ ሀብትም በከሳሾች አውራሽ በአቶ ግርማ ብሩ ስም ነው፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ወረዳ 09 ቁጥሩ 076/ሀ/ የሆነውን ቤት ለከሳሶች ያስረክቡ የቤቱን ኪራይ 10200 /አስር ሺህ ሁለት መቶ ብር/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ተከሳሽ ለከሳሾች ይክፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ቤቱ የመልስ ሰጭዎች /ተጠሪዎች/ አውራሽ መሆኑ በውርስ ማጣራት ሂደት ተረጋግጧል፡፡ የውርስ አጣሪው ሪፖርት በፍርድ ቤት ፀድቋል፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው በማለት አፅንቶታል፡፡

5. አመልካች መስከረም 28 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ከተጠሪዎች አውራሽና ወላጅ አባት ጋር ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ተጋብተን ስንኖር ሁለተኛ ተጠሪን ወልጃለሁ አመልካች የሟች አቶ ግርማ ብሩ ሚስት መሆኔና ተጠሪዎች ደግሞ የሟች ልጆችና ወራሾች መሆናቸው በመዝገብ ቁጥር 376/88 ጥር 6 ቀን 1989 ዓ.ም በፍርድ ቤት ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች ወራሽነታቸውን ካረጋገጡ ከአስራ ሶስት ዓመት በኋላ በ2002 ዓ.ም ውርስ እንዲጣራላቸው ጠይቀው እኔም ይህንን ጥያቄ በመቃወም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተከራክሬ የውርስ ማጣራቱ የእንቺን መብት የሚነካ አይደለም ተብሎ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ አመልካች የአከራካሪው ቤት ግማሽ ባለንብረት ስለመሆኔ ከሟች ባለቤቴ ጋር የተሰጠን የጋራ የቦታ ማረጋገጫ ሰነድ የሚያሳይ ሲሆን ንብረቱም በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ሀብት ነው፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች የንብረት ታስረክበኝ ጥያቄ እያቀረቡ የጋራ ባለሀብትነት መብቴን በማለፍ ንብረቱን ለተጠሪዎች እንዳስረክብ የተሰጠው ውሣኔ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎችና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የሚጥስ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

6. ተጠሪዎች በበኩላቸው ታህሳስ 2 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጡት መልስ አመልካች የውርስ አጣሪው ቤቱ የሟች ግርማ ብሩ የግል ንብረት ነው በማለት የቀረበውን ሪፖርት በማፅደቅ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ተከራክረው ክርክራቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ ቤቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት የምታቀርበው የሕግ መሰረት የለውም፡፡ ቤቱም በጋብቻ የተፈራ ሣይሆን ሟች ከአባቱ በስጦታ ያገኘው ንብረት ነው፡፡ ጉዳዩ ክርክር ሲደረግበት የቆየ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ታህሳስ 22 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የክስ መቃወሚያና የፍሬ ጉዳይ ክርክር ውድቅ በማድረግ ቤቱን ለተጠሪዎች እንድታስረክብ የሰጡት ውሣኔ ተገቢነት ያለው መሆኑን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

8. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪዎች የሚች አቶ ግርማ ብሩ ውርስ እንዲጣራላቸው ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30327 አመልካች አቅርበው የነበረውን መቃወሚያና ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ብይን ይዘት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች የቤት ቁጥር 076 የግል ቤቴ ነው፡፡ ውርስ እንዲጣራ የቀረበው ጥያቄም በአስር ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው የሚል የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች ያቀረቡት የውርስ ይጣራልን ጥያቄ ነው፡፡ ውርስ ሲጣራ የውርስ አጣሪው ወራሾች ኑዛዜ፣ የሚች ዕዳና ንብረት መለየት እንጂ በሶስተኛ ወገኖች የመፋለም መብትን የሚያሳጣ ውሣኔ መስጠት አይችልም የውርስ አጣሪው ስራ ውርስ ማጣራት እንጂ የአሁኑ የመቃወም አመልካች ንብረት ወይም ቤት አይደለም ብሎ በዚህ መዝገብ በቤት ቁጥር 076 ላይ የተሰጠ ውሣኔ የለም" ስለዚህ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ የመቃወም አመልካች መብት ሊነካ የሚችል ውሣኔ ያልተሰጠ በመሆኑ የመቃወም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ አልተቀበልነውም በማለት ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11408 ሰኔ 9 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው፣ በሰበር ችሎት የሚታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በሰበር መዝገብ ቁጥር 72275 ታህሳስ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ማጣሪያ ችሎት ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡
9. ተጠሪዎች የሚች ውርስ እንዲጣራ ጥያቄ ባቀረቡበትና የውርስ አጣሪው ሪፖርት በፀደቀበት በመዝገብ ቁጥር 30327 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የአመልካችን የመቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ ያደረገው የውርስ አጣሪው ሪፖርት ቤቱ የሚች የግል ንብረት ነው ወይስ የአመልካች የጋራ ሀብት የሚለው ጭብጥ የማይመለከትና በቤቱ ላይ መብት ያለው ማናቸውም ሶስተኛ ወገን በቤቱ ላይ ያለውን መብት የባለሀብትነት መብት ለማስከበር ክርክር ከማቅረብና ከመፋለም የማይገደብ ነው በቤት ቁጥር 076 ላይ የተሰጠው ውሣኔ የለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ተጠሪዎች ቤቱን እንድትለቅና እንድታስረክባቸው ያቀረቡት ክስ ለመቃወም አመልካች ያቀረበችው የይርጋ ክርክርና ሌሎች የመከራከሪያ ሀሳቦችና ማስረጃዎች በመቀበልና በመመርመር ውሣኔ መስጠት ሲገባቸው፣ ቤቱ በውርስ አጣሪ የሚች ንብረት ነው ተብሎ ውሣኔ ተሰጥቶበታል በማለት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ የክሱ መቃወሚያና ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30327 ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ ይዘትና ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
10. የሚች ውርስ እንዲያጣራ የተመደበ የውርስ አጣሪ፣ አንድ ንብረት የሚች የግል ንብረት አለመሆኑ አከራካሪ ሆኖ ሲያገኘው፣ ንብረቱ የሚች የግል ንበረት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመመስረት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ማስረጃ በመመርመር በመመዘን ውሣኔ የመስጠት ስልጣን የለውም፡፡ ከዚህ አንፃር ቤቱ የሚች የግል ንብረት መሆኑ ለውርስ አጣሪው ሪፖርት ተገልጿል በማለት አመልካች የባለሀብትነት ክርክር ሣይቀበሉና ማስረጃዎን ሳይመረምሩና ሳይመዝኑ ውሣኔ መስጠታቸው አመልካች ፍትህ የማግኘት መብት የሚያጣብብ ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ አመልካች የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በመቃወም ያቀረቡት ክርክር የአንቺን መብት የሚነካ አይደለም በማለት ውድቅ

ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች ንብረት ያስረክቡኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በመቃወም ቤቱ የጋራ ሀብቴና የግል ንብረቴ ነው በማለት ያቀረበችው ክርክር ሣይታይ የሚታለፍ መታለፉ አመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የተረጋገጠለትን የንብረት ባለቤትነት መብት ለማስከበርና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1206 መሰረት የመፋለም መብቱን ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የማቅረብና የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 የተረጋገጠውን ፍትህ የማግኘት መብቷን በሚጥስ ሁኔታ በቤቱ ላይ አለኝ የምትለው መብትና ጥቅም በፍርድ ሳይጣራና ሣይረጋገጥ የሚቀርበትን ክፍተት የሚፈጥር ነው ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ንብረቱን ሙሉ በሙሉ ለተጠሪዎች እንድትለቅና እንድታስረክብ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32817 የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 118115 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ላይ አመልካች ያቀረበችውን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያና የመከላከያ መልስ እንዲሁም የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመርመር በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

የሰ/መ/ቁ. 88084

ህዳር 19 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች**:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች**:- ወ/ሮ ወጋየሁ ታምሩ ቀረቡ

**ተጠሪ**:- 1. የወ/ሮ አስካለ ወሰኔ ወራሽ ፍሬዘውድ ጌታቸው ቀረቡ

2.አቶ በኃይሉ ከፍያለው ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ቤት ይገባኛል ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኗ 1ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም፡- አመልካች የሟች ወ/ሮ አይከልክሉሽ ደስታ መንገሻ ወራሽ ስለመሆናቸውን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አረጋገጠው ማስረጃውን የያዙ ሁኖ ከሟች ሊያገኙ የሚገባውን የውርስ ሃብት 1ኛ ተጠሪ ከፊሉን እያከራዩ በመጠቀም ላይ እንደሚገኙ ገልፀው የውርስ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ሃብቱ እንዲጣራላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በሰጡት መከላከያ መልስም ጥያቄው በይርጋ የሚታገድ መሆኑንና የሚጣራ የውርስ ንብረት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም ይርጋን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር አልፎ ውርሱ እንዲጣራ ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ አመልካችም ወደ ክርክሩ ገብተው በውርስ ማጣራት ሂደቱም እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡የውርስ ማጣራት ተግባሩን እንዲያከናወኑ በፍርድ ቤት የተሾሙት የውርስ አጣሪም የሟቿ ብቸኛ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የአሁኗ አመልካች መሆኗን፣ የውርስ ንብረቱን በተመለከተ ደግሞ የአሁኗ አመልካች ለይተው ያቀረቡት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ቀበሌ 14/21 ቁጥሩ 482 የሆነው ቤት ሁኖ ይህ መኖሪያ ቤት በ1ኛ ተጠሪና በሟች አይከልክሉሽ ደስታ በውርስ ተይዞ ቆይቶ በኃላ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝና በመንደር ውል ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ የሸጡ መሆኑ መረጋገጡን፣በቤቱ ብር 1900.00(አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር) መሰብሰቡን ማጣራቱን ገልጸ ጉዳዩን ለፍርድ ቤት የመለሰለት ሲሆን የውርስ ሪፖርቱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ አስተያየት ከተቀበለ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ በቤቱ ላይ አመልካች የሟች አይከልክሉሽ ደስታ ድርሻን የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ ቤቱ በብር

115,000.00 (አንድ መቶ አስራ አምስት ሺህ) ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በቅን ልቦና የተሸጠ መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ አመልካች የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ግማሽ ድርሻ አላቸው ሲል የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማሻሻል ማፅደቁን ገልጾ ይኼው ማስረጃው ለግራ ቀኙ እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፤የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በውርስ የሚያገኙን የቤቱን ግማሽ ድርሻ 1ኛ ተጠሪ ሐሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ ይዘው በመንደር ውል ለ2ኛ ተጠሪ መሸጣቸው ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርደ ቤቶች አመልካች ሊያገኙ የሚገባው የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ግማሽ ነው በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ስለቀረቡ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች በአከራካሪው ቤት ብቸኛ ወራሽና ባለቤት መሆናቸው በተረጋገጠበት 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ሕጋዊ መብት ያልነበራቸው መሆኑ ባልተካደበት፣2ኛ ተጠሪ ሕጋዊ መብት ከሌላቸው 1ኛ ተጠሪ መግዛታቸው ባላከራከረበት የቅን ልቦና ገዥ ናቸው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የመወሰናቸው አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡በመሆኑም ከዚሁ ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የሟች ወ/ሮ አይከልክሉሽም ደስታ ብቸኛ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው መረጋገጡን፣1ኛ ተጠሪ የሟች ወራሽ ነኝ በማለት ይዘው የነበሩት ማስረጃ በአመልካች ተቃዋሚነት መሰረዙን፣አመልካች በውርስ ይገባኛል የሚሉት ቤትን በሟች ወ/ሮ አይከልክሉሽም ደስታ እና በ1ኛ ተጠሪ ወላጅ እናት በእማኂይ ወ/ጊዮርጊስ ስም የተመዘገበ እንደሆነና ቤቱም እኚህ አሚኂይ ከሞቱ በኂላ 1ኛ ተጠሪና የአመልካች እናት በጋራ በውርስ ሃብትነት ይጠቀሙት እንደበር፣የአመልካች እናት ከሞቱ በኂላ 1ኛ ተጠሪ ብቸኛ ወራሽ ነኝ በማለት አሳውጀው የወራሽነት ማስረጃ ይዘው የቤቱን ስመ ሃብት አዙረው የተገኙ መሆኑን፣ይህን ቤት በመንደር ውል ለአሁኑ 2ኛ አመልካች በብር 115,000.00 1ኛ ተጠሪ መሸጣቸውን ከውርስ ማጣራት ሂደቱ ጀመረው አምነው የሚከራከሩ ቢሆንም ሰነዱ ግን በውርስ አጣሪውም ሆነ በፍርድ ቤት ያልቀረበ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው አንድ ንብረት ለሌላ ሰው በሕጋዊ መንገድ ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት መብት ሲኖረው ብቻ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ በሕግ ጥብቃ የማይደረግለት ወይም የሌለ መብት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም፡፡ይህ ተቀባይነት ያለው የሕግ መርሕ ነው፡፡የሌላ ሰው ንብረት ለመሸጥ፣ለማስተላላፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ ሕጋዊ የሆነ ስልጣን ሊኖር ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣም 1ኛ ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ግማሽ ድርሻ ላይ በሕጉ አግባብ ጥብቃ የሚደረግላቸው መብት ሳይኖር ቤቱን ለአሁኑ 2ኛ አመልካች በመንደር ውል አስተላልፌአለሁ በማለት መከራከራቸው በሌላቸው

መብት ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2884 አግባብ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ አይደለም፡፡አንድ ሰው ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚችለው በህግ ጥበቃ የሚደረግለትንና ያለውን መብት እንጂ የሌለውን መብት ሊሆን እንደማይችል ተቀባይነት ያለው የህግ ጽንሰ ሐሳብ በመሆኑ የአቶ እንዳልካላቸው አካሉና የአቶ ግርማ ወ/የስ ተግባር የተጠሪን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀፅ 40(1)(2) ድንጋጌዎች ጥበቃ ያገኘውን የንብረት ባለቤትነት መብት ሊጎዳ አይገባም፡፡

1ኛ ተጠሪ የወ/ሮ አይከልክሉሽም ደስታ ወራሽ ነኝ በማለት ማስረጃ ከያዙ በኋላ  የቤቱን ስመ ሃብቱን የሚያሳይ ማስረጃ መያዛቸውን ገልጸው የተከራከሩ ሲሆን አመልካችም ቢሆን ይህንኑ ሳይክዱ ስመ ሃብቱ የዞረው በሐሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ በመሆኑ በሕግ ፊት ውጤት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሠጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀስውን ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊገመት እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው የሕግ ግምት ፍፁም የሆነ ወይም ደምዳሚ ማስረጃ አይደለም፡፡ግምቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት ነው፡፡በመሆኑም አንድ ሰው በአስተዳደር አካል የተሰጠ ካርታ በመያዙ ብቻ በካርታው የተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሕጋዊ ባለሃብት እንደሆነ ሕጉ ግምት ቢወስድለትም ይህ ግምት ግን ካርታው የተሰጠበትን አግባብ  ከደንቡ፣ከአሰራሩና ከስልጣኑ ውጪ እንዲሁም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሰረት ማስረጃው ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ የሕጉን ሕሊናዊ ግምት ማፍረስ እንደሚቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ በሐሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ ስመ ሃብቱን መያዛቸው የአመልካችን መብት ቀሪ የማያደርገው መሆኑን ከተጠቃሽ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዙት ሙሉ ባለመብት ካልሆኑ 1ኛ ተጠሪ  በመንደር ውል በመግዛት መሆኑ ከተረጋገጠ ሕጋዊ ባልሆነ ሽያጭ መነሻ ቤቱን አግኝቼአለሁ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የአመልካችን ክርክር ዋጋ የሚያሳጣበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡1ኛ ተጠሪ ውሉን በውልና ማስረጃ ያላደረጉ መሆኑ ግልፅ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች የ2ኛ ተጠሪን ተግባር ሕጋዊ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት የቅን ልቦና ገዥ ናቸው በሚል ምክንያት ነው፡፡ይሁን እንጂ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው በውሉ ለገዥው መድህን ለመሆን ግዴታ ገብቶ ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ የገዛውን ገዥ ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 997 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ቢሆንም አመልካች ይህንኑ ግዴታ በተገቢው መንገድ ተወጥተዋል ለማለት የሚቻል ያለመሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያስገነዝብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡2ኛ ተጠሪ በመንደር ውል ቤቱን የገዙ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ተገቢውን ማጣራት አድርገውና በጥንቃቄ የገዙና ቅን ልቦና ያላቸው ናቸው ተብሎ ሕጋዊ ገዥ ናቸው ሊባሉ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በአጠቃላይ 2ኛ ተጠሪ  አከራካሪውን ቤት የገዙት የፍርድ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት

ካለመሆኑ በላይ የመንደር ውሉን ሰነድን እንኳን ያላቀረቡት ካርታው በ1ኛ ተጠሪ ስም ተስርቶ ተሰጥቷል በሚል ምክንያት ብቻ የሽያጭ ውሉ ሕጋዊ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1)(2) የተከበረላቸው እና በፍትሓ ብሔር ሕጉ ስለውርስ በሚደነግጉት ድንጋጌዎች ጥበቃ የሚደርግለት የባለሃብትነት መብታቸው ከሕግ አግባብ ውጪ ስለመደረጉ በተረጋገጠው የሽያጭ ውል ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት አለመኖሩን በመገንዘብ የበታች ፍርድ ቤቶች የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለሃብት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ናቸው በማለት በአይነት የውርስ ሃብት ነው በማለት መወሰን ሲገባቸው አመልካች የሽያጩን ገንዘብ እንዲወስዱ ሲሉ የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 32341 ሚያዚያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118918 ታህሳስ 09 ቀን 2005 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ቀበሌ 14/21 ቁጥሩ 482 የሆነው መኖሪያ ቤት በ1ኛ ተጠሪና በሟች አይከልክሉሽም ደስታ በውርስ ተይዞ የቆየ በመሆኑና ለ2ኛ ተጠሪም በሕጋዊ ሽያጭ ያልተላለፈ በመሆኑ የአመልካች ግማሽ ድርሻ በውርስ ሕጉ በተመለከቱት የክፍፍል ስርዓቶች መሰረት የሚገባቸው ነው ብለናል፡፡ የኪራይ ገንዘቡን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. የ2ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውል ሕጋዊ አይደለም ብለናል፡፡2ኛ ተጠሪ የሽያጩን ገንዘብ ከ1ኛ ተጠሪ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፤

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 86049

መስከረም 20 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች - ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሻፊ አብዱራህማን አብዱ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ አንሻ እንድሪስ - ቀረቡ

2. አቶ ኢተፋ በቀለ

3. ወ/ሮ ደምሴ (ፋጡማ) አሊቶ } አልቀረቡም

**ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በኢሉ ገላን ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመፋለም የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርበው በአጃጂ ከተማ ውስጥ ቁጥሩ 858 እና ቁጥሩ 859 የሆነ ቤት አለኝ፡፡ በእነዚህ ቤቶች ከዚህ በፊት የእህል ንግድ ሳከናውንባቸው ቆይቼ ኪሳራ ስለደረሰብኝ ቤቶቹን ዘግቼ ሥራ ፍለጋ ሌላ ቦታ ሄጄ ቆይቻለሁ፡፡ በዚህ ወቅት የተዘጉትን ቤቶች ቀበሌው በመክፈት ለሌሎች ሰዎች ሲያከራየው ቆይቷል፡፡ እኔም ከሄድኩበት ተመልሼ ቤቴ እንዲለቀቅልኝ ስጠይቅ ከተማው አስተዳደር በጽሁፍ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የቀበሌው አስተዳደርም ለተከራዮቹ(ተጠሪዎች) በጽሁፍ አሳውቋል፡፡ ተከሳሾችም ቤቱን ለእኔ ኪራይ እየከፈሉ ለመኖር ጠይቀውኝ በወር ብር 5 (አምስት ብር) አከራይቻቸዋለሁ፡፡ እኔም የቤቱን ግብር ያለማቋረጥ እየከፈልኩ እገኛለሁ፡፡ ሆኖም በማላውቀው ሁኔታ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ የቀበሌው አስተዳደር ቤት ኪራይ ከተከራዮች እየተቀበለ በመሆኑና ተከሳሾች ቤቱን እንዲለቁ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቀበሌው የቤት ኪራይ መቀበሉን እንዲያቆምና ተከሳሾች ቤቱን እንዲያስረክቡኝ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተጅ ቀበሌ 01 በአንደኛ ተከሳሽነት ቀርቦ ቤቱ በደርግ ጊዜ የተወረሰ ነው፡፡ የከሳሽ ንብረት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዎችም(ተከሳሾች) ቤቱ መንግስት ወርሶን ያከራየንና ለረዥም ጊዜ በእጃችን

የቆየ ነው፡፡ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፣ ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

2. የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ የአምቦ ከተማ አስተዳደር ክስ የቀረበባቸውን ቁጥራቸው 858 እና 859 የሆኑ ቤቶች ቀበሌው አላግባብ የያዘባቸው መሆኑን በማረጋገጥ ቤቱ እንዲለቀቅ ደብዳቤ ጽፏል፡፡ የቀበሌው አስተዳደርም ተከራዮቹ ቤቱን ለከሳሽ እንዲለቁ በማለት በደብዳቤ አሳውቋል፡፡ ከዚህ በኋላ ተከሳሾች ቤቱን ከከሳሽ ፈቃድ ውጭ የሚይዙበት የህግ መሰረት የሌለ በመሆኑ ቤቱን ለቅቀው ለከሳሽ እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከሕግ ውጭ የተወረሱ ቤቶች መዳኘት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት አይደለም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ጸንቷል፡፡

3. አመልካች በ01/05/2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ቤቶቹ ከአዋጅ ውጭ የተወረሱ ቤቶች አይደሉም፡፡ ቤቶቹን ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የእህል ንግድ ሳከናውንባቸው የነበሩ የግል ንብረቶች መሆናቸውንና የንግድ ኪሳራ ሲደርስብኝ ዘግቼ ወደሌላ ቦታ በመሄድ ቀበሌው ከፍቶ ሲያከራያቸው የነበሩ መሆናቸውን በአስተዳደሩ ክፍል ተረጋግጧል፡፡ ይህም በመሆኑ እኔ ያቀረብኩት የመፋለም ክስ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ሆኖ እያለ፤ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር ችሎት ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በ11/06/2005ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱ በመንግስት የተወረሰ ሥለሆነ አመልካች አላግባብ ተወርሶብኛል የሚል ከሆነ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያቅርቡ በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በ28/06/2005 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ለሥር ፍ/ቤት ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ መሰረታዊ ባህሪና ይዘት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች እንዲለቀቁለት የሚጠይቃቸው ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት በትርፍነት ያልተወረሰና ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 በኋላ በእሱ እጅ የነበሩና የእህል ንግድ ሲያከናውንባቸው የነበሩ መሆናቸውን በክሱ የገለጸ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቤቶቹ ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 ውጭ በባለስልጣን ቃል ትዕዛዝ ወይም በቀላጤ ያልተወረሱ መሆኑና አመልካች በሚነግድበት ወቅት ስለከሰረና ቤቶቹን ዘግቶ አካባቢውን ለቆ ለረዥም ጊዜ በመጥፋቱ የቀበሌው አስተዳደር ቤቶቹን ከፍቶ ማስተዳደርና ለሌሎች ሰዎች ማከራየት የጀመረ መሆኑን በክሳቸው ገልፀዋል፡፡

6. ይህ አመልካች በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነው ተጅ ቀበሌ 01 ቀበሌ ቤቶቹን የያዘውና ማስተዳደር የጀመረው በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ተወርሰው ወይም ከአዋጅ ውጭ በባለስልጣን ቃል ትዕዛዝ ወይም በቀላጤ ሳይሆን የቤቶቹ ባለቤት በመጥፋቱና ቤቶቹ ተዘግተው ረዥም ጊዜ በመቆየታቸው በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2257 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የስራ አመራር ተግባር ለመፈፀም በወሰደው እርምጃ ነው የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ አመልካች በማስረጃነት ያቀረባቸውና አንቦ ከተማ አስተዳደርና ቀበሌው አስተዳደር የጻፏቸው ደብዳቤዎች ይህንን የአመልካችን ክስ ባህሪና ይዘት የሚመለከቱ ናቸው፡፡
7. በጥቅሉ ሲታይ አመልካች ክስ ያቀረበው በአዋጅ የተወረሰ ቤት ለማስመለስ ወይም ከአዋጅ ውጭ በባለስልጣን ቃል ትዕዛዝ ወይም በቀላጤ የተወሰደባቸውን ቤት ለማስመለስ አይደለም፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበው በቤቶቹ ላይ ያለውን የባለሃብትነት መብት ለማስከበርና ለመፋለም ነው፡፡ ይህንን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች እንጅ የፕራይቬታይዜሽን ኤጅንሲ ወይም ሌላ አካል አይደለም፡፡ የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ይግባኝና አመልካች የሰጠውን መልስ በመመርመር በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

# ከውል ውጪ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁጥር 89504

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን
2ኛ. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት } የቀረበ የለም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ግራ ቀኙ በሥር ፍ/ቤቶች ባደረጉት ክርክር ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮች በመነሳት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በመዳረግ ለቀረበው የጉዳት ካሣ ክስ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች ለንብረት ጉዳት ካሣ መድን በመግባቱ ምክንያት የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና በሶስተኛ ወገን ተግባር ጉዳት ደርሶበታል በሚል በገባዉ የመድን ዋስትና ግዴታ መሰረት በተጎዳው መኪና ባለቤት እግር ተተክቶ በመዳረግ ክስ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው በተጎጂው መኪና ባለቤት እግር ተተክቶ በመዳረግ የሚጠይቀውን የጉዳት ካሣ ገንዘብ መጠየቅ የሚችለው ከማን ነው? የሚለውን ነው፡፡

በቀጥታም ሆነ በመዳረግ ሶስተኛ ወገን ተግባር ጥፋት ሳቢያ በደረሰ ጉዳት የጉዳት ገንዘብ ከማን ላይ መጠየቅ እንደሚቻል ጉዳዮን በቀጥታ በሚመለከተው አግባብነት ካለው የፍ/ብሔር ህግም ሆነ በአንድ ጉዳይ በተከሳሽነት መጨመር የሚገባቸው ወይም የሚችሉት ወገኖች እነማን እንደሆኑ በሚያመለክተው ስነ-ስርዓታዊ ህጎች በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ መሰረታዊ ሆነ ሥነ-ስርዓታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ከሳሽ የሆነው ወገን በክስ የሚጠይቀውን ገንዘብ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ማግኘት እንዲችል እነማንን አጣምሮ መክሰስ እንደሚችል ከመደንገጉ በቀር በጉዳት ካሣ ክስ ምክንያት ሊጠየቁ የሚችሉትን ወገኖች ሁሉ አጣምሮ መክሰስ እንዳለበት በህጉ ግዴታ አልተጣለበትም፡፡ አጣምሮ መክሰስ የሚገባውን ሁሉ በቶሎ እና ክርክሩ በተነሣበት የዳኝነት አካል አጣምሮ ያለመክሰሱ ተግባር በማግኘትም ሆነ በማጣት ረገድ በእራሱ ላይ ጉዳት ከሚያስከትል በቀር በጉዳዩ ላይ



www.chilot.me

የሚመለከታቸውን ሁሉ በአንድ ላይ በአንድ ፍ/ቤት አጣምሮ እንዲከስ በህግ የተጣለበት ግዴታ የለም፡፡ በዚህም መሰረት የአሁን አመልካች የጉዳት አድራሹ መኪና ባለቤት ነው ባለው በአሁን 1ኛ ተከሳሽ ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ ይህ 1ኛ ተከሣሽም ጉዳት ያደረሰው መኪና ባለቤት ስለመሆኑ እንደ ህጉ አነጋገር የመኪናውን ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ በማረጋገጥ የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677፣1896 እና 2081ና በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 36/2/ መሰረት የአንድነትና የነጠላ ግዴታ ካለባቸው ወገኖች መካከል የአሁን አመልካች በከሳሽነቱ የመኪናዉ ባለቤት ላይ ክስ የማቅረብ መብት ያለው በመሆኑና 1ኛ ተጠሪም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 18 እና 2156 መሰረት ኃላፊነቱን በመጨረሻ በሚሸከመው ወገን ላይ በተራው ተተክቶ ክስ ከሚያቀርብ በቀር ልከሰስ አይገባም በማለት ለመከራከር ህጉ መብት አይሰጠውም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ ለዚህ ጉዳይ መነሻ በሆነው ክስ ላይ መጠቀስ ያለበት የመኪናው ባለቤት ማን ነው? የሚለው ሳይሆን ተሽከርካሪው ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበት የነበረው ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የመኪናው ባለቤት መሆኑ ቢረጋገጥም ከሳሽ ይህንኑ 1ኛ ተጠሪን ለመክሰስ ከህግ የመነጨ መብት የለውም የሚለውን ትርጉም በመከተል የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ከዚህ በላይ በፍርድ ሐተታው ከተገለፀው ህጋዊ ምክንያት አንፃር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. ይግባኝ ሰሚው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁጥር 126387 ጥር 15 ቀን 2005 ዓ.ም እና በኮ/መ/ቁጥር 190104 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጡት ፍርዶች ሁሉ ተሽረዋል፡፡
2. የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሰ/ቁ 5-01-00002 ኢ.አ የሆነው ተሽከርካሪ ባለቤት በመሆኑ ምክንያት ብቻ ለቀረበበት የጉዳት ካሣ ገንዘብ ክስ ከህጉ የመነጨ የመካስ ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡ ስለሆነም የመካስ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ታውቆ በሌላው የኃላፊነት ነክ ክርክሩ ረገድ ማለትም ጥፋት አለ የለም? ጉዳት ደርሷል አልደረሰም? የጉዳት ልክስ ምን ያህል ነው በሚል በፍሬ ነገር ክርክር ደረጃ የተነሣ ክርክር ካለ በስር ፍ/ቤት በአቤቱታ ፅሑፍ አቀራረብ የክርክር ደረጃ አንስቶ ከተከራከረበት ነጥብ አንፃር በማየት ጉዳዩ ታይቶ ይወሰን ዘንድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 341 መሰረት ጉዳዩን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ደረጃ የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ሮ/ብ

የሰ/መ/ቁ. 91710

ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ሕጻን ሪያን ሚፍታህ ሞግዚት ወ/ሮ ፋጡማ በሽር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ኤልሲውዲ ኬብልስ ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡የአመልካች ሞግዚት በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ የከሳሽን እውቅናና ፈቃድ ሳያገኝ የህፃኑን ፎቶ ከሰኔ ወር 2000 ዓ/ም ጀምሮ ለማስታወቂያ ስራ በመጠቀም ግዙፍ የሆነ የማስታወቂያ ሰሌዳ በማሰራት ድርጅቱንና የድርጅቱን ምርቶች በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ቦታዎች እና ግብጽን ጨምሮ በተለያዩ ሃያ አምስት ሀገራት በኢተርኔት ሲያስተዋውቅ መቆየቱን፣ይህ ሕገ ወጥ ተግባር በመሆኑ ተገቢውን የካሳ ክፍያ እንዲፈፅም ቢጠየቅም ፈቃደኛ ሳይሆን ቆይቶ በኋላ ላይ ብር 15,000.00 (አስራ አምስት ሺህ ብር) ለመክፈል ቢደራደሩም ክፍያው በማስታወቂያ ስራ ከተገኘው ጥቅም ጋር ሲነፃፀር ተመጣጣኝ ያልሆነና አነስተኛ በመሆኑ ከሳሽ ሊስማሙ ያለመቻላቸውን ዘርዝረው ከሰኔ ወር 2000 ዓ/ም ጀምሮ እስከ የካቲት ወር 2004 ዓ/ም ለማስታወቂያ ስራ ለተጠቀመው የህፃኑ ፎቶ ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ) እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱንም የተጠሪ በኩል የቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገር ደረጃ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ሲሆን የካሳውን መጠንም በተመለከተም በርትዕ ብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) ሊሆን እንደሚገባው ወስኖ ይህንኑ የገንዘብ መጠን ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የአሁኗ አመልካች ደግሞ የካሳ መጠኑ ላይ ቅር በመሰኘት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱ የአመልካችን መስቀለኛ ይግባኝ ሰርዞ በተጠሪ ይግባኝ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፀናው ሲሆን በካሳ መጠኑ ላይ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ግን በማሻሻል ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) እንዲሆን ወስኗል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በጉዳዩ ላይ ካሳን በተመለከተ ሁለቱም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ

የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል ምክንያት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ተጠሪ የህጻኑን ፎቶ ለማስታወቂያ ስራ የተጠቀመበት ስለመሆኑና ይህንንም ሲያደርግ ከሕፃኑ ሞግዚት ተገቢውን ፈቃድ ያላገኘ መሆኑ እንዲሁም በማስታወቂያው ተጠሪ የኤሌክትሪክ ኬብል ምርቶችን በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች በሰሌዳ ለጥፎ ማስታወቁን፣በግብጽና በሌሎች ሃያ አምስት ሃገራት በኢንተርኔት ሲያስተዋውቅም የሕፃኑን ፎቶ ጥቅም ላይ ያዋለ መሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ተጠሪም ቢሆን በዚህ ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ስርዓቱን ጠብቆ በበላይ ፍርድ ቤት ስለመቀየሩ ገልጾ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ስለሆነም ተጠሪ የህጻኑን ፎቶ ለኤሌክትሪክ ኬብል ምርቶቹ ለማስተዋወቅ ያለሕፃኑ ሞግዚት ፈቃድ መጠቀሙ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27 ድንጋጌ ስር ባለፎቶግራፉ ወይም ባለስዕሉ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ ወይም ስዕል በሕዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይቻል የተመለከተ በመሆኑና በፍ/ሕ/ቁጥር 28 ስር የተመለከተው ልዩ ሁኔታ ስለመኖሩም ተጠሪ ጠቅሶ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የሕፃኑ ፎቶ ጥቅም ላይ ለዋለበት የማስታወቂያ ስራ ተጠሪ ካሳ የማይከፍልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡በዚህ ሰበር አከራካሪ የሆነው የካሳ መጠኑ ሲሆን ካሳው የሚከፈልበትን አግባብ በተመለከተ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የሕጉ ክፍል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) ድንጋጌ ስር አስፍሯል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት በርትዕ አስፈላጊ ሁኖ ሲታይ ስዕሉን በአደባባይ በመለጠፍና በመሸጥ የተጠቀመው ሰው በዚሁ ምክንያት ያገኘው ሀብት ተመዛዛኝ በሚሆንበት መጠን ዳኞች ካሳ እንዲከፍል ሊወስኑበት እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የካሳውን መጠን ክዶ በመከራከሩና አመልካችም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 በተመለከተው አግባብ ትክክለኛውን የካሳ መጠን በማስረጃ ያለማስረዳታቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የካሳውን መጠን ብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) እንዲሆን የወሰነ ሲሆን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘትም በስርዓቱ መሰረት የመስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የካሳ መጠኑን የሕጻኑ ፎቶ በማስታወቂያው ከተገለፁት የምርት አይነቶች ጋር የሚኖረውና ሊያስገኝ ከሚችለው ጥቅም አንፃር፣ከነባራዊው ሁኔታ በመነሳት በመመርመር በስር ፍርድ ቤት የተወሰነው የካሳ መጠን የባዛ ሁኖ ማግኘቱን ጠቅሶ ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) የካሳ መጠን ሊሆን እንደሚገባ ወስኗል፡፡ይህ የበታች ፍርደ ቤቶች የካሳ ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡የአመልከች የመስቀለኛ ይግባኝም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ታይቶ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ይህም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 340 እና 337 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የተከተለ መሆኑን ከሚያስገነዝብ ውጪ የአመልካች የመስቀልኛ ይግባኝ ሳይታይ የታለፈ ነው ለማለት የማያስችል በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝም የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም ካሳን አስመልክቶ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸውን

የጉዳት ካሳ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት 182576 መጋቢት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 135075 ሰኔ 24 ቀን 2005 ዓ/ም የተሻሻለው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ለአመልካች በርእት ብር 150,000.00(አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ተጠሪ እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈፀመም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡*

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሐሣብ

በዚህ ጉዳይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ የህፃን ሪያን ሚፍታህን ፎቶ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ላሉት 4 ዓመታት ያለፈቃዳ ምርቱን በሐገር ውስጥ ግብጽ እና በሌሎች 25 ሃገራት በተለያዩ መንገዶት ሲያስተዋውቅበት መቆየቱን ካረጋገጠ እና ለክሱም ተጠሪ ኃላፊ መሆኑን ከወሰነ በኃላ የካሣ መጠኑን በተመለከተም ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090፣ 2091፣2102 እና 29/2/ ድንጋጌዎች ይዘት አኳያ በመመርመር አመልካች እንዲከፍለው የጠየቀውን የካሣ ክፍያ ብር 400,000 እንዳለ ባለመቀበል እና በሌላ በኩልም ተጠሪ የህፃኑን ፎቶ በመጠቀም ያገኘው ጥቅም በትክክል ምን ያህል እንደሆነ ሂሣቡ ተሰልቶ በግልጽ የታወቀ ነገር ባይኖርም ሆኖም ንግ ፎቶውን ለምርቱ ማስታወቂያነት የተጠቀመበትን የጊዜ እርዝማኔ እና ማስታቂያ የተሰራጨበትን ሃገራት ብዛትና የስርጭት አድማሱን ግምት ውስጥ በማስገባት እና በሁለቱም በኩል ግንዛቤ ውስጥ ገብተው ሲታዩ የሚገቡትን አጠቃላይ ሁኔታዎች በመመዘን ተጠሪ በርትእ ብር 200,000 ለህፃን ሪያን እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

በተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ኃላፊነትን በተመለከተ በበታች ፍ/ቤት የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል ሙሉ በሙሉ ካፀና በኃላ የካሣ መጠኑን በተመለተ የሰጠውን የውሣኔ ክፍል ግን ብር 200,000 የተጋነነ ነው በማለት መጠኑን ወደ ብር 150,000 በመቀነስ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ሆኖም ግን በመርህ ደረጃ የካሣ መጠንን አስመልክቶ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ደኞች በተወሰነ ፍርድ ላይ ለበላይ ፍ/ቤቶች ይግባኝ ለማለት አይቻልም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2152 ሥር ከተደነገገው አኳያ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም የካሣ መጠንን በተመለከተ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚቀፈቀደው በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2153 ሥር እንደተመለከተው ልዩና የተበቁ ሁኔታዎች ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችም

* የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካሣ አከፋፈሉን ሲወስን ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የማይገባቸውን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ እንዲገቡ አድርጐ ከሆነ ወይም ግንዛቤ ውስጥ መግባት የነበረባቸውን ሁኔታዎች ሣያስገባ ቀርቶ እንደሆነና፤
* የካሣ መጠኑም በግልጽ ከአእምሮ ግምት ውጭ በሆነና የተወሰነውም በማድላት ወይም በዝንባሌ መሆኑ እርግጥ ሆና የተገኘ እንደሆነ፤
* እንዲሁም በፍ/ቤቱ የተወሰነው የካሣ ገንዘብ በሒሣብ ረገድ ስህተት ያለበት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከፍ ሲል እንደተገለፀው ለአመልካች ሊከፍል የሚገባውን የካሣ ክፍያ ከማስታወቂያው ጊዜ ቆይታ እና የስርጭት እንድማሱን ግምት ውስጥ በማስገባት እና ጉዳዩንም ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 29/2/፣ 2102፣2090 እና 2091 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስ አኳያ አገናዝቦ ተጠሪው ካገኘው ጥቅም ጋር ተመዛዛኝ ነው ያለውን ብር 200,000 ለአመልካች እንድከፍለው ወስኗል ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ እንደሚታወቀው ልጆች በተፈጥሮአቸው ከአዋቂ ሰው በተለየ ሁኔታ ተወዳጅ እና የሰውን ስሜት የሚስቡ በመሆናቸው ተጠሪም ከዚህ ውጭ ባልሆነ ምክንያት ያለምንም የልጅም ሆነ የልጁ ሞግዚት ፈቃድ ውጭ ፎቶውን ለምርቱ ማስተዋቂያነት ተጠቅሞ ጥቅም እስካገኘ ድረስ ለህፃኗ ካሣ የማይከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ በዚሁ አግባብ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በርትእ ተገቢ ነው ያለውን ተመዛዛኝ የሆነ ውሣኔ ሰጥቷል ሆኖም ግን ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2152 እና 2153 ድንጋጌዎች ይዘት አኳያ በበታች ፍ/ቤት የተሰጠውን የኪሣራ ገንዘብ በይግባኝ ክርክር ደረጃ ተመልክቶ ውሣኔውን ለመለወጥ የሚያስችለው በቂ የሕግ እና የፍሬ ነገር ምክንያት ሣይኖር የተጋነነ ነው በሚል ምክንያት ወደ ብር 150,000 መቀነሱ አግባብ አይደለም፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የሕጉን ድንጋጌወች ይዘትም ያገናዘበ አይደለም ይህ በሕጉ ረገድ የተፈፀመው ስህተትም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መታረም ሲገባ በአብላጫ ድምጽ እንዲፀና መደረጉ ተገቢ አይደለም በማለት ስሜ በ3ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ የልዩነት ሐሳቤን አስቀምጫለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 92020

ታህሣስ 15 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች፡- 1. የኢ.ፌ.ዲ.ፌዴሬሽን ምክር ቤት } ነ/ፈጅ ጥሩነሽ ገረመው ቀረቡ

2. አቶ ተስፋዬ ጌታሁን

ተጠሪ፡- ቄስ ማሞ ይታፈሩ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ምንም የጥቅም ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ አቅመ አዳም ያልደረሰን ሕፃን በተሽከርካሪ ጭኖ በመንዝ ሂደት ተሽከርካሪው ተገልብጦ ሕፃኑ ለሞት ሲዳረግ የመኪናውን ባለንብረትና አሽከርካሪው ስላለባቸው ፍትሐብሔር ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የተታየው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ተከሣሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ 2ኛ አመልካች አሽከርካሪ በመሆን የ1ኛ አመልካች ንብረት የሆነውን የሰሌዳ ቁጥር 4-14199 ኢት ፒካፕ የሆነ መኪና ሲያሽከረክር ግንቦት 08 ቀን 2002 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍል ከተማ ቀበሌ 03/04 ብረት ድልድይ ከተባለ ቦታ ወደ ፈረንሣይ ኢንባሲ አቅጣጫ እያሽከረከረ በውጪ እቃ መጫኛ ላይ እድሜው 13 አመት የሆነ ደረጃ ማሞ የተባለ ህፃን ጭኖ በመንዝ ላይ እያለ ሕፃኑ ወድቆ እንዲሞት ማድረጉ ሕፃኑን በሕይወት እያለ ጫማ በመጥረግ ለተጠሪ ገቢ ሲያገኙላቸው የነበረ መሆኑን በጉዳቱ ምክንያት ለህክምናም ሆነ ለቀብር ስነ ስርዓት ወጪ ያወጡ መሆኑን፣ ሕፃኑ በሕይወት ቢኖሩ ኑሮ እድሜው ሃምሳ ዓመት እስኪሞላው ለተጠሪ ያስገኝ የነበረው የቀን ገቢ ብር 8.00 እንደሚቀጥልና በመሞቱ ምክንያት ግን መቋረጡን ዘርዝረው ይህንኑ ገቢና በጉዳቱ ምክንያት ያወጡትን ወጪ በድምሩ ብር 119,870.00 (አንድ መቶ አስራ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ብር) እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና የቀረበው የካሳ ክፍያም የሕግ መሰረት የሌለው መሆኑን



www.chilot.me

ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ተደርጓል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የተጠሪን ምስክሮች በመስማት ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾችን ለክሱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን ጣልቃ ገቡን ግን ከክሱ ነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ የካሳውን መጠን በተመለከተም በርትዕ በድምሩ ብር 31,300.00 (ሰላሳ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር) እንዲሆን ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኙ በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አመልካቾች ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በክርክሩ ውስጥ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡት ነጥቦች የተጠሪ ልጅ የሕዝብ ማመላለሻ ባልሆነው የ1ኛ አመልካች መኪና በ2ኛ አመልካች በእቃ መጫኛው ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ ወድቆ ለሕልፈተ ሕይወት መዳረጉና 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች ተቀጣሪ ሰራተኛ መሆናቸው፣ ለጉዳቱ መድረስ ጥፋቱ የሹፌር መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣ በመሰረቱ የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2089/1/ የሚገኘው ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በሚለው በፍታብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 ስር ነው፡፡ ተጠሪ አመልካቾች የከሰሱትም ከውል ውጪ ደረሰ የሚለውን ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው ህፃኑ የተባለው ጉዳት የደረሰበት በ1ኛ አመልካች መኪና በመገጨቱ ሳይሆን፣ በመኪናው ላይ በ2ኛ አመልካች እውቅና ተሳፍሮ ሲሄድ ከመኪናው በመውደቁ ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ መኪናው የ1ኛ አመልካች ንብረት ነው፡፡ ሆኖም መኪናው ገንዘብ በማስከፈል ሰዎችን የሚያጓጉዝ የንግድ መኪና ሳይሆን ለመንግስት ስራ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ህፃኑ በመኪናው ላይ ስለመሳፈሩ 1ኛ አመልካች ያውቃል ወይም ማወቅ ይጠበቅበታል ተብሎ አይገመትም፡፡ መኪናው የተሰማራው ሰዎችን ለማጓጓዝ ባለመሆኑ 1ኛ አመልካች ሚቱን ህፃን በማሳፈር ያገኘው ጥቅም አለ ብሎ ለመደመደም የሚቻልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ እነዚህን ሁኔታዎች ከተረጋገጡ ቀጥሎ መታየት ያለበት አመልካቾች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆኑበት የሕግ አግባብ አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2081/1/ እንደተደነገገው የመኪናው ባለቤት መኪናው በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት አግባብ አለ፡፡ ይህ እንግዲህ በአጠቃላይ የተቀመጠ የኃላፊነት መርህ ሲሆን፣ በቁ 2089 ደግሞ ልዩ ሁኔታ ማለትም የመኪናው ባለቤት ኃላፊ የማይሆንበት ሁኔታ ተደንግጎአል፡፡ ከድንጋጌው ርእስ መገንዘብ እንደሚቻለው ጉዳቱ የደረሰው ጥቅም በሌለው ግንኙነት ጊዜ ሲሆን የመኪናው ወይም ጉደቱን ያደረሰው ንብረት ባለቤት ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡ ከላይ እንዳመለከትነው ተጠሪ በአመልካች መኪና የተገለገለው ለአመልካች ጥቅም በማያስገኝ ሁኔታ ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ 1ኛ አመልካች በዚህ ረገድ ጥፋት ፈጽሞአል አልተባለም፡፡ ይልቁንም የ1ኛ አመልካች ሹፌር፤ 2ኛ አመልካች ጥፋት መፈፀሙ ተረጋግጧል ተብሎ 1ኛ አመልካች ኃላፊነቱን እንዲወስድ

መደረጉን የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በግልጽ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2089/2/ ድንጋጌ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ ስር የተቀመጠውን መርህ በልዩ ሁኔታ ያስቀመጠ ሲሆን ባለሃብቱ ወይም ጠባቂው ጥፋት ማድረጋቸው ከተረጋገጠ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ድንጋጌው ያሳያል፡፡ በዚህ ልዩ ሁኔታ አነጋገር መሰረት የመኪናውን ባለሃብት ወይም ጠባቂውን ጥቅም በሌለው ግንኙነት መኖሩ ቢረጋገጥም ተጠያቂ ማድረግ የሚቻለው ባለሃብቱ ወይም ጠባቂው ጥፋት ካለባቸው ብቻ ነው፡፡ በድንጋጌው ስር ባለሃብት የሚለው ቃል ግልጽ ሲሆን ጠባቂ የሚለው ቃል ግን ግልጽነት የጎደለው መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በዚህ ረገድ በተጠሪ በኩል ለቃሉ እየቀረበ ያለው ክርክር ባይኖርም ተቀጣሪ ሹፌር ጠባቂ በሚለው ቃል የሚሸፈን ነው ወይስ አይደለም የሚለው የሕግ ጥያቄን ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአማርኛው አቻ የእንግሊዘኛ ቃሉ "holder" በሚል የተቀመጠ ሲሆን ይህ ቃል በሕግ መዝገበ ቃላት ከተሰጠው ትርጉም አንዱ a person who possesses or uses property በሚል የተቀመጠ መሆኑን ታዋቂው የብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት ያሳያል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ጠባቂ የሚለው ቃል ለራሱ ጥቅም መኪናውን ይዞ የሚገኘውን ሰው መሆኑን ነው፡፡ ሹፌር በሰራው ምክንያት ላጠፋው ጥፋት ካልሆነ በስተቀር አሰሪው የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ባለሃብት ተጠያቂ የሚሆንበት አግባብ የሌለ መሆኑን ተጠቃሹን ድንጋጌው ከፍ/ህ/ቁጥር 2126/2/፣2127፣2130 እና ከፍ/ሕ/ቁጥር 2131 ድንጋጌዎች ይዘት ጋር በማገናዘብ ስናነብ የምረዳው ጉዳይ ነው፡፡ የ1ኛ አመልካች ሹፌር የሆኑት 2ኛ አመልካች ስራውን ሲሰሩ የፈፀሙት ጥፋት የሌለ ስለመሆኑ ወይም ጥፋቱ የ2ኛ አመልካች የግላቸው ስለመሆኑ 1ኛ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2126/2/ እና 2127 ድንጋጌዎች አግባብ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ ይልቁንም ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ከሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሆነውን የተጠሪ ልጅ ህፃን ደረጀ ማሞን በእቃ መጫኛው ላይ 2ኛ አመልካች በስራ ላይ እያሉ ጭነው ለህልፈት መዳረጋቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አንድ ባለሃብት ጥቅም በሌለው ግንኙነት ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነት የሚወስድበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 38457 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍ/ቤትን የሚያስገድድ የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ቢሆንም ይህ ጉዳይ ግን ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ ሊታይ የሚገባው ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም በሰ/መ/ቁጥር 38457 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመሰረታዊ ፍሬ ነገሮች በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጉዳይ ጋር የሚገኛኝ ሁኖ ስላልተገኘ ለውሳኔው መሰረት ለማድረግ የምንገደድበት ሁኖ አልተገኘም ምክያቱም ጉዳቱ የደረሰው ህፃን ላይ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግለት ለሚገባው ለዚህ ህፃን 2ኛ አመልካች በ1ኛ አመልካች ስራ ላይ እንዳሉ ባሉበትና ጥንቃቄ ሳያደርጉ በተሽከርካሪ እቃ መጫኛ ጭነው ሲጓዙ ለህልፈት የዳረጉት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 38457 የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ሲነፃፀር ከተበዳዩም ሆነ በተበዳዩና በባለንብረቱ ከነበረው ግንኙነት ጋር የሚገናኝ አይደለምና ህፃናት በኢ.ፌ.ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 36/2/፣15 እና 25 ድንጋጌዎች እንዲሁም ኢትዮጵያ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶም በሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3፣ 6/1/ በአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4/1/፣5/1/ ድንጋጌዎች በሕይወት የመኖርና የአካል ደህነት ጥበቃ የተደረገላቸው መሆኑ ግልጽ ስለሆነ የካሳ ክፍያ ጉዳይም እነዚህን ሕጎችን ሁሉ እግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ነው በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካቾች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የማይሆኑበት

አግባብ የለም ሲጠቃለልም የሰር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በውጤት ደረጃ ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 37334 ሰኔ 17 ቀን 2005 ተሰጥቶ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 140091 ሐምሌ 11 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብሕ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ጸንቷል
2. አመልካቾች በተጠሪ ልጅ ላይ ደረሰ ለተባለው የሞት ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በድምሩ ብር 31,300.00 /ሰላሳ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ በሚመለከት ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ

ት ዕ ዛ ዝ

ሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የመስማሚያ ሀሳብ

እኔ ስሜ በሁለተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምፅ አመልካች ለተጠሪ ካሳ መክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ደረሰበት ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ፡፡ ሆኖም አብላቻው ድምፅ በሌሎች መዝገቦችና ተሳፋሪዎች ካሳ ሊያገኙ አይገባም በማለት በሰጣቸው የህግ ትርጉሞች የማልስማማ በመሆኑ የመኪናው ባለሀብት ሰራተኛው ላጠፋው ጥፋት ተጠያቂ በመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2089 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ መሰረት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የመስማሚያ ሀሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

ቤ/ዮ

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

የሰበር መዝገብ ቁጥር 88432

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ/ም

**ዳኞች**፡-1. ተሻገር ገ/ሥላሴ

2. አልማው ወሌ

3. ዓሊ መሐመድ

4. ረታ ቶሎሣ

5. ሙስጠፋ አሕመድ

**አመልካች**፡- ወጣት ደሣለኝ ወንታ የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- አቶ ኡስማን መሐመድ የቀረበ የለም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በጋሞ ጎፋ ዞን የሳውላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ አመልካች ተጠሪ መንገድ ላይ በቆለለው አፈር ምክንያት በደረሰብኝ አደጋ የአካል ጉዳይ የደረሰብኝ ስለሆነ ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ በሣውላ ከተማ ኩረቲ 01 ቀበሌ በሚገኘው መኪና መንገድ ተከሣሽ /ተጠሪ/ ለቤት መምረጊያ የሚሆን አፈር ቆልሏል፡፡ ተከሣሽ የቆለለው አፈር በምሽት ለማየት የሚያስቸግር ሲሆን ተከሣሹ ምልክት አላስቀመጥም፡፡ ከሣሽ በመንገዱ መስከረም 13 ቀን 2004 ዓ.ም በምሽቱ በአንድ ሰአት የሞተር ሣይክል እያሽከረከርኩ ስጓዝ ከማይታየው ተከሣሽ በቆለለው አፈር ላይ በመውጣቴ ሞተር ሣይክሉ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ አደጋ ደርሶብኛል፡፡ በደሰረብኝ አደጋ 12 የፊት ጥርሶች ወልቀዋል፡፡ የመንጋጋ ጥርሴም ጉዳት ደርሶበታል ስለዚህ ተከሣሹ በአውራ ጐዳና ላይ በግልጽ በማይታይ ሁኔታ ያለምልክት በቆለለው አፈር ምክንያት ለደረሰብኝ ጉዳት ብር 108810 /አንድ መቶ ስምንት ሺ ስምንት መቶ አስር ብር/ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ ኃላፊነት የሚያስከትል ምንም ተግባር ያልፈፀምኩ



www.chilot.me

በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝ ለአደጋው ተጠያቂ መንጃ ፈቃድ ለሌለው ለከሣሽ ሞተር ሣይክል ያዋሠው ሠውና ከሣሽ ነው፡፡ ከሣሽ መንጃ ፈቃድ አለኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

2 የሥር ፍርድ ቤት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሞተር ሳይክሉ ከቁጥጥር ውጭ የወጣው የቴክኒክ ብቃት ስለሌለውና አሽከርካሪው (ከሳሽ) ብቃት ስለሌለው ሊሆን ስለሚችል ተከሳሽ ለከሳሽ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን ይግባኝ ከመረመረና የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተከሳሽ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት ለሥር ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡የሥር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል ከሰማ በኃላ በከሳሽ(አመልካች) ላይ ለደረሰው ጉዳት ተከሳሽ(ተጠሪ) በከፊል ኃላፊ ነው በማለት ተከሳሽ ለከሻስ ብር 12235(አስራ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ብር) ካሳ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሥር ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ በአመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካቾች መጋቢት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ባልተፈቀደ የህዝብ ጎዳና አፈር መቆለሉና መንገዱ አፈር ተቆልሎበት ምልክት አለማስቀመጡ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ጉዳት የደረሰብን በተጠሪ ጥፋት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ አይደለም በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በመንገዱ ላይ አፈር የቆለለበት መሆኑን አስቀድሞ ያውቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ጉዳት የደረሰበት ከመሥመሩ ውጭ ሲያሽከረክር ነው፡፡ አመልካች በዚህ ሁኔታ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ስለሆነ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራረዋል፡፡ አመልካች በ07/10/2005 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረነል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ በፈጸመው ከፊል ጥፋት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታውን የተወጣ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሳኔአቸው አረጋግጠዋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ዕውነትን

የማፈላለግ ሥልጣናቸውን በመጠቀም በአመልካች ላይ አደጋው የደረሰው ተጠሪ በህዝብ አውራ ጎዳና መንገድ ላይ አፈር በመቆለሉና መንገዱ አፈር የተቆለለበት መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ባለማስቀመጡ አመልካች በምሽት መስመሩን ይዞ ሞተር ሳይክል በማሽከርከር ላይ እያለ ከተቆለለው አፈር ላይ በመውጣቱ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ መመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

6. ይህም አመልካች በተጠሪ ድርጊት የደረሰበትን ጉዳት ልክና የአካባቢ ሁኔታዎችን መሰረት በማረግ ተከሳሹ/ ተጠሪ/ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2141 በተደነገገው መሰረት የማስረዳት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን ያሳያል ለጉዳቱ አመልካች በከፊል አስተዋጽኦ የበረከተ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ቢሆንም ተጠሪ የመንገዱን ቀርጽ አፈር ቆልሎ በመቀየሩና መንገዱ አፈር የተቆለለበት መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ባለማድረጉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069 መሰረት ለአደጋው እና በአደጋው ምክንያት በአመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት በከፊል በኂላፊነት ተጠያቂ መሆኑን የሚያስቀረው አይደለም ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ ለጉዳቱ ምንም አይነት ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የጋሞጎፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የሳውላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ጸንቷል
3. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 82154

መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች** ፡- አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የንጽህና እቃዎችን ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም አቅርቦት ውልን መሠረት አድርጐ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ ክስ ይዘትም የአሁኑ አመልካች በ2001 ዓ.ም የበጀት አመት ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ መደበኛ ተማሪዎች አገልግሎት የሚውል የንጽህና እቃዎች ግዥ ጨረታ በአዲስ ዘም 67ኛ አመት ቁጥር 337 ነሐሴ 17/2000 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው ጨረታ ማስታወቂያ አውጥቶ የአሁኑ ተጠሪ ተወዳድረው የተሻለ ዋጋ አቅራቢ መሆናቸው ተረጋግጦ የአሁኑ አመልካችም የተጠሪን አሸናፊነትን በቁጥር አምዩ 92128/42 በቀን 13/02/2001 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የገለፀላቸው መሆኑን ተጠሪ በአስር ቀናት ውስጥ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የጠቅላላ ዋጋ 10% ብር 63,468.50 (ስልሳ ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ ምስንት ብር ከሀምሳ ሳንቲም) የአሁኑ አመለካች በስሙ ባስከፈተው ባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግ እና በሚሰጠው ኘርግራም መሠረት የአሁኑ ተጠሪ እቃዎችን እንዲያቀርቡ ውል እንዲፈጽሙ ያዘዛቸው መሆኑን በዚህም መሠረት ተጠሪ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትናዉን ገንዘበ ሕዳር 02 ቀን 2001 ዓ/ም በውል በመፈፀም አስይዘው በውሉ መሠረት ለአሁኑ አመልካች ብር 634,685.00 (ስድስት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) የሚያወጣ የንጽህና እቃዎችን አቅርበው አመልካችም ገቢ በማድረግ ዋጋውን የከፈላቸው መሆኑን ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ተጠሪን ጠቅላላ የጨረታውን ዋጋ 25% ማለትም የብር 333,155.00 (ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ብር) እቃ እንዲያስገቡ አዝዟቸው በዚሁ ትእዘዝ መሠረት የእቃ ግዥ መጠየቂያ ቀርቦ በአመልካች መስሪያ ቤት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተፈርሞና ደብዳቤው ተሰጥቶ የብር 333,155.00 ዋጋ ያለው እቃ ተጠሪ ገዝተው ለአመልካች በማቅረብ ንብርቱን ለአመልካች በሞዴል 19 ጣምራ ቁጥር 098954 በሆነው ገቢ አድርገው ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን የአመልካች ማስሪያ ቤት የእቃ ግዥ ንብረት አስተዳደር ክፍልም እቃውን ቆጥሮ ከተረከበ በኂላ ለአመልካች መስሪያ ቤት ፋይናንስ መመሪያ እቃውን ስለመረከቡ ማረጋገጫ የሰጠ መሆኑንና በውሉ መሠረት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ጥያቄ ቢያቀርቡም አመልካች

ፈቃደኛ ያልሆነ መሆኑን ዘርዝረው አመልካች ብር 333,155.00 ከተለያዩ ወጪና ኪሣራ እንዲከፍል ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ሕዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም የተደገው ውል የራሱን ፍጻሜ ያገኘ በመሆኑ ለክሱ መሠረት ሊሆን እንደማይገባ ተጠሪ የማይመጥን እቃ እንዲያስገባ የአመልካች ተቋም የበላይ ኃለፊ በየጽሑፍ ደብዳቤ ያላዘዙ መሆኑንና ተጠሪ ከበታች ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር የልታዘዘ ግዢ በሕገ ወጥ መንገድ በመነገድ ወደ ተቋሙ እንዲገባ መደረጉን ያለጨረታ ግዥ እንዲፈፀም የሚደረገውም በፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 68(2(ሀ)) ላይ እንደሰፈረው የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በጣም አስቸኳይ በሆነና ቢዘገይ በመስሪያ ቤቱ ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥርና የመስሪያ ቤቱ የስራ አፈፃፀም ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን በማመን በጽሑፍ ስረጋገጥ ብቻ እንጂ በሌላ ሰው ትእዛዝ ያጨረታ ግዥ መፈፀም እንደሌለበት መደንገጉን ተቋሙ ለጨረታ ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በግዥ ፈፃሚ አካላት የበላይ ኃላፊ ውሳኔ መግባት የሚችለው ለአንድ ጊዜ እስከ ብር 30,000.00 ብቻ መሆኑን የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ እንደሚያዝና የንብረት አስተዳደር የእቃ ግዥ ጥያቄ አቅርቦም በዚሁ ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ ግዥው የመንግስትን ግዥ መመሪያ በመጠበቅ እንዲፈፀም መታዘዙን ሆኖም አግባብነት የሌለውን ጥቅም ለተጠሪ ለማስገኘት አስበውና አቅደው ከመንግስት ግዥ መመሪያ ውጪ አቶ ቶማስ ወልዱ ተጨማሪ ጽሑፍ ያስገባ በመሆኑ ስለእቃው አገባብ በግላቸው ከሚጠየቁ በስተቀር አመልካችን የሚያስጠይቅ ሕጋዊ ውል የሌለ መሆኑን እቃው ያላገባብ የገባ መሆኑን አቶ ቶማስ ወልዱ ተረድተው ለስራ ወጪ እንደሆነ መግለፁንና ይህ ግለሰብ ከአቶ ብዙነህ ደሞዝ ጋር ሁነው ባጠፉት ጥፋት ለተጠሪ ከሚጠየቁ በስተቀር አመልካችን እንደማያስጠይቀው ግለሰቦቹ ወደ ክሱ እንዲገቡ ተደርጐ ክርክሩ እንዲመራና ከሕግ ውጪ ወደ ዩኒቨርሲቲው የገቡት እቃዎችም ብልሽት ቢደርስባቸዉ አመልካች ተጠያቂ ሊሆን ስለማይችል ተጠሪ የመጋዝን ኪራይ ከፍለው እቃዎችን እንዲረከቡ እንዲደረግና እንዲሁም በቀድሞው ውል መሠረት ፈሳሽ ሳሙና ባለአራት ሊትር በጀርካን ሆኖ ዋጋው ብር 60,000.00 ሆኖ እያለ ያለአግባብ ወደ ሊትር በመለወጥ የአንድ ሊትር ዋጋ ብር 60,000.00 በማስላት ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ መሆኑን ተደርሶበት ያለ ሆኖ በድጋሚ በማጭበርበር ጥቅም ለማግኘት ክስ መመስረቱ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዝበ ከዳኝነት ወጪ ከ7% የጠበቃ አበል ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዝህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለደቡብ ብሄር በሄረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኝ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩ ተመርምሮ በድምጽ ብልጫ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመጽናት ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፣፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ከተጠሪ ጋራ በሀዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም ተደርጐ ከተፈፀመው ውል ውጪ የካቲት 03 ቀን 2001 ዓ.ም በተጨማሪነት ተደረገ የተባለው ውል ከመንግስት ግዥ መመሪያ ውጪ ተጠሪ ከአመልካች ተቋም የበታች ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር ያደረጉትና በሕጉ አግባብ ያልፀደቀ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል አለ በማለት ለክሱ መሠረት የሆነውን ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰናቸው የላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐላቸው ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ

በጽሁፍ እንዲከራከሩ የተደረገ ሲሆን የከርክራቸው መሰረታዊ ይዘትም በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ተመልክተናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ስሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በስር ፍርድ ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የጠየቃቸው ሰራተኞች ወደ ክርክሩ ሳይገቡ ውሳኔ መስጠቱ ስነ ስርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በሕጉ አግበብ ስለመደረጉ ክርክር ያልቀረበበትና ህዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረጉትን የንጽህና እቃዎች ግዥ ውል ፈፃሚ እንዲያገኝ አድርጉው አሁን እያከራከራቸው ያለው የካቲት 03 ቀን 2001 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የንጽህና እቃዎች ውል መሆኑን ይህ ውል በቀድሞው ውል ጠቅላላ ብር 634,685.00 ( ስድስት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) ዋጋ 25% ማለትም የብር 333,155.00 (ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ብር) እቃ እንዲያስገቡ ተጠሪ በአመልካች ታዝዘው በዚሁ ትእዛዝ መሠረት የእቃ መጠየቂያ ቀርቦ በአመልካች መስሪያ ቤት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተፈርሞና ደብዳቤው ተሰጥቶ የብር 333,155.00 ዋጋ ያለው እቃ ተጠሪ ገዝተው ለአመልካች በማቅረብ ንብረቱን ለአመልባች በሞዴል 19 ጣምራ ቁጥር 098954 በሆነው ገቢ አድርገው ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑንና የአመልካች መስሪያ ቤት የእቃ ግዥ ንብረት አስተዳደር ክፍልም እቃውን ቆጥሮ ከተረከበ በኋላ ለአመልካች መስሪያ ቤት ፋንናንስ መመሪያ እቃውን ስለመረከቡ ማረጋገጫ የሰጠ መሆኑን ተጠሪ ጠቅሰው የሚከራከሩ ቢሆነም ይህ ሁሉ የሆነው ግን የአመልካች መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ተገቢውን ትእዛዝ አድራጉቱን ፈፀሙ ለተባሉት የበታች ሰራተኞች አስተላልፈው ስለመሆኑ ያለመረጋገጡን ነው፡፡ የበታች ፍርድ በቶች አመልካችን ለክሱ ተጠያቂ ያደረጉት እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖራቸውን አረጋጋጠው የአመልካች ሠራተኞች ከአመልካች ጋር ባላቸው የሥራ ግንኙነት መሠረት የደረሱበትን ኪሣራ ወይም ጉዳት አመልካች ሊጠይቅ የሚችለው ሠራተኞቹን እንጂ ከተጠሪ ጋር መከራከሪያ ሊያደርገው አይችልም በሚል ምክንያት መሆኑንም ውሳኔው የሚሳይ መሆኑን ተረድተናል፡፡

በመሠረቱ አንድ ውል የሕግ ጥበቃ የሚያገኘው በሕጉ አግባብ የተቋቋመ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ) ድንጋጌ ጋር በጣምራ ስናነብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ውሉ ሕጉን በሚቃረን መልኩ የተቋቋመ መሆኑ እየተረጋገጠና ውሉን ተዋውሏል የተባለ ተዋዋይ ወገንም ውሉ ሕጋዊ አይደለም በማለት ክርክር እያቀረበ በውሉ እንዲገደድ ማድረግ የመዋዋል ነፃነትን መሰረታዊ መርህ የሚጥስና ፍላጐቱንና ፈቃዱን ያልሰጠ ሰው ግዴታውን እንዲወጣ በማድረግ ሌላኛው ተዋዋይ ነኝ የሚል ወገንም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዲያገኝ የማድረግ ውጤት የሚስከትል ከመሆኑም በላይ በተለይ እንዲህ አይነቱን ግዴታ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበው በመንግስ መስሪያ ቤት ከሆነ የመንግስት ግዥን ስርአት ለመስያዝ የወጣውን ሕግ ውጤት አልባ የሚያደርግ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ አንድ የመንግስት ሠራተኛ በሕጉ የተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር እያለ ከዚሁ ኃላፊነትና ተግባር አድማስ ውጪ ባደረገው ግንኙነት በተቋሙ ግዴታ የሚያስከትል ተግባር ፈጽሞ ከተገኘም ኃላፊነቱን ሊወስድ የሚገባው እንዲ አይነቱን ተግባር ያከነወነው ሰራተኛ በግሉ ከሚሆን በስተቀር

ተቋሙ ሲሆን የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ አንድ የመንግስት መስሪያ ቤተ ለሰራተኛው ተግባር ኃላፊነት ሊህረው የሚችለው በሰራተኛው የተፈፀመው ጥፋት የሥራ ጥፋት ሆኖ ሲገኝ ሲሆን አንድ ጥፋት የስራ ጥፋት ነው ተብሎ የሚወሰደውም ጥፋት አድራጊው በዚህ ጥፋት ላይ የወደቀው በቅን ልቡና በስልጣኑና ለስራው ክፍል መልካም ያደረገ መስሎት የፈፀመው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ከዚህ ውጪ በሆነ በማናቸውም ሌላ ጉዳይ ግን ጥፋቱ እንደግል ጥፋት ሁኖ እንማሚቆጠር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2126 እና 2127(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስረዳሉ፡፡ ጥፋቱ በቅን ልቦና ያልተፈፀመ መሆኑም በተቃራኒ ማስረጃ ሊረጋገጥ እንደሚችልና ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ ግን የራተኛው አሰራር በቅን ልቦና እንደተሰራ በሕጉ ግምት እንደሚወሰድበት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2127/3/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከላይ የተመለከቱት የሕግ ጉዳዮች በፍርድ ተገቢውን አልባት የሚሰጥባቸው ደግሞ በክርክሩ የግድ ተካፋይ የሆነው ወገኖች በክርክሩ እንዲሳተፉ ተደርጐ ጉዳዩ በተገቢው ማስረጃ በጥንያቄ ሲጣራ ነው፡፡

በመሠረቱ በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሲቀርብና የክሱም ምክንያት የብዙ ሰዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ ወይም ኃላፊነት ያለበትና ግዴታውን ሊወጣ የሚገባው የትኛው ወገን መለየት የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከእነሱ አንዱ ወይም ከፊሉ ክስ በቀረበ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ መብትና ጥቅም የሚነካ ወይም ግዴታው በሕጉ አግባብ እንዲወጣ ሊደረግ የሚችል ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በሕጉ አግባብ ተጠያቂ የሚሆን ወገንም የክርክሩ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ የሚመነጨው ከዚህ አግባብ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎችን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 36/5/ ጋር ተጣምረው ሲነበቡ የሚያገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ተካፋይ ሳይሆነ የሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ ውጠት የማይኖረው ስለመሆኑም የተጠቃሽ ድንጋጌዎች መንፈስ ያሰረዳል፡፡ በመሆኑም በክሱ መግባት ያለበት ተከሳሽ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆንና በቀረበው ክስና መልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ሊያዘው የግድ የሚል ስለመሆኑ ሥነ ሥርዓቱ የሳያል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቼው ወገኖች ማለት ደግሞ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ፡ በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመኖቸውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 40 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ድንጋጌው ክርክሮች ወደፊት እንዳይነሱ በማድረግ የወጪ ጊዜና ጉልበትን ብክነት በመቆጠብ አፋጣኝ ዳኝነት የመስጠትን የስነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ አላማ ያገናዘበ ነው ተብሎ ይታሳባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ውሉ የተገባው በመንግስት ግዥ መመሪያ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 68(2)(ሀ)) ድንጋጌ መሠረት በአመልካች መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የጽሑፍ ትእዛዝ የተላለፈ ትእዛዝ መኖር ያለመኖሩን በተመለከተ ከአመልካች ሰራተኞች ጋር ተደረገ የሚሉት የቀድሞ ውልን መነሻ በማድረግ ሕጋዊ ስርዓትን የተከተለ ስምምነት አለ የሚሉ ሲሆን በዚህ ረገድ በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ደግሞ ውሉ ላይ መጻፃፎች እንዲኖሩ ያደረጉት ሰራተኞች ከተጠሪ ጋር ተመሳጥረው ያደረጉት ተግባር እንጂ ሕጋዊ አይደለም በማለት በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ አመልካች የተቋሙ ሰራተኞች ተግባሩን የፈፀሙት ከተጠሪ ጋር ተመሳጥረው ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር ሰራተኞቹ ወደ ክርክሩ እንዳገቡ ተደርጐ የግራ ቀኙ

ማስረጃ ተሰምቶ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2126 እና 2127 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ተፈፃሚነት የነበረውን የመንግስት የግዥ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር ተዛመዶ ዳኝነት የማስጥበት እንጂ አመልካች ከወዱሁ በሰራተኞቹ የግል ጥፋትም ቢሆንም እንኳን ሃላፊነቱ የአመልካች ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ ሕጋዊ አካሄዱን በተከተለ የተደረሰ መደምደሚያ አይደለም፡፡ የአመልካች ሰራተኞች ተግባሩን የፈፀሙት ከቅን ልቦና በመነጨ ሁኔታ ነው? ወይስ ከዚህ ውጪ ነው? ተጠሪስ የእቃዎቹን አቅርቦት ለአመልካች የፈፀሙት ከሰራተኞቹን የመመሳጠር ተግባር ፈጽመው ነው ወይስ ሕጋዊ አንድ ጠንቃቃ ነጋዴ ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ አድርገው የንገድ ስራው የግድ የሚለውን አካሄድ ተከትለው ነው? የእቃቹ አቅርቦት ከተጠሪ ጋር የነበረውን የቀደመ ግንኙነት መሠረት አድርጐ እንዲከናወን የተጠሪ ተቋም የበላይ ኃላፊ ለሰራተኞቹ በሕጉ አግባባ ያስተላለፉት እትዛዝ አለ ወይስ የለም? የተላለፈ ትእዛዝ አለ ከተባለም ሰራተኞቹስ ስራውን ያከናወኑት በበላይ ኃላፊ ትእዛዝ መሠረት መሆን ያለመሆኑ ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ተገቢውን ማጣራት ማድረግን የሚጠይቁ ሲሆን ይህ ሁሉ መከናወን ያለበት ግን ሰራተኞቹን የክርክሩ ተሳታፊ በማድረግ የመደመጥ መብታቸውን በማስከበር እና የፍታ ብሄር ስነ ሥርዓት ሕጉን አይነተኛ አላማ በማገናዘብ ሌላ ክርክር ወደፊት እንዳይነሳ የሚያደርግ የክርክር አመራርት ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ ሲጠቃለልም የስር ፍርድ ቤቶች ተገቢ ባልሆነ የክርክር ደረጃ አመልካች ለሠራተኞቹ ተግባር ጭምር ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል በሚል ምክንያት የአመልካች ሰራተኞች የሆነት አቶ ቶማስ ወልዴ አቶ ብዙነህ ደመወዝ የተባሉት ግለሰቦች ወደ ክርክሩ ይግበልኝ የሚለውን የአመልች ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ለማለት አልተቻለም ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ግለሰች ወደ ክርክር ሳይገቡ የተሠጠው ውሳኔ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አለነም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በጋሞ አከባቢ ከተፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10689 ነሐሴ 14 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በደበ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 56013 ግንቦት 03 ቀን 2004 ዓ.ም በድምጽ ብልጫ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ተቋም ሰራተኞች የሆነትና ከእቃው አቅርቦት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበራቸው የተባሉ አቶ ቶማስ ወልዴና አቶ ብዚነህ ደመወዝ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን ያለባቸው መገኖች በመሆኑ ለቀረበው ክስና መልስ መከላከያቸውን እንዲያቀርቡ የጋሞ አከባቢ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሠጥቶ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

እ/ብ

# የዳኝነት ሥልጣን



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 81934

የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአቀቂ ቃሊት ክ/ከተማ ወረዳ 5 ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡- ሃምሳ አለቃ ታምራት ከበደ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከንግድ ስራ ፈቃድ ማገድ ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በአ/አበባ ከተማ መስተዳድር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ በአቃቂ ቃሊት ክ/ከተማ ወረዳ 5 ክልል ውስጥ ባለኝ የመኖሪያ ቤት ይዞታዬ ላይ የመኪና ማቆሚያ ንግድ ስራ ህጋዊ ፍቃድ ተሰጥቶን እየሰራሁ እያለሁ ተጠሪ በቁጥር 415/2004 ታህሳስ 23 ቀን 2004 ዓ/ም በተፃፈ ማስጠንቀቂያ እየሰራህ ያለው የንግድ ስራ ከፀጥታ ከጤና እና ከአካባቢ ብክለት አንፃር በአካባቢ ጥበቀ ላይ ከፍተኛ ችግር እያደረሰ ነው በሚል ምክንያት የንግድ ፍቃድን ለማገድ ሁከት ስለፈጠረብን የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁ 686/2002 ዓ.ም አንቀጽ 37/ሀ/ መሰረት እግድ መስጠቱ ህጋዊ እርምጃ በመሆኑ የቀረበው የሁከት ይወገደልኝ አቤቱታ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ወድቅ ተደርጎ እንዲሰናበት በመጠየቅ መልስ ስጥቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የከተማ መ/ደ/ፍ/ቤትም የተጠሪ መኪና ማቆሚያ ንግድ ስራ በአካባቢው የጤናም ሆነ ብክለት ላይ ችግር ማስከተሉ በማስረጃ ሳይደገፍ የንግድ ስራ ፈቃዱ በአመልካች መታገዱ የሁከት ተግባር በመሆኑ የተፈጠረው ሁከት ይወገድ ሲል ወስኖል አመልካችም ይህን ውሣኔ በመቃወም ቅሬታውን ለከተማ መስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡ እንዲሁም አቤተታውን ለከተማው መስተዳድር ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም አሁንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ሐምሌ 24 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ አመልካች በአዋጅ ቁ 686/2002 አንቀጽ 37/1/ሀ/ መሰረት ተጠሪ የፈጠረው ችግር አስኪ.ታረም ድረስ የንግድ ስራ ፈቃዱን ማገዱ በህግ የተሰጠን ስልጣን ሲሆን ይህም በተሰጠን ስልጣን መሰረት ሀላፊነትና ግዴታችን መወጣት እንጂ የሁከት ተግባር ሊባል የማይችል በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ

የተፈጠረ ሁኩት የለም ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዘንድ ጠይቋል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የገባል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠ ሲሆን አመልካችም የመ/መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል አስተዳደራዊ እርምጃን በሚወስደበት ጊዜ በተወሰደው አርምጃ መብቴ ተነክቷል፡፡ የሚል ሰው ካለ መብቱን በምን አይነት ሰርዓት እና መንገድ ሊያስከብር ይችላል? የሚለው ነጥብ በቅድሚያ ታይቶ የምላሽ የሚሻ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህን ጉዳይ በተመለከተ አግባብነት ያለው ህግ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 ሲሆን አዋጅ አንቀጽ 61ም በአስተዳደራዊ አርምጃዎች ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ በሚለው የድንጋጌው ርዕስ ስር በዚህ አዋጅ መሰረት በመዝገቢው መስሪያ ቤት ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ሰው ሊኖረው ከሚችለው ቅሬታ ጋር በተያያዘ በህግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ለመደበኛ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል በሚል በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መንፈስ ደግሞ መረዳት የሚቻለው በህግ ጥያቄዎች ላይ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የፍሬ ነገር ክርከርን በሚመለከት መደበኛ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማየት ስልጣን ያለተሰጣቸው መሆኑን ነው፡፡ ከህግ አተገባበር ጋር በተያዘ የተፈጠረ ስህተት ካለ እሱን በተመለከተ ብቻ ተቀብለው ከማረም ውጭ የፍሬ ነገር ክርክርችን በማስረጃ አጣርተው ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለችውም በተያዘው ጉዳይም ሁከት ይወገደልኝ በሚል የቀረበውን የክሱን ፍሬ ነገር በተመለከተ የስር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙን በማከራከርና በማስረጃ በመጣራት የሰጡት ውሳኔ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ምክንያት የህግ መሰረት ያለው አይደለም በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የፍሬ ነገር ጉዳይን በሚመለከት አከራክረው የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ የአ/አበባ አስተዳደር መ/ደ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. መደበኛ ፍ/ቤቶች ከንግድ ምዝባና ፈቃድ ጋር በተያዘ የሚነሱ የፍሬ ነገር ክርክሮችን አይተው ለመወሰን ስልጣን የላቸውም፡፡
3. ተጠሪ የህግ ጉዳይን ወይም ጥያቄን በተመለከተ ብቻ በአዋጅ ቁ 686/2002 61 መሰረት ስልጣን ላለው መደበኛ ፍ/ቤት አቅርቦ መብቱን ለማስከበር ይህ ውሳኔ አይከለክለውም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርከር ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 86817

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** የኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - ዐ/ህግ ቢኒያም አብርሃም ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ግሎሪ ኢትዩጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ጫንያለው ከበደ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከአስጎብኚና የጉዞ ወኪል የንግድ ፈቃድ ስራ ጋር በተያያዘ ለአንድ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ይዘት በአጭሩ ድርጅታቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የኢንቨስትመንት ባለስልጣን የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ የተሠጠው መሆኑን፣በዚሁ መሰረት መንግስት በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሰጠውን ከቀረጥ ነጻ መብት ተጠቅሞ በደንብ ቁጥር 146/2000 አግባብ በተሠጠው መብት መሰረት ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች አስፈላጊውን ሁኔታ ሁሉ አሟልቶ፣ተሽከርካሪዎችን ገዝቶ ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ የአሁኑን አመልካች በመጠየቅ ሐምሌ 15 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ መኪኖቹ ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነጻ ሁነው እንዲገቡ በፈቀደው መሰረት ተሽከርካሪዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ፎርማሊቲዎችን አሟልተው ቀረጥ ሳይከፈልባቸው መግባታቸውን፣ ተጠሪ መኪኖቹን ወደ ስራ ከአሰማራ በኂላ ከሶስቱ መኪኖቹ አንዱ ከ10 ሰው በታች የሚጭን ስለሆነ ቀረጥና ታክስ መክፈል አለብህ በ ማለት አመልካች መጠየቁን፣ ተሽከርካሪዎቹን አስመልክቶ መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች የመግለፅና የማሳወቅ ስልጣን የተሠጠው ለትራንስፖርት ባለስልጣን መሆኑ እየታወቀና ይኼው ባለስልጣን ማብራሪያ ተጠይቆ ሚኒባስ ማለት አሽከርካሪውን ሳይጨምር ከ7-14 ሰው የሚጭን መሆኑን ገልጾ ማብራሪያ መስጠቱንና በዚህ አግባብ አመልካችም ሲያስተናግድ ቆይቶ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ባልታወቀ ሁኔታ ቀረጥና ታክስ ካልከፈልክ ማለቱ ያላግባብ መሆኑን ዘርዝሮ ሁከቱ ተወግዶ የአመልካች የቀረጥ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ ሁኖ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ቀርቦም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ለማየት የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ እርምጃው በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት አድርጎ የተከናወነ መሆኑን በመጥቀስና ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የህግ ማዕቀፎችን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም አመልካች ስልጣንን መሰረት አድርጎ ያነሳውን ክርክር በተመለከተ የተጠሪ ጥያቄ ከቀረጥ ነጻ መብት የተያያዘ እንጂ ከቀረጥና ከታክስ አከፋፈል ጋር የተያያዘ አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎታል፡፡ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የአመልካች ጥያቄ ሕጋዊ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ማየቱ በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ መሆኑንና በአከራካሪው መኪና ላይ የአመልካች የቀረጥና የታክስ ይከፈል ጥያቄ በሕጉ በተፈቀደው አግባብና ስልጣኑን መሰረት አድርጎ የተከናወነ ሁኖ እያለ ተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ጭብጥ ሳይመሰርትና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በአግባቡ ሳይመለከት የአመልካች ጥያቄ አግባብ አይደለም ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ የግራ ቀኙ ክርክር በፅሑፍ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ ማስናገዱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ባለው የኢንቨስትመንት ፈቃድ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ በመሰማራት ለስራው የሚገለገልባቸውን ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ከታክስ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ፈልጎ ይህንኑ በማመልከት ስለተፈቀደለት አስፈላጊ ዶክመንቶችን በማሟላት መኪኖችን ገዝቶ ከአስገባና ስራ ላይ ከአሰማራ በኂላ ከገቡት ተሽከርካሪዎች ውስጥ አንዱ ከአስር ሰው በታች የሚጭን በመሆኑ ቀረጥ ሊከፍልበት ይገባል በማለት አመልካች መስሪያ ቤት መጠየቁን ገልጾ ጥያቄው ሁከት በመሆኑ ሊቆም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን፣የአመልካች ዋና የመከራከሪያ ነጥብ ደግሞ ለተጠሪ የቀረበው አይነት ጥያቄ በአመልካች መቅረቡ በሕጉ የተፈቀደና በጥያቄው ቅሬታ ያለው ወገንም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አግባብ በአመልካች መስሪያ ቤት በተዘረጋው ስርዓት ቅሬታውን ማቅረብ፣በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካደረበትም ጉዳዩ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ከሚቀርብና በስርዓቱ መሰረት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለበላይ ፍርድ ቤቶቸ ቅሬታው ታይቶ ከሚስተናገድ በስተቀር በቀጥታ ክስ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት ጉዳይ አይደለም፣ከአስር በታች የሆነ ሰው የሚጭን መቀመጫ ያለው ተሽከርካሪ ደግሞ "ሚኒባስ" በሚለው ትርጉም አይካተትም በሚል መሆኑን ነው፡፡

ከላይ ከተገለፀው የግራ ቀኙ ክርክር መረዳት የሚቻለው ተጠሪ የቀረጥና የታክስ ነጻ መብት አለኝ በማለት ከመጥቀሱ ውጪ አከራካሪው ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ተብሎ በሕጉ አግባብ ሊመደብ የሚችል መሆን ያለመሆኑ የክርክሩ መሰረታዊ ጭብጥና ግራ ቀኙን የሚያከርከር ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ከእቃው አመዳዳብ፣የጉምሩክ ስነስርዓት፣ ከቀረጥና ታክስ አከፋፈል ጋር ተያይዞ ቅሬታ መነሳቱን የሚያመላክት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀጽ 87 (1) ስር በግልጽ እንደተመለከተው በእቃዎች አሰያየም፣አመዳደብ ወይም በታሪፍ

ልክ ላይ ተቃውሞ ካለ እንዲሁም በተጠቃሹ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሐ) ስር እንደተመለከተው ማንኛውም ከጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ጋር በተያያዘ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው አካል አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ቀጥታ ለፍርድ ቤት ሳይሆን በተጠቃሹ አዋጅ በተዘረጋው የይግባኝ ስርዓት መሆኑ ተመልክቷል፡፡የይግባኝ አቀራረብ ስርዓቱም ጉዳዩ ከአመልካች መስሪያ ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቀርቦ ከታዬ በኋላ ቅሬታ ያለው ወገን በአንቀጽ ንዑስ ቁጥር 5 መሰረት ለግብር ይግባኝ ሰሚ መቅረብ እንደአለበት፣ ከዚያም በአንቀጹ ንኡስ ቁጥር 9 መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረብ እንደአለበት፣በዚህ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገንም በአንቀጹ ንኡስ ቁጥር 10 ድንጋጌ አግባብ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 112 እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቀጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች አግባብ ለበላይ ፍርድ ቤት እንደየቅደምተከተሉ ይግባኙንና የሰበር አቤቱታውን ማቅረብ እንደሚችል የድንጋጌዎች አቀራራጽና ይዘት ያሳያል፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ የአመልካች የቀረጥና የታክስ ክፍያ ጥያቄ አግባብነት የለውም የሚለው የተጠሪ ክርክር በእነዚሁ አዋጆች በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ታይቶ እልባት ከሚያገኝ በስተቀር በቀጥታ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት እና ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ አይተው ውሳኔ የሚሰጡበት አግባብ አይኖርም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩ ሲቀርብላቸው ጉዳዩን በቀጥታ የማየት ስልጣን እንደሌላቸው በመገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9፣231(1(ለ)) እና 244(2(ሀ)) መሰረት መመለስ ሲገባቸው ክሱን በመቀበልና በማከራከር ውሳኔ መስጠታቸው የሕጉን አካሄድ የተከተለ ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ባቀረቡት የቀረጥና የታክስ ክፍያ ጥያቄ ላይ ስልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው፣የክርክሩን አጠቃላይ ይዘት አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 176250 ነሐሴ 13 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በ07/02/2004 ዓ/ም የተገለጸውና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117291 ጥር 06 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የመደበኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን ጥያቄ በቀጥታ ክስ በመቀበልና በመመልከት ውሳኔ ለመስጠት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 89530

ጥቅምት 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ቲኤንቲ ኮንስትራክሽንና የንግድ ስራዎች ድርጅት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ እያዩ ደጀኔ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተመሰረተ የስራ ግንኙነትን መሰረት አድርጎ የተነሳውን ለተሰራ ስራ የሚከፈል ክፍያ ይከፈለኝ ጥያቄን ለማየት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለውን አካል የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በድሬዳዋ አስተዳደር አስተዳደር ቀበሌ 02 ማህበራዊ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ የክስ ይዘትም፡- ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ድርጅት ውስጥ በወር ብር 2000.00 ተቀጥረው ስራ መስራታቸውንና ለሰሩት ስራ ብር 2000.00 ያልተከፈላቸው መሆኑን ዘርዝረው ይህንኑ ገንዘብ አመልካች እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ሊታይ የማይችል መሆኑንና ክፍያው ለተጠሪ ያልተፈጸመው ተጠሪው በፈጸሙት ጥፋት መሆኑንና ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ብር 3000.00 ብድር ወስደው አንድ ሺህ ብር ብቻ ከፍለው ቀሪውን ባለመክፈላቸው መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ጉዳዩ የቀረበለት የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በማየት አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ከተለያዩ ወጪዎች ጋር በድምሩ ብር 2134.00 ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኙን ቢያቀርብም ግራ ቀኙ ከተራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታይ ሁኖ እያለ በአዋጅ ቁጥር 416/1996 ከተሰጠው ስልጣን ውጪ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ ተደርጎ ለተጠሪ ጥሪ ቢደረግላቸው ጥሪው በሕጉ አግባብ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የታቸው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ቅጥር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መስርተው ስራ መስራታቸውንና ለሰሩት ስራ ደመወዝ ያልተከፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ የገንዘቡን መጠን ለይተው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የመጠቃቸውን፣አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የተጠሪ ክስ መሰረት ያደረገው ቅጥርን በመሆኑ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የማይወድቅ መሆኑን ገልፆ የተከራከረ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙት ፍርድ ቤቶችና ሌሎች የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ስልጣናቸው በአዋጅ ቁጥር 416/1996 ከአንቀጽ 31 እስከ 42 ድረስ በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መሰረት የተዘረጋ ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 41(1) ድንጋጌ በተለይ ሲታይም የአስተዳደሩ ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ግምታቸው ከብር 2000.00 ያልበለጡ የገንዘብና የንብረት ክርክሮችን የማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑን በግልጽ ደንግጓል፡፡በሌላ በኩል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን በተመለከተ ሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የተለየ ሕግ አውጥቶ አዋጁን መሰረት አድርገው የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን ያላቸውን አካላት ለይቶ ማስቀመጡን የአዋጁ አንቀጽ 138 እና 142 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል፡፡ይህ ህግ የገንዘብ መጠንን ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገባ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የተቋቋመውን ግንኙነት መሰረት አድርጎ የሚነሳው የግል የስራ ክርክር በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደሚታይ፣የወል የስራ ክርክር ከሆነ ደግሞ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚዳኝበትን አግባብ የዘረጋ ነው፡፡በመሆኑም ሕጉ ለአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቶች ልዩ ሕግ እንደመሆኑ መጠን ለጉዳዩ ከሌሎች ሕጎች ሁሉ የበላይ ተፈፃሚነት አለው፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ መሆኑን በግልጽ ጠቅሰው ክስ በመሰረቱበት ሁኔታ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የገንዘቡ መጠን ብር 2000.00 መሆኑን ብቻ በመመልከት፣ጉዳዩን ከአዋጅ ቁጥር 377/196 አንጻር በመመልከት ስልጣኑ መሆኑን ሳያረጋግጥ ጉዳዩን ተቀብሎ ማየቱ ከአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 41(1)፣ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9(1) እና 231(1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ፣በጉዳዩ የተሰጠው ውሳኔ በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ስልጣን በሌለው አካል የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 02 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0113/05 ጥር 14 ቀን 2005 ዓ/ም ተሠጥቶ በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00336 መጋቢት 27 ቀን 2007 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተመሰረተውን ግንኙነት መሰረት አድርጎ የሚቀርበውን ክርክር የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ጥያቄአቸውን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የማቅረብ መብታቸውን ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝግብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ል/ተ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 90737

ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሴ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የንጋት ኮከብ ሽማቾች ኃ/የተ የግል ማህበር ጠበቃ አቶ እሸቱ ጓንጉል ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ የሴፍ እንድሪስ
2. አቶ መክብብ አሰፋ
3. አቶ ፀጋ መሰለ
4. አቶ ወጋየሁ ላቀው
5. አቶ ጎንጀባ ጎንባ
6. አቶ ጎሳዬ ጎቴ

(1–6) ቀረቡ

7. አቶ መንግስቱ ታደሰ አልቀረቡም
8. አቶ ይልማ ኪዳነ ወልድ
9. አቶ ዘካሪያስ ሀ/ማርያም
10. አቶ አብጤ ካኦ

(8–10) ቀረቡ

በዚህ መዝገብ እና በሰ/መ/ቁ 90738 ያሉት ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ከመሆናቸውም ሌላ የቀረበው የህግ ክርክርና የነገር ጭብጥም አንድ ዓይነት በመሆኑ ሁለቱን መዝገቦች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 11(1) መሰረት በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከተራ ቁጥረ 1-5 ያሉት ያሁን ተጠሪዎችም በመ/ቁ/40407 ተከሳሾች ነበሩ፡፡ መ/ቁ/40406 በሆነው ደግሞ የአሁን አመልካች ከሳሽ ፣ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 ያሉ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ቁጥሩ 40407 በሆነው መዝገብ ከሳሽ በቀን 27/09/2004 ዓ/ም ያቀረበው ክስ፡- ከሳሽ ማህበር በህብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 የተቋቋመ ሲሆን ተከሳሾችም የማህበሩን የእለት ተዕለት ሥራ እንዲሰሩ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጠው ከ20/07/2003- 27/11/2003 በማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባልነትና በዕቃ ግዥ ሲሰሩ ከከሳሽ የመተዳደሪያ ደንብ ውጪ ህገ ወጥ አሰራር በመከተል በሥልጣናቸው ያለአግባብ በመገልገል የማህበሩን ገንዘብ ብር 369,202.75 መውሰዳቸው በኦዲት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከ9% ወለድ ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ከሳሽ መ/ቁ/40406 በሆነው ደግሞ በመ/ቁ/ 40407 የተጠቀሱትን ተከሳሾች ጨምሮ በድምሩ በ10 ተከሳሾች ላይ ግንቦት 27/1004 ያቀረበው ክስ ተመሳሳይ ሆኖ ተከሳሾቹ ከ01/07/2001-19/07/2003 ዓ/ም የከሳሽ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ ፣ የዕቃ ግዥ እና ቁጥጥር ኮሚቴ ሆነው ሲሰሩ ሥልጣናቸውን ያለአግባብ በመገልገል የማህበሩን ብር 176,587.31 ማጉደላቸው በኦዲት ሪፖርት ስለተረጋገጠ ይህንኑ ገንዘብ ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሾችም ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በህብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 በክፍል ዘጠኝ በአንቀጽ 46 መሰረት በቅድሚያ ጉዳዩ መታየት ያለበት በእርቅ መሆኑን፣ በእርቅ ማለቅ ካልቻለም ለሽምግልና ዳኝነት ጉባዔ ቀርቦ የሚወሰን ሆኖ ሳለ ከሳሽ በቀጥታ ለፍርድ ቤት ያቀረበውን ክስ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ አከራክሮ ለመወሰን ሥልጣን የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ክስና ተከሳሾች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንጽ 46 እና 49 ጋር አገናዝቦ በመመርመር፡- የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የማህበሩ አባል መሆናቸውን ያልተካካዱ ስለሆነና ጉዳዩም በቀጥታ በእርቅ ካልሆነም በሽምግልና ሊታይ የሚገባ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ አከራክሮ ለመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የለውም ሲል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 244(2)(ሀ) መሰረት ሁለቱንም የክስ መዝገቦች ዘግቷል፡፡

ከሳሽም በሁለቱም መዝገቦች ይግባኝ የጠየቀ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ አመልካች በሁለቱም መዝገቦች በዋናነት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብ ሲጠቃለል፡- ተጠሪዎች የአመልካች ማህበር የመተዳሪያ እና የፋይናንስ ደንብ ተከትለው ባለመሥራታቸው ምክንያት በኦዲት ሪፖርት የተረጋገጠውን የጉድለት ገንዘብ እንዲከፍሉ በአዋጅ ቁጥር 147/1991

አንቀጽ 39(1)(ሀ) መሰረት ጥረት ቢደረግም ፈቃደኞች ሆነው ባለመገኘታቸው በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ያጎደሉትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ በሚል የቀረቡትን ክሶች የሥር ፍርድ ቤቶች በአባላት መካከል እንደተነሳ አለመግባባት ቆጥረው በዕርቅ ወይም በሽምግልና ሊፈታ የማይችለውን ጉዳይ ከአዋጁ አንቀጽ 46 እና 49 ዓላማና መንፈስ ውጪ በዕርቅ እና በሽምግልና ሊታይ የሚገባ እንጂ ለፍርድ ቤት ቀጥታ የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም በሚል ክሶቹን በብይን ውድቅ ያደረጉት ከዚህ በላይ የተቀመጡትን የአዋጁን ድንጋጌዎች ያላገናዘበና በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 37(2)(ሀ) -የህብረት ስራ ማህበራት ክስ መስርተው ፍትህ የማግኘት መብት አላቸው በሚል የተደነገገውን የሚቃረን ስለሆነ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በተከሰሱበት የክስ መዝገብ በየበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- አመልካች የህብረት ሥራ ማህበር ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ የቀድሞ የማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ወይም በአዋጁ አገላለጽ ሹሞች በመሆናችን በመካከላችን የተፈጠረው አለመግባባት ሊታይ የሚገባው ከፍርድ ቤት ይልቅ በአዋጁ አንቀጽ 46፣47 እና 49(3) መሰረት በእርቅ ወይም በሽምግልና ዳኝነት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብለዋል፡፡

አመልካችም ተጠሪዎች ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች በቀጥታ ያቀረቧቸውን ክሶች ለማየት የዳኝነት ሥልጣን የለንም ሲሉ የክስ መዝገቦቹን የዘጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው አከራክረው ለመወሰን የስረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን እንደሌላቸው በመግለጽ የክስ መዝገቦቹን የዘጉት የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የማህበሩ አባል መሆናቸውን ያልተካካዱ ስለሆነ ጉዳዩ በቀጥታ በእርቅ ካልሆነም በሽምግልና ሊታይ ይገባል በሚል ነው፡፡ የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 402/1996 አንቀጽ 46 በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 49(1-4) የተመለከቱት ክርክሮች ለሽምግልና ዳኝነት ከመቅረባቸው በፊት ተከራካሪ ወገኖች በሚመርጡት 3ኛ ወገን በእርቅ መታየት ይችላል በሚል የተደነገገ ሲሆን በዕርቅ ያላለቁ እንደሆነ ደግሞ ለሽምግልና ዳኝነት እንደሚቀርቡ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 47(1) ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ/70351 በቀን 17/11/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት፡- ማህበሩ የሚጠይቀው ጉድለትን መሰረት ያደረገ ገንዘብ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 47 እና 49 መሰረት በዕርቅ ወይም በሽምግልና መታየት አለበት ሊባል የሚችል አለመሆኑን ፤ይልቁንም በአዋጁ አንቀጽ 26(2)፣39 (1)(ለ)(ሐ) እና በደንብ ቁጥር 106/1996አንቀጽ 14(ሀ)(ሐ)(መ) መሰረት የማህበሩ የሥራ ሀላፊዎች ያጎደሉትን ገንዘብ እንዲተኩ በቀጥታ ክስ ለፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚቻል በተመሳሳይ ጉዳይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በመሆኑም በተጠሪዎች ላይ አመልካች በሁለቱም መዝገቦች ክስ ያቀረበው የከሳሽ ማህበር የሥራ አመራር አካላት፣የቁጥጥር ከሚቴ እና ዕቃ ግዥ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ በእጃቸው የገባውን የማህበሩን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋል በማጉደላቸው ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍሉ እንዲወሰን በሚል እስከሆነ ድረስም ክስ የቀረበባቸውን ገንዘብ በተመለከተ ክርክር ተደርጎ በማስረጃዎች በሚረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሰረት ውሳኔ

የሚሰጥበት ጉዳይ እንጂ አስቀድሞ በእርቅ ካልሆነም በሽምግልና ዳኝነት ከታዬ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 52 መሰረት በይግባኝ ሥርዓት ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ሊመጣ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑ ይህን ችሎት ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ የአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 47፣ 49፣26(2)፣39 (1)(ለ)(ሐ) እና ደንብ ቁጥር 106/1996 አንቀጽ 14(ሀ)(ሐ)(መ) መሰረት ተፈጻሚነትን በተመለከተ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ባላገናዘበ መልኩ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለቱም መዝገቦች በቀጥታ የቀረቡ ክሶችን አከራክሮ ለመወሰን ሥር ነገር የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ሲል የክስ መዝገቦቹን በብይን የዘጋውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ብይን ተገቢ ነው ሲል ያጸናው መሰረታዊ ሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/40406 በቀን 25/07/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን ፣እንዲሁም በመ/ቁ/40407 በቀን 26/07/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ከ/ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ከተመለከተ በኋላ በመ/ቁ/135108 በቀን 15/9/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና በመ/ቁ/135110 በቀን 22/09/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቧቸው ክሶች በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 49 ሥር የተደነገጉትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ አይደለም፡፡ ስለሆነም ክሶቹ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ በመሆናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራክሮ ለመወሰን ስረ ነገር ሥልጣን አለው በማለት የተዘጉትን የክስ መዝገቦች በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ወገኖች በማከራከር፣ ማስረጃዎችን በማስማትና በመመዝን በጉዳዩ ላይ የበኩሉን ውሳኔ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራቀኙ ወገኖች የየራቸውን ይቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. የዚህ ፍርድ ግልባጭ ከሰ/መ/ቁ/ 90738 ጋር ተያይዞ ይቀመጥ፡፡
2. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሮ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 90920

ህዳር 06 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዓባይ ኢንሹራንስ አ.ማ

ተጠሪዎች፡- አቶ አለማየሁ አሰፋ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የልማት ድርጅት በክልል ወረዳ ፍርድ ቤት በተጀመረ ክስ የጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሲሆን ጉዳዩን የወረዳው ፍርድ ቤት ለማየት የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአቶ ኃይለጊዩርጊስ አበጀ ላይ በውጫሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ሁኖ ተከራክሯል፡፡የተጠሪ ክስ ይዘትም፡- ንብረትነቱ የስር ተከሳሽ የአቶ ኃይለጊዩርጊስ አበጀ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-22157 ተሽከርካሪ መኪናቸውን ነሐሴ 11 ቀን 2003 ዓ/ም በመግጨት ጉዳት አድርሶባቸው ለጥገናው ብር 13,970.00 (አስራ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባት ብር) ማውጣታቸውንና በጉዳቱ ምክንያት ደግሞ ብር 15,000.00 ገቢ የተቋረጠባቸው መሆኑን በመጥቀስ በድምሩ ብር 28,970.00 (ሃያ ስምንት ሺኅ ዘጠኝ መቶ ሰባ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መነሻ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የተደረገ ሲሆን ለክሱ በሰጠው መልስም ግጭቱን አደረሰ የተባለው የደንበኛው መኪና ለጉዳቱ ኃላፊ ስለመሆኑ በትራፊክ ማስረጃ ያለመረጋገጡን፣ለተቋረጠ ጥቅም ደግሞ ለደንበኛው የሰጠው ሽፋን የሌለና በመድን ውሉ የተገለለ ጉዳይ በመሆኑ ኃላፊነት እንደሌለው ገልጾ ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም በጉዳዩ ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመለክቶ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻሩና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ኃላፊነቱ ተጣርቶ እንዲወሰን ለወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መልሶለት ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ ኃላፊነቱን የአመልካች ደንበኛ ነው በማለት የደመደመ ሲሆን የካሳ መጠኑን በተመለከተም ብር 26,230.43 (ሃያ ስድስት ሺኅ ሁለት መቶ ሰላሳ ብር ከአርባ ሶስት ሳንቲም) መሆኑን ገልጾ ይኼው ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፈል፣አመልካች የውል ግዴታው ከዚህ በታች ከሆነ ተከሳሽ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር

አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በወረዳው ፍርድ ቤት የታዬው ያልስልጣኑ መሆኑንና የተቋረጠ ገቢ አመልካቸ የሚከፍልበት የሕግ አግባብም የሌለ መሆኑን ጠቅሶ መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመራም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ውሳኔ የሰጠው የውጫሌ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ነበረው? ወይስ አልነበረውም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሰረት ከሳሽ ክሱን ያቀረበው በመኪናቸው ላይ ለደረሰበት ጉዳት ያወጡት ወጪ እንዲተካላቸውና የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፈላቸው ሲሆን የክርክሩ የገንዘብ መጠንም በድምሩ ብር 28,970 (ሃያ ስንምት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ብር) ነው፡፡በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/200 በአንቀጽ 28(1)(ለ)) እና በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 226(1) መሰረት የከሳሽ የዳኝነት ጥያቄ የሚወድቀው በወረዳው ፍ/ቤት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡አመልካች ጣልቃ ገብ ሁኖ የተከራከረ ሲሆን ጣልቃ ገብነት በፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ አግባብ የተፈቀደ አንዱ የክርከሩ ተሳታፊነት የሚገለፅበትና የራሱን የቻለ መሰረታዊ አላማ ያለው፣በስነ ስርዓት ሕጉ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡በ1958ቱ የፍትሃ ብሄር ስነ ስርዓት ሕግ ወደ ክርክሩ ሊገባ የሚችልበት ስርዓት የተለያየ ቢሆንም ይህ ስርዓት አገሪቱ ከምትከተለው የፌዴራል ስርዓትና በዚሁ ስርዓት ከተዘረጋው የፍርድ ቤቶች አደራጃጀት ጋር ተጣጥሞ በመታየት ስራ ላይ ሊወል የሚገባው መሆኑ ይታመናል፡፡በመሆኑም አንድን ጉዳይ የፌዴራል ወይም የክልል ብሎ ለመየት ይቻል ዘንድ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተቀመጠው መስፈርት ታይቶ የጉዳዩን የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣንም ከዚሁ አንጻር መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 ስር አንድን ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ለማለት የሚያችሉ ምክንያቶች ተገልጸዋል፡፡የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተቋቋመና የተመዘገበ የልማት ድርጅት ሲሆን በፌዴራል መንግስቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑ እና እስከ ብር 500,000 ግምት ያለው የገንዘብ ክርክር የማየት ስልጣን ደግሞ በፌዴል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 5(6) እና በአንቀጽ 14 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80 (4) እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መንግስት በአንቀጽ 64(4) በተመለከተው የስልጣን ውክልና መሰረት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ በክልሉ የሚነሱ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የተሰጠው ለክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን በሕገ መንግስቱ አልተሰጠውም፡፡የሥረ ነገረ የስልጣን ጥያቄ በማናቸውም የክርክር ደረጃ የሚነሳና ፍርድ ቤቱም በራሱ አነሳሽነት ጭምር ማየት የሚችለው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም የውጫሌ የወረዳው ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ወደ ክርክሩ መግባቱ ጉዳዩን ከስረ ነገር ስልጣኑ

ውጪ የሚያደርገው መሆኑን ተገንዝቦ ክሱ ጣልቃ ገቡን ባካተተ ሁኔታ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቀርብ ዘንድ ጉዳዩን ዘግቶ ማሰናበት ሲገባው ክርክሩን ቀጥሎ በማየት ውሳኔ መስጠቱና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ የተፈጸመውን ስህተት ሳያርም መቅረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1(ለ)) ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 90005 በቀረበው ተመሳሳይ የሕግ ጥያቄ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር የማይጣጣም ሁኖ ስለአገኘነው የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በውጫሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05563 በ23/04/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 36566 በ17/08/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁኑ አመልካች በጣልቃ ገብነት ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተቀብሎ ማየት በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 5(6) መሰረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የስር ከሳሽ ለውጫሌ ወረዳው ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረውን ክስ የአሁኑን አመልካች ጭምር በተከሳሽነት በማካተት ስልጣኑ ለሆነው ለሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት የማቅረብ መብቱ በዚህ ውሳኔ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡

4.በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# ወንጀል



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 78470

ሚያዝያ 7 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካቾች፡-** አቶ ታሪኩ ጫኔ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ ፡-** የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

***መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡***

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ ሰው በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በጉዳዩ ላይ በወንጀል የሚጠይቅበት ሕጋዊ አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ላይ ተጠሪ ክስ ያቀረበው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1ሀ(ለ)) እና 413(ሀ) እና (ለ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ነሐሴ 20 ቀን 2001 ዓ/ም በኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለስልጣን የአካባቢና ምግብ ጨረር መጠን ክትትል ባለሙያ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት እና በመንግስት ሀብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ከመስሪያ ቤቱ ፈርመው የተረከቡትን የቀረጥና የማጋጋዣ ዋጋ ሳይጨምር ግምቱ ብር 76.867.34 የሆነን ዩኒቨርሳል ሰርቬየር ሜትር ሞዴል አር፣ጂ፣ኤስ የሆነ የጨረር መጠን መከላከያ መሳሪያ (Universal servey meter) RGS-200 እና የርቀት መቆጣጠሪያ ያለው በባትሪ የሚሰራ ባለ ብዙ ዘርፍ አገልግሎት ዲጂታል የራጂ ማሽነሪ፣ የጥፋት መቆጣጠሪያ ኪት (digital diagnostic quality control)(RAD-Check plus model p6 526 multifunction meter with remot control model Rmt 240 A and collimation test too) የተሰኙ መሳሪያዎችን አመልካቹ በአዳማ ከተማ የአዳማ ሆስፒታል የራጅ መሳሪያዎችን ፍተሻ እንዲያከናውን ታዞ በተጠቀሰው ቀን በስር ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበረውና ከመስሪያ ቤቱ ሹፌር በሆነው በአቶ አረጋዊ ታደገ በሚሽከረከር መኪና በመጫን ወደ ናዝሬት ከወሰዱ በኃላ በተጠቀሰው ሆስፒታል ተገኝተው የምርመራ ስራቸውን ማከናወናቸውን ተከትሎ እንዚህን መሳሪያዎች ለመስሪያ ቤቱ ማስረከብ ሲገባቸው ያለአግባብ ለመበልጸግ ንብረቶችን ባለመመለሳቸውና በመሰወራቸው የመውሰድና የመሰወር የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ነው፡፡ አመልካች ክደው ተከራክረው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን ያሰማ ሲሆን አመልካችም የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን ያለመከላከላቸው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት በክሱ ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ጥፋተኛ አድርጎ

በስድስት ወር ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ ብር እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበውም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በንብረቱ ላይ የፍ/ብሔር ክስ ቀርቦባቸው ሃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መጨረሻና አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመስጠት ስልጣን ባለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰሚ ችሎት ውሳኔ በተሰጠበት ሁኔታ ጥብቅ የሆነ ማስረጃ ምዘና በሚጠይቀው የወንጀል ጉዳይ ላይ ጥፋተኛ መባላቸው በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ ምዘና መርህን ያላገናዘበ መሆኑን ጠቅሰው መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፍ/ብሄር ጉዳይ ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ ተወስኖ እያለ በወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው ተብሎ በእስር እንዲቀጡ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

አመልካች በንብረቶቹ መሰወርና መውሰድ በፍትሐ ብሔር ተከሰው ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ በሰ/መ/ቁጥር 69179 የተወሰነ መሆኑን፣ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች በወንጀል ጉዳዩም የተሰሙ መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከሩ ነጥቦች ሲሆን አከራካሪው የሕግ ጥያቄ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ነፃ የተባለ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚጠይቅበት ሕጋዊ አግባብ አለ? ወይም የለም? የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ የወንጀል ችሎት በፍትሓ ብሔር ችሎት ውሳኔ ሊገደድ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የለም በማለት የሚከራከር ሲሆን አመልካች በበኩላቸው በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ ምዘና መርሁ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ የማስረጃ ምዘና መርህ የጠበቀ በመሆኑ በፍትሓ ብሔር ጉዳይ ነፃ የተባለ ሰው በተመሳሳይ ጉዳይና ማስረጃ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበት ሕጋዊ አካሄድ የለም በሚል የሚከራከሩ መሆኑን ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር በማስረጃነት አግባብነት እና ብቃት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2149 ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ያስገነዝበናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል የተሰጠ ውሣኔ በፍትሐብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት አግባብነት የሚኖረው በወንጀል ክሱ በወንጀል ፍ/ቤት ተከሣሹ ጥፋተኛ ተብሎ ከተወሰነ ስለመሆኑ እና ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የወንጀል ክስ ማስረጃ አመዛዘን መርህ ከፍትሐብሔር የበለጠ ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚጠይቅ መሆኑ ነው፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎችም በፍትሐብሔሩ ጉዳይም የቀረቡና የተሰሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በወንጀሉና በፍትሐብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍትሐብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁል ጊዜ በፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነትን የማያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና አላማ ያስገነዝበናል፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 46386 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍ/ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን በወንጀል ጉዳይ የቀረበ

ማስረጃ ክብደት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ለፍትሐብሔሩ ክርክር ብቃት ያለው ማስረጃ መሆኑና በፍትሐብሔር ክብደት ሊሰጠው አይገባም የተባለ ማስረጃ ለወንጀሉ ክስ ሲቀርብ ክብደት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በጉዳዩ በፍትሐብሔር ክስ ቀርቦባቸው ኃላፊነትን የሚያስከትል ድርጊት አልፈጸሙም ንብረቶቹን በጥንቃቄ አስቀምጠው እያለ ከራሳቸው ቁጥጥር ውጭ በሆነና በሌላ ሰው በተፈፀመ የስርቆት ተግባር ንብረቶቹ መጥፋታቸው ተረጋግጧል በማለት በሰ/መ/ቁጥር 69179 በሆነው አስገዳጅና የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታ አመልካች በጉዳዩ በሙስና ወንጀል ተከሰው በፍትሐብሔር የቀረቡት ተመሳሳይ ማስረጃዎች በቀረበበትና በተሰሙበት እንዲሁም ተመሳሳይ ፍሬ ነገር በተረጋገጠበት ሁኔታ ጥብቅ የሆነ የማስረጃ ምዘና በሚጠይቀው የወንጀል ጉዳይ አመልካች የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል፣ አድራጎቱም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘትና በመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ የተፈፀመ ነው ተብሎ ድምዳሜ መያዙ መሰረታዊ የሆነ የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህን ባልተከተለ ሁኔታ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ድርጊት አመልካች በፍትሐብሔር ተከሰው ነጻ ከተባሉበት ድርጊት ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ጋር የሚጣረስና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94166 ነሐሴ 20 እና 23 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 73873 ጥር 02 ቀን 2004 ዓ.ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ሐ) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል ፡፡
2. አመልካች የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸማቸው በወ/መ/ሕ/ሥሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አልተረጋገጠባቸውም ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

## የመስማሚያ ሀሣብ

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ እስማማለሁ፡፡ ነገር ግን አብላጫው ድምጽ በወንጀል የተሰጠ የጥፋተኝነት ውሣኔ በፍትሐ ብሄር ጉዳይ በማስረጃነት ሲቀርብ ስለሚኖረው ውጤትና በፍትሐ ብሄር የተሰጠ ውሣኔ በወንጀል ጉዳይ ስለሚኖረው ውጤት የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 2149 ድንጋጌ በሰጠው ትርጉም የማልስማማ መሆኔ ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ ጽፌለሁ፡፡

የፍትሐ ብሄር ሕገ ቁጥር 2149 በወንጀል ተከስሶ በነጻ መለቀቅ የፍትሐ ብሄር ኃላፊነትን የማያስቀር መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ ይኸ ድንጋጌ ቀድሞ በፍትሐ ብሄር ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም የተባለ ሰው በወንጀል ጉዳይ ሲከሰስ ማስረጃዎቹ ተመሣሣይ ሲሆን ከወንጀሉ ክስ በነጻ የሚሰናበት መሆኑን የሚደነግግ አይደለም፡፡

ድንጋጌው የራሱ የሆነ ልዩ ባህሪና ዓላማ ያለው በመሆኑ የታቃርኖ አተረጓጎም “Acontrario Interpretation” ተግባራዊ ሊሆንበት የሚችል አይደለም፡፡ በፍትሐብሄር ጉዳይ ተከራካሪዎቹ ግለሰቦች በመሆናቸው በራሳቸው ችሎትና ያለጠበቃ ተከራክረው በወንጀል የተጠረጠረው ወይም የተከሰሰው ሰው የፍትሐ ብሄር ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ሊወሰን የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ በወንጀል ጉዳይ በፍትሐ ብሄር የተሰሙትን ምስክሮችና ማስረጃ በተጠናከረ ሁኔታ በማቅረብ ዕውነቱን እንዲያወጡም ማድረግና የተከሣሹ ማስረጃ ዕምነት የማይጣልበት መሆኑን በማሳየት በወንጀል የተከሰሰው ሰው ወንጀል መፈፀሙን በሌላ ሁኔታ ለማስረዳት ከተቻለ ተከሣሹ በፍትሐ ብሄር ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም በመባሉ ብቻ ከወንጀል ክሱ በነጻ እንዲሰናበት የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 2149 ድንጋጌ ሊተረጎም አይገባውም፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ላይ በፍትሐ ብሄር ከተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ በተለየ ሁኔታ በወንጀል በቀረበው ማስረጃ ተጠሪ አላረጋገጠም፡፡ ይህም የተጠሪ መልስ አመልካች ወንጀል የፈፀመ መሆኑን በበቂ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ አብላጫው ድምጽ አመልካች በነጻ እንዲለቀቅ መወሰኑ ተገቢ ነው ብየ በምክንያቱ ላይ ብቻ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 85237

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዘካሪያስ ገ/ጻዲቅ አለማየሁ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ጉዳይ በድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይገባም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረተው ክስም በሁለት ምድብ የተከፈለ ነው፡፡አንደኛው ክስ አመልካች ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት አስቦ በቦሌ ክፍለ ክተማ ቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኘውን ንብረትነቱ የአቶ ታደሰ ሙለታ መኖሪያ ቤት የሆነውን ከተከራየ በኋላ ካርታ ላሳድስላችሁ ብሎ በውክልና ከወሰደ በኋላ ቤቱን ለመሸጥ ሺል በመታወቁ የተሠጠው ውክልና ተነስቶ ክስ ቀርቦበት ይህ ቤት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት, አግድ ተሰጥቶ እያለ ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ/ም ሐሰተኛ ሰነድ የእግድ ትእዛዝ አዘጋጅቶ እግድ እንዲነሳ ከአደረገ በኋላ የግል ተበዳይ ታደሰ ሙለታ ውክልና የተሰጠው በማስመሰል በሐሰተኛ ውክልና በመገልገል ቤቱን በብር 1,030,000.00(አንድ ሚሊዩን ሰላሳ ሺ.ህ ብር) ለወ/ሮ ሰናይት ብርሃኑ ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ሽጦ ለግል ጥቅም በማዋል በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 696(ሐ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ ማታለል ፈፅሟል የሚል ሲሆን ሁለተኛ ክስ ደግሞ በሐሰተኛ ሰነዶች በመገልገል የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 378 ድንጋጌን ተላልፏል የሚል ነው፡፡የአሁኑ አመልካችም ክሱን ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ስድስት የሰው ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ ክሱን ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ ከተገነዘበ በኋላ የአመልካችን የመከላከል መብት በመጠበቅ የመከላከያ ማስረጃዎችን ሰምቷል፡፡ከዚኅም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በክሱ መሰማት ጊዜ ቀድሞ በጉዳዩ ላይ ተከሰው በነፃ የወጡ መሆኑን የገለጹ መሆኑን የተረዳ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የመከራከሪያ ነጥብ ቀድሞ አመልካች ተከሰው ነጻ የወጡበት ጉዳይ በኋላ ከቀረበባቸው ክስ ጋር ልዩነት ያለው ነው በማለት በሚል ምክንያት ውድቅ ያደረገው ሲሆን ዋናውን ጉዳይ በተመለከተም አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎች የአቀቤን ማስረጃዎችን ያላስተባበለ መሆኑን በመግለጽ የመከላከያ ማስረጃዎችን ውድቅ በማድረግ አመልካችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሰው በቀረቡት ሁለቱም ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ አድርጎታል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመልከቱን በማግለፅ ለሁለቱም ክሶች በድምሩ በ17(አስራ ሰባት)አመት ፅኑ እና በብር 40,000.00(አርባ ሺ.ህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት

ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኝም፡፡የአሁኑ የሰበር አቡቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ላይ ቀድሞ ክስ ቀርቦበት በነፃ ተለቀው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የነፃ መለቀቁ ውሳኔ ጸንቶ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ አልፌው አመልካችን በድጋሚ ክስ ቀርቦ በመቀበል ተጠያቂ በማድረግ መወሰናቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ስር የተመለከተውን የሚጥስ ነው በማለት መከራከሩንና በዚህ ምክንያት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ቀድሞ በፌዴራል መጀረመያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ;ጥር 64230 ክስ ቀርቦበት በነጻ ተሰናብቶ ይኼው ውሳኔ በመ/ቁጥር 109368 በይግባኝ ቀርቦ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጸንቶ ባለበት ሁኔታ ሁኔታ በድጋሚ ክስ ቀርቦበት በወንጀል ተጠያቂ የመባሉትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለአሁኑ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በአመልካች ላይ የተሰጠው በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 696(ሐ) እና 378 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊቶቹን መፈፃማቸው ተረጋግጧል ተብሎ መሆኑን፣አመልካች በነፃ ተሰናብቼአለሁ በማለት የሚከራከሩበት ጉዳይ ደግሞ አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል ተብሎ ክስ ቀርቦባቸው የነበረ መሆኑን፣በሁለቱም ክሶች የቤቱ ባለንብረት የተባሉትና ለክርክሩ ምክንያት የተባለው የቤት ሕጋዊ ባለንበብት የሆኑት ግለሰብ አቶ ታደሰ ሙለታ የተባሉት መሆናቸውን፣አመልካች በነጻ ወጡ የተባለበት የወንጀል ድርጊት ዝርዝር ይዘቱ ሲታይም አመልካቹ ያግባብ ለመበልፀግ ሳይሆን የንብረቱን ባለቤት በንብረቱ እንዳጠይቀምበት ለማድረግ በማሰብ ታህሳስ 30 ቀን 2002 ዓ/ም በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 ልዩ ቦታው የቦሌ ክፍለ ከተማ መስተዳደር ግቢ ውስጥ የግብለ ተበዳይ አቶ አጋ ሙሉታ በሰጡት ህጋዊ ውክልና ተጠቅሞ የቤት ቁጥቱ 52716 የሆነውን ኦርጂናል የቤት ካርታ ወስዶ ባለመመለሱ የግል ተበዳይ ንብረትነቱ የአቶ ታደሰ ሙሉታ የሆነውን በውክልና የሚያስተዳድሩበትን ኦርጅናል የቤት ካርታና ፕላን ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ/ም ከወሰደ በኂላ የግል ተበዳይ መልስልኝ ሲሉት ባለመመለሱ በሌላ ሰው ሃብት ያላግባብ መገለገል ወንጀል ፈጽሟል የሚል መሆኑን፣የአሁኑ ክስ ግን በሐሰተኛ ሰነድ የአቶ ታደሰ ሙሉታን ንብረት በመሸጡ ከባድ የማታላል ወንጀል ፈጽሟል፣በሐሰተኛ ሰነድም ተገልግለዓል የሚል ሁኖ ድርጊቶቹ የተፀሙበት ጊዜና ሁኔታ ቀድሞ ቀርቦ ከነበረው ክስ ጋር የተለያዩ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪብሊክ ሕገ መንግስት የወንጀል መርህ ተደርገው ከተደነገጉት መብቶች አንዱ አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነት ተረግጋግቶ በተቀጣበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና መከሰስና መቀጣት የሌለበት መሆኑን የሚደነግግው አንቀጽ 23 ይገኝበታል፡፡ይህ መርህ በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ውስጥም በአንቀጽ 2(5) ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(4) መሰረት የአገሪ የህግ አካል በተደረጉ አለምአቅፍ ስምምነቶች ውስም

የሲቭልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 14 ስር ያስቀመጠው ድንጋጌ ይህንኑ ያረጋግጣል።በመሆኑም ይህ መብት በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መሆኑ ግልጽ ሲሆን መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ በሕጉ የተቀመጡት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ የግድ ይላል።አንድ ሰው በድጋሚ ልከሰስ አይገባም ብሎ ለመከራከር በሕጉ ይዘትና መንፈስ መሰረት መሟላት ያለባቸው ሕጋዊ መስፈርቶች ተከሳሹ በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ መሰረት ተከሶ የነበረ መሆኑና ቀድሞ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆን በሚገባ መረጋገጥ ስለመሆናቸው ከመርሁ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው።የዚህ መርህ ዓይነተኛ አላማም ዜጎች በአንድ የወንጀል ድርጊት በተደጋጋሚ በሚቀርብ ክስ ስጋት ውስጥ ከመኖር ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ ነው ተብሎ ይታሰባል።በሌላ በኩል መርሁ ተግባራዊ ሲደረግ በሕጉ የተቀመጡት መመዘኛዎችን በጥንቃቄ በማየት የተከሳሹን መብት ተገቢ በሆነ ሁኔታ ለማስከበር ከማስቻሉም በላይ አጥፊዎች ከወንጀል ድርጊት ነጻ እንዳይወጡና ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግና የወንጀል ሕጉን ዓላም በሚያሳካ መልኩ ተግባራዊ መደረግ ያለበት መሆኑ የሚታመን ነው። ስለሆነም ከላይ የተመለከቱትን ሕጋዊ መመዘኛዎችንና ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መመልከቱና ዳኝነት መስጠቱ ተገቢነት ይኖረዋል።

የአመልካችን ጉዳይ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በቀድሞው ክስ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥትቶ አመልካች በነፃ የተሰናበቱ መሆኑን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥ 64230ና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 109368 የሚያረጋግጡት ሀቅ ሲሆን በእነዚህ መዛግብት የታዬው ጉዳይ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በሌላ ሰው ሃብት ያላግባብ መገልገል ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው የተከሰሱትና በኂላም ፍርድ ቤቶቹ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተጠሪን ነፃ ያደረጉበት ምክንያት አመልካች የወሰዳቸው የቤት ካርታዎች በሽያጭና በብድር ውል መያዣነት መሆኑን ተረጋግጧል በሚል ነው።ይህም የሆነው በክሱ ላይ የተጠቀሳን የባለቤትነት ደብተር ካርታና ፕላን እንዲያወጡ እንዲረከቡ ውክልና ሰጪው ለአመልካች ውክልና መስጠታች በመረጋገጡ፣የቤቱ ባለቤት ከባለቤታቸው ጋር በመሆኑን ቤቱን ለአመልካች በመሸጣቸውና በአሁኑ አመልካችና በአቶ ታደሰ ሙለታ የገንዘብ ብድር ውል ተደርጎና በፍርድ ቤት አመልካቸ አቶ ታደሰ ሙለታን በመክሰስ በመ/ቁጥር 88655 የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ለአሁኑ አመልካች የተፈረደላቸወ መሆኑን በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት ፍርድ ቤቶቹ ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው ምክንያት ነው።ባሁኑ ጉዳይ አመልካች የተከሰሱት የግል ተበዳይ ቤት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍድ ቤት በመ/ቁጥር 165253 እግድ ተሰጥቶ እያለ ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ/ም በሐሰተኛ ሰነድ የእግድ ትዕዛዝ በማዘጋጀት እግዱ እንዲነሳ ከአደረገ በኂላ የግል ተበዳይ የአቶ ታደሰ ሙለታ ወክልና የተሰጠው በማስመሰል በሐሰተኛ ውክልና በመገልገል ቤቱን ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ሸጠዋል በሚል ነው።ስለሆነም አመልካች ቀድመው በግል ተበዳይ ላይ የፍትሓ ብሔር ክስ አቅርበው የነበሩ መሆኑ ቢረጋገጥም በፍርድ ቤት የተሰጠውን እግድ ግን ለውጠዋል፣እግድ የተነሳ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃም ሐሰተኛ ነው በማለት አቃቤ ክስ መመሰረቱን በግልጽ የምንረዳው ጉዳይ ነው።አመልካች ከግል ተበዳይ ወሰዱ የተባሉትና ስለመኖሩ በመ/ቁጥር 64230 በቀረበው የወንጀል ክስ ተረጋግጧል የተባለው የውክልና ሰነድም በጥር ወር 2002 ዓ/ም ውስጥ መሻሩ አሁን እያከራከረ ባለው የወንጀል ጉዳይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል ተብሎ በአቃቤ ሕግ በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበባቸውም የካቲት 17 ቀን

2002 ዓ/ም ስለመሆኑ በፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 64230 ጋር ተያይዞ ካለው የክስ ማመልከቻ ተመልክተናል፡፡እንዲህ የግል ተበዳይ ቤት የተሸጠው በሐሰተኛ የፍርድ ቤት እግድ ማንሻ ትዕዛዝና የውክልና ስልጣን ስለመሆኑ በሰው ምስክርነትም ሆነ በፎረንሲክ ምርምራ ውጤት ማስረጃዎች በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ በቀደመው ክስ አመልካች የግል ተበዳይን በቤቱ እንዳይገለገል አድርጓል የተባለው የቤቱን ካርታ ሊመልስ አልቻለም ተብሎ ሲሆን በሁለተኛው ክስ ግን ሐሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት የግል ተበዳይን ቤት ሸጧል በሚል ነው፡፡ በግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ወይም በፊት አመልካች የግል ተበዳይን ቤት በሕጋዊ መንገድ የገዙት ስለመሆኑም አልተረጋገም፡፡በመሆኑም አመልካች አሁን የቀረበበት ክስ ዝርዝር ይዘቱ፣የድርጊቱ አፈጻጸም እና ጥሰት ተደርጎበታል የተባለው የግል ተበዳይ የመብት አድማስ ቀድሞ ክስ ከቀረበበት ጉዳይ ዝርዝር ይዘት ጋር የማይገናኝ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት በአንደ ጉዳይ በድጋሚ በወንጀል የተከሰሱ መሆናቸውን ገልጸው ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አላገኘንም፡፡

የወንጀል ድርጊቶችን አፈጻጸም በተመለከተ አመልካች ግልጽ የሆነ የሰበር ቅሬታ ያላቀረበቡት ቢሆንም ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርደ ቤቶች በሚገባ ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑና ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ሲታይም የተለዬ ድምዳሜ የሚያዝበት ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ያልወጡትን ሰነዶችን ከመንግስት መስሪያ ቤቶች እንደወጡ በማስመሰል፤በሐሰተኛ መንገድ በማዘጋጀት የግል ተበዳይን ቤት የሸጡ መሆናቸው በአንቀፅ 696(ሐ) ስር የተመለከተውን መተላለፋቸውን የሚያሳይ ሲሆን ይህንኑ ቤቱን ለመሸጥ አድራጎት ጥቅም የዋሉት ሐሰተኛ ሰነድ መሆኑ ደግሞ ይኼው አድራጎት በተገቢው ድንጋጌ በተደራቢነት የሚያስጠይቃቸው መሆኑን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 699 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም አመልካች በአንቀጽ 696(ሐ) እና 375 ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ መባላቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2)፣58 እና ከወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር ሲታይ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው ድንጋጌዎች ከሚያስቀጡት የቅጣት መጠንና ከቅጣት አጣጣል መርሆዎች እንዲሁም ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 101193 ሕዳር 21፣ታህሳስ 02 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79603 መስከረም 30 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ሐ)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ለማረሚያ ቤቱ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች በአንድ የወንጀል ድርጊት ድጋሚ አልተከሰሱም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**እ/ብ**



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ.85596

መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** እነ ሰይፉ ደስታ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ - አልቀረበም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሠጠው የቅጣትና የቅጣት አፈፃፀም ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በከባድ ቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፊንፊኔ ዙሪያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆኑ ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-41869 በማሽከርከር ላይ እያለ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም ከቀኑ ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን ጫናጮ ከተማ ቀበሌ 01 ፌኔት ግዛው የተባለች ልጅ በመግጨት በከባድ ቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል፡፡ አመልካች አደጋው ተከስቷል፡፡ ከአቅሜ በላይ በሆነ ሁኔታ ህፃኗን ገጭቻለሁ በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የሰው ምስክሮችና የትራፊክ ፕላን መግለጫ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ ተጠሪ መከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) የተመለከተውን በመተላለፍ በከባድ ቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ነው በማለት ውሳ ሰጥቷል፡፡

የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ አመልካች በህፃኗ ወላጆች ብር 35,000 (ሰላሳ አምስት ሺ ብር) ካሳ የከፈለ መሆኑን፣ የዘወትር ፀባዩ መልካም የነበረ መሆኑንና በዐቃቤ ህግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመዘርዝር አመለካች በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ቀላል እስራትና በብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የቅጣት ውሳኔውን በማሻሻል አመልካች በስምንት ወር እስራትና በብር 700(ሰባት መቶ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው

ችሎት የቅጣት ውሳኔው ሳይፈፀም አመልካች ለሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ መስጠት ተገቢ ሆኖ ያገኘው መሆኑን በመግለፅ፣ የቅጣት ውሳኔው ለሁለት ዓመት ተገድቦ እንዲቆይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የእስራትና የገንዘብ ቅጣቱን የወሰነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያወጣውን የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2000 ሳይከተል ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የቅጣት ውኔሳ አፅንቶታል፡፡

የእስራት ቅጣት አፈፃፀሙንም በተመለከተ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የእስራት ቅጣቱ አፈፃፀም ለሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ ታግዶ እንዲቆይ የሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር አመልካች የተወሰነበትን የአንድ ዓመት ከስድስት ወር የእስራት ቅጣት ይፈፅም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን የቅጣት ውሳኜ የሻረው ያለበቂ ምክንያትና ሕጋዊ መሰረት ነው፡፡ ተጠሪ የቅጣት ውሳኜው አፈፃፀም መገደብ የለበትም በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ቅጣቱ የእስራት ቅጣትና መቀጮ በጣምራ የያዘ መሆኑን ገልፆ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ቅጣቱ በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ ያመይገደብበትን ምክንያት በውሳኔው ሳገልፅና ሳይዘረዝር ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቅጣት ውሳኔው እንዲገደብ የሠጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ ጥር 2 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ የወንጀል ህጉንና የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ማፅናቱ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ምንም አይነት ሙያዊ ጥንቃቄ ባለማድረጉና በፍጥነት በማሽከርከር ህፃኗን ገጭቶ የሞት አደጋ አድርሷል፡፡ ይህ የአመልካች አድርጎት የቅጣት ውሳኔውን ለመገደብ የሚያስችል ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቅጣት ውሳኔው እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር እሎት መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ጥር 24 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያደረጉት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የእስራት ቅጣት አፈፃፀሙ በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ ተገድቦ እንዲቆይ የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ህጉን መሰረታዊ ድንጋጌዎችና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 16 መሰረት በማድረግ የአንድ ዓመት ከስድስት ወር እስራትና ብር 1500(አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) መቀጮ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የቅት ውሳኔ የሻረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን በተዛባ መንገድ በመተርጎም መሆኑን ከውሳኜ ይዘት ተረድተናል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት

የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በመሻር፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ማፅናቱ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታይ በጭብጥነት የተያዘ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አመልካች በአንድ ዓመት ከስድስት ወር የእስራት ቅጣትና በብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

2. በዚህ ሰበር ችሎት አከራከሪ የሆነው ጭብጥ በአመልካች ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት ውሳኔ አፈፃፀም ለሁለት አመት የሙከራ ጊዜ ሊገደብ ይገባዋል ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ይግባን ሰሚው ችሎት በአመልካች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም ለሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ እንዲገደብ ውሳኔ የሰጠው የቅጣት ውሳኔው መገደቡ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192 የተመለከተውን መሰረታዊ ዓላማ የሚያሳካ ነው በማለት እንደሆነ ከውሳኔው ተረድተናል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የእስራት ቅጣቱ አፈፃፀም እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ የሻረው አመልካች ከባድ በሆነ ቸልተኝነት የግል ተበዳይን በመግጨት የሞት አደጋ አስከትሎባታል በማለት ነው፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አመልካች የወንጀል ህጉን አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ በከባድ ቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱን በመመልከት ብቻ የቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም ለመገደብ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ሆኖም በተከሳሽ ላይ የተወሰነ የቅጣት ውሳኔ ከመገደቡ ወይም የገደብ ውሳኔው ከመሻሩ በፊት የቅጣት ገደብ ስለሚከለከልበትና ስለሚሻርበት ሁኔታ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና አላማ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሳሽ የቅጣት አፈፃፀም እንዲገደብ ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ መስጠት የማይችሉባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 194 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች፣ አንደኛውን ሁኔታ አመልካች የሚያሟላ ስለመሆኑ በውሳኔው አልገለፀም፡፡ ይህም በአመልካች ላይ የተወሰነውን የቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም እንዳይገደብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 የተዘረዘሩት የመከላከያ ምክንያቶች በሌሉበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በወኝጀል ሕጉ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱን በመመልከት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቅጣት ውሳኔው እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ፣ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ መሰረት ያላደረገ ነው፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ አመልካች የተወሰነበት የእስራት ቅጣት ከሚፈፀም ይልቅ የቅጣት ውሳኔው ታግዶለት አመሉ ቢፈተን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 190 በተደነገገው መሰረት የአመልካችን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻልና አመልካችን ወደመደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚያስችል መሆኑ ስለ አመልካች ባሀሪ ማህራዊና አቋም፣ የትምህርት ደረጃና የወንጀለኛነት ባህሪና ፀባይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለው በይግባኝ ሰሚው ችሎት የታመነበትና ውሳኔ የተሰጠበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ከተሰጠው የሰበር ሥልጣን በመውጣት ስለአመልካች ጠባይ አመልካች ከጥፋቱ ሊታረምና ሊሻሻል ስለሚችልበት ሁኔታ ያሉትን ፍሬ ጉዳዮች በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 190 እና 192 መሰረት ቅጣቱ እንዲገደብ የሰጠውን ወሳኔ መሻሩ የሕግ መሰረት

ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔና የሕግ ትርጉም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 32280 እና በሌሎች መዝገቦች የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያልተከተለና የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት በሁለት ዓመት ሙከራ ጊዜ እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰራታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በአመልካች ላይ የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ ሊገደብ አይገባም፣ አመልካች የእስራት ውሳኔውን ይፈፅም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡
2. በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የወሰኑት የአንድ ዓመት ከስድስት ወር የእስራት ቅጣት በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ ተገድቦ እንዲቆይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 190 እና አንቀጽ 192 መሰረት ወስነናል፡፡ በዚህ በኩል የእስራት ቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም እንዲገደብ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 190፣ አንቀጽ 192 እና አንቀጽ 194 መሰረት ያደረገ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት በማለት ወስነናል፡፡
3. በአመልካች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም ለሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ የተገደበ መሆኑን እንዲያውቁት ለኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽንና ፍትህ ቢሮ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 86570

ሚያዝያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ጌታቸው ገላዬ ፈረደ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ክልል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ሰው የመግደል ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ባሁኑ አመልካች እና አቶ ሰይፈ ገ/ሚካኤል በተባሉት ግለሰብ ላይ በሐዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተከሳሾቹ በዋና ወንጀል አድራጊነትና ተካፋይነት ሰኔ 02 ቀን 2004 ዓ/ም በሀዋሳ ከተማ ባህል አዳራሽ ክፍለ ከተማ በአደሬ ቀበሌ ፋሚሊ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው ቤት ሟች ቡቼ ወይም ብስራት ተፈሪ የተባለውን የአሁኑ አመልካች በያዘው ሽጉጥ ተኩሶ ግራ ብብቱን መትቶ እንደገደለውና የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ ደግሞ የውሲኪ ጠርሙስ ይዞ ሟች እንዳይቀሳቀስ ያደረገውና ሟች የተመታበት ሽጉጥ ቀላህ በመሰወር የአሁኑን አመልካች የረዳ መሆኑን ዘርዝሮ ተከሳሾቹ ሆነ ብለው በፈፀሙት ከባድ የግድያ ወንጀል በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ32(1(ሀ) እና 539(1ሀ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም እንደክሱ ድርጊቱን ያለመፈፀማቸውን ጠቅሰው ጥፋተኛ ያለመሆናቸውን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም ድርጊቱን ራሱ ለመከላከል ሲሉ የፈፀሙት መሆኑን የሚያሳይ ጭብጥ አስይዘው የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአመልካች ድርጊት በሕጋዊ መከላከል ስር የማይወድቅ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ጠቅሶ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክረክር ውድቅ በማድረግ የወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰ ሲሆን ድርጊቱ የሚሸፍነው ደግሞ በአቃቤ ክስ በተመለከተው ድንጋጌ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 540 ስር ነው በማለት አመልካችን በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ያላቸው ሲሆን ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን ጋር አዛምዶ መመልከቱን ገልፆ አመልካችን በ15 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ መባላቸውን በተመለከተ ያፀናው ሲሆን ቅጣቱን በተመለከተ ግን አሻሽሎ ስምንት ዓመት ሊሆን ይገባል ሲል ምክንያቱን ጠቅሶ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ

ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበል የቀረ ሲሆን የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ድርጊቱን በሕጋዊ መከላከል ስር የሚሸፍን ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካችን በወንጀል ተጠያቂ ማድረጋቸው ከህጉ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ የአመልካች አድራጎት በሕጋዊ መከላከል ስር የማይሸፈን ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ጠቅሶ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በወንጀል ድርጊት ተጠያቂ መደረጋቸው ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሟችን መግደላቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ድርጊት ሕጋዊ መከላከል ነው፡፡ በወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም በማለት መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን በወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው በማለት ውሳኔ ሊሰጡ የቻሉት አመልካች ከሟች ጋር ተጣልተው በሰዎች ከተገላገሉ በኃላ ሟች ወደ አመልካቹ በመሄድ ላይ እያለ አመልካቸ ሌሎች አማራጮችን ሳይጠቀሙ የጦር መሳሪያ ያልያዘውን ሟች ወደ አመልካቹ ሳይጠጋ ተኩሰው መምታታቸው በሕጋዊ መከላከል ስር የሚሸፈን አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካቹ ሟች በሕይወቱ ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል ሳንጃ ይዞ በመምጣት ጥቃት ሊሰነዝርብኝ ሲል ድርጊቱን መፈፀሜ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን ውድቅ ማድረጋቸው ያላግባብ ነው በማለት አድራጎታቸው በሕጋዊ መከላከል ስር እንዲወድቅ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ ባግባቡ ያልታዩላቸው መሆኑን በመግለጽ የሚከራከሩ መሆኑንም ተረድተናል፡፡ ሆኖም አመልካቹና ሟቹ ተጣልተው ቆይተው ሰዎች ከገላገሏቸው በኃላ ሟቹ ወደ አመልካች የሥራ ቦታ ተመልሶ በመሄድ ላይ እያለ በሽጉጥ ጥይት ተመትቶ ስለመሞቱ ከመረጋገጡ ውጪ አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ ሟቹ በህይወት አትኖራትም ብሎ ዝቶ ከሄደ በኃላ ሳንጃ ይዞ በመመለስ ሌላ አማራጭ በሌለበት ሁኔታ ጥቃት ሊያደርስ ሲል ነው ድርጊተጁ የተፈፀመው በማለት የሚያነሷቸው ፍሬ ነገሮች ፍሬነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያላረጋገጧቸው በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረት ከተሰጠው ስልጣን አንፃር በዚህ የሰበር ደረጃ ተቀባይነት የሚሰጣቸው ነጥቦች አይደለም፡፡ ይህ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተትን ከማረም ውጪ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በሕግ አልተሰጠውምና፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጧቸው ነጥቦች አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ ከሚያነሷቸው ጋር የማይጣጣሙ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረቡትን የአመልካችን ቅሬታዎችን የምንቀበላቸው ሁነው አልተገኘም በበታች ፍርድ ቤበቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እንዳለ ይዘን ጉዳዩ በህጋዊ መከላከል ስር የሚወድቅ መሆን ያለመሆኑን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ህጋዊ መከላከል በወንጀል የሚያስቀጣው የራስን ወይም የሌላውን ሰው መብት ህገ ወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈጸመ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪብሊክ የወንጅል ሕግ አንቀጽ 78 ይዘትና መንፈስ የምረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ሕጋዊ መከላከል የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትለው ተመጣጣኝ የሆነ ዘዴ ወይም መሳሪያ በመጠቀም በቅርብ መድረሱ የማይቀረውን ህገ ወጥ የሆነ ጥቃት ለመከላከል አስፈላጊ የሆነ ድርጊት መፈፀም ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪብሊክ የወንጀል ህግ አንቀፅ 78 እነ 79 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ በግልጽ ያሳያል፡፡ አመልካች በሕይወታቸው ጥቃት እንዳይደርስ ሌላ አማረጭ ያልተጠቀሙ መሆኑን ሟቹ ከያዘው መሳሪያ ተመጣጣኝነት የሌለውን መሳሪያ  መጠቀማቸው በሚገባ የተረጋጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ድርጊቱ የተፈፀመው በህጋዊ መከላከል ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 541 ስር በተመለከተው አኳኋን ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን የማሳለፈው አድራጎት ነው እንዳይባልም ድርጊቱ የተፈፀመው አመልካቹና ሟቹ ጠብ አስነስተው በሰዎች ተገላግለው ከተለያዩ በኃላ በመሆኑ ቅጣትን የሚያቀሉ ምክንያቶች ሰውን የመግደል ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት  የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጡት ነጥቦች ስንነሳ የአመልካች አድራጎት መበህጋዊ መከላከል ስር የሚሸፈን ሁኖ ስላላገኘነው በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው አመልካች በቅጣት አወሳሰን ጊዜ የበታች ፍርድ ቤቶች የወንጀሉን ደረጃ ከባድ ነው በማለት መመደባቸው ተገቢ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ውሳኔ ሲሰጥ የያዘው ድምዳሜ መሰረት ያደረገ እንጂ ይሕ የሥር ፍርድ ቤት ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተለውጦ ወንጀሉ መካከለኛ ደረጃ ተብሎ የተመደበ መሆኑን መሰረት ያላደረገ የክርክሩን ሂደት የማያሳይ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም አመልካች በወንጀል ተጠያቂ ናቸው ተብሎ በተራ ቁጥር የሰው  መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላላገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12474 ጥቅምት 14 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58175 ታህሳስ 04 ቀን 2005 ዓ.ም ቅጣቱ ብቻ ተሻሽሎ የፀናው እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር58330 ታህሳስ 18 ቀን 2005 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች ድርጊት በሕጋዊ መከላከል የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
3. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲየስፈጽም ለማ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 80119

የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረቶ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ተድላ ተገኝ ጉዳይ ተከታይ ቢያዝን አበራ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ሕግ የረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተው ክስ በአምስት ምድብ የተከፈለ ሲሆን አንደኛው ክስ በ1949 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 667(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ጥር 10 ቀን 1995 ዓ/ም ለአቶ አመሸ ጌታሁን በሰጡት የብር 40,000.00(አርባ ሺህ) ገንዘብ ብድር በወር 10% እንዲከፍል በመጠየቅና በመዋዋል ገንዘቡን በማበደር ተበዳይ ወለዱን ለወራት ሲከፍሉ ቆይተው በማቋረጡ በፍርድ ቤት ተከሰው በጠቅላላ ከእነወለዱ ብር 58,000.00(ሃምሳ ስምንት ሺኅ ብር) ቤቱን ሸጦ እንዲከፈል በማድረጋቸው የአራጣ የወንጀል ድርጊት ፈጸመል የሚል ሲሆን 2ኛው ክስም አመልካች ቀኑ በትክክል ባልታወቀበት በነሐሴ ውር በ1994 ዓ/ም ለግል ተበዳይ አቶ አሰፋ አበበ በወቅቱ የገጠመውን የገንዘብ ችግር ምክንያት በማድረግ ብር 20,000.00(ሃያ ሺኅ ብር) በማበደር በህግ ከተፈቀደው የወለድ መጠን በላይ በወር 10% ሊከፍል በመዋዋልና በመያዣነት የገንዘብ መጠን የተፃፈበትን ቼክ በተበዳይ የተፈረመና በአመልካች ልጅ ስም የተፃፈ በመቀበል ብድሩን በመስጠት ተበዳይ ዋናውን ገንዘብ ከፍለው ወለዱን ብር 18,000.00 ሳይከፈሉ በመቅረታቸው በፍርድ ቤት ክስ በመመሰረት የመኖሪያ ቤታቸውን ያሸጡ መሆኑን በመጥቀስ ነባሩን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 667(1) ተላልፈዋል የሚል ነው፡፡3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ክሶችም በተለያዩ ግለሰቦች፣በተለያዩ ጊዜያት ከተፈጸሙ የአራጣ ወንጀል ድርጊቶች ጋር የተያያዙ ሁነው በስር ፍርድ ቤት በተለያየ የክርክር ደረጃ አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ የተደረጉባቸው ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

አመልካችም ክሱን ከተረዱት በኋላ በሶስተኛው ክስ ላይ ተቃውሞ ከማቅረባቸው ውጪ በሌሎች ክሶች ላይ ተቃውም የሌላቸው መሆኑን በመግለጸቸው ምክንያት ስለየድርጊቱ አፈጻጸም የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ክደው ተከራክሯል፡፡አቃቤ ሕግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስጃዎች ያሉት መሆኑን ገልጾ ማስረጃዎችን አስምቷል፡፡የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላም የአመልካች የመከላከል መብቱ ተጠብቆላቸው የመከላከያ ማስረጃዎች ተሰምተዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች የመከላከያ ማስጃዎች የአቃቤ ሕግ

ማስረጃዎችን ለማስተባበል የሚችሉ ሳይሆኑ የሚያጠናክሩ ሁነው መገኘታቸውን ገልጾ የመከላከያ ማስረጃዎችን ውድቅ በማድረግ አመልካችን በሁለት ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ ቅጣቱን በተመለከተ ደግሞ ለሁለቱ ክሶች ለእያንዳንዳቸው በአንድ አመት ከስድስት ወር፣በድምሩ በሶስት አመት ፅኑ እስራትና በብር 4000.00(አራት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአቃቤ ሕግ ክስ ይዘት በወንጀል ሕጉ ስለአራጣ የተደነገገውን ድንጋጌ እንደማያቋቁም፣አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ አቀራረብና የማስረዳት ግዴታ በሕጉ የተመለከተውን መመዘኛ ያላሟላ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኛነት ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ላይ ከተጠቀሱት ክሶች ውስጥ በተራ ቁጥር ሁለት በተጠቀሰው የወንጀል ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተው ክስ ብዛቱ አምስት ሲሆን ጥፋተኛ የተባሉት ግን በሁለት ክሶች ብቻ ሁኖ በእነዚህ ክሶችም አመልካች የግል ተበዳዮች የገንዘብ ችግር ያጋጠማቸው መሆኑን በማወቅና በተለያዩ ዘዴዎች የግል ተበዳዮችን በማግኘት በተለያዩ ጊዜያት፣ለተለያዩ ግለሰቦች የተለያየ መጠን ያለውን የገንዘብ ብድር ሰጥተው ከህግ ከተደነገገው ውጪ የወለድ ተመን ሲያስከፍሉ ቆይተዋል፣በዚህ አድራጎታቸውም የአራጣ ወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል በሚል ነው፡፡አመልካች የወንጀል ድርጊቶችን ክዶ የተከራከረ ሲሆን አቃቤ ሕግ በኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ ከአሰማ በኋላ የቀረቡት ማስረጃዎች የወንጀል ድርጊቱ ስለመፈጸሙ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት በበቂ ሁኔታ መመስከሩን ፍርድ ቤቱ በመገንዘብ አመልካች የአመልካችን የመከላከል መብት ያከበረላቸው ሲሆን አመልካች የመከላከያ ማስረጃዎቹን አቅርበዋል፡፡በዚህ ችሎቱ እንዲታይ በጭብጥነት ለተያዘው የሁለተኛ ክስ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ለመከላከል ያቀረቡት በፍርድ ቤት የተሰጠውን የፍትሀ ብሔር ክስ ውሳኔዎችን ሲሆን ፍርድ ቤቱም እነኚህን የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎች ይዘት በመመዘን የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን የማስተባበል ብቃት የሌላቸው መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮ ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡በዚህ ረገድ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም በክሱ ለተጠቀሱት ግለሰብ መያዣ ይሆነው ዘንድ ቼኩ ተፅፎ የተሰጠው ለአመልካች ልጅ እንጂ ለአመልካች አይደለም፣የፍትሃ ብሄር ክሱ የሚያሳየውም አመልካችን ሳይሆን የአመልካችን ልጅ ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የአመልካች ልጅ የተሰጣቸው ቼክ መነሻው ለግል ተበዳዩ አመልካች የሰጡት ብድር መሆኑንና ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን፣ አመልካች ብድሩን ለግል ተበዳይ ማበደራቸውን፣የብድሩ ወርሃዊ የወለድ መጠንም ሕጋዊ ያለመሆኑን ከማረጋገጡም በተጨማሪ

የአመልካች ልጅ በወንጀሉ አፈጻጸም ተሳታፊ ነበሩ ከሚያስኝ በስተቀር አመልካችን ከወንጀል ተጠያቂነት የማያድናቸው መሆኑን በፍርዱ ሐተታ ላይ በገለፀው ምክንያት መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ይህ የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል፡ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ከተቀመጡባቸው ድርጊቶች ሁለተኛው ክስ በልጃቸው ስም በመያዣነት በተሠጠው ቼክ እና የልጁ ተወካይ በመሆን የተበዳይን ቤት ማሸጡ ሆኖ ባለበት የስር ፍርድ ቤቶች በአራጣ ማበደር ወንጀል ጥፋተኛ ማለታቸው ተገቢ መሆን ያመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው የቼኩ መነሻው የአመልካች ብድር መሆኑና ወለዱም ሕጋዊ ያልነበረ መሆኑ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለመረጋገጡ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ አመልካችን ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፡፡ይልቁንም አመልካች በድርጊቱ በነባራቸው ተሳትፎ መጠን በወንጀል የሚጠየቁ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡በመሆኑም አመልካች ድርጊቶችን ስለመፈፀማቸው አቃቤ ሕግ በማሰረጃቹ አላስረዳም፤በመከላከያ ማስረጃዎችም ተደግፌአለሁ በማለት አመልካች የሚያቀርቡት የሰበር ቅሬታ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ሁኖ ስለአገኘነው ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን አንጻር የምንመለከታቸው ሁኖ ስላለአገኘን አልፈናል፡፡

በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡትን ነጥቦች ይዘን ወደ ሕጉ ጥያቄ ስንመጣ አመልካች ከሕግ ከተደነገገው ውጪ በወር 10% በማስከፈል ለግል ተበዳዮች ገንዘብ ማበደራቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ከአበደሩት ገንዘብ እጥፍ የሆነ ገንዘብም ከግል ተበዳዮቹ የሰበሰቡና ንብረታቸውም እንዲሸጥ ያደረጉ በመሆኑ አድራጎታቸው የአራጣ ወንጀል የሚያቋቋም ሁኖ አግኝተናል፡፡ቅጣትን በተመለከተ የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ የምንመረምረው ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 45515 መጋቢት 03 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02-04311 ሚያዚያ 02 ቀን 2004 ዓ/ም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 23702 ሚያዚያ 24 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ሐ) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በሁለት የአራጣ የወንጀል ድርጊቶች ጥፋተኛ ተብለው በሶስት አመት ፅኑ እስራትና በብር 4000.00(አራት ሺህ)የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ተብሎ በተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠ የቅጣት ውሳኔ የፀና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ይጻፍ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

እ/ብ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 79389

መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ሪታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካቾች፡-** 1. ዶ/ር ታጀዲን ያህያ
2. አቶ መሐመድ ጀማል } ቀርቧል

**ተጠሪ፡-** የአማራ ክልል ዐ/ሕግ አቶ አዱኛ ማራዊ - ቀርቧል

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በሌላ ሰው ጥቅም የስራ አመራር ላይ የተፈፀመ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በአ/ብ/ክ/መንግስት ደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካቾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ 702/3/ በመተላለፍ በደሴ ከተማ ቀበሌ 09 ማዕከል መርከዘል ብርሃን የሚባል ለሙስሊሙ ማህበረሰብ በበጐ አድራጐትነት ወይም በወቅፋ የተሰጠ ለትርፍ ያልተቋቋመ ህጋዊ ሰውነት ያለውን ድርጅት 1ኛ አመልካች ከሟች ወላጅ አባቱ በተሰጠው የኑዛዜ ውክልና መሰረት የድርጅቱን ስራ ሊመራ ሲገባ ድርጅቱ ከተቋቋመ ዓላማ ውጪ በስሙ የንግድ ፈቃድ በማውጣት ወደ አትራፊ ንግድ ድርጅት ቀይሯል፤2ኛ አመልካችም ድርጅቱን ወደ ግል ድርጅት እንዲዞር በማሰብ አዲስ የሚቋቋም ተቋም በማስመሰል በሚያዝያ ወር 1992ዓ.ም ንግድ ፈቃድ በማውጣት የድርጅቱን ገቢና ሃብት ለግል ጥቅማቸው በማዋል በሌላ ሰው የንብረት ጥቅም ስራ አመራር ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ክስ የቀረበባቸው ሲሆን አመልካቾችም እንዲቀርቡ ከተደረገ በኋላ ወንጀሉን አለመፈፀማቸው ክደው የእምነት ክህደት ቃላቸውን በመስጠታቸው ዐ/ህግ እንደ ክሱ የሚያስረዱለትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ ከተሰሙና ከተመረመሩ በኋላ አመልካቾች ወንጀሉን መፈፀማቸው ተረጋግጦባቸዋል በማለት እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ አመልካቾችም በትዕዛዙ መሰረት ወንጀሉን ለመከላከል የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረቡ ቢሆንም በዐ/ህግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ማስተባበል አልቻሉም በሚል የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠባቸው በኋላ 1ኛ አመልካች በ6 ወር እና 2ኛ አመልካች ደግሞ በ1 ወር እስራት እንዲቀጡ ከተወሰነ በኋላ በወ/ህጉ አንቀጽ 192 መሰረት ቅጣቱ በ2 ዓመት የፈተና ጊዜ በመስጠት እንዲገደብላቸው ተደርጓል፡፡ በ1ኛ አመልካች የተሰጠው የድርጅቱ ንገድ ፈቃድም ከንግድ መዝገብ ተሰርዞ ድርጅቱ በቀድሞ ሁኔታ እንዲተዳደር በማለት ተጨማሪ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

አመልካቾችም በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለዞኑ ከፍ/ፍ/ቤትና ክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ሁለቱም ፍ/ቤቶች ተመሣሣይነት ባለው መልኩ የስር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ሚያዝያ 30 ቀን 2004ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህንኑን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ የቀረበብን ክስ በወ/ህጉ ቁ. 217/1/ሠ/ መሰረት በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን ጉዳዩ ቀደም ሲል በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ቀርቦ ውሣኔ ያገኘ መሆኑ እየታወቀ እንደገና በወንጀል ቀርቦና ታይቶ ጥፋተኛ መባላችን ስህተት መሆኑን ድርጅቱም በጐ አድራጐት ድርጅት ነው መባሉ ስህተት መሆኑን የድርጅቱ ንግድ ፈቃድ በእኔ 1ኛ አመልካች ቢወጣም የድርጅቱ ካርታና ኘላን በድርጅቱ ስም ያለ መሆኑንና የድርጅቱ ንግድ ፈቃድም በ1ኛ አመልካች እንዲወጣ የተደረገው አቅም ካላቸው ተማሪዎች መጠነኛ ክፍያዎችን በመቀበል ለተለያዩ ወጪዎችና ለአስተማሪዎች ደመወዝ እንዲውል መደረጉ ድርጅቱን ከተረጅነትና በዘላቂነት ከችግሩ ለማውጣት በማሰብ እንጂ የግል ጥቅምን ለማሟላት አይደለም፡፡ ይልቁንም 1ኛ አመልካች ከግል ወደ 500,000 ብር በላይ ለድርጅቱ እርዳታ ማድረጌ ጥፋተኛ የተባልኩበትን ወንጀል ለመፈፀም ሀሳብ የሌለኝ መሆኑ እየታወቀ ጥፋተኛ ሆነን መቀጣታችንና የድርጅቱ ንግድ ፈቃድም ተሰርዞ በቀድሞ ሁኔታ እንዲተዳደር በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ እንዲወሰንላቸው በመከራከር ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጎ የበኩሉን መልስ ሰጥቶበታል፡፡ አመልካቾችም የመ/መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበባቸው ውሣኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በውሣኔዎቹ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው መሆን አለመሆኑን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውና በደሴ ከተማ ቀበሌ 09 መርከዘል ብርሃን ተብሎ የሚጠራው ት/ቤት በመጀመሪያ በበጎ አድራጊዎች ሲቋቋም ለትርፍና የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት የተቋቋመ ሣይሆን በበጎ አድራጎት ማህበር ዓይነት ወላጅ አልባ የሆኑ ህጻናትን በነጻ ማስተማር አረብኛ ቋንቋንና ቅዱስ ቁራንን ማስተማርና እንዲሁም መስጊዶችን ለመስራት የተቋቋመ ስለመሆኑ በእነዚህ በጎ አድራጉ በሆኑ ሰዎች በተሰበሰበ ንብረት አማካኝነት ት/ቤቱ የመምስረቻ ጽሑፍ ተቀረፆለት በ1984ዓ.ም የተቋቋመ መሆኑና ከተቋቋመም በኋላ ለተወሰኑት ዓመታት ስራውን ያለምንም ክፍያ በነጻ ሲያከናውን የቆየ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ነገር ነው፡፡ ይሁን እንጂ በኋላ ላይ 1ኛ አመልካች ድርጅቱን እንዲመራ ከሟች አባቱ በኑዛዜ በተሰጠው ኃላፊነትና 2ኛ አመልካችም ከ1ኛ አመልካች ባገኘው ውክልና መነሻነት የት/ቤቱን ስራ በመምራት ላይ እያሉ በ1992ዓ.ም የድርጅቱን ንግድ ፈቃድ በ1ኛ አመልካች እንዲወጣ በማድረግ በፊት ከተቋቋመለት ዓላማ ወጪ ወደ ንግድ ድርጅትነት ቀይረው እስከ አሁን በዚሁ አኳኋን እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ት/ቤቱ በፊት ያለ ክፍያ በነጻ ሲያከናውን የነበረው ስራ ቀርቶ አሁን ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች ገንዘብ እየሰበሰቡ መሆናቸውን አመልካቾችም አይክዱም፡፡ የተከሰሱበት ድርጊትም ይሄው ነው፡፡ ይህ ድርጊት ደግሞ እስከ አሁንም ሣይቋረጥ የቀጠለ በመሆኑ በወ/ህጉ አንቀጽ 219/2/ ስር እንደተመለከተው በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የይርጋ ክርክርን በሚመለከት የቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚህ ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ጉዳዩ ከዚህ ቀደም በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቶ እያለ በድጋሜ በወንጀል ተከስን ጥፋተኛ መባላችን አግባብ አይደለም በሚል የቀረበው ክርክርም ቢሆን በፍታብሔር ኃላፊነት ተከሰው በጉዳዩ ላይ ስልጣን ባለው አካል ውሣኔ መስጠቱ በወንጀል ህጉ በኩል ያለውን ኃላፊነት ሊያስቀር የሚችል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ

የቀረበው አቤቱታ ከወ/ህጉ አንቀጽ 2/5/ እና እንዲሁም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 130/2/ለ/ አኳያ ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነም፡፡ የተከሰሱበት ድርጊትም በህግ ወይም በውል አማካኝነት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ያለአግባብ በመገልገል በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት በሚያደረስ አኳኋን በጎ አድራጎት የነበረን ድርጅት ወደ ንግድ ድርጅትነት ቀይሯል በሚል ሲሆን ይህ ድርጊትም ስለመፈፀሙ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ስልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች መፈፀሙ የተረጋገጠው ድርጊትም አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ህጉን ድንጋጌ አንቀጽ 702/3/ ስር የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበባቸው ውሣኔዎች ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው ሆኖ ስላላገኘን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በዚህ ጉዳይ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ደቡብ ወሎ መስተደደር ዞን ከፍ/ፍ/ቤትና እንዳሁም በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጡት ውሣኔዎች በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ.195/2/ለ/2/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/ጥ**

የሰ/መ/ቁ. 86845

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

**አመልካች፡-** የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ ዋልታንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሰለሞን ዩሐንስ ከጠበቃ ተስፋዬ አባተ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውም የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ሕግ ተጠሪን ጨምሮ በአምስት ሰዎች ላይ በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1(ሀ) እና 407(1)(ሀ)(ለ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በስልጣን ያላግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በማለት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ተጠሪው ጥፋተኛ ተብለው በሶስት አመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እና በብር 2000.00 (ሁለት ሺህ) እንዲቀጡ በተሰጠው ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፈዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ተጠሪን በወንጀል ተጠያቂ መደረጉን ተቀብሎ አድራጎታቸው የሚወድቀው ግን የስራ ግዴታን መጣስ በሚያስጠይቀው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(1) ድንጋጌ ነው በማለት ቅጣቱን በተመለከተ ደግሞ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው በመውጣት በአራት ወር ቀላል እስራት እና በብር 600.00 እንዲቀጡ አሻሽሎ በመወሰኑ ነው፡፡

አመልካች በተጠሪው ላይ ያቀረበው ክስ ዝርዝር ይዘት ተጠሪው የወ/ህ/ቁ 32(1(ሀ) እና 407(1(ሀ)(ለ)) በመተላለፍ በትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዩን ማህበር ምህንድሰና መምሪያ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ የተሰጣቸውን የስልጣን ችሎታ ከመጠን በላይ አሳልፈው በመገልገል ሕገ ወጥ ጥቅምን ለሳባ ኢንጂነሪንግ ለማስገኘትና በመንግስትና ሕዝብ ጥቅም ላይም ጉዳት ለማድረስ በማሰብ የትራንስፖርት እና ኮንስትራስክሽን ዲዛይን አክሲዩን ማህበር ለጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 002/97 በ29/10/2004 እ.ኤ.አ በአወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት አዲስ ሪግ ግዥ ተፈጽሞ እቃው በውለታውና በ"እስፔስፊኬሽኑ" መሰረት በትክክል ሳይቀርብ በኢንስፔክሽን ኮሚቴው በቀረበው ሪፖርት ላይ የሪጉ አካል ስለሆነው የውሃ ፓምፕ የተገለጸው በ"ስፔሲፊኬሽን"ና "ሰርቴፊኬት ኦፍ ኦርጂን" መሰረት እንዳልሆነ እና አሮጌ መሆኑ ተገልጾላቸው እያለ አዲስ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ርክክቡ እንዲፈፀም ሰኔ 02 ቀን 1998 ዓ/ም ለጂ.ኦ ቴክኒካል ምህንድስና ዋና ክፍል በጽሑፍ ትዕዛዝ በመስጠት እንዲሁም ከሣባ ኢንጂነሪግ ጋር ሚያዚያ 06 ቀን



www.chilot.me

1998 ዓ/ም በተደረገው ውይይት ተገዛ የተባለው ሪግ የውሃ ፓምፕ አሮጌ እና የማያገለግል መሆኑን በውይይት ጊዜ ተገልጾ እያለ የመስሪያ ቤቱን ጥቅም በሚጎዳ አኳኋን ስለውሃው ፓምፕ የተገለፀውን ጉዳይ ወደ ጎን በመተው በሌሎች አነስተኛ ጉዳዮች ላይ ብቻ ስምምነት በመፈሙና "አክሴፕታንስ ሰርተፊኬት" እንዲፃፍ በማድረጋቸውና ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ሁነው በሙሉ ፍላጎታቸውና እውቃታቸው በብር ከፍተኛ ወጪ የተገዛው ንብረት ለመንግስት ያላግባብ ገቢ እንዲሆን በማድረግ ጉዳት አድርሰዋል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ የቀረበባቸውን የወንጀል ክስ ክደው ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ዓቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰውና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ዓቃቤ ሕግ እንደክስ አቀራረቡ አስረድቷል በማለት ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን በመስጠቱ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃቸውን አቅርበዋል፡፡ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪን መከላከያ ማስረጃዎችን የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን የሚያስተባብሉ አይደሉም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎ ተጠሪን በቀረበባቸው የወንጀል ክስ ጥፋተኛ ናቸው በማለት በሶስት አመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እና በብር 2000.00 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በተጠሪ ላይ የተሰጠውን የጥፋተኛነት ውሳኔ ድንጋጌውን በመቀየር ያፀናው ሲሆን ቅጣትን በተመለከተ ግን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ መውጣት ተገቢ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ጠቅሶ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ በመውጣት በአራት ወር ቀላል እስራትና በብር 600.00 ተጠሪው እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት በአመልካች የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ ግራ ቀኙን በጽሑፍ እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት ክሱን መጀመሪያ በቀረበበት ፍ/ቤትና ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ፍ/ቤት የተሰጡ ውሣኔዎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ በሚከለተው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዋና ቅሬታ የተጠሪ አድራጎት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ))እና በአንቀጽ 4107(1(ሀ)(ለ) ስር የሚሸፈን ነው፣ይህ ቢታለፍ እንኳን አድራጎቱ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 411 ስር የሚወድቅ እንጂ እንደይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ድምዳሜ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420 ስር የሚሸፈን አይደለም፣ከተጠሪ ጋር የተከሰሱት ግለሰቦችም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባሉትና የተቀጡት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 411 ስር ነው፣ተጠሪ በውሉ አግባብ ያልቀረበ መሆኑን በኢንሲፔክሽን ኮሚቴ ተረጋግጦና ይህንኑ እያወቁ በጻፉት የአክሴፕታንስ ሰርቲፊኬት በመንስግስት ላይ ጉዳት መደረሱ ተረጋግጦ እያለ አድራጎታቸው የሙያ ግዴታ በመጣስ የሚሸፈን ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው፣እንዲሁም ተጠሪው ለግዥው ስፔሲፊኬሽን ሲሰራ ያልነበሩ መሆኑ ተጠያቂ የሆኑት ከግዥው በኋላ ለነበረው ሂደት በመሆኑና ከሌሎች የማኔጅመንት አባለት ጋር ሁነው የግዥ ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ማድረጋቸውም የተጠሪ ጥረት ምን እንደሆነ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት እና ወንጀሉ ውጤቱን ከአገኘ በኋላ በሌላ ሰው በተፈፀመ የፍትሃ ብሄር ክስና ክርክር መነሻ ሁኖ በመሆኑ አንቀፁን ለመለወጥ የማያስችሉ ምክንያቶች ናቸው፣ተጠሪው የአደገኛነት ባህርይ ያላቸው ናቸው የሚል ነው፡፡ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካች የሰበር ቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑንና ጥፋተኛ የተባሉትም የወንጀል መስራት ሀሳብ ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ መሆኑን ዘርዝረው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከትነውም ከዚሁ ከቀረበው አቤቱታ አንፃር ነው። ይህ ችሎት በዋናነት መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ተፈፅሟል ሲባል ብቻ ውሣኔዎችን የሚመለከት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ለውሣኔዎቻቸው መሠረት ያደረጉዋቸውን ፍሬ ነገሮች ትክክለኛነት ወደማጣራት ወይም ግራ ቀኙ ያቀረቡዋቸውን ማስረጃዎች ወደ መመዘን አልሄደም፣ይልቁንም እነዚህን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዳሉ በመውሰድ የተረጋገጠው ፍሬነገር በተጠሪ የቀረበውን ክሱ የሚያቋቁም መሆን አለመሆን የሚመለከተውን የሕግ ነጥብ ተመልክቷል።

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት እንደቻልነው ተጠሪ የትራንስፖርትና የኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማህበር የምህንድስና ኃላፊ ሁነው ሲሰሩ አከራካሪውን ሪግ ከውሉ ውጪ የቀረበ ስለመሆኑ በሚመለከተው ኮሚቴ ተረጋግጦ እያለና ተገቢ ያልሆነ ቃል ጉባኤ ከሌሎች የማኔጅመንት ኮሚቴ አባለት ጋር ሁነው ይዘው የርክክብ ደብዳቤ በመጻፍ ለአቅራቢው ክፍያው እንዲፈፀም አድርገው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 407(1(ሀ)(ለ) በሚዛረር ሁኔታ በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል የሚል ነው።

በፍርዱ ሂደት ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሪጉ በውሉ በተመለከተው ስፔሲፊኬሽን መሰረት ያልመቅረቡንና ተጠሪም ሆነ ሌሎች አብሯቸው የተከሰሱት የድርጅቱ ኃላፊዎች እውቀት የነበራቸው መሆኑ በማስረጃ ማረጋገጡን የገለፀ ሲሆን በዚህ ረገድ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የተለየ ድምዳሜ የሌለው መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል።የርክክብ ደብዳቤ ሊፃፍ የቻለው መሰረታዊ ምክንያትም ይሄው በማሽኑ ላይ ያለው ችግር ታውቆ አቅራቢው ድርጅት ችግሩን እንዲያስተካክል የድርጅቱ ተወካይ ባለበት ውይይት ተደርጎ በአስራ አምስት ወራት ውስጥ ችግሩን እንደሚያስተካከል ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኂላ ስለመሆኑም በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል።ይህ ችሎትም ይህ የተጠሪ አድራጎት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተጠቀሰው ድንጋጌ መስፈርት ጋር በማያያዝ ትክክል መሆን አለመሆኑን ተመልክቷል። ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ እቃው እንደውሉ የሚቆፍር መሆኑ ተፈትሾ እና ተረጋገጦ ርክክብ ይፈፀም የሚል ሀሳብ በማኔጅመንቱ ስብሰባ ሲያቀርቡ የሳባ ኢንጀነሪግ ተወካይ አቅራቢው ድርጅት የማስሞከር ግዴታ እንዴለለበት በመግለፃቸው በዋስትናው ጊዜ አስራ አምስት ወራት ውስጥ ጉድለት ካለ አስተካክላለሁ በማለታቸው የእቃው ርክክብ እንዲፈፀምና የአክሴፕታንስ ሰርቲፊኬት ለመስጠት ስምምነት ተደርሶ ተጠሪውም ስምምነቱ ላይ መድረሳቸው፣ተጠሪ ከሚመሩት የዲዛይን መመሪያ በ14/11/1998 ዓ/ም በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ ማሽኑ አዲስነቱ ተረጋግጧል፣ገቢ ይሁን ተብሎ በመፃፉ የመልካም አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ (Perfomance bond) ለአቅራቢው ድርጅት ከተለቀቀለት በኂላ ሪጉ ሲፈተሽ በውሉ የተገለጸውን የ158 ሜትር ጥልቀት እንደማይቆፍር በፍሬ ነገረ ደረጃ መረጋገጡን ነው።

እነዚህ ፍሬ ነገሮች በግልጽ የሚያሳዩት ተጠሪ የሪጉን አዲስነት ከማረጋገጥ ጀምሮ የአስራ አምስት ወራት የዋስትና ጊዜ ውስጥ ጉድለቱ እንዲስተካከል የአቅራቢው ድርጅት ተወካይ ያቀረበው ሃሳብ ተጠሪው ጭምር ተሳታፊ በሆኑበት ኮሚቴ ተቀባይነት አግኝቶ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ ለአቅራቢው እንዲለቀቅ የሚያደርግ ተግባር እስከተፈፀመባቸው ሂደቶች ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው።እነዚህ ፍሬ ነገሮች ተጠሪው የመወሰን ስልጠን የነበራቸው መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው።የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 420 ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው የመወሰን ሥልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ባለቸው ሰዎች ነው።እነዚህ ሰዎች በአንቀጽ 407 አግባብ የሚጠየቁት ግልፅ በሆነ ሁኔታ አንድን ሰው ለመጥቀም ወይም ራሳቸውን ለመጥቀም በማሰብና ኃላፊዎቻቸውን ለማሣሣት የፈፀሙት ጉልህ ተግባር መኖሩ ሲረጋገጥ ነው።ይህ እስካልተረጋገጠ ድረስ በሥልጣን

አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው ሊጠየቁ አይገባም። ስለሆነም በአንቀጽ 420 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ተጠሪው የሙያ ተግባሩንና ሥራው በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈፀሙ ምክንያት በመንግስት ላይ ጉዳት አድርሰዋል ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ የለም።የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤተ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም።

የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈንበት ድንጋጌ ስንመለከትም አመልካች በአንቀጽ 407 ስር ሊሆን በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኘው ሁኖ አልተገኘም።ምክንያቱም ከተጠሪ ጋር የተከሰሱት ግለሰቦች በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 76525 እና 76941 በሆኑት ታይቶ አድራጎታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ) እና 411(1(ሀ)(ለ) ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑና ውሳኔዎቹ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ለሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርብም መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በመ/ቁጥር 86844 እና 86846 በሆኑ መዛግብት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ በመሆኑ  ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 4፣41 እንዲሁም ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25 ድንጋጌዎች አኳያ በሕግ ፊት እኩል ሁኖ የመታየት መብት አንፃርም ሆነ የወንጀል አድራጎቱን የበለጠ የሚሸፈነው ድንጋጌ አንቀጽ 407 ሳይሆን 411(1(ሀ)(ለ) ሁኖ ተገኝቷልና።

በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 411 ሥር ወንጀል የሚያቋቁሙት ድንጋጌዎች የሚገኙት በንኡስ አንቀፅ (1) (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ነው። ማንኛውም በዚህ አንቀፅ ሥር የተከሰሰ ሰው በዚህ አንቀፅ ሥር ከተመለከቱት ውስጥ የትኛውን ወንጀል እንደፈፀመ በግልፅ በሚያመለክት ሁኔታ ክስ ሊቀርብበትና ሊከላከል ይገባል።ተጠሪ የዲዛይን መምሪያ ኃላፊ ሁነው የሪጉን አዲስነት ተረጋግጧል በማለት ማስረጃ እንዲቀርብ ማድረጋቸውም ሆነ የዋስትናውን ጊዜ በተመለከተ በአቅራቢው ድርጅት ግዴታ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ተሳትፈው ከውሉ ውጪ በሆነ ሁኔታ ስምምነት ላይ መደረሳቸው ሲታይ የመንግስት ሥራን በማይመች አኳኋን መምራታቸውን የሚያሳይ ነው።

ከላይ ከተገለጹትና በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ያለውና ሊጠቀስ ይገባ የነበረው አንቀፅ 411(ሐ) መሆኑን ተገንዝበናል። በዚህ አንቀፅ መሠረት የወንጀል ተጠያቂነት የሚከተለው ደግሞ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፣ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ተጠቅሞ በጠቅላላው በሥራው ሥልጣን መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የሕዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጐዳ ተግባር በማናቸው ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ" ነው።

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 411 አንድን ሰው ጥፋተኛ የሚያደርገው በሕጉ የተቀመጡት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ነው።ክሱ ላይ እንደተገለፀው አንዱ መሟላት ያለበት መስፈርት በዚሁ አንቀፅ የተከሰሰው ሰው የማይገባ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ለሦስተኛ ወገን ለማስገኘት መንቀሳቀሱ ነው። አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ሪጉ አዲስ ነው በማለት ርክክቡ እንዲፈፀም የአክሴፐታንስ ሰርቲፊኬት መፃፋቸው ጥፋት ነው የተባለ ሲሆን የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብም በዚህ ደብዳቤ መነሻ ለአቅራቢው ድርጅት መከፈሉ ተረጋግጧል።ይህ ደግሞ በስራቸው ሥልጣን መሠረት በአደራ የተሰጣቸውን ወይም ሊጠብቁትና ሊከላከሉት የሚገባውን የሕዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጐዳ ተግባር መፈፀማቸውን የሚያሳይ ነው።በመሆኑም ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በአንቀጽ 411(1(ሐ)) ስር ሆኖ ስለአገኘነው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2))  እና

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2/ መሠረት በመለወጥ ተጠሪ በወንጀል ህግ አንቀፅ 411(1(ሐ)) ስር የተመከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

የቅጣቱን መጠን በተመለከተ በሌሎች የተጠሪ ግብረአበሮች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅጣት ሲወስን ወንጀሉ ከውል አፈፃጸም ጋር ተያይዞ የተፈጸመ መሆኑንና ውሉም እንዲፈርስ የተደረገ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በቅጣት አወሰሳን መመሪያው አንቀፅ 13(2) መሰረት ሊጣል የሚገባው ዝቅተኛ የወንጀል ደረጃውን ያገናዘበ ቀላል  እስራት ቅጣት ሊሆን እንደሚገባ፣በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 13(3) መሰረት የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ያለውን ቅጣት ርዝመት ለአራት እኩል ተካፍሎ የሚመጣው ዝቅተኛ ወንጀል ደረጃ የቅጣት ፈቅድ ስልጣን ከአንድ አመት እስከ አንድ አመት ስድስት ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን፣ይህም ፍቅድ ስልጣን በቅጣት አወሰሳን መመሪያ አባሪ አንድ ከእርከን 7 ስር የሚሸፈን መሆኑን ግንዘቤ ውስጥ አስገብቶ እያንዳንዱ አጥፊ በግል ያቀረበውንና ሕጋዊ የቅጣት ማቅላያ ምክንያት በመቀበል ተገቢ ነው ያለውን እስከ ስድስት ወር ቀላል እስራት እና ብር 1000.00 የገንዘብ መቀጮ ቅጣት ያስተላለፈ በመሆኑ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረታዊ አላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በተጠሪ ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠንም ከላይ በግብረ አበሮቹ ላይ ቅጣት ሲወሰን ተፈፃሚ የሆነውን አካሄድ ሊከ,ተል የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በቀላል እስራት በመሆኑና ቀላል እስራት ደግሞ ከአስር ቀን እስከ ሶስት አመት ሚደርስ ስለሆነ በመመሪያው አንቀጽ 13(3) መሰረት መነሻና መድረሻው መካከል ያለውን ቅጣት ርዝመት ለአራት እኩል ተካፍሎ የሚመጣው ዝቅተኛ ወንጀል ደረጃ ቅጣት ፍቅድ ስልጣን ከአንድ አመት እስከ አንድ አመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡በዚህ ፍቅድ ስልጣን ያለው ቅጣት በመመሪያው አባሪ አንድ እርከን ሰባት ስር የሚሸፈን ነው፡፡በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን ተጠሪ ሪኮርድ የሌለባቸው፣የቤተሰብ አስተዳደሪ እና የዲስክ መንሸራተት በሽታ ያለባቸው መሆኑ በፌዴራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በቅጣት ማቅላያነት የተያዙ ምክንያቶች ስለሆኑ ይህ ችሎትም የሚቀበላቸው በመሆኑ ሶስቱ የቅጣት ማቅላያ ምክንያቶች ሲያዙ እርከኑ ወደ እርከን አራት ይወረዳል፡፡በዚህ እርከን የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከአራት ወር እስከ ሰባት ወር እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በስድስት ወር ቀላል እስራት ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሠረት የበታች ፍርድ ቤቶችን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በማሻሻል ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ሲጠቃለልም የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በአቃቤ የሕግ ማመልከቻ በተጠቀሰው ድንጋጌ ወይም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተጠቀሰው ድንጋጌ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 411(1(ሐ)) ድንጋጌ በመሆኑና ቅጣቱም ከዚህ ድንጋጌ አንጻር የሚጣል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አሻሽለናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡

## **ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57547 ታህሳስ 11 እና 26 ቀን 2004 ዓ/ም፣በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 77102 ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ/ም የተሻሻለው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ)) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ) እና 411(1(ሐ)) ድንጋጌ ስር ነው ብለናል፡፡ቅጣቱን በተመለተከተም ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በስድስት ወር ቀላል እስራትና በብር 1000.00 ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በዚህ ችሎት እንዲቀጡ ከተወሰነባቸው የእስራት ጊዜ በላይ በጉዳዩ ላይ የታሰሩ መሆኑ ስለተረጋገጠ የእስራት ዋራንት እንዲጻፍ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፣የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ ግን ተጠሪ ያልከፈሉትን ቀሪ ገንዘብ ካለ አመልካች ተከታተትሎ ገቢ እንዲያስደርግ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 81178

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** የኢዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ - ዐ/ሕግ ሜቴ አቶምሳ እና አሰፋ ሐፎስ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ከበደ ተሰራ - ጠበቃ ተስፋዬ ኃ/ማርያም እና ወ/ሮ መሰረት ስዩም ቀረቡ

2. አቶ ሌንጫ ዘገየ - ሌንጫ ዘገየ

አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ቁጥሩ 81178 በሆነው በዚህ መዝገብ፣በ2ኛተጠሪ ላይ ደግሞ ቁጥሩ 81179 በሆነው መዝገብ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ ተጣምሮና ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ተጠሪዎቹ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በተናጠል በተለያየ መዝገብ ተከሰው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠባቸው የወንጀል ክሶች መካከል ሁለቱንም ተጠሪዎች በ1ኛ ክስ ከተመለከተው ወንጀል በነፃ በማሰናበት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አመልካች በተጠሪዎቹ ላይ በተለያዩ መዝገቦች ያቀረባቸውን የተለያዩ የወንጀል ክሶች የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ፤

በ1ኛ ተጠሪ ላይ በአምስት ክሶች የጥፋተኝነት እና በድምሩ የሃያ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ከብር 165,000 መቀጮ ጋር፤ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በአምስት ክሶች የጥፋተኝነት እና በድምሩ የአስራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ከብር 100,000 መቀጮ ጋር፤ ውሳኔ መስጠቱን፣በውሳኔው ቅር በመሰኘት ሁለቱ ወገኖች ያቀረቡለትን ይግባኝ የመረመረው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን ይግባኝ በተመለከተ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁለቱንም ተጠሪዎች ከ1ኛ የወንጀል ክስ በአብላጫ በነጻ በማሰናበት እና በሌሎች የወንጀል ክሶች ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን ቅሬታ በሙሉ ድምጽ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱን፤አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ በተመለከተም የተጠሪዎቹ የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ በተደረገባቸው የወንጀል ክሶች በተጠሪዎቹ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተጥሎ የነበረውን የቅጣት መጠን ከፍ በማድረግ በ1ኛ ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት በአምስት የወንጀል ክሶች ተጥሎ በነበረው የሃያ አመት ጽኑ እስራት ምትክ በይግባኝ ደረጃ የጥፋተኝነት ውሳኔው በጸናባቸው አራት የወንጀል ክሶች የ25 ዓመት ጽኑ እስራት፤በ2ኛው ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት በአምስት የወንጀል ክሶች ተጥሎ በነበረው የ13 ዓመት ጽኑ እስራት ምትክ በይግባኝ ደረጃ የጥፋተኝነት ውሳኔው በጸናባቸው አራት የወንጀል ክሶች የ20 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት በመጣል ውሳኔ መስጠቱን፤በ2ኛ ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተጣለው



www.chilot.me

የመቀጮ መጠን በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያልተለወጠ ሲሆን በ1ኛ ተጠሪ ላይ ተጥሎ የነበረው የብር 165,000 መቀጮ ወደ ብር 300,000 ከፍ መደረጉንና እና በንብረት ውርስ ረገድም አንዳንድ ማሻሻያዎች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መካተታቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ከላይ እንደተገለጸው በተጠሪዎቹ ላይ በ1ኛ ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመሰረዝ ተጠሪዎቹ በእነዚህ የወንጀል ክሶች ረገድ በነጻ እንዲሰናበቱ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አመልካች በሶስት መዝገቦች ያቀረበው አቤቱታ ቁጥሩ 81117 በሆነው መዝገብ ተጣምሮ ከታየ በኃላ ተጠሪዎቹ ብድርን እንደመደበኛ ስራቸው በማድረግ በተደጋጋሚ ጊዜ ቼኮችን፣የቦታ ካርታን፣የንግድ ፍቃድን እና የመኪና ሊብሬን መያዣ በማድረግ ለተለያዩ ሰዎች በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በብድር ይሰጡ እንደነበር ከፍተኛ ፍ/ቤት በማስረጃ አረጋግጦ የጥፋተኝነት ውሳኔ በሰጠበት ሁኔታ ተጠሪዎቹ ብድር መስጠትን እንደመደበኛ ስራ በማድረግ ተደጋጋሚ ብድር መስጠታቸውም ሆነ ብድሩን የሰጡት በተደጋጋሚና በከፍተኛ መጠን መሆኑ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አነጋገር አንፃር የባንኮችንና የሌሎች የገንዘብ ተቋማትን ስራ ያለ ፍቃድ ሰርተዋል ለማለት የማይቻል በመሆኑ ድርጊቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 61 መሰረት በአራጣ ወንጀል ክስ ስር ተጠቃሎ የሚታይ ነው በማለት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የመሰረዙን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለመመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎቹ በተያዘላቸው ቀጠሮ መልስ ባለማቅረባቸው መብታቸው ከታለፈ በኃላ 1ኛ ተጠሪ በተያዘላቸው ቀጠሮ መልስ ያላቀረቡበትን ምክንያት ገልጸው በተፈቀደላቸው መሰረት በጠበቆቻቸው የተዘጋጀና የተፈረመ መልስ በማያያዝ የክርክሩ ተካፋይ ሆነዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የተጠሪዎቹን ይግባኝ በከፊል በመቀበል በፌ/ከ/ፍ/ቤት ከተሰጠው ውሳኔ ውስጥ በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ ተጠሪዎቹ ከእነዚህ ክሶች በነጻ እንዲሰናበቱ በድምጽ ብልጫ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በተጠሪዎቹ ላይ ቀርቦ የነበረው 1ኛ ክስ ተመሳሳይ ድንጋጌ የተጠቀሰበት ሆኖ ይዘቱ በጥቅል ሲታይ ተጠሪዎቹ በገንዘብና በባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሸ) እና 2 (ሀ)ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የብድር ስራ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ከብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፍቃድ ሳይኖራቸው ለተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ በብድር በመስጠትና ለብድሮቹም ቼኮችንና የተለያዩ ሰነዶችን በመያዣነት በመቀበል ለባንኮችና ለመሰል ፋይናንስና አክሲዮን ማህበራት የተፈቀደውን የባንክ ስራ በህገወጥ መንገድ እንደንግድ ስራ በተደጋጋሚ የመስራት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን ወንጀሉን ፈጽመዋል የተባሉትም 1ኛ ተጠሪ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ አምስት ጊዜ ለአንድ ድርጅት በድምሩ ብር 12,090,000 ፤2ኛ ተጠሪ በአስር ዓመታት ውስጥ በ25 የውል ሰነዶች ለ11 ተበዳሪዎች በድምሩ ብር 3,711,111 በብድር በመስጠት መሆኑን የክሶቹ ዝርዝር ያመለክታል፡፡ሁለቱ ተጠሪዎች በየቀረበባቸው 1ኛ ክስ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን፣በየክሶቹ በተመለከተው የጊዜ ወሰን፣የድግግሞሽ መጠን እና ሁኔታ በየክሶቹ ለተጠቀሱት ግለሰቦችና ድርጅቶች በብድር መስጠታቸውን ክሱ የቀረበለት ፌ/ከ/ፍ/ቤት በማስረጃ አጣርቶ ያረጋገጠ ሲሆን በክሶቹ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠባቸውም ተጠሪዎቹ ከሳሽ ወገን ያስረዳባቸውን ፍሬ ነገሮች በመከላከያቸው አላስተባበሉም

በማለት ነው፡፡በክሶቹ የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር በተጠሪዎቹ መፈጸሙ በማስረጃ ተጣርቶ ተረጋግጦአል መባሉ በመሰረቱ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔውን በሰጠው አብላጫ ድምጽም ቢሆን አልተነቀፈም፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ግዙፋዊ ፍሬነገሩ ተረጋግጦአል መባሉን ተቀብሎ ነገር ግን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔውን በአብላጫ ድምጽ ለመሰረዝ የሰጠው ዓይነተኛ ምክንያት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በቀረበው 1ኛ ክስ ማንኛውም ሰው "...በማናቸውም ሌላ አኳኃን የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ ወንጀል የተሰራበት እንደሆነ ወንጀል የተሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀለኛ ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡" የሚል አነጋገር እና "ወንጀሉ የተፈጸመው ሥልጣንን መከታ በማድረግ ወይም በመንግስት ስራ አጋጣሚ ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትን ለማካበት ወይም በተደጋጋሚ ሲሆን ወንጀል የተሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 20,000 የማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡" የሚል አነጋገር ያዘሉት የአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሸ) እና (2)(ሀ) ድንጋጌዎች በተደጋጋሚ፣ለንግድ መጠን እና ለበርካታ ተበዳሪዎችም ቢሆን በግለሰብ ደረጃ ብድር የመስጠት ስራ የተከለከለ ወይም የሚያስቀጣ የወንጀል ተግባር መሆኑንና እና ብድር የመስጠት ስራ ሊከናወን የሚችለው በባንክ ብቻ መሆኑን በግልጽ እንደማይደነግጉ፣ፍ/ቤቶች ሕግን ከመተርጎም የማይታገዱ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገወጥነቱ በሕግ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደ ወንጀል ሊቆጥሩትና ቅጣት ሊወስኑበት እንደማይችሉ፣በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሳል በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደ ወንጀል ሊቆጥሩት እንደማይችሉ በወንጀል ህግ በአንቀጽ 2 ስር የተደነገገ በመሆኑ ወንጀልነቱ በግልጽ ባልተደነገገ ድርጊት በተጠሪዎቹ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መተላለፉ መሰረታዊ የሆነውን የህጋዊነት መርህ የሚጻረር ነው የሚል መሆኑን የውሳኔው አጠቃላይ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

እንደተባለው በከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለቱ ተጠሪዎች በ1ኛ ክስ ጥፋተኛ ተብለውበት የነበረው የገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሸ) እና (2)(ሀ) ድንጋጌዎች ይዘቱ ቀደም ሲል የተገለጸውንና በተጠሪዎቹ መፈጸሙ የተረጋገጠውን ግዙፋዊ ፍሬነገር በወንጀልነት የሚፈርጁ ወይም የሚደነግጉ አለመሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት አብላጫ ድምጽ የሰጠውን ሰፊ ትችት እና የደረሰበትን ድምዳሜ በበኩላችን ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የወንጀል ሕግ በተወሰኑ ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ ህጉ ደንግጎ ሲገኝ ግምት የሚወስድባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በመሰረታዊነት ግን የአንድ ድርጊት ወይም ግድፈት ወንጀልነት በሕጉ በግልጽ ተደንግጎ መገኘት የሚገባው መሆኑ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 በተመሳሳይ ሁኔታ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለድርጊቱ እና ስላፈጻጸሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 112 የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ የድርጊቱ ወይም የግድፈቱ ወንጀልነት በሕጉ በግልጽ ያልተደነገገ በሆነ ጊዜ ወንጀልን ለማቋቋም ከሚያስፈልጉት ፍሬ ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው ሕጋዊ ፍሬ ነገር የተጓደለ ስለሚሆን ከወ.ሕ.አ. 23(2) መሰረታዊ ድንጋጌ አንጻር ወንጀል ተፈጽሞአል ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የወንጀል ሕግን መሰረታዊ መርሆዎች መሰረት በማድረግ በተጠሪዎቹ በቀረበለት ይግባኝ መነሻ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ በዚህ ረገድ ተጠሪዎችን በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪን አስመልክቶ በመ.ቁ. 59831 በ03/08/2004 ዓ.ም.፣2ኛ ተጠሪን አስመልክቶ በመ.ቁ. 55859 በ01/08/2004 ዓ.ም. ከሰጠው ውሳኔ ውስጥ በተጠሪዎቹ ይግባኝ መነሻ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በመ.ቁ. 82321 በ09/09/2002 ዓ.ም.፤በ2ኛ ተጠሪ ላይ ደግሞ በመ.ቁ. 82644 በ16/06/2002 ዓ.ም. በአንደኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ በዚህ ረገድ ተጠሪዎቹን በማሰናበት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቶአል፡፡
2. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ክርክሩ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ከተወሰነው መ.ቁ. 81179 ጋር እንዲያያዝ ይደረግ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 90089

ጥቅምት 20ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዘኒት አባቡ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ዐ/ህግ በሌለበት ታየ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጧል፤**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረውም በቤ/ጉ/ክ/መንግስት አሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡ የቀረበው ክስም አመልካቿ የወ/ህ/ቁ27/1/ 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በባሞበሲ ወረዳ ባሞበስ ከተማ 02 ቀበሌ ጥቅምት 14 ቀን 2004 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 1፡00 ሰዓት አካባቢ የግል ተበዳይ ጠይባ መሐመድ መኖሪያ ቤት አካባቢ የግል ተበዳይ በሆድዋ ላይ በመምታት ሆድዋ ውስጥ የነበረው ፅንስ ቦታውን እንዲለቅና የመውለጃ ቀን ያልደረሰ ፅንስ በሆድዋ ውስጥ እንዲሞት በማድረግ የምጥ አመጣጥና ከ4 እስከ 5 ከወሊድ በኃላም የደም መርጋትና የደም መፍሰስ እንዲፈጠር በማድረግ በፈፀመችው የመግደል ሙከራ ወንጀል ተከሳለች የሚል ሲሆን አመልችም ፍርድ ቤት ቀርባ የዕምነት ክደት ቃሏን ስትጠየቅ የወንጀሉን ያልፈፀመች መሆኑን ክዳ ቃልዋን ሰጥታለች ቀጥሎም ፍ/ቤቱ በግራ ቀኙ በኩል የተቆጠሩትን ምስክሮች አስቀርቦ ከሰማ እና ጉዳዩንም ከመረመረ በኃላ ድርጊቱ ተፈፅሟል በተባለበት ጊዜ ማለትም ከጥቅምት 9 አስከ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ አመልካች ዕቃዋን ለመውሰድ ሱዳን ሀገር ልዩ ቦታው ኩርሙክ ተብሎ የሚጠራ ቦታ ሄዳ እዚያ የነበረች እና በቦታው አለመኖሯ በመከላከያ ማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ በሌላ በኩልም አመልካች እንደተባለው በእርግጥም በወቀቱ በቦታው ብትኖርና ጉዳቱን የፈፀመች ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ ወዲያውኑ ለፖሊስ ሪፖርት በተደረገ እና አመልካችም ሳትቆይ ወዲያውኑ ቁጥጥር ስር በዋለች ነበር በማለት አመልካቿ ድርጊቱን አለመፈፀሟን በበቂና አሳማኝ ሁኔታ ተከላክላለች በማለት በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 149(2) መሠረት ከክሱ በነጻ እንድትሰናት በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ሰጧል፡፡

የአሁን ተጠሪም (የስር ከሳሽ) በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረቡና ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ በጉዳዩ ላይ እንዲከራከሩ ካደረገ በኃላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች በክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ የ8ወር እርጉዝ የነበሩትን የግል ተበዳይ በክንዷ ሆዷን እንደመታቻት የግል ተበዳይም ወዲያውኑ በዚሁ ምክንያት ህመም እንደተሰማና ፅንሱም መላወሱን እንዳቆመ በኃላም የግል ተበዳይዋ ወደ ሀኪም ቤት ተወስደው ሲታዩ ሽሉ ሞቶ በመገኘቱ በህክምና መሳሪያ እንዲወጣ መደረጉንና ሆኖም

ግን የግል ተበዳይ በዚሁ ጉዳት ምክንያት የታመቀና የረጋ ደም መፍሰስ ያጋጠማት ስለመሆኑ የግል ተበዳይ ጨምሮ በዐ/ህግ በኩል ቀርበው በበታች ፍ/ቤት በተሰሙት ምስክሮች ቃል እና ህክምና ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ገልጾ በአንፃር ግን በአመልካች በኩል የተሰሙት መከላከያ ምስክሮች ቃል በተለይም አመልካቿ በተጠቀሰው ጊዜ ኩርሙክ ቦታ ሄዳ እዚያ የነበረች ስለመሆኑ በምን አግባብ ሊያውቁ እንደተቻሉ በሚመለከት የአንዱ ምስክር ቃል ከሌላው የሚጣረስ በመሆኑና በዚህም ምክንያት ክብደት እንደማይሰጠውና ተዓማኒነት የሌለው መሆኑ እየታወቀ የበታች ፍ/ቤት ተከሳሽዋ ወንጀሉን ተከላክላለች በማለት በነፃ እንዲሰናበቱ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢነት የሌለውና ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከሳሿ ክሱ በቀረበበት የህጉ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ሊባል ይገባል በማለት የጥፋተኝነትም  የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ከህጉ ጋርም አገናዝቦ መመልከቱን ከገለፁ በኃላ በ3 ዓመት ከ 7 ወር ፅኑ እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስኗል የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎትም ጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለውም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበል አልፏል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በጥቅሉ ጥፋተኛ የተባልኩበትን ድርጊት አለመፈፀሜና በመከላከያ ማስረጃ በሚገባ በማረጋገጥ የተከላከልኩ ስለመሆኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመርምሮ የተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ተሽሮ ጥፋተኛ ተብዬ መቀጣቴና እንዲሁም ይኼውም ክልሉ ሰበር ችሎትም መፅናቱ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳው ሊሻርልኝ ይህ የሚታፍ ከሆነም አባት የሌላቸው ልጆች የማሳድግ መሆኔንና የመሳሰሉት ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ ሳይፈፀም በገደብ ታግዶ እንዲቆይ አሊያም እንዲቀነስልኝ የሚል ነው አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለሰበር ክርክር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ምክንያት ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ በጽሑፍ እንዲሰጥ መጥሪያ እንዲደርሰው የተደረገ ቢሆንም ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር አቤቱታ በቀረበት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል  ላለት ይቻላል ? ወይ ወይስ አይቻለም የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ የግራ ቀኙን ምስክሮች ስምቶና ጉዳዩንም መርምሮ የሥር ተከሳሻ ወንጀሉን ተከላክላለች በሚል ምክንያት በነፃ እንዲሰናበት በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በአሁን ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ካደረገ በኃላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች በመካከላቸው የነበረውን ጥል መነሻ በማድግ የ8 ወር እርጉዝ የሆነችውን የግል ተበዳይ  ጠይባ መሐመድን በሆድዋ ላይ በክንዷ መትታ ጉዳት ያደረሰችባት መሆኑ የግል ተበዳይዋም በዚሁ ምክንያት ከተመታችበት ቦታ ሳትንቀሳቀስ ብርቱ ህመም እንደተሰማትና ፅንሱም መላወሱን ማቆሙን ከዚያም ሀኪም ቤት ተወስዳ በባለሙያ ምርም ሲደረግላት ፅንሱን ሞቶ በመገኘቱ ምክንያት በህክምና መሳሪያ እንዲወጣ መደረጉንና ከግል ተበዳይዋም ብዙ የረጋና የታመቀ ደም በመፍሰሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባት ስለመሆኑ በምስክሮች ቃልና ህክምና ማስረጃ መረጋገጡን የገለፀ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ በስር ተከሳሽ በኩል የተሰሙት የመከላከያ ምስክሮች ቃል አንዱ ከሌላው ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ተአማኒነት የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመለወጥ በአመልካች የጥፋተኝነት ውሳኔ

ካስተላለፈ በኃላ በ3 ዓመት ከ7 ወር ፅኑ እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ቅጣት ጥሏል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት ክል ሰበር ችሎትም ውሳኔው ስህተት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

እንግዲህ እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ወንጀሉን ሊያስተባሉ አልቻም ሚል ድምዳሜ የጥፋተኝነት ውሳኔውን ሊሰጥ የቻለው በህግ የተሰጠውን የማስረጃ ምዘና ተግባሩን መነሻ በማድረግ መሆኑን ከውሳኔው ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ተጠቅሞ ያረጋጠውን ፍሬ ነገር ይህ ችሎትም እንዳለ የሚቀበለው ጉዳይ ይሆናል እንጂ በዚህ ረገድ የሚቀርበውን ክርክር ችሎቱ ለማት በህግ ስልጣን አልተሰጠውም፡፡

በሌላ በኩል እነዚህን በይገባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች መነሻ በማድግ በህግ አተገባበር ረገድ በበታች ፍ/ቤቱ ውሳኔ ላይ የተፈጠረ ስህተት መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ስንመለከተው ደግሞ አመልካች የ8ወር እርጉዝ በቀጥታ በሆዷ ላይ የመታችሁ ከመሆኑ አኳያ ድርጊቱ በወ/ህ/ቁ581/ለ)፤ 27(1) 540 ስር የተመለከተውን የግድያ ሙከራ የሚያቋቁም በመሆኑ በዚህ ረገድ በጥፋተኝቱ ውሳኔ ላይ የተፈጠረ ስህተት አላገኘንም፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የቀረበው የሰበር አቤቱታም ቢሆን ቅጣቱ በወ/ህ/ቁ192 መሠረት ሳይፈፀም ታግዶ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስች ምክንያቶች ተሟልተው ባልተገኙበት ሁኔታ ቅጣቱን ማገድ የማይችል ሲሆን መጠኑን በተመለከተም ከደረሰው ጉዳትና ወንጀሉ ክብደት አኳያ በስር ፍ/ቤት የተጣለው ቅጣት ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የቤ/ጉሙዝ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ03748 በ24/7/2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁጥር 04446 በ17/8/2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቷል፡፡

2. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የፀና መሆኑን አመልካች በሚገኙበት ማረሚያ ቤት በኩል ይገለፅላቸው ፡፡ ይፃፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለ

የሰ/መ/ቁ. 93741

ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች:-** አቶ አብነት ዋቆ ብሩ - ጠበቆች መሃመድ አሚን እና ጫንያለው እሸቱ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በጂማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም:- አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) ስር የተመለከተውን በተመላለፍ በሾፌርነቱ ሙያቸው የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ/ም ከጠዋቱ 12:30 ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-28157 ኦሮ የሆነውን ሚኒባስ መኪና እያሽከረከረ ከጅማ ከተማ ወደ አጋሮ ከተማ ሕዝብ ጭኖ በማሽከርከር ላይ እያሉ መንገዱን ለቅቆ ከእንጨት ጋር አጋጭቶ በመገልበጥ የተሽከርካሪው ረዳት የሆነው አብዲ ዋቆ የገደላቸው በመሆኑ በፈፀሙት በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም የክስ ማመልከቻው ደርሷቸው ክሱን እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ዳኛ በመሆናቸው ያለመከሰስ መብት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው በክሱ ላይ ተቃውሞ እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አቃቤ ሕጉ አመልካቹ ድርጊቱን እንደፈፀሙ ወዲያውኑ የተያዙ መሆናቸውን ገልፀው ያለመከሰስ መብታቸው ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡትን አስተያየት በመቀበል የክስ ተቃውሞውን ያለፈው ሲሆን የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን የክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ አቃቤ ህግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸውና ሟች በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ሕይወታቸው ያለፈ መሆኑን አቃቤ ህግ በማስረጃዎቹ ያስረዳባቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ታምኖበት ይህንኑ እንዲያስተባብሉ እድል ተሰጥቶ አመልካች አደጋው የደረሰው በድንገተኛ አደጋ አጋጣሚ መሆኑን የሚያሳይ ጭብጥ አስይዘው የመከላከያ ማስረጃ ያሰሙ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎቹ የዐቃቤ ህግ ማስረጃዎቹን ያላስተባበሉ መሆኑን በመጥቀስ አመልካችን በአቃቤ ህግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጓቸዋል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት በመቀበልና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ በአንድ አመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት እና በብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን የሰበር አቤቱታቸውን

እንደየቅደም ተከተላቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም ቅሬታቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ቁጥር 195(1) መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 16 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የአመልካች ያለመክሰስ መብት የታለፈው ያላግባብ መሆኑን፣ አመልካች ድርጊቱን የፈፀሙት በወንድማቸው ላይ ሆኖ ከአቅም በላይ በሆነ የአደጋ አጋጣሚ ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤቶች መታለፉ ያላግባብ መሆኑን፣ የቅጣት ውሳኔም ተገቢነት የሌለው መሆኑና የእስራት ቅጣቱ መገደብ ሲገባው መታለፉም ያለግባብ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነውው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ጥፋተኛ መባላቸው ከሰ/መ/ቁጥር 42703 አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌወች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልጽ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደምተከተከላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በምክንያትነትና በውጤት መካከል ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 24 በተመለከተው አግባብ ግንኙነት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ሲያሽከረክሩት የነበረው ተሽከርካሪ ተገልብጦ ሟችን ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ/ም መግደላቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች የሚከራከሩበት ነጥብ ሟች የሞቱት በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለውን የባለሙያ የምስክርነት አስተያየት፣ በአደጋው ቦታ የተነሳውን ፕላንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል መዝኖ አመልካች የተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ቀርተው አደጋው መድረሱን ማረጋገጡን ደምድሟል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ማስረጃ ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ከመሆኑም በላይ ታአማኒነቱ ሲታይ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 በተመለከተው የማስረጃ ምዘና አግባብ ጉዳዩን ለማስረዳት በቂና አሳማኝ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ይህን ማስረጃ

ክብደት ሊሰጠው አይገባውም ነበር ለማለት የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች አደጋው በድንገተኛ አጋጣሚ የተከሰተ ነው በማለት የሚያቀርቡት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር በዚህ ችሎት ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57 በግልፅ እንደሰፈረው “ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆነም በአንፃሩ አንድ ሰው “የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57(2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የሕጉ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ህግ ድርጊቱ የተፈፀመው ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረደፋት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ ድርጊቱ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሳሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከሕጉ መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ቸልተኛ ነበር? ወይስ አልነበረም? የሚለው ጥያቄ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው በመሆኑም የሕጉን ይዘት እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው፡፡ ይኸውም፡- ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አደርጓል የሚባለው፡-

(ሀ) ድርጊቱ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን ፣ ወይም

(ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያሰቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡”

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የመባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው ነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው እድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀጽ 59(1) ይደነግጋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በሙያቸው አሽከርካሪ ሆነው እያለና በአሽከርካሪነት ሙያው ደግሞ የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-28157 ኦሮ የሆነውን ሚኒባስ መኪና እያሽከረከረ ከጅማ ከተማ ወደ አጋሮ ከተማ እያሽከረከሩ ተገቢውን ጥንቃቄ ከማድረግ ጉድለት መኪናው ተገልብጦ ሚች የሞቱ በመሆኑ አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ስር የማይጠበቁበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡

ስለሆነም አመልካች የጥፋተኝነት ውሳኔውን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ክርክር ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23፣24፣57፣57 እና 543(2) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) መሰረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሊቀጣ የሚገባው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ነው፣ ቅጣት ደግሞ ሊጣል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ነጥቦች በማመዛዘን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ ቅጣት ሲጥል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር እና በወንጀል ሕጉ ከተመለከቱት የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ጋር በማገናዘብ ቅጣቱን መወሰኑን የገለፀ ቢሆንም ሟቹ የአመልካች ወንድም በመሆናቸው ምክንያት ቅጣቱን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1) መሰረት ማክበዱ የሕግ መሰረት ያለውና የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ አላማ የሚያሳካ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ይሄው ምክንያት ሊያዝ የማይገባው ከሆነ አመልካችን ሊያርማቸው፣ ሌላውን ደግሞ ሊያስጠነቅቅ የሚችለው የቅጣት መጠን አንድ አመት ቀላል እስራት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም የቅጣት ውሳኔ ክፍል ግን በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 26643 ነሐሴ 03 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 167016 ነሐሴ 12 ቀን 2005 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 123422 ነሐሴ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(2)) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኛ ናቸው መባላቸው በአግባቡ ሲሆን ቅጣቱ ግን ተገቢ ያልሆነ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተይዞ እንዲከብድ የተደረገ በመሆኑ ምክንያቱን ውድቅ በማድረግ አመልካች ሊቀጡ የሚገባው የቅጣት መጠን በአንድ አመት ቀላል እስራት ነው ብለናል፣ የገንዘብ መቀጮው ብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) እንዲቀጡ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ይገለጽለት ብለናል፡፡
4. ***መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 93173

ታህሳስ 17 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች ፡- 1.አቶ ተዋበ እስጢፋኖስ

2. ወ/ሮ አበራሽ አስራት

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ

***መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡***

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ለሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በምዕራብ አርሲ ዞን ቆሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች እንደቅደምተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ክሱም፡- ተከሳሾች በኢ/ፌ/ዲ/ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(3) እና 481(1) (ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ በክሱ የተዘረዘሩትን ህገ ወጥ የጦር መሳሪያዎችንና ጥይቶችን በቤታቸው አከማችተው በፍርድ ቤት የብርበራ ትዕዛዝ ቤታቸው በፖሊስ ሲፈተሽ የጦር መሳያዎቹና ጥይቶቹ ስለተገኙ ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

1ኛ ተከሳሽም በሰጡት የእምነት ክህደት ቃል በክሱ ከተጠቀሱት ጦር መሳሪያዎች መካከል በተወሰኑት ላይ ፍቃድ ያለኝ ሲሆን ከቤቴ የተገኘ ቦንብ ባለመኖሩ የፈጸምኩት ወንጀል የለም፣ጥፋተኛም አይደለሁም ሲሉ ክደው የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃል ስለመስጠታቸው የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያመላክት አይደለም፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም 1ኛ ተከሳሽ ፈቃድ አለኝ ያሉአቸውን የጦር መሳሪያዎች በተመለከተ ፍቃድ የተሰጠበትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማዘዙ የሁለት ቺኮዝ ፣የክላሽንኮፕ ፣የኡዝ እና ካርቤን መሳሪያዎች ፍቃድ የተሠጠባቸውን ማስረጃዎች ማቅረባቸውን በፍርድ በማስፈር ኤፍ1-1 የሆነ ቦንብና በክሱ ተዘርዝረው ፍቃድ የሌላቸውን የጦር መሳሪያዎች በተመለከተም የከሳሽ ምስክሮችን ቃል ከሰማ በኂላ በሰጠው ውሳኔ የተሰጠው የብርብራ ትዕዛዝ የ1ኛ ተከሳሽ እና ሼህ አህመድ ሐጂ አህመድ የተባሉት ግለሰብ ቤቶች እንዲበረበሩ ሲሆን የሚበረበሩ የጦር መሳሪያዎች ዓይነት በዝርዝር በፍርድ ቤት ብርበራ ትዕዛዝ ካለመገለጹም ሌላ ብርበራው የተካሄደው 1ኛ ተከሳሽ በሌሉበት ቤታቸው ተሰብሮ በመሆኑ ብርበራው የተካሔደው ህጋዊ አካሄዱን ጠብቆ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁን

እንጂ ተከሳሾች ይህን ያህል የጦር መሳሪያ በቤት ውስጥ ማስቀመጣቸው ተገቢ ባለመሆኑ ሊማሩበትና የአካባቢውም ሌሎች ሰዎች ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ እንዲሁም ብርበራው የህጉን ሥርዓት ተከትሎ ያልተደረገ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ክስ የቀረበባቸውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) በመቀየር በወንጀል ህግ አንቀጽ 809 ጥፋተኞች ናቸው ሲል እንዳንዳቸው በብር 50 (አምሳ) እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ከሳሽም በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሸኘት ይግባኙን ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከራቸው በኋላ በሰጠው ውሳኔ፡- በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፖሊስ የመልስ ሰጪዎችን ቤት ሲፈተሽ የጦር መሳሪያዎቹ መገኘታቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፣የስር ፍርድ ቤትም ይግባኝ ባይ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ የመልስ ሰጪዎችን ማስረጃዎች መስማት ሲገባው መልስ ሰጪዎቹ ያቀረቡትን መቃወሚያ መነሻ በማድረግ የጦር መሳሪያዎቹን ፍቃድ እንዲያቀርቡ በማድረግ በቀረበው ማስረጃ ላይ ይግባኝ ባይ አስተያየት ሳይሰጥበት ከመዘገቡ ጋር ማያያዙ ተገቢነት የለውም፣እንዲሁም መልስ ሰጪዎቹ እንዲከላከሉ ብይን ሳይሰጥ ያለአግባብ ክስ የቀረበባቸውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመቀየር ቀላል ቅጣት የወሰነው መልስ ሰጪዎችንና መሰሎቻቸውን የማያስተምር እንዲሁም የህዝቡን መረጋጋት የማያረጋግጥ ጉድለት ያለበት ውሳኔ ነው፡፡ በመሆኑ የይግባኝ ባይ ምስክሮች የመልስ ሰጪዎች ቤት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲፈተሽ ቦንብ እና ኡዝ መትርየስ የተባሉት በግል የማይያዙና ፈቃድ የማይሰጥባቸው የጦር መሳሪያዎች የተገኙ ስለመሆናቸው በማረጋገጣቸው ክስ በቀረበባቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኞች ሊሆኑ ይገባል ሲል በዚሁ ድንጋጌ እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት እስራትና በብር 3000 እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ተከሰሾችም በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የይግባኝ ቅሬታቸውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(1) መሰረት የሰረዘባቸው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከራቸው በኋላ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔና በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል የሰበር አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረጉ ለዚህ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች በአቤቱታቸውም የጠቀሱት ቅሬታ ነጥብ ሲጠቃለል፡- የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት ያስተላለፉብን የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባ ነው የሚል ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- አመልካቾች የጦር መሳሪያዎቹን በቤታቸው አከማችተው የተገኙት ለንግድ አላማ ስለሆነ ክስ በቀረበባቸው ወንጀል ህግ አንቀጽ ጥፋተኞች ናቸው በሚል የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው የሚነቀፍበት ምክንያት ባለመኖሩ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾችም ተጠሪው ላቀረበው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካቾች የፈጸሙት ወንጀል በወንጀል ህግ 481(1)(ሀ) የሚሸፈን ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአመልካቾች ቤት በፍርድ ቤት በተሰጠ የብርበራ ትዕዛዝ በፖሊስ ሲፈተሽ ቦንብ እና ኡዝ መትርየስ የተባሉት በግለሰብ ደረጃ የማይያዙና ፈቃድ የማይሰጥባቸው የጦር መሳሪያዎች የተገኙ ስለመሆናቸው የተጠሪ ምስክሮች ለሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው ካስረዱት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ ይህን የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ይህ ችሎትም የሚቀበለው ነው፡፡ ይህንኑ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ይዘን ክስ ወደቀረበበት የወንጀል ህግ አንጽ 481(1)(ሀ) ስንመለስ፡- ማንም ሰው መንግስት አደጋ ላይ ስለመጣል በተወሰኑት ድንጋጌዎች ከተመለከተው ውጪ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማናቸውንም አይነት የጦር መሳሪያዎች፣ፈንጂዎች፣ወይም ጥይቶች በመነገድ ዓለማ የሰራ፣ከውጭ አገር ያስመጣ ፣ወደ ወጭ አገር የላከ፣ያጓጓዘ፣የገዛ፣የተቀበለ፣ያስቀመጠ፣ያከማቸ፣የደበቀ ፣ለሽያጭ ያቀረበ ወይም እንዲዘዋወሩ ያደረገ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ በዚሁ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ሆኖ እንደሚቀጣ ተመልክቷል፡፡ አመልካቾችም በብርበራ ከቤታቸው የተያዙትን የጦር መሳሪያዎች ውስጥ ፈቃድ የላቸውም የተባሉትን የጦር መሳሪያዎች በቤታቸው ውስጥ ያከማቹት ለንግድ በሚል እንደሆነ የተጠሪ ማስረጃዎች ስለማስረዳታቸው የሥር ወረዳ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚያመላክት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 481(1)(ሀ) በተነገረው መሰረት አንድን ሰው በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነው ለማስኘት ግለሰቡ መሳሪያዎቹን ያከማቸው ወይም በድንጋጌው ከተዘረዘሩት ድርጊቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ድርጊቶች የፈጸመው በመሳሪያዎቹ ለመነገድ በሚል እንደሆነ ከሳሽ ሊያስረዳ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) በጠቅላላው ለአንቀጽ 481 ከተሰጠው ርዕስ ወይም ስያሜ ጋር በማያያዝ ሊተረጎም የሚገባ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾቹ የፈጸሙት ወንጀል በወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ስር የሚሸፈን ሆኖ አላገኘነም፡፡ ይልቁንም ይህ ችሎት እንደሚገነዘበው አመልካቾች ፈቃድ የሌላቸውን የጦር መሳሪያዎችንና ጥይቶችን በቤታቸው አከማችተው የመገኘታቸው ሁኔታ የኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ የወንጀል ህግ አንቀጽ 808(ሀ) የጦር መሳሪያዎችን ና ጥይቶችን ስለመቆጣጠር የተደነገገውን የሚጥስ ሆኖ ስለሚገኝ በዚሁ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የጥፋኝነትና ቅጣት ውሳኔ ሊተላለፍባቸው የሚገባ ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት አመልካቾችን በወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ጥፋኞች ናቸው ሲሉ በዚሁ ድንጋጌ የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፉባቸው በዚሁ ድንጋጌ ስር ጥፋተኞች ሊሆኑ የሚያስችሉት ህጋዊ ፍሬ ነገሮች ስለመኖራቸው ተጠሪው ባላስረዳበት ሁኔታ ስለሆነ ውሳኔው በከፊል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/12859 በቀን 04/12/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/119417 በቀን 10/05/2005ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/146183 በቀን 13/12/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 195(2) (ለ)(2) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. አመልካቾች እንዳንዳቸው በ2 ዓመት እስራትና በ3000 ብር እንዲቀጡ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት የሰጡትን የውሳኔ ክፍል ሽረናል፡፡
3. አመልካቾች ጥፋተኞች ናቸው ሊባል የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(3) እና አንቀጽ 481(1)(ሀ) ስር ሳይሆን በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና 808(ሀ) ስር ነው በማለት በመወሰን በዚሁ ድንጋጌ እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በ3 (ሦስት )ወር እስራት ሊቀጡ ይገባል ብለናል፡፡ሆኖም አመልካቾቹ በዚሁ ወንጀል የታሰሩበት ጊዜ ከ3 ወር በላይ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንጻር ስለተረዳን በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ ከሆነ ዛሬውኑ ከሚገኙበት ማረሚያ ቤት እንዲለቀቁ አዘናል ፡፡ ለሚገኙበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ ብለናል፡፡
4. ፈቃድ የሌላቸውን የጦር መሳሪያዎችና ጥይቶች መንግስት እንዲወርሳቸው የሥር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሠጠው የውሳኔ ክፍልና ይህንኑ የውሳኔ ክፍል የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት በማጽናት የሰጡት የውሣኔ ክፍል አልተካም ብለናል፡፡

   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

የሰ/መ/ቁ/89276

መሥከረም 23 ቀን 2006 ዓ ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ተሸገር ገ/ ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሙሥጠፋ አህመድ

**አመልካች** ተፈሪ ሚናሞ አልቀረቡም

**ተጠሪ** የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ዐቃቤ ሕግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሶዶ ከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09361 ህዳር6ቀን 2005 ዓ.ም፣ የሰጠው ፍርድና የወላይታ ዞን ከፍተኛፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 23731በ ጥር 9ቀን 2005ዓ.ም የሰጠው ውሳኔናየደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎትመሰረታዊ የህግ ሥህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡በሥር ፍርድ ቤት አመካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ተከሳሽ (አመልካች) በወኝጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ለራሱ ብልጽግና ለማግኘት አስቦ ተካሳሹ የቅርብ ጓደኛው የሆነውን የግል ተበዳይ አቶ አሰፋ ደመቀ ሶዶ መርካቶ ክፍለከተማ ከሚገኘው የግል ድርጅቱ( ግሮሰሪ)በህዳር ወር 2003 ዓ.ም ዓ.ም በመሄድ ጨረታ አሸንፌአለሁ በማለትና በሚስቱ ሥም የተዘጋጀ ፐርፎርማ በማስያዝ ብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) ከወሰደ በኋላ ግል ተበዳዩ በሽማግሌ ሲጠቀው ካመነ በኋላ ገንዘቡን ያልከፈለው ስለሆነ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ መጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ አመልካች ወንጀል አልፈጸምኩም፣ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡
2. ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ሥድስት የሰው ምስክሮች አቅርቧል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ የተጠሪ ምስክሮች የግል ተበዳይና አመልካች ጓደኛሞች መሆናቸውን፣ አመልካች የጋምጎፋ ዞን ደንባ ጎፋ ወረዳ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት አላቂ ዕቃ ለማቅረብ በጨረታ አሸንፌአለሁ፡፡ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) ስጠኝ በማለት በዕምነት ወስዶ አልመለሰም፡፡ ሌሎቹ ምስክሮች የግል ተበዳይንና አመልካችን ሲያሸማግሉ አመልካች ገንዘቡን የወሰደ መሆኑን ለሽማግሌዎቹ ያመነ መሆኑን የመሰከሩ

መሆኑን ጉዳዩ ያሳያል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከግል ተበዳይ በአደራ ወሰድኩት ገንዘብ ላለመኖሩ ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤትየግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኃላተከሳሽ ጨረታ አሸንፌአለሁ በማለት ከግል ተበዳይ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያ ወሰደውንብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) ያልመለሰ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በ አንድ ዓመት ከ አምስት ወር እሥራት እንድቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝለ ወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችንናየተጠሪን ክርክር ከሰማ በኂላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠውን የጥፋኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር195 ንዑስ አንቀጽ2(ለ)2 መሰረት አጽንቶታል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡

4. አመልካች ሚያዚያ 11ቀን200ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታየሥር ፍርድ ቤት፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትየሰጡትውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የግል ተበዳይ የሰጠው ምስክርነት ለአመልካች ብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) በብድር ሰጥቸው አልመለሰልኝም የሚል ነው፡፡ይህ ፍታብሔራዊ ግኑኝነትን ሚመለከት እንጂ ወንጀል አይደለም፡፡ በተጠሪ ክስም ሆነ ማስረጃ እኔ እንደፈጸምኩት የተገለጸው ተግባር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነነውን የእምነት ማጉደል ወንጀል የማቃቁምና በወንጀል ሕጉ በወንጀልነት ያልተደነገገነው፡፡ እንደዚሁም ተጠሪ ክስና ማስረጃ አመልካች በወንጀል ህጉ አንቀጽ23 መሰረት የህግ፣ የግዙፍ ተግባርና ሞራል ሁኔታ በተሟላበት ሁኔታ ወንጀል የፈጸምኩ አለመሆኑ፡ያላረጋገጠበት ሆኖ እያለ የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤት፣ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካችበወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከአምስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ23 የሚተላለፍና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሥለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶትና መልስ የሚያቀርብበት ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶት መልስ ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገጸው ሲሆን እኛምየሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካችበወኝጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከአምስትስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጡት ውሳኔተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥበመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለ መወሰን በመጀመሪያ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ መሰረታዊ ፍሬ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

6. ተጠሪ አመልካች የእምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ስለመሆኑ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ በይዘቱ፣ የግል ተበዳይና አመልካች ጓደኛሞች እንደሆኑ፣ አመመልካች የጋምጎፋ ዞን ደንባ ጎፋ ወረዳ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት አላቂ ዕቃ ለማቅረብ በጨረታ አሸንፌአለሁ፡፡ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) ስጠኝ በማለት የጠየቀው መሆኑንና ገንዘቡን የግል ተበዳዩ አመልካችንሰነዶችን በሚስቱ በኩል በማስፈረም በመያዥነት ይዞ ገንዘቡን ለአመልካች የሰጠው መሆኑን፣ አመልካች ገንዘቡን ለግል ተበዳይ ያልመለሰ መሆኑን እንዳስረዱ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትና ከላይ የተገለጹት ተግባራት የግል ተበዳይና በአመልካች መካከል የመሰረቱት ግኙኝነት አደራ ሰጭና የአደራ ተቀባይ ነው ወይስ አበዳሪና የተበዳሪ ግኑኝነት አመልካችና የተጠሪ ግኑኘነት አበዳሪና የተበዳሪ ግኑኙነት አላቸው ቢባልህጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው የሚሉት ጥያቄዎች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

7. ከላይ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ፣ዝርዝር ይዘትናመሰረታዊ ዓላማ መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ በወንጀል ህጉ በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝርበት ምእራፍ ሁለት በልዩ ሁኔታ በተንቀሳቃሽ ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝረው ክፍል አንድ ሥር የተደነገገ የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሰረታዊ ባህሪ፣ ይዘትና የሚስከትለውን ኃላፊነት የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 ድንጋጌ የአማረኛ ቅጅ ቃል በቃል ሲነበብ ማንም ሰው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይምለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው የደረገ፣የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን መሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ3 የተከሳሹ ወንጀል ሃሳብ ግምት ሚደነግግ ሲሆን ይዘቱም ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ማዋል ሀሳብ እንዳለው ይቆጠራል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

8. የእንግሊዘኛውን ቅጅ ስንመለከት- Breach of Trust የሚል ርዕሥ ያለው አንቀጽ 675 Whoever, with intent to obtain for himself or to procure for a third person an unjustifiable enrichment, appropriates, or procures for another, takes or causes to be taken, misappropriates, uses to his own benefit or that of a third person, or disposes of for any similar act, in whole or in part, a thing or a sum of money which is the property of another and which has been delivered to him in trust or for a specific purpose, is punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment, or with rigorous imprisonment not exceeding five years. በማለት በንዑስ አንቀጽ1 የሚደነግግ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ3 The intent to obtain for himself or to procure for third person an unjustifiable enrichment shall be presumed where the criminal is unable upon call, to produce or repay the thing or sum entrusted, or at the time when he should have returned it or accounted there for. በማለት ይደነግጋል፡፡

9. አመልካች ከግል ተበዳይ ጨረታ ያሸነፍኩ ስለሆነ ለሥራ ማስኪጂያና ለቅድመ ክፍያ ብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) የጠየቀና የግል ተበዳይም የአመልካችን ሰነዶች በመያዥነት ይዞ የሰጠው መሆኑን በተጠሪ ማስረጃ እንደተገለጸ ተረድተናል፡፡ አንድ ሰው ለሌላወ የተበደረውን ነገር በአይነቱ ለመመለስ ተገዳጅ በማድረግ ገንዘብ ወይም በማገልገል የሚያልቅ ሌላ ነገር ለተበዳሪው ለመስጠትና ኃብትነቱን ለማስተላለፍ የሚፈጽሙት ተግባር የማያልቅ ነገር ብድር እንደሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2471 ከተሰጠው ትርጓሜ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንድን ነገር በብድር መሥጠትና አንድን ነገር በአደራ መስጠት የተለያየ ባህሪና ይዘት ላቸው ናቸው፡፡ አደራ አደራራ ተቀባዩ አደራ አስቀማጩ ሰጠውን ዕቃ ተቀብሎ በአደራ እንዲያስቀምጥለት የሚገባው ግደታና ተግባር መሆኑንከፍታብሔር ሕግ ቁጥር2779 ከተሰጠው ትርጓሜ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአደራ የተቀበሉትን ገንዘብ ለአደራ አስቀማጩ አለመመለስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 በመተላለፍ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ሊያጠየቅ የማይችል የወንጀል ተግባር ነው፡፡

10. በአንጻሩ ተበዳሪ በብድር የወሰደውን ገንዘብ በወቅቱ አለመክፈሉ አግባብነት ባላቸው ህግ ድንጋጌዎች በፍታብሔር ከሚጠየቅ በሰተቀርየወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 ተላልፏል ተብሎ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ሊጠየቅ የማይችል መሆኑንከወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ ዝርዝር ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡.ማንም ሰው በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቀው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይምለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ፡፡ የአመልካች አድራጎትየወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ3 በሚደነግገው ወንጀል ሃሳብ ግምት የማይሸፈን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

11. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በህግ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ እንደማይችል በህገ መበንግስቱ አንቀጽ22 ንዑስ አንቀጥ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው የህግ ፣የግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ23 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ከላይ ዘረዘርነው የግዙፍ ድርጊት የህግ የሃሳብ ሁኔታዎች አልተሟሉም፡፡ ይህ ሁኔታ መሟላቱን ሳያረጋግጡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካችበወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድዓመት አምስት ወር እሥራት እንዲቀጣ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ፣ዝርዝር ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሰርታዊ የህግ ስህተት ያለበት በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የሶዶ ከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት ፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛፍርድ ቤትናየደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ቁጥር195 ንዑስ አንቀጽ2(ለ)1 መሰረት ተሸሯል፡፡

2. አመልካች ጨረታ አሸንፌለሁ በማለት ለሥራ ማስኬጃና ለቅድመ ክፍያ የሚሆን ብር21000( ሃያ አንድ ሺ ብር) ከግል ተበዳዩ  በብድር የወሰደውን ገንዘብ  ለግል ተበዳይ አለመክፈሉ ( አለመመለሱ) አመልካችን በወንጀል ሕግ  አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1  ድንጋጌ መሰረት በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቀው ባለመሆኑ በነጻ ይሰናበታል በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካች ከቀረበበት ወንጀል ክስ በነጻ ተሰናበተ በመሆኑ ከእስር እንዲለቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 91535

የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ አህመድ አደም በሽር - ከጠበቃ ሌ/ኮ ስንታየሁ ደመቀ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የአማራ ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን በህክምናና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የመስራት የወንጀል ክስ አስመልክቶ በሶስቱም የክልሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች ተሰጥቶ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በ03/07/2004 ዓ.ም. በተዘጋጀ የክስ ማመልከቻ በኮምቦልቻ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት 3ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 535(3)(ሀ) እና (መ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የህክምና መመርመሪያ መሳሪያዎችን በአግባቡ የመያዝ ሙያዊ ግዴታ እያለባቸው በ21/11/2003 ዓ.ም. በኮምቦልቻ ከተማ በቀበሌ 03 ክልል የኮምቦልቻ ጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች የግል ክሊኒኮችን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ በተገኙበት ጊዜ ተከሳሹ ሀያት በተባለ መካከለኛ ክሊኒክ በህክምና ባለሙያነት እየሰሩ በነበረበት ጊዜ አንዱን የሽንት መመርመሪ መሳሪያ ለሶስት በመሰነጣጠቅ አብዝተው ሲሰሩ የተገኙ በመሆኑ በህክምና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የመስራት ወንጀል አድርገዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ተጠሪ በክሱ መሰረት ያስረዱልኛል ያላቸውን ሶስት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቶአል፡፡ የጽሁፍ ማስረጃም አቅርቦአል፡፡ፍ/ቤቱም ተጠሪ በክሱ መሰረት ያስረዳ መሆኑን ገልጾ አመልካቹ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 142 በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አመልካች መሳሪያዎቹ ለልምምድ የሚላኩ የህክምና ሙያ ተማሪዎች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ እንጂ ለሕክምና ስራ የዋሉ አለመሆናቸውን ያስረዱልናል በማለት የሰው እና የጽሁፍ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከክሱ ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ አመልካቹ በተጠሪ ማስረጃ የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር በማስረጃው አላስተባበለም በማለት በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት እና ቀጥሎም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል በአመልካቹ ላይ የአራት ዓመት ጽኑ እስራት እና የብር 16,000 መቀጮ

ቅጣት ወስኖአል፡፡አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ይግባኝ በማቅረባቸው የደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔውን በትዕዛዝ ሲያጸናው የሰበር ክርክሩን የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የጥፋተኝነት እና የጽኑ እስራት ቅጣቱን በማጽናት እና መቀጮውን ብቻ ወደ ብር 10,000 በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ሶስት ቦታ ተሰነጣጥቆአል የተባለው የሽንት መመርመሪያ መሳሪያ ድርጊቱ በራሱ ጥፋት መሆን አለመሆኑን ከወ.ሕ.አ. 535(ሀ)እና (መ) አንፃር፣ይህ ቢታለፍ የዐ/ሕግ ምስክሮች ወደ ክሊኒክ ሲሄዱ በተሰነጣጠቀ የሽንት መመርመሪያ መሳሪያ ባለሙያዎቹ ሲጠቀሙ አላየንም ባሉበት ሁኔታ አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመከለተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው ነጥብ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መሰረት የማስረዳት ግዴታውን ተወጥቶአል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቹ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ክደው የተከራከሩ ሲሆን በዐ/ሕግ በኩል የክስ ነጥቡን ለማስረዳት የቀረቡት የተጠሪ ምስክሮች ለቁጥጥር ተግባር በተሰማሩበት ጊዜ አመልካች በሚሰሩበት የመመርመሪያ ክፍል ውስጥ ከሚገኘው ጠረጴዛ ላይ 68 የተሰነጣጠቁ የሽንት መመርመሪያ መሳሪዎችን (ዲፕ ስቲክስ) ማግኘታቸውን ከመግለጽ ውጪ በእነዚህ መሳሪያዎች አመልካቹ ሲገለገሉበት ስለማየታቸው ወይም አመልካቹ ቀደም ብለው የተገለገሉባቸው ስለመሆኑ ወይም በክፍሉ ውስጥ ተቀምጠው የተገኙት በአመልካቹ በአገልግሎት ላይ ሊውሉ ታስበው ስለመሆኑ በማረጋገጥ የሰጡት ምስክርነት አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡የጽሁፍ ማስረጃውም የሽንት መመርመሪያ መሳሪያዎችን ሰነጣጥቆ መጠቀም ተገቢ ስላለመሆኑ የሙያ አስተያየት የተሰጠባቸው ናቸው፡፡የኮምቦልቻ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ የሰጠውና በኃላም አልተከላከሉም በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ያስተላለፈባቸው ይዘቱ ከላይ በተገለጸው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሲሆን በበኩላችን ይህ ማስረጃ ዐ/ሕግ በክሱ መሰረት አስረድቶአል ለማለት የሚያስችል መሆን አለመሆኑ በአግባቡ መጤን የሚገባው ሆኑ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገ ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወ.ሕ.አ. 23(1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በወ.ሕ.አ. 32(1) ስር ተደንግጎአል፡፡በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው

የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ.ሕ.አ. 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡በሌላ አነጋገር ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቶአል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 142 መሰረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በዐ/ሕግ በኩል በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጡት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች አመልካች በሚሰሩበት የመመርመሪያ ክፍል ውስጥ ከሚገኘው ጠረጴዛ ላይ 68 የተሰነጣጠቁ የሽንት መመርመሪያ መሳሪዎችን(ዲፐ ስቲክስ) መገኘታቸው ብቻ ሲሆን አመልካቹ ተላልፈውታል ተብሎ የተጠቀሰባቸው ድንጋጌ የሚቀጣው ደግሞ ደህንነቱና ጥራቱ ባልተረጋገጠ፣በተከለከለ፣በተበላሸ፣በተጭበረበረ፣በተበከለ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት በሚያደርስ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ መገልገልን ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለህክምና ተግባር በእነዚህ መሳሪዎች ሲገለገሉ አልተገኙም፤ተቀምጠው የተገኙት ለሕክምና አገልግሎት ከዋሉ በኃላ ወይም ለማዋል በማሰብ ስለመሆኑም አልተረጋገጠም፤የሽንት መመርመሪያ መሳሪያዎቹ የተሰነጣጠቁት በምን ምክንያት እንደሆነም አልተገለጸም፡፡በመሰረቱ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 ስር በግልጽ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ይዘቱ ከላይ የተገለጸው የዐ/ሕግ ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርግ ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረበው መልስም ይህንኑ በመገንዘብ በአመልካቹ ላይ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ ቢሻር ተቃውሞ የሌለው መሆን ገልጾአል፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት  በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 መሰረት ተከሳሹን ማሰናበት ሲገባው የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱም ሆነ በመጨረሻም የዐ/ሕግን ማስረጃ አላስተባበለም በማለት በአመልካች ላይ የሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የጥፋተኝነት የቅጣት ውሳኔ ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ የሆኑ የወንጀል ሕግ እና የወንጀል ስነስርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች አቶ አህመድ አደም በሽርን አስመልክቶ በኮምቦልቻ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 202797 በ21/09/2004 ዓ.ም.ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመ.ቁ. 0205343 በ27/09/2004 ዓ.ም. እና በመ.ቁ. 27041 በ19/10/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ እና በውሳኔ የፀናው የጥፋተኛነት ውሳኔ፤እንዲሁም በኮምቦልቻ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 202797 በ24/09/2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 0205343 በ27/09/2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 27041 በ19/10/2005 ዓ.ም. የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ባቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ አመልካች ወንጀሉን ማድረጋቸውን ያላስረዳ እና በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ ያልተወጣ በመሆኑ አመልካች ከተከሰሱበት በህክምናና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የመስራት የወንጀል ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. በአመልካች ላይ ተጥሎ የነበረው የአራት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተሻረ ቢሆንም አመልካች ቀደም ሲል በዚህ ችሎት ትዕዛዝ በራሳቸው ዋስትና በዋስ የተለቀቁ በመሆኑ ለማረሚያ ቤት የሚተላለፍ ትዕዛዝ አይኖርም፡፡
4. አመልካች ተጥሎባቸው የነበረውን የመቀጮ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ አድርገው ከሆነ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡
5. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

# ባንክና

# ኢንሹራንስ

የሰ/መ/ቁ 78180

መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጠበቃ አትናፍን]ጋሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስቴር ንጉሴ ወኪል የአሮ ኤፍሬም ንጉሴ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመድን ዋስትና ሽፋን ውል የሚሻሻልበትን ሥርዓት የሚመለከት ነው። የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2004 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 10522 የካቲት 09 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ለተጠሪ አመልካች በድምሩ ብር 73,523.00 ከዳኝነት፣ ከሕጋዊ ወለድ እና ከ10 የጠበቃ አበል እንዲሁም በቁጥር ከብር 500.00 ወጪ ጋር እንዲከፍል የሠጠውና በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 150259 መጋቢት 07 ቀን 2004 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ግድፈት የተፈጸመበት ነው በማለት እንዲሻርለት ስለጠየቀ ነው።

ጉዳዩ የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በስር ተከሳሽነት፣ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ በከሳሽነት ነው።

የተጠሪ ክስ ይዘቱም አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 2-78918 አ.አ በሚል ለምትታወቀውና ንብረትነቷ የአሁኑ ተጠሪ ለሆነችው የኪራይ መኪና የኢንሹራንስ ሽፋን ሰጥቶ የነበረ መሆኑን፣ ይህ መኪና በተጠሪ ተወካይ አቶ ስንታየሁ ተካልኝ ለተባለ የመንጃ ፈቃድ ላለው ሰው ተከራይቶ የተከራየው ሰው በማሽከርከር ላይ እያለ የፊት ጎማው ፈንድቶ በመገልበጥ በመኪናው ላይ የአካልና የመካኒካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፣ ከአመልካች ላይ ባላቸው የመድን ውል በዚህ መኪና ላይ አደጋ እንደደረሰ የሚጠግኑ ጋራጆችን አወዳድረው የዋጋ ማቅረቢያ ከሰበሰቡ በኂላ አመልካች ኢንሹራንስ ከገባው ሰው ወይም እሱ ከቀጠረው ሹፌር ወጪ በሌላ ሶስተኛ ወገን ሲሽከረከር አደጋ የደረሰበት ስለሆነ የደረሰውን ጉዳት ለመተካት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ጥገናውን ወይንም ለጥገናው የሚያስፈልገውን ወጪ አልቀበልም ማለቱን፣ ከዚህ በኂላ ተጠሪ ይህን መኪና አካል ጨረታውን ባሸነፊው ጋራጅ አሰርቶ ለውስጥ እቃ ጉዳት የሚያስፈልገውን የመለዋወጫ እቃም አወዳድሮ ከአሸናፊው ጋራጅ ላይ ማግኘቱን

ገልፆ አመልካች ከጉዳቱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ መኪናውን ለማስነሳት፣ ለትራንስፖርት የወጣውን የማስጠገኛ ዋጋ በድምሩ ብር 76,523.00 ለተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ለደረሰው አደጋ በሕጉ አግባብ ከተጠሪ ጋር የገባው የመድን ዋስትና ውል እንደሌለ፣ ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ተጨማሪ ውል ላይ ቀደም ብለው ያደረጉትን የኢንሹራንስ ሽፋን መኪናው ላይ አደጋ የደረሰው ኢንሹራንስ ገቢው ወይም እሱ ከቀጠረው ሹፌር ውጪ በሶስተኛ ወገን ሲሽከረከር ከደረሰ ኢንሹራንስ ሰጪን የማይመለከተው መሆኑን በመግለጽ ስምምነት መደረጉን ገልፆ ኃላፊነት የለብኝም በማለት በኃላፊነት ረገድ የተከራከረ ሲሆን በኃላፊነት መጠኑ ላይም የአደጋ መነሻ ብር 3000.00 ሳይቀነስ መቅረቡ ተገቢ ያለመሆኑን፣ መኪናውን ለመጫን ብር 5000.00 ከፍያለሁ የሚሉትም ሐሰት መሆኑን፣ በመኪው ላይ የደረሰ የመካኒካል አደጋ ለመኖሩ በባለሞያ የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ በተደረገው ጨረታ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ስራውን መውሰድ ሲገባው ከፍተኛውን ያቀረበ መውሰዱ ያላግባብ መሆኑን፣ ለመካኒካል ጉዳት ያስፈልጋል ተብሎ ከተጫራቾች ቀረበ የተባለው ፕሪፎርማ እርስ በራሱ የሚጋጭ መሆኑን ገልጾ ገንዘቡንም ልከፈል አይገባም በማለት የተከራከረ ሲሆን ገንዘቡን ክፍል የሚባል ከሆነም ተጠሪ የመለዋወጫ እቃዎችን ሊመልስ ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ተጨማሪ ውሉን የማያውቁት መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ተጠሪ በሕጉ አግባብ ያደረጉት የተጨማሪ የመድን ሽፋን ውል መኖሩ መረጋገጡን፣ በዚህ ውል ደግሞ የመድን ሽፋን የተሰጠው መድን ገቢው ወይም እሱ በቀጠረው ሹፌር እየተሽከረከረ ባለበት ጊዜ እንጂ በሌላ ሶስተኛ ወገን ሲሽከረከር አደጋ ከደረሰ አመልካች ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን መገለጹን በምክንያትነት ይዞ የተጠሪን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎልታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ አመልካቹ ውሉ ስለመሻሻሉና ይህን ውል ስለማሻሻሉ ለተጠሪ ያሳወቀ መሆኑን አላስረዳም በሚል ምክንያት ተጨማሪ የመድን ውል የለም ሲል በቀድመው የመድን ውል መሰረት አደጋው እንደሚሸፍን ጠቀሶ ለጉዳዩ አመልካችን ኃላፊ ያደረገ ሲሆን የካሳውን መጠን በተመለከተ ደግሞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሶለት የስር ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች ለተጠሪ ብር 73,523.00 ከዳኝነት፣ከሕጋዊ ወለድ እና ከ10 የጠበቃ አበል እንዲሁም በቁጥር ከብር 500.00 ወጪ ጋር እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ውሳኔውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 377 መሰረት አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አሁን በተያዘው መዝገብ ላይ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተጨማሪ የመድን ሽፋን ውል ስለመኖሩ የተጠሪ ወኪል መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም የጻፋት ማመልከቻ ቀርቦ እያለ ይኼው ሳይታይ ታልፎ ተጨማሪ ውል የለም ተብሎ ለአደጋው ሽፋን እንዳለው ተደርጎ ካሳውን ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ጠበቃቸው በሰጡት መልስ አመልካች ኃላፊነቱን አስመልክቶ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ያልጠበቀ መሆኑን፣ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ የተባለውም ተጨማሪ ውሉን ተጠሪ ያልፈረሙበትና የሚያውቁት ስለመሆኑ ባለማስረዳቱ መሆኑን፣ መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም የተጠሪ ወኪል ጻፉ የተባለበት

ማመልከቻም በክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ታይቶ የሚታመን አይደለም፣ ተጨማሪ ውል ስለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም ተብሎ ውድቅ የተደረገ እና በዚህ ችሎት ሊመዝን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ከሰ/መ/ቁጥር 76942 አንፃር ሲታይ የሰበር ማቅረቢያ ጊዜው ያላለፈ መሆኑን በመጥቀስና ሌሎች የሰበር አቤቱታ ነጥቦችን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚመለከተው መልኩ መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት ተጨማሪ የመድን ሽፋን ስምምነት አልተደረገም ተብሎ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ መባሉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለተጠሪ ጥያቄ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከረው አደጋው መድን የገባው ወይም እርሱ ከቀጠረው ሾፌር ውጪ በሰ ሶስተኛ ወገን ሲሽከረከር ከደረሰ ሽፋን የሌለው መሆኑ ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተጨማሪ ውል ስምምነት አድርገናል፣ ይኼው ውል ስለመኖሩ ደግሞ የተጠሪ ወኪል መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም የፃፋት ማመልከቻ ያሳያል በማልት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ተጨማሪ ውል የለም፣ አላውቀውም፣ በቀደመው መሰረት አደጋ ሽፋን አለው በሚል ነው፡፡ በቅድሚያ ተጠሪ ኃላፊነቱን አስመልክቶ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ጊዜውን ጠብቆ የቀረበ አይደለም በማለት ያቀረቡትን ተቃውሞ ተመለክተናል፡፡

አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ኃላፊነቱን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ የካቲት 13 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ በመ/ቁጥር 76942 ተከፍሎ ለባለሶስቱ የሰበር አጣሪ ችሎት ቀርቦ እስከ ሚያዝያ 03 ቀን 2004 ዓ.ም ተገቢው ትዕዛዝ ሳየሰጥበት ከቆየ በኂላ የኃላፊነቱን መጠን ተመልክቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት የታዘዘው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የካቲት 09 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቶ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት መጋቢት 07 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በማፅናቱ አመልካች በዚሁ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን መጋቢት 17 ቀን 2004 ዓ.ም ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ጉዳዩ አሁን በተያዘው መዝገብ ተከፍቶ የሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ.ም ሊመረመር የሚገባ የሕግ ነጥብ መኖሩን አምኖ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ ሲሆን ሚያዝያ 02 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 76942 ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ባሁኑ መዝገብ አጠቃልሎ ማቅረቡንና ጉዳዩም ያስቀርባል የተባለ መሆኑን በመዘርዘር በሰ/መ/ቁጥር 76942 የቀረበው መዝገብ እንዲዘጋለት አመልክቶ የሰበር አጣሪ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ዋናውን ጉዳይ ሳይመለከት የዳኝነት ገንዘቡ በደንቡ መሰረት ተቀንሶ እንዲመለስለት በማዘዝ መዝገቡን ዘግቶአል፡፡ በመሆኑም አመልካች በኃላፊነት ውሳኔው ላይ በወቅቱ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የካሳ መጠን ክርክሩ ደግሞ በሰበር አጣሪው ችሎት የቀረበው የኃላፊነት ቅሬታ መቋጫ ሳያገኝ አስቀድሞ እልባት አግኝቶ የካሳው መጠን ውሳኔ ቅሬታ ለአጣሪ ችሎቱ ቀርቦ በኃላፊነት ጉዳይ ላይም ቅሬታ ተጠቃልሎ ቀርቦ ታይቶ

ተገቢው ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑን ስለተገነዘብንና በአንድ ጉዳይም ሁለት መዝገቦች መከፈት የሌለባቸው በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡት መቃወሚያ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22(4) እና ከክርክር አመራር ስርዓት አንጻር ተገቢነት ያለው ሁኖ ስላላገኘን አልተቀበልነውም፡፡ ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ ከላይ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 657 ስለኢንሹራንስ ውሉ ፎርማሊቲ የሚደነግገውም ሀሳብ የያዘ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት የኢንሹራንስ ውል የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ በሚባል ጽሁፍ እንደሚገለጽና የመድህን ገቢውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ በፖሊሲው ላይ መድህን ሰጭው ከፈረመ ህጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት በመድህን ሰጭው እና በመድህን ገቢው መካከል እንደሚመሰረት ተቀምጧል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የንግድ ሕጉ ልዩ የሆነ የኢንሹራንስ ውል እንደመሆኑ መጠን ከጠቅላላው ሕግ የበላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚደረግ መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያሳዩን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የኢንሹራንስ ውል አደራረግ አፈጻጸሙ በጠቅላላ የውል ሕግ የሚመራ ግንኙነት አይደለም፣ ይህ ሰበር ችሎትም የኢንሹራንስ ውል አደራረግ አፈጻጸሙ በጠቅላላ የውል ሕግ የሚመራ ግንኙነት አይደለም፣ ይህ ሰበር ችሎትም የኢንሹራንስ ውል አለ ለማለት መድን ሰጪው በሚያዘጋጀው ፖሊሲ ላይ መፈረም እንዳለበት በን/ሕ/ቁጥር 657 ላይ ከመመልከቱ በስተቀር መድን ገቢው መፈረም እንደሚገባው ያልተመለከተ በመሆኑና በውል ማቅረቢያ ሰነዱ ላይ መድን ገቢው ከፈረመና በፖሊሲው ላይ ደግሞ መድን ሰጪው ከፈረመ በሁለቱ መካከል የመድን ውሉ ስለመደረጉ በቂ መሆኑን በሰ/መ/ቁ. 24703 ሚያዝያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ እንዲሁም የኢንሹራንስ ፖሊሲ ተጨማሪ በሆነ ጽሑፍ ካልሆነ በቀር ሊለወጥ እንደማይቻል የን/ህ/ቁጥር 657(2) አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሲታይም ፖሊሲው ወይም የፖሊሲው ተጨማሪ ጽሁፍ ከመፈረሙ በፊት ለጊዜው ኢንሹራንስ ሰጪው ኢንሹራንስ ለሚገባው ሰው ፖሊሲው ወይም ለፖሊሲው ተጨማሪ ጽሑፍ እስከ ተፈረመ ድረስ ማረጋገጫ መድን የሚሆነው ጽሑፍ የሠጠው እንደሆነ ኢንሹራንስ ሰጪውና ኢንሹራንስ ገቢው አንዱ ለአንዱ ግዴታ እንደገቡ ይቆጠራል በሚል ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አይነተኛ ዓላማም ውሉ ስለመኖሩ የሚረጋገጠው በጽሑፍ በሆነ ሰነድ መሆኑን ማሳየት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ከመድን ገቢው ወይም እራሱ ከቀጠረው ሾፌር ውጪ መኪናው ሲሽከረከር አደጋ ከደረሰ የመድን ሽፋን የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ተጨማሪ ውል አለ በማለት የተከራከረው ሰነዱን በማቅረብና ይህንኑ ሰነድ ተጠሪ ባይፈርሙበትም ሰነዱ ያለ ነው፣ ሰነዱ የለ መሆኑንም በተጠሪ ወኪል መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም ያቀረቡት ማመልከቻ ያሳያል በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጨማሪ ውሉ ተጠሪ የሚያውቁት ስለመሆኑ አመልካች አላስረዳም፣ መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም ተጻፈ የተባለ ማመልከቻም የሚታመን አይደለም በማለት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው መሆኑን ውሳኔው ያሳያል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተጠሪ በተጨማሪ ውል ላይ መፈረም አለመፈረማቸው የሚያስከትለው የሕግ ውጤት ምንድነው የሚለውን ከመታየቱ በፊት ሰነዱ በተጠሪ የማይታወቅ፣ ማመልከቻውም የማይታመን ነው ወደሚለው ድምዳሜ ፍሬ ነገርን የማጣራት፣ ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በዚህ ችሎት የሚታይበት አግባብ የሌለ መሆኑን

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) ሀ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪ ደረሰ የተባለውን አደጋ የሚሸፈነው የቀደመው ውል በተጨማሪ ውል ስለመለወጡ ፈቃዳቸውን የሰጡ ወይም ተጨማሪ ውሉን ያወቁት የነበረ መሆኑን ፍሬ ነገሩን በመመርመርና ማስረጃን በመመዘን የሚይዘው ድምዳሜ የለም፡፡ በመሆኑም በተጠሪ ወኪል መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም ተፃፈ የተባለው ማመልከቻ በማስረጃነት ቀርቦ ሰነዱ የማይታመን መሆኑና ተጠሪ ተጨማሪ ውሉን እንደሚያውቁት ሊያስረዳ እንደማይችል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የቀደመውን ውል ከአስር ወር ቆይታ በኂላ አሻሽዬዋለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ ጥያቄ በመሆን ከላይ ከተጠቀሱት የንግድ ህጉ ድንጋጌዎችና ከን/ሕ/ቁጥር 659 ድንጋጌ አኳያ ሊታይ የሚገባው ሁኖ አላገኘነም፡፡ በካሳ መጠኑ ላይ የቀረቡት ክርክሮችም የፍሬ ነገርና የማስረጃ ክርክሮች በመሆናቸው በዚህ ችሎት የሚታዩበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም የአመልካች የሰበር አቤቱታ የመሰረታዊ ሕግ መመዘኛን የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ልዩን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 10522 የካቲት 09 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በኮ/መ/ቁ 121982 ነሐሴ 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፣ እንዲሁም በዚሁ ችሎት በመ/ቁጥር 150259 መጋቢት 07 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ለተጠሪ አመልካች በድምሩ ብር 73,523.00 /ሰባ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሶስት ብር/ ከዳኝነት፣ ከሕጋዊ ወለድ እና ከ10 የጠበቃ አበል እንዲሁም በቁጥር ከብር 500.00 ወጪ ጋር እንዲከፍል የተሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይምለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 90793

ታህሳስ 04 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሪታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ግሎባል ኢንሹራንስ አልቀረበም

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ፍጹም ላቀው
2. ወ/ሮ ብስኩት ዘለቀ

} ጠበቃቸው አትናቦን ነጋሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም የከሳሾች አውራሽ የጋራ ንብረት የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3.19516 ኦ.ሮ ሚኒባስ መኪና በተከሳሽ ኩባንያ የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው ሲሆን በ20/10/2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡10 ሲሆን ከአዳማ ወደ አዲስ አበባ እየተጓዘ ቢሾፍቱ ከተማ መግቢያ ላይ ትክክለኛ ምልክት ሳያሳይ መንገድ ዘግቶ የቆመውን መኪና በመግጨት ከፍተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰበት ሲሆን ተከሳሽም መኪናውን አንስቶ የተጎዱ ተሽከርካሪዎች ወደሚጠገኑበት ቦታ ወስዶ መኪናውም ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የተሽከርካሪውን ዋጋ ብር 350,000 ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ለከሳሾች ከገለጸ በኋላ መኪናው ላይ አደጋ የደረሰው ትርፍ ሰው በመጫኑ ምክንያት በመሆኑ ክፍያውን እንደማይፈጽም ስለገለጸልን የሚፈለግበትን ብር 350,000 ከ20/10/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ 9% ጋር እንዲከፍል ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም በሰጠው መልስ፡- ለመኪናው ኢንሹራንስ የተገባለትና ከአደጋ ቦታም እንዲነሳ የተደረገ ቢሆንም ስለአደጋው ፖሊስ ሪፖርት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ በመኪናው ላይ አደጋ በደረሰበት ጊዜ 18 ሰዎችን ጭኖ የነበረ መሆኑን ገልጿል፡፡ በከሳሾችና እና በከሳሽ መካከል የተደረገው የውል ስምምነትም በኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ የተመሰረተ ሲሆን አደጋው የደረሰበት መኪናም ሹፌሩን ሳይጨምር የመጫን አቅሙ 11 ሰው ሆኖ እያለ 7 ሰዎችን በትርፍ ጭኖ በጠቅላላው 18 ሰዎችን ጭኖ የደረሰ አደጋ መሆኑና አደጋውም የደረሰው ከአቅም በላይ በመጫኑ ምክንያት ፍሬን እንዳይታዘዝ በማድረጉና መሪውንም ወደሚፈለግበት መምራት ባለመቻሉ ነው፡፡ ኢንሹራንስ ዋስትና የተገባለት ተሽርካርካሪ መጫን ከሚችለው አቅም በላይ ትርፍ በመጫን አደጋ በደርሰበት ጊዜ



www.chilot.me

በኢንሹራንስ ፖሊሲ አንቀጽ 6 በተመለከተው መሰረት አደጋ የደረሰበትን መኪና ዋጋ ተከሳሽ የመክፈል ግዴታ ስለማይኖረው ክሱ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከተከሳሽ ድርጅት እና ከኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ድርጅት አንድ አንድ የሰርቬይ ባለሙያ በማስቀረብ ሙያዊ ምስክርነታቸውን በመስማት እንዲሁም ከትራፊክ ፖሊስ ስለአደጋው የቀረበውን ሪፖርት ከባለሙያዎቹ የምስክርነት ቃል በማገናዘብ እና በመመርመር በሰጠው ውሳኔ፡- ከአቅም በላይ መጫን አደጋ አያስከትልም ማለት የማይቻል ቢሆንም ከትራፊክ ፖሊስ  የቀረበው የመኪና አደጋ ሪፖርት ለአደጋው መድረስ መንስኤ የሆነው በፍጥነት በማሽከርከርና በማንቀላፋት መሆኑን ከሚገልጽ ውጪ አደጋው መኪናው ከአቅም በላይ በመጫኑ ምክንያት መሆኑን የማያመለክት ስለሆነና ሪፖርቱም አደጋ በደረሰበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ መሰረት አድርጎ የቀረበ በመሆኑ የሚታመን ነው፤በሌላ በኩል ተከሳሽ አደጋ የደረሰው ከአቅም በላይ መኪናው በመጫኑ ነው ቢልም በከሳሾችና ተከሳሽ መካከል በ30/08/2012 የተፈረመው የኢንሹራንስ ውል ስምምነት ኢንሹራንስ የተገባለት መኪና ከአቅም በላይ ወይም ትርፍ ሰው ጭኖ ቢገኝ ካሳ አይከፈልም የሚል ባለመሆኑ የውል ስምምነቱ ለሚደርሰው የሞት አደጋ፣የአካል ጉዳት እንዲሁም በንብረት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ካሳ የሚከፈል መሆኑን ስለተስማሙና ይህም ስምምነት በፍ/ህ/ቁ/1731(1) መሰረት ህግ ሆኖ ስለሚያስገድድ ተከሳሽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ፣ለዳኝነት የተከፈለውን እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ሊከፍል ይገደዳል ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታም የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦች ፡-ጉዳት የደረሰበት ሚኒባስ መኪና የኢንሹራንስ ሽፋን ዋስትና የተገባለት ቢሆንም በወቅቱ 18 ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓጓዝ መንገድ ዳር ተበላሽቶ ከቆመ መኪና ጋር ተጋጭቶ 14 ሰዎች ሞተው 4 ሰዎች የተጎዱ መሆኑን የአድአ ወረዳ ፖሊስ በደብዳቤ ከገለጸው የተረጋገጠ ሲሆን በኢንሹራንስ ውሉም ሆነ በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በተሰጠው የባለቤትነት ማረጋጫ ደብተር(ሊብሬ)የመኪናው የመጫን አቅም 11 ሰው ብቻ መሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ መኪናው 7 ሰዎችን በትርፍነት ጭኖ ጉዳቱ በመድረሱ በኢንሹራንስ ኩባንያ ፖሊሲ ጠቅላላ ማግለያ በሚለው ክፍል ተራ ቁጥር 6 ‹‹ በኢንሹራንስ ውሉና ከሚመለከተው አካል በተሰጣቸው የባለቤትነት ማረጋጫ ደብተር ላይ ከተገለጸው ሰው ብዛትና መኪናው ካለው መቀመጫ ብዛት በላይ ጭኖ ለሚደርስ አደጋ ኢንሹራንስ ኩባንያው ማንኛውንም ክፍያ ለመክፈል ኃላፊነት አይኖርበትም ›› ስለሚል ይህንንም ግዴታ ኢንሹራንስ ሰጭም ሆነ ኢንሹራንስ ገቢው በንግድ ህግ አንቀጽ 657(2-3) መሰረት በተጨማሪ የማግለያ ውል የግዴታ ስምምነት የተፈራረምን ስለሆነ አመልካች የጉዳት ካሳውን ለመክፈል እንደማልገደድ በመጠቀስ ያቀረብኩትን ክርክር ፍርድ ቤቶቹ ሳይቀበሉት ያለፉት አግባብነት የለውም፤

አንድ መኪና ከአቅም በላይ ጭኖ ሲጓዝ እንደፈለጉት መሪም ሆነ ፍሬን መያዝ መቆጣጠር እንደማይቻል እና ከአቅም በላይ መጫን ለአደጋ ምክንያት እንደሚሆን የባለሙያ ምስክርነት በተሰጠበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ከአቅም በላይ መጫን ለአደጋ ምክንያት አይሆንም፣እንዲሁም በኢንሹርነስ ፖሊሲው ላይ ከሳሾች ግዴታ ገብተው

የፈረሙት ነገር ስለሌለ የመኪናውን ግምት፤የጠበቃ አበል 10 ፐርሰንት ወጪ ኪሳራ ብር 500 ጨምሮ አመልካች ሊከፍል ይገባል ሲሉ የወሰኑት ተቀባይነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡-በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በተደረገው የኢንሹራንስ ዋስትና ውል የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና ትርፍ ሰው ከጫነ አመልካች ኃላፊነት አይኖረውም በሚል አልተስማማንም፣ በዚህ መልኩ ስለመዋዋላችን የሚገልጽ ማስረጃም አመልካች ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አላቀረበም፤አመልካች የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው በማለት ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበውም የፖሊሲ ቁጥር የሌለው ለማስታወቂያ ተብሎ የተዘጋጀውን ብሮሸር በመሆኑ ተጠሪዎችን የሚያስገድድ አይሆንም፤ እንዲሁም በተሸርከርካሪው ላይ አደጋ የደረሰው በፍጥነት በመንዳትና በአሽከርካሪው ማንቀላፋት ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ የትራፊክ ፖሊስ ማስረጃ የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ አመልካች አደጋው የደረሰው ትርፍ ሰው በመጫኑ ምክንያት ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች ላቀረቡት መልስም አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- ጉዳት ለደረሰበት መኪና ተጠሪዎች የጠየቁትን ገንዘብ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የንብረት ኢንሹራንስ ውል ስለመደረጉ በግራ ቀኙ የታመነ ጉዳይ ሲሆን አመልካችም የተጠሪዎች ንብረት ለሆነው ጉዳት ለደረሰበት ሚኒባስ መኪና የብር 350,000 የዋስትና ሽፋን ሰጥቷል፡፡ መኪናውም በደረሰበት አደጋ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን የግራ ቀኙን ወገን እያከራከራቸው የሚገኘው ደግሞ ኢንሹራንስ ሰጪው ለደረሰው ጉዳት በሰጠው ዋስትና ሽፋን መሰረት ኃላፊ የመሆኑና ያለመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በመኪናው ላይ ለደረሰው ጉዳት የዋስትናውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለብኝም ሲል በዋናነት የሚከራከረው መኪናው ላይ አደጋ ሊደርስ የቻለው የመጫን አቅሙ 11 ሰዎች ሆኖ ሳለ በትርፍነት ሰባት ሰዎችን በመጫኑ ምክንያት ክብደት በመጨመሩ የመኪናው መሪና ፍሬን እንደልብ ባለመታዘዛቸው ነው፡፡ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ከተቀመጡት ጠቅላላ የማግለያዎች በአንቀጽ 6 የኢንሹራንስ ዋስትና ሽፋን የተሰጠው መኪና መጫን ከሚገባው የሰው ቁጥር በላይ በትርፍነት ጭኖ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ አመልካች ኩባንያ የዋስትናውን ገንዘብ የመክፈል ሀላፊነት እንደሌለበት ተመልክቷል በሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ግን በኢንሹራንስ ፖሊሲው ተጠቅሷል በሚል አመልካች ቢከራከርም በማስረጃነት የኢንሹራንስ ፖሊስ ነው በማለት ያቀረበው ለማስታወቂያ ሥራ ተብሎ የተዘጋጀ ብሮሸር እንጂ ትክክለኛ የኢንሹራንስ ፖሊሲ አይደለም፣እንዲሁም አመልካች የጠቀሰው የማግለያ ምክንያትም አመልካችና ተጠሪዎች በገባነው የኢንሹራንስ ውል ያልተጠቀሰ በመሆኑ የሚያስገድደን አይደለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የንብረት ኢንሹራንስ ውል ከተለያዩ የውል አይነቶች አንዱ ሲሆን ውሉም ህጋዊ የሆኑ ተግባራት በሚከናወኑበት ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በዋስትናው ሽፋኑ መሰረት ለመካስ በማሰብ ሊደረግ የሚገባ ነው፡፡

በፍ/ህ/ቁ/1678 (ለ) እንደተመለከተው አንድ ውል በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ ለማከናወን ሊደረግ ይገባል፡፡ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የንብረት ኢንሹራንስ ውልም በህጉ መሰረት የተደረገ ነው፡፡ ሆኖም ህጋዊ ውል የሚደረገው በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደውን ድርጊት ወይም የህግ ክልከላ የተደረገበትን ጉዳይ በማከናወን ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ወይም በሚኖረው ፍላጎት መነሻ ሊሆን አይገባም፡፡ የተጠሪዎች መኪና ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውል መሆኑ የታመነ ጉዳይ ሲሆን ይህንኑ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜም የትርንስፖርት አዋጅ፣ደንብና መመሪያዎችን መከተል ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን አደጋው በደረሰበት ወቅትም መኪናው መጫን ከሚገባው 11 ሰዎች በላይ 7 ሰዎችን ጭኖ ሲጓዝ እንደነበር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን ተጠሪዎቹም ቢሆኑ መኪናው ትርፍ ሰዎችን አልጫነም ሲሉ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ መኪናው ከጫናቸው 18 ሰዎች ውስጥም በወቅቱ 14 ሰዎች መሞታቸው ከክርክሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ መኪናው በህጉ ከተቀመጠው የሰው ቁጥር በላይ መጫኑ የትራንስፖርት ህጉን የሚጥስ ሲሆን ህጉ ተጥሶ ከተፈቀደው የሰው ቁጥር  በላይ ሰዎችን ጭኖ ሲጓዝ ለደረሰው አደጋ አመልካች የዋስትናውን ሽፋን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት ሊኖረው አይችልም፡፡

በአጠቃላይ በመኪናው ላይ ጉዳቱ የደረሰው ያለውን የትራንስፖርት ህግ በመጣስ ከወንበር በላይ በትርፍ 7 ሰዎችን ጭኖ ስለመሆኑ ለሥር ፍርድ ቤት የትራፊክ ፖሊስ በማስረጃነት ከላከው ሪፖርት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በመንገድ ትራንስፖርት ህግ ከሚፈቅደው ውጪ ትርፍ ሰዎችን ጭኖ ሲጓዝ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ሆኖ ባለበት የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች በኢንሹራንስ ውሉ መሰረት የዋስትና ሽፋን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ሲሉ  የወሰኑት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/15121 በቀን 14/08/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/161389 በቀን 15/08/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. ተጠሪዎች የትራንስፖርት ህጉን ጥሰው ከወንበር በላይ ትርፍ ሰዎችን ጭነው መኪናው እየተጓዘ በመኪናቸው ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች የዋስትናውን የሽፋን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አይኖርበትም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

# አፈፃፀም



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 78206

ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካቾች**፡-1. ወ/ሮ ዩስራ አብዱልሙኢን
2. አቶ ሁሴን አብዱልሙኢን
3. ዶ/ር አህመድ አብዱልሙኢን
} ጠበቃ መሰረት ስዩም ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ አብዱልቀኒ አብዱልሙኢን ጠበቃ ጥጋቡ ጌጤ ቀረቡ

**መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 የተመለከተውን ድንጋጌ አተገባበር የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካቾች በየመን አገር ፍ/ቤት በተሰጠ ፍርድ ባለመብት መሆናቸውን ገልፀው ይህንኑ በውጭ አገር ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያስፈጽምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ሲሆን የአሁን ተጠሪም የመን አገር በተሰጠው ፍርድ የክርክር ተካፋይ ስላልነበርኩ መብቴን የነካ ፍርድ ስለሆነ ፍርዱ ሊፈፀም አይገባም በማለት ከዚህ በፊት በአመልካቾች ጥያቄ መሰረት ተሰጥቶ የነበረውን ፍርድ ተቃውሟል፡፡ አመልካቾችም ክርክሩ በየመን አገር ሲደረግ ተጠሪው ኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበረ ፍ/ቤቱ ወኪል አቁሞለት በወኪል የክርክር ተከፋይ የነበረ መሆኑንና ይህንንም ክርክር ተጠሪው ማቅረብ የሚችለው ፍርዱን ለሰጠው ለየመን አገር ፍ/ቤት እንጂ ለዚህ ፍ/ቤት አይደለም በማለት መልሳቸውን የሰጡበት ስለመሆኑ የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሰጠው ብይን ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳይ ተመልክቶ በኮ/መ/ቁ 78860 በቀን 17/9/2003ዓ.ም በዋለው ችሎት ከዚህ ቀደም አመልካቾች በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ ይፈፀምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456-461 የተመለከተውን ቅደመ ሁኔታ ያሟላ መሆኑ ታይቶና በፍርድ ባለዕዳነትም የተሰየሙት ወገኖች ያልተቃወሙት ስለሆነ ፍ/ቤቱ በዚሁ መዝገብ በቀን 25/2/02ዓ.ም በዋለው ችሎት በውሣኔው መሰረት እንዲፈፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤቱ የፍርድ ተቃዋሚ ሆኖ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ

358 መሰረት ይፈጽም የተባለው ፍርድ ስህተት አለበት እኔ በክርክሩ ሳልሳተፍ የተሰጠ ፍርድም በመሆኑ መብቴን ተነክቷል በማለት የቀረበው ክርክር ሊቀርብ የሚገባው ጉዳዩን አከራክሮ ፍርዱን በሰጠው በየመን አገር ፍ/ቤት እንጂ ፍርዱ በሚፈፀምበት ፍ/ቤት አይደለም፡፡ ችሎቱ እያየ ያለው የአፈጻጸምን ጉዳይ እንደመሆኑ በዚህ የአፈጻጸም ጉዳይ ሊታይ የሚገባው የክርክር ዓይነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሰረት ፍርዱን ለማስፈፀም ሲባል በተያዘ ንብረት ላይ የሚቀርብ አቤቱታ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ የተቃውሞ ክርክር ያቀረበበት ጉዳይ በየመን ሀገር ፍ/ቤት ፍርድ ያረፈበት ንብረት የሚመለከት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሰረት የሚሸፈን አይደለም፡፡ በመሆኑም ተቃውሞው ተቀባይነት የለውም የሚለውን የፍርድ ትንታኔ ሰጥቶ ከዚህ በፊት እንደየመን አገር ፍ/ቤት ፍርድ ይፈፀም ሲል ሰጥቶት የነበረውን ትዕዛዝ አጽድቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ እኔ በክርክሩ ሳልካፈልበት የተሰጠው ፍርድና ለማስፈፀም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሀ/ መሰረት በሁለቱ አገሮች ፍርድን ለማስፈፀም ስምምነት ሣይኖር በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢት/ያ ፍ/ቤቶች እንዲፈፀም መበየኑ ተገቢ አይደለም ይሻርልኝ በማለት ባቀረበው ክርክር መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 70047 ጥር 30 ቀን 2004ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ፡-

በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢት/ያ ለማስፈፀም የሚቻለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456-461 በተደነገገው መሰረት መሆን ይገባዋል፡፡ በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ/ 458/ሀ/ በኢት/ያና ፍርዱን በፈረደው አገር መካከል ፍርዱን የማስፈፀም ስምምነት ሊኖር ይገባል፡፡ ኢት/ያና የመን በፍርዱ ላይ ማህተም ማድረጋቸው የፍርድ ሰነድ ከየመን ወደ ኢት/ያ ሲገባ የሰነዱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሲባል የተከናወነ የማስተባበል ስራ እንጂ በአገሮች መካከል ፍርድን ለማስፈፀም ስምምነት መደረጉን አያመለክትም፡፡ ስለሆነም ይኸው የህጉ ማሟያ ሣይሟላ የተሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡ በማለት ከወጭና ኪሣራ ጋር ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በዚሁ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በተሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ላይ የአሁን አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡

በዚህ የሰበር ደረጃም ሁለቱም ወገኖች ያላቸውን ክርክር በጽሑፍ አቅርበው ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ ባጭር ባጭሩ በይዘት ደረጃ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥርአት ህጉ የተመለከተው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ በሁለት ዓበይት ምዕራፎች የተመለከተ ሲሆን በምዕራፍ 1 ላይ የተመለከተው በኢት/ያ ግዛት ውስጥ የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች ሲሆን በምዕራፍ 2 ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456 እስከ 461 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ደግሞ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብይን የሚፈፀምበትን ሁኔታ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከዚህ ከህጉ አቀራረጽ መገንዘብ የሚቻለው ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ በይዘቱ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት እንጂ ለአፈጻጸሙ ምክንያትና መነሻ ከሆነው ፍርድ ጋር በተያያዘ የሚነሣን ክርክር ለመጋበዝ ወይም ለማስተናገድ የሚያስችል አይደለም፡፡

ሆኖም ምንም እንኳ ጉዳዩ በይዘቱ የአፈጻጸም ጉዳይ ቢሆንም ይፈፀም የተባለው ፍርድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ከመሆኑ የተነሣ ይህንኑ ፍርድ በኢት/ያ ፍ/ቤቶች ዕውቅና ተሰጥቶት ለማስፈፀም የሚቻለው

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 የተመለከቱትን ቅደመ ሁኔታዎች መሟላታቸው የተረጋገጠ እንደሆነ ብቻ መሆኑን በግልጽ ተመልክቷል፡፡

እነዚህ በዚሁ ድንጋጌ የተመለከቱት ፍርዱን ለማስፈፀም የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውንና አለመሟላታቸውን አስመልክቶ ክርክር በቀረበ ጊዜም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 459 እና 460 በተደነገገው መሰረት ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርበውን ሙግት ሰምቶ ዳኝነት የሚሰጠው እራሱ የፍርዱን አፈጻጸም የያዘው ፍ/ቤት ነው፡፡

በህጉ የተመለከተው ትክክለኛ የጉዳዩ አካሄድ ይህ ሆኖ እያለ የአፈጻጸም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የክርክር አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 አንጻር በማየት ጉዳዩን ሰምቶ የመወሰን ስልጣኑ እና የዳኝነት ስራ ተግባሩ መሆኑ እየታወቀ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ፍርዱን በሰጠው በየመን አገር ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚገባው እንጂ በዚህ ፍርዱን ለማስፈፀም ሲባል የአፈጻጸም ጉዳዩ በቀረበለት ፍ/ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠው ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን እና ከላይ የተመለከቱትን ስነ ስርአታዊ ድንጋጌዎች ትክክለኛ አፈጻጸም የተከተለ አይደለም፡፡

የአሁን ተጠሪም በመቃወሚያነት ካቀረባቸው ክርክሮች መካከል ይፈፀም በተባለው ፍርድ በተሰጠበት ጊዜ የመከራከር መብቴ አልተጠበቀም ይህንኑ ፍርድ በኢትዮጵያ አገር ፍ/ቤቶች ለማስፈፀም የሚቻል ስለመሆኑ በሁለቱ አገሮች መካከል ስለዚሁ ጉዳይ የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ አልተረጋገጠም የሚሉት ሁለቱ የመከራከሪያ ነጥቦች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 /ሀ/ እና /ሐ/ የሚወድቁ ሲሆኑ ሌሎች በተለይም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በኢትዮጵያ በሚገኙ የኃይማኖት ፍ/ቤቶች ታይቶ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ በየመን ሀገር ፍ/ቤት ሊስተናገድ አይገባም የሚለው ክርክሩ በዚህ በተያዘው የአፈጻጸም ጉዳይ ቀርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት ስርአት አልተዘረጋም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 ስር የተመለከቱትን ነጥቦች በይዞታቸው ማየት እንደሚቻለው በአለም አቀፍ ህግ የሁለት አገሮችን ግንኙነት ከሚገዛው የአለም አቀፍ ህግ መርህና በኢትዮጵያ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው የሲቪልና የፖለቲካ አለም አቀፍ ስምምነት በአንቀጽ14 ስር የተመለከተውን በህግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ፊት የመዳኘት እና በክርክር በእኩል አይን የመታየት መብትን ለማስከበር ሲባል የተመለከቱትን መብቶች ተከብረውና ተጠብቀው የተሰጠ ፍርድ መሆኑ ታውቆ ማስፈፀም እንዲቻል በኢትዮጵያ ዝርዝር ህግ የተመለከቱ አንኳር ነጥቦች ናቸው እንጂ ማንኛውንም የክርክር ነጥቦች ባካተተ መንገድ የተቀረፀ ባለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው የክርክር ነጥብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ጋር የተገናኘ መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ የሚገባው በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህም አንጻር የአሁን ተጠሪ በቁጥር 458/ሀ/ የተመለከተውን ድንጋጌ ተንተርሶ ፍርዱን በኢትዮጵያ አገር ባሉ ፍ/ቤቶች ለማስፈፀም የሚያስችል በሁለቱ አገሮች ተመሣሣይ ስምምነት ስለመኖሩ አልተረጋገጠም በማለት ሲከራከር የአሁን አመልካቾች በበኩላቸው በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ በሁለቱም አገሮች በሚመለከታቸው ክፍሎች ተረጋግጦ የገባ መሆኑን የሚያመለክቱ ሰነዶችን ከማቅረባቸውም ባሻገር ስለዚሁ ጉዳይ ተጨማሪ ማስረጃ ይቅረብልን በማለት እንደጠየቁ ከጉዳዩ አመጣጥ ተረድተናል፡፡ ይህ ጉዳይ በአገር ደረጃ የሚደረግ ስምምነት በመሆኑ ይህ አይነት ስምምነት

ስለመኖሩና አለመኖሩ የማረጋገጥ ግዴታ እንደማንኛውም በተከራካሪ እጅ እንደሚገኝ ማስረጃ ተቆጥሮ መቅረብ በሚገባው ጊዜና አኳኋን ካልቀረበ በቀር ተቀባይነት የለውም የሚል የጠበቀ የስነ ስርዓት መስፈርትን የሚከተል አይደለም ይልቁንም ይህ አይነቱ የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345(1)ለ እንደተመለከተው የሚቀርበው ማስረጃ ለጉዳዩ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል ከመሆኑ በላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተገቢ መስሎ ቢታየው በማናቸውም ምክንያት በተከራካሪው ወገን ጠያቂነትም ሆነ በእራሱ አነሣሽነት ይኸው አይነት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ለመፍቀድ ለማዘዝ ስልጣን ያለው በመሆኑ በዚህ አግባብ ይኸው የሁለቱ አገሮች ስምምነት ያለ መሆኑንና አለመሆኑን ለሚመለከታቸው መንግስታዊ ክፍሎች በትዕዛዝ ማጣራት እየተገባው በአመልካቾች የቀረበው ማስረጃ ስለማስረጃው ትክክለኛነት ከሚያረጋግጥ በቀር ስምምነት ስለመኖር ለማስረዳት ብቃት የለውም በሚለው ብቻ ተገድቦ የሰጠው ዳኝነት የማስረጃ አቀባበል ስርዓትን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ረገድ የአሁን ተጠሪ የተጨማሪ ማስረጃው ጥያቄ ስርዓቱን ጠብቆ በጊዜው የቀረበ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚለውም ክርክሩ በተመሣሣይ ምክንያት የህግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሀ/ በተመለከተው ድንጋጌ አፈጻጸም ላይ ብቻ ተወስኖ የሰጠው ዳኝነት በመሆኑ ምክንያት የአሁን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሐ/ መሰረት ይፈፀም በተባለው ፍርድ አሰጣጥ ሂደት የክርክር ተካፋይ አልነበርኩም የመደመጥ መብቴ አልተከበረም በሚል ባነሳው ክርክር ሳቢያ አመልካቾችም በፍርዱ ሂደት ተጠሪው ኢት/ያ ውስጥ የነበረ በመሆኑ በሀገሪቱ ህግ መሰረት ወኪል በፍ/ቤቱ ቆሞለት የታየ ጉዳይ ነው በማለት በመከራከራቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሐ/ በዝምታ እንዳለፈው ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፍርድ ተረድተናል፡፡ ፍርድ ቤቱ ደርሶበት እንደነበረው መደምደሚያ ፍርዱን በዚህ አኳኋን መስጠት የሚቻል ሰለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 247/4/ እና 182/3/ የተደነገገ ቢሆንም በፍርዱ መሰረት አድርጎ በያዘው የህግ ጭብጥ ላይ የሰጠው ዳኝነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ መሰረት ያለው ሆኖ ባለመገኘቱ የአሁን ተጠሪ በተደራቢነት አቅርቦት የነበረውን ነገር ግን በዝምታ ያለፈው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሐ/ ጋር በተያያዘ የተነሣውን የመደመጥ መብት የመከበርና ያለመከበር ሚሚያ ሁኔታንም በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ እንደገና ተመልክቶ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 70047 ጥር 30 ቀን 2004ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. በፍርድ ሀተታው ላይ እንደተገለፀው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሀ/ እና 458/ሐ/ በተመለከተ ግራ ቀኙ ባቀረቡት ክርክር ላይ ብቻ ተወስኖ እንዲሁም በቁጥር 458/ሀ/ን በሚመለከት በአሁን አመልካቾች በኩል የቀረበውን የተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ጥያቄ ተቀብሎ በአመልካቾችም ሆነ በእራሱ አነሣሽነት ማስረጃውን በማየትና በማስቀረብ አስፈላጊውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መዝገቡን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት**

## የመስማሚያ ሀሣብ

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምጽ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን በደረሰበት መደምደሚያና በሰጠው ውሣኔ እስማማለሁ፡፡ ሆኖም ጉዳዩ መመለስ ያለበት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሣይሆን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆን ይገባዋል የሚል ሀሣብ ያለኝ በመሆኑና ጉዳዩ ሲመለስ በጭብጥነት ሊያዙ ስለሚገቡ ጉዳዬች ከአብላጫው ድምጽ የምለይባቸው ነጥቦች ያለ በመሆኑ ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ ጽፌለሁ፡፡

1. የመጀመሪያውን የመስማሚያ ኃሣቤ መነሻ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ብይን ይዘትና ባህሪ ነው፡፡ አመልካቾች በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥቅምት 25 ቀን 2002ዓ.ም ውሣኔ ሲሰጥ የአሁን ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 459 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ቀርቦ አስተያየቱን አልሰጠም፡፡ ተጠሪ በእሱ በኩል የሚቀርቡ መከራከሪያዎች ሣይሰሙ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውሰጥ ተፈጻሚ እንዲሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 460/1/ መሰረት የሰጠው ውሣኔ ተሰርዞ የመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባዋል ወይም አይገባውም? የሚለው ጭብጥ እሱ ባለበት ታይቶ እንዲወሰንለት ጥቅምት 10 ቀን 2003ዓ.ም የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ያቀረበ መሆኑን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 78860 ግንቦት 19 ቀን 2003ዓ.ም ከሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በክርክሩ ተካፋይ ሣይሆን የአመልካቾችን አቤቱታ በመቀበል በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ተፈጻሚ እንዲሆን ጥቅምት 25 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በመሰረታዊ ይዘቱና ባህሪው በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 458 የተደነገጉትንና ሌሎች አስፈላጊ መስፈርቶች የሚያሟላ በመሆኑ ፍርዱ በኢትዩጵያ ግዛት ክልል ባሉ ፍርድ ቤቶች ሊፈፀም የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥና በፍርድ ዕውቅና ለመስጠት የተሰጠ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 460

ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጸ 2 መሰረት የተሰጠ ውሣኔ ነው፡፡ ይህ ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ለመቃወምና እንዲሰረዝ ለማድረግ የሚቻልበት ስርዓት ከፍተሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 እስከ ፍታሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 460 ተዘርግቷል፡፡

3. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የተቃወመው በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ሊፈፀም የሚችል ነው በማለት ፍርድ ቤቱ ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 460 የሰጠውን ውሣኔ መሆኑን ሣያገናዝብና በየመን አገር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ሊፈፀም የሚችል መሆኑን የሚረጋገጥና ዕውቅና የሚሰጥ ውሣኔ እንጂ የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዳልሆነ ሣይገነዘብ ተጠሪ መቃወሚያውን ማቅረብ ያለበት ፍርዱን ለሰጠው የየመን አገር ፍርድ ቤት እንጂ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም፡፡ እንደዚሁም ክርክሩ የአፈጻጸም ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ተጠሪ ጥቅምት 25 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠሁትን የአፈጻጸም ውሣኔ መቃወም አይችልም የሚል ይዘት ያለው ብይን ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡

4. ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥቅምት 25 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በመሰረዝ እኔ ባለሁበት ጉዳይ ታይቶ እንዲወሰን ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ ማድረጉን በመቃወም ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች እንዲፈፀምላቸው እየጠየቁ ያሉት በየመን አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዩጵያ ሊፈፀም ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም በማለት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358/ሀ/ መሰረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በእኔ እምነት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ፍ/ቤቱ ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ያቀረበውን ክርክር በመቀበልና የአመልካቾችን ክርክርና ማስረጃ በመቀበል በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠት አለበት ወይም የለበትም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት የስር ፍ/ቤት የተጠሪን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻና የአመልካቾችን ክርክር በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት ጉዳዩን መመለስ ነበረበት፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍ/ቤት ወደ ይዘቱ ገብቶ ያላየውንና ውሣኔ ያልሰጠበትን ጭብጥ ማለትም በየመን አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዩጵያ ሊፈፀም ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የሰጠው ውሣኔ አመልካቾች በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ሊፈፀም ይገባል የሚሉበትን የተሟላ ክርክርና ማስረጃ የማቅረብ መብትና ተጠሪም በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ሊፈፀም አይገባውም የሚልበትን የተሟላ ክርክርና ማስረጃ የማቅረብ መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ እንደዚሁም በዚህ ጭብጥ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ተከራካሪዎቹ ሊኖራቸው የነበረውን የይግባኝ መብት ያጣበበ ነው  የሚል ሀሣብ አለኝ

5. ከዚህ አንጻር ከሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካቾች በኢትዩጵያ ውስጥ እንዲፈፀምላቸው የጠየቁት የየመን ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ሊፈፀም የሚችል ነው ወይስ አይደለም?  በሚለው ጭብጥ ላይ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት መመለስ ነበረበት፡፡ ይህንን አለማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት በሰበር በመሻር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዩጵያ ውስጥ ሊፈፀም ይችላል ወይስ አይችልም? በሚለው ጭብጥ ላይ የአመልካቾችንና የተጠሪን የተሟላ ክርክርና

ማስረጃ ሰምቶ እንዲወሰን ሊመለስለት ይገባል፡፡ አብላጫው ድምጽ ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ችሎት መመለሱ አመልካቾችና ተጠሪ በስር ፍ/ቤት የተሟላ ክርክርና ማስረጃ የማቅረብ መብታቸውን የሚያሣጣና የይግባኝ መብታቸውንም የሚያጣብብ ነው የሚል ሀሣብ ያለኝ በመሆኑ ጉዳዩ መመለስ የሚገባው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ችሎት ሣይሆን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆን ይገባዋል በማለት ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ ጽፌለሁ፡፡

6. ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ሁለተኛው ምክንያት አብላጫው ድምጽ ጉዳዩን ወደ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የመለሰው አመልካቾች በኢትዩጵያ ውስጥ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት በየመን አገር የተሰጠ ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358/ሀ/ እና /ሐ/ ድንጋጌዎች የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማጣራት ውሣኔ እንዲሰጥበት በማዘዙ ነው፡፡ በእኔ በኩል ይግባኝ ሰሚው ችሎት በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ከ/ሀ/ እስከ ከ/ሠ/ የተደነገጉትን ሁሉንም መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማጣራትና በማረጋገጥ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባል የሚል ሀሣብ አለኝ፡፡ በተለይም ተጠሪ አመልካቾች በየመን አገር በተሰጠ ፍርድ የፍርድ ባለመብት ሁነንበታል የሚሉት ጉዳይ በኢትዩጵያ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበትና በፍርድ ያለቀ ነው የሚል መቃወሚያና ክርክር እንዳቀረበ አብላጫው ድምጽ በውሣኔው ካሰፈረ በኂላ ይህን ጉዳይ በኢትዩጵያ ሸሪዓ ፍ/ቤት ውሣኔ ያገኘ ነው የሚለው መቃወሚያ ሊስተናገድ የሚችልበት ስርዓት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጠር 458 እንዳልተዘረጋ ውሣኔው በገጽ 17 በመጨረሻው ፖራግራፍ በመግለጽ የሰጠው ምክንያትና የሕግ አተረጓጎም አልተቀበልኩትም፡፡

7. ተጠሪ ጉዳዩ በኢትዩጵያ የሸሪያ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘና በፍርድ ያለቀ ነው በማለት ያቀረበው መከራከሪያ በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ ይፈፀምልን በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን ጥያቄ ለመቃወምያ ሊሆን የሚችል መሰረታዊ መከራከሪያ ነው የሚል ሀሣብ አለኝ፡፡ በአገራችን በፍርድ በተቋጨ ጉዳይ ሌላ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5/1/ ተደንግጓል፡፡ ይህም የአገሪቷ ፍ/ቤቶች በሕግ በተሰጣቸው የዳኝነት ስልጣን መሰረት በማድረግ አከራክረው የመጨረሻ ውሣኔ በሰጡት ጉዳይ የውጭ አገር ፍ/ቤቶት የሰጡት ውሣኔ አለና ይፈፀምልን የሚል ጥያቄ ቢቀርብ የኢትዩጵያ ፍ/ቤቶች ይህንን ጥያቄ የመቀበል የአገሪቱ ፍ/ቤቶች በፍርድ የሰጡት ጉዳይ ላይ የውጭ አገር ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ ተፈጻሚ እንዲሆን የሚፈቅዱበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ በእኔ እምነት ጥያቄው ከጅምሩ የአገሪቱን ፍርድ ቤቶች ብሄራዊ የዳኝነት ስልጣን የሚጋፋ ስለሆነ ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ነው የሚል ሀሣብ አለኝ፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ጉዳዩ በሸሪዓ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው የሚለውን ክርክር የቀረበ ቢሆንም ጉዳዩ በኢትዩጵያ የሸሪዓ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሰጥቶበታል ወይስ አልተሰጠበትም? ጉዳዩ በሸሪዓ ፍ/ቤት

ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ አመልካቾች በዚያው ጉዳይ በየመን አገር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች በመያዝ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማጣራትና በማረጋገጥ ውሣኔ እንዲሰጥበት የሰበር ችሎት መመሪያ /ትዕዛዝ/ ሊሰጥ ይገባዋል የሚል ሀሣብ አለኝ፡፡ ስለመሆኑም የሰበር ችሎት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 70047 ጥር 30 ቀን 2004ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሻርና ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን በደረሰበት መደምደሚያ የምስማማ ቢሆንም ከላይ በዝርዝር በገለጽኳቸው ነጥቦች ከአብላጫው ድምጽ የምለይ በመሆኑ ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ አስፍሬአለሁ፡

**የማይነበብ የአንድ ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/ጥ**

የሰ/መ/ቁ. 88867

ታህሳስ 28 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች:-** ሪዩስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማህበር

**ተጠሪ:-** የአክሱም ኮንስትራክሽን ባለቤት አቶ ጌታሁን ሁሴን

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ የፍርድ ባለእዳ የሆነ ንብረት ከአንድ በላይ በሆኑ የፍርድ ባለገንዘቦች ለፍርድ አፈፃፀም በእያንዳንዳቸው በተናጠል እንዲከበር ተደርጐ በሚገኝበት ጊዜ አፈፃፀሙ በንብረቱ ላይ ሊቀጥል የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ባስከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ መነሻነት ነው፡፡ የጉዳዩ አጀማመርም አመልካች በተጠሪ ላይ የገንዘብ ክፍያ አስፈርደው የፍርድ ባለመብት ሲሆኑ አፈፃፀሙም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ 185082 በሆነው ቀርቦ እና አመልካችም ይሄንኑ ፍርድ ለማስፈፀም ሲባል የተለያዩ የፍርዱን ባለእዳ ንብረቶችን ያስከበረ ቢሆንም ሆኖም ግን እነኝህ ንብረቶች በሌላ የፍርድ ቤቱ መዛግብት ላይ በሌሎች ፍርድ ባለገንዘቦችም የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው በመሆኑ የአሁኑ አመልካች እግዱን አስነስተው ሲቀርቡ ወይም ሌላ የፍርድ ባለእዳ ንብረት አፈላልገው ሲቀርቡ አፈፃፀሙ ሊቀጥል ከሚችል በቀር በሌላ ጉዳይ የእግድ ትዕዛዝ በተሰጠባቸው ንብረቶች ላይ የይሸጡ ትዕዛዝ መስጠት አይቻልም በማለት የፍርድ ባለመብቱን ጥያቄ ባለመቀበል የአፈፃፀም መዝገብ ጉዳዩን ሲመራ በነበረው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በትዕዛዝ እንዲዘጋ ተደርጓል፡፡

የአሁኑ አመልካችም በትዕዛዙ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተቀባይነት አላገኘም አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም አመልካች ያስከበረውን ንብረት በሌሎች መዛግብት ላይ ሌሎች የፍርድ ባለመብቶችም የእግድ ትዕዛዝ አሰጥተውበት ከሆነም ፍ/ቤቱ እነዚህን ፍ/ባለመብቶች አስቀርቦ በመመርመር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 403 ድንጋጌ ይዘት አኳያ በአፈፃፀም የተያዘውን ንብረት ለመከፋፈል የሚያበቃ ውሳኔ ካላቸው እንደየገንዘባችን መጠን ንብረቱ ተሸጦ እንድንከፋፈል መደረግ ሲገባ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይችልም በማለት ፍርዱ ሳይፈፀም የአፈፃፀም መዝገቡን መዝጋቱ በአግባቡ ባለመሆኑ የሥር

ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ ተሽሮ አፈፃፀሙ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 403 ድንጋጌ ይዘት አኳያ እንዲፈፀም ይታዘዝልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እና በቃልም በችሎት እንዲሰሙ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም በበኩላችን አመልካች በሌላ መዛግብት ላይ በሌሎች ፍርድ ባለመብቶች በንብረቱ ላይ የተሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ካላደረገ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይችልም ተብሎ የአፈፃፀም መዝገቡ በስር ፍ/ቤቶች መዘጋቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪ በ1993 ዓ/ም ወደ ብር 1,172,503.06 (አብዛኛው ገንዘብ በ10.5% እና የተወሰነው ቀሪ ገንዘብ ደግሞ በ9% ከሚታሰብ ወለድ ጋር) ለአመልካች ይክፈል ተብሎ ፍርድ የተሰጠበት መሆኑን፣ አመልካችም ይሄንኑ ፍርድ ለማስፈፀም ሲባል የፍርድ ባለእዳ የሆኑ የተለያዩ ንብረቶችን የዕግድ ትዕዛዝ ሲያሰጥባቸው የቆየ ቢሆንም እዳው እስከአሁንም ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ አለመጠናቀቁን፣ በመሆኑም የፍርድ ባለመብቱ በፍርድ ባለእዳ ባለቤት በወ/ሮ እፀገነት ታዬ ስም በካርታ ቁጥር 32435 ተመዝግቦ የሚገኘውንና የቤት ቁጥሩ 2089 የሆነውን መኖሪያ ቤት በአፈፃፀም ተሸጦ እዳው እንዲከፈለው ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን፣ ሆኖም ግን ይህ ንብረት ሌላ ባለገንዘብ በሆነው አንበሳ ኢንሹራንስም በተመሳሳይ ፍ/ቤት አፈፃፀም መ/ቁ 1251/92 በሆነው መከበሩንና እንዲሁም ይሄው መኖሪያ ቤት በዳሽን ባንክም በብድር ለተሰጠ እዳ በመያዣ ውል መያዙንም ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ችሎትም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ ጉዳዩን ከህጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

በመሰረቱ ፍርድ የተፈረደለት ሰው እንደፍርዱ እንዲፈፀምለት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል እና የአፈፃፀሙ ስነ-ስርዓትም የሚመራበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 378 እና የፍርድ አፈፃፀም ጉዳይን አስመልክቶ የተደነገጉ ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት በአንድ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ ፍርዱ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁ የፍርድ ባለገንዘቦች ካሉም አፈፃፀሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 403 ድንጋጌ መሰረት ሊስተናገድ እንደሚችል ህጉ ያመላክታል፡፡ ይሄውም በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ተከብሮ የተያዘ ወይም በፍርድ ቤቱ ዘንድ ተቀማጭ የሆነ ሀብት ከመያዙ ወይም ከመቀመጡ በፊት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በባለሀብቱ ላይ አስፈርደው እንደፍርዱ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁ የፍርድ ባለገንዘቦች ሲቀርቡ ፍ/ቤቱ በፍርዱ መሰረት ያለመፈፀሙን ካረገገጠ በኋላ ተገቢውን ኪሳራ እና ወጪ ቀንሶ የተያዘውን ሀብት በውሳኔው መሰረት እንዲከፋፈሉ ይደረጋል በሚል በተጠቃሹ ድንጋጌ ስር በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በተጠሪ ላይ የገንዘብ እዳ በ1993 ዓ.ም አስፈርደው እና ገንዘቡም ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት በአፈፃፀም ተሸጦ እንዲከፈለው እየጠየቀ ያለ ሲሆን ሌላኛው የፍርድ ባለገንዘብ የሆነው አንበሳ ኢንሹራንስም ከዚህ የተለየ ነው በሚል ከግራ ቀኙ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ንብረቱም በፍ/ቤቱ ተከብሮ የተያዘ መሆኑ እስከተገለፀ እና እንዲሁም በድንጋጌው ስር የተመለከቱት ሌሎች መስፈርቶችም እስከተሟሉ ድረስ አመልካችን ጨምሮ የሁሉም የፍርድ ባለመብቶች የአፈፃፀም ጥያቄ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 403

ድንጋጌ ይዘት አኳያ በንብረቱ ላይ ቀጥሎ ሊስተናገድ ይገባል እንጂ አመልካች ሌላ የፍ/ባለመብት በሌላ የፍ/ቤቱ አፈፃፀም መዝገብ ላይ ያስጠውን የእግድ ትዕዛዝ አስነስቶ ካልቀረበ በቀር አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይችልም መባሉ የስነ-ስርዓት ህጉን የተከተለ አካሄድ ሆኖ አላገኘነም፡፡ በሌላ በኩል በንብረቱ ላይ የመያዣ ውልን መነሻ በማድረግ ከሌሎች ፍርድ ባለገንዘቦቹ የተለየ ወይም የቀዳሚነት መብት አለን የሚሉ ወገኖችም ካሉ ጥያቄው ሲቀርብ እንደየአግባብነቱ ታይቶ ተገቢው ምላሽ የሚሰጥበት ይሆናል እንጂ አፈፃፀሙ በዚህ ምክንያት ከወዲሁ ሊቀጥል አይችልም መባሉም ተገቢ አይደለም፡፡

ስለሆነም አፈፃፀሙን ሲመራ የነበረው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችን ጨምሮ በተጠሪ ላይ የገንዘብ ክፍያ ፍርድ አሰጥተው እና ገንዘቡም እንዲከፈላቸው የአፈፃፀም ጥያቄ ያቀረቡ የፍርድ ባለገንዘቦችን አስቀርቦ ጥያቄያቸውን በመመርመር እና ጉዳዩንም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 403 ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ አኳያ አገናዝቦ በመመልከት አፈፃፀሙ ቀጥሎ እንደፍርዱ ሊፈፀም በሚቻልበት አኳኋን አፈፃፀሙን መምራት ሲገባ ጉዳዮቹ በየተናጠል በመምራት እና በስተመጨረሻም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው የአፈፃፀም ጉዳይ ሊቀጥል አይችልም በማለት የአፈፃፀም መዝገቡን መዝጋቱ እና ይሄውም በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ መታረም ሲገባ መፅናቱ ስለፍርድ አፈፃፀም የተመለከቱትን የፍ/ብሔር ስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 185082 በ12/2/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 128399 በ7/6/2005 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከዚህ በላይ በፍርዱ ክፍል እንደተጠቀሰው በኮ/መ/ቁ 185082 እንዲቋረጥ የተደረገው የአፈፃፀም ጉዳይ እንዲቀጥል በማድረግ እና ጉዳዩንም ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 403 እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አኳያ አገናዝቦ አፈፃፀሙ እንዲመራ በማድረግ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን የአፈፃፀም ውሳኔ እንዲሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

***መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 89088

ታህሳስ 17 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዩጵያ ንግድ ባንክ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡ -አቶ ሞላ እርቄ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለፍርድ አፈጻጸም የተያዘ ንብረት በሁለተኛ ጊዜ በሀራጅ ሲሸጥ የሚችልበትን ዋጋ መጠን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በኢሊባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባስከፈተው የአፈፃጸም መዝገብ ነው፡፡አመልካች ለተጠሪ ብድር ሰጥቶ በብድር ውሉ መሰረት ባለመከፈሉ ክስ መስርቶባቸው ተጠሪ የተበደሩትን ገንዘብና እና ወለድ ከወጪ እና ኪሳራ ጋር ለአመልካች እንዲከፍሉ ተብሎ ተወስኖ አፈፃጸሙ በዚህ ውሳኔ መሰረት ቀጥሎ የተጠሪ የተለያዩ ንብረቶች ተሸጠው ለእዳው ገቢ የሆኑ ቢሆንም ብር 209,000.00(ሁለት መቶ ዘጠኝ ሺህ ብር) በመቅረቱ ይህንኑ የገንዘብ መጠን ለማስፈጸም ንብረትነቱ የተጠሪ መሆኑ በተረጋገጠና በኢሊባቦር ዞን ጮራ ወረዳ ክልል ውስጥ የሚገኝ ባህርዛፍ አመልካች ለፍርዱ ማስፈፀሚያነት እንዲሸጥለት አመልክቶ ባህርዛፍ በብር 125,500.00(አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ብር) ተገምቶ ቀርቧል፡፡ከዚህም በኋላስ 1ኛ ጨረታ በቀረበው ግምት መሰረት በሐራጅ እንዲሸጥ አፈፃጸሙን የያዘው ፍርድ ቤት በማዘዝ በ1ኛ ጫረታ ሳይሸጥ ቀርቷል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ንብረቱ በሁለተኛ ጫረታ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ሰጥቶ ጫረታው ሳይከናወን ቀርቶ ይህንኑ መነሻ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሲሰጥ ባህርዛፉ በ2ኛ ጨረታ ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች እንዲሸጥ በማለት ጠቅሷል፡፡በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪ ንብረት በሁለተኛ ጫረታ ሲሸጥ ከባለሙያ ግምት በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ እንዲሸጥ ተብሎ መታዛዙ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 428 ድንጋጌን ያላገናዘበ እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ጫረታ የሚካሄድበትን አግባብ በተመለከተ ከፍተኛ ዋጋ ለአቀረበ የሚል ሁኖ እያለ ይኼው ትዕዛዝ በበላይ ፍርድ ቤት ባልተሻሻለበት በራሱ ችሎቱ መለወጡ ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ

መርምረናል፡፡እንደመረመረው እንዲሸጥ የታዘዘው የተጠሪ ንብረት በሁለተኛ ጫረታ የሚሸጥ ከሆነ ከግምት በላይ ከፍተኛ ዋጋ ነው መሸጥ ያለበት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለላባቸው እዳ ንብረታቸው የሆነው ባህርዛፍ እንዲሸጥ ትእዛዝ ተሰጥቶ በ1ኛው ጫረታ ገዥ ባለመገኘቱ በሁለተኛ ጫረታ እንዲሸጥ የታዘዘ መሆኑን፣በዚህ ጊዜ ንብረቱ ሲሸጥ ግን በ2ኛ ጫረታ ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ንብረቱ እንዲሸጥ ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የመጀመሪያ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዥ አለመቅረቡ ከተረጋገጠ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 428(1) እንደተመለከተው ድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡በመጀመሪያው ጫረታ ማስታወቂያ በተገለፀው የዋጋ ግምት መነሻ ተጫራች ካልቀረበ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 428(1) መሰረት ድጋሚ ማስታወቂያ በማውጣት በሁለተኛ ጨረታ እንደሚደረግ፣ንብረቱም የሚሸጠው በሁለተኛ ጨረታ ማስታወቂያ ጥሪ መሰረት ውድድር በማድረግ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች እንደሆነ ተጠቃሹ ድንጋጌ ያሳያል፡፡በድንጋጌው *"--------ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብ ተጫራች-----------"* የሚለው ሐረግም የሚያስገነዝበው በመጀመሪያ ጫረታ ጊዜ በግምቱ መነሻ ተጫራች ያልቀረበ በመሆኑ የፍርድ ባለመብቱም በፍርድ ያገኘው ውሳኔ እንዲፈፀምለት፣ባለእዳውም ያለበትን ግዴታ እንዲወጣ ማድረግ ይቻል ዘንድ በሁለተኛ ጨረታ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ባለሙያ በገመተው ዋጋ መነሻ ሳይገደብና ከዚያም ባነሰ የዋጋ መነሻ ጫረታ ሊደረግ እንደሚችልና ንብረቱም ሊሸጥ የሚችለው ከተወዳዳሪዎች ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራቾች መሆኑን ነው፡፡ እንዲህም ሲሆን ይህ በውድድሩ ጊዜ የተገኘው ከፍተኛ የተባለው ዋጋም በመጀመሪያ ጫረታ ጊዜ ከተመለከተው የዋጋ መነሻ ዝቅ ሊል እንደሚችል መታወቅ አለበት እንጂ ፍርድ ቤት በሁለተኛ ጫረታ ጊዜም ዋጋው ከባለሙያው ግምት ሊያንስ አይገባም በማለት የሚገድበው አይደለም፡፡በሁለተኛ ጨረታ ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ በተገኘ ከፍተና ዋጋ ላቀረበ ተጫራች እንዲሸጥ የግድ ማድረግ የንብረቱ ዋጋ የባለሙያውን ግምት ካልደረሰ ንብረቱ የሚሸጥበት ሁኔታ እንዳይኖር በማድረግ ባለገንዘቡ ገንዘቡን እንዳያገኝ፣ባለእዳውም ግዴታውን እንዳይወጣ የማድረግ ውጤትን የሚያስከተል በመሆኑ የፍርድ አፈፃጸም ስርዓት የሚቀበለው አካሄድ ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪ ንብረት በሁለተኛ ጨረታ ሲሸጥ ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች እንዲሸጥ በማለት የሠጡት የአፈጻጸም ትዕዛዝ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 428(1) ድንጋጌ ያላስቀመጠው መስፈርት መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06920 ሰኔ 25 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 153062 ጥር 14 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በሁለተኛ ጨረታ ጊዜ ለፍርድ አፈጻጸም የተያዘ ንብረት ሊሸጥ የሚገባው ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ሳይሆን ግምቱን ሳይጠብቅ  ከተወዳዳሪዎች መካከል ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች ነው ብለናል፡፡በዚህ መሰረት አፈጻጸሙን እንዲቀጥል ጉዳዩን ለኢሊባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 85764

መስከረም 21 ቀን 2006ዓ/ም

**ዳኞች**፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካቾች**፡-1. አቶ ኃ/ሚካኤል ታደሰ የቀረበ የለም

2. ወ/ሮ ሽዋዬ አምዴ ቀረቡ

3. አቶ ዮሴፍ ታደሰ ቀረቡ

4. ወ/ሪት አመቤት ታደሰ የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- አቶ ተስፉ ታደሰ የቀረበ የለም

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሸበደኖ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የአፈፃፀም ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በፍርድ ባለመብትነት ቀርበው የፍርድ ባለዕዳው የአባታችንን ውርስ ሀብት እንዲያካፍል በተሰጠው ፍርድ መሰረት እንዲፈፅም ይወሰንልን በማለት ያቀረቡት የአፈፃፀም ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ቀርቦ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተገቢ ነው የሚለውን አፈፃፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት በሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ በሰበር ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
2. አመልካች በ22/4/2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አፈፃፀም ክስ ያቀረበበትን ፍርድ የተሰጠው ሸበደኖ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ዋናው ፍርድ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድርስ ቀርቦ የፀና ነው፡፡ ይህንን ፍርድ ለማስፈፀም ክስ ስናቀርብ ጉዳዩ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሚታይ በመሆኑ ጉዳዩን

ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በ1/8/2005 ዓ.ም ተጠሪዎች መልስ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
4. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የአፈፃፀም ክስ ያቀረቡበት ፍርድ በሸበድኖ መጀመሪያ ፍርድ ቤት ውርሱ እንዲጣራ ተደርጎ የተወሰነና በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ታይቶ የፀና በመጨረሻም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44135 የካቲት 11 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የሸበድኖ መጀመሪያ ፍርድ ቤት ውሣኔና የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮ አመልካቾች የፍርድ ባለ መብት የሆኑበት ፍርድ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካቾች በሸበዲኖ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አፈፃፀም ክስ ያቀረቡት የሥር ፍርድ ቤትም አፈፃፀም ክሱን በመቀበልና በመመርመር 15/08/2004 ዓ.ም አፈፃፀም ትእዛዝ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44135 የካቲት 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ መሠረት በማድረግ ነው፡፡
5. የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ የሚቀርበው ፍርዱን ለፈረደው ፍርድ ቤት እንደሆነና ፍርድ የማስፈፀም ስልጣን ያለው ፍርድን የፈረደው ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ እንዲያስፈጽም ውክልና የተሰጠው ፍርድ ቤት እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁ 378 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44135 የካቲት 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ የማስፈፀም ስልጣን ያላቸው የክልሉ ፍርድ ቤቶች እንጂ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አይደሉም፡፡ የአፈፃፀም ስልጣን መሠረቱ ፍርዱ መስጠት ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ ለማስፀም የሚያስችል ውክልና ማግኘት መሠረት ያደረገ እንጂ የፍርድ ባለእዳውን ወይም የፍርድ ባለመብቱ የሚኖሩበትን ክልል /የከተማ አስተዳደር/ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡
6. ከዚህ አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤትም አፈፃፀም ክሱን በመቀበልና በመመርመር በ15/08/2004 ዓ.ም አፈፃፀም ትእዛዝ የሰጠውና በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ትእዛዙን በይግባኝ በማየት ያፀናው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁ 378 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ለአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2/ በተዛባ መንገድ በመተርጎም ጉዳዩን በሰበር ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡



www.chilot.me

## ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 57927 መስከረም 30 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤትና የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የአፈፃፀም ትዕዛዝ በሰበር አይቶ የመወሰን ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡
3. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአምልካቾችን የሰበር አቤቱታ በመመርመር ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

# ልዩ ልዩ



www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 81023

ግንቦት 05 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፋ አህመድ

**አመልካች**፡- አቶ ገላና ኦልጅራ  ጠበቃ አቶ ግርማ ሚደቅሳ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡** 1. አቶ ገዛኸኝ ፋይስ ጠበቃ አቶ ብርሃኑ ይማም ቀረቡ

2. አቶ ብርሃኑ ገመዳ

3. የለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ አስተዳደር
የመሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ጽ//ቤት } አልቀረቡም

አመልካች በሁለተኛ ተጠሪና በሶስተኛው ተጠሪ ላይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 81444 ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር በፍታብሔር ስነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 11 ንዑስ አንቀፅ 5 መሰረት ከዚህ ከቀረበው ክርክር ጋር በማጣመር መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪና በሶስተኛው ተጠሪ ላይ ያቀረብኩትን ክስ በመዝገብ ቁጥር 05753 በማየት ታህሳስ 13 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140154 አይቶ ሚያዝያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በዚህ መዝገብ ያቀረበውን ሰበር አቤቱታና አመልካች የፊንፊኔ ዙሪያ አሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05762 የአመልካችን የሁለተኛውን ተጠሪና የሶስተኛውን ተጠሪ ክርክር ሰምቶ ጥር 8 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140153 ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 81444 ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል ለገዥው የሚያስገኘውን መብትና በገዥ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ሊያቀርባቸው የሚችለውን የመብት ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲታይ በመዝገብ ቁጥር 05753 አመልካች ከሳሽ አንደኛ ተጠሪና ሶስተኛ ተጠሪ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ እንደዚሁም በመዝገብ ቁጥር 05762

አመልካች ከሳሽ ሁለተኛ ተጠሪና ሶስተኛ ተጠሪ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል የክርክሩ መነሻ አመልካች ከላይ በተገለጹት መዛግብት በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ነው፡፡

1. አመልካች ለስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05762 በአንደኛ ተጠሪና በሶስተኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ አንደኛ ተጠሪ በስሙ የተመራውንና የካርታ ቁጥር L/x/L/D/132/00 የሆነውን በ140 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰራ ጅምር ቤት ሕዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በተደረገ የጅምር ቤት ሽያጭ ውል ብር 85,000 /ሰማኒያ አምስት ሺ ብር/ ሽጦልኛል አንደኛ ተጠሪ ጅምር ቤቱንና የቦታውን ካርታና ፕላን አስረክቦኛል፡፡ ቤቱን በስሜ ለማዛወር እንድችል ልዩ የውክልና ስልጣን ተሰጥቶኛል፡፡ እኔም የገዛሁትን ቤት የቦታውን ፕላን በማስቀየር ፎቅ ቤት ለመገንባት የሚያስችለኝ የስራ ፕላን ተሰጥቶኝ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር/ ወጭ በማድረግ የግንባታ ስራ በመስራት ግንባታውን በማጠናቀቅ ላይ እገኛለሁ ሆኖም አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ በሽያጭ ውል ለእኔ ያስተላለፈውን የጅምር ቤቱና የቦታው ካርታና ፕላን እንደጠፋበት ሀሰተኛ መግለጫ ለሁለተኛው ተከሳሽ /ሶስተኛ ተጠሪ/ በማቅረብ አዲስ ካርታና ፕላን ተሰጥቶታል አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ በሀሰት አጭበርብሮ ባገኘው ካርታና ፕላን መሰረት በውል ለእኔ የሸጠለኝንና ያስረከበኝን ጅምር ቤት እንድትሸጥ እንድትለውጥና ለሶስተኛ ወገን እንድታስተላለፍ የውክልና ስልጣን ለሌላ ሴት ወ/ሮ ትዕግስት ወርቁ በመስጠት ለእኔ የሰጠኝን ውክልና ስልጣን ሽሮታል፡፡ ስለሆነም ለእኔ በሽያጭ ውል ያስተላለፈውን ጅምር ቤት እንድትሸጥ እንደትለውጥና ለሶስተኛ ወገን እንድታስተላለፍ አንደኛ ተከሳሽ/አንደኛ ተጠሪ/ ለሌላ ሴት የሰጠው ልዩ የውክልና ስልጣን እኔ በቤቱ ላይ ያገኘሁትን መብት የሚጥስ በመሆኑ በፍርድ ፈራሽ ሆኖ እንዲሻርልኝ፡፡ አንደኛው ተከሳሽ/አንደኛ ተጠሪ/ በሽያጭ ውል ለእኔ ያስተላለፈውን የቦታውንና የቤቱን ካርታና ፕላን እንደጠፋበት ሀሰተኛ መግለጫ ለሁለተኛው ተከሳሽ በማቅረብ ያገኘው ካርታና ፕላን በማጭበርበር የተገኘ ካርታና ፕላን ስለሆነ እንዲሰረዝልኝ አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ የሽያጭ ውሉን የሚያፈርስ ተግባር የፈፀመ በመሆኑ በሽያጭ ውሉ የተቀመጠውን የመቀጫ ገንዘብ ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺ/ ብር እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ሁለተኛው ተከሳሽ/ሁለተኛው ተጠሪ/ የቤቱን ስመ ሀብትና ካርታ በስሜ እንዲያዛውር ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡
2. አመልካች ለስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05753 /በሁለተኛ ተጠሪና በሶስተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስና የጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ ከላይ በዝርዝር ከተገለፀው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ልዩነቱ አመልካች የካርታ ቁጥሩ L/x/L/D/1223/00 የሆነውን የሁለተኛ ተጠሪ ቤት ህዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በብር 85,000 /ሰማንያ አምስት ሺ ብር/ የገዛ መሆኑንና ሁለተኛ ተጠሪ ጅምር ቤቱን የቦታውንና የቤቱን ካረታና ፕላን አስረክቦኝ ብር 250,000/ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ብር/ በማውጣት ፎቅ ቤት ገንብቶ በማጠናቀቅ ላይ እያለ ሁለተኛው ተጠሪ የቦታውና የቤቱ ካረታና ፕላን የጠፋበት መሆኑን ሀሰተኛ መግለጫ ለሶስተኛው ተጠሪ አቅርቦ አዲስ ካርታና ፕላን ከወሰደ በኋላ ጀምር ቤቱን እንድትሸጥ እንድትለውጥና ለሶስተኛ ወገን እንደታስተላልፍ ለወ/ሮ ትዕግስት ወርቁ ልዩ የውክልና ስልጣን የሰጠ መሆኑ ነው፡፡ አመልካች ለሁለተኛ ተጠሪ ለትዕግስት ወርቁ የሰጠው ውክልና እንዲሻር በሀሰት መግለጫ የተሰጠው ካርታና ፕላን እንዲሰረዝና ሁለተኛ ተጠሪ 15,000/አስር አምስት ሺ

ብር/መቀጫ ገንዘብ እንዲከፍልና ሶስተኛ ተጠሪ የቤቱን ስመ ሀብት ካርታና ፕላን በስሙ እንዲያዛውር ፍርድ እንዲሰጥለት ጠይቋል፡፡

3. በሁለቱም መዛግብት ተጠሪዎች በተከሰሱበት መዝገብ በተከሳሽነት ቀርበው የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያዎችን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን የማየት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለውም አንድ ሰው ለሌላው ሰው የሰጠው ውክልና እንዲሻር ጥያቄ ለፍርድ ቤት ሳይሆን ለሚመለከተው አካል መቅረብ ያለበት ነው የካርታ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተቀብሎ ውሳኔ የመሰጠት የአስተዳደር አካላት እንጅ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የላቸውም የስም ይዛወርልኝ ጥያቄም ውሉን በተናጠል ለከሳሽ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ያፈረስነው ስለሆነ የሕግ መሰረት የለውም የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡
4. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር ከመረመር በኂላ ከሳሽ ካርታና ፕላን እንዲሰረዝለት ያቀረበው ጥያቄ በአስተዳደር አካላት የሚወሰን እንጅ በፍርድ ቤት ታይቶ የሚወሰን አይደለም፡፡ ከሳሽ ልዩ የውክልና ስልጣን እንዲሻርለት ያቀረበውን ጥያቄ የመወሰን ስልጣን ያለው ውልን የሚመዘግበው አካል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ስልጣን አለው ቢባል እንኳን በመጨረሻ የጠየቀው ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺ ብር/ ስለሆነ ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድቤት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ሳይሆን የወረዳ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት ሁለቱንም መዛግብት በመዝጋት አመልካችንና ተጠሪዎችን አስናብቷቸዋል፡፡
5. አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቀጥር 05762 ሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140153 የስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05753 የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140154 አቅርቧል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሁለቱ ይግባኝ መዛግብት አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና የተጠሪዎችን ክርክር ከሰማ በኂላ አመልካችና ተጠሪዎች የኦሮሚያ ክልልና የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በመሆናቸውና አመልካች የጠየቀው ዳኝነት ብር 15,000 ብቻ እንዲከፈለው ባለመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው የውሣኔ ክፍል ስህተት ያለበት ነው ሆኖም በውጤቱ ደረጃ አመልካች ካርታ እንዲሰርዝለት እና ልዩ የውክልና ስልጣን እንዲሻርለት ያቀረበው ጥያቄ በሚመለከታቸው አስተዳደር ክፍሎች የሚወሰን እንጂ በዳኝነት የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም ያለው ውሣኔ ክፍል ትክክል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው በማለት በሁለቱም መዛግብት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የውሣኔ ምክንያት ብቻ በማሻሻል ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡
6. አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላል ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140154 የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በሰበር መዝገብ ቁጥር 81023 ሀምሌ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል እንዲሁም አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140153 የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በሰበር መዝገብ ቁጥር 81444 ሀምሌ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቀርቧል፡፡ አመልካች በሁለቱ መዛግብት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘት እኔ በውል የገዛሁትንና የተራከብኩት ጅምር ቤት ካርታና ፕላን እንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ

ተጠሪ ለመሸጥ ለመለወጥ እንዲመቻቻው በማሰብ የቤቱና የቦታው ካርታና ፕላን እንደጠፋባቸው ሀሰተኛ መግለጫና ማስረጃ ለሶስተኛ ተጠሪ በማቅረብ የተሰጣቸው አዲስ ካርታና ፕላን የእኔን መብት የሚጎዳና በሀስትና በማጭበርበር የተሰጠ መሆኑ ተረጋግጦ በፍርድ እንዲሰረዝልኝ ያቀረብኩትን የዳኝነት ጥያቄ ፍርድ ቤቶች አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አላቸው ስለዚህ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ በውል ለእኔ የሸጠልኝንና እኔ ከፍተኛ ገንዘብ ወጭ በማድረግ የገነባኃቸውን ቤቶች፣ በሀሰተኛ መግለጫና ሐሰተኛ ማስረጃ ተጠቅመው ያወጡትን አዲስ ካርታና ፕላን ጋር ወ/ሮ ትእግስት ወርቁ እንድትሸጥ እንድትለውጥና ለሶስተኛ ወገን ቤቶቹን እንድታስተላልፍ የሰጧት ልዩ የውክልና ስልጣን በንብረቴ የተሰጠና እኔ በቤቶቹ ላይ ያለኝን መብት የሚጎዳ ነው፡፡ የውክልና ስልጣኑ የውል ሰነድ ነው፡፡ ስለዚህ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረብኩት ጥያቄ የግራ ቀኞችንን ማስረጃ በመስማት ውሣኔ የሚሰጡት ፍርድ ቤቶች እንጂ የውልና ማስረጃ የመዝገባ ስልጣን ያለው አካል አይደለም፡፡ ስለዚህ ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን ስልጣን እንደሌላቸው በመግለጽ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው በማለት አመልክቷል፡፡

7. አንደኛ ተጠሪ ሕዳር 7 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስና ሁለተኛው ተጠሪ ሕዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ተመሣሣይ ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡ የውክልና ስልጣን አንድ ወገን ወካይነት የማቋቋምና ሊሻር የሚችል በመሆኑ የውክልና ሰነዱን በመመርመር ፍርድ ቤቶች ሊሰርዙትና ሊሽሩት ይችላሉ በማለት አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያደረግነው ጅምር ቤት ሽያጭ ውል በሕጉ የተገለፀውን ፎርም እንደማያሟላ ገልፀን ውሉን ሰርዘነዋል አመልካች የወሰደውን ካርታና ፕላን እንዲመልስልን ስንጠይቀው ጠፍቶብኛል በማለት እንቢተኛ በመሆኑ ለሚመለከተው የፖሊስ ክፍል አመልክተንና በበክልቻ ኦሮሚያ ጋዜጣ ጥሪ በማስድረግ የቤት ካርታና ፕላን ሶስተኛው ተጠሪ ተሰጥቶናል ይህም በሀሰት የመጣ ካርታና ፕላን ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲያፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሶስተኛ ተጠሪ በበኩሉ በሁለቱ የሰበር መዛግብት አመልካች ላቀረበው የሰበር አቤቱታ ጥቅምት 21 ቀን 2005 ዓ.ም እና ሕዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ አንደኛውን ተጠሪ ሁለተኛው ተጠሪና የቤትና የቦታ ካርታና ፕላን እንደጠፋባቸው በተናጠል በማመልከታቸው ጉዳዩ በፖሊስ በኩል የተሰጠውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ በጋዜጣ ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ጥሪ አድርጌ ተቃዋሚ የልቀረበ በመሆኑ ለአንደኛና ለሁለተኛ ተጠሪዎች አዲስ የቤት የቦታ ካርታ ፕላን ሰጥቻለሁ፡፡ ይህንን የፈፀምኩት በሕጉ የተደነገገውን ሥርዓት በመከተል የሰበር አቤቱታውን ውድቅ ሆኖ በነፃ እንድሰናበት ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርቧል አመልካች ተጠሪዎች ለሰጡት መልስ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

8. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ተጠሪዎች በዚህ መዝገብና ከዚህ መዝገብ ጋር በተጣመረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 81444 ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረባቸው የዳኝነት ጥያቄዎች በፍርድ የማያልቁ በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ውሣኔ የሚሰጥባቸው ናቸው በማለት ውድቅ ማድረጋቸውን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

9. ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ለማቅረብ መነሻ የሆነውን መሠረታዊ ጉዳይና የክርክሩ ጭብጥ በፍተሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተደነገገው መሠረት በመለየትና በመመስረት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ ለመስጠት የዳኝነት ኃላፊነታቸውን የተወጡ መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ጉዳይ አከራካሪ መሠረታዊ ጭብጥ አንደኛው ወገን የጠየቀውና ሌላኛው ወገን የካደው መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246 የሚደነግግ ሲሆን የአንድ ክርክር ጭብጥ የሚመሠረተው ከሣሽ በክስ በማመልከቻው የገለፀው እና ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ተከሣሽ ክሱን ለመከላከል ያቀረበውን የጽሑፍ መልስና ክሱን ለመከላከያ ያቀረበው የጽሑፍ ማስረጃና ተከራካሪዎች ለፍርድ ቤት የቃል ምርመራ የገለፁትን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍተሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ይደነግጋል፡፡

10. አመልካች በተጠሪዎች ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ መሠረታዊ መነሻ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ሕዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረገው የካርታ ቁጥሩ L/X/L/D/131/00 የሆነውን ጅምር ቤት በብር 85,000 /ሰማንያ አምስት ሺ ብር/ ለመግዛት የተዋዋለው ውልና ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ሕዳር 19 ቀን 2001 ዓ.ም የካርታ ቁጥር L/X/L/D/1223/00 የሆነ ጅምር ቤት ለመግዛት የተዋዋለው ውል ነው አመልካች በውል የገባውን ግዴታ በመፈፀምና የገባቸውን የቤት ዋጋ በመክፈል የቤቶቹን ካርታዎች እና ጅምር ቤቶቹን ከአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ተረክቦ የጅምር ቤቶቹን ፕላን በማስቀየር ከፍተኛ ወጭ በማውጣት ፎቅ ቤቶችን በመገንባት በማጠናቀቅ ሒደት ላይ እያለ ተጠሪዎች በውል የገቡትን ግዴታ በመጣስና በውል ያገኘውን መብት ዋጋ ለማሣጣት የተለያዩ ተግባራትን ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በሽያጭ ውልና በፍተሐብሔር ሕግ ቁጥር 2879/1/ መሠረት ለእኔ ያስተላለፉትን ካርታ በሐሰት ጠፋቶብናል የሚል ማመልከቻና ማስረጃ ለሶስተኛው ተጠሪ በማቅረበ አዲስ ካርታ መውሰዳቸው በዚህ አዲስ ካርታ መሠረት እኔ የገዛሁትን እና ወጭ አውጥቼ የገነባኋውን ቤት ትእግስት ወርቁ እንድትሸጥ እንድትለወጥ ወይም ለሶስተኛ ወገን እንድታስተላልፍ ልዩ የውክልና ስልጣን የመስጠት ተግባር ፈጽመዋል እነዚህ ተግባራት በፍርድ ተመርምረው ይሰረዙልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስና ክርክር አቅርቧል፡፡

11. ተጠሪዎች በበኩላቸው ከአመልካች ጋር ውል ከተዋዋሉና የቤቱን ዋጋ ከተቀበሉ በኃላ ውሉ ጐድቶናል በሚል ሃሣብ የተቀበሉትን ገንዘብ የመለሱ መሆኑንና ውሉም የፈረሰ መሆኑን ገለፀው እንደተከራከሩ አመልካች የወሰደውን ካርታና ፕላን ጠፋቶብኛል ስላላቸው አዲስ ካርታ ፕላን የወጣ መሆኑ ቤቱ ንብረታቸው መሆኑን ገልፀው እንደተከራከሩ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔው ካሠፈራቸው መሠረተ ሃሣቦች ተረድተናል፡፡

12. ከላይ የገለጽናቸው አመልካችና አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር መሠረታዊ ጭብጦች

/ሀ/ አንደኛ ተጠሪ የካርታ ቁጥሩ L/X/L/D/131/00 የሆነውን ቤት ለአመልካች ለመሸጥ ሕዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረገውን የጅምር የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ተጠሪ የተቀበለውን የቤቱን ዋጋ ለአመልካች መልሷል ወይስ አልመለሰም፣

/ለ/ ሁለተኛ ተጠሪ የካርታ ቁጥር L/X/L/D/1223/00 የሆነ ጅምር ቤት ለአመልካች ለመሸጥ ሕዳር 12 ቀን 2001 ያደረገው ውል ፈርሶ ሁለተኛ ተጠሪ የተቀበለውን የቤቱን ዋጋ ለአመልካቾች መልሷል ወይስ አልመለሰም?

/ሐ/ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪና በሁለተኛ ተጠሪ ጋር በተናጠል ያደረገው የጅምር ቤት ግዥ ውል በሕጉ አግባብ አልፈረሰም ቢባል አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉን ሲዋዋሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2879/1/ መሠረት ለአመልካች አሣልፈው የሱጡት የቤትና የይዞታ ካርታና ፕላን እንደጠፋባቸው ሀሰተኛ መግለጫ በማቅረብ አዲስ ካርታና ፕላን ከሶስተኛው ተጠሪ መወሰዳቸው ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም?

/መ/ ሶስተኛው ተጠሪ ለተጠሪዎች አዲስ የቤትና የቦታ ካርታና ፕላን ሲሰጥ የቀድሞው ካርታና ፕላን ተጠሪዎች ጠፍቶብናል በማለት ባቀረቡት ማመልከቻና ማስረጃ መሠረት መሠረዙ በሶስተኛ ወገን /አመልካች/ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለማስወገድ ተጠሪዎች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1197 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በቂ ዋስትና እንዲሰጡ አድርጓል ወይስ አላደረገም?

/ሠ/ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪና ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር በተናጠል ያደረገው የቤት ሽያጭ ውል በሕጉ አግባብ አይፈረስም ከተባሉ ተጠሪዎች በውል ለአመልካች የሸጡትን ቤት ወ/ሮ ትእግስት ወርቁ እንድትሸጥ እንድትለውጥ በማናቸውም ወገን ለሶስተኛ ወገን እንድታስተላለፍ ልዩ የውክልና ሰልጣን መስጠት ይችላሉ ወይስ አይችሉም? አይችሉም የሚባል ከሆነ ውጤቱ ምንድ ነው?

/ረ/ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ብር 150,000 / አንድ መቶ ሃምሣ ሺ ብር/ ከአንደኛ ተጠሪ በገዛው ጅምር ቤት 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሣ ሺ ብር/ ከሁለተኛው ተጠሪ በገዛው ጅምር ቤት ላይ ወጭ አውጥቶና የቤቱን ፕላን ወደ ፎቅ አስለውጦ የግንባታ ሥራ ሠርቷል? ወይስ አልሰራም? ሠርቷል የሚባል ቢሆን ውጤቱ ምን ይሆናል?

/ሰ/ ሶስተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪና ለሁለተኛ ተጠሪ የሰጠውን አዲስ ካርታና ፕላን በመሰረዝ የቤቱቹን ስመሃብት ወደ አመልካች እንዲዛወር ማድረግ ይገባዋል ወይስ አይገባውም? የሚሉት ጭብጦች ላይ በግራ ቀኙ የቀረቡ ማስረጃዎችን በመስማት በመመርመርና በመመዘን ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በፍርድ መወሰን የሚጠይቅ ነው፡፡ እነዚህን ከላይ የገለጽናቸውን ተያያዥነት ያላቸው ጭብጦች በፍርድ የሚያልቁ እንጂ የአስተዳደር ክፍሎች ግራ ቀኙን በማከራከርና ማስረጃ በመስማት በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚጨርሷቸው ጉዳዮች አይደሉም፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጣመሩት የሰበር መዝገቦች የቀረበውን ጉዳይ በዳኝነት እንደማያልቁ በመግለጽ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05753 እና በመዝገብ ቁጥር 05762 የሰጣቸው ውሣኔዎች ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140154 እና በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140153 የሰጣቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡
3. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገበ ቁጥር 05753 እና የመዝገብ ቁጥር 05762 በማንቀሣቀስ ከላይ በተራ ቁጥር 12 የተገለፁትን ጭብጦች በመመስረትና ማስረጃ በመስጠት ሌሎች ተያያዥነት ያላቸወን ጉዳዩች በማጣራት በጉዳዩ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁ 341/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 80301

ሚያዝያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ አንተነህ ሲሳይ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ - ነገረ ፈጅ አሸናፊ ስዩም ቀረበ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17701 ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዲስፐሊን ጥፋት የተፈፀመ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ በይግባኝ የታየው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው፡፡

1. ተጠሪ አመልካች ከባድ የዲስፐሊን ጥፋት የፈፀመ መሆኑ በቢሮው የዲስፐሊን ኮሚቴ የተረጋገጠ መሆኑን ገልፆ ከሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ከስራ የተሰናበተ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ፅፏል፡፡ አመልካች በቢሮው የዲስፒሊን ኮሚቴና በቢሮ ኃላፊው የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች ከባድ የዲስፐሊን ጥፋት ፈፅሟል ያለው አያት አክሲዮን ማህበር ከአዲስ አበባ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን ጋር የሊዝ ውል አፈፃፀም በተመለከተ አለመግባባት ተፈጥሯል፡፡ ሁለቱ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ለመጨረስ ከተስማሙ በኂላ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣንን የሚወክል የህግ ባለሙያ መወከል አስፈላጊ በመሆኑ አመልካች ውክልና ተሰጥቶታል፡፡ አመልካች ይህንን የስራ ግዴታውን በመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት ሰርቷል፡፡ ለግልግል ዳኛ አበል እንዲከፍል ትዕዛዝ ሲሰጡ ከሌሎች የግልግል ዳኞች ጋር አብረው መወሰናቸው የመንግስት ሰራተኞችን ስነ ምግባር የጣሰ ነው፡፡ የግልግል ዳኛ በመሆናቸው የተከፈላቸውን አበል ለፍትህ ቢሮ ተመላሽ እንዲያደርጉ በቢሮው ኃላፊው ሲጠየቁ እንቢተኛ በመሆን ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት ነው በማለት ከስራ ያሰናበተው መሆኑን በመግለፅ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተከራክሯል፡፡ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አመልካች የፈፀመው የዲስፒሊን ጥፋት የሌለ መሆኑን በመዘርዘር የዲሲፐሊን ኮሚቴና የቢሮው ኃላፊ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች ያልተከፈለው ደመወዝ

ተከፍሎት ወደ ሥራው እንዲመለስ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ግ/ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

2. ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የከተማው የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ ለሰራበት አበል መቀበሉና አበሉን ለፍትህ ቢሮ እንዲመልስ ሲጠየቅ እንቢተኛ መሆኑ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ነው፡፡ አመልካች የበላይ ኃላፊውን ትዕዛዝ አላከበረም በማለት የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የዲስፒሊን ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡
3. አመልካች ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የግልግል ዳኛ ሆኖ እንዲሰየም ደብዳቤ ፅፏል፡፡ የግልግል ጉባኤው በፍ/ስ/ስ/ሕ/ግ/ቁጥር 318(5) በተደነገገው መሰረት የአበል ክፍያ ወስኗል፡፡ የግልግል ዳኛ ሆኜ ተሰይሜ ለሰራሁበት የተከፈለኝን አበል ለቢሮው እንዳስገባ የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ትዕዛዝ ሰጠኝ አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ ገቢ የማደርግበት ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ግዴታ የለብኝም፡፡ ስለዚህ አበል ለመመለስ ፈቃደኛ አይደለህም በማለት የዲስፒሊን ጥፋት እንደፈፀምኩ የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡
4. ተጠሪ መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ እያለ አበል መቀበል፣ አበልም ከተቀበለ በኋላ ወክሎ የላከው መስሪያ ቤት ለማስረከብ ፈቃደኛ አይደለም ይህም ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት በመሆኑ የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡
5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት ፈፅሟል በማለት የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
6. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካችን የመደብኩት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን ከአያት አክሲዮን ማህበር ጋር በሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር ባለው አለመግባባት፣ አመልካች የሙያ ምክርና ድጋፍ ለመሬት አስተዳደር ባለስልጣኑ እንዲሰጥ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ተጠሪ በፅሁፍ የገለፀልኝ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣንና የአያት አክሲዮን ማህበር አለመግባባት በግልግል አይቶ ውሳኔ የሚሰጠው የግልግል ጉባኤ አባልና የግልግል ዳኛ ሆኜ እንድሰራ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ አንድ ጉዳይ በፍርድ ቤት ወይም በግልግል ጉባኤ በሚታይበት ወቅት ለአንደኛው ወገን የሕግ ምክርና ድጋፍ እንዲያደርግ የተመደበ ባለሙያ ያለበት ሙያዊ ኃላፊነትና ሊከተለው የሚገባው የስነ ምግባር ደንብ በሁለቱ ወገኖች መካከል የተነሳውን አለመግባባት በግለግል ዳኝነት አይቶ ውሳኔ እንድሰጥ ከተመደበ ባለሙያ ካለበት ኃላፊነትና ሊከተለው ከሚገባው የስነ ምግባር ደንብ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪ አመልካችን የመደበው ለመሬት አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን የሕግ ድጋፍና ምክር አገልግሎት እንዲሰጥ ነው? ወይስ የግልግል ጉባኤ አባል ሆኖ የሁለቱን ተከራከሪ ወገኖች ክርክርና ማስረጃ ለመስማት ውሳኔ እንዲሰጥ የሚለው ነጥብ መለየት አለበት፡፡

7. ተጠሪ ለመሬት አስተዳደርና ግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤና ተጠሪ ሚያዝያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ለአያት አክሲዮን ማህበር በፃፈው ደብዳቤ፣ አመልካች የሁለቱን ጉዳይ በግልግል እንዲያይ በግልግል ዳኝነት የተሰየመ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የመሬት አስተዳደርና የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣንና ለአያት አክሲዮን ማህበር መካከል የሊዝ ውል በተመለከተ የተፈጠረውን አለመግባባት በግልግል የሚያው የግልግል ጉባኤ አባል ሆኖ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ተጠሪ በፅሁፍ መድቦታል፡፡ የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ባለሙያ (የግልግል ዳኛ) ሆኖ የተሰየመበትን ስራ በሚሰራበት ጊዜ ሊከተለው የሚገባው የሙያ ስነ ምግባር ዳኛ የሚከተለውን ሥነ ምግባር እንደሆነና ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 351 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

አንድን ጉዳይ በግልግል አይቶ እንዲወሰን የተቋቋመው የግልግል ጉባኤ የግልግል ዳኛ በጉዳዩ ገለልተኛና ነፃ ሆኖ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በአግባቡ ሰምቶ የመወሰን ግዴታ እንዳለበትና ይህ በተጓደለ ጊዜ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ በይግባኝ ሊታረም እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 351 ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፡፡ በተለይም የአንቀጽ 351 ንዑስ አንቀጽ (2)(መ) የግልግል ወይም የሽምግልና ዳኝነት አባል የሆነ ሰው በስራው አፈፃፀም ላይ በዳኛ ሊፈፀም የማይገባውን የአድሏዊነት እና የመጥፎ ባሕሪይ ፀባይ ማሳየት እንደሌለበት የሚደነግግ ይዘት ያለው ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ ከተሰየመ በኋላ የግልግል ጉባኤ አባልነቱ ግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ የመስማት የመመዘንና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁጥር 317 ድንጋጌዎች መሰረት ከማድረግ ክርክሩን የመምራትና የቀረበለትን ክርክርና ማስረጃ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ የመሰለውን ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

የግልግል ጉባኤው ከሚወስናቸው ውሳኔዎችና ከገላጋይ ዳኞቹ ሊከፈል የሚገባውን የአበል መጠን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 318 ንዑስ አንቀጽ 5 በግልፅ ተመልክቷል፡፡

አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ ሲሰራ አንድ ዳኛ ማሟላት የሚገባውን የሙያ ስነ ምግባር ደንብ ማሟላት ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ የግልግል ዳኛ ሆኖ ተለይቶ የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃ መስማትና ውሳኔ መስጠት አመልካች ከተቀጠረበት መደበኛ ሥራ/ የህግ ምክርና ድጋፍ/ መስጠት በእጅጉ የተለየ ከባድ ኃላፊነት ነው፡፡ ከዚህ በላይ የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ሰው በግልግል ዳኝነቱ የተጣለበትን በአግባቡ ካልተወጣ ራሱን የቻለ የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት መሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 399(1) ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመበት ጉዳይ በውሳኔ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጉዳዩን ተከራካሪ ወገኖችን በእኩልነት የማየት ነፃና ገለልተኛ ሆኖ የመስማት የመመርመርና ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነቱን ያልተወጣ ስለመሆኑ ተጠሪ በክርክሩ አልገለፀም፡፡ ተጠሪ አመልካች የግልግል ዳኛ የሆነው የቢሮው ወኪል ሆኖ ነው በማለት ያቀረበው ክርክርም የህግ መሰረት የለውም፡፡ አመልካች በክርክሩ የግልግል ዳኛ እንዲሆን የተመረጠውና የተሰየመው በተጠሪ ፈቃድና ሥምምነት ነው፡፡ አመልካችና የግልግል ዳኛ ሆኖ ተሰይሞ ጉዳዩን



www.chilot.me

በግልግል ዳኝነት ማየት ከጀመረ በኋላ ተጠሪን እያማከረና በግልግል ዳኝነት አባልነቱ የሚሰጠውን ብይንም ሆነ ውሳኔ በተጠሪ እያፀደቀና እያስፈቀደ ሊሰራ አይችልም፡፡ አመልካች እንደማንኛውም ዳኛ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ጉዳዩን ማየትና የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡

ከዚህ አንፃር ካየነው አመልካች በግልግል ዳኝነት ተሰይሞ የሰጠውን ብይን (ተከራከሪዎች የግልግል ጉባኤ ወጭና አበል እንዲሸፍኑ) የግልግል ጉባኤው ሲወስን፣ አመልካች መስማማቱን እንደ ድስፒሊን ጥፋት ማቅረቡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁጥር 351 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) በአመልካች ላይ ከተጣለበት የዳኛ ሥነ ምግባር የመከተልና ገለልተኛ ሆኖ ብይንና ውሳኔ የመስጠት ግዴታን የሚፃረር ነው፡፡ የአበል ክፍያን በተመለከተ የግልግል ጉባኤው እንደ አንድ ፍርድ ሰጭ ተቋም፣ ተከራከሪዎች ካልተስማማቸው በይግባኝ ሊያስለውጡት የሚችሉበት ሥርዓት በተዘረጋበት ሁኔታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁጥር 318 ንዑስ አንቀጽ 2(5) የወሰነው እንጅ አመልካች በግሉ ከአያት አክስዮን ማህበር የተቀበለው ገንዘብ አይደለም፡፡ አበሉ ለአመልካች የተከፈለው አመልካች በተጠሪ ከተቀጠረበት የሕግ ምክርና ድጋፍ የመስጠት ስራ የተለየ ኃላፊነትና ሥልጣን ባለው የግልግል ጉባኤ የግልግል ዳኛ ሆኖ ለሰራው ስራና ለሰጠው ለአገልግሎት ነው፡፡

ስለዚህ አመልካች ለአንድ ልዩ ጉዳይ የግልግል ዳኛ ሆኖ ለሰጠው አገልግሎት እንደማንኛውም የግልግል ጉባኤ አባል የተከፈለው የአበል ክፍያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 6/2000 አንቀጽ 31 የሚጥስ የሥነ ምግባር ጥፋት ተደርጎ ሊያዝ የሚችል አይደለም፡፡

ተጠሪ አመልካች ሰራተኛው በመሆኑና የግልግል ዳኛ ሆኖ አመልካች በጉዳዩ የተሰየመው በእሱ ፈቃድና ስምምነት መሆኑን መሰረት በማድረግ የአበል ክፍያውን አመልካች ገቢ ሊያደርግ ይገባዋል በማለት የሚያቀርበው የሕግ መሰረት የለውም፡፡ ስለዚህ አመልካች በግልግል ዳኛ ሆኖ ለሰጠው ግልጋሎት እንደ ማንኛውም የግልግል ጉባኤ አባል የተከፈለውን አበል ለተጠሪ ገቢ አለማድረጉን ከባድ የስነ ምግባር ጥፋት ነው በማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሠጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ ሲሰራ የፈፀመው ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት የሌለ በመሆኑ ተጠሪ የአመልካችን ውዝፍ ደመወዝ በሕጉ መሰረት ከፍሎ ወደ ስራ ሊመልሰው ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

***መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 88060

መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አ/ማህበር ነ-ፈጅ አቶ አሰፋ ዓለሙ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ምስጋናው ጥሩነህ ጠበቃ አቶ ውቤ አለነ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት የለውም በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት አግባብነት በክርክር ሂደት ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮችና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በሚል ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ወሰደ የሚባለው ከኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ መሆኑንና በዚህ ገንዘብ ምክንያት ክስ በቀረበበት ጊዜ ደግሞ የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ በሽያጭ ወደ አሁኑ አመልካች የተላለፉ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው በመንግሥት እጅ የነበረ የልማት ድርጅት ከመሸጡ በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ አለኝ የሚለውን ገንዘብ የልማት ድርጅቱ በሽያጭ ከተላለፈ በኋላ የመሰብሰብ መብት ያለው ማን ነው? የሚለው ነው፡፡

ለዚሁ አከራካሪ ነጥብ አግባብነት ባለው የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ባለአደራ ቦርድን ለመቋቋምና ሥልጣንና ተግባሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 208/92 አንቀጽ 5 እና 6 ላይ "የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታነት፣ ወደ አክሲዮና ማህበር በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለሀብቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ ተሰብሣቢ ሂሣቦችን ለመሰብሰብ፤ ዕዳዎችን ለመረከብና የፍርድ ቤት ጉዳዮችን ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

በዚህም ጉዳይ የመንግሥት የልማት ድርጅት የነበረው የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ በሽያጭ ወደ አሁን አመልካች በመተላለፉ ምክንያት የተሸጠው የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ ከመሸጡ በፊት የነበረው ተሰብሣቢ ሂሣብና የነበረበት ዕዳ



www.chilot.me

ወደ ገዥው የማይተላለፍ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ከላይ በተጠቀሰው ሕግ መሠረት ተሰብሣቢ ሂሣቡንም ሆነ ዕዳውን በሚመለከት ለመሰብሰብም ለመረከብም ኃላፊነት እና ግዴታ የተጣለበት ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እንደሆነ መደንገጉ እየታወቀ የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካን በሽያጭ ወደ አሁን አመልካች እንዲተላለፍ በተደረገበት የሽያጭ ውል አንቀጽ 4.5 ላይ “ ገዥው የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር የሸጠውን የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካን ቋሚ ንብረትንና ዕዳን ሁሉ የመረከብ ግዴታ እንዳለበት ስለመደንገጉ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

ይህም መሆኑ ከተረጋገጠ በአዋጅ ቁጥር 208/92 አንቀጽ 5 እና 6 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የተሸጠው የመንግሥት የልማት ድርጅት ከመሸጡ በፊት የሚሰበስባቸው ተሰብሣቢ ሂሣቦች እና ዕዳዎች በሽያጭ ውል መሠረት ወደ ገዥው የማይተላለፉ ሆኖ በተመለከተ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በዚህ በተያዘው የሽያጭ ውል ላይ የተሸጠው ድርጅት የነበረው ዕዳ ሁሉ ወደ ገዥው እንደሚተላለፍ በግልጽ እስከተመለከተ ድረስ ዕዳውን ተሸካሚ ከሆነ በሽያጭ ውል ከተመለከተው የድርጅቱ ቋሚ ንብረት ባሻገር ተሰብሣቢ የሂሣብ ሰነዶችንም የመሰብሰብ መብትና ሥልጣን ብቻ ተነጥሎ ለባለአደራ ቦርድ ተሰጥቷል ወደ ሚል መደምደሚያ ሊያደርስ የሚቻል አይደለም፡፡ ይህ የሽያጭ ውል ከአዋጅ ዓብይ ዓላማ አንፃር ለሕግ ተፃራሪ ነው እስከልተባለ ድረስ የባለ አደራ ቦርድ ሥልጣንና ተግባር ወደ ገዥው ሊተላለፉ በማይችሉ የተሸጠው ድርጅት ውጤትና ግዴታ ላይ የተወሰነ ነው፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ ይዘቱን ግብር ዓላማውን ከሽያጭ ውሉ ይዘት ጋር በማገናዘብ ተመልክተው የሰጡት ትርጉም እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች ክስ የቀረበበት ጉዳይ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ እና ከሽያጭ ውሉ አንፃር ተገናዝቦ ከታዬ ክሱን በአሁኑ ተጠሪ ላይ ለማቅረብ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት አለው ከሚባል በቀር የተለዬ ትርጉም የሚያሰጥ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህም የትርጉም መስመር ባሻገር የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ግዴታ በትክክል እና ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ተመልክቶ ሕግን መሠረት ያደረገ ፍርድን መስጠት እንዲቻል ከተዘረጋው የክርክር አመራር ሥርዓት አንፃርም ይታይ ቢባል ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲመች የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.40/2/ በተመለከተው መሠረት ማድረግም እየተቻለ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ብቻ በመገደብ የአሁን አመልካች በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ መብት የለውም በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የአሁን አመልካች በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የለውም በሚል ተወስኖ የበላይ የሆነው በአማራ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ጉዳዩን ተመልክቶ በመ/ቁ. 468/01 ታህሣሥ 10 ቀን 2005 ዓ.ም ይህንኑ ውሣኔ በማጽናት የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ተሽሯል፡፡

2/በጉዳዩ የአሁኑን አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው ክርክር የሚያመለክት በመሆኑና አስፈላጊም ሆኖ በተገኘ ጊዜ ባለጥቅሙ ነው የተባለውንም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የሥነ ሥርዓት ሕጉ የሚፈቅድ በመሆኑ ይህንኑ ወገን የክርክር ተከፋይ በማድረግ ክርክሩ ቀጥሎ ይወሰን ዘንድ ጉዳዩን ወደ ክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት ወስነናል፡፡

3/ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በማሰማት ውሣኔ እስኪሰጠው ድረስ ላወጡት ወጭና ኪሣራ በየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

የሰ/መ/ቁ 88959

ህዳር 17 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት ነ/ፈጅ አባይነህ ዘውዱ

ተጠሪ፡- ደብረ አማን ተክለኃማኖት ቤተክርስቲያን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍረድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 190802 ጥቅምት 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 128307 ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወን ነው፡፡ ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክስን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በካርታ ቁጥር 11/35/77/00 በሚታወቀው ይዞታ ኃይማኖታዊ አገልግሎት ለህዝብ የምሰጥበት ህጋዊ ይዞታ ቦታ አለኝ፡፡ ከሳሽ ኃይማኖታዊ በዓላት የማከብርበት ምዕመናኑ መኪና የሚያቆሙበት በከፍተኛ ወጭ ያፀዳሁትና ከቀበሌ አስተዳደር በብሔራዊ ደህንነትና ከፖሊስ ጋር በመተባበር የፓርኪንግ አገልግሎት ሥር በሆኑ ወጣቶች የምሰጥበት ለአንድ መቶ አራት ዓመታት በያዝኩት ቦታ የፓርኪንግ አገልግሎት መስጠቴን እንዳቆም ተከሳሽ ታህሳስ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በፅሑፍ ትዕዛዝ በመስጠት ሁከት የፈጠርብኝ በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድ ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርባለች፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ (ተጠሪ) የሁከት ክስ ያቀረበችበት ቦታ ከከሳሽ ህጋዊ ይዞታ እና አጥር ውጪ የሚገኝ ክፍት ቦታ ነው፡፡ ቦታው በካርታው ውስጥ የተጠቃለለ አይደለም፡፡ በቦታው ላይ ቀደም ሲል የኢትፍሩት ኮንቴነርና ተንቀሳቃሽ ሽንት ቤት ተቀምጦበት እንደነበር ከሳሽ ለክሳቸው ገልፀዋል፡፡ ተከሳሽ የመንግስት ቦታ የማስተዳደር ስልጣን በህግ ተሰጥቶታል፡፡ ከህብረተሰቡ በቀረበለት አቤቱታ መሰረት ከሳሽ የፓርኪንግ አገልግሎት እንዳትሰጥ መከልከሉ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ ቦታው ከአጥር ውጭ የሚገኝ ቢሆንም ከሳሽ በእጇ አድርጋ ይዛ ስትገብርበት የኖረችው ይዞታዋ ነው፡፡ ተከሳሽ የዚህን ቦታ ከሳሽ የፓርኪንግ አገልግሎት እንዳትሰጥ የፃፈው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ የፓርኪንግ አገልግሎት

እንዳትሰጥ የፃፈው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነው ስለዚህ የፓርኪንግ አገልግሎት እነዳይሰጥ የሰጠው ትዕዛዝና ክልከላ ተወግዷል፡፡ በክሳሽ ይዞታ ላይ የፈጠረው ሁከት ይወገድ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች ሚያዝያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ቦታው የተጠሪ ይዞታ አይደለም በቦታው የነበረው የኢትፍሩት ኮንቴነርና ጊዜያዊ ሸንት ቤት የተነሳው በአስተዳደሩ ፈቃድ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ቦታውን የፓርኪንግ አገልግሎት እንዳትሰጥበት የፃፍኩት ደብዳቤ የሁከት ተግባር አይደለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ መሬቱ ለረዥም ዓመታት በእኛችን አድርገን ስንጠቀምበት የነበረ ህጋዊ ይዞታችን ነው፡፡ ስለዚህ በይዞታችን ላይ የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላት እንድናከብር ለምዕመናን የፓርኪንግ አገልግሎት እንዳንሰጥ አመልካች የወሰነው ውሰኔ የሁከት ተግባር በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች ሰኔ 13 2005 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልስ መልሱ ውሳኔው ደንብ ቁጥር 14/1996 ድንጋጌዎችን ያገናዘበ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ በአጥር ካጠረውና በካርታ ቁጥር 01-11.35/77/00 ከሚታወቀው ቦታው ፊት ለፊት የሚገኘው ቦታ ላይ የምትሰጠውን የፓርኪንግ አገልግሎት እንድታቆም አመልካች የፃፈው ደብዳቤ የሁከት ተግባር ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ያቀረበችበት ቦታ ከቤተክርስቲያኑ አጥር ክልል ውጭ የሚገኝና የቤተክርስቲያኗን ህጋዊ ይዞታ በሚያረጋግጠው የካርታ ቁጥር ል11-35/77/00 የማይጠቃለል ነው፡፡ አከራካሪው ቦታ በቤተክርስቲያኗ ፊት ለፊት የሚገኝ ተጠሪ ከመቶ ዓመታት በላይ ኃይማኖታዊ በዓላትን ለማክበር ምእመናን ፀሎት ለማድረግና መኪኖቻቸውን ለማቆም ሲጠቀሙበት የኖሩ መሆኑን ተጠሪ ከስር ፍርድ ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበችው ክርክር በግልፅ አስፍራለች፡፡ ከዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የከተማ ቦታ የማስተዳደርና የትኛው ቦታ ለምን አይነት አገልግሎት መዋል እንዳለበት የመወሰን ስለጣን ያለው የከተማው አስተዳደር ነው ወይስ የቦታው ተጠቃሚና ባለይዞታ ነን የሚለው ግለሰብ ድርጅት ወይስ ኃማኖታዊ ተቋም? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

6. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ማስተዳደር ሥልጣን ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንደሆነ በአዋጁ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2(ሰ) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ከወረዳው ክልል ሥር ያለውን ከተማ መሬት ማስተዳደር የትኛው ቦታ ለፓርኪንግ አገልግሎት የሚውል ስለመሆኑ የትኛው ለፓርኪንግ አገልግሎት እንደሚሆን የከተማዋን መሪ ፕላን የማህበረሰብ ደህንነትና የፀጥታና ሌሎች ቦታዎችን በማገናዘብ የመወሰን ሥልጣን ያለው አመልካች ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) እና አንቀፅ 38 ድንጋጌዎች ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. አመልካች ከላይ በገለጽነው ህግ ድንጋጌ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የወረዳ አስተዳደር ስልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን የወጣውን አዋጅ መነሻ በመድረግ ተጠሪ ከይዞታው ፊት ለፊት ባለው ቦታ ላይ የፓርኪንግ አገልግሎት መስጠቷ ለህዝብ ደህንነትና ፀጥታ አስጊ በመሆኑ አገልግሎቱን እንድታቆም የፃፈው ደብዳቤ አመልካች በህግ የተጣለበትን ኃላፊተን እየተወጣ መሆኑን የሚያሳይ እንጅ የሁከት ተግባር አይደለም በመሆኑም አመልካች ተጠሪ በአጥር ከታጠረውና ከህጋዊ ይዞታው ፊት ለፊት ባለው ቦታ ላይ የምትሰጠውን የመኪና ፓርኪንግ አገልግሎት እንድታቋርጥ በቁጥር ል/ክ/ከ/ወ/አስ/624/2004 ታህሳስ 12 ቀን 2004 ዓ.ም የፃፈው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የሁከት ተግባር ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2(ሰ) አንቀፅ 33 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የፃፈው ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ሁከት ተግባር አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በወረዳው ክልል ውስጥ ያለውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ማስተዳደርና የከተማውን ፕላን መሰረት በማድረግ የትኛው ቦታ ለምን ዓይነት አገልግሎት መዋል እንዳለበት መወሰን ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 36/1995 እንደተሻሻለ ደብዳቤ መፃፉ ሁከት አይደለም በሚል ወስኗል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

የሰ/መ/ቁ. 92546

ታህሣስ 18 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱራዛቅ ኢብራሒም ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ህግ ድንበሩ አንዳርጌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፍትህ ሚኒስቴር ሚንስትር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣውን የዐቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/1991 ድንጋጌዎች በሚጥስ ሁኔታ ዐቃቤ ሕግነት ተመድቤ ሣገለገል የነበረኩትን አመልካች ከሥራ እንድስናበት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሚኒስትሩ ውሣኔም በቁጥር 02/አሠአ.128/10/1 ግንቦት 8 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተገልፆልኛል፡፡ የፍትህ ሚስቴር የአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/1991 ከሚደነግገው ውጭ ካለአግባብ ስልጣኑን በመጠቀም ከሁለት ወር በላይ ከሥራና ከደመወዝ አግዶ አቆይቶኛል፡፡ ከሁሉም በላይ አመልካች ቀርቦብኝ የነበረውን የዲሲፕሊን ክስ በበቂ ሁኔታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያላስረዳ በመሆኑ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሣያስፈልገኝ በነፃ የተሰናበትኩ መሆኑን በመግለጽ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤው ውሣኔ ሰጥቶ ውሣኔው በቁጥር 24/ሠ-16/91/4 ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ገልፆልኛል፡፡ ይህንን የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ሚኒስትሩ ሲሽር ለቀረበብኝ ይግባኝ መልስ እንድሰጥ እድል እልተሰጠኝም፡፡ እንደዚሁም የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ ከተሻረም ጉዳዩ ወደ ጉባኤው ተመልሶ የመከላከያ ማስረጃውን የማቅረብ መብቴ ሊጠበቅ ሲገባው የእኔን የመከራከርና የመከላከል መብት ሣይጠበቅ የተሰጠው ውሣኔ ደንብ ቁጥር 44/1991 እና የውሣኔ አሠጣጥ ስርዓትን የሚጥስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸ የሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሰበር አይቶ እንዲያርምልኝ በማለት ነሐሴ 6 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡
2. አመልካች ከሰበር አቤቱታው ጋር በማያያዝ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ አመልካች የዲስፐሊን ጥፋት የፈፀመ ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ ከቀረበበት የዲስፐሊን ክስ የመከላከል ማስረጃ ማቅረቡ ሣያስፈልገው በነፃ የተሰናበተ መሆኑን በመግለጽ በቁጥር 24/ሠ-16/91/4 ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም የፃፈውን



www.chilot.me

ደብዳቤና በፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ፊርማ አመልካች ከሥራ የተሰናበተ መሆኑን በመግለጽ በቁጥር 02/አሠደ-128/10/1 ግንቦት 8 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ በማያያዝ አቅርቧል፡፡

3. አመልካች ላቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ መልስ በጽሑፍ እንዲያቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ተጠሪ መስከረም 30 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ የሻረው በአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/1991 አንቀጽ 78 እና አንቀጽ 79 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ባስተላለፈው ውሣኔ መሠረት ነው፡፡ ውሣኔው በደንቡ መሠረት የተሰጠ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ጥቅምት 15 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. የጉዳዩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር የአቃቤ ሕግ አስዳደር ዋና ጉባኤ የሰጠውን ውሣኔ የሻረው አስገዳጅነት ያላቸውን የሕግ ሥርዓቶች በመከተልና የደንብ ቁጥር 44/9/ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ የዲስፐሊን ክስ የቀረበበት ዐቃቤ ሕግ በደንቡ የተጠበቁለት መሠረታዊ መብቶችን መመርመር አስፈላጊ ነው የዲስፐሊን ክስ የቀረቡለት አቃቤ ሕግ ላይ ያቀረበበትን የዲስፕሊን ክስ ለማጣራትና አቃቤ ሕጉ በሕጉ መጣራት ማስረጃዎችን ለማሠባሠብ አስፈላጊውን የአፈፃፀም ሥነ ሥርዓት መጠቀም እንዳለበት በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ ጉባኤው ይህንን የማጣራት ግዴታውውን በመወጣት ከተገቢ የውሣኔ ሃሣብ ላይ ለመድረስ በዲስፐሊን የተከሰሰው አቃቤ ሕግና መሥሪያ ቤቱ እያንዳንዳቸው ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ ማድረግ እንዳለበት በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ አቃቤ ሕጉ በመስሪያ ቤቱ የቀረበለትን ክስና ማስረጃ የማስተባበልና መከላከያ የሚሆኑት ነጥቦች የማቅረብና የመከላከያ ማስረጃ የመስማት መብት ያለው መሆኑ የሚደነግግ ነው፡፡
6. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ክስ የቀረበበት አቃቤ ሕግ ለቀረበበት ክስ መልስና መከላከያ ለማቅረብ እንዲቻል የቀረቡትን ክስ በዝርዝር የሚገልጽ የክስ ጽሑፍ ክሱን ለማረጋገጥ የቀረበበትን ማስረጃ መልስ የሚሰጥበት ቀን ሠዓት ቦታ ከሚገልጽ መጥሪያ ጋር እንዲደርሰው ማድረግ እዳለበት በደንቡ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ይህም አቃቤ ሕጉ የቀረበበትን የዲሲፐሊን ክስ ለመከላከል የሚችልበትንና ማስረጃ የሚሰማበትን ቀን የማወቅ መብት ያለው መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ የሰጠው የአመልካች የመከላከያ ማስረጃን በመስማትና በመመዘን እንዳልሆነና፣ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የተጠሪን ምስክሮቹ ከሰማ በኃላ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ የአቃቤ ሕጉን /የአመልካችን/ መከላካያ ማስረጃ መስማት አስፈላጊ አይደለም በማለት ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ ሣይሰማ የተጠሪን ክስ በደንቡ አንቀጽ 84 ንዑጽ አቀጽ /ሀ/ በሚደነግገው መሠረት ውድቅ በማድረግ አመልካች በተከሰሰበት የዲስፐሊን ጥፋት አልፈፀመም በማለት በነፃ ያሰናበተው መሆኑ ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም በፃፈውና በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ ይዘት በሚገልፀው ደብዳቤ ለመረዳት ይቻላል፡፡
7. በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ክርክር ጉዳዮች ሚኒስትር ዴኤታ ይግባኝ ለፍትሕ ሚኒስትሩ ያቀረቡ መሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር ተረድተናል፡፡ የክርክር ጉዳዮች

ሚኒስትር ዴኤታ በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሚኒስትሩ ማቅረቡ የደንቡን አንቀጽ 85 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ ሕጋዊነቱ ክርክር የሚያስነሣ አይደለም፡፡ አክራካሪው የሆነው ሚኒስትር ዴኤታው በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉብኤ ውሣኔ ቅር በመሠኘት የቀረበውን ይግባኝ ሚኒስትሩ ያስተናገደበት ሥርዓትና ሚኒስትሩ አቃቤ ሕግ የአስዳደር ጉባኤ ውሣኔን በመሻር አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ በደንቡ አመልካች በአንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጠውን ክስን የመከላከልና የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብት በጠበቀ ሁኔታ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ነው፡፡

8. ሚኒስቴር ከአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የቀረበውን ይግባኝ የማያስተናግድበት ዝርዝር ሥርዓት በደንቡ አንቀጽ 85 አልተደነገገም፡፡ ሆኖም ይህ ማለት በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በዲስፒሊን የሚያስከስስ በቂ ማስረጀ በሚንስትር መሥሪያ ቤቱ አልቀረበበትም ተብሎ በደንቡ አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ መሠረት የዲስፒሊን ክሱ የተሰራበትን አቃቤ ሕግ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ዝርዝር ይዘት አውቆ መልስ እንዲሰጥበት ሣያደርግ ሚኒስትሩ ሚኒስቴር ዴኤታው ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ብቻ በማየት ውሣኔ ይሰጣል ማለት እንዳልሆነ በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገገው የአቃቤ ሕጉ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ የማወቅና የመከላከያ መልስን ማስረጃውን የማቅረብ መብት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሚኒስቴር አመልካች ተጠቃሚ የሆነበትን የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ በደንቡ አንቀጽ 85 መሠረት በይግባኝ አይቶ ውሣኔውን የሚያሻሽለው ወይም የሚሽረው በሆነ ጊዜ በደንቡ አንቀጽ 82 እና አንቀጽ 83 የተደነገጉት ሥርዓቶች በመከተል አቃቤ ሕጉ የቀረበበትን ይግባኝ ማመልከቱ በጽሑፍ እንደደረሰውና መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ የአቀቤ ሕጉን የመከራከርና የመሰማት መብት የማክበር ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

9. ስለዚህ ምክንያቱ በደንቡ አንቀጽ 85 በሚኒስትሩ የተሰጠው የይግባኝ ስልጣን አስተዳደራዊ ስልጣን ሣይሆን የዳኝነት ነክ ስልጣን መሆኑ ነው፡፡ የዳኝነት ወይም ከፊል የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ክርክርና ክርክሩን የሚደግፉለትን ማስረጃ የማቅረብና ፍትሕ የማግኘት መብት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 እውቅናና ጥበቃ የተሰጠው መብት ነው የዳኝነት ነክ ስልጣን በሕግ የተሰጠው አካልም ለተከራካሪዎቹ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25 የተደነገገው የእኩልነትና እኩል የሕግ ጥበቃና ዋስትና የማግኘት መብት በማክበር ተከራከሪዎቹ ክርክራቸውን እንዳያቀረቡ ማድረግና ለተከራካሪዎች እኩል እድል የመስጠትና ጉዳዩን ገለልተኛ ሆኖ የመመርመር ውሣኔ የመስጠት ግዴታ አለበት ከዚህ አንፃር በያዝነው ጉዳይ ሚኒስትሩ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም መስሪያ ቤት ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ለአመልካች እንዲደርሠውና መልስ እንዲሰጥበት ሣያደግ አመልካች የዲስፐሊን ጥፋት አልፈፀመም ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ መሻሩ ከላይ በዝርዝር የገለጽነውን አስገዳጅ የሆኑ ክርክር አሠራር ሥርዓትና ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. ሚኒስትሩ መሥሪያ ቤቱ በአንቀጽ 85 መሠረት የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ያቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ አመልካች ደርሶት መልስ እንዲሰጥበት ሣያደረግ ውሣኔውን መሻሩ የመጀመሪያ ክርክር አሠራር ሒደት የፈፀመው ስህተት መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሚኒስትሩ የሰጠውን ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ምክንያቱም የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በሚኒስተር መ/ቤቱ በአመልካች ላይ የቀረበውን የዲሲፐሊን ክስ ውድቅ ያደረገው የዲሲፐሊን ክስ የቀረበው መስሪያ ቤት

አመልካች የዲስፕሊን ጥፋት የፈፀመ መሆኑን በማስረዳት ያቀረባቸው ምስክሮችና ማስረጃዎች ክሱን አላስረዱም የዲስፕሉን ክስ የቀረበው አካል ክሱን በበቂ ማስረጃ ያላስረዳ በመሆኑ ተከሣሹ /የአመልካቹ/ የመከላከያ ማስረጃ መስማት አስፈላጊ አይደለም በማለት አመልካች በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠበቀለትን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና የማሰማት መብት በማለፉ እንደሆነ የሰበር አቤቱታው ጋር ተያይዞ የቀረበው የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔን በያዙት ከሚገለፀው ደብዳቤ ተረድተናል፡፡

11. ሚኒስትሩ በደንቡ አንቀጽ 85 መሠረት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቀረበውን የተሰማው ማስረጃ የዲስፕሊን ክሱ በዚህ ሁኔታ ለማስረዳት የሚችል ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ መሻር ጉባኤው ጉዳዩን እንደገና በማየትና አመልካች በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና የማሰማት መብት ተጠቅሞ የሚያቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በማስማት ጉባኤው ውሣኔ እንዲሰጥ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ሚኒስትሩ ይህንን ሥርዓት ለመከተል ካልፈገለ አመልካች ለአቀቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በመከላከያ ማስረጃ አድርጎ የቆጠራቸው ምስክሮች እዲያቀረብና እንዲያሰማ በማድረግ ሌሎች የመከለካያ ማስረጃውን ተቀብሎ በመመርመር አመልካች በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 የተሰጠውን የመከላከያ ማስረጃ የማቀረብ መብት በማክበርና በማስከበር ውሣኔ የመስጠት ኃላፊት አለበት ሚኒስተሩ የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብት የሚከበርበት ሁኔታ ሣይፈጥር ወይም አመልካች የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርብ እድል ሣይሰጥ የአቀቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔን በመሻር አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ የአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/1991 አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስ እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች ሚኒስትሩ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔን በመሻር አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ አስገዳጅ የሆኑ የክርክር አመራር ሥርዓት ያልተከተለና የአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 85 ድንጋጌዎችን መሠረታዊ ይዘት መንፈስና አላማ ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 79/1/ ድንጋጌዎችን መሠረት ማድረግ ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. ሚኒስትሩ የክርክር ጉዳዮች ዴኤታ ባቀረበው ይግባኝ ባይ አመልካች መልስ እንዲሰጥ ሣያደግርና የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብት ሣያከብርና እንዲከበር ሣያደርግ አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 75877

መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-**የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር - ዜናዬ ታደሰ

አሰለፈች መርሻ } ጠበቆች ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ -ነገረፈጅ ሙዑዝ ገ/ልዑል ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በተጠሪ የታገደ ገንዘብ ይለቀቅልኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በይግባኝ ደረጃ የታየው በተጠሪ ቦርድ ነው፡፡ በዚህ ቦርድ አቤቱታ አቅራቢ የነበረው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የአቤቱታው ዋና ሐሳብም አመልካች ማህበር ከውጭ ካገኘው እስከ 12,000,000.00 (አስራ ሁለት ሚሊዮን) ብር በጀት በመጠቀም በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ መሰረት እስከ መጨረሻው ለመስራት ዝግጅት ሲያደርግ መቆየቱን፣ ኤጀንሲው ታህሳስ 14 ቀን 2002 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ በበጎ አድራጎት ማህበሩ የባንክ አካውንት ውስጥ ከነበረው ከ10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን) ብር በላይ እንዳገደበት እና 1,596,229.00 እንደለቀቀለት፣ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 ተፈጻሚነት ከየካቲት 06 ቀን 2002 ዓ/ም በኂላ እንደሚሆን በኤጀንሲው ተገልፆ እያለ የዝግጅት ስራ እስከዚያው ድረስ ለመጨረስ አመልካች እየተንቀሳቀሰ በነበረበት ወቅት በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 10 የአዋጁ አፈፃፀም መሸጋገሪያ ጊዜ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታ፣ አዋጁ ነባር ድርጅቶችን ቀድሞ የነበራቸውን ሀብትና ንብረት ይዘው እንዲሸጋገሩ የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ሳይኖሩበት፣ ማህበሩ ከኪራይ ነጻ ሆኖ ለተገልጋዮች ነጻ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችለውን ቤት ለመግዛት ብር 8,600,000.00 (ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ብር) እንደሚያስፈልገው ለኤጀንሲው አቅርቦ እያለና ቀድሞ ይህን እንዳያስፈጽም በፍትህ ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባና ጽ/ቤት የፈቃድ እድሳት ቆሞ በመቆየቱ አመልካች ማስፈጸም ያለመቻሉን፣ በመሸጋገሪያ ጊዜ ለመጠቀም አመልካች ያቀዳቸውን ተግባራት ለማከናወን የባንክ አካውንቱ በኤጀንሲው በመታገዱ ምክንያት ማህበሩ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መውደቁን በመዘርዘር ቦርዱ አመልካች በመሸገገሪያ ጊዜ ለማስፈጸም ያቀዳቸውን እቅዶችን ለማሳካት፣ የድርጅት ሰራተኞችን ደመወዝ በግማሽ እንዲቀንስ አድርጎ ባለበት ሁኔታና ለጋሾች ገንዘቡን አመልካች ድርጅት ባለመጠቀሙ መልሰው እንዲወስዱት ከማድረግ በሴቶች መብት ላይ የሚሰራው አመልካች ድርጅት



www.chilot.me

እንዲጠቀምበት ይወስንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በአዋጁ መሰረት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ መመዝገቡንና የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ደግሞ ከ10 ከመቶ በላይ ከውጭ ገቢ ምንጭ መጠቀም እንደማይችል አዋጁ የሚከለክል መሆኑንና ማኅበሩ ከውጭ የሰበሰበው በርካታ ገንዘብ የነበረው ከመሆኑም በላይ አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 በኋላም በርካታ ገንዘብ ከውጭ የገቢ ምንጮች የሰበሰበ መሆኑን፣ አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም በኋላ በቀድሞ ሕጎች የተገኙ መብትና ግዴታዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት አዋጁን የማይቃረኑ ከሆኑ ብቻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 111(1) መደንገጉንና ድርጅቱ ኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ በመሆኑ ገንዘቡን ለተሰማራበት ዓላማ መጠቀም የማይችል መሆኑን፣ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከአገር ውስጥ 90% የሚያመነጭ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ መመዝገቡን ከመመዝገቡ በፊት ከውጭ ምንጭ የሰበሰበው ገንዘብ መጠቀም ስለማይችል በኤጀንሲው መታገዱን፣ በአዋጁ መሰረት ገንዘቡን ለሌላ ድርጅት ማስተላለፍ ቢቻልም ኤጀንሲው የወሰደው አቋም ግን በየአመቱ 90% ከአገር ውስጥ አመንጭቶ ለኤጀንሲው ሲያቀርብ ቀሪው 10% ደግሞ ከታገደው ገንዘብ ውስጥ እየተለቀቀለት መንቀሳቀስ እንዲችል የሚያደርግ መሆኑን ዘርዝሮ አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ቦርዱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 104 በተዘረጋው የይግባኝ ስርዓት መሰረት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የቦርዱ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ አከራካሪውን ገንዘብ ለማገድ ሕጉ ስልጣን የማይሰጠው መሆኑና እገዳውም የተደረገው አመልካች ድርጅት ሕጉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በልዩ ልዩ ሁኔታና ሕጋዊ መንገዶች ከውጭ ምንጭ የተገኘ ገንዘብ መሆኑና ለቤት መግዣ እቅድ ይዞ ፈቃዱ ባለመታደሱ ምክንያት እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ያልቻለ መሆኑን፣ የአመልካች የመከራከር መብት በቦርዱ በአግባቡ ያልተጠበቀለት መሆኑን ዘርዝሮ በጠቅላላው ገንዘቡ የሚታገድበት ሕጋዊ አግባብ ያለመኖሩንና የተጠሪ እርምጃም ሕገ መንግስቱንና አለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ስምምነትን የሚጻረር ስለመሆኑ ጠቅሶ ገንዘቡ የሚታገድበት ሕጋዊ አግባብ የለም ብሎ መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 111(1)፣ አዋጁን ለማስፈፀም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 10(2) እና የፍትህ ሚኒስትር መጋቢት 16 ቀን 2001 ለተለያዩ የፌዴራልና የክልል አካላት በአዋጁ መሰረት የምዝገባና የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት እስከሚጀምር ድረስ ነባር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቀደም ሲል ሲሰሩ በነበረበት ሁኔታ ስራቸውን መቀጠል እንደሚችሉ በመግለጽ ከፃፈው ደብዳቤ አንፃር ለመመርመር ሲባል ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለቦርዱ አቤቱታውን ሊያቀርብ የቻለው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመፅናቱ በፊትም ሆነ የምስክር ወረቀት እስከተሰጠበት እስከ ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ከውጭ የተሰበሰበውን ገንዘብ ያላግባብ አግዶብኛል፣ ይህንን ለማድረግም አዋጁም ሆነ ደንቡ አይፈቅዱለትም፤ ስልጣን አይሰጡትም በሚል

ምክንያት መሆኑን ነው። በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የሠበር ቅሬታም ተጠሪ በሕጉ ስልጣን ያልተሰጠው ከመሆኑም በላይ የአዋጁንና የደንቡን ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍትህ ሚኒስቴር መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ/ም የተፃፈው ደብዳቤ ይዘት ባላገናዘበ መልኩ እገዳውን ማከናወኑንና በቦርዱ በነበረው ክርክርም የመከራከር መብቱ በስነ ስርአት ሕጉ መሰረት ሳይጠበቅለት የቀረ ስለመሆኑ ዘርዝሮ መከራከሩን ተመልክተናል።

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከውጪ የሚሰበሰበው ገንዘብን መሰረት በማድረግ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት ትርጉም፣ አይነታቸውንና ዓላማቸውን ለይቶ ገደብ ያደረገ ስለመሆኑ የሚያመላክቱ ድንጋጌዎችን ይዞ ይገኛል። ይህንኑ መለኪያ መሰረት አድርጎም አዋጁ ሶስት አይነት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በአገሪቱ የህግ ማዕቀፍ የሚታወቁ መሆኑን የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል። የአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ ቁጥር (2)፣ ንዑስ ቁጥር (3) እና ንዑስ ቁጥር (4) ድንጋጌዎች እንደየቅደምተከተላቸው ሲታዩም የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት እና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጀት በሕጉ የሚታወቁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማህበራት አይነቶች መሆናቸውን በመጥቀስ ትርጓሜአቸውን አስቀምጠው እናገኛለን። የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶና የማህበራት አይነት የሚወሰነው በመሰረታዊነት የገቢ ምንጭን በመመርኮዝ ስለመሆኑ ያስረዳል። በመሆኑም በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ኢትዮጵያዊ ነው ተብሎ ሊመደብ የሚገባው በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት መመስረቱ ብቻ ሳይሆን ከውጪ ምንጮች የሚገኘው የገቢ መጠን ከጠቅላላ ገቢው አስር ከመቶ (10%) የማይበልጥ ሲሆን ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል። ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከጠቅላላ ገቢው ከአስር ከመቶ በላይ የሆነውን ገቢ ከውጭ ምንጮች ስለማግኘቱ ከተረጋገጠ የኢትዮጵያ ነዋሪ ተብሎ እንደማይመደብ በአዋጁ አንቀፅ 2(2) እና 2(3) የተቀመጡት የትርጓሜ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል። ሕጉ በዚህ ረገድ ያስቀመጠው የትርጉም መሰረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚሰማራበትን ዓላማ ለመለየትም መለኪያ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 14 ድንጋጌ ከላይ ከተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር ተጣምሮ ሲነበብ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው።

የአዋጁ አንቀፅ 14(2) የበጎ አድራጎት ዓላማዎችን የዘረዘረ ሲሆን በአንቀፁ ንኡስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ስር ደግሞ ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተለይተው የተሰጡትን ዓላማዎችን በግልፅ አስቀምጧል። በዚህ ንኡስ ድንጋጌ መሰረት ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ብቻ ተለየተው የተሰጡት ዓላማዎች የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ማበረታታት፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጾታ እና የሐይማኖት እኩልነት መረጋገጥን ማበረታታት፣ የሕጻናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፣ የግጭት አፈታትን ወይም እርቅን ማስፋፋት እና የፍትህና የሕግ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር ስለመሆናቸው በግልጽ ተለይቶ ተደንግጓል። አዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አይነትና ዓላማቸውን ለይቶ ከማስቀመጡም በላይ አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ እንደሚችል፣ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች፣ የመሻሻገሪያ ድንጋጌዎች እንዲሁም አዋጁ የሚፀናበትን ጊዜ እንደየቅደምተከተላቸው በአንቀፅ 109፣ 110፣ 111 እና በአንቀፅ 112 ስር አስቀምጧል። በዚህ አግባብም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001 አውጥቶ ከጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደረገ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 621/2001 ደግሞ ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 112 በግልጽ ያሳያል። የአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 ንዑስ ቁጥር (1) ድንጋጌ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና

ግዴታ አዋጁን እስካልተቃረነ ድረስ ብቻ እንደሚቀጥል ሲደነግግ ንዑስ ቁጥር (2) ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ድርጅት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ/ም መመዝገቡንና አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከፀናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 በፊትና በኋላ በርካታ ገንዘብ ከውጭ የገቢ ምንጮች የሰበሰበ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው፣ አቤቱታውን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የተጠሪ መስሪያ ቤት ቦርድና ጉዳዩን በይግባኝ እንዲመለከት በአዋጁ አንቀፅ 104(3) መሰረት ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ አመልካችም በርካታ ገንዘብ ከውጭ ምንጮች አዋጁ ቁጥር 621/2001 ከመፅናቱ በፊትም ሆነ ከጸና በሁዋላ መሰብሰቡን ሳይክድ አንዱ የክርክር ነጥብ አድርጎ የሚያቀርበው ጉዳይ አመልካች ድርጅት ገንዘቡን የሰበሰበው ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ቤት ለመግዛት ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊት በማህበርነት ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከወጣ በኋላ በአዋጁ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ዳግም የተመዘገበ በመሆኑ አዋጁ ከጸና በኋላ በአዋጁ ለኢትዮጵያ ማህበር የተፈቀዱትን ዓላማዎች መስራት ያለበት በአዋጁ መሰረት በመሆኑና ይህንኑ ዓላማ ለማስፈጸም ደግሞ ቀድሞ ከውጭ የገቢ ምንጭ ያገኘውን ገንዘብ ለመጠቀም የሚችልበት አግባብ የለም በማለት ቦርዱና ይግባኙን የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ ገንዘቡ ለቤት ግዥ ዓላማ የሚውል ነበር በማለት የሚያቀርበው ክርክር የክርክሩን ሂደት እና ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት የተሰጠውን የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ያላገናዘበ የፍሬ ነገር ክርክር ሁኖ ስለአገኘን የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

እንዲሁም አዋጁ በአንቀጽ 108 ስር አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወደ ሌላ በጎ አድራጎት ድርጅት አይነት ሊቀይር ከፈለገ የሚችል ስለመሆኑ የሚያሳይ ሲሆን አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 18(3) ድንጋጌ ስር ደግሞ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ከውጪ ምንጭ ያገኘውን ገንዘብ ይዞ በሕጉ አግባብ ኢትዮጵያዊ ለመባል የማይችል ስለመሆኑ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ መሰረት እንደገና መመዝገቡ ከውጭ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወደ ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንደተቀየረ አያስቆጥረውም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅት ኢትዮጵያዊ ለመባል መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችና ለኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በሕጉ የተፈቀዱለትን ዓላማዎች አይነት ሳይለይ የቀረበ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ነጥብ ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18 ተፈጻሚነት የሚኖረው በአዋጁ መሰረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈቃድ አግኝቶ ከተመዘገበ በኋላ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች አዋጁ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊት በሕጉ አግባብ ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን አዋጁ ከወጣ በኋላ ዳግሞ ተመዝግቦ በአዋጁ ለኢትዮጵያዊ ድርጅት ወይም ማህበር የተፈቀዱትን ዓላማዎችን ይዞ እንደሚንቀሳቀስ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አዋጁ ከፀናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ከውጭ ምንጭ ከ10% በጀት በላይ መሰብሰብ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የአዋጁን አንቀጽ 2(2)(3)፣ 14(5) እና የደንብ ቁጥር 18(3) ድንጋጌዎችን አንድ ላይ

በምናነብበት ጊዜ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክርም የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ ስላላገኘን የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ከታገደው ገንዘብ ውስጥ ብር 4,987,781.20 ያህሉ አዋጁ ከመፅናቱ በፊት የተሰበሰበ መሆኑን፣ ቀሪው ገንዘብም በችሮታ ጊዜ የተሰበሰበ በመሆኑ አዋጁንና ደንቡን ይቃረናል ሊባል አይችልም፣ የምዝገባ ውጤቱም ከታህሳስ 07 ቀን 2002 በኋላ ነው በማለትም ክርክር አቅርቧል፡፡ ለዚሁ ክርክሩ መሰረት የሚያደርጋቸው የሕግ ድንጋጌዎቹም የአዋጁ አንቀፅ 111(1) የደንቡን አንቀጽ 10(2) ድንጋጌን ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 111 ርዕሱ "የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች" በሚል የተቀመጠ ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው ንዑስ አንቀፅ አንድ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ አዋጁን እስካልተቃረኑ ድረስ እንደሚቀጥል ሲያስቀምጥ፣ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ ያለባቸው ስለመሆኑ በአስገዳጅ መልኩ ደንግጓል፡፡ የደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 10(2) ደግሞ የድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከጸናበት ጊዜ ከአንድ አመት በኋላ ይሆናል ሲል አስቀምጧል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩ ቅራኔ ያላቸው ናቸው ለማለት የሚቻል ሳይሆን እርስ በእርሳቸው የተጣጣሙ ናቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በመሸጋገሪያ ጊዜው ውስጥ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በሕጉ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበሰብ የሚፈቀድበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም የመሸጋገሪያ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ ቀደም ሲል በነበሩ ሕጎች የተገኙ መብቶች እና ግዴታዎች አዲስ ሕግ ሲወጣ አከራካሪ እንዳይሆኑ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ግልጽ ምላሽ ለመስጠት ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩም ቀደም ሲል ለተገኙት መብቶችና ግዴታዎች ተፈፃሚነት ያጣው ሕግ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ሳይሆን በአዲሱ ሕግ እንዲሸፈኑ መደረጉን የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ የሕግ ማዕቀፍ የሌለውና ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 ዓላማ ጋር አንድ ላይ የማይሄድና የማይጣጣም በመሆኑና እንደ አይነታቸውና ባሕርያቸው በተለያዩ ድንጋጌዎች ስለሚገዙ አዋጁ በወጣ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አስፈላጊ መሆኑ መደንገጉ አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጁ የተከለከሉ ዓላማዎችን በቀድሞው ሕግ መሰረት ማከናወን መቀጠል የማይቻል ስለመሆኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ/ም የፍትሕ ሚኒስቴር ፃፈ የሚለውን ደብዳቤ ይዘት ጠቅሶ ያቀረበውን ክርክር ስንመለከተውም የደብዳቤው ይዘት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መፅደቁን አስታውሶ መንግስት በአዋጁ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የሚመዘግብና የሚከታተል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ለማቋቋም በሂደት ላይ ያለ ስለመሆኑ ጠቅሶ ኤጀንሲው ተቋቁሞ በአዋጁ መሰረት የምዝገባና የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት እስከሚጀምሩ ድረስ ነባር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከዚህ በፊት ይሰሩ በነበሩበት ሁኔታ እየሰሩ መቀጠል እንደሚችሉ ለሚመለከታቸው የአስፈጻሚ አካላት ስርኩላሩ መተላለፉን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ሰርኩላር ይዘቱ የሚያስገነዝበው የአዋጁን አፈጻጸም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ኤጀንሲው እስከሚቋቋም ድረስ የሚመለከታቸው አካላት ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ተግባራት የሚያሳይና አዋጁን ለማስፈፀም ይቋቋማል የተባለ ኤጀንሲ ከተቋቋመ በኋላ ግን ሁሉም ነገር በአዋጁ መሰረት መሰራት ያለበት መሆኑን የሚያስረዳ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 2(2) እና 111(2)፣ በደንቡ አንቀጽ 10(2) ድንጋጌዎች መሰረት በችሮታው ጊዜ የራሱን አደረጃጀት በማስተካከል ያልተጠናቀቁ ስራዎችን ለማጠናቀቅ እንዲችል ሕጉ በሰጠው ችሮታ

ጊዜ መንቀሳቀስ የሚገባበት እንጂ ገቢውን ከአዋጁ ይዘትና መንፈስ ውጪ እንዲሰበስብ እድል የሚሰጠውና የአዋጁን አላማ ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ተፈጻሚ የሚሆን አይሆንም፡፡

አመልካቹ ተጠሪ በአዋጁ አንቀፅ 90 ስር ሰፊ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በማመን የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት የሚከራከረው ተጠሪ ገንዘቡን ማገድ የሚችለው አዋጁ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ጊዜ በኋላ ጀምሮ ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር ተፈጽሞ ሲያገኝና ድርጅቱን ከአደጋ ለመጠበቅ አስፈላጊ ሁኖ ሲያገኘው ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

ተጠሪ በሕግ ተቋቁሞ አዋጅ ቁጥር 621/2001 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በሕጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል ያወጣቸውን ደንቦች ለማስፈጸም የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 6 ስር ከተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባራት ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን መፈጸም እንደሚችል በተጠቃሹ አንቀፅ ፊደል "ቸ" ስር ከተቀመጠው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ማየት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 90 መሰረት ለኤጀንሲው የተሰጠውን ስልጣን ስንመለከተው በተጠቃሹ የአዋጁ ድንጋጌ የንብረት ጥበቃ ወይም እገዳ ተግባር የሚፈፀመው ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም በማህበር መፈጸሙ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት ያሳያል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ ያገደው በአዋጁ አንቀፅ 90 መሰረት ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር በአመልካች ተፈጽሟል በሚል አይደለም፡፡ ይልቁንም በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ዓላማ አመልካች ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚያደርገው ሁኖ እያለ አዋጁ ከጸናበት ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ከውጪ ምንጭ በርካታ ገንዘብ ሰብስቧል፣ አመልካች ዓላማው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ሁኖ እስከተመዘገበ ድረስ ይህንኑ ከውጪ የተገኘውን ገንዘብ ለዓላማው ማስፈፀሚያነት ሊያውለው አይችልም በሚል ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ መፍትሔው ምን እንደሆነ አዋጁን ለማስፈፅም የወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18 ምላሽ ይሰጣል፡፡ ይህ የደንቡ ድንጋጌ በኢትዮጵያ ውስጥ በአዋጁ መሰረት ፈቃድ አግኝቶ የተመዘገበ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በበላይ አካሉ ውሳኔ ወደ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሊቀየርና የምስክር ወረቀት ሊያገኝ እንደሚችል በንዑስ ቁጥር አንድ በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን ማንኛውም የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሲለወጥ በባለቤትነቱ ስር ያለን ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት ለተለወጠው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሊያስተላልፍ እንደማይችል፣ በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ መሰረት ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ለመለወጥ ያመለከተ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የነበረው ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት በድርጅቱ የበላይ አካል ወይም **በኤጄንሲው ውሳኔ** ተመሳሳይ ዓላማ ላለው የውጪ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተላለፍ እንደአለበት የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለትና ሶስት እንደየቅደምተከተላቸው ኃይለ ቃልን በያዘ አቀራረፅ ያስቀመጡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካችን አይነት የበጎ አድራጎት ድርጅት ህጉ ከመፅናቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከሕግ ውጪ ከውጭ ምንጭ የሰበሰበውን ገንዘብ ተጠሪ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተመሳሳይ ዓላማ ላለው ድርጅት ወይም ማህበር ማስተላለፍ እንደአለበት የደንቡ አንቀጽ 18(3) በግልጽ ያሳያል፡፡ እንግዲህ በአመልካች የተፈፀመው ተግባር ላይ ተጠሪ በሕጉ ሊያደርገው ይገባ የነበረው ገንዘቡን ከማገድ የበለጠ ውጤት ያለውን፤ ገንዘቡን ለሌላ ተመሳሳይ

ድርጅት ወይም ማህበር ማስተላለፍን የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ከህጉ ከተቀመጠው ያነሰ እርምጃ ተጠሪ መውሰዱ አመልካችን የጠቀመ ነው ከሚባል በስተቀር ለተጠሪ በሕግ ከተሠጠው ስልጣን አድማስ ውጪ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ሊሆን የሚችለው በሕጉ ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር ውጪ ተፈጽሞ ሲገኝ እንጂ በውጤቱ በሕጉ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር ከሚያስከትለው ያነሰና ፍትሓዊ ነው የሚለውን አስተዳደራዊ እርምጃ በመፈፀሙ ተግባሩ ከስልጣኑና ከተግባሩ አድማስ ውጪ ነው ለማለት የሚያስደፍርበት ሕጋዊ ምክንያትና አግባብ የለም፡፡ በሕግ ያልተከለከለን ተግባር መፈፀም ተቀባይነት የማያገኝበት አግባብም የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ስልጣንና የተወሰደውን እርምጃ መሰረት አድርጎ ያቀረበው ክርክርም ከአዋጁ አንቀጽ 90 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም በደንቡ አንቀጽ 18(3) ስር ከተመለከቱት እርምጃዎች ውጤት አኳያ ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

እንዲሁም አመልካች የታገደውን ገንዘብ ለምን እንደሚያውለው የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቤ ተቀባይነት አላገኙም፣ የተጠሪ መልስም እንዲደርስ አልተደረገም በማለት ያቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦች በሰበር አቤቱታው ላይ ያነሳ ሲሆን በአመልካች በኩል ለቦርዱ ቀርቦ ያልታየለት ማስረጃ ስለመኖሩና የመከራከር መብቱም የተጣበበት ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ ባለመሆኑ ይህ ችሎት በዚህ የክርክር ደረጃ የሚቀበላቸው የቅሬታ ነጥቦች ሁነው አልተገኙም፡፡ ይልቁንም አመልካች በቦርዱ የመከራከር እድል እንደተሰጠው ከቦርዱ ውሳኔ ማረጋገጡን፣ የአመልካች የቤት መግዛት እቅድም በቦርዱ መታየቱን፣ ሆኖም አመልካች ቀድም ሲል ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ መቋቋሙና ከአስራ ስድስት አመታት በላይ በሚቆይበት ጊዜ ስራውን የሚያከናውንበትን ቤት ሳይገዛ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 እና በደንብ ቁጥር 168/2001 በተሰጠው የችሮታ ጊዜ ቤቱን ለመግዛት እቅድ ማቀዱንና ለቤት መግዣ ገንዘብ ከለጋሾች ጋር አዲስ ስምምነት በማድረግ በችሮታ ጊዜ ውስጥ እንደቀድሞው ስራውን መቀጠሉን አመልካች ራሱ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ያመነው ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ በግልጽ ያሳፈረው ጉዳይ ስለሆነ የአመልካች ድርጅት የመከራከር መብት አልተጠበቀም፣ ገንዘቡን ለቤት ግዥ ለማዋል ይችል እንደነበር የሚያስረዱለት ማስረጃዎች አልታዩለትም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ አመልካች ማህበር ረዥም አመታት ያህል ስራ ላይ የነበረና ገንዘቡን ቀድሞ ያገኘው ከሆነ የፈቃድ መታደስ መዘገየት ከቤት ግዥ እና አፈጻጸም ጋር ተያያዥነት የሌለውና አሳማኝነት የሌለው ምክንያት ስለመሆኑ ፍሬ ነገሩን በሚያጣራውና ማስረጃዎችን በሚመዝነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠው ስልጣን አንፃር በዚህ ረገድ የቀረቡትን የአመልካችን የቅሬታ ነጥቦች የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዝና ጉዳዮች በመሆናቸው የሚቀበላቸው ሁነው አልተገኙም፡፡

ሲጠቃለልም የአመልካች ተግባር በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 2(2፣3፣እና 4)፣6፣ 14(5)፣90፣111 እና 112፣እንዲሁም በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 10(2)፣18(3) እና 36 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ ገንዘቡ በተጠሪ እንዳይታገድ የሚያደርግበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ተጠሪ ገንዘቡን ማገዱም ሆነ አመልካች ከአገር ውስጥ የገቢ ምንጭ 90% ያህሉን መሰብሰቡ እየተረጋገጠ ከታገደው ገንዘብ ውስጥ 10% እንዲለቀቅለት መደረጉ ሕጋዊ ከሚባልና በውጤቱም ፍትሃዊ ነው ተብሎ ከሚደመደም በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1. በተጠሪ ቦርድ ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 108157 ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት በድምጽ ብልጫ ፀንቷል፡፡
2. የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ውሳኔው በ09/02/05 ዓ.ም ተነበበ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

## የሃሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በአራተኛው ተራ ቁጥር የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ የስራ ባልደረቦች ከሰጡት የህግ ትርጉምና ከደረሱበት መደምደሚያ የተለየሁባቸው ዝርዝር ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 31 በተደነገገውና በወቅቱ ስራ ላይ የነበረውን የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የሴቶች መብት ማስከበርን መሰረታዊ ዓላማው አድርጎ ሲሰራና አገልግሎት ሲሰጥ የበጎ አድራጎት ድርጅት መሆኑ ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡አመልካች በመጀመሪያ ሲመሰረትና በመንግስት ተመዝግቦና ፈቃድ ተሰጥቶት ሲንቀሳቀስ በነበረበት ወቅት ተፈፃሚነት የነበረው የፍትሐብሔር ሕግ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት የወጣ ህግ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ ስለማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች አመሰራረት፣ አሰራር፣ ተግባርና ኃላፊነት እንደዚሁም የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት የደነገጋቸው ድንጋጌዎች ክፍተት ያለባቸው አሁን ካለው ህገመንግስታዊ ስርዓትና ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌዎች ያለባቸውን ክፍተቶችና ችግሮች እንደዚሁም በወቅቱ ያልሸፈኗቸውና ምላሽ ያልሰጣቸው ነባራዊ ችግሮችና ያለንበትን ዘመን በማገናዘብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ለማስተዳደር አዋጅ ቁጥር 621/2001ን አውጇል፡ አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና እንደሚሆን በአንቀጽ 112 የሚደነግግ ሲሆን አዋጁ የካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በነጋሪት ጋዜጣ ታውጆ ወጥቷል፡፡

   የፍታብሔር ህጉ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በአገሪቱ ሊቋቋሙና ተመዝግበው እና ፈቃድ አግኝተው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ማህበሮች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የአገር በቀል (ብሔራዊ) ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የውጭ አገር ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚል መንገድ የሚከፈል የነበረ መሆኑን የፍታብሔር ህጉ አንቀጽ 404 እስከ አንቀጽ 549 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ አዋጅ ቁጥር 621/2001 በኢትዮጵያ ውስጥ ሊቋቋሙ ተመዝግበውና ፈቃድ አግኝተው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ሶስት አይነት ማህበሮችና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንደሚኖሩ ይደነግጋል፡፡ ከነዚሁም " የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት" የኢትዮጵያ ነዋሪዎች

የበጎ አድራጎት ድርጅትና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንደሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2፤ ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንዑስ አንቀጽ 4 ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡

የፍትሐብሔር ህጉ አገር በቀል ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሊሰሯቸው የሚችሏቸውን ተግባራትና ተግባራቸውን ለማከናወን ጥቅም ላይ በሚያውሉት የገንዘብ ምንጭ ላይ የሚጥለው ገደብ አልነበረም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 ህግ አውጭው የዜጎችን መደራጀትና ማህበር የመመስረት መብት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ለህብረተሰቡ ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታና ማህበራቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚያከናውኑት ተግባር አገራዊ አጀንዳ በማራመድና የአገራቱን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳያ መከናወን እንዳለባቸው በማመንና ማህበራቱ የበጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማቸውን ለማሳካት ጥቅም ላይ ሊያውሉት የሚገባውን የገንዘብ ምንጭ መወሰን አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል (በ) እስከ ፊደል (ነ) የተዘረዘሩት ተግባራት ለማከናወን የሚችሉት የኢትዮጵያ የበጎ አድጎት ድርጅቶች ብቻ እንደሆኑና የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከአስር ፐርሰንት በላይ ከውጭ የተገኘ የገንዘብ ምንጭ መጠቀም እንደማይችሉ በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የደነገገ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

አከራካሪ የሆነው ጉዳይ በአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገጉት መሰረታዊ ሁኔታች ከመደንገጋቸው በፊት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 31 የተደነገገውን የመደራጀትና ማህበር የመመስረት መብትና ከላይ መሰረታዊ ባህሪያቸው የተገለጹትን የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ተቋቁሞ ለአመታት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ በነበረው አመልካቹ ላይ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ የሚሆነው አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ከየካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጅ ቁጥር 621/2001 ድንጋጌዎችና ሌሎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን የደንብ ቁጥር 168/2002 ድንጋጌዎች በመጥቀስና በመተርጎም አዋጁ ከየካቲት 1 ቀን 2001 ጀምሮ በአመልካችና በሌሎች ነባር ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ፣ተጠሪ አመልካች ከውጭ ምንጭ የሰበሰበውን ገንዘብ ማገዱ የአዋጁንና ከደንብ ቁጥር 168/2002 ድንጋጌዎች የተከተለ ነው ከሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

2. በእኔ እምነት ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ሲያውጅ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 እና በፍታብሔር ህጉ መሰረት ተቋቁመውና ተመዝግበው የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩት ማህበሮችና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ፈርሰው እንደአዲስ እንዲደራጁና እንዲመሰረቱ የሚያስገድድ ግልፅ ድንጋጌ አላካተተም፡፡ እንዲሁም ህግ አውጭው አዋጁ በመውጣቱ በፊት ተቋቁመው የተለያ ተግባራትን ሲፈፅሙ የነበሩ ማህበሮችና የበጎ አድራጎት ደርጅቶች፣ አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአዋጁ መሰረት ተመዝግበው ፈቃድ እስኪያገኙ ድረስ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተሰጣቸውን ፈቃድ በመጠቀምና አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የነበራቸውን መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ ማናቸውንም እንቅስቃሴ ከማድረግ ራሳቸውን ተገድበው ማቆየት ያለባቸው መሆኑን በግልጽ አልደነገገም፡፡ በአንፃሩ ህግ አውጭው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በነበረው ህግ መሰረት ተመዝግበውና ተቋቁመው የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ የነበሩ ማህራትና በጎ አድራጎት

ድርጅቶች አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና የመመዝገብ ግዴታ እንዳለባቸው በአዋጁ አንቀጽ 711 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ደንግጓል፡፡ ይህም ህግ አውጭው በአዋጁ መሰረት በሚመሰረቱ አዲስ ማህበሮችና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በአዋጁ መሰረት እንደገና በሚመዘገቡ ነባር ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በተመለከተ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ የተለያየ እንደሆነና አዋጁ ለነባር ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ የችሮታ ጊዜ የሚሰጥ መሆኑን የሚያሳይ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህንንም ሀሳብ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ለማስፈፀም የሚችል ደንብ የማውጣት ስልጣን በአዋጁ አንቀጽ 109 የተሰጠው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 168/2002 ድንጋጌዎች የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

ደንብ ቁጥር 168/2002 በአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረት የሚመሰረቱና የሚቋቋሙ ማህበራት የሚመዘገቡበትን መደበኛ የምዝገባ ስርዓት በደንቡ በአንቀጽ 3 እስከ አንቀጽ 9 ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ደንቡ ከአዋጁ ከመውጣቱ በፊት ተቋቁመው የነበሩ ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በድጋሚ ስለሚመዘገቡበት ሥርዓት በአንቀጽ 10 እና በአንቀጽ 11 ይደነግጋል፡፡ በተለይም ደንብ ቁጥር 168/2002 በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁ ከመፅናቱ በፊት የተመዘገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ያለምንም ክፍያ ኤጀንሲው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በድጋሚ ይመዘግባሉ፡፡ የድጋሚ ምዝገባ የሚካሄድበት ዝርዝር በኤጀነሲው ይወሰናል "በማለት በአንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነገገ ሲሆን፣" አዋጁ ከመፅናቱ በፊት በተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ በአዋጁ መሰረት የሚፈፀመው ድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በኋላ መሆኑን በደንቡ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ደንግጓል፡፡

ይኸም በአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 112 የተደነገገው አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ማለትም ከየካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና እንደሚሆን የደነገገው አጠቃላይ መርህ ቢኖርም አዋጅ ቁጥር 621/2001 አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ተመዝግበው ሲንቀሳቀሱ በነበሩ ማህበራትና የበጎ አድራጎት ላይ በአዋጁና በደንቡ መሰረት የሚከናወነው ድጋሚ ምዝገባ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው አዋጁ ከፀና ከአንድ ዓመት በኋላ ማለትም ከየካቲት 6 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ፣ የአዋጁን አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 2ኛ አንቀጽ 109 እና ከደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች ጋር በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል የሚል ምክንያት አለኝ፡፡

3. አዋጅ ቁጥር 621/2001 በአመልካችና ሌሎች አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በህግ መሰረት ተመዝግበው ሲንቀሳቀሱ በነበሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበሮች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው አዋጁ ከወጣ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረስኩት ከላይ በዘረዘርኩት ምክንያት ብቻ አይደለም፡፡ በእኔ እምነት አዋጅ ቁጥር 621/2001 የደነገገው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እያንዳንዷን ድንጋጌ በጥንቃቄና አንድ ለዩ ሁኔታ ለመግለፅ ወይም ለመቆጣጠር በማሰብና አንድ አላማ ለማሳካት የሚል ደንግጎታል ተብሎ ሊታሰብ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህዝብ ከፍተኛ አደራና ኃላፊነት የተሸከመው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጁን ሲያውጅ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ድንጋጌዎች መሰረት

በማድረግና በህገ መንግስቱ የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት በተሟላ ሁኔታ ለመወጣት ተገቢውን ሁሉ ጥንቃቄ በማድረግ በሰከነ ሁኔታ አስቦና አመዛዝኖ ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው መንገድ የአዋጁን ቅርፅና ይዘት አጽድቋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከላይ ከገለፅኳቸውን መሰረታዊ መነሻዎች በመያዝ ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ሲያውጅ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 እና በወቅቱ ስራ ላይ በነበረው የፍታብሔር ህግ መሰረት ተመዝግበውና ፈቃድ አግኝተው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች

- አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በመመሥረቻ ፅሁፋቸውንና መተዳደሪያ ደንባቸውን መሰረት በማድረግ ጀምረዋቸው የነበሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያጠናቅቋቸው የሚችሏቸውን ተግባራት እንዲያጠናቅቁና የተሟላ የፋይናንስና የክንዋኔ ሪፖርታቸውን እንዲያዘጋጁ ለማድረግ
- በህግ ወይም በወል ያገኟቸውን መብቶች ለማስከበርና በህግ ወይም በውል የተጣለባቸውን ግዴታ እንዲፈፅሙ ለማስቻል፣
- አዋጁ ከመውጣቱ በፊትና አዋጁ መሰረት በድጋሚ ከመመዝገባቸው በፊት ያፈሩት እሴትና ያገኙት ገንዘብ በአዋጁ መሰረት በድጋሚ ለሚመዘገቡበት ዓላማ ሊያውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ ለምሳሌ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን እንዲያጠኑና ሰርተው በሚያገኙት ገቢ ላይ ተመስርተው ዓላማቸውን ለማሳካት የሚችሉበት ድርጅታዊ ሁኔታ እንዲያመቻቹ
- በድጋሚ ከመመዝገባቸው በፊት የከናወኗቸው ተግባራት፣ የሰበሰቡት ገንዘብና የላባቸውን ዕዳ በባለሙያ በማስጠናት በድጋሚ ምዝገባ ወቅት ግልፅና የተሟላ መረጃ ለማቅረብ እንዲችሉና ሌሎች እንዚህን መሰል ተግባራት በመፈፀም በአዋጁ መሰረት እንደገና ለመመዝገብና ተግባርና ኃላፊነታችውን እንዲወጡ በመሸጋገሪያነት የሚፈፅሙ ተግባሮችን ፈፅመው የሚያጠናቀቁበት የአንድ ዓመት የችሮታ ጊዜ ሰጥቷቸዋል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ በእኔ እምነት የአዋጁ አንቀጽ 211 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የደንብ ቁጥር 168/2002 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረታዊ ዓላማና ህጋዊ ውጤት ነባር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የድጋሚ ምዝገባው ውጤት ከማግኘቱ በፊት በሽግግር ወቅት ሊፈጸሙና ሊጠናቀቁ የሚገባቸው ተግባራት ለመፈጸም የሚችሉበት የችሮታ ጊዜ መስጠት ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ህግ አውጭው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ተዘግበው ሲንቀሳቀሱ የቆዩ ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ፈርሰው እንደአዲስ መመስረትና መመዝገብ ይገባቸው መሆኑን በግልጽ የሚደነግግ ድንጋጌ ወይም ነባር ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በአዋጁ መሰረት በድጋሚ እስኪመዘገቡ ማናቸውም እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ የሚገደብ ግልፅ ድንጋጌ በአዋጁ ውስጥ በማካተት አዋጁን ያወጣው ነበር፡፡ ህግ አውጭው የተከተለው የህግ አቀራረፅና የድንጋጌዎቹ ይዘት ለነባር ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ምክንያታዊ የሆነ የአንድ ዓመት መሸጋገሪያ የችሮታ ጊዜ የሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው ብዬ ስለማሰብ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

4. ከላይ በገለፅኩት የህግ አተረጓጎም የምሰጠው ሌላም ተጨማሪ ምክንያት አለ፡፡ ይኸውም ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ያወጀው ሶስት መሰረታዊ ዓላመዎችን ለማሳከት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ህግ አውጭው በአዋጁ ሊያሳካቸው የሚፈልጋቸው መሰረታዊ ዓላማዎች፣

* የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የተረጋገጠውን የዜጎች የመደራጀት መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ህግ ማውጣት
* የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በኢትዮጵያ ህዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመደገፍና ለማሳለጥ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማውጣት፣
* አዋጁን ለማስፈጸም የሚችል አስፈፃሚ አካል (የበጎ አድራጎት ማህበራት ኤጀንሲ) ማቋቋምና ስልጣንና ኃላፊነቱን ለመወሰን እንደሆነ ከአዋጁ መግቢያና ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ህግ አውጭው አዋጁን ሲያወጣ ሊያሳካቸው የሚፈልጋቸው እነዚህ መሰረታዊ ዓላማዎች ህግ አውጭው አዋጁን ሲያውጅ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 የተደነገገውን የመደራጀትና ማህበር የመመስረት መብት ለማስከበር የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ማውጣት ግዴታ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጣለበት መሆኑን በማገናዘብ ህጉን ያወጣ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ህግ አውጭው አዲስና የተሟላ የህግ ማዕቀፎች ያወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደዚሁም ህግ አውጭው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ለህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 የተረጋገጠላቸውን መብት በመጠቀም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በነበረው ያልተሟላ የህግ ማዕቀፍ መሰረት ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት የመሰረቱት ዜጎች መብት የማክበር ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት ያውቃል፡፡ ስለዚህ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት በማቋቋም ህገ መንግስታዊ መብታቸውን ዕውን ሲያደርጉ የኖሩ ዜጎች ማህበራቸውን አዲስ ከወጣው ህግ ጋር በሚጣጣም መንገድ እንዲያደራጁ የአዋጁን መስፈርት ከማሟላትና በድጋሚ ለማስመዘገብ የሚያስፈለጋቸውን መስፈርት ለማሟላት የሽግግር ጊዜ /የችሮታ ጊዜ/ የመስጠት ኃላፊነት እንዳለበት በመረዳት የአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ በማካተት አዋጁን አውጥቷል የሚል እምነት አለኝ፡፡

አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብ እንዲያወጣ በአዋጁ አንቀጽ 109 ስልጣን የተሰጠው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት "የድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ድጋሚ ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ከአንድ አመት በኂላ ይሆናል" በማለት በደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ የደነገገበት ምክንያት ህግ አውጭው አዋጁን ያወጣው የዜጎችን የመደራጀትና ማህበር የመመስረት ህገ መንግስታዊ መብት ማክበርና የማስከበር ግዴታውን ለመወጣት የሚችለውን ማናቸውንም ጥንቃቄ በማድረግ አዋጁን ያወጀና የአዋጁ አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረታዊ ዓላማም ለነባር በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ የአዋጁን ተፈፃሚነት በአንድ ዓመት ያህል በማዘግየት በመሸጋገሪያ ጊዜ ማጠናቀቅ የሚገባቸውን ተግባርና እንዲያጠናቅቁ እድል ለመስጠት መሆኑን በአግባቡ በመገንዘቡ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለዚህ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ዓላማና መሰረታዊ ግብ በደንብ ቁጥር 168/2002 የተገለፀ ከመሆኑ በላይ የድንጋጌውን ነባራዊ ተፈፃሚነት የሚዘረዝር በመሆኑ የደንቡ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2፣ የአዋጁን አንቀጽ 112 እና አንቀጽ 111 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የሚቃረን አይደለም ብዬ አስባሁ፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅኩት ምክንያት ተጠሪ አመልካች በቀድሞው ህግ በፊት በነበረው መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ለመፈፀም ያቀዳቸውንና የጀመራቸውን ተግባራት ለማጠናቀቅና ለአመልካች ጽ/ቤት መግዢያ እንዲውል የሰበሰበውን ገንዘብ ለአመልካች በአዋጁ አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 2 በደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 የተሰጠው የችሮታ ጊዜ ማለትም እስከ የካቲት 6 ቀን 2002 የተሰጠው ጊዜ ከማለቁ በፊት ማገዱ የህግ መሰረት የሌለው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

5. ከላይ በዝርዝር የገለፅኳቸው ጠቅላላ የህግ አተረጓጎም ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው ተጠሪ አምልካች በአዋጁ መሰረት በድጋሚ ከመመዝገቡ በፊት አመልካች ያፈራቸውን እሴቶችና ያጠራቀመውን ገንዘብ ምንጩን እንዲያስረዳ የመጠየቅና አመልካች በድጋሚ ሲመዘገብ፣ ለዓላማው ማስፈፀሚያ የሚሆነው የተጠራቀመ ገንዘብና ሌላ ንብረት መጠን ላይ ገደብ የመጣል ስልጣን በአዋጅ አልተሰጠውም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በአዋጁ መሰረት የሚመሰረት አዲስ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከመመዝገቡ በፊት የሚያሰባስበው ገንዘብ ወይም ንብረት ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ ሊሆን እንደማይችል የአዋጅ ቁጥር 61/2001 አንቀጽ 65 ንኡስ አንቀጽ 3 በግልፅ ይደነግጋል፡፡
   አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ተመዝግበው ለዓመታት ሲንቀሳቀስ የቆየ ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 አንቀጽ 2 እና በደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በድጋሚ ሲመዘገብ በንብረትነት ይዞት ሲመዘገብ ስለሚችለውን የገንዘብና የንብረት መጠን የሚገድብ ከአዋጁ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 3 ጋር ተመሳሳይ ድንጋጌ በአዋጁ አልተካተተም፡፡ ይህም በድጋሚ ምዝገባው ማህበሩ የነበረውን ንብረትና ያጠራቀመውን ገንዘብ ይዞ በድጋሚ ሊመዘገብ እበንደሚችልና ተጠሪ በህግ ያልተደነገገን ገደብ እና ሁኔታ አመልካች በድጋሚ ከመመዝገቡ ከአንድ ቀን በፊት በመጣል የአመልካች ገንዘብ ያገደ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደዚሁም የአዋጁ አንቀጽ 90 እና የደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች በዚህ ጉዳይ በጭብጥነት የተያዘውን ጉዳይ ለመወሰን ተጠቃሽና ተፈፃሚ ሊሆኑ የማይችሉና ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው ድንጋጌዎች ናቸው ብዬ ስለማስብ አብላጫው ድምፅ ተጠሪ እነዚህን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ አመልካች በድጋሚ ከመመዝገቡ ከአንድ ቀን በፊት የአመልካችን ገንዘብ የማገድም ሆነ ለሌላ ተመሳሳይ ድርጅት የመስጠት ስልጣን እንዳለው በመተንተን በሰጠው የህግ ትርጉም አልተስማማሁበትም፡፡
6. ተጠሪ ካገደው አመልካች ካጠራቀመው ገንዘብ ውስጥ አመልካች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ ማለትም ከየካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በፊት ያሰባሰበው ገንዘብ እንደሚገኝበት በግራ ቀኙ ክርክር በከፍተኛው ፍ/ቤትና በአብላጫው ድምፅ ውሳኔ ተገልጿል፡፡ ይህም ተጠሪ አመልካች አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ሥራ ላይ በነበረው የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ያገኘውን ገንዘብ ወደኋላ በመሄድ ያገደና የአዋጅ አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መሰረታዊ መርህ የሚጥስ ተግባር ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ በመሰረቱ በአዋጁ የኢትጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከካፒታላቸው አስር በመቶ በላይ ከውጭ ምንጭ እንዳይጠቁሙ ገደብ የተደረገበት ዋንኛ ምክንያት የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የተሰጣቸው የችሮታ ጊዜ ከማለቁ በፊትና አዋጁ ከመውጣት በፊት ያጠራቀሙትን ገንዘብ ለመሰረታዊ ዓላማቸው ማሳኪያ እንዳያውሉ ለመከልከል አይደለም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ በአዋጁ በውጭ

ገንዘብ ድጋፍ ላይ የተጣለው ገደብ ዋና ዓላማው ኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በውጭ ድጋፍ ላይ መንጠልጠላቸው አላማቸውን በራሳቸው አቋምና ገቢ ለማሳካት ጥረት እንዳያደርጉ የሚያደርግና አንድ አንድ ጊዜም የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በለጋሽ ወገኖች የሚቀመጡ ምክንያታዊ ያልሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ለመቀበል የሚገደብበትና ለብሔራዊ አገራዊ ጥቅም እርባና የሌላቸው ነገሮችን ለጋሾች እንዲፈፅሙ የሚፈልጓቸው ተግባራት እንዲፈፅሙ የሚገደዱበትን ሁኔታ ለመከላከልና ለማስወገድ በማሰብ ነው፡፡ አመልካች ለጽ/ቤት መግዢያነት ያጠራቀመውን ገንዘብ መጠቀሙ ወደፊት በራሱ አቅም ዓላማውን ለማሳካት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ከሚደግፈው በስተቀር አዋጁ ከመውጣቱ በፊትና አመልካች በድጋሚ ከመመዝገቡ በፊት የውጭ የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉለት ለጋሾች ሚጣልበት አስፈላጊ ቅድመሁኔታ ቢኖር ቅድመ ሁኔታውን እንዲቀበል የሚያስገድደው አይደለም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለዚህ አመልካች በድጋሚ ምዝገባ በፊት የተጠራቀመውን ገንዘብ ለጽ/ቤት መግዣነት መጠቀሙ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረታዊ ዓላማ የሚጥስ እንደሆነ በማድረግ ተጠሪ የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሰረትና ድጋፍ የሌለው ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 6 በገለፅኳቸው ምክንያቶች አብላጫው ድምፅ ተጠሪ አመልካች አዋጁ ከመውጣቱ በፊትና ከወጣ በኋላ ከውጭ ያሰባሰበውን ገንዘብ ማገዱ ህግን መሰረት ያደረገ ነው በማለት የሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ ባለመስማማት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ት/ዘ

## በ2005 ዓ.ም. የሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | 1 | |
| 1 | በአሰሪ ከተደረገ የሥራ ቦታ ዝውውር ጋር በተያያዘ ሠራተኛው ወደነበረበት ሥራ ቦታና መደብ እንዲመለስ በፍ/ቤት ሲወሰን አሰሪው ሠራተኛው የሥራ ዝውውሩ ከመከናወኑ በፊት ይሰራበት ወደነበረበት ቦታና የሥራ መደብ በትክክል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ፣ | 78536 | በደሌ ቢራ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ አልማው ቤዛ | ታህሳስ 5/2005 | 2 |
| 2 | ሠራተኛ ተቀጥሮ የሚሰራበትን አሰሪ ተቋም መልካም ስምና ዝና እንዲሁም ጥቅምና ህልውና አደጋ ላይ በሚጥሉ ተግባራት የሚፈጽመው ጥፋት መጠንና ደረጃ እና የሚወሰድበትን እርምጃ ለመወሰን ሠራተኛው ከሚሰራው የሥራ አይነትና ባህሪ እንዲሁም ከአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መንፈስና ዓላማ አንፃር መታየት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ሸ)(ረ) | 77134 | ወሰኔ የህክምና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር<br>እና<br>ዶ/ር ክብረወሰን አለማየሁ | ጥቅምት 8/2005 | 5 |
| 3 | የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሰው በሌላ የመንግስት ሥራ ተቀጥሮ ያለአግባብ የወሰደው የጡረታ አበል እንዲመለስ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑና የይርጋ ጊዜውም ግለሰቡ በሌላ የመንግስት ሥራ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣<br>አንድ የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኂላ መልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በቋሚነትም ይሁን በጊዜያዊነት እንዲሁም ደመወዙ ከጡረታ አበሉ ያነሰ ሆነም አልሆነ ከደመወዙና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 46(1) (2)<br>አዋጅ ቁ.209/55 አንቀጽ 30(2)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1677(1) | 72341 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ታዬ አበራ | ህዳር 21/2005 | 9 |
| 4 | የሥራ ክርክር ችሎት አንድን ሠራተኛ ያለአግባብ የተሰናበተ ነው በሚል ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ወደኂላ ቀደም ብሎ ካለ ጊዜ ጀምሮ አሰሪው ወደ ሥራ እንዲመልስ በሚል ውሣኔ የሰጠ እንደሆነ ሠራተኛው ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ ደመወዝ ለማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ፣ | 83012 | ዝዋይ ሮዝ ድርጅት<br>እና<br>ወ/ሮ ፋንቱ ያሲን | ጥር 14/2005 | 14 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያለው የህግ ባለሙያ በሙያው አገልግሎት ለመስጠት ከ3ኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ውል የሚፈጠረው ግንኙነት በእውቀት ሥራ ውል ላይ የተመሠረተ እንጂ ሠራተኛውን እንደ የስራ መሪ ወይም ተቀጣሪ የማያስቆጥረው ስለመሆኑ፡ በአዋጅ ቁ.377/96 የማይገዛ ስለመሆኑ፣ | 81405 | አቶ አህመድ ሲራጅ እና የአወሊያ ዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት | ጥር 29/2005 | 20 |
| 6 | አንድ ሠራተኛ መብቱን ለማስከበር በአሰሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መመስረቱ ብቻ ከአሠሪው ጋር ለወደፊት የሻከረ ግንኙነት ይፈጥራል የማያስብልና የስራ ውሉ እንዳይቀጥል ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43(3) | 82336 | የአብጃታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር እና ማርታ አበበ | ጥር 02/2005 | 22 |
| 7 | ቀደም ሲል ስናገኘው የነበረው የደመወዝ መጠን የተቀነሠ ስለሆነ እንዲስተካከልልን በማለት በሠራተኞች የሚቀርብ ክስ የወል የሥራ ክርክር ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ | 78865 | የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት እና እነ አቶ ገ/ስላሴ ኃ/ማርያም (ስምንት ሰዎች) | ጥር 28/2005 | 26 |
| 8 | •ከሥራ ቅጥር ግንኙነት ጋር በተገናኘ አንድ ሥራ "ቀጣይነት ያለው" ነው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ • አንድ ሥራ በባህሪው "ቀጣይነት ያለው" ነው ለማለት ስራው ረዘም ላለ ጊዜ መስራቱን ብቻ ሣይሆን የሥራው ባህሪ ከአሠሪው ድርጅት (ተቋም) አይነተኛ ሥራ ጋር የሚሄድና በመደበኛነት የሚከናወን መሆኑን ጭምር ማረጋገጥ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣ | 80350 | ሸራተን አዲስ እና እነ አቶ ገናናው ከበደ (ሃምሳ አንድ ሰዎች) | ጥቅምት 20/2005 | 29 |
| 9 | የጡረታ መውጫ እድሜ ወሰንን በተመለከተ አሰሪው ከሠራተኛ ማህበር ጋር የሚያደርገው ስምምነት ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው በተመሣሣይ ጉዳይ ለሠራተኛ በህግ ከተደነገገው ይልቅ የህብረት ስምምነቱ የተሻለ (የበለጠ) ጥቅም የሚያስገኝ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 134(2),24(3) አዋጅ ቁ. 715/2003 አንቀጽ 17(1) | 80079 | የመቶ አለቃ ጥላሁን ታችበሌ እና ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር | ህዳር 19/2005 | 35 |
| 10 | አንድ ሠራተኛ በባህሪው ቀጣይነት ባለው ሥራ ላይ መቀጠሩ መረጋገጡ ብቻ ሠራተኛው ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24(1) | 79853 | የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን እና እነ አቶ ጌታቸው ደበበ (14 ሰዎች) | ህዳር 04/2005 | 38 |
| 11 | ሥራና ሰራተኛን ከመምራት እና ከመቆጣጠር ባለፈ በሠራተኛ ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ ለመውሰድም ሆነ | 79212 | ሮያል ከረሜላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና | ጥቅምት 19/2005 | 43 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከሥራ ለማሠናበት ስልጣን በሌለው የቅርብ አለቃ ሠራተኛው ሥራ እንዲለቅ የተነገረ መሆኑ የሥራ ውል ተቋርጧል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 3(2)(ሐ) | | ወ/ሪት ፀሐይ ብርሀኑ | | |
| 12 | የሥራ ውል ወይም በሌላ ሠነድ ሠራተኛው ስምምነቱን ባልሰጠበት ሁኔታ አሰሪ የሆነው አካል እህት ድርጅት ወደ ሆነ ተቋም (ድርጅት) ሰራተኛውን አዛውሮ ለማሰራት አሠሪ መብት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 83068 | ዲ.ኤች.ገዳ ብርድልብስ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ወ/ሪት ቅድስት ጌታቸው | ታህሳስ 30/2005 | 46 |
| 13 | አንድ ሠራተኛ በሥራው አፈፃፀም ምዘና ደካማ ነው በማለት የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚቻለው ምዘናውን ሠራተኛው በተቀጠረበትና በተመደበበት የሥራ አይነት (መስክ) ላይ በማድረግ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 42, 43(1) | 82335 | ሆሊ ኤንጀልስ ት/ቤት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና መ/ር መልካም አለማየሁ | ጥር 01/2005 | 49 |
| ውል | | | 53 | | |
| 14 | በተዋዋይ ወገኖች በተደረገ የጽሁፍ ሰነድ ላይ የሚገኝ የስምምነት ቃል እንዲሁም በሰነድ ላይ ስለተመለከተው (ስለተፃፈው) ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ውሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው በሚል ለመደምደም የሚቻለው እንደ ውለታው አይነት የጽሁፉ ውል አደራረግን በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በተሟላ ሁኔታ የተዘጋጀና የያዘ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት በህጉ አግባብ ባልተደረገበት ሁኔታ በውሉ ላይ የሠፈሩት ማናቸውም የውል ቃሎች ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዳሉ የሚታመኑና በማናቸውም የሰው ምስክርነት ቃል ማስተካከል አይቻልም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ አንድ ውል በህግ ፊት የፀና ነው እንዲባል በህግ ውሉ የሚደረግበትን አግባብ በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በተመለከተ የተደረገ ካልሆነ በቀር ውሉን መሠረት በማድረግ እንደውሉ ይፈፀምልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ2005(1),1678(ሐ),1719(2,17 | 78398 | እነ አቶ ሽፈራው ደጀኔ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሲሳይ አበቡ | ጥቅምት 19/2005 | 54 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 23) | | | | |
| 15 | የአላቂ ነገር ብድር ውል ጋር በተገናኘ፣ የመመለሻ ጊዜው በግልጽ ተለይቶ የተሰጠን የገንዘብ ብድር በተመለከተ አበዳሪው በውሉ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላ ተበዳሪው የብድሩን ገንዘብ እንዲመለስ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ፣<br>የብድሩ ገንዘብ መክፈያ ጊዜው በተወሰነ የብድር ውል ስምምነት ገንዘብ የተበደረ ወገን የመክፈያ ጊዜው ካለፈበት (ካበቃበት) ጊዜ ጀምሮ ወለድ ለመክፈል ስምምነት ያልተደረገ ቢሆንም፣ በድሩን ከነ ህጋዊ ወለዱ ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2482(2)(3),2483, 2489(1),1676, 2478 | 74950 | ወ/ሮ ዙብዳ ኑረ ኬርሰማ<br>እና<br>ወ/ሮ ሚሊዮን ዳግም ሙሴ (አራት ሰዎች) | ህዳር 5/2005 | 58 |
| 16 | • ከውል አመስራረትና መቋቋም ጋር በተገናኘ ዝምታ በመርህ ደረጃ ውልን እንደመቀበል ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑና አንድ ውል፣ ተሻሽሏል ለማለት የሚቻለው ማሻሻያው አስቀድሞ በተደረገው የአፃፃፍ ስርዓት አይነት የተከናወነ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>• የግልግል ጉባኤ አንድን ጉዳይ በማየት የዳኝነት መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው ተከራካሪ ወገኖች ከተስማሙበትና የሚፀና ወይም ዋጋ ያለው ግዴታ መኖሩን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1682,1683,1684,1722,200 1<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 356(ሀ) | 63063 | ኢትዮ ቴሌኮም<br>እና<br>ፒቲኢ ኢንተርናሽናል ኢንኮፖሬትድ | ህዳር 03/2005 | 62 |
| 17 | ከውርስ ሽያጭና ከስጦታ ውል የመነጨን የባለቤትነት መብት አስመልክቶ በሚነሣ የንብረት ክርክር የይርጋ ጉዳይ በተነሣ ጊዜ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ለጉዳዩቹ አግባብነትና ተፈፃሚነት ባለው የህግ ክፍል እና የህግ ይዘት ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ | 71537 | እነ ወ/ሮ የሻረግ ከበደ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን | ታህሳስ 02/2005 | 73 |
| 18 | የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አመዘጋገብ ጋር በተያየዘ በተፈፀመ ስህተት ንብረቱን በመያዣ የያዘው ወገን የሚደርስበትን ጉዳትና ኪሣራ ኃላፊነቱን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመወጣት ስህተቱን የፈፀመው የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ጉዳትና ኪሣራውን በመያዣ በተያዘው ንብረት ዋጋ መጠን ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1640(2), 3052, 3053(1),3081 | 75743 | የዳንግላ ማዘጋጃ ቤት ፍትህ ቢሮ፣ ዐ/ህግ<br>እና<br>እነ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 17/2005 | 78 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 19 | ከዋስትና ውል ጋር በተገናኘ ዋስ የሆነ ወገን በውሉ ላይ የተመለከተውን ፊርማ የእርሱ አለመሆኑን ወይም የውሉን ቃል በተመለከተ በመካድ በግልጽ ባልተከራከረበት ሁኔታ ውሉ በሁለት ምስክር ፊት የተደረገ አይደለም በሚል የሚቀርብ ክርክር የዋሱን ግዴታ ተፈፀሚነት የሚያስቀር ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1727(2) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.83,235 | 79907 | ልዩ የገንዘብ እገዛ ተቋም እና እነ ወ/ሮ የወይንሐረግ ትዕዛዙ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 02/2005 | 82 |
| 20 | ገቢ ለማስገኘት በተዘጋጀ ልዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን በተደረገ ጨረታ ተሣታፊ በመሆን የጨረታውን ገንዘብ በመክፈል መሬት ተረክቦ ለልማት ለማዋል በሚል ጨረታው ተወዳድሮ የጨረታው አሸናፊ የሆነ ወገን ጨረታውን ካዘጋጀው አካል ጋር የውል ስምምነት እንዳደረገ የሚቆጠር በመሆኑ በጨረታ ያሸነፈበትን የገንዘብ መጠን ለአዘጋጁ ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ፤ህ/ቁ.1771(1),1688(2),1757 | 76825 | ጭላሎ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የአዳማ ከተማ የባኩ ሸነን ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት | ጥር 14/2005 | 85 |
| 21 | በብድር የሚሰጥ ገንዘብ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ሊያቋቁሙት ስለሚችሉት የወለድ ምጣኔ (መጠን)፣ የውል ግዴታውን ያልፈፀመ ወይም ያዘገየ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ስለሚከፍለው የኪሣራ መጠን፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1803(2),1790(2),1800,2479(3),2488, 2489 | 81857 | አቶ አብዱልቃድር ጁሐር እና አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ጥር 13/2005 | 89 |
| 22 | ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች በመካከላቸው የሚነሣን አለመግባባት (ክርክር) በግልግል ዳኝነት እንዲያይ በሚል በውሉ የተሰየመ አካል በከሰመ ጊዜ ተዋዋዮች በጋራ ስምምነት ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት የሚያይ አዲስ አካል ለመሰየም ከሚችሉ በቀር አስቀድሞ የተሰየመው አካል በመክሰሙ ምክንያት ፍ/ቤት ጉዳዩን በግልግል ለማየት የሚችል አካል ለመሰየም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3336(1),3328(2),3337,3331,3325-3344,3329 | 80722 | የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፓርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት እና ዲ ኤም ሲ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር | ጥር 01/2005 | 93 |
| 23 | ከግንባታ ሥራ ውል ጋር በተገናኘ የሚከፈል ክፍያ የሥራው ባለቤት የሆነው አካል በግንባታው ሂደት የሥራ ትዕዛዞችን እየሰጠ የሥራውን አካሄድ የመወሰንና ሥራውን በሚፈቅደው አይነት እንዲፈፀም የሥራ ተቋራጩን የማዘዝ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ የሥራ ተቋራጩ ከሥራው ባለቤት ጋር | 71972 | አቶ ካሣሁን አያሌው እና የምስራቅ ጎጃም ጎዛምን ወረዳ ጤና ጽ/ቤት | ጥር 1/2005 | 97 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተደረገውን የግንባታ ሥራ ውል፣ በሥራው ባለቤት በተሰጡት ፕላኖች፣ ግንባታ ዲዛይን አይነቶችና የዋጋና የሥራ ማስታወቂያ መሠረት ግንባታውን የማካሄድ ግዴታ ያለበት በመሆኑ የሥራው ባለቤት በግንባታው ሥራ ውል ሰነዱ ላይ ከተመለከተው ክፍያ ውጪ በተጨማሪነት በባለቤቱ ፈቃድና ትዕዛዞች መሠረት ለተሠሩ ሥራዎች ክፍያ ለመክፈል አልገደድም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በህጉ አግባብ በባለቤቱ የተሰጡ ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዞች የሥራ ውሉ አካል ተደረገው የሚወሰዱ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.3244,3225,(1)(2),3152(1),3266(1),3263,3265(3) | | | | |
| 24 | በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት ከወጣው መመሪያ ቁ.3/2004 አፈፃፀምጋር በተገናኘ የንግድ ቤቱን በማከራየት ከሚያገኙት ገቢ ውጪ ሌላ ገቢ የሌለውና በእድሜ አዛውንት የሆነ ተከራይ የኪራይ ውል ሊቋረጥ የማይገባ ስለመሆኑ፣<br>መመሪያ ቁ.3/2004 አንቀጽ 6(1) | 83448 | እነ ወ/ሮ ሙሉወርቅ ኃ/ገብርኤል (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሪት ጽጌ መብራቴ | ጥር 30/2005 | 103 |
| 25 | • በአንድ ውል የተመለከተን እዳ ለማረጋገጥ ሲባል አዲስ ሰነድ በተዋዋይ ወገኖች የማደራጀት ተግባር የውል መተካት አድራጎት ነው ለማለት የሚቻለው በሁለተኛው ውል በግልጽ የተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>• በባህር ላይ የሚደረግ የማጓጓዣ ውልን አስመልክቶ አጓዡ ለውሉ ምክንያት የሆነው እቃ (ንብረት) ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው አቤቱታ ዕቃውን ከተረከበበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፣<br>የባህር ህግ ቁ.146,203<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1826,1828,1829(ሀ) | 80642 | የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>ባርጉባ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ታህሳስ 02/2005 | 109 |
| 26 | አንድ ውል የአስተዳዳር ውል ነው ለማለት በህግ ወይም በተዋዋይ ወገኖች ግልጽ በሆነ ቃል የአስተዳደር መ/ቤት ውል ነው የተባለ እንደሆነ ወይም ደግሞ ተዋዋዮቹ ውል ያደረጉበት ጉዳይ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር ተያያዥና ለሥራ ውሉ አፈፃፀም የአስተዳዳር አካልን (ፍ/ቤትን) ተካፋይነት ያለማቋረጥ የሚጠይቅ መሆኑን እንዲሁም በአጠቃላይ የውሉን አይነትና | 80464 | ወይራ እንጨትና ብረት ሥራ ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማህበር<br>እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ | ታህሳስ 16/2005 | 113 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ባህሪ፣ የውለታውን አይነተኛ ጉዳይ ብሎም የተዋዋዮችን ማንነት መመልከት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.3132<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ) | | | | |
| 27 | • የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው በሚል የተደነገገው ድንጋጌ የይርጋ የጊዜ ገደብን የሚደነግግ ሣይሆን የመያዣ ውሉ ቀሪ የሚሆንበት ወይም በህግ ውድቅ የሚደረግበት (Lapse of Mortgage Right) ስለመሆኑ፣<br>• የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘ ባንክ በመያዣው ላይ ያለው መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆነው የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አስር ዓመት ከማለፉ በፊት በመያዣ መብቱ መገልገል ያልጀመረ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 (1)(3) | 78444 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>አቶ ጥጋቡ ተፈራ | ጥቅምት 22/2005 | 116 |
| 28 | •በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል ባለመፈፀሙ ምክንያት የጉዳት ኪሣራ እንዲከፈል በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በውሉ ለዚሁ ዓላማ ተዋዋዮቹ ካመለከቱት የገንዘብ መጠን በላይ እንዲከፍል ለማስገደድ የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>•የመልካም ሥራ አፈፃፀም ቦንድ መሰረታዊ ዓላማ በውል የተመለከተው ጉዳይ እንደውሉ ስለመፈፀሙ (የሚፈፀም ስለመሆኑ) ለማረጋገጥ ስለመሆኑ፣<br>•አንድን ዕቃ ማቅረብ ጋር በተያያዘ የተደረገ ውልን አስመልክቶ በአቅራቢው በኩል ከእቃው ዋጋ ጋር በተገናኘ በመንግስት የታወቀ የዋጋ ግሽበት መከሰቱ አቅራቢው ውሉን ሙሉ ለሙሉ ለማቋረጥ የሚያስችለው በቂ ምክንያት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3183(2),3188(1),1731,1734,1732,1889 | 69797 | ወ/ሮ ሂላላ ሱሌማን<br>እና<br>ጎንደር ዩኒቨርስቲ | ታህሳስ 04/2005 | 121 |
| **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | | **129** |
| 29 | አንድ ለእዳ መክፈያነት በአፈፃፀም በጨረታ እንዲሸጥ በተደረገ ንብረት ጨረታ ላይ በመካፈል የጨረታው አሸናፊ ከሆነ በኋላ የጨረታ ሽያጩን ለመፈፀም ያልቻለ ወገን ንብረቱ በቀጣይ | 72017 | አቶ ጉታ ኤጀታ<br>እና<br>አቶ ሙደሲር ረዲ | ጥቅምት 20/2005 | 130 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በወጣ ጨረታ ቀርቦ ሲሸጥ የተገኘው የሽያጭ ዋጋ ዝቅተኛ የሆነ እንደሆነ የመጀመሪያው ጨረታ አሸናፊ ለተከሰተው የዋጋ ልዩነት ለፍርድ ባለዕዳው በካሣ መልክ እንዲከፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429 | | | | |
| 30 | በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ተቋማት (ወገኖች) በድሀ ደንብ ዳኝነት ሳይከፍል በፍ/ቤት ለመስተናገድ የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቋሙ ከሚገኝበት የገንዘብ አቋም አኳያ ተገናዝቦ መታየት ያለበት ስለመሆኑና ተቋሙ የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም (Financial status) ለመለየት ተቀባይነት ስለሚኖረው የማስረጃ አይነት፣ ለዳኝነት የሚከፈለውን ገንዘብ ለመክፈል አልችልም በሚል በድሀ ደንብ ለመስተናገድ የህግ ሰውነት የተሰጠው ተቋም የሚያቀርበው አቤቱታ ሊስተናገድ ስለሚችልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 467 | 79555 | ቤተልሄም ፋርማሲ ቲዩካል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ታህሳስ 02/2005 | 133 |
| 31 | • በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43 መሠረት ወደ ክርክር እንዲገባ የተደረገ 3ኛ ወገን በክርክሩ ሂደት ሊያነሣ ስለሚችለው የክርክር አይነትና አድማስ፣ 3ኛው ወገን ሊያነሣ የሚችላቸው የክርክር ፈርጆች በአንድ በኩል ከተከሣሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሣሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሣሽ እግር ተተክቶ ተከሣሽ ለከሣሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፣ ኃላፊነት አለበት የሚባል ቢሆን እንኳን ሊከፈል የሚገባው የካሣ ክፍያ መጠን ላይ ከከሣሽ ጋር ንጽጽር በማድረግ መሟገት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሣሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር ስለመሆናቸው፤ 3ኛ ወገን ጣልቃ ገብ በክርክር ሂደቱ መሟገት የሚችለው ከተከሣሽ ጋር ብቻ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 አስፈላጊነት ተከታታይ ክስ ሳይኖር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በአንድነት እንዲታዩ በማድረግ የኃላፊነት መጠኑን እንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት ለመስጠት ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 መሠረት ጣልቃ | 79465 | ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ እና እነ አቶ አገኘው ገረመው (ሁለት ሰዎች) | ጥር 14/2005 | 136 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚገባ ወገን ከመነሻውም ከተከሳሹ ጋር የህግ ወይም የውል ግንኙነት የለኝም በማለት ክርክር ያቀረበ እንደሆነ በመካሄድ ላይ ባለው ክርክር ተሣታፊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር ስለመሆኑና ይህን መሰል ክርክር ራሱን በቻለ ሌላ መዝገብ ታይቶ ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43(1),76<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1896,1897,1908,1909<br>የንግድ ህግ ቁ.687,688,683 | | | | |
| 32 | • የወጪና ኪሣራ ክፍያ ጉዳይ ሊስተናገድ ሊወሰን የሚገባው በዋናው ጉዳይ ፍርድ (ውሣኔ) በተሰጠበት መዝገብ ስለመሆኑ፣<br>• ወጪና ኪሣራ ክፍያን በተመለከተ ማን መክፈል እንዳለበት በዋናው ጉዳይ ላይ ተለይቶ ከተወሰነ በኂላ ምን ያህል መክፈል እንዳለበት በተመለከተ ደግሞ ዋናው ፍርድ ባረፈበት መዝገብ የወጪና ኪሣራ ዝርዝር ቀርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ስለቀረበው የወጪና ኪሣራ አስፈላጊነት ስለመጠኑ እና በእርግጥም ወጪና ኪሣራ ስለመውጣቱ በተመለከተ የበኩሉን ክርክር ካቀረበ በኂላ የወጪና ኪሣራ ልኩ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 183, 378, 462-464 | 83701 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ ህንደያ እንድሪስ ወኪል አብዲ ዓሊ | ጥር 27/2005 | 140 |
| 33 | አንድን ክርክር ለማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ህጋዊነት አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክር ሊቀርብና ታይቶ ሊወሰን የሚገባው በዚያው ዋናው ጉዳይ በቀረበበት ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣ | 74890 | ወ/ሮ ሚስጢር ሰለሞን<br>እና<br>እነ አቶ ፍቃዱ ካሣሁን (አምስት ሰዎች) | ጥር 30/2005 | 142 |
| 34 | • አንድ መዝገብ ላይ የተከሰሱ ሰዎች የኃላፊነት ምንጩ ከተለያየ የህግ ማዕቀፍ (ክፍል) በሆነ ጊዜ አንደኛው ወገን የተነሣው የይርጋ ክርክር በሌላኛው ወገን እንደተነሣ የማይቆጠር ስለመሆኑ፣<br>• በአንድ ክስ (መዝገብ) ተጣምረው በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊነት አለባችሁ ተብለው ከተከሰሱ ወገኖች መካከል አንደኛው ወገን የሚያነሣው የይርጋ መቃወሚያ ያለቅድመ ሁኔታ በሌላኛው ተጣምሮ የተከሰሰው ወገን ላይ ተፈፃሚነት አለው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• በፍ/ብሔር ጉዳይ የአንድነትና የነጣላ ኃላፊነት ከተለያዩ የህግ ክፍሎች እና ከተለያዩ ምክንያቶች ሊመነጭ የሚችል ስለመሆኑ፣ | 80723 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር<br>እና<br>እነ ዋቅቶሉ አብደሳ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 29/2005 | 145 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ህ/ቁ.1852<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.244(3),36 | | | | |
| 35 | • ለተሰጠ የብድር ገንዘብ አመላለስ በመያዣ የተያዘ በኪሣራ የፈረሰ ማህበር (ድርጅት) ንብረት በሀራጁ ጨረታ የተሸጠ በመሆኑ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ እና ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>• በመያዣ የተያዘውን ንብረት በባንኩ በሀራጅ የተሸጠ በመሆኑ በባለዕዳው በኩል ቢሸጥ የተሻለ ዋጋ ያስገኝ ስለነበረ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>በህግ የተቋቋመ ባንክ በብድር የሰጠው ገንዘብ በአዋጅ ቁ.97/90 እና 216/92 መሠረት አስቀድሞ ለብድሩ አመላለስ ዋስትና ይሆን ዘንድ ከያዛቸው መያዣዎች መካከል አንዱን በመምረጥ በሐራጅ ሊሸጥ ይገባል፣ ለመሸጥ የተንቀሳቀሰበትን የመያዣ ንብረት ከመሸጥ ድርጊት ይታቀብ ይህም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሰጥልን በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ህግን ባለመከተል የፈፀመው ስህተት ቢኖርና በባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ግን ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለዕዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ እና ፍ/ቤቶችም ሀራጁን ለማስቆም ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>• የሰበር ችሎት የሚሰጠው አስገዳጅነት ያለው የህግ ትርጉም አንድ ክርክር የቀረበበት ጉዳይ (ድርጊት) ከተፈፀመ በኋላ ስለሆነ የተሰጠው የህግ ትርጉም በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394-449,224<br>አዋጅ ቁ.97/90 አንቀጽ 3,4<br>አዋጅ ቁ.216/92<br>አዋጅ ቁ.98/90<br>አዋጅ ቁ.2584 | 84353 | ጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር ሒሣብ አጣሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች<br>እና<br>ወጋገን ባንክ አ/ማህበር | ጥር 02/2005 | 149 |
| 36 | • አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ብይን መስጠቱ ፍርዱ ለከሣሽ በሚጠቅም መልኩ (መንገድ) የመወሰኑን ሁኔታ በአስገዳጅነት የሚያስከትል ነው ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣ | 82427 | ዩኒስ ቡራሌ ሲጋል የራይስ ጫት ላኪዎች ማህበር<br>እና<br>አቶ አብዲ አልሚ | ጥር 27/2005 | 155 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • የማህበር ሊቀመንበርን ከስልጣን ለማንሳት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 70(ሀ) | | መሐመድ | | |
| **የንግድ ሕግ** | | | | | **159** |
| 37 | የእሽሙር ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሌለው እንዲሁም በጽሁፍ መረጋገጥና ሌሎች የንግድ ማህበሮችን በተመለከተ የተደነገጉት የማስታወቅና የማስመዝገብ ሥርዓቶች የማይፈፀምበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ የእሽሙር ማህበርን አስመልክቶ ማህበሩ እንዲፈረስ በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዬችን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የእሽሙር ማህበር የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርገው በሸሪኮቹ ስም ስለመሆኑና ሸሪኮቹም እንደተራ ተዋዋይ ወገኖች የሚታዩ ስለመሆናቸው<br>የንግድ ህግ ቁ. 212(1),272 | 76394 | አቶ ወርቁ ወ/ዓዲቅ<br>እና<br>እነ የአቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ወራሾች (ሰባት ሰዎች) | ህዳር 18/2005 | 160 |
| 38 | አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) የሚጨበጥና የማይጨበጥ እንዲሁም የሚንቀሣቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት መብቶች ምን ምን እንደሆኑ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ስለመሆኑ<br>አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ሥራውን የሚያከናውንበት የንግድ ቦታ ኪራይ መብት የማህበሩ ህልውና ጋር የሚያያዝ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>•የንግድ ድርጅቱ የፈረሰ ቢሆንም የንግድ ሥራውን ሲያከናውንበት የነበረውን ቦታ በሌላ ጉዳይ በፍርድ እንዲለቅ በተወሰነ ጊዜ የማህበሩ ሒሳብ ተጣርቶ አለመጠናቀቅ ቦታውን ላለማስለቀቅ ምክንያት ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣ | 80599 | ጀሸዋ ኢነድ ካሌቤ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ወ/ሮ እንቁጣጣሽ አሰፋ | ጥር 15/2005 | 164 |
| **ቤተሠብ** | | | | **168** | |
| 39 | በአንድ ቦታ ከተደረገ በኋላ በሌላ ጊዜ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ እንዲረጋገጥና ማህተም እንዲደረግበት የተደረገ የኑዛዜ ሰነድ በህጉ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት እንደተደረገ ኑዛዜ የማይቆጠር ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.881,882 | 74734 | ወ/ሮ ትዕግስት ሽባባው<br>እና<br>እነ እህት አለማው ወርቁ (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 20/20085 | 169 |
| 40 | • የኮንዶሚኒየም ቤትን በጋብቻ ወቅት እያሉ የደረሳቸው ባልና ሚስት የቤቱ ቅድመ ክፍያ በጋብቻ ወቅት ከተፈራ | 74451 | አቶ ደረጀ ማዘንጊያ<br>እና<br>ወ/ሮ ፍሬህይወት | ጥቅምት 20/2005 | 173 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የጋራ ሀብት የተከፈለ እንደሆነና ቤቱን ለማሳመርና ለሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ከጋራ ሀብቱ ወጪ በማድረግ ጥቅም ላይ በዋለበት ሁኔታ ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ እንደሆነ ቤቱ ለተጋቢዎቹ፣ ሊከፋፈል ስለሚችልበት አግባብ፣<br>• በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ቤተሰብ የመመስረት መብት በመጠቀም ጋብቻ የፈፀሙ ወንዶች እና ሴቶች በጋብቻው አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመን እንዲሁም በፍቺ ጊዜ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ፣<br>የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 35(1) | | ጴጥሮስ | | |
| 41 | • የኑዛዜን ፎርማሊቲና የይዘቱን ህጋዊነት አስመልክቶ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ተቃውሞውን አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ወገን በሌላ ጊዜ በድጋሚ የኑዛዜው ይዘት ጋር በተገናኘ ተናዛዡ ከውርስ ነቅሎናል፣ እንዲሁም ሊደርሰን ከሚገባው ድርሻ ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ደርሶብናል በሚል ኑዛዜው እንዲሻር የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• ኑዛዜ የህጉን ፎርማሊቲ የጠበቀ ነው በሚል በፍ/ቤት መጽደቅ ኑዛዜው መብታችንን ይነካል በማለት ክርክር የሚያቀርቡ ወገኖች ክርክራቸውን ለዳኝነት አካል ከማቅረብ የማይከለክል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.51, 216, 217<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123 | 77169 | እነ አቶ ተሾመ ገበየሁ<br>እና<br>ወ/ሮ ሊሻንወርቅ ገበየሁ | ጥር 17/2005 | 176 |
| 42 | የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ቀደም ሲል ጋብቻ የነበረው እንደሆነ የጠፋው ሰው መመለስ በመጥፋት ውሣኔው የፈረሰውን ጋብቻ እንደገና ተመልሶ ህይወት እንዲዘራ (እንዲፀና) የማድረግ ውጤት አለው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>በፍ/ቤት የተሰጠ የመጥፋት ውሣኔ መሻር በመጥፋት ውሣኔው መሠረት የፈረሰን ጋብቻ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮ (ግለሰቡ ከተመለሰበት ቀን ጀምሮ) መልሶ እንዲቋቋም (እንዲፀና) ለማድረግ የሚያስችል ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.170,171 | 74791 | ወ/ሮ ውቢት ሕሩይ<br>እና<br>የሀዋሣ ከተማ ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት | ጥር 17/2005 | 180 |
| 43 | አንድ ወራሽ የወራሽነት መብት በሌለው ንብረት ላይ ከህግ ውጪ የወራሽነት ሠርተፍኬት መያዙ በተረጋገጠ ጊዜ ይኸው ማስረጃ እንዲሰረዝ አቤቱታ ሊቀርብ ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.998(1) | 73247 | አቶ ልዑል ኪዳነማርያም<br>እና<br>እነ ሰብለ ኪዳነማርያም | ጥር 14/2005 | 184 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | (ሶስት ሰዎች) | | |
| ጉምሩክ/ግብር/ ታክስ | | | | 187 | |
| 44 | • በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቅቆ ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ወይም ወደ ውጪ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>• "የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠናቀቀ" ማለት ስለሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 66(1), 2(17),66(29),66(2) | 71070 | ተሸአብ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | መስከረም 21/2005 | 188 |
| 45 | የተሸከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው በተሸከርካሪው የተፈፀመ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ህግን የመጣስ ወንጀል ከራሱ እውቀት ወይም ፈቃድ ወጪ መሆኑን ማስረዳት የቻለ እንደሆነ የተፈፀመው ወንጀል ክብደት እየታየ የገንዘብ መቀጮ ከፍሎ ተሽከርካሪው ሊለቀቅለት (ላይወረስ) የሚችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 109(1)<br>የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መመሪያ ቁ.50/2003 አንቀጽ 6(2) | 76976 | የጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሊሻን ከተማ ገብሬ | መስከረም 22/2005 | 191 |
| 46 | •የውጭ ምንዛሬ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር ያለህጋዊ እውቅናና ፈቃድ ማስወጣት የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣<br>•የወንጀል ድርጊትን የፈፀምኩት ባለማወቅ ነው በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለውና ህግን አለማወቅ ይቅርታ የማያሰጥ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 99<br>አዋጅ ቁ. 591/2000 አንቀጽ 20(3)<br>የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 2(2),25,23(2),81(1)(3) | 80296 | አቶ ሳምሶን መንግስቱ<br>እና<br>የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ጥር 30/2005 | 194 |
| ንብረት | | | 199 | | |
| 47 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ህጋዊነትና ተቀባይነት ጋር በተናኘ የምስክር ወረቀቱ ሊሰጥ የቻለው የንብረት ባለሀብትነት መብትን ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው እንዴት መተላለፍ እንዳለበት በህጉ የተመለከተውን ደንብና ሥርዓት ሳይከተል ስለሆነ የንብረቱ ባለሀብት ስለመሆንን የህግ ግምት መውሰጃ የሆነው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ቀሪ ነው፣ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ሊረጋገጥ የሚችል | 75414 | ወ/ሮ ዋሪቴ ቡቡሳ<br>እና<br>እነ የጎልጀታ ከተማ አስተዳደር (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 22/2005 | 200 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የዳኝነት ጥያቄ እንጂ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1195,1196 | | | | |
| 48 | በአንድ ወቅት የነበረን የተገነባ የመንገድ ደረጃ መነሻ (መሠረት) በማድረግ በመንገዱ ግራ ቀኝ አዋሣኝ በሆነ ይዞታ ላይ ተገቢውን ርቀት በመጠበቅ ንብረትን ያፈራ ሰው በሌላ ጊዜ የመንገዱ ደረጃ ከፍ እንዲል በመደረጉ የተነሣ በአዋሣኝ ይዞታው ላይ ግለሰቡ ያፈራቸው ንብረቶች ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ፣ ጉዳት ያደረሰው ወገን ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት (የሚኖርበት) ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 65/1936 አንቀጽ 2(ሀ)<br>አዋጅ ቁ. 66/1936 አንቀጽ 1(ለ)<br>አዋጅ ቁ. 455/1997,የኤ.ፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(8) | 75343 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ በላይ ሀሰን | ህዳር 17/2005 | 204 |
| 49 | አንድ ሰው የሌላ ሰው ንብረት ይዞ ሲጠቀም ከቆየና ንብረቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ንብረቱን ከጥፋት ወይም ከብልሽት ለማዳን ሲል ተገቢውን ወጪ ያወጣ እንደሆነ ይኸው ወጪ በህጋዊ ባለሀብቱ እንዲተካለት ለመጠየቅ የሚችለው ወጪው የግድ አስፈላጊ ከሆነና በቅን ልቦና የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>ወጪው በክፉ ልቦና የተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ግን እቃውን (ንብረቱን) እንዲመልስ የተደረገው ሰው እንዲተካለት የጠየቀውን ወጪ መጠን ዳኞች ሊቀንሱት ወይም ጭራሹንም ሊያስቀሩት የሚችሉ ስለመሆኑ፣<br>በንብረቱ (እቃው) ላይ የተደረገው ወጪ «በክፉ ልቦና የተደረገ ነው» የሚባለው ወጪው በተደረገበት ጊዜ (ወቅት) ወጪው እንዲተካለት የሚጠይቀው ሰው ንብረቱን (እቃውን) ለባለቤቱ ለመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያወቀ እንደነበር ወይም ማወቅ ይገባው የነበረና ርትዕም ሲያስገድድ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ<br>2172(1),2171(1),2168,2169 | 81081 | ወ/ሮ ፍሬህይወት መብራህቱ ገ/መድህን<br>እና<br>እነ አቶ መብራህቱ ገ/መድህን /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 13/2005 | 207 |
| 50 | • የመኪና ሽያጭ ውል መደረጉን (መኖሩን) ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት፣<br>• የመኪና /ተሽከርካሪ/ ባለሀብትነት (ስመ ሀብት) እንዲተላለፍለት የሚጠይቅ ሰው ሊያቀርባቸው ስለሚገቡና | 81406 | እነ አቶ አህመድ ኢብራሀም (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አመሀ ተ/ወይኒ | ጥር 13/2005 | 211 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተቀባይነት ስላላቸው ማስረጃዎች<br>አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ፣<br>• አከራካሪ ሆኖ የቀረበን አንድ ፍሬ ነገር ማስረዳት ስለሚቻልበት የማስረጃ አይነት አግባብነት ባለው ህግ በተለይ የተቀመጠ ግለጽ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ አቅርቦ ጉዳዩን ለማስረዳት ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1186(1),(2),2001(1)<br>ስለ ተሽከርካሪ መለያ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁ.681/2002 አንቀጽ 6(3)(4) | | | | |
| 51 | የመሬት ባለ ይዞታ የሆነ አርሶ አደር ይዞታውን ላለበት እዳ ለ3ኛ ወገን በመያዣነት ለመስጠት ወይም በስጦታ የቤተሰብ አባል ላልሆነ ሰው ለማስተላለፍ መብት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ እና/ወይም የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ ከመነሻው ውጤት የሌለውና ፈራሽ ስለመሆኑ፣<br>• የውሉ መሠረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 130/99<br>አዋጅ ቁ.89/89 አንቀጽ 2(3)<br>አዋጅ ቁ. 456./97 አንቀጽ 8(2),1) | 79394 | አቶ አብደላ ኢብራሒም<br>እና<br>አቶ ኡሶ አብዲ | ጥቅምት 06/2005 | 215 |
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | **218** |
| 52 | • የፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳዳር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት የቴሌኮሚኒኬሽን ወይም የኤሌክትሪክ ሀይል አውታር ስለመኖሩ እንዲሁም ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታን ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሚኒኬሽንና በኤሌክትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑና በዚህም የተነሳ በቸልተኝነት ግንባታ በማከናወን ጉዳት ያደረሰ ወገን በኃላፊነት የሚጠየቅ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.464/97 አንቀጽ 3(3)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. | 77238 | ኢትዮ ቴሌኮም<br>እና<br>አቶ ንጉሴ ተፈራ | ህዳር 03/2005 | 219 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2027(1),2035(1),2028(1),2091<br>አዋጅ ቁ.49/89 አንቀጽ 23(1) | | | | |
| **የዳኝነት ሥልጣን** | | | 223 | | |
| 53 | • አንድ ሰው በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰን የሚችለው ከህግ የመነጨ መብት ያለው መሆኑን በክሱ ውስጥ በዝርዝር በፍሬ ነገር ደረጃ ማመልከት የቻለ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>• ሀይማኖታዊ (መንፈሣዊ) ትምህርት ለመስጠትና ለማሰልጠን በሚል ከሚቋቋሙ ተቋማት ጋር በተገናኘ በተማሪነት ማን እንደሚመለመል፣ ምን ምን መስፈርቶች ሊሟሉ እንደሚገባ፣ የመስፈርቶቹ መሟላትና አለመሟላት እንዲሁም በተቋሙ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ከትምህርት አቀባበል ሂደት ወቀት ሊገልጿቸው ስለሚገቡ የዲሲፕሊን ጉዳዬች ወዘተ በሀይማኖት ተቋማቱ የሚወሰን ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮችን መደበኛ ፍ/ቤቶች አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>• የግለሰብ ፍትህ የማግኘት መብት በፍ/ቤቶች ተግባራዊ ሊደረግ የሚችለው በፍርድ ሊያልቁ የሚባቸው ጉዳዬችን በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 | 77479 | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቅድስት ሥላሴ መንፈሣዊ ኮሌጅ<br>እና<br>አቶ አሰግድ ሣህሉ | ጥቅምት 06/2005 | 224 |
| 54 | የፌዴሬሽን ምክር ቤት የኢፌዴሪ ህገ መንግስትን ለመተርጐም ባለው ስልጣን ተጠቅሞ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና ጉዳዩ በሚመለከተታቸው አካላት መከበርና መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ የሚቀርብለትን አቤቱታ ህጋዊነት መርምሮ በመወሰን ሂደት ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል (quasi judicial body) እንደመሆኑ መጠን በህገ መንግስቱ የተጠበቁትን ፍትህ የማግኘት፣ የመሰማትና በእኩል ሚዛን የመታየት (የመዳኘት) መብት በሚያስከበር መልኩ ክርክሮችን ሊያስተናግድና ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 62(1),37<br>አዋጅ ቁ. 251/93 አንቀጽ 3(1),56(1)<br>አዋጅ ቁ. 87/86 አንቀጽ 8,9 | 43511 | እነ የአቶ ዋሲሁን መኮንን ሚስትና ወራሾች /8 ሰዎች/<br>እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥቅምት 23/2005 | 228 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337, 336, 339 | | | | |
| 55 | የአቃቤ ህግ ሙያን በሹመት የሚያከናውኑ ሰዎች ጋር በተገናኘ ቅጥር፣ ዝውውርና የደረጃ እድገትን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው አካል የአቃቤያነ ህግ አስተዳደር ጉባኤ ስለመሆኑና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>ደንብ ቁ.24/99 አንቀጽ 46(3), 41, 44, 2 (4)<br>አዋጅ 568/2000 አንቀጽ 2(7),3,10(1),4,5<br>የአ/አ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ.6/2000 አንቀጽ 2(5)(ሐ) | 75034 | አዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>አቶ መኮንን ተክሉ | ህዳር 03/2005 | 234 |
| 56 | • የፍ/ቤቶች የግዛት ስልጣን በዋነኛነት መሠረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበት ቦታ ለተከራካሪ ወገኖች የሚኖረውን አመቺነት ሲሆን የሥረ ነገር ስልጣን መሠረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ይዘት፣ የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ጥቅም ክብደትና መጠን እንዲሁም የጉዳዩን የውስብስብነት ደረጃ ስለመሆኑ፣<br>• ፍርድን የማስፈፀም ጉዳይ በስረ ነገር ክርክር ተረጋግጠው የፍርድ ሀይል ያገኙትን የተከራካሪ ወገኖች መብቶችና ግዴታዎች በሥነ ሥርዓት ህጉ የተደነገገውን የአፈፃፀም ስርዓት ተከትለው እንዲፈፀሙ ከማድረግ ውጪ አዲስ መብትና ግዴታ የሚቋቋምበት ሂደት ስላለመሆኑና የማስፈፀም ስልጣን በመርህ ደረጃ የፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣንን የሚከተል ስለመሆኑ፣<br>• አስፈላጊ እና ተገቢ በሆኑ ሁኔታዎች ሥረ ነገሩን የወሰነ ፍ/ቤት በአፈፃፀም ጉዳዮችን በውክልና የሥረ ነገር ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ሊያስተላልፍ ስለመቻሉ፡<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371, 372, 9, 10 | 75788 | እነ አቶ በረከት ኃ/ኪሮስ (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ጎይቶም ኃ/ኪሮስ | ህዳር 05/2005 | 238 |
| 57 | የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ (የኮንትራት) ሠራተኞች ቅጥር ጋር በተገናኘ በሠራተኛ እና በቀጣሪው መካከል የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ የመደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ ክስም ሆነ በይግባኝ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 22(3) ,2(1) | 81963 | አቶ አስፋው ጉደታ<br>እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ታህሳስ 03/2005 | 242 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ | | | | |
| 58 | በአዋጅ ቁ. 515/1999 መሠረት የተቋቋመና የሚተዳደር የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተ ተቋሙ በራሱ ገቢ የሚተዳደር በመሆኑ ምክንያት አዋጅ ቁ. 377/96 ን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ለማየት ስልጣን አላቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96<br>አዋጁ ቁ. 515/99<br>አዋጅ ቁ. 553/99 አንቀጽ 6(1), 14(2)(ለ)<br>አዋጅ ቁ. 545/99 | 80005 | የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ቦጋለ ዱንፋ | ጥቅምት 09/2005 | 245 |
| 59 | የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ መብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ክርክርን ለማየት ስልጣን ያለው አካል የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ስለመሆኑ፣<br>• የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የቀረበላቸውን ጉዳይ በህጉ አግባብ ያስተናገዱና ውሣኔ የሰጡ መሆኑን የማረጋገጥና የመቆጣጣር ኃላፊነትና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.9,231<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10(22)<br>አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2(1)<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ)<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 142, 147<br>አዋጅ ቁ. 345/95<br>አዋጅ ቁ. 209/55<br>አዋጅ ቁ. 715/2003<br>ደንብ ቁጥር 202/2003 | 83425 | አብጀታ ሻላ ሶዳ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አብጃታ ሶዳ አሽ መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር | ጥር 02/2005 | 248 |
| **ወንጀል** | | | | 254 | |
| 60 | በወንጀል ጉዳይ የወንጀል ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር ጋር በተገናኘ ፖሊስ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ላይ የሚያደርገው ምርመራ የይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጠው ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ.221 106(1), 420(2), 271 (1)(ሠ) 219 (2) | 77097 | እነ አቶ ሀይላይ ተክሉ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የመቀሌ ከተማ ሰሜን ምድብ ዐ/ህግ | ጥቅምት 20/2005 | 255 |
| 61 | አንድ ተከሳሽ የተከሰሰበትን የወንጀል ክስ ይዘት በሚገባ ተረድቶና አድራጐቱን | 77842 | አቶ ሳሚ ሁሴን<br>እና | ታህሳስ 03/2005 | 258 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በተመለከተም እንደቀረበበት የወንጀል ክስ በዝርዝር መፈፀሙን ገልፆ በማመን የእምነት ቃሉን ሰጥቷል በሚል መነሻ በተከሣሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ በአግባቡ ተሰጥቷል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>ፍ/ቤቶች ተከሣሹ የቀረበበትን ክስ በተመለከተ በድርጊቱ አፈፃፀም ረገድ የገለፀውን ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታ በመዝገብ ላይ ባለማስፈር በደፈናው ክሱን አምኗል በማለት የሚሰጡት የጥፋተኛነት ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ፣<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ.134(1)<br>የወ/ህ/አ.23 | | የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | | |
| 62 | • ተከሳሽ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርባቸው ስለሚችላቸው መከራከሪያዎች<br>• ተከሳሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት የሚያቀርባቸው መቃወሚያዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130 ላይ የተመለከተቱት ጉዳዬች ጋር ብቻ በተገናኘ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ የማይችልና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተፈፃሚ በነበረው ህግ ከተመለከተው የቅጣት ጣሪያ በላይ ሊቀጣ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• የወንጀል ህግ ወደ ኃላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑና ዳኞች ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ክስ የቀረበበት ድርጊት ወንጀል ስለመሆኑ የሚደነግገው ህግ ፀንቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን ከተረዱ በማናቸውም ጊዜ አንስተው ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉ ስለመሆኑ፣<br>• ፍ/ቤቶች በዐ/ህግ የቀረበ የወንጀል ክስ በህገ-መንግስቱና በወንጀል ህጉ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር የተቀመጡ መርሆዎችና ድንጋጌዎችን የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ፣<br>የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 5(2) ,13(1), 22(1 )<br>የወ/ህ/አ. (414/96)3,402,419,5(2)<br>የወ/ህ/ቁ.(214/74) | 73514 | ተስፋዬ ጡምሮ እና የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ | ህዳር 06/2005 | 261 |



www.chilot.me

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት (ICCPR) አንቀጽ 15(1)<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130(2)(1) | | | | |
| 63 | አንድ የንግድ ድርጅት (ማህበር) የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግንና ማሻሻያውን ተላልፏል በሚል በወንጀል ጥፋተኛ ሊሰኝና ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የህግ ሰውነት የተሰጠው (legal personality) ድርጅት የወንጀል ተካፋይ ሊሆን የሚችልበት አግባብ፣<br>• የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው ኃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም ህጋዊ ግዴታን በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ስለመሆኑና የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተከስሶ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ እስከተሰጠበት ድርስ ድርጅቱ የወንጀሉ ተካፋይ እንደሆነ የሚቆጠር ስለሆነ ጥፋተኛ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ. 34(1),(2)<br>አዋጅ ቁ. 285/95 አንቀጽ 56(1) | 74237 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>አብካለ እንደሻው ጠቅላላ የንግድ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር | ጥቅምት 19/2005 | 266 |
| 64 | • ፍ/ቤቶች በወንጀል ረገድ የሚሰጧቸው ማናቸውም ውሣኔ በወ/ህ/አ. 2 የተደነገገውን የህጋዊነት መርህ መሠረት በማድረግ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>• ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በሚል ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉት በወንጀል ህግ በግልጽ የተደነገገ ድንጋጌ የተመለከተ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>• በወንጀል ጉዳይ አንድ ንብረት (ሀብት) እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሊወሠን የሚችለው ንብረቱ (ሀብቱ) አንድን ሰው ለወንጀል ሥራ እንዲያነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳው ወይም ደግሞ ወንጀሉን ለፈፀመበት ዋጋ እንዲሆነው የተሰጠው ወይም ሊሠጠው የታቀደን ማንኛውም ጥቅም የተመለከተ ንብረት (ሀብት) ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ ወይም ንብረቱ (ሀብቱ) የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም ያገለገለ | 75387 | እነ አቶ ወርቁ ፍቃዱ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የቤ/ጉ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ህግ | ጥር 17/2005 | 271 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወይም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች ጋር የተያያዘ ወይም የተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ. 98,100,140, 2(1) (2) | | | | |
| 65 | • በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በቅጣት አወሣሠን መመሪያው የተሸፈነ እንደሆነ ቅጣቱ በመመሪያው አግባብ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• በወ/ህ/አ 539(1)(ሀ) ድንጋጌ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ሊቀነስለት የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ. 539(1)(ሀ)<br>የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ቁ.1/2002 አንቀጽ 16(7) | 82572 | መሪጌታ ፍቅረማርያም ካሴ<br>እና<br>የቤንች ማጂ ዞን | | 274 |
| **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | **278** | | |
| 66 | መድን ሰጪ የሆነ አካል በመድን ውሉ ለተመለከተው አደጋ ብቻ ለመድን ገቢው የመድን ሽፋን ለመስጠት የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ ቁ. 663(1),665(1) | 76977 | ኒያላ ኢንሹራንስ (አ.ማ)<br>እና<br>እነ አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 07/2005 | 279 |
| **አፈፃፀም** | | | **283** | | |
| 67 | • በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰው ሰው ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ንብረቱ በቅጣት ለመንግስት እንዲወረስ በተወሰነ ጊዜ በአፈፃፀም ደረጃ ከአጥፊው (ወንጀለኛው) ንብረት ውስጥ ለቤተሰቡ ህይወትና መተዳደሪያ ሊውል የሚገባውን ድርሻ ለመወሰን ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>• በውርስ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ከተወሰነው የአጥፊው (የወንጀለኛው) ሀብትና ንብረት ውስጥ ለቤተሰቡ ህይወት መተዳደሪያ ሊውል የሚገባው ድርሻ ሊሸፍናቸው የሚገባው የወጪ አይነቶችና መጠናቸው፣<br>• የአጥፊው (ወንጀለኛው) ጋር ጋብቻ የመሠረተ ሰው እንዲወረስ ከተወሰነው ንብረት ግማሽ ድርሻ የነበረው መሆኑን መሠረት በማድረግ በአፈፃፀም የሚያነሣው የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ጥያቄው እንደ መብት አቤቱታ | 79860 | ወ/ሮ ራኬብ መለሰ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | ህዳር 06/2005 | 284 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 98(ለ)(መ), 98(3)(ለ) | | | | |
| 68 | ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ በአንድ በቀረበ የዋና ጉዳይ ክርክር ሒደት የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ንብረት በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ በአፈፃፀም ደረጃ በተጠቃሹ ንብረት ላይ አፈፃፀም እንዲቀጥል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>ቀደም ሲል በዋና ጉዳይ ክርክር በፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲታገድ የተደረገ መሆኑ የታወቀ ንብረት ላይ በድጋሚ በተመሳሳይ ንብረት ላይ መብትን ለማስከበር በሚል በሌላ ጊዜ በአፈፃፀም ደረጃ የሚቀርብ ጥያቄ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 81616 | ወጋገን ባንክ አ.ማ.<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሠላማዊት ጥላሁን /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 15/2005 | 288 |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | **291** | |
| 69 | ባለ ሶስት አውታር (three dimention) ቅርጽ ሥራ ከባለቤቱ ፈቃድና ፍላጐት ውጪ በወረቀት ላይ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ማድረግ የቅጂ መብት ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 34(4) | 78856 | የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወዳጆችና ቤተሰቦች ማህበር<br>እና<br>አቶ ኤሊያስ አሰጋሽኝ | ታህሳስ 15/2005 | 292 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | **297** | |
| 70 | • ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተገናኘ በወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ የተጣለበትን ቅጣት ፈጽሞ ያጠናቀቀ ሰው በፍርድ ቤት መሰየም በግለሠቡ የጡረታ መብት ላይ ስለሚኖረው ውጤት<br>• በመሰየም ሊገኝ የሚችለው መብት ግለሰቡ ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን መብት ሳይሆን ግለሰቡ ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ፊት ሊጠበቅለት የሚገባውን መብት በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>• የመንግስት ሰራተኛ የነበረና የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሠው በወንጀል ጉዳይ ተከስሶና ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ በፍ/ቤት ቢያንስ የ3 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት በመሆኑ የጡረታ መብቱን እንዲያጣ የተደረገ ሠው ከቅጣቱ በኂላ በፍ/ቤት መሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን የጡረታ መብቱን መልሶ ለማግኘት የማያስችል ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ. 231,235(1),232<br>አዋጅ ቁ. 209/55 | 61221 | አቶ አከለ ምህረቱ<br>እና<br>የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | መስከረም 22/2005 | 298 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 5/67<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 52/1/ | | | | |
| 71 | • ከጡረታ መብት ጋር በተገናኘ በሠራተኞች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለማየት ስልጣን ያለው አካል የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ስለመሆኑና በኤጀንሲው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ሠራተኛ ቅሬታውን ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>• የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ በፍሬ ነገር ረገድ የመጨረሻ ስለመሆኑና በውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ቅሬታ ያለው ሠራተኛ አቤቱታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቀ. 714/2003 አንቀጽ 56(1) (4), 57 | 72928 | አቶ አበራ ኪዳኔ<br>እና<br>የጋሞ ጎፋ ዞን አርባ ምንጭ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት | ጥቅምት 09/2005 | 303 |
| 72 | • ከጡረታ መብት አበል ተጠቃሚነት ጋር በተገናኘ የእድሜ አቆጣጠርና ውጤቱን በተመለከተ የሚቀርብ አቤቱታን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያለው የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ስለመሆኑና በውሣኔው ቅሬታ ያለው ወገን ለኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>• በኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጥ ውሣኔ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ ስለመሆኑና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለው በማለት አቤቱታ ያለው ሠራተኛ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀጽ 4(1),54(3),56(4)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343, 9, 231 | 80964 | የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ አቶ አበረ ቦከን (ሶስት ሠዎች) | ጥቅምት 23/2005 | 305 |
| 73 | የመንግስት ዩኒቨርስቲ መምህራንን በተመለከተ ከዲሲፕሊን ግድፈት ጋር በተገናኘ የሚሰጥ ውሣኔ በአስተዳደር ፍ/ቤት በይግባኝ ሊስተናገድ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>አዋጅ ቁ. 515 /99 አንቀጽ 2(8),22(3),32(3)<br>አዋጅ ቁ. 650/2001 አንቀጽ 44(ጎ) | 78945 | ደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ<br>እና<br>መምህር ባዬ ዋናያ የዳ | መስከረም 22/2005 | 311 |
| 74 | • በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ በሌላ በኩል የጉምሩክ ደንብ በመተላለፍ ወንጀል ባለቤቱ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦበት ተሽከርካሪውም | 81215 | ወጋገን ባንክ (አ.ማ.)<br>እና<br>የኢትዮጵያ | ጥር 03/2005 | 315 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በመንግስት እንዲወረስ ውሣኔ የተሰጠበት እንደሆነ በህግ ፊት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊፈፀም ስለሚገባው ጉዳይ<br>• በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ ከመያዣው በኋላ በኮንትሮባንድ ወንጀል ምክንያት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን በፍ/ቤት የመጨረሻ ፍርድ ባረፈበት ጊዜ ባለመያዣው በተሽከርካሪው ላይ ያለው የቀዳሚነት መብት እንዲሁም የውርስ ትዕዛዙ (ውሣኔው) ተፈፃሚ ሊደረጉ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2828, 2857(1), 3059<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 98(1)<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 91(2) | | ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | | |
| 75 | • የሥራ ግዴታን ካለመወጣት ጋር በተገናኘ ሠራተኛ የሆነ ሰው ከአሰሪው የተረከበው ንብረት ላይ ጉዳት እንዲከሰት በማድረጉ ወይም ንብረቱ እንዲጉድል (እንዲጠፋ) በማድረጉ ምክንያት በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በተመሣሣይ ጉዳይ ሠራተኛው በአሰሪው ንብረት ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን በፍትሐብሔር ሊጠየቅ ስለመቻሉ፣<br>• ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሠራተኛው በአሰሪው ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ጉዳት የደረሰበትን ንብረት በተመለከተ በፍትሐብሔር ተጠያቂ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 515<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149 | 78414 | የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እና<br>እነ አቶ ቶላ መገርሣ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 07/2005 | 321 |
| 76 | አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በህጉ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበስብ ሊፈቀድ የማይችል ስለመሆኑ፡<br>አዋጅ ቁ. 621/2001 አንቀጽ 2(2),(3)(4),14(5), 14(2), 6, 90, 111(2), 112,108,110,<br>ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18(3),10(2),36 | 74036 | የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ እና<br>የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ | መስከረም 23/2005 | 325 |